# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ክሉሌ መልአኩ

__አሳታሚ፡__ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

አዲስ አበባ 1986 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ


ገጽ

መግቢያ ........................................................ 7

## ክፍል አንድ

### ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ትልቁ ቈስጠንጢኖስ (እስከ 313 ዓ.ም)

ዘመነ ሐዋርያት (እስከ ሐዋርያው ዮሐንስ ዕረፍት ፤ 100 ዓ.ም) ........................................ 12

ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች . 28

የስደት ዘመናት (ዘመነ ሰማዕታት ፤ 64–313 ዓ.ም) ..... 33

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መናፍቃንን በመቃወም ያደረገችው የመንፈስ ተጋድሎ ........................................ 37

የጥንት ክርስቲያኖች ሥርዓተ እምነት አፈጻጸም ........ 39

በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ መቶ ዘመናት የቤተ ክርስቲያን አመራር ........................................ 41

ለክርስትና ትምህርት መስፋፋት የረዱ .................... 42

የክርስትና ድል መንሣትና መስፋፋት .................... 43

በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ዘመን መናፍቃንን ለመቃወም የተደረጉ ታላላቅ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤዎች (ሲኖዶሶች) ........................................ 45

በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ዘመን የተነሡት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ........................................ 49

በአራተኛው መቶ ዘመን የነበሩት አምስቱ ሊቃነ ጳጳሳት (ፓትርያርኮች) ........................................ 55




www.ethiopianorthodox.org

በኦርየንታል (በተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ ፣ በግሪክ ኦርቶዶክስ ፣ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ካሉት የሃይማኖትና የሥርዓት ልዩነቶች ጥቂቶቹ (ዋና ዋና ዎቹ) ........................................................ 56

## ክፍል ሁለት

### የኦርየንታል (የተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ

### ምዕራፍ ፩

የእስክንድርያ (የግብጽ ፣ የኮፕት) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........................................................ 61

### ምዕራፍ ፪

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ 123

### ምዕራፍ ፫

የሶርያ (የአንጾኪያ ፣ ያዕቆባዊት) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........................................................ 143

### ምዕራፍ ፬

በደቡብ ሕንድ የሐዋርያው ቶማስ (የማላባር ፣ የኬራላ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........................ 152

### ምዕራፍ ፭

የአርመን (ጎርጎርዮሳዊት) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........................................................ 157



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ሦስት

### የምሥራቅ (የግሪክና የእስላቮኒክ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ታሪክ ............................................................ 166

ምዕራፍ ፩

የቍስጥንጥንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ .... 177

ምዕራፍ ፪

የእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ...... 179

ምዕራፍ ፫

የአንጾኪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ .......... 180

ምዕራፍ ፬

የኢየሩሳሌም ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ...... 181

ምዕራፍ ፭

የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ .............. 182

ምዕራፍ ፮

የሩማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........... 190

ምዕራፍ ፯

የሰርቢያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ............ 191

ምዕራፍ ፰

የቡልጋርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ......... 193



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፱

የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ .............. 195

ምዕራፍ ፲

የቆጵሮስ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........... 197

ክፍል አራት

የምዕራብ (የካቶሊክና የፕሮቴስታንት) አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ

ምዕራፍ ፩

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ .......................... 200

ምዕራፍ ፪

የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ........... 258

ክፍል አምስት

በ20ኛው መቶ ዘመን የተጀመረው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ንቅናቄ (ጉባኤ ፣ ማኅበር) ............................................. 311

የክርስትናን እምነት የሚከተሉ ምእመናን ቍጥር ግምት .................................................... 326




www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

ከዚህ በታች መጽሐፉን ስላዘጋጀሁበት ምክንያትና ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አጠቃላይ መግቢያ (መግለጫ) እጽፋለሁ ።

ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሣሣሁት ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የአምስቱን የኦርየንታል (የተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ሳስተምር መጠነኛ ዝግጅት ስላደረግሁ ነው ። ይህም ዝግጅት የተሟላ ባይሆንም ቅሉ ፡ ካህናትና ምእመናን በእምነት አንድ ስለሆንነው የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ አጠቃላይ ዕውቀትና ግንዛቤ እንዲያገኙ በማለት ታሪኩ በትንሣኤ መጽሔት እየታተመ በተከታታይ በመውጣት ላይ ነው ። ሆኖም በመጽሔት እያሳተሙ ማውጣቱ ብዙ ጊዜ ስለሚፈጅ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ጋር የቤተ ክርስቲያንን በክርስቶስ መመሥረት ፡ የግሪክ ኦርቶዶክስን ፣ የካቶሊክን ፡ የፕሮቴስታንትን በሃያኛው መቶ ዘመን የተጀመረውን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ንቅናቄ (ጉባኤ ፣ ማኅበር) በአምስት ክፍሎች አዘጋጅቼ ሁሉንም "የቤተ ክርስቲያን ታሪክ" በሚል ርእስ አቅርቤአለሁ ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ለወደፊት ብዙ መጻሕፍትን በመመልከትና ከሊቃውንት በመጠየቅ በቀጣዩ እትም ተሻሽሎ እንደሚወጣ ተስፋ አደርጋለሁ ። ሆኖም መጽሐፉን የሚያነቡ ሁሉ ለወደፊት ተሻሽሎ በሚታተምበት ጊዜ ለማስተካከል የሚያስችል ገምቢ አስተያየት እንዲለግሱኝ በትሕትና እጠይቃለሁ ።

መጽሐፉን ሳዘጋጅ የተጠቀምሁባቸው አብዛኛዎቹ መጻሕፍት በውጭ ሀገር ቋንቋ የተጻፉ ስለሆኑ ዓመተ ምሕረቶች የተጻፉት እንደ አውሮጳ አቈጣጠር ነው ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ያሉት ዓመተ ምሕረቶች ግን እንደ ኢትዮጵያ አቈጣጠር ተጽፈዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ እንደፊተኞቹ መጻሕፍቶቼ ሁሉ አሁንም ይህን መጽሐፍ መርምሮና የጐደለውን አሟልቶ ለሕትመት እንዲበቃ ስላደረገልኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው ። ምናልባት በመጽሐፉ ውስጥ ስሕተት መስሎ የሚታይ ቢገኝ የሚመለከት እኔን ነው ። እንዲሁም ይህን መጽሐፍ አዘጋጅቶ



www.ethiopianorthodox.org

እንዳሳትም በሐሳብ የረዱኝንና ያበረታቱኝን ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/አማኑኤልን አመሰግናለሁ ። በመጨረሻም መጽሐፉ ለካህናትና ለምእመናን ጠቃሚ ሆኖ እንደሚገኝ አምናለሁ ።

እዚህ ድረስ መጽሐፉን ለማዘጋጀት የተነሣሣሁበትን ምክንያት ተመለከትን ። ቀጣዩ ደግሞ ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚገልጸው አጠር ያለ መግቢያ ነው ።

ሀ) <u>ቤተ ክርስቲያን</u> ። ሕፃን ሽማግሌ ፣ ድኻ ሀብታም ፣ ወንድ ሴት ፣ የተማረ ያልተማረ በመባባል ሳንለያይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ" (ማቴ· 18፥20) ብሎ ባስተማረው መሠረት ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበት ፣ በአንድነት ፈጣሪያችንን ለማምለክ የምንሰበሰብበት ቅዱስ ቦታ ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት መሆኑን የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ይባላሉ ።

ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የዋጃትና ራሷ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ፣ መሪዋና አጽናኟ መንፈስ ቅዱስ ነው (የሐዋ· 20፥28 ፤ 9፥31 ፤ ኤፌ· 5፥ 26 ፤ ቆላ· 1፥18)።

ክርስትና ከተመሠረተች ጀምሮ ክርስቲያኖች በየቤቱና በየዋሻው እየተሰበሰቡ ለፈጣሪያችን ምስጋና ሲያቀርቡ ከቆዩ በኋላ መጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ የተሠራ ፊልጵስዩስ በሚባለው ሀገር ነው ።

ለ) <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u> ። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ መንፈሳዊት ዓለም ስለሆነች ፣ የተለየ ታሪክ አላት ። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፣ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ መሠረትነት ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘመናችን ድረስ ያለውን ታሪኳን ፣ እንደምን እንደተመሠረተች ፣ እንደምን የዓለም ሕዝብ እንደተቀበላት ፣ በየጊዜው ከአባላቷና ከተቃዋሚዎቿ የተሰነዘሩባትን የኑፋቄ ትምህርቶችና ስደቶች በጽና ሃይማኖት በመቋቋም (በመጋደል) እንደምን እንዳሳለፈቻቸው ፣ የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት እንዳስፋፋችና ይህንንም የመሳሰለውን ሁሉ ያስተምረናል ።

ሐ) <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምንጮች (መገኛዎች)</u> ።

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በዝርዝር ለማጥናት የሚፈልግ ሰው ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምንጮች የሆኑትን ልዩ ልዩ መጻሕፍት መመልከት ይገባዋል ። እነሱም የሚቀጥሉት ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

1ኛ/ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ። 2ኛ/ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፏቸው መጻሕፍት ። በየጊዜው በተደረጉት ጉባኤዎች የተወሰኑትና ነገሥታት ስለ ቤተ ክርስቲያን የደነገጓቸው ሕጎች ናቸው ። 3ኛ/ ታሪኩ በተፈጸመበት ቦታ ተገኝተውና ዘመን ኖረው የቤተክርስቲያንና የውጭ ታሪክ ጸሐፊዎች የጻፏቸው መጻሕፍት ናቸው ። 4ኛ/ በየጊዜው የተገኙ ትና የሚገኙት የክርስቲያኖች መቃብር ፣ መቅደሶች ፣ ሥዕሎች ፣ ገንዘቦች፣ ጽሑፎችና እነዚህን የመሳሰሉት የአርኬዎሎጂ (የጥንታውያን ነገሮች ምርመራ) ቅርሶች ናቸው ።

መ) <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አከፋፈል</u> ። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሦስት ክፍሎች ይከፈላል ።

1ኛ/ መጀመሪያው ፣ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል ። ጌታ ቤተ ክርስቲያንን በሐዋርያት ላይ ከመሠረተበት ዘመን ጀምሮ እስከ ትልቁ ቈስጠንጢኖስ ድረስ ነው (እስከ 313 ዓ·ም) ።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች የጥንት ቤተ ክርስቲ ያን ታሪክ የሮማ መንግሥት እስከ ወደቀበት እስከ 476 ዓ·ም ድረስ ነውም ይላሉ ።

2ኛ/ ሁለተኛው ፣ የመካከለኛው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል ። ከትልቁ ቈስጠንጢኖስ ጀምሮ ቊስጥንጥንያ በቱርኮች እጅ እስከ ወደቀች በት ጊዜ ድረስ ነው (313—1453 ዓ·ም) ።

3ኛ/ ሦስተኛው ፣ አዲሱ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል ። ቊስጥንጥንያ በቱርኮች እጅ ከወደቀችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ ነው (1453—1993 |1986| ዓ.ም) ።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች በየራሳቸው እምነት ላይ ታላላቅ ድርጊቶች የተፈጸሙባቸውን ዘመናት መሠረት በማድረግ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በተለያዩ ጊዜዎች ይከፍሉታል ።

በዚህ መጽሐፍ የተከተልሁት አከፋፈል ከላይኛው ለየት ያለ ነው ። ይኸውም ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ (451 ዓ·ም) ያለው ታሪክ በክፍል አንድ ተገልጿል ። እስከ አምስተኛው መቶ ዘመን ድረስ በእምነት አንድ የነበረችዪቱ ቤተ ክርስቲያን በኬልቄዶን ጉባኤ ከተለያየች በኋላ ተለያይተው የሚኖሩትና በሃያኛው መቶ ዘመን የተጀመረው የዓለም



www.ethiopianorthodox.org

አብያተ ክርስቲያናት ንቅናቄ (ማኅበር ፥ ጉባኤ) ታሪክ ከሁለት እስከ አምስት ባሉት ክፍሎች ውስጥ ተጽፏል ።

ሠ) <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጠቃሚነት</u> ። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከዓለም ታሪክ አንደኛውን ክፍል ይዞ ስለሚገኝ ፥ የሕዝቦችን የሥልጣኔ እርምጃና ታሪክ ለማጥናት ለሚፈልግ ሰው ሁሉ በጣም ጠቃሚ ነው ። በተለይ ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በሚያጠና በት ጊዜ የእምነቱን ታሪክ ፥ እንዲሁም አባቶቻችን በየጊዜው ባስተማ ሩት መንፈሳዊ ትምህርት የሕዝቡ ጠባይ እንዴት እንደ ተሻሻለ ለማወቅና ራሱንና ምእመናንን በእግዚአብሔር መንገድ ለመምራት ይችላል ። ከዚህም በስተቀር የቤተ ክርስቲያንን ከፍተኛነትና ጠቃሚነት ለመገንዘ ብና ለምእመናንም ለማስገንዘብ እንዲችል ይረዳዋል ።

ረ) <u>ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ የነበረው የዓለም ሕዝብ አምልኮና አኳኋን</u> ። ክርስትና ለዓለም ሕዝብ ያስገኘችውን ከፍ ያለ ጥቅም ለመረዳት ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ የነበረውን ሕዝብ አምልኮና ጠባይ ከዚህ በታች ባጭሩ እንመልከት ።

በዚያን ዘመን ምንም እንኳ የዓለም ገዥ የነበረው የሮም መንግሥት በኃይሉ ፥ በዕውቀቱ ፥ በሥልጣኔው ፥ በሀብቱና በማንኛውም ነገር ዝናው በዓለም የታወቀና የገነነ ቢሆንም ፥ የአምልኮውና የግብረ ገብነቱ አኳኋን እጅግ በጣም አሳዛኝና የተበላሸ ዝቅተኛ ግምት የተሰጠው ነበር ። ሐዋርያው ጳውሎስ "የማይጠፋውንም የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ" (ሮሜ 1፥23—25) ብሎ እንዳስተማረው ሁሉ ሕዝቡ ፍጡራን የሆኑ ብዙ ዓይነት ጣዖታትን ያመልኩ ነበር ። እንዲሁም ብዙዎችን ሰዎች ለሰው ልጅ የሚገባውን ነጻነት ነፍገው በባርነት ያሠቃዩአቸውና ባሮች ናችሁ በማለት እንደ ዕቃ ይመለከቷቸው ነበር ። ሴትም ነጻነቷን ተገፋ በቤቷ እንደ ቤተሰብ ነበረች ።

በዚያ የዓለም ሕዝብ ጣዖት በሚያመልክበት ዘመን በእግዚአብ ሔር ያመልክ የነበረው የእስራኤል ሕዝብና የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነበር።

ምንም እንኳ ከአይሁድ መካከል ጥቂቶቹ ፍጹም እምነት ስለነበራ ቸው ፥ የክርስቶስን ወደዚህ ዓለም መምጣት ቢጠባበቁ (ዮሐ· 1፥46 ፥ ሉቃ· 2፥ 25 32) ብዙዎቹ ግን የተሳሳተ እምነትን በመከተል በነቢያት



www.ethiopianorthodox.org

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው ትንቢት ስለ ምድራዊ ገዥ ነው አሉ።

ጸሐፍትና ፈሪሳውያንም ይፈጽሙት የነበረው አምልኮ ለመታየትና ውዳሴ ከንቱን በመሻት ነበር እንጂ እግዚአብሔርን በመፍራትና በማክበር ከልብ የመነጨ አልነበረም ። ከአይሁድ መካከል ፈሪሳውያን ትንሣኤ ሙታን መኖሩን ሲያምኑ ፣ ሰዱቃውያን አያምኑም ነበር (ማቴ·22፡23) ።

ያን ጊዜ በአይሁድና በሳምራውያን መካከል ታላቅ ጠብ ነበረ ። ምክንያቱም ሰማርያ የሚኖሩ አይሁድ በምርኮ ምክንያት ከአሕዛብ ጋር በጋብቻ ተቀላቅለው ስለነበረ ፣ ከብሉይ ኪዳንም መጀመሪያዎችን አምስቱን የሙሴን መጻሕፍት ብቻ ስለተቀበሉና ኢየሩሳሌም ወደ ነበረው ቤተ መቅደስ ሄደው አምላካቸውን በማምለክ ፈንታ ገሪዛን በተባለው ተራራ ላይ የራሳቸውን ቤተ መቅደስ ሠርተው እግዚአብሔርን ስላመለኩ ፣ እንዲሁም አንዳንዶቹ ጣዖትንም ስላመለኩ አይሁድ በጣም ይጠሏቸው ነበር (ዮሐ· 4፡9) ።

የዚህ ዓለም ሕዝብ ከላይ እንደተመለከትነው ባለ አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ወድቆ ሳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ልጆች ከወደቅንበት ኃጢአት በደሙ ለማዳን መጥቶ በሰው ልጆች መካከል ልዩነት የማታደርግ የሰውን መንፈስ ጥም የምታረካና ከእግዚአብሔር ልጅነት የምታሰጥ እውነተኛይቱን የክርስትናን ሃይማኖት መሠረተልን ።

## ሉሌ መልአኩ



www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል አንድ

## ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ትልቁ ቈስጠንጢኖስ (እስከ 313 ዓ.ም)

### ዘመነ ሐዋርያት (እስከ ሐዋርያው ዮሐንስ ዕረፍት ፣ 100 ዓ.ም)
### ከልደት እስከ ጰንጠቆስጤ
### ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጀምሮ እስከ ጰንጠቆስጤ ድረስ የተፈጸሙ ሥራዎች

ሐዋርያው ጳውሎስ "ጊዜውም በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ..." (ገላ. 4፡4) እንደሚለው ሁሉ እግዚአብሔር ለአባታችን ለአዳም በሰጠው ተስፋ መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ከወደቅንበት ኃጢአት ለማዳን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ቤተልሔም ተወለደ ። ለእናቱና ለዘመዶቹም እየታዘዘ አደገ (ሉቃ. 2፡51)።

በሠላሳ ዓመቱ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠመቀ ። የባሕርይ ልጅነቱን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አስመሰከረ ። ከዚያ ቀጥሎ 40 መዓልት፡ 40 ሌሊት ከጾመ በኋላ በኢየሩሳሌም ማስተማር ጀመረ ። ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያትና ሰባ ሁለቱን አርድእት መረጠ ። በመዋዕለ ስብከቱም ልዩ ልዩ የሆኑ ታምራትን በማድረግ ድውያንን ፈወሰ ። ሙታንን አስነሣ ። የአይሁድ ካህናት ግን የሚያደርጋቸውን ታምራት አይተው የሚያስተምረውን ትምህርት ሰምተው በማመን ፈንታ ተቃወሙት ። የሕዝቡም ጠባይ ግልብጥብጥ ስለነበረ አንዳንድ ጊዜ የጌታን ሥራ ሲያደንቅ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ይቃወም ነበር ። ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ካስተማረ በኋላ የሆሣዕና ዕለት በሕዝቡ ታጅቦ በምስጋና ወደ ኢየሩሳሌም ገባ (ማቴ. 21፡9) ። የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ከሊቃነ ካህናት በተላኩት ወታደሮች በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ ውስጥ በተያዘ ጊዜ ጴጥሮስና



www.ethiopianorthodox.org

ዮሐንስ ሲቀሩ የቀሩት ሐዋርያት ጥለውት ተበተኑ (ማቴ· 26፡56)። ከሁለቱም ጌታ እስከ ተሰቀለበት ጊዜ የቈየ ዮሐንስ ብቻ ስለነበረ ፤ እዚያው እመስቀሉ ሥር ሳለ እመቤታችንን እንዲረዳት ከጌታ አደራ ተቀበለ (ዮሐ·19፡26) ።

ጌታ በተሰቀለ ጊዜ የተደረጉት ታምራት ሐዋርያትን ሊያደፋፍሩአቸው ቻሉ ። የሐዋርያትን ኃዘንና ጭንቀት ወደ ደስታ ፤ ፍርሃታቸውን ወደ ድፍረት ፤ ተስፋ መቊረጣቸውን ተስፋ ወደ ማድረግ የለወጠው የጌታ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ መነሣት ነው ። ከመቃብር ከተነሣ በኋላ በዚህ ዓለም አርባ ቀኖች ቈየ ። በነዚህ ቀኖች ውስጥ ለሐዋርያት በገሊላና በኢየሩሳሌም እየተገለጸ ምሥጢራትን እየፈጸመ የሐዋርያነት ሥራቸውን እንዴት እንደሚሠሩ ሲያስረዳቸው ከሰነበተ በኋላ ዐረገ ።

መቶ ሃያ የሚሆኑ ደቀ መዛሙርት ተሰብስበው ሳለ ጴጥሮስ ጌታን በካደው በይሁዳ ፈንታ ሌላ ሐዋርያ እንዲተካ ጠየቀ ። በሐሳቡ ሁሉም ስለተስማሙ ፤ ፍጹሙን እንዲመርጥ ወደ እግዚአብሔር ከጸለዩ በኋላ ለኢዮስጦስና ለማትያስ ዕጣ ቢጥሉ ፤ ዕጣው ለማትያስ ስለወጣለት ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቈጠረ (የሐዋ· 1፡26) ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ካህናት በጣም ታላቅ ለሆነው መንፈሳዊ ሥራቸው በጸሎት በአንብሮተ እድ የሚሾሙ ሆነዋል ።

## ጌታ ከሙታን በተነሣ በኀምሳኛው ቀን (የጰንጠቆስጤ ፤ የጰራቅሊጦስ ዕለት) የመንፈስ ቅዱስ መውረድና የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት

እስከ ጰንጠቆስጤ ድረስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአዘዛቸው መሠረት ሐዋርያት ተስፋውን ሲጠባበቁ ቈይተው ጌታ በዐረገ በዐሥረኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ተሰጣቸው ። ሐዋርያትም በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የእግዚአብሔርን ክብር ይናገሩ ጀመር ። በዚያን ጊዜ ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለእግዚአብሔር መንግሥት ስብከት አደረገ ። የተሰበሰበውም ሕዝብ ልብ በስብከቱ ስለተነካ ሦስት ሺህ የሚሆኑ ክርስትናን ተቀብለው ተጠመቁ ። በሐዋርያትና በነዚህ በተጠመቁት መጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች (የሐዋ· 2፡41 ፤ ኤፌ· 2፡20 ፤ ራእ· 21፡14)።

የጰንጠቆስጤ ዕለት ካመኑት አይሁድ መካከል አብዛኞዎቹ ከፍልስጥኤም ውጭ በየሀገሩ ተሰደው የሚኖሩ ስለነበሩ ፤ የበዓሉ ጊዜ ሲያልቅ



www.ethiopianorthodox.org

ወደየመጡበት ሀገር ተመልሰው የክርስትናን ትምህርት ላልሰማው ሕዝብ ስላሰሙ ፤ ከፍልስጥኤም ውጭ የወንጌል መልእክተኞችና የቤተ ክርስቲያን መሥራቾች ሆኑ ። ያን ጊዜ በወረደው መንፈስ ቅዱስ ኃይል በጥቂት ጊዜ ውስጥ የጣዖት አምልኮና የተሳሳቱ እምነቶች ሁሉ ሊጠፉና በክርስትና የዓለም መልክ ሊለወጥ ቻለ ። መንፈስ ቅዱስ ለዘለዓለም በቤተ ክርስቲያን ላይ አድሮ ይኖራል ። ከስሕተት ጎዳና ጠብቆ ወደ እውነት ይመራታል ። የእውነተኛዎችንም ክርስቲያኖች ልብ ከዚህ በፊት በመንፈሳዊ ቅናት መልቶት ነበር ። ለወደፊትም ይመላዋል ።

## ሐዋርያት ያደረጉአቸው መጀመሪያዎች ታምራትና ከአይሁድ የደረሱባቸው ስደቶች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ልዩ ልዩ ታምራት እንደሚያደርጉ አስቀድሞ "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል ፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ ፤ ... እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ ፤ እነሱም ይድናሉ" (ማር· 16፡17–18) ሲል ባስተማረው መሠረት ከጰንጠቆስጤ በኋላ ጴጥሮስና ዮሐንስ ለጸሎት ወደ ምኩራብ ሲሄዱ ሲወለድ ጀምሮ አንካሳ የነበረውን ሰው ጴጥሮስ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ሥልጣን ፈወሰው ። የአይሁድ ካህናት ጴጥሮስ ያደረገውን ታምርና ስብከት በመስማት ተናደው ጴጥሮስንና ዮሐንስን አሰሩአቸው ። ዳግመኛም በኢየሱስ ስም እንዳያስተምሩና ታምራት እንዳይሠሩ በዛቻ አስፈራር ተው ፈቷቸው ። ሐዋርያትም ዛቻውን ከጉዳይ ሳይጽፉ ያስተምሩና ታምራት ያደርጉ ጀመር ። ያደረጉአቸውም ታምራት በመላ ፍልስጥኤም ስለተሰሙ በሽተኞች ሁሉ ለመዳን ሐዋርያት ወደአሉበት በብዛት ይጐርፉ ነበር ። የሃይማኖት ኃላፊዎች የነበሩት አይሁድም ይህንን ወሬ ሰምተው በጣም ስለተሸበሩ ሐዋርያት ተይዘው ለፍርድ እንዲቀርቡ አዘዙ። የካህናት አለቃው ስለ ኢየሱስ እንዳያስተምሩ በማለት የሰጣቸ ውን ትእዛዝ ባለመፈጸማቸው ዘለፋቸው ። ያን ጊዜ ጴጥሮስ በታላቅ ድፍረት ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል ። ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር የሚያግደን ማንም የለ በማለት መልስ ስለሰጠ ሊቀ ካህናቱና ፈራጆቹ በጣም ተበሳጩ ።

የሕግ አስተማሪና በሕዝቡም ፊት ክብር የነበረው ገማልያል



www.ethiopianorthodox.org

ለፈራጆቹ መልካም ምክሩን እንዲህ ሲል አቀረበ "… ተውአቸው ፤ ይህ አሳብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደሆነ ይጠፋልና ፤ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም ፤ በእርግጥ ከእግዚአብ ሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ" (የሐዋ· 5፥38–39) ። ስለዚህ የገማልያል ንግግር ፈራጆችን ስለአስታገሣቸው ለማስፈራሪያ ያህል ሐዋርያት ተገርፈው ተለቀቁ ። እነሱም "ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአ ችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ ። ደስ ይበላችሁ ። ዋጋችሁ በሰማያት ብዙ ነውና ። … (ማቴ· 5፥ 11–12) ብሎ ጌታ ያስተማረውን በማሰብ የተቀደሰ ሥራቸውን በበለጠ ደስታ ቀጠሉ ። ቀስ በቀስም የክርስቲያኖች ቊጥር ከሴቶችና ከልጆች በስተቀር 5ሺህ ያህል ሆነ (የሐዋ. 4፥4) ።

## የመጀመሪያዎች ክርስቲያኖች ሕይወት

በኢየሩሳሌም ውስጥ በተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ሥር የነበሩት ክርስቲያኖች ከሰዓት በኋላ ጊዜ ወስነው በኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ በያዕቆብ ፣ በማርቆስ እናት በማርያም ቤትና እነዚህን በመሳሰሉ ቤቶች እየተሰበሰቡ የሐዋርያትን ትምህርት ይሰሙ ነበር (የሐዋ· 12፥ 12)። በስብሰባውም ጊዜ የወንጌልን ትምህርት በተለይም የክርስቶስን ትንሣኤ በዐይናቸው ያዩ መሆናቸውን እያረጋገጡ ያስተምሩአቸው ነበር። ከዚህም በስተቀር ከብሉይ ኪዳን ስለ መሲሕ የሚናገሩት ትንቢቶች በኢየሱስ ክርስቶስ መፈጸማቸውን አስፋፍተው ያስረዱአቸው ነበር ። እንዲሁም በየጊዜው ሥጋውን ደሙን በአንድነት እየተቀበሉ አንድነታቸውን አጽንተው ይኖሩ ነበር ። ደግሞ በወንድማማችነት መንፈስ የተሳሰሩ መሆናቸውን በመግለጽ በአንድነት በአንድ ማዕድ ላይ ተቀምጠው ይበሉ ነበር ። እነዚህም አገልግሎቶች የሚፈጸሙበት ቀን እሑድ ነበር ። ማንኛውም ሰው የቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን የሚችለው ኃጢአቱን ተናዞ ተጠምቆ ሐዋርያት እጃቸውን በመጫን መንፈስ ቅዱስን ከአሳደሩበት በኋላ ነበር ። በምእመናን ሁሉ ዘንድ መንፈሳዊ ደስታ ፣ ትሕትና ፣ ፍቅርና እነዚህን የመሳሰሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ጐልተው ይታዩ ነበር ። ከእነሱም መካከል የማስተ ማር፣ ትንቢት የመናገር ፣ ታምራት የመሥራት ኃይል የተሰጣቸው ነበሩ (የሐዋ· 11፥28) ።



www.ethiopianorthodox.org

ከክርስትና እምነት ውጭ የነበረው ሕዝብ በክርስቲያኖች ሕይወት ላይ የተደረገውን ታላቅ ለውጥ በማየት ወደ ክርስትና እምነት በብዛት ስለመጣ የክርስቲያኖች ቍጥር እየበዛ ሄደ ። በዚያን ጊዜ የነበሩ ክርስቲያኖች ከመካከላቸው ችግርን ለማስወገድ በማሰብ እየተሰበሰቡ ገንዘብ በማዋጣት መከራና ችግር የደረሰባቸውን ሁሉ በሚገባ ይረዱአ ቸው ነበር ። ሀብታሞች ያለአንዳች አስገዳጅ በወንድምነት ፍቅር ተስበው በፈቃዳቸው ርስታቸውን እየሸጡ ለድኾች እንዲያካፍሉላቸው ለሐዋርያት ይሰጡ ነበር ። እንደዚህ ያለውን ርዳታ ካደረጉት መጀመሪ ያው ሰው ከቆጵሮስ የሄደው አይሁዳዊው በርናባስ (ዮሴፍ) ነበር (የሐዋ· 2፡42–47 ፤ 4፡ 32–37) ።

ሐዋርያው ጳውሎስም በንፍገት መንፈስ በመመራት ወንድሞቻ ቸው ሲራቡ እያዩ ባለማዘን ብቻቸውን የሚበሉትን "በመብላት ጊዜ እያንዳንዱ የራሱን እራት ይበላልና ፤ አንዱም ይራባል አንዱ ግን ይሰክራል …" (1ቆሮ· 11፡21–22) በማለት በማኅበር ከድኾች ጋር አብረው እንዲበሉ የሰጠው ምክር በዚሁ መሠረት ነው ።

አይሁድ ክርስቲያኖችን ገሊላውያን ፣ ናዝራውያን ይሏቸው ነበር ። ክርስቲያኖች ግን ወንድሞች ፣ ደቀ መዛሙርት እየተባሉ ይጠሩ ነበር (የሐዋ· 1፡15 ፤ 6፡1)። ክርስቲያን መባል ግን በኋላ በአንጾኪያ የተጀመረ ነው ። ይህንንም ክርስቲያን የሚለውን ስም የአንጾኪያ ሰዎች ያወጡላ ቸው ክርስቶስ የተባለውን በማምለካቸው ሲያፌዙባቸው ነበር (የሐዋ· 11፡26) ።

## የሰባቱ ዲያቆናት ምርጫ

የክርስቲያኖች ቍጥር በየጊዜው እየበዛ ስለሄደ በአንድነቱ ሥራ ውስጥ ሥራውን ተግተው አክብረው የሚፈጽሙ ግብረ ገቦችና ሥራ የማይወዱ ሰነፎች ተገኙ ። በዚህ ምክንያት በአንድነቱ ውስጥ መነቃቀፍ ተጀመረ ። ሐዋርያትም ይህን ሰምተው እንደዚህ ያለውን መነቃቀፍ ለማስቀረት ሲሉ ክርስቲያኖችን ሁሉ ሰብስበው የኛ ዋና ዓላማ ሕዝቡን ማስተማር ስለሆነ ተማከሩና ለዚህ ሥራ የሚሆኑ ጥበብን የተመሉ የጋለ መንፈሳዊ ቅናት ያላቸው ፣ በሕዝብ ዘንድ የተወደዱና መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሰባት ሰዎች ምረጡ አሏቸው ። ሰባቱም በሕዝብ ድምፅ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ከተመረጡ በኋላ ሐዋርያት እጃቸውን ጭነው በጸሎት ሾሟቸው ። ከተመረጡ በኋላ ተባብረው ስለሠሩ የወንጌል ስብከት እየተስፋፋ ምእመናን እየበዙ ሄዱ ። ከአሪት ካህናትም ብዙዎች አመኑ (የሐዋ· 6፡2–7)። ለእነዚህ እንዲረዱአቸው በሐዋርያት ጥያቄ ለተመረጡት 7 ሰዎች ቤተ ክርስቲያን የክህነትን ማዕርግ በመስጠት ዲያቆናት (ረዳቶች ፣ አገልጋዮች) ብላ ሰየመቻቸው ።

## እስጢፋኖስ ቀዳሚ ሰማዕት

እስጢፋኖስ ፍጹም እምነት ፣ የጋለ መንፈሳዊ ቅናትና ታምር የማድረግ ጸጋ ነበረው ። ከተሰጠው ሥራም በስተቀር ጊዜ ባጋጠመው ቍጥር በየምኵራቡ እየዞረ ለአይሁድ ዓለምን ለማዳን ስለመጣው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን እየጠቀሰ አስረዳቸው ። እሱም የሚናገረው በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ ስለ ነበር ፣ በመቃወም ይከራከሩት የነበሩትን መልስ ስላሳጣቸው በቅናት መንፈስ በመመራት እሱን ለማጥፋት የሙሴን ሕግ ይነቅፋል ፣ እግዚአብሔርን ይሰድባል ብለው የሐሰት ምስክሮች አስነሡበት ። ይህም የሐሰት ወሬ በሕዝቡ ዘንድ ስለተነዛ እውነት መስሎ ታየ ። አንድ ቀን አይሁድ በቅናት መንፈስ በመመራት እስጢፋኖስን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ይዘው ወደሸንጎ ወሰዱት ።

ቀደም ብለው የተሰናዱት የሐሰት ምስክሮችም "ይህ ሰው ኦሪትንና ቤተ መቅደስን ይነቅፋል ፤ በዚህ በተቀደሰው ስፍራ በሕግም ላይ የስድብን ነገር ለመናገር አይተውም ፤ ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ቤተመቅደስ ያፈርሰዋል ፤ ሙሴም ያስተላለፈልንን ሥርዓት ይለውጣል ሲል ሰምተነዋል" ብለው መሰከሩበት (የሐዋ· 6፡13–14)።

በዚያን ጊዜ የእስጢፋኖስ ፊት እንደ መልአክ ፊት ሲያበራ አዩት ። የካህናት አለቃው መልስ እንዲሰጥ ቢጠይቀው ስለተከሰሰበት በመመለስ ፈንታ ፣ አይሁድ ከጥንት ጀምረው እግዚአብሔርን በመቃወም ስለሚያደርጉት መጥፎ ሥራ የተሰማውን ኃዘን ለመግለጽ ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ እስከ መድኃኒታችን ኢየሱስ ድረስ ያለውን የቅዱሳት መጻሕፍትን ጽሑፍ በሚገባ ተረከላቸው ። ይኸውም አይሁድ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሕገ ኦሪትን ትተው ሞሎክ የተባለውን ጣዖት አመለኩ ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ መወለድ ትንቢት የተናገሩትን ነቢያት



www.ethiopianorthodox.org

ገደሉ ። ጌታንም በግፍ ሰቀሉ በማለት ገልጾ ነገራቸው ። አይሁድ የእስጢፋኖስን ንግግር ከሰሙ በኋላ እሱን በመቃወም በታላቅ ቁጣ ተሞሉ ። ጥርሳቸውንም አፋጩ ። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔርን ክብር ፣ ኢየሱስንም በእግዚአብሔር አብ ዕሪና ተቀምጦ አየ ። እስጢፋኖስም የተገለጠለትን ምሥጢር በዙሪያው ለተሰበሰበው ሕዝብ በመግለጥ እንዲህ ሲል ተናገረ ። "እነሆ ፣ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጦ አያለሁ" (የሐዋ·7፥56) ። አይሁድ እነዚህን ንግግሮች በእግዚአብሔር ላይ እንደተሰነዘሩ ስድቦች በመቍጠር ያለፍርድ ቤት ውሳኔ ዘለው ያዙት ። ከከተማም አውጥተው በድንጋይ ወግረው ገደሉት ። ወጋሪዎች ሲወግሩት ልብሶቻቸው እጆቻቸውን በመያዝ ግራ እንዳያጋቡአቸው ለማቃለል በማሰብ በዚያን ጊዜ የክርስትና አሳዳጅ የነበረው ሳውል ልብሶቻቸውን ይጠብቅላቸው ነበር ። የሚወረወሩት ድንጋዮችም እንደ ክረምት በረዶ በላዩ ላይ ሲወርዱበት ተንበርክኮ እንዲህ ሲል ጸለየላቸው ፣ "ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው" (የሐዋ· 7፥60)። እነዚህን ቃላት ከተናገረ በኋላ ዐረፈ። ደጋግ የሆኑ ክርስቲያኖች በድኑን ወስደው እንባ በእንባ እየተራጩ ቀበሩት ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም በስሙ ቤተ ክርስቲያን አሳንፃ በዓሉን ጥር 1 ቀን ታከብራለች ።

በዚያን ጊዜ አይሁድ ክርስትናን እናጠፋለን ብለው ባነሡት ስደት ምክንያት ከሐዋርያት በስተቀር ወደ ሰማርያ ፣ ፊኒቅያ ፣ ቆጵሮስና ሶርያ (አንጾኪያ) የተሰደዱት ክርስቲያኖች ሁሉ በየሄዱበት ሀገር ስላስተማሩ ፣ ይህ ስደት ክርስቲያኖችን በማጥፋት ፈንታ ለክርስትና መስፋፋት በጣም ጠቀመ ።

## ፊልጶስ

ከእስጢፋኖስ ዕረፍት በኋላ ከአይሁድ በክርስቲያኖች ላይ በተነሣው ስደት ምክንያት ኢየሩሳሌምን ለቀው ከተሰደዱት አንዱ ፊልጶስ ነበር ። የእርሱም ከኢየሩሳሌም መራቅ ወንጌልን ከኢየሩሳሌም ውጭ እንዲያስተምር ምክንያት ሆነው ። በሰማርያ ውስጥ አስተምሮና ታምራት አድርጎ ብዙ ሰዎችን አጠመቀ ። በጥንቈላ ሥራው ሰዎችን ያታልል የነበረው ጠንቋዩ ሲሞንም በክርስቶስ አምኖ ተጠመቀ ። ሐዋርያትም የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ በሰሙ ጊዜ ፣ ከኢየሩሳሌም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ሰማርያ ሄደው በተጠመቁት ላይ



www.ethiopianorthodox.org

እጃቸውን በመጫን ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ሲያሳድሩባቸው ሲሞን ስላየ እንደነርሱ ያለ ሥልጣን እንዲኖረው ፈለገ ። ወዲያውም ብዙ ገንዘብ በሐዋርያት ፊት አቅርቦ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን የማሳደር ሥልጣን ለእርሱም እንዲሸጡለት ልመናውን አቀረበ ። ጴጥሮስም ጥያቄውን በመቃወምና እምነተ ቢስነቱን በመግለጽ የእግዚአብሔር ስጦታ በገን ዘብ ይገዛል ብለህ ማሰብህ በጣም ታላቅ ጥፋት ነው አለው ። ሲሞንም ከዚያች ጊዜ ጀምሮ ከቤተ ክርስቲያን አባልነት ተወገደ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ማዕርገ ክህነት ለማግኘት ጉቦ የሚሰጡና ለመስጠትም የሚቀበሉ ሁሉ ሲሞናውያን ተብለው ይጠሩ ጀመር ። እንደዚህ ያለውን አጉል ሥራ ሲፈጽሙ የሚገኙ ሁሉ ማዕርገ ክህነታቸውን ይገፈፋሉ ። ከዚህ በኋላ ሲሞን በውጪ ክርስቲያን መስሎ እየታየ ውስጥ ውስጡን የክርስትናን እምነት በመቃወም በሰማርያ ሰዎች ዘንድ ይሰብከው የነበረውን የተሳሳተ ሐሳቡን በክርስቲያኖች ዘንድ መንዛት ስለጀመረ የመጀመሪያው ከሐዲና የከሐዲዎች መሪ የሚል ስም ተሰጠው ።

ጴጥሮስና ዮሐንስ ሥራቸውን ከፈጸሙ በኋላ ሰማርያ በሚገኙት መንደሮች እየሰበኩ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ። ፊልጶስም ከሰማርያ ወደ ጋዛ እንዲሄድ መንፈስ ቅዱስ ስለአዘዘው ሄደ ። በዚያም መንገድ አንድ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለ ሥልጣን ኢየሩሳሌም ሄዶ በዓል አክብሮ ወደ ሀገሩ በመመለስ ላይ ሳለ በሠረገላው ላይ ተቀምጦ የኢሳይያስን መጽሐፍ ገልጦ ዓለምን ለማዳን ስለመጣው መሲሕ ሕማም ፥ ሞትና ትንሣኤ የሚናገሩትን ትንቢቶች (ኢሳ 53፡7) እያሰማ ሲያነብ ፊልጶስ ሰምቶ የምታነበውን ታውቀዋለህን አለው ። ጃንደረባውም ያስተማረኝ ሳይኖር በምን አውቀዋለሁ ፤ ነቢዩ ይህን የተናገረ ስለራሱ ነውን? ወይስ ስለ ሌላ እባክህ አስረዳኝ አለው ፤ በሠረገላውም ላይ አስቀመጠው ፤ እንዲህ ሲል ተረጐመለት ፥ ይህ የኢሳይያስ ትንቢት በአይሁድ እጅ በተሰቀለውና በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈጸመ ገለጸለት ። ይህንንም እየተነጋገሩ ሲሄዱ ከውኃ ደረሱ ፥ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምኖ ተጠመቀ ። ፊልጶስም ከአጠመቀው በኋላ ከፊቱ ተሰወረ ። በዚህ አኳኋን በአፍሪካ አሕጉር ክርስትናን በመቀበል መጀመሪያ የሆነው ይህ ኢትዮጵያዊ መኰንን የክርስትናን እምነትና ትምህርት ወደ ሀገራችን



www.ethiopianorthodox.org

አመጣልን (የሐዋ·8፡ 27–39) ።

ፊልጶስ ጉዞውን በመቀጠል በባሕር አጠገብ ወደምትገኘው አዛጦን ወደምትባለው ከተማ ሄደ ። ከዚያችም ከተማ በስተቀር ለፍልስጥኤም ዋና ወደብ ወደነበረችው ቂሣርያ እስኪደርስ ድረስ በባሕር ዳር የነበሩ ከተማዎችን አስተምሯል ።

## ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት

ሐዋርያው ጴጥሮስ (ስምዖን ፡ ኬፋ) ። ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከመከተሉ በፊት በጌንሳሬጥ ባሕር ዓሣ አጥማጅ ነበር። ከተከተለው በኋላ ግን የጰንጠቆስጤ ዕለት የወንጌልን ትምህርት አስተምሮ በአንድ ጊዜ ሦስት ሺህ ሰዎችን አሳመነ (የሐዋ·2፡41) ። ከእስጢፋኖስ ዕረፍት በኋላ ኢየሩሳሌም ውስጥ ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ሲያስተምርና ታምራት ሲያደርግ ቈይቶ ክርስትና በመላው ፍልስጥ ኤምና በጎረቤት ሀገሮች እንደ ተስፋፋች ስለሰማና ስላየ ልዳ ፡ ኢዮጴ ፡ ቂሣርያ በተባሉ ከተሞች እየዞረ አስተማረ ። ብዙ ታምራትም አደረገ ። ኢዮጴ ሳለ ባየው ራእይ መሠረት የወንጌልን ቃል ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብም መስበክ መገባቱን በማመን በቂሣርያ የነበረውን አረማዊ ውን የመቶ አለቃ ቆርነሌዎስን ከነቤተ ሰቡ አጠመቀው (የሐዋ· 10፡48)።

በ36 ዓ·ም ከፋሲካ በዓል ቀደም ብሎ ጴጥሮስ ታሰረ ። ሞቱም ከበዓሉ በኋላ እንዲፈጸም ተወስኖ በእስር ቤት በጥብቅ ሲጠበቅ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ የታሰረበትን ሰንሰለት ፈትቶ እስከ መጨረሻው የእስር ቤቱ የብረት በር ድረስ መርቶ አውጥቶ ከሚጓዘው ካደረሰው በኋላ ተሰወረው ። እሱም ክርስቲያኖች በአንድነት ወደሚሰበሰቡበት ወደማር ያም ቤት ሄዶ ላገኛቸው ሁሉ እግዚአብሔር ያደረገለትን ምሕረት ነግሮ ወደ ሌላ ቤት ሄደ ።

በ50 ዓ·ም ጴጥሮስ ኢየሩሳሌም ውስጥ በተደረገችው በሐዋርያት ጉባኤ ተካፋይ በመሆን ለተላለፈው ውሳኔ መሳካት ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል (የሐዋ·15፡7–11) ። ከሐዋርያት ጉባኤ በኋላ ጳውሎስ አንጾኪያ ውስጥ ከጴጥሮስ ጋር እንደተገናኙ ይጽፋል (ገላ 2 ፡ 11) ። ጴጥሮስ በስሙ የሚጠሩ ሁለት መልእክታት ጽፏል ።



www.ethiopianorthodox.org

የሮም ንጉሠ ነገሥት ኔሮን (37–68 ዓ·ም) በክርስቲያኖች ላይ ባስነሣው ስደት ከብዙ ሰማዕታት ጋር ጴጥሮስ በመስቀል የቁልቁሊት ተሰቅሎ ፣ ጳውሎስ አንገቱን በሰይፍ ተቆርጦ በሰማዕትነት ዐረፉ ።

የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች እንዲህ ይላሉ ፤ በኔሮን የታዘዘው ስደት እንደተጀመረ ክርስቲያኖች ጴጥሮስን ለጊዜው ዘወር ብሎ ከሞት በመትረፍ ወንጌልን የማስተማር ተግባሩን እንዲቀጥል በማሰብ እንዲሸሽ ስለ ለመኑት እሺ ብሎ የከተማዋን ቅጽሮች ወጣ እንዳለ ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ሮም ከተማ ሲገባ ተገለጸለት ። ጴጥሮስም "ጌታ ሆይ ወዴት ትሄዳለህ?" ብሎ ቢጠይቀው "እንደገና ለመሰቀል ወደ ሮም እሄዳለሁ" ብሎ መለሰለት ። ይህንንም እንደሰማ ጴጥሮስ ልቡ ጥልቅ በሆነ ስሜት ስለተነካና እሱም ሰማዕትነት እንዲቀበል የጌታ ፈቃድ መሆኑን ስለተገነዘበ ወደ ሮም ተመልሶ "ጌታ እንደተሰቀለው ያለ ስቅለት ስለማይገባኝ ዘቅዝቃችሁ ስቀሉኝ" ብሎ በመስቀል በሰማዕትነት ዐረፈ ። ጴጥሮስና ጳውሎስ ያረፉትም በ66 ዓ·ም· ነው ።

በ2ኛው መቶ ዘመን የነበረው ጋይዮስ ጴጥሮስ በቫቲካን ኮረብታ ፣ ጳውሎስ በኦስቲያ መንገድ መቀበራቸውን መስክሯል ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም የዕረፍታቸውን መታሰቢያ በዓል ሐምሌ 5 ቀን ታከብራለች ።

ሉቃስ የጳውሎስ ደቀ መዝሙር ስለነበረ በጻፈው በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የጳውሎስን ሥራ አብራርቶ ሲጽፍ የጴጥሮስን በመጠኑ ጽፏል ። በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ግን ከሐዋርያት ሁሉ ስለ ጴጥሮስ የተጻፈው ይበዛል ።

<u>ሐዋርያው ጳውሎስ</u>። ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም ውጭ ከሚኖሩ የብንያም ዘር ከሆኑ አይሁድ (ፈሪሳውያን) ጠርሴስ በተባለች ቦታ ተወለደ። ክርስትናን ከመቀበሉ በፊት ሳውል ይባል ነበር ። አባቱ የሮማዊነት ዜግነት ዕድል ያገኘ ሰው ስለነበር ፣ ይህ ዜግነት ለልጁ ለጳውሎስ ተላለፈ። ወላጆቹ የአይሁድን ሃይማኖት የሚያስተምር ረቢ (መምህር) እንዲሆንላቸው ስለፈለጉ ለትምህርት ወደ ኢየሩሳሌም ሰደዱት ። እሱም ከትምህርቱ ጋር የዕለት ምግቡን ለማግኘት የሚያስችለውን ድንኳን አሰፋፍን ተማረ (የሐዋ· 18፡3) ። በኢየሩሳሌም ዝነኛ ለነበረው የሕግ መምህር



www.ethiopianorthodox.org

ለገማልያል ተማሪ በነበረበት ጊዜ አብረውት ይማሩ ከነበሩት ይልቅ በጣም ብልኅና ንቁ እንደነበረ፤ እንዲሁም አባቶቹ አይሁድ ለአስተማሩት ሃይማኖት ቀናተኛ እንደነበረ ራሱ ይናገራል (ገላ·1፥14) ።

የወንጌል ትምህርት ለጳውሎስ ከኦሪት የሚለይ ትምህርት መስሎ ስለታየው ለኦሪት ሃይማኖት ቀንቶ ክርስቲያኖችን ያሳድድ ጀመር (ገላ·1፥13) ። እነሱንም በሚያሳድድበት ጊዜ እምነተ ጠንካራነታቸውን ፥ ታጋሽነታቸውን ፥ ደፋርነታቸውን ፥ በመካከላቸው የነበረውን ፍቅር ፥ እንዲሁም የእስጢፋኖስን ንግግሮች ስለተመለከተ በልቡ ውስጥ አንድ ዓይነት የአድናቆት ስሜት ተፈጥሮበት ነበር ።

ከፍልስጥኤም ውጭ በሶርያ ውስጥ በምትገኘው በደማስቆ ብዙ አይሁድ ክርስትናን እንደተቀበሉ በሰማ ጊዜ ፥ ወዲያው እነዚህን ክርስትናን የተቀበሉትን አይሁድ አስሮ ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት የሚያስችለውን ደብዳቤ ከሊቀ ካህናቱ ተቀብሎ ፥ መንገድ መሪዎችን አስከትሎ ፥ ወደ ደማስቆ ሲሄድ ወደ ከተማው በቀረበ ጊዜ በላዩ ላይ ኃይለኛ የመብረቅ ብርሃን ስለ አንጸባረቀበት ወደ መሬት ወደቀ ። ወዲያውም "ሳውል ፥ ሳውል ፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ?" የሚል ድምፅ ሰማ ። እሱም "ጌታ ሆይ ፥ ማን ነህ?" አለው ። ጌታም "አንተ የምታሳድደኝ እኔ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ ፥ በተሳለ ችንካር ላይ ብትቆም ላንተ ይብስብሃል ..." ብሎ መለሰለት (የሐዋ· 9፡4–5 ፤ 26፥14) ። ከዚያም በኋላ ሐናንያ በጌታ ትእዛዝ በጳውሎስ ላይ እጁን ጫነበት ። አጠመቀውም ። ሦስት ቀን ሙሉ ታውረው የነበሩ ዐይኖቹም ተከፈቱ ። እህልም በልቶ በረታ ። ወዲያውኑ በየምኩራቦቹ እየዞረ አይሁድ በሙሉ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ድኅነትን እንዲያገኙ በማለት ሲሰብክ ፥ ለሃይማኖታቸው ቀናተኛ የሆኑ አይሁድ ሰምተው እንዴት ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረው ይህ የክርስትናን ሃይማኖት ያስተምራል ? በማለት በጥብቅ ተቃወሙት ። ይህም መቃወም አደገኛ ስለነበረ ፥ አይሁድ እሱን ለመግደል ስለቈረጡ እንዳያመልጣቸው የከተማውን ቅጥር ዙሪያ ሌት ከቀን በጥብቅ ያስጠብቁ ጀመር ። ክርስቲያኖችም ይህንን የወንጀል አድማ ስለሰሙ ጳውሎስን በቅርጫት ውስጥ አድርገው በቅጥሩ ላይ አውርደው እንዲያመልጥ አደረጉት ። እሱም ወደ ዓረብ ሀገር ሄደ ፤ ከዚያም ወደ ደማስቆ ተመልሶ የሐዋርያነቱን ሥራ ሲሠራ ቈይቶ ከ3 ዓመታት በኋላ ከጌታ ደቀ መዛሙርት ጋር ለመተዋወቅ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ።



www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያት ግን ስለ ጳውሎስ ማመን ተጠራጥረው ሳለ ጳውሎስን በደንብ የሚያውቀው በርናባስ ስለጠንካራ እምነቱ አረጋግጦ ነገራቸው ። ኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁድ ሊገድሉት ስለዶለቱበት ከ15 ቀናት ይበልጥ ሳይቈይ ወደጠርሴስ ሄደ (ገላ· 1 ፥ 18) ።

በአንጾኪያ የክርስቲያኖች ቍጥር እየበዛ ስለሄደ ከኢየሩሳሌም በርናባስ ሄዶ የተቻለውን ያህል ሲያስተምር ቈየ ። ነገር ግን ለዚህ ከባድ ሥራ የጳውሎስም ርዳታ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ጳውሎስን ከጠርሴስ ወደ አንጾኪያ አመጣው ። እዚያም ከፍ ያለ የማስተማር ተግባሩን ጀመረ ። ጳውሎስ በሚያስተምርበት ጊዜ ከአይሁድ ወገን ክርስትናን የተቀበሉ ሰዎች ከአሕዛብ ወገን ክርስቲያን የሆኑትን ሁሉ ከጥምቀት በኋላ እንደ ግዝረት ያሉትንና የፈሪሳውያንን ልማድ በጥብቅ መጠበቅ ይገባችኋል እያሉ ስለ አስቸገሩአቸው ፥ ክርስትናን የተቀበሉ አሕዛብ ያይሁድን ልማድ በመጠበቅ ቀስ በቀስ የክርስትናን እምነት ትተው ወደ አይሁድ እምነት ጭልጥ ብለው እንዳይሄዱና ፥ በዕድሜ የገፉትንም ክርስትናን ከመቀበላችሁ በፊት ተገዘሩ ሲሉአቸው ያመናል እያሉ ወደ ጣዖት አምልኮአቸው እንዳይመለሱ ስለ ፈራ ፥ ከበርናባስ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ከላይ የተጠቀሰውን በክርስትና መስፋፋት ላይ የተፈጠረውን አደገኛ እንቅፋት ለጴጥሮስ ፥ ለዮሐንስ ፥ ለያዕቆብና በኢየሩሳሌም ለነበሩት ሁሉ ገልጦ አስረዳቸው ። ሐዋርያትም የጳውሎስን ሐሳብ መርምረው ከተከራከሩበት በኋላ ከአሕዛብ ወገን ክርስትናን የተቀበሉ ሁሉ ከአይሁድ ወገን ክርስትናን ከተቀበሉት ጋር ትክክል መሆናቸውንና ግዝረትን ፥ ሌላውንም የፈሪሳውያንን ልማድ ለመጠበቅ የማይገደዱ መሆናቸውን በአንድ ቃል አጸደቁ ። የዚህም ጉባኤ ውጤት በጳውሎስ ፥ በበርናባስና ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን በተላኩ ሰዎች እጅ በአንጾኪያ ፥ በሶርያ ፥ በቂልቅያ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በተላከላቸው ጊዜ ፥ ከአሕዛብ ወገን ክርስትናን የተቀበሉት ሰዎች ደስታ በጣም ከፍ ያለ ሆነ ። ይህችም በ50 ዓ·ም ኢየሩሳሌም ውስጥ የተደረገችው የሐዋርያት ጉባኤ ተብላ ትጠራለች ። በዚህ አኳኋን ጳውሎስ ክርስትናን ከመዳከምና እስከ መጥፋት ከመድረስ አዳናት ለማለት ይቻላል ። ምክንያቱም በዘመናችን ያሉት ክርስቲያኖች ብዙዎቹ ከአሕዛብ ወገን የነበሩ ናቸው እንጂ ከአይሁድ ወገን ከነበሩት በመጠኑ ናቸው (የሐዋ·15፥2–35) ።

ጳውሎስ በሜዲትራንያን ባሕር ዳር ለዳር በሚገኙ ሀገሮች በኢየሩሳ



www.ethiopianorthodox.org

ሌም ፡ በሮማ ፡ በአቴና ፡ በቆሮንቶስ ፡ በኤፌሶን ፡ በተሰሎንቄ ፡ ከአንጾኪያ አንስቶ እስከ እስጳኝ ድረስ ባሉ ሀገሮች ክርስትናን ከፍ ባለ ትጋት አስተምሮአል ። ሕዝቡን አስተምሮ ለመሠረታቸውም አብያተ ክርስቲያናት የእምነት ማጽኛ ፡ የግብረ ገብነት መሪ የሚሆኑ 14 መልእክታት ጽፎላቸዋል ።

አራት ጊዜ ባደረጋቸው ጉዞዎች በየቦታው እየዞረ በሚያስተምር በት ጊዜ አብረው በመሥራት የረዱት በርናባስ ፡ ወንጌላዊው ማርቆስ ፡ ሲላስ (ስልዋኖስ)፥ ቲቶ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ወንጌላዊው ሉቃስና ሌሎችም ነበሩ ።

<u>ሐዋርያው ዮሐንስ</u> ። ጌታ ይወደው የነበረው የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ በፍልስጥኤም ፡ ከፍልስጥኤም ውጭም ክርስትና እንድትስፋፋ ከጴጥሮስ ጋር በመተባበር አስተምሯል (የሐዋ· 4 ፡ 1 — 22 ፤ 8 ፡14) ። እንዲሁም ኢየሩሳሌም ውስጥ በተደረገችው በሐዋርያት ጉባኤ ተገኝቶ ለተፈጸሙት ሥራዎች ተካፋይ ሆኖ ነበር (ገላ· 2 ፡ 9) ። ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ እመቤታችንን እንዲያገለግላት አደራ የሰጠው ለዚሁ ለወንጌላዊው ዮሐንስ ነበር (ዮሐ· 19 ፡ 26) ።

ከጳውሎስ ዕረፍት በኋላ በ66 ዓ·ም ዮሐንስ ከኢየሩሳሌም ወደ ኤፌሶን ሄዶ እዚያ ተቀምጦ በትንሿ እስያ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት በማስተማር ሲያገለግል ቈየ ። በዶሚቲያኖስ ዘመነ መንግሥት (81—96 ዓ·ም) ዮሐንስ ወደ ፍጥሞ ደሴት ተሰዶ በእስር ቤት ሳለ እዚያው ራእየ ዮሐንስን ጻፈ ። ከዶሚቲያኖስ ሞት በኋላ ወደ ኤፌሶን ተመልሶ ፡ "ልጆቼ እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ ። የጌታ ትእዛዝ ይህች ስለሆነች ፡ ይህችን በመፈጸም ትእዛዛቱን ሁሉ ለመፈጸም ትችላላችሁ" እያለ ያስተምራቸው ነበር ። ዮሐንስ ኤፌሶን ውስጥ እስኪያረጅ ድረስ ቈይቶ በትራይአኖስ ዘመነ መንግሥት (98—117 ዓ·ም) መጀመሪያ ላይ ዐረፈ ይባላል ። ጥቂቶች ደግሞ በማቴ· 16፡28 ፤ በዮሐ· 21፡22 የተጻፈውን በመከተል አልሞተም ይላሉ ። እሱም ከራእየ ዮሐንስ በስተቀር በስሙ የሚጠሩ አንድ ወንጌልና ሦስት መልእክታት ጽፏል ። በጻፈው ወንጌል ውስጥ ምሥጢረ ሥላሴን አምልቶና አጉልቶ ስለጻፈ ነባቤ መለኮት (ቴዎሎጎስ) የሚል ስም ተሰጠው ።

<u>ሐዋርያው ያዕቆብ</u> ። የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ ኢየሩሳሌም ውስጥ ለተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኖ በማስተማር ከፍ ያለ



www.ethiopianorthodox.org

አገልግሎትን አበርክቷል ። የክርስትናን ትምህርት በትጋት ማስተማሩ በአይሁድ ዘንድ እንደ ወንጀል ስለ ተቈጠረበት ፣ ሄሮድስ አግሪጳ አይሁድን ለማስደሰት በሰጠው ትእዛዝ መሠረት በ44 ዓ·ም እንገቱን በሰይፍ ተቆርጦ በሰማዕትነት ዐረፈ (የሐዋ· 12 ፣ 2) ።

<u>ሐዋርያው እንድርያስ</u> ። የጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ለሐዋርያ ነት በጌታ ቃል መጀመሪያ ተጠራ ። ጌታንም ከመከተሉ በፊት የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ነበር (ዮሐ· 1 ፣ 41) ። መጀመሪያ የስብከት ሥራውን በፍልስጥኤም ጀመረ ። ቀጥሎም በእስኪሲያ ፣ በስራኪ ፣ በመቄዶንያ ፣ በትንሿ እስያ ፣ በግሪክ ሀገር አስተማረ ። የቊስጥንጥንያን ቤተ ክርስቲያን የመሠረተ እሱ ነው ይላሉ ። ፓትራ በምትባለዋ ሀገር ሲያስተምር በጣዖት አምላኪዎች እጅ በመስቀል ላይ በደንጊያ ተወግሮ በሰማዕትነት ዐረፈ ። የሐዋርያው እንድርያስን አጽም (ራስ ቅል) የኢጣሊያ የመስቀል ጦረኞች በ1208 ዓ·ም ከቊስጥንጥንያ ወደ ሮም ወስደውት ሲኖር በ1964 ዓ·ም ፖፕ ጳውሎስ 6ኛ ለግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተመልሶ እንዲሰጥ አደረገ ።

<u>ሐዋርያው ቶማስ (ዲዲሞስ)</u> ። ጌታ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለሐዋርያት በተገለጠበት ጊዜ ቶማስ ስላልነበረ ፣ የጌታ መከራ መስቀልን ተቀብሎ መሞት እጅግ አሳዝኖት ለብቻው ሆኖ ሲያዝን ከቈየበት ቦታ ሲመለስ ጌታን አየነው ቢሉት ፣ ሳላይ አላምንም አላቸው ። ጌታም እንደ ገና ለሁሉም ተገለጠላቸው ። በዚያን ጊዜ ቶማስ በጣቱ የጌታን የተወጋ ጎኑን ፣ የተቸነከረውን እጁንና እግሩን ዳስሶ አይቶ አመነ (ዮሐ· 20 ፣ 19—28) ። ቶማስ በፋርስ በሕንድ አስተማረ ።

<u>ሐዋርያው ማቴዎስ (ሌዊ)</u> ። ማቴዎስ የቀረጥ ሥራውን በሚያከና ውንበት ጊዜ ጌታ ስለጠራው ወዲያው በቤቱ ታላቅ ግብዣ አድርጎ ጓደኞቹ የነበሩ ቀራጮችን ወደ ጌታ አቅርቦ ካገናኛቸው በኋላ ሁሉንም ትቶ ተከተለው (ሉቃ· 5 ፣ 27—32) ። ጌታን ከመከተሉ በፊት ሌዊ ይባል ነበር (ማር· 2 ፣ 14) ። ከተከተለው በኋላ ግን ማቴዎስ ተብሎ ይጠራ ጀመር (ማቴ· 9 ፣ 9) ። በስሙ የሚጠራውን ወንጌል የጻፈው እሱው ነው ።

ማቴዎስ መጀመሪያ በፍልስጥኤም ፣ ቀጥሎ በኢትዮጵያ ፣ በፋርስ ፣ በመቄዶንያና በሕንድ አስተማረ ።

<u>ሐዋርያው ፊልጶስ</u> ። የቤተ ሳይዳው ፊልጶስ ጌታ ተከተለኝ ባለው



www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ወዲያው ጥሪውን በመቀበል ጌታን ከመከተሉም በተጨማሪ ናትናኤልንም ወደ ጌታ ያቀረበ እሱ ነው ። (ዮሐ· 1 ፡ 44 47) ። እንዲሁም የአሕዛብን ወገን (ነገድ) የወከሉ ግሪኮችም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጌታ ቀርበው የተማሩ በፊልጶስና በእንድርያስ አቅራቢነት ነበር (ዮሐ· 12 ፡ 20 22) ።

ፊልጶስ ሳያይ ለማመን የሚያዳግተው ሰው ስለነበር የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ኢየሱስን "ጌታ ሆይ ፡ አብን አሳየንና ይበቃናል" ብሎ ቢጠይቅ ፡ ጌታም "አንተ ፊልጶስ ፡ ይህን ያህል ዘመን ከናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን ? እኔን ያየ አብን አይቷል ፡ እንዴትስ አንተ አብን አሳየን ትላለህ ? እኔ በአብ እንዳለሁ ፡ አብም በኔ እንዳለ አታምንምን ? ..." (ዮሐ· 14 ፡ 8 11) በማለት ለክርስትና እምነት መሠረት የሆነውን የእግዚአብ ሔር አብንና የእግዚአብሔር ወልድን አንድነት ምሥጢር አስረዳው ።

ፊልጶስ ወንጌልን ትንሿ እስያ ውስጥ በምትገኘው በፍርግያ አስተማረ ።

ሐዋርያው በርተሎሚዎስ። ጌታችንን ከተከተለ በኋላ የወንጌልን ትምህርት በዓረብ ሀገር ፡ በሕንድና በአርመን አስተማረ ።

ሐዋርያው ስምዖን (ናትናኤል) ለሕገ ኦሪት ቀናተኛው ፡ ቀነናዊው ፡ የቃናው ሰው ። ለሐዋርያነት ከመጠራቱ በፊት ለሕገ ኦሪት ቀናተኛ ፈሪሳዊ ስለነበር ቀናተኛ ተባለ ። እሱም ወንጌልን በመስጴጦምያ ፡ በግብጽ፣ በሰሜን አፍሪካ ሰበከ (ማቴ· 10 ፡ 4 ፤ ዮሐ· 21 ፡ 2) ።

ሐዋርያው ያዕቆብ ። የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ከፍልስጥኤም በስተቀር ወንጌልን በፋርስና በግብጽ አስተምሯል የሚሉ አሉ ።

ሐዋርያው ይሁዳ (ልብድዮስ ፡ ታዴዎስ) ። ይሁዳ በፍልስጥኤም ፡ በሶርያ ፡ በአርመን ፡ በመስጴጦምያና በፋርስ አስተማረ ።

ሐዋርያው ማትያስ ። ጌታን ሸጦ በገዛ እጁ ታንቆ በሞተው በአስቆሮቱ ይሁዳ ፈንታ በዕጣ በመመረጥ ከሐዋርያት ተራ ተቈጠረ (የሐዋ· 1 ፡ 15 — 26) ። እሱም ወንጌልን በግብጽ ፡ በቀጰዶቅያና በኑብያ ሰበከ ።

ወንጌላዊው ማርቆስ (ዮሐንስ) ። ኢየሩሳሌም ውስጥ ክርስቲያኖች በቤቷ ለጸሎት ይሰበሰቡ የነበረችው የማርያም ልጅ ነው (የሐዋ· 12 ፡ 12)። በርናባስ አጎቱ ነበር ። ከጳውሎስም ጋር አብሮ አስተምሯል ። በተለይ ግን የጴጥሮስ ተከታይና ተማሪ ስለነበር ልጄ ይለዋል (1ጴጥ.



www.ethiopianorthodox.org

5 ፥ 13) ። ከጴጥሮስ የሰማውን (የተማረውን) መሠረት በማድረግ በስሙ የሚጠራውን ወንጌል መጻፉን የኢራጶሊስ ጳጳስ ፓፒያስ መስክሮአል ። ማርቆስ ወንጌልን በማስተማር የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን መሥርቶ በሰማዕትነት ዐረፈ ።

የቬኑስ ነጋዴዎች በ፱ኛው መቶ ዘመን የቅዱስ ማርቆስን አጽም ወደ ሀገራቸው ወስደው በከተማቸው ውስጥ ባለው በታላቁ የቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል በክብር አስቀምጠውት ከቈየ በኋላ በ1968 ዓ.ም. ወደ ግብጽ ተመልሶ አዲስ በተሠራው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክብር ተቀምጧል (ዐርኛል) ።

ወንጌላዊው ሉቃስ ። አንጾኪያ ውስጥ የግሪክ ወገን ከሆኑ ጣዖት አምላኪዎች ተወለደ ። በጳውሎስ አስተማሪነት ክርስትናን ተቀብሎ የእሱ ደቀ መዝሙር ሆኖ ሲያስተምር ኖረ (2 ጢሞ. 4፡11) ። ሐኪምም ነበር (ቈላ.4 ፡ 14) ። ሠዓሊም እንደ ነበረና የእመቤታችንን ሥዕል በመጀመሪያ የሣለ እሱ ነው በማለት ብዙዎች ይተርካሉ ።

በስሙ የሚጠራውን ወንጌልና የሐዋርያትን ሥራ የጻፈ እሱ ነው ። ከመምህሩ ከጳውሎስ ዕረፍት በኋላ በአካይያ ወንጌልን አስተማረ ። ወንጌልን ሲሰብክ ሲባስ በተባለ ሀገር ውስጥ በሰማዕትነት ዐረፈ ።

ማሳሰቢያ ፥ 1ኛ/ ማርቆስና ሉቃስ ቍጥራቸው ከሐዋርያት ሳይሆን ከሰባ ሁለቱ አርድእት ነው ። እንዲሁም ቍጥራቸው ከሰባ ሁለቱ አርድእት የሆነው በኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የነበረው የጌታ ወንድም የተባለው ያዕቆብና ወንድሙ ይሁዳ በየስማቸው የሚጠሩትን መልእክታት ጽፈዋል ።

2ኛ/ ከዚህ በላይ ታሪካቸውን የተመለከትነው የጌታ ደቀ መዛሙርት እላይ በተጠቀሱት ሀገሮች ወንጌልን በትጋት ሲያስተምሩ አንገታቸውን በሰይፍ በመቈረጥ ፥ በመሰቀል ፡ በእሳት በመቃጠል ፥ በመጋዝ በመሰንጠቅና እነዚህን የመሳሰሉ ልዩ ልዩ ሥቃዮችን በመቀበል በሰማዕትነት ዐረፉ ።

## ፀሐዋርያት ዘመን ስለ ክርስትና መስፋፋት የረዱ ሴቶች

ሴቶች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሲያስተምር ከነበረበት ዘመን ጀምረው ስለ ክርስትና መስፋፋት ከፍ ያለ አገልግሎትን አበርክተዋል ። ጌታ ሐዋርያትን አስከትሎ ወንጌልን በየቦታው እየዞረ



www.ethiopianorthodox.org

ሲያስተምር ማርያም መግደላዊት ፣ ዮሐና ፣ ሶስናና ሌሎችም ሴቶች በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር (ሉቃ· 8 ፣ 1 — 3) ። የአልዓዛር እኅቶች ማርታ ምግብ በማዘጋጀት ፣ ማርያም የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ያገለግሉት ነበር (ሉቃ· 10 ፣ 38 — 42) ። ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ ሴቶች ሸኙትውታል (ማር. 15 ፣41) ። ተሰቅሎ ሳለ በታላቅ ኀዘን ተውጠው በመስቀሉ ሥር ነበሩ (ዮሐ· 19 ፣ 25) ። ትንሣኤውንም በመጀመሪያ ያበሠሩ ሴቶች ናቸው (ማር· 16 ፣ 1 — 13) ።

የማርቆስ እናት ማርያም ቤቷን ለኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች መሰብሰቢያና መጸለያ አድርጋ ነበር (የሐዋ· 12 ፣ 12) ። ፌቤን በቆሮንቶስ የክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነበረች ። ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች የጻፋትን መልእክት የወሰደችለት እሷ ናት (ሮሜ 16 ፣ 1) ። ብዙ ሴቶች ለድኾች ፣ ለሙት ልጆች ምጽዋት በመስጠት ይረዱ ነበር ። ከነሱም አንዲ ጣቢታ ነበረች (የሐዋ· 9 ፣ 36) ።

በሐዋርያት ዘመን ከአሕዛብና ከአይሁድ ወደ ክርስትና የመጡት በዕድሜ የገፉ ሴቶች ቍጥር እጅግ ብዙ ስለ ነበር ፣ የተጠመቁትን ሴቶች ሜሮን የሚቀቡአቸው ፣ የታመሙትንም ቀንዲል የሚቀቡ ሴቶች ነበሩ ። እነሱም ዕድሜአቸው ከስልሳ ዓመት ያላነሰ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ባልቴቶች ነበሩ (1 ጢሞ. 5 ፣ 9 — 10) ። በዚህ አኳኋን ከላይ የተጠቀሱት ባልቴቶች የሚያገለግሉት ሴቶችን ብቻ ስለ ነበር ፣ እንደ ዲያቆኑ መላ የቤተ ክርስቲያንን አባሎች ስለማያገለግሉ የተሟላ የዲቁና ተግባር አልነበራቸውም ።

## ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች

ሐዋርያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውን ትምህርት ለክርስቲያኖች መመሪያና አጽናኝ እንዲሆናቸው ሐዲስ ኪዳንን እንደጻፉ ሁሉ ፣ ከሐዋርያት ቀጥለው በአንደኛውና በሁለተኛው መቶ ዘመን ላይ የተነሡት የክርስትናን ትምህርት ከሐዋርያትና ከደቀመዛሙርቶቻቸው የተማሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ክርስቲያኖች በደረሱባቸው ስደቶች ምክንያት ተስፋ እንዳይቈርጡ አጽናንተዋቸዋል ። እንዲሁም በየጊዜው በተነሡት መናፍቃን ትምህርት እንዳይታለሉ ለመምከር ፤ የክርስቲያኖችን ፍላጎት ለማርካት ፣ በእምነታቸው ጸንተው በመኖር የእግዚአብሔርን ልጅነት የሚያሰጡአቸውን መጻሕፍት ጽፈዋል ። ጽሑፎቻቸውም የተዘጋጁት በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ትምህርቶች ላይ ተመሥርተው



www.ethiopianorthodox.org

ነበር ።

ከነሱም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ <u>የሮም ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ቀሌምንጦስ (91 — 100)</u> ።

ቀሌምንጦስ ሮም ተወልዶ መንፈሳዊ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ማዕርገ ክህነትን ከሐዋርያው ጴጥሮስ ተቀብሎ አራተኛው የሮም ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ሆነ ።

እሱም በሮምና በአካባቢዋ ሀገሮች ወንጌልን በትጋት አስተምሮ ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ መለሰ ።

አውሳብዮስና አንዳንድ ሊቃውንት ቀሌምንጦስ ክርስትናን የተቀበለ በጳውሎስ አስተማሪነት ስለነበረ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ መልእክቱ 4 ፡ 3 ያነሣው በማስተማር ሥራው ረዳቱ የነበረውን ይህንኑ ቀሌምንጦስን ነው ይላሉ ።

ቀደም ሲል ቆሮንቶስ በነበሩ ምእመናን መካከል የተነሣውን ሁከት (1ቆሮ. 1፡10 17) ሐዋርያው ጳውሎስ በምክርና በተግሣጽ ቢያበርደውም ትሉ ፡ በቀሌምንጦስ ጊዜ ደግሞ ሁከቱ እንደገና ያገረሸው ጥቂት ሰዎች በቅናት መንፈስ በመመራት በካህናቱ ላይ በመነሣታቸው ነበር ። ቀሌምንጦስ ይህንን አሳዛኝ ዜና እንደሰማ እንደዚህ ያለውን መጥፎ ተግባር እንዲተውና በመካከላቸውም ሰላም እንዲሰፍን ለመምከር በ96 ዓ·ም በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ጥቅሶች (ትምህርት) ላይ የተመሠረቱ (የተደገፉ) ሁለት መልእክታት ጽፎ በየጊዜው በጸሎተ ቅዳሴ ወቅት ለምእመናን እንዲነበብላቸው በማለት ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ላከ ። የቆሮንቶስ ጳጳስ አቡነ ዲዮናስዮስ በ170 ዓ·ም ለሮሙ ፖፕ ለሶቴር በላከው ደብዳቤ በቀሌምንጦስ የተጻፈችው መጀመሪያዪቱ መልእክት በሰንበትና በበዓላት ቀን በቤተ ክርስቲያን ለሚሰበሰቡ ምእመናን በየጊዜው በመነበብ ላይ መሆኗን ገልጾለታል ። እንዲሁም ሄሬኔዎስና ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ከዚችው መልእክት ጥቅሶችን በጽሑፎቻቸው ውስጥ በማስገባት በሮሙ ጳጳስ በቀሌምንጦስ መጻፏን መስክረዋል ።

ቀሌምንጦስ በዚችው በመጀመሪያዋ መልእክት ውስጥ ስለ ጴጥሮስ ሮም መቀመጥና ማስተማር ፡ ጳውሎስ ወደ እስጳኝ ስላደረገው ጉዞ ፤ ኔሮን ባስነሣው ስደት ጳውሎስና ጴጥሮስ ከብዙ ክርስቲያኖች ጋር በሰማዕትነት ስለማረፋቸው ፡ ማዕርገ ክህነት ከጌታና ከሐዋርያት ሲወርድ ሲዋረድ



www.ethiopianorthodox.org

ስለመምጣቱና ምእመናንም ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ካህናት የሚሰጡአቸውን ትምህርት እንዲቀበሉና እንዲታዘዙ መዘተ· በማለት ጽፏል ።

የሁለተኛዋ መልእክት (መጽሐፍ) ይዘቷ ምእመናን ንስሐ ገብተው እግዚአብሔርን በሙሉ ልቦናቸው እንዲያገለግሉ ፤ የተቀደሰ ኑሮን እንዲኖሩና ትንሣኤ ሙታን መኖሩን አምነው እንዲቀበሉ የሚገልጽ ስብከት ነው ።

ቀሌምንጦስ ከጳውሎስ መልእክታት ውስጥ ከአንደኛ ቆሮንቶስ ፤ ከሮሜና ከኤፌሶን መልእክታት አንዳንድ (ጥቂት) ጥቅሶችን በጽሑፎቹ ውስጥ አስገብቷል ።

ከላይ የተጠቀሱት የሁለቱ መልእክታት ይዘት ጠቃሚ ከመሆኑ የተነሣ አንዳንድ ሊቃውንት ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር በማስተካከል ሲቀበሉአቸው ፤ ሌሎች ደግሞ ከአዋልድ (ከአፖክሪፋ) መጻሕፍት ጋር ይቈጥሩአቸዋል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የቀሌምንጦስን መልእክታት ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር በማስተካከል ተቀብላቻቸዋለች ።

እላይ ከተጠቀሱት በስተቀር በጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ጽሑፎቻቸው ተቀባይነትን እንዲያገኙ በማሰብ በአዘጋጆች ስም ሳይሆን በቀሌምንጦስ ስም የተጻፉ የክሕደት ትምህርቶችን የያዙ ፤ ፕሴውዶ ክሌምንትስ (በቀሌምንጦስ ስም በሐሰት የተጻፉ መጻሕፍት) በሚል ስም የሚጠሩ ብዙ አዋልድ መጻሕፍት በምእመናን ዘንድ ተሰራጭተው ነበር።

ቀሌምንጦስ ከአሕዛብ ብዙዎችን ወደ ክርስትና መመለሱ እንደወንጀል ስለተቈጠረበት በንጉሥ ትራያኣኖስ (ትራጅአን) ትእዛዝ በስደት ሲንገላታ ከቈየ በኋላ አንገቱ ላይ በመልሕቅ ታስሮ ጥቁር ባሕር ውስጥ ተጥሎ በሰማዕትነት ዐረፈ ።

2ኛ/ <u>የአንጾኪያ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ አግናጥዮስ (ቴዎፎሮስ) 35-110 ።</u>

ከቅዱስ ጴጥሮስና ከኤውዲዮስ ቀጥሎ ሦስተኛው የአንጾኪያ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ የተሾመው የወንጌላዊው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር አግናጥዮስ ነበር ። ደቀ መዛሙርቱ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ቀርበው "በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን ? " ባሉት ጊዜ ስለ ትሕትና ለማስተማር "ሕፃንም ጠርቶ በመካከላቸው አቁሞ እውነት እውነት እላችኋለሁ ... እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ በመንግሥተ



www.ethiopianorthodox.org

ለማየት የሚበልጥ እሱ ነው" (ማቴ·18፥ 1-4) በማለት በመካከላቸው ያቆመው ሕፃን አግናጥዮስ ነበር ። ስለዚህ አንዳንድ ሊቃውንት ለአግናጥዮስ በግሪክኛ (በጽርዕ) የተሰጠው ቴዎፎሮስ የሚለው ስም እግዚአብሔር ወልድ በእቅፉ የተሸከመው ማለት ነው ሲሉ ፣ ሌሎች ደግሞ ራሱ አግናጥዮስ እግዚአብሔርን በመላ ልቡ (ሰውነቱ) የተሸከመ ማለት ነው ይላሉ ።

አግናጥዮስ ሰማዕትነትን ለመቀበል በእስር በሮማውያን ወታደሮች ታጅቦ ከሶርያ ወደ ሮም ሲወሰድ እዝሚርን በሰነበተበት ጊዜና ሮም እስኪደርስ ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ በዚያ በስደቱና በመከራው ዘመን ክርስቲያኖች ለካህናት እንዲታዘዙ ለመምከር ፣ ለማጽናናት ፣ ከመናፍቃን ትምህርት እንዲርቁ በማለት በሮምና በትንሿ እስያ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አጫጭር ለክርስቲያኖች በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሰባት መልእክታት ጽፏል ። ይኸውም ወደ ሮም ሲጓዝ እዝሚርን ውስጥ የአቡነ ፖሊካርፕ እንግዳ ሆኖ በሰነበተበት ወቅት ኤፌሶን፥ ማግኔሲያ ፣ ትራሌስና ሮም ለነበሩት ክርስቲያኖች አራት መልእክታት ጽፎ ሲልክ ፣ ከእዝሚርን ተነሥቶ ጉዞውን በመቀጠል ጥሮአስ እንደደረሰ ፊላደልፊያ ፣ እዝሚርን ለነበሩ ክርስቲያኖችና ለአቡነ ፖሊካርፕ ሦስት መልእክታት ጽፎ ልኳል ። በእስረኛነት ይዘውት የሄዱት ወታደሮችም መልእክታቱን በሚጽፍበትና በሚልክበት ወቅት አንዳችም መሰናክል (ተቃውሞ) አላደረጉበትም ።

አንዳንድ ሊቃውንት ቀደም ሲል ምንም ያልጻፈው አግናጥዮስ እዝሚርን ሲደርስ በዛ ያሉ መልእክታትን መጻፍ የጀመረው በአቡነ ፖሊካርፕ አነሳሽነት (ጉትጎታ) ምክንያት ጭምር ነበር ይላሉ ። መልእክታቱንም በእጅ በመጻፍ የረዳው የኤፌሶኑ ዲያቆን ብሩሑስ ነበር።

ወደ ሮም በጻፉት መልእክቱ ሰማዕትነት ለመቀበል ስላደረበት ጉጉት ሲገልጽ ፣ በሌሎች መልእክቶቹ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን ከቅድስት ድንግል ማርያም ስለመወለዱ ፣ ወንጌልን ስለማስተማሩ ፣ ስለመሰቀሉ ፣ ስለሞቱና ስለ ትንሣኤው አብራርቶ ጽፏል። እንዲሁም ስለቅዱስ ቊርባንና እውነተኛዋን የክርስትና እምነት ጠባቂዎች ጳጳሳት ስለመሆናቸው ገልጿል ። በተጨማሪም የክርስቶስን ሥጋ መልበስና (መዋሐድና) መከራ መቀበል ከሚክዱ ዶሴቲክስ



www.ethiopianorthodox.org

ከተባሉት መናፍቃን ትምህርት ክርስቲያኖች እንዲርቁ በመምከር ጽፏል። እንዲሁም ክርስትናን ከመቀበላችሁ በፊት የአይሁድን ሃይማኖትና የረበናትን ልማድ ተከተሉ እያሉ ምእመናንን ግራ ያጋቡ ከነበሩት ቢጽ ሐሳውያን እንዲጠነቀቁና እንዲርቁ ምክሩን ለግሷል ።

መምህሩ ወንጌላዊው ዮሐንስም በወንጌሉና በመልክታቱ ውስጥ እላይ የተጠቀሱት የሁለቱ ኑፋቄዎች እራማጅ የሆኑ አባላት ያስተማሩትን የክሕደት ትምህርት በጥብቅ ተቃውሞ ጽፏል ።

አግናጥዮስ ስለ ሦስቱ ማዕርገ ክህነት አብራርቶ ጽፏል ። አግናጥዮስ በክርስትና እምነቱ በመጽናቱና ምእመናንም እንዲጸኑ በማስተማሩ በትራይአኖስ ዘመነ መንግሥት በክርስቲያኖች ላይ በተነሣው ስደት ወቅት በ110 ዓ·ም ወደ ሮም ተወስዶ ኮሎሲየም በተባለው የቲያትር ቦታ ትርእይቱን በፈንጠዝያ በሚመለከተው በሮማ ሕዝብ ፊት ለአንበሶች በመጣል በሰማዕትነት ዐረፈ ። ከአውሬዎች የተረፉት አጽሞቹ አብረው ወደሮም በሄዱት ወዳጆቹ ወደ አንጾኪያ ተወስደው በክብር ተቀምጠዋል ይባላል ።

3ኛ/ <u>የእዝሚርን ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ፖሊካርፕ (አቡሊካርዮስ) 69–155 ።</u>

ፖሊካርፕ እዝሚርን ውስጥ በ69 ዓ·ም ተወለደ ። እሱም ሐዋርያት ወንጌልን በዓለም አስተምረው ካለፉ በኋላ ኤፌሶን ውስጥ በሕይወት የነበረው የወንጌላዊው ዮሐንስ ደቀመዝሙርና የኢሬኔዎስ አስተማሪ ነበር ። በመምህሩ በዮሐንስ የእዝሚርን ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ተሹሞ ሳለ ክርስቲያኖችን ለማጽናናትና ከመናፍቃን ትምህርት እንዲርቁ ለመምከር ሲል ብዙ መልእክታት ጽፏል ። ከመልእክታቱም ውስጥ እስከ ዛሬ ድረስ ያለችው ወደ ፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የላካት መልእክት ብቻ ናት ። ይህቺውም መልእክት የተጻፈችበት ምክንያት የሚከተለው ነው ። ቅዱስ አግናጥዮስ ሰማዕትነት ለመቀበል ወደ ሮም ሲጓዝ ተገናኝተው ላነጋገሩት የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ለእምነታቸው ማጽኛ የሚሆን መልእክት ቅዱስ ፖሊካርፕ አዘጋጅቶ እንዲልክላቸው እንዲጠይቁት ነግሮ በመከራቸው መሠረት የአግናጥዮስን መልእክታት ቅጅዎችና የራሱን መልእክት ጭምር እንዲልክላቸው ፖሊካርፕን ጠየቁት ። እሱም የጠየቁትን ክርስቲያኖች ፍላጎት ለማርካት እራሱ ዘንድ የነበሩትንና ዲያቆን ብሩሑስ ያስቀመጣቸውን የአግናጥዮስ መልእክታት ቅጅዎች ሰብስቦ ራሱ ካዘጋ



www.ethiopianorthodox.org

ጃት መልእክት ጋር ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ላከላቸው ።

ፖሊካርፕ በፊልጵስዩስ መልእክቱ ውስጥ እንደ ወዳጁ እንደ አግናጥዮስ የምእመናን ሞራል የታረመ እንዲሆን ፣ ምእመናን በችግር ላይ ለወደቁት ምጽዋት እንዲሰጡ ፤ ቤተ ክርስቲያን ሀገሪቱን ለሚያስተዳድሩ መጸለይ እንደሚገባት ፤ ስለ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ከኃጢአት ለማዳን ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለድ ወዘተ አብራርቶ ጽፏል። በዚችው መልእክት ውስጥ ከጳውሎስ መልእክታት፣ ከቀሌምንጦስ ዘሮም መልእክታት ብዙ ጥቅሶችን አስገብቷል ።

የግኖስቲክስን ኑፋቄ መሥራች የሆነውን የቫሌንቲኑስን የክሕደት ትምህርት ተቃውሟል ። እንዲሁም በ155 ዓ·ም ፖሊካርፕ ሮምን ሲጐበኝ የፋሲካን በዓል በራሱና በጓደኞቹ እንደምትመራው እንደ ታናሿ እስያ ቤተ ክርስቲያን አይሁድ በሚያከብሩበት ቀን የሮም ቤተ ክርስቲያንም እንድታከብር ፖፕ አኒሴቱስን ቢጠይቀው አይሆንም ስላለው ሁለቱም ከስምምነት ላይ ሳይደርሱ ወደ ስብከተ ሀገሩ ወደ እዝሚርን ተመለሰ ። በመካከላቸው ግን የመለያየት መንፈስ አልተፈጠረም ነበር ።

ፖሊካርፕ በአንጦንዩ ፒዩ ዘመነ መንግሥት በ155 ዓ·ም ተይዞ ክርስቶስን እንዲክድ ቢጠየቅ 86 ዓመታት ሙሉ ሳገለግለው ያልበደለኝ ንና የሚወደኝን አምላኬን አልክድም በማለት በእምነቱ ስለጸና እዝሚርን በነበረው የጨዋታ እስታዴየም (ቦታ) ውስጥ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት በእሳት ተቃጥሎ በሰማዕትነት ዐረፈ ። ከቃጠሎው የተረፉ አጽሞቹም በክርስቲያኖች ተወስደው ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክብር መቀመጣቸው ይተረካል ።

እላይ ከተጠቀሱት ሌላም እንደ ኢራጵሊስ ጳጳስ እንደ ፓፒያስ የመሳሰሉም ተነሥተው ክርስትናን አስተምረዋል ።

## የስደት ዘመኖች (ዘመነ ሰማዕታት) 64–313 ዓ·ም
## ቤተ ክርስቲያን ስለ ቀጥተኛው እምነቷ የተጋደለችበት ዘመን ለክርስትና ትምህርት መስፋፋት እንቅፋት የሆኑትና በክርስቲያኖች ላይ የተደረገውን ስደት ያመጡት ምክንያቶች

ክርስትና መስፋፋት እንደ ጀመረች ወዲያው እርምጃዋን የሚያሰናክሉ ከፍ ያሉ እንቅፋቶች ገጠሟት ። ከ64–313 ዓ·ም ድረስ በክርስቲያኖች ላይ ከፍ ያለ ሥቃይና ስደት ደረሰባቸው ። ጌታ በምእመናን ላይ ይህ



www.ethiopianorthodox.org

እንደሚደርስባቸው ቀደም ብሎ እንዲህ ሲል ተናግሯል ፡ "እኔን አሳደውኝ እንደ ሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዷችኋል" (ዮሐ. 15፡20 ፡ ማቴ. 5፡11) ።

በዚያን ጊዜ ከነበሩት ከዓለም ሃይማኖቶች አንዱ ነገሥታቱን ማምለክ ስለነበረ ፡ እነሱን የማያመልክና መሥዋዕት የማያቀርብ እንደ ወንጀለኛ ይቈጠር ነበር ። ስለዚህ የሮም ነገሥታት አማልክት ነንና አምልኩን ሲሉ ፡ ክርስቲያኖች የምናመልክ እግዚአብሔርን ነው ። ነገሥታቱ ግን ገዥዎቻችን ስለ ሆናችሁ ከልብ በመውደድ እናከብራችኋለን ስላሉ እንደ ወንጀለኞች ተቈጠሩ ። ስለዚህ ነገሥታቱንና ጣዖታቱን አለማምለካቸው እንደ በጥባጮችና አደገኞች አስቈጠራቸው ። ሰላማዊነታቸውንም ለማስረዳት ቢሞክሩ ሰሚ አጡ ። ጣዖት ጠራቢዎች ሥራቸው እንዳይቋረጥ በማሰብ ፡ አይሁድም ሕዝባቸው ወደ ክርስትና እምነት ጭልጥ ብሎ እንዳይሄድ በመፍራት ክርስቲያኖችን እንደ ጠላት ይመለከቷቸው ነበር ።

## ከሕዝቡ ዘንድ በክርስቲያኖች ላይ የቀረቡት ስብቀቶችና የሐሰት ክሶች የሚከተሉት ናቸው

1ኛ/ ክርስቲያኖች ጣዖት ማምለክን እምቢ ብለው እውነተኛውን አምላክ በማምለካቸው አምላክ የሌላቸው ከሐዲዎች ተባሉ ።

2ኛ/ የተሰበሰበውን ሕዝብ ለማስደሰት ከግብረገብነት ውጭ ወደሚሠሩባቸው የቲያትር ቦታዎች ፡ ሰዎችና አውሬዎች ፡ እንዲሁም ሰዎችና ሰዎች ወደሚዋጉባቸውና ያለ ወንጀል በግፍ የታሰሩ እስረኞች ለአንበሶች ወደሚጣሉባቸው ቦታዎች ክርስቲያኖች ለማየት ስለማይሄዱ ግማሽ ሰዎች ተባሉ ።

3ኛ/ የጌታን ሥጋና ደም በመቀበላቸው ሕፃናትን እያረዱ ደማቸውን ጠጥተው ሥጋቸውን ይበላሉ ተባሉ ።

4ኛ/ በሮም ግዛት ውስጥ ረኀብ ፡ ቸነፈር ፡ የመሬት መንቀጥቀጥና እነዚህን የመሳሰሉ በደረሱ ቍጥር በከሐዲዎች በክርስቲያኖች ምክንያት የሮም አማልክት ተቈጥተው ያወረዱብን ቅጣቶች ናቸው ብለው ያምኑ ነበር ።

እንደነ ኰአድራቱስ ፡ አሪስቲዲስ ፡ ጀስቲን ፡ ታቲያን ፡ አቲናጎራስ ፡ ቴዎፍሎስ ዘአንጾኪያ ወዘተ. የመሳሰሉ አፖሎጂስቶች ለክርስትና



www.ethiopianorthodox.org

እምነት ጠበቃ (ተሟጋች) በመሆን ከሕዝቡ ፣ ከገዥዎችና ከነገሥታቱ ፊት ድረስ እየቀረቡ በቃልና በጽሑፍ ከላይ የተጠቀሱት ክሶች ውሸት መሆናቸውን ፤ በዓለም ካሉት እምነቶች ሁሉ እውነተኛዋ ሃይማኖት ከአሪት ጀምሮ ትንቢት በተነገረለት በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተችው ክርስትና ብቻ መሆኗን ፤ የክርስትናም ትምህርት የሕዝቡን ጠባይ የሚያርም መሆኑን በመግለጽ ይከራከሩ ነበር ። በዚህ አኳኋን ክርስቲያኖች የመንግሥትን ሕግ አክባሪዎችና እውነተኞች ሲሆኑ ሳለ ፣ በክርስቲያኖች ላይ የሚያሳብቁት አይሁድና ክርስቲያኖችን የሚያሳድዱ አሕዛብ ሕገ ወጦች መሆናቸውን ያስረዱ ነበር ። እነዚህም ሊቃውንት ይህንን እውነተኛ ነገር መናገራቸውና በጽሑፍ ማስፈራቸው እንደ ወንጀል ተቈጥሮባቸው በሰማዕትነት ዐረፉ ።

## የስደት ዘመኖች በሁለት ይከፈላሉ

1ኛ/ ከ64–250 ዓ·ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በጠቅላላ አጥፏቸው የሚል ዐዋጅ ስላልታወጀ ፣ በአንድ ሀገር የነበሩ ክርስቲያኖች ሲሠቃዩ ፣ በሌላ ሀገር የነበሩት ደግሞ በሰላም ይኖሩ ነበር ።

2ኛ/ ከ250–313 ዓ·ም ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ በማቋረጡ ምክንያት ዕረፍት ቢያገኙም ፣ ክርስቲያኖች እንዲጠፉ ጠቅላላ ዐዋጅ ስለታወጀ ያለርኅራኄ በጭካኔ ተፈጁ ።

### በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ መቶ ዘመናትና በአራተኛው መጀመሪያ በክርስቲያኖች ላይ ከታወጁት አሰቃቂ ሥቃዮች ከዚህ በታች ዋና ዋናዎችን እንመልከት

1ኛ/ <u>በኔሮን ትእዛዝ የተነሣው ስደት (54–68 ዓ·ም)</u> ።

በ64 ዓ·ም የሮም ከተማ ሁለት ሦስተኛው በታላቅ የእሳት ቃጠሎ አመድ ሆነ ። ብዙ ሰዎችም ተቃጠሉ ። ይህንንም ቃጠሎ ያስነሣው ራሱ ኔሮን ነበር ። ምክንያቱም አሮጌው ከተማ ጠፍቶ አዲስ ከተማና ሰፊ ቤተ መንግሥት እንዲሠራለትና ቃጠሎውንም እያየ ለመደሰት ስለፈለገ ነው። በሀብቱ መቃጠልና በዘመዶቹ ማለቅ ከተቈጣው ሕዝብ ለማምለጥ ኔሮን በሐሰት ይህን ቃጠሎ ያስነሡት ክርስቲያኖች ናቸው ስላለ ፣ ከ64–68 ዓ·ም ድረስ በሮም ከተማ ውስጥ በሚገኙት ክርስቲያኖች ላይ ከፍ ያለና አሰቃቂ ሥቃይ ተፈጸመባቸው ። ጴጥሮስና ጳውሎስም እዚያው በሰማዕት



www.ethiopianorthodox.org

ነት ዐረፉ ። ግማሾችን በከብት ቆዳ እየጠቀለሉ ለውሾች ጣሉአቸው ። ሌሎችን ደግሞ በየእንጨቱ ላይ እየሰቀሉ አቃጠሉአቸው ። የቀሩትንም በሰም እየነከሩ በጨለማ ጊዜ እንዲያበሩላቸው በአትክልት ቦታዎች አቃጠሉአቸው ። በመጋዝም ሰነጠቁአቸው ። በዚህ አኳኋን በሮም ከተማ የነበሩት ክርስቲያኖች በሰማዕትነት ዐረፉ ። ከላይ የተጠቀሰው ሥቃይ የተፈጸመበት ቦታ የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን የተሠራበት ቫቲካን ይተባለው ስፍራ ነው ።

2ኛ/ <u>በዶሚቲያኖስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት(81–96 ዓ.ም) ።</u>

ዶሚቲያኖስ በ81 ዓ.ም በሮም ነግሦ ዐሥራ አምስት ዓመት ገዛ ። እሱም እንደ ኔሮን ጨካኝ ስለነበር በ96 ዓ.ም ክርስቲያኖችን ለማሳደድ አምላክ የሌላቸው (አቴይስቶች) ናቸው ፤ የመንግሥትም ጠላቶች ናቸው ብሎ በማስወራት ልክ በኔሮን ጊዜ የተፈጸመው ዓይነት ሥቃይ ሮም በነበሩት ክርስቲያኖች ላይ ብቻ ሳይሆን ከሮም ከተማ ውጭም በነበሩ አንዳንድ አውራጃዎች ውስጥ በሚኖሩት ክርስቲያኖችም ጭምር እንዲፈጸምባቸው አዘዘ (ዐወጀ) ። በዚያን ጊዜ ብዙ ክርስቲያኖች አለቁ ። በሰማዕትነት ካለቁትም መካከል የጳውሎስ ደቀ መዛሙርት ጢሞቴዎስና አናሲሞስ ይገኙባቸዋል ። ወንጌላዊው ዮሐንስም ወደ ፍጥሞ ደሴት ተወስዶ በእስር ቤት (በግዞት) እንዲኖር የተደረገው በዚሁ ወቅት ነው ።

3ኛ/ <u>በትራይአኖስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (98–117 ዓ.ም) ።</u>

ትራይአኖስ በሮም ግዛት ሥር በነበሩ አውራጃዎች ለሚገኙ እንደራሴዎቹ ሁሉ ክርስቲያኖችን እንዲያሠቃዩ የሚያዝዝ የተለያዩ የማሠቃየት ዘዴዎችን የያዙ ደብዳቤዎችን ላከ ። እንደነዚህ ያሉ ደብዳቤዎች ከደረሱአቸው አንዱ የትራይአኖስ የቅርብ ወዳጅ ፕሊኒአስ የተባለው ነበር ። በዚያን ጊዜ ለጣዖት አንሰዋም ፤ ጣዖትም አናመልክም ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ በሞት ተቀጡ ። ሰማዕትነት ከተቀበሉትም መካከል ከያዕቆብ ቀጥሎ የኢየሩሳሌም ጳጳስ የነበረው ስምዖን በስቅላት ፤ የአንጾኪያው ጳጳስ አግናጥዮስ ሮም ተወስዶ ለአንበሶች በመጣል በሰማዕትነት ዐርፈዋል ።

4ኛ/ <u>በማርቆስ አውሬሊያኖስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (161–180 ዓ.ም) ።</u>

ማርቆስ አውሬሊያኖስ ቸር ሰው ቢሆንም ቅሉ ፣ በክርስቲያኖች ላይ ከባድ ስደት እንዲፈጸምባቸው አዘዘ ።



www.ethiopianorthodox.org

ሜሌቶንና አቲናጐራስ የተባሉት አፖሎጂስቶች (የክርስትና ጠበቆች ፣ ተሟጋቾች) ለመንግሥት ታማኝና ታዛዥ በሆኑ ክርስቲያኖች ላይ ለምን ጣዖት አላመለካችሁም በማለት በግፍ የታዘዘው የስደት ዐዋጅ በተግባር ላይ እንዳይውል በ170 ዓ·ም በመላ ክርስቲያኖች ስም ያቀረቡትን አቤቱታ ንጉሡ ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት አልተቀበለውም ። ክርስቲያኖች እምነታቸውን እንዲክዱ ቢጠየቁ እምቢ ስላሉ ፣ በዚያን ወቅት (ሰሞን) በግዛቱ የተከሰተው ረሀብ ፣ ቸነፈር ወዘተ· በክርስቲያኖች አምላክ ቢስነት ጣዖቶቻችን ተቈጥተው ያወረዱብን መከራዎች ናቸው በሚል ሰበብ ሰውነታቸው ተበጣጥሶ እስኪወድቅ ድረስ በግርፋትና በተለያዩ ቅጣቶች እየተቀጡ አለቁ ። በዚያን ጊዜ በግፍ ካለቁት ሰማዕታት መካከል ፓራስኬቪ ትገኛለች ። እሷም ስለ ክርስትና እምነቷ ልዩ ልዩ ሥቃይ ከተቀበለች በኋላ አንገቷን በሰይፍ በመቈረጥ በሰማዕትነት ዐረፈች ። እንዲሁም በደቡብ ፈረንሳይ የሊዮን ጳጳስ አቡነ ፎቲኑስ በሰማዕትነት ያረፈው በዚሁ ወቅት ነው ።

5ኛ/ <u>በሴፕቲሚዮስ ሴቪሩስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (193–211 ዓ·ም)</u>።

6ኛ/ <u>በዳክዮስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (249–251 ዓ·ም)</u> ።

7ኛ/ <u>በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (284–305 ዓ·ም)</u> ።

<u>ማሳሰቢያ</u> ከ5–7 ተራ ቍጥር ስማቸው የተጠቀሰው ሮማውያን ነገሥታት በክርስቲያኖች ላይ ያወጁት ስደት ታሪክ በክፍል ሁለት ውስጥ ስለተጻፈ ከዚያ ተመልከት ።

## ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መናፍቃንን በመቃወም ያደረገችው የመንፈስ ተጋድሎ

ቤተ ክርስቲያን እላይ ከተጠቀሱት ከሮማውያን ነገሥታት የደረሱባትን ሥቃዮች በመቀበልና እንዳትጠፋ በመጋደል ላይ ሳለች ፣ ከውስጧ ደግሞ አደገኞች የሆኑ ጠላቶች ተነሡባት ። እነሱም ከሐዋርያት ጊዜ ጀምረው የነበሩት መናፍቃን ናቸው ። መናፍቃን ማለት ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን ቀጥተኛ እምነት ተቀብለው በማመንና በማስተማር ፈንታ ተቃዋሚ የሆኑ የክሕደት ትምህርቶችን የሚያስተምሩ ናቸው ።

ምንም እንኳ በየጊዜው የተነሡት ልዩ ልዩ መናፍቃን ቍጥር ብዙ ቢሆንም ከዚህ በታች ጥቂቶችን እንመልከት ።



www.ethiopianorthodox.org

1ኛ የመጀመሪያዎች መናፍቃን ቢጽ ሐሳውያን (ዩዛይዞንዶ͟ስ) ይባላሉ ። እነሱም ከአይሁድ ወገን ክርስትናን በመቀበል ተጠምቀው ፡ ተመልሰው ወደ አይሁድ ሃይማኖት ያዘነበሉት ናቸው ። ከአሕዛብ ወገን ክርስትናን የተቀበሉትን አስቀድማችሁ የአይሁድን ሃይማኖትና የረበና ትን ልማድ ያዙ እያሉ ያስገድዷቸው ነበር ። ጳውሎስንም በማስተማር ሥራው በጣም አውከውት ነበር ። ነገር ግን በ50 ዓ·ም ኢየሩሳሌም ውስጥ በተደረገችው በሐዋርያት ጉባኤ ተፈረደባቸው ።

2ኛ/ ግኖስቲክ የተባሉት የተለያዩ የኑፋቄ ትምህርቶችን የሚያስተ ምሩ እንጃዎች ያሏቸው ከሐዲዎች ናቸው ። እነሱም ጥልቅ የሆነ ምሥጢራዊ ዕውቀት ያለን የክርስትና ፈላስፎች ነን በማለት ደግና ክፉ የሆኑ ሁለት ትልልቅ አማልክት አሉ ። ደግ ነገር ሁሉ ከደጉ አምላክ ሲመጣ ፡ ክፉው ነገር ደግሞ ከክፉው አምላክ ይመጣል ። ከነዚህም ከትልልቆቹ አማልክት ሌሎች ትንንሾች ደጎችና ክፉዎች አማልክት ተገኙ ። እነሱም ዘመናት ተብለው ይጠራሉ ። ከደጋጉ አንዱ ኢየሱስ ነው አሉ ። ዓለምን የፈጠረ ከክፉዎች አማልክት አንዱ ነው አሉ ። እንዲሁም ጌታ በምትሀት እንጂ በእርግጥ ሥጋን መዋሐዱን ካዱ ። በሚሰቀልበትም ጊዜ በምትሀት ተለውጦ የስምዖን ቀሬናዊውን ቅርፅ ስለወሰደ ፡ ባለማወቅ ጌታችን ኢየሱስ መስሏቸው አይሁድ የሰቀሉት የጌታን መስቀል ተሸክሞ የነበረውን ስምዖን የተባለውን ቀሬናዊውን ሰው ነው አሉ ። እንዲሁም ግማሾቹ ደግሞ ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ሰውነቱን በመስቀል ላይ ትቶ ወደ ሌላ አምላክነት ተለወጠ እያሉና እነዚህን የመሳሰሉ የክሕደት ትምህርቶችን አስተማሩ ። በዚህ አኳኋን በብሉይ ኪዳን ትምህርት መሠረት የዓለምን ፈጣሪ እግዚአብሔርን በመካዳቸው ፡ የወልድንም ሥጋን መዋሐድ ፡ መከራ መቀበሉን ፡ መሞትና መነሣት በመካዳቸው ፡ ከሰው ልጆች መካከልም ድኅነት የሚያገኙ ፍጹም የሆነ መንፈሳዊ ዕውቀት ያላቸው ጥቂቶች ብቻ ናቸው በማለታቸው ቤተ ክርስቲያን ለምታደርገው መንፈሳዊ ተልእኮ አደገኞች ነበሩ ። በተጨማሪም ክርስቲያኖችን ለማታለል በሐዋርያት ስም የክሕደት ትምህርት የያዙ ወንጌሎችንና መልእክቶችን እየጻፉ ለሕዝብ ስላደሉ ፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያትን መጻሕፍት ከእነዚህ መጻሕፍት ለመለየት ቅዱሳት መጻሕ ፍት አለቻቸው ።

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሐዋርያትና በአርድእት የተጻፉ በልዩ



www.ethiopianorthodox.org

ልዩ ጊዜና ሀገር ነው ። የተጻፉትም በጠቅላላው ለቤተ ክርስቲያን ነው ። ስለዚህ በሐዋርያት ዘመን እንደዛሬው ተሰብስበው በአንድ ላይ አልተጠ ረዙም ነበር ። ነገር ግን ከላይ እንደጠቀስነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከ2ኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ጀምራ እስከ 5ኛው መቶ ዘመን ድረስ መርምራ ከከሐዲዎች መጻሕፍት ለይታ 27ቱን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብቻ ተቀበለች ። በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት በመውደማቸው ቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍት ችግር ደርሶባት ስለነበር በዚያን ጊዜ በትልቁ ቈስጠንጢኖስ ትእዛዝ አውሳብዮስ ዘቂሣርያ ለቊስጥንጥንያ አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉ 50 መጽሐፍ ቅዱስ አስጽፎ አዘጋጀ ።እንዲሁም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የሆኑ እንደ ጸሎተ ሃይማኖትና እንደ ምሥጢረ ሥላሴ ያሉ ትምህርቶችን አሰናድታ ለክርስቲያኖች ሰጠች ። የሰማርያው ጠንቋዩ ሲሞን ፣ ሳቶርኔሉስ ፣ ማርሲዮን ፣ ቫሲሊዲስ ፣ ቫሌንቲኑስ ወዘተ ቊጥራቸው ከነዚህ ከሐዲ ዎች ነው ።

3ኛ/ ሌሎች ከሐዲዎች ደግሞ <u>አንዲትሪአዲክ</u> ይባላሉ ። እነሱም የክርስትና እምነት መሠረት የሆነውን የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የተቃወሙ ናቸው ።

ከነሱም <u>ጳውሎስ ሳምሳጢስ</u> የተባለው የአንጾኪያው ኤጲስ ቆጶስ (260–272 ዓ·ም) "አምላክ አብ ብቻ ነው ። ወልድ ግን በእግዚአብሔር ጥበብ የተሞላ ነው እንጂ አምላክ አይደለም" ብሎ የክሕደት ትምህርት ስለአስተማረ ቤተ ክርስቲያን አውግዛ ለየችው ።

በ3ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ የተነሣው <u>ሰባልዮስ</u> የተባለው መናፍቅ ደግሞ ሥላሴ አንድ ገጽ አንድ አካል ናቸው በማለት "አንድ የሆነው እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን አብ ፣ በሐዲስ ኪዳን ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ በመሆን በሦስት ዓይነት መንገዶች ተገለጸ " ብሎ የክሕደት ትምህርት አስተማረ ። የእስክንድርያው ዲዮናስዩስ ሰባልዮስን በመቃወም የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት አስፋፍቶ ጻፈ ።

## የጥንት ክርስቲያኖች ሥርዓተ እምነት አፈጻጸም

1ኛ/ <u>የጸሎት ቦታዎች</u> ።

ሐዋርያት ለስብከት ወደመላው ዓለም ከመበተናቸው በፊት በጊ ዜው በነበሩ በምዙራብ አሪቱና ጽርሐ ጽዮን በተባለው በማርቆስ እናት



www.ethiopianorthodox.org

በማርያም ቤት እየተሰበሰቡ ይጸልዩ ነበር ። ኋላ ግን የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን በፊልጵስዩስ አገር ስለተሠራች ፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የጸሎት ቤት መለየት ፣ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ተጀመረ ።

ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ምእመናን ባልበዙበት ቦታ ስደትና መከራ በበዛበት ዘመን በየዋሻው ፣ በየቦታው ሥርዓተ እምነታቸውን ይፈጽሙ ነበር ። በ2ኛው መቶ ዘመን ላይም ቤተ ክርስቲያን መሥራትን እያስፋፉ ሄዱ ።

ከዚህም በኋላ ከሠዓሊዎች ፣ ከቅርፅ ዐዋቂዎች ፣ ከወርቅ ሠራተኞች ወገን ምእመናን እየበዙ ስለሄዱ የቤተ ክርስቲያንን ምሥጢራት የሚገልጹ ልዩ ልዩ ሥዕሎች ተሣሉ ። የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ፃሕል፣ ጽዋዕ ፣ ጽንሐሕ ፣ መስቀል ፣ እነሱንም የመሰሉት ሁሉ ተሠሩ ።

2ኛ/ ክርስቲያኖች ይፈጽሟቸው የነበሩ ሥርዓታት ።

ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ካህናት በሚፈጽሟቸው በሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን (ንስሓ ፣ ጥምቀት ፣ ሜሮን ፣ ቍርባን ፣ ክህነት ፣ ተክሊልና ቀንዲል) ለክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ጸጋ ይሰጣቸው ነበር ። ክርስቲያኖች ካመኑ ከተጠመቁ በኋላ በየቀኑ በተለይም እሑድ እየተሰበሰቡ መጀመሪያ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንብበው ካህኑ ስብከት ካደረገ በኋላ ንኡሰ ክርስቲያን (ካቴኩሜኒ) የተባሉት ይወጡ ነበር ። ከውስጥ ያሉት ከጸለዩና ከዘመሩ በኋላ ጥዋት ሥጋ ወደሙን ይቀበሉ ነበር ። እንዲሁም ዘወትር ፍቅርን በተመላ መንፈስ ድኻ ሀብታም ሳይባባሉ በአንድ ላይ ይመገቡ ነበር ።

ማስታወሻ ፡ ሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን የተባሉትን ፣ ሌሎች ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ይሏቸዋል ።

3ኛ የበዓላት ቀኖች ።

ከጌታ ትንሣኤ በኋላ በሐዋርያት ዘመን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን የተነሣባት ዕለተ እሑድ ሰንበተ ክርስቲያን ተብላ ትከበር ጀመር (ራእ 1፡10 ፣ የሐዋ·20፡7 ፣ 1 ቆሮ·16፡2) ። አይሁድ ከፈርዖን እጅ ነጻ ሆነው ከግብጽ የወጡበት ፋሲካ የጌታን ሞትና ትንሣኤ በማሰብ ወደ ክርስቲያን በዓልነት ተለወጠ (1ቆሮ·5፡7) ። እንዲሁም አይሁድ ለካህናት ዐሥራት ያወጡበት የነበረው የጰንጠቆስጤ በዓል ለሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ምክንያት በማድረግ ወደ ክርስቲያን በዓልነት ተለ



www.ethiopianorthodox.org

ወጠ። ረቡዕ አይሁድ ጌታን ለመያዝ የተማከሩበት ፥ ዐርብ ጌታን የሰቀሉበት ቀኖች ስለሆኑ ፡ የጾም ቀኖች አደረጉአቸው ። የሰማዕታትም የበዓላት ቀኖች በየጊዜው ተወስነው ይከበሩ ጀመር ።

ፋኛ/ የክርስቲያኖች ጠባይና ልማድ ።

በመጀመሪያዎቹ በሦስቱ መቶ ዘመናት የነበሩት ክርስቲያኖች ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያልታየ እጅግ መልካም ጠባይ ነበራቸው ። አይሁድና አሕዛብ ራስን በመውደድና በትዕቢት ተመልተው በነበሩበት ዘመን ክርስቲያኖች ራስ መውደድን አምዘግዝገው ጥለው ከልብ እርስ በርሳቸው ይፋቀሩ ነበር ። ፍቅራቸውንም ድኾችን በመርዳት ፥ የተማረኩትን በገንዘባቸው ነጻ በማውጣት ፥ በሽተኞችን በማስታመም ፥ እንግዶችን በመቀበልና እነዚህን በመሳሰሉ ደጋግ ሥራዎች በመግለጻቸው አሕዛብ “ክርስቲያኖች እንዴት እንደሚዋደዱ ተመልከቱ” ሲባባሉ ይሰሙ ነበር። በዚያን ጊዜ ክርስቲያኖች አሽከሮቻቸውን እንደ ወንድሞቻቸው ይመለከቱአቸው ነበር (ኤፌ· 4፡22–32 ፤ 6፡5–9፤ ቈላ·4፡1) ።

የክርስቶስን ፈለግ በመከተል ብዙዎቹ ድንግልናን ፥ ተባሕትዎን ያዙ ። ኋላ ግን በድንግልና ላይ ለአክሊለ ሦክ መታሰቢያ ምልክት ቆብ ያደርጉ ጀመር ። ከቀኑም በ7ቱ ጊዜያት ይጸልዩ ነበር (መዝ·119፡164) ። ሥራቸውንም ሲጀምሩና ሲጨርሱ ፊታቸውን በትዕምርተ መስቀል ያማትቡ ነበር ። ይህ ሁሉ ሲሆን ከስንዴ መካከል አንዳንድ እንክርዳድ እንደማይጠፋ ሁሉ እንዲሁም በዚያን ዘመን እንደ አናንያና ሰጲራ ያሉ ክፋዎች አልጠፉም ነበር (የሐዋ. 5፡1–11 ፤ 6፡1) ። ነገር ግን እንደነዚህ ያሉት ሁሉ የሚገባ ቅጣታቸውን ተቀብለዋል ። በክሕደት ምክንያት የተሳሳቱትም ንስሐ ገብተን አንመለስም ሲሉ ከቤተ ክርስቲያን አባልነት አውግዘው ይለዩአቸው ነበር ።

## በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ መቶ ዘመናት የቤተ ክርስቲያን አመራር

ጌታ ለሐዋርያት የዓለምን ሕዝብ እንዲያስተምሩ በሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት (ማቴ·28፡ 19–20) በየሀገሩ እየዞሩ በማስተማር ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ከመሠረቱ በኋላ ፥ ወንጌል ያልተሰበከለትን ሌላውን ክፍለ ሀገር ለማስተማር ሲሄዱ የመሠረቷቸውን አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉና የሚያስተዳድሩ ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾሙ ነበር ። የተሾሙትም ለክርስቲያኖች ኃላፊዎች ፥ ጠባቂዎችና የሚፈጸሙ



www.ethiopianorthodox.org

ትንም አገልግሎቶች የመፈጸም የበላይነት ሥልጣን ነበራቸው ። ኤጲስ ቆጶሳቱም የአገልግሎቱ ሥራ ስለበዛባቸው ቀሳውስትን ሾሙ ። እንዲሁም ለኤጲስ ቆጶሳቱና ለቀሳውስቱ ረዳት እንዲሆኑ ዲያቆናት ተሾሙ ። በዚህ አኳኋን ሦስቱ ማዕርገ ክህነት ለካህናት ተሰጡ ። ከጌታ ለሐዋርያት፣ ከሐዋርያትም ለኤጲስ ቆጶሳት ሥልጣነ ክህነትን የመስጠት ሀብት (ሥልጣን) ተሰጣቸው (ዮሐ·20፡22 23 ፣ የሐዋ· 6፡3–9 ፣ 1ጢሞ·4፡14 ፤ 2ጢሞ· 1፡6፡ ቲቶ 1፡5) ።

<u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባዘዛቸው መሠረት ሐዋርያት ካስተማሩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 5ኛው መቶ ዘመን ድረስ ክርስትና የተሰበከችባቸው ሀገሮች የሚከተሉት ናቸው ።</u>

ፍልስጥኤም ፣ ትንሿ እስያ ፣ አንጾኪያ ፣ ሶርያ ፣ ቆጵሮስ ፣ ቀርጤስ ፣ አቴና ፡ የግሪክ አውራጃዎች ቆሮንቶስ ፡ ኤፌሶን ፣ ተሰሎንቄ ፣ ፊልጵስዩስ፣ ሮም ፡ የዓረብ ሀገር ፡ እስጳኝ ፡ ግብጽ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ሰሜን አፍሪካ (ካርቴጅ) ፣ አርመን ፡ ፋርስ ፡ ሕንድ ፡ ፈረንሳይ ፣ ብሪታንያ ፣ ሩማንያና ሌሎችም በሜዲትራንያን ባሕር ዙሪያ የሚገኙ ሀገሮች ናቸው።

## ለክርስትና ትምህርት መስፋፋት የረዱ የሚከተሉት ናቸው

ሀ) ብሉይ ኪዳን እስክንድርያ ውስጥ ከክርስቶስ ልደት በፊት በዳግማዊ በጥሊሞስ (ፕቶሎሚ) ትእዛዝ (285—246 ዓመተ ዓለም) ከእብራይስጥ ሕዝቡ ወደሚሰማው ወደ ግሪክ ቋንቋ በሰባ ሊቃናት (ረበናት) ስለተተረጐመ ከአሕዛብ ብዙዎቹ በእግዚአብሔር አመኑ ። ቀጥሎም ነቢያት አስቀድመው ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ ትንቢት የተናገሩለት ኢየሱስ ሲወለድ በእሱ በማመን ክርስትናን ተቀበሉ ።

ለ) የሮም መንግሥት ዓለምን መግዛቱ ለክርስትና ትምህርት መስፋፋት ጠቀመ ። ምክንያቱም ሰፊው የሮም ግዛት እንደዛሬው በየመንግሥታቱ ስላልተከፋፈለና በየቦታው ቁም ፣ የይለፍ ወረቀት አሳይ የሚል ጠረፍ ጠባቂ ስላልነበረ ፣ አምረው የተሠሩ መንገዶችና የባሕር ወደቦች ስለነበሩና እንዲሁም በወታደሮች ትጋት ቀማኞች ስለጠፉ ሰባኪዎች ክርስትናን ለማስተማር ወደየፈለጉበት ሀገር እንደልባቸው ይሄዱ ነበር ።

ሐ) ታላቁ እስክንድር ከሮም መንግሥት መስፋፋት ቀደም ብሎ ብዙ ሀገሮችን ገዝቶ ስለ ነበር ፣ ዐሱ ጊዜና ጌታም በተወለደበት ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

የግሪክ ቋንቋ በዓለም ተስፋፍቶ ስለነበር ፣ ወንጌልን ለመስበኪያ ጠቀመ። ሐዲስ ኪዳንም የተጻፈ በጽርዕ ፣ በሮማይስጥ ፣ በዕብራይስጥ ቋንቋ ነው ።

መ) ከፍልስጥኤም ውጭ ይኖሩ የነበሩት አይሁድ የፋሲካንና የጰንጠቆስጤን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ሳለ ፣ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ በተሰጠበት ቀን በጴጥሮስ ስብከት ክርስትናን የተቀበሉት ወደየመጡበት ሀገር ተመልሰው አስተማሩ ።

ሠ) ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ 1፡22—32 እንደሚገልጸው ሁሉ በዚያን ጊዜ የነበረው ሕዝብ ግብረ ገብነት በጣም ተበላሽቶ ነበር ። አገልጋዮችና ሴቶች ለሰው ልጅ የሚገባውን መብት ተገፈው በሥቃይ ላይ ነበሩ ። በዚያ ሕዝቡ ለኃጢአት በተገዛበት ዘመን ጳውሎስ በገላትያ 3፡28 በሚያስተምረው መሠረት የክርስቶስ ተከታዮች ወንጌልን ስለሰበኩ ሕዝቡ የክርስትናን እምነት ተቀበለ ።

ረ) የክርስቲያኖች ደኅ ሀብታም ፣ አሽከር ጌታ ሳይባባሉ እርስ በርስ መፋቀርና ሐዋርያት በየቦታው ይሠሩአቸው የነበሩት ታምራት የሕዝቡን አእምሮ ስለ ማረኩት ሕዝቡ ክርስትናን ተቀበለ ።

## የክርስትና ድል መንሣትና መስፋፋት

### ትልቁ ቈስጠንጢኖስ

ክርስትና ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ በሦስቱ መቶ ዘመናት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ ስደቶች ቢደርሱባት ሕዝቦችን በማጽናናትና በማስተማር ተግታ ሠራች ። ይህንም የተቀደሰ እርምጃ በምታደርግበት ጊዜ የብዙ ክርስቲያኖች ንጹሕ ደም በግፍ ፈሰሰ።

የክርስቲያኖችን ጸሎት በመስማትና በግፍ የፈሰሰውን ደማቸውን በመመልከት እግዚአብሔር በትልቁ ቈስጠንጢኖስ አድሮ በ313 ዓ.ም ለክርስቲያኖች ሙሉ ነጻነትን ሰጣቸው ።

ቈስጠንጢኖስ ሰርቢያ ኒሳ (ዩጎዝላቪያ) በምትባል ቦታ ከቁንስጣና ከእሌኒ በ272 ዓ.ም ተወለደ ። በጦር ሜዳዎች ብዙ የጀግንነት ሥራዎችን ስለሠራ በሠራዊቱ ዘንድ ይወደድ ነበር ። ከአባቱ ሞት በኋላ ሕዝቡና የጦር ሠራዊቱ ንጉሠ ነገሥት አድርጎ ሾመው ። እሱም በጦር ሠራዊቱና በውጭ የነበሩትን ክርስቲያኖች በመልካም ዐይን ይመለከታቸው ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

አንድ ጊዜ ቈስጠንጢኖስ ከጠላቱ ከመክስምያኖስ ሊዋጋ ሲል እንዴት አድርጎ ጠላቱን እንደሚያሸንፍ በማሰላሰል በሐሳብ ባሕር ሲዋኝ በ312 ዓ·ም ሌሊት በራእይ "በዚህ የመስቀል ምልክት ጠላትህን ታሸንፋለህ" የሚል ጽሑፍ ያለበት የሚያበራ መስቀል ከሰማይ አየ ። እሱም ይህ በራእይ ያየው መስቀል እግዚአብሔር በቸርነቱ የሰጠው መሆኑን ተገንዝቦ በማመን ፥ በሰንደቅ ዓላማው ላይ የወርቅ መስቀል አስቀርፆ ፥ ከሠራዊቱ ፊት አስይዞ ዘመተ ። ወዲያው ሙልቢያ በተባለው በቲቤር ወንዝ ድልድይ ላይ ጠላቱን ድል ነሥቶ በጠቅላላው የሮም መንግሥት ግዛቶች ሁሉ ገዥ ሆነ ።

ክርስትናን ስለ ወደደ በ313 ዓ·ም ሚላን በተባለች ከተማ ውስጥ ለክርስትና የነጻነት ዐዋጅ ዐወጀ ። አብያተ ክርስቲያናትንም አሳነፀ ። በንዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት የተወረሰው የክርስቲያኖች ንብረትና ሀብት ፥ የአብያተ ክርስቲያናትም ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ እንዲመለሱ አዘዘ ።

ይህም ለክርስትና ከፍ ያለ ውለታ የተደረገበት ታላቅ ጊዜ ነበር ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በክርስቲያኖች ላይ ይፈጸም የነበረው ስደት ቆመ ። ክርስትና የመንግሥቱ ሃይማኖት ስለሆነች በሚገዛቸው ሀገሮች ሁሉ እሑድ የዕረፍት ቀን እንድትሆን ወሰነ ። ይህም የዕረፍት ቀን ስለተገኘ ማንኛውም ሰው ባሮችም ጭምር ሳይቀሩ የነፍሳቸውን ድኅነት ለማግኘት ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ ቃለ እግዚአብሔርን ለመስማት መልካም ዕድል አጋጠማቸው ። ቈስጠንጢኖስና እናቱ እሌኒ ንግሥት ክርስትናን ተቀበሉ ። እሌኒ ከልጅዋ በፊት ተጠምቃ ብዙ የቅድስና ሥራዎችን ሠራች ። ይኸውም በ327 ዓ·ም ጌታ የተሰቀለበትን መስቀል አስቈፍራ አገኘች ። የመቃብሩንም ቦታ አግኝታ በላዩ ላይ በጌታ ትንሣኤ የሚጠራ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን አሠራች ።

ቀደም ሲል የሮማ ዜጋ ያልሆነ ወንጀለኛ በስቅላት መቅጫ የነበረው መስቀል ጌታ ተሰቅሎ በደሙ ዓለምን ስላዳነበትና ቈስጠንጢኖ ስም ጠላቱን ድል ስለነሣበት በክርስቲያኖች ዘንድ የተከበረና የሠራዊቱ ምልክት ሆነ ።

ከናቱ ሞት በኋላ በጸና ስለታመመ በኒቆሚድያ ኤጲስ ቆጶስ በአውሳብዮስ እጅ ኒቆሚድያ በሚባል ቦታ ተጠምቆ በ337 ዓ·ም



www.ethiopianorthodox.org

በተወለደ በ65 ዓመቱ ዐረፈ ።

አንዳንድ ሊቃውንት ቈስጠንጢኖስ ጥምቀትን እስከ ዕለተ ሞቱ ያዘገየው በዚያን ጊዜ ጥምቀት በሕይወት ዘመን የተሠራውን ኃጢአት ሁሉ ያስተሰርያል ተብሎ ይታመን ስለነበር የሠራው ኃጢአት ሁሉ በአንድነት እንዲሰረይለት በመሻት ነበር ይላሉ ። ሌሎች ደግሞ በግዛቱ ሥር ይኖሩ የነበሩት አረማውያን በመንግሥቱ ላይ እንዳይነሡበት በመስጋት የመጠመቂያውን ጊዜ አዘገየው ይላሉ ።

## በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ዘመን መናፍቃንን ለመቃወም የተደረጉ ታላላቅ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤዎች (ሲኖዶሶች) የሚከተሉት ናቸው

### መጀመሪያው የኒቅያ ጉባኤ ።

በ3ኛው መቶ ዘመን አጋማሽ ላይ ሊብያ ውስጥ የተወለደው አርዮስ አንጾኪያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በሉሲያን መምህርነት መንፈሳዊ ትምህርቱን ከተማረና ካጠናቀቀ በኋላ ፥ የቅስና ማዕርግ ተቀብሎ እስክንድርያ ውስጥ ሲያገለግል ቈይቶ በ318 ዓ·ም "ወልድ ፍጡር ነው እንጂ አምላክ አይደለም" እያለ የክሕደት ትምህርት ማስተማር ጀምረ ። የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ እለእስክንድሮስ አርዮስን ይህን የተሳሳተ የክሕደት ትምህርት ማስተማሩን እንዲተው ቢመክረው እምቢ ስላለ አወገዘው ። ቈስጠንጢኖስም ነገሩን ስለሰማ እለእስክንድሮስና አርዮስ ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ እንዲጨርሱት በማለት ወደ እስክንድርያ የሃይማኖት ጉዳይ አማካሪው የነበረውን አስዮስ የተባለውን መልእክተኛ ከደብዳቤ ጋር ልኮ ነበር ። ነገር ግን አርዮስ ይህንኑ የክሕደት ትምህርት ማስተማር መቀጠሉንና ጠቡም በቀላሉ የማይበርድ መሆኑን መልእክተኛው ለቈስጠንጢኖስ ስለነገረው ፥ ቈስጠንጢኖስ በ325 ዓ·ም በትንሿ እስያ ውስጥ በጥቁር ባሕር ወደብ አካባቢ በምትገኘው ኒቅያ በተባለች ከተማ ውስጥ ጉባኤ እንዲደረግ አዘዘ ። በዚህም ጉባኤ ከአርዮስ ተከታዮች በስተቀር ከየአብያተ ክርስቲያናቱ የተላኩ 318 ሊቃውንት (ጳጳሳትና ቀሳውስት) ተገኙ ። ንጉሡ ቈስጠንጢኖስም በጉባኤው ተገኝቶ ነበር ። በዚህ ጉባኤ ውስጥ እግዚአብሔር ወልድ ቀዳማዊ አምላክ ስለመሆኑ ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን እየጠቀሱ አርዮስን በጥብቅ የተከራከሩ አፈ ጉባኤው



www.ethiopianorthodox.org

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ እለእስክንድሮስና እስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት መንፈሳዊ ትምህርቱን ያጠናቀቀው ረዳቱ ሊቀ ዲያቆን አትናቴዎስ ነበሩ ። በጉባኤው የተቀመጡት 318ቱ ሊቃውንት የሁለቱን ወገን ክርክር በጽሞና ከሰሙ በኋላ የአርዮስ ትምህርት ክሕደት መሆኑን ተገንዝበው ከነተከታዮቹ አወገዙት ። እነሱም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑንና ከአብም ጋር ትክክል መሆኑን የሚገልጽ ጸሎተ ሃይማኖትን በከፊል፣ አምስቱ አዕማደ ምሥጢርንና ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆኑ ሌሎችንም ሥርዓቶች ሠሩ ።

ማሳሰቢያ ። የጀሖባ ምስክሮች (የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኒዎች፣ ጌታ ሺህ ዓመት ወደፊት ይነግሣል ባዮች፣ ሮሳላውያን) በሚባሉና በሌሎችም ልዩ ልዩ ስሞች የሚጠሩት አሁን በዘመናችን የአርዮስን የክሕደት ትምህርትና ከክርስትና እምነት ውጭ የሆኑ ትምህርቶችን ያስተምራሉ ።

ሁለተኛው የቍስጥንጥንያ ጉባኤ ።

የቍስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ መቅዶንዮስ "መንፈስ ቅዱስ መላክ ተኛ ነው እንጂ ከአብና ከወልድ ጋር በመለኮት አንድ አይደለም ። ከአብና ከወልድ በታች ነው" የሚል የክሕደት ትምህርት አስተማረ ።

እንዲሁም በሶርያ የምትገኝ የላኦዲኪያ ኤጲስ ቆጶስ አቡሊናርዮስ "ወልድ በመለኮት ከአብ ጋር አንድ ነው ። ከማርያም ሥጋን በለበሰ ጊዜ ግን ነፍስና ዕውቀት የሌለውን ሥጋ ለበሰ ። ለለበሰውም ሥጋ መለኮት ነፍስና ዕውቀት ሆነው" የሚል የክሕደት ትምህርት አስተማረ ። በቍስጥንጥንያው ንጉሥ በቀዳማዊ ቴዎዶስዮስ ዘመነ መንግሥት 150 ጳጳሳት ተሰብስበው በ381 ዓ.ም በቍስጥንጥንያ ሁለተኛውን ጉባኤ አደረጉ።

በጉባኤው ላይ ከቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎችን እያቀረቡ ሁለቱን መናፍቃን በጥብቅ የተከራከሩአቸው ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚና ዙና ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ነበሩ ። የጉባኤው ተካፋዮችም የሁለቱም ትምህርት ክሕደት መሆኑን ተገንዝበው መቅዶንዮስንና አቡሊናርዮስን አወገዟቸው ። ወዲያውም የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ፡ ከአብና ከወልድ ጋር ትክክል መሆኑን የሚገልጽ ጽሑፍ በኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት በተጻፈው በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ "ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ..." የሚለውን ጨምረው ጻፉ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ሦስተኛው የኤፌሶን ጉባኤ ።

የቍስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ንስጥሮስ "ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት የእግዚአብሔር አብ ልጅ ስለሆነ ከአብ ጋር ትክክል ነው ፡ ከመቤታችን ሰውነትን በነሣ ጊዜ ግን አካሉ ሁለት ነው ። አንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ፣ አንዱ የማርያም ልጅ ነው ። አምላክ ከሰው ለመወለድ ስለማይችል እመቤታችን ማርያም የክርስቶስ እናት ናት እንጂ የአምላክ እናት አይደለችም" የሚል የክሕደት ትምህርት ስላስተማረ በዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ዘመነ መንግሥት በ431 ዓ·ም በኤፌሶን 200 የሚሆኑ ጳጳሳት ተሰብስበው ጉባኤ አደረጉ ። በዚህም ጉባኤ ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ትክክል መሆኑን ፣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗን አረጋግጠው ንስጥሮስን አወገዙት ።

ጉባኤው ከመደረጉ በፊትና በጉባኤውም ላይ ከቅዱሳት መጻሕፍት ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን እያቀረበ ንስጥሮስን በጥብቅ የተከራከረው የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ ነበር ።

<u>ማሳሰቢያ</u> ። የኦርየንታል (የተዋሕዶ) አብያተ ክርስቲያናት የሚቀበሉአቸው ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሦስቱን ጉባኤዎች ነው ። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ግን በሦስቱ ላይ ቀጥለን የምንመለከተውን የኬልቄዶንንና ከስድስተኛው እስከ ስምንተኛው መቶ ዘመን ድረስ የተደረጉ የልዮንን ትምህርት የሚደግፉ ፤ እንዲሁም ለጌታ ፣ ለቅዱሳን ፣ ለጻድቃን ፣ ለሰማዕታትና ለመላእክት ሥዕሎች የአምልኮ ሳይሆን የአክብሮት ስግደት መገባቱን የሚገልጹ ሌሎች ሦስት ጉባኤዎች በመጨመር ባጠቃላይ የሰባት ጉባኤዎችን ውሳኔ ትቀበላለች ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በሰባቱ ላይ ዐሥራ አራት በመጨመር የሃያ አንድ ጉባኤዎችን ውሳኔ ትቀበላለች ።

## አራተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ።

በቍስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ቆሞስ የነበረው አውጣኪ "እግዚአብሔር ወልድ ከመቤታችን ከድንግል ማርያም ሰውነትን በነሣ ጊዜ አምላክነቱ ሰውነቱን ስለዋጠው ረቀቀ" ብሎ የክሕደት ትምህርት ስላስተማረ በመርቅያን ዘመነ መንግሥት 650 ኤጲስ ቆጶሳት በተገኙበት በ451 ዓ·ም· ቍስጥንጥንያ ከተማ አጠገብ በምትገኘው ኬልቄዶን በተባለች ከተማ ውስጥ የተደረገው ጉባኤ አወገዘው።



www.ethiopianorthodox.org

ማሳሰቢያ፡፡ የአውጣኪን የክሕደት ትምህርት የኦርየንታል (የተዋሕዶ) አብያተ ክርስቲያናትም ይቃወሙታል። እላይ ከተጠቀሰውም በስተቀር የሮማው ሊቀ ጳጳሳት ቀዳማዊ ልዮን " ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት" የሚል ጽሑፍ (ጦማር) በኬልቄዶን ጉባኤ ለተሰበሰቡት ኤጲስ ቆጶሳት ስለላከ፥ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ጌታ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለው ትምህርት ስሕተት ነው ብሎ ልዮንን አወገዘው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት በእምነት ተለያዩ። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም በልዮን ትምህርት ተስማማች።

የቅዱስ ዲዮስቆሮስን ትምህርት የሚከተሉ የኢትዮጵያ ፣ የእስክንድርያ፣ የሶርያ፣ የአርመን፣ የሕንድ ተዋሕዶ (ኦርየንታል) አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ መሆኑን፥ መለኮትና ትስብእትም ያለመለየት፥ ያለመቀላቀል፥ ያለመለወጥ ስለተዋሐዱ አንድ አካል፥ አንድ ባሕርይ፥ አንድ ፈቃድ፥ አንድ ግብር መሆኑን ታምናለች።

ማሳሰቢያ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት የቅዱስ ዲዮስቆሮስን ትምህርት የሚከተሉት አምስቱ የኦርየንታል( የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ) አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርኮች፥ ሊቃነ ጳጳሳት፥ ጳጳሳት፥ ኤጲስ ቆጶሳትና ቀሳውስት ከኬልቄዶን ጉባኤ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ ውስጥ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከጥር 7 እስከ 13 ቀን 1957 ዓ·ም ድረስ ታላቅና ታሪካዊ ጉባኤ አድርገው፥ በውስጣቸው ብዙ ንኡሳን ክፍሎችን በያዙ በስድስት አንቀጾች ተነጋግረው ውሳኔ ሰጥተዋል።

ስድስቱ አንቀጾችም የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ/ ዘመናዊው ዓለምና አብያተ ክርስቲያኖቻችን።

2ኛ/ በመንፈሳዊ ትምህርት ተባብሮ መሥራት።

3ኛ/ ተባብሮ ወንጌላዊ ሥራን መሥራት።

4ኛ/ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት።

5ኛ/ በአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል ያለው ነዋሪ ዝምድና የሚጸናበትን ሁኔታ የሚከታተል ድርጅት ማቋቋም።

6ኛ/ ስለ ዓለም ሰላምና ፍትሕ።



www.ethiopianorthodox.org

## በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ዘመን የተነሡት
## የቤተ ክርስቲያን አባቶች

ክርስትና ነጻነቷን ካገኘች በኋላ በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ዘመን የተነሡት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በመንፈሳዊና በፍልስፍና ትምህርት ከፍ ያለ ዕውቀት ነበራቸው። የወንጌል ትምህርት በዓለም እንዲዳረስ በማስተማርና መጻሕፍትን በመጻፍ ከደከሙት አባቶች ጥቂቶችን ከዚህ በታች እንመልከት።

1ኛ/ <u>ቅዱስ አትናቴዎስ</u፦ በ295 ዓ·ም እስክንድርያ ውስጥ ተወልዶ የትምህርት ጊዜው ሲደርስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያጠና ጀመር። በወጣትነቱም ዘመን ከአባ እንጦንስ ጋር መንኖ በበረሐ ጥቂት ጊዜ ቈይቶ ነበር። ቀደም ብለን በተመለከትነው በኒቅያ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ ከአርዮስ ጋር በመከራከርና የክሕደት ትምህርቱን በማጋለጥ ረድቷል። ከሊቀ ጳጳሱ ከእለእስክንድሮስ ዕረፍት በኋላ በ328 ዓ.ም. የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ።

እሱም በዘመኑ ከነበሩት አርዮሳውያን ጋር እየተከራከረ ምእመናንን በትጋት አስተማረ። የአርዮስ ወገኖችም ለበላይ ባለሥልጣኖች በሐሰት በማሳበቅና በመክሰስ አምስት ጊዜ ያህል እንዲሰደድ አድርገዋል። ባልሠራው ወንጀል በግፍ ይህ ሁሉ ስደትና መከራ ሲደርስበት ምእመናንን ከማስተማር ተግባሩና ከቀጥተኛ እምነቱ አልተናወጸም ነበር።

በደረሱበት ስደቶች ምክንያት ጤናው ስለታወከ እስክንድርያ ውስጥ በ373 ዓ·ም ዐረፈ። በኢትዮጵያ መጀመሪያው ጳጳስ በመሆን የክርስትናን እምነት ላስፋፋው ለአቡነ ፍሬምናጦስ ( ሰላማ፣ ከሣቴ ብርሃን) የጵጵስና ማዕርግ ሰጥቶ የላከው አትናቴዎስ ነው። የአርዮስን የክሕደት ትምህርት የሚቃወሙና ለምእመናን የሚጠቅሙ ብዙ መጻሕፍት ጽፏል።

2ኛ/ <u>ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ</u>፦ ቀጰዶቅያ በምትገኝ ቂሣርያ ውስጥ በ330 ዓ·ም ከሀብታም ቤተሰቦች ተወለደ። ለተወሰነ ጊዜ ጠበቃ ሆኖ ይሠራ ነበር። ባስልዮስን በመጀመሪያ የክርስትናን ትምህርት ያስተማረችው እናቱ ኤሚሊያ ስትሆን፣ ከፍ ያለ ጊዜአዊ ዝና የሚያስገኝለትን ዓለማዊ ሥራ ትቶ በተቀደሰው የክህነት ተግባር ላይ በመሰማራት



www.ethiopianorthodox.org

ክርስትናን ለማስፋፋት እንዲችል በመምራት ያበቃችው እኅቱ ማክሪና ናት። የትምህርት ጓደኛውም ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ነበር።

የሪቶሪክንና (የንግግርንና) የፍልስፍናን ትምህርት ቂሣርያ፥ ቊስጥንጥንያና አቴና ተምሮ ይህንኑ በማስተማር ጥቂት ጊዜ ከሠራ በኋላ ግብጽ የሚገኙትን መነኰሳትና ገዳማት በቅርብ ሆኖ ለመመልከት ሄደ። በግብጽ፡ በፍልስጥኤም ፡ በሶርያ የነበሩትን ገዳማት ጐብኝቶ ጳንጳ በምትባል ቦታ መንኵሶ በበረሐ መንኖ አምስት ዓመት ቈየ። የቂሣርያው ኤጲስ ቆጶስ አውሳብዮስ ስላረፈ በ370 ዓ·ም· ኤጲስ ቆጶስ እንዲሆን ተመርጦ ተሾመ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምእመናንን በማስተማር፡ የአርዮሳውያንን የኑፋቄ ትምህርት በመቃወምና ልዩ ልዩ የክርስትናን ትምህርት የያዙ መጻሕፍትን በመጻፍ ከፍ ያለ አገልግሎት አበርክቷል። እሱም በ379 ዓ·ም ዐረፈ።

3ኛ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፦ ቀጰዶቅያ ውስጥ እንዚናዙ አጠገብ በምትገኝ አሪዞን በምትባለው ቦታ በ328 ዓ·ም ተወለደ።

እናቱ ኖና የክርስትናን ትምህርት በትጋት ስላስተማረችው በጥቂት ጊዜ ውስጥ የክርስትናን እምነት ተቀበለ። መጀመሪያ ቂሣርያ፡እስክንድርያና አቴና ውስጥ፥ ቀጥሎም በብዙ ሀገሮች እየዞረ ከተማረ በኋላ ወደ ሀገሩ ወደ እንዚናዙ ተመልሶ የቅስናን ማዕርግ ተቀብሎ ቤተ ክርስቲያንን ያገለግል ጀመር፥ ቀጥሎም ቅዱስ ባስልዮስ ሳሲማ ለምትባለዋ አውራጃ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾመው። እንዲሁም በ380 ዓ·ም ወደ ቊስጥንጥንያ ሄዶ ፓትርያርክ ሆኖ አስተማረ። እዚያም በሚያስተምርበት ጊዜ የአርዮሳውያንን የክሕደት ትምህርት በመቃወም የወልድን አምላክነት የሚገልጹ ከቅዱሳት መጻሕፍት ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን እየጠቀሰ አንድነትንና ሦስትነትን አስፋፍቶና አብራርቶ ስላስተማረ ከሕዝቡ ነባቤ መለኮት (ቴዎጐሎስ፡ ቴዎሎጐስ) የሚል ስም ተሰጠው።

በ381 ዓ·ም ቊስጥንጥንያ ውስጥ ለተደረገችው ለሁለተኛዪቱ ጉባኤ ሊቀ መንበር ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ነበር።

በየጊዜው በትጋት ከማስተማሩም በስተቀር ለክርስቲያኖች የሚጠቅሙ ብዙ መጻሕፍት ጽፏል። እሱም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከቊስጥንጥንያ ፓትርያርክነት በፈቃዱ ተሰናብቶ ወደ ተወለደበት ቦታ ወደ አሪዞን ተመልሶ ሁል ጊዜ ይመኘው የነበረውን ጸጥ ያለ የብሕትውና ኑሮን



www.ethiopianorthodox.org

መኖርና መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማዘጋጀት ላይ ሳለ ባደረበት ሕመም ምክንያት በ390 ዓ.ም ዐረፈ።

4ኛ/<u>ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ</u>፦ ቅዱስ ቄርሎስ እስክንድርያ ውስጥ በ380 ዓ.ም ተወልዶ ትምህርቱን እዚያው ተምሮ አጠናቀቀ። አባ መቃርስ ወደነበረበት ገዳም ሄዶ የብሕትውና ኑሮ በመኖር እዚያ ይሰጥ የነበረውን ትምህርትም ቀስሟል።

አጐቱ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ እንዳረፈ በ412 ዓ.ም የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ። ቀደም ሲል አትናቴዎስ የአርዮስን የክሕደት ትምህርት በጥብቅ እንደተቃወመ ሁሉ፤ ቄርሎስም የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ንስጥሮስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት አካላት፤ ሁለት ባሕርያት አሉት፤ እመቤታችን ማርያምም የክርስቶስ እናት እንጂ የአምላክ እናት አይደለችም በማለት ያስተማረውን ኑፋቄ በጥብቅ በመቃወም ስለ አንድ ባሕርይ (ስለተዋሕዶ)፤ ስለ እመቤታችን ወላዲተ አምላክነት አብራርቶ አስተምሯል።

ቄርሎስ በ430 ዓ.ም እስክንድርያ ውስጥ ጉባኤ ጠርቶ ከክሕደት ትምህርቱ አልመለሰም ያለውን ንስጥሮስን አወገዘው። ወዲያውም ዐሥራ ሁለት የግዝት ዓረፍተ ነገሮችን (አንቀጾችን፤ አናሴማ) የያዘ ጽሑፍ ለንስጥሮስ ልኮ በዐሥር ቀን ውስጥ ንስሐ ገብቶ የኑፋቄ ትምህርቱን እርግፍ አድርጎ እንዲተው ቢጠይቀው አሻፈረኝ በማለቱ በ431 ዓ.ም ሁለት መቶ የሚሆኑ ጳጳሳት ተሰብስበው በሦስተኛዋ የኤፌሶን ጉባኤ ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ትክክል መሆኑን፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗን አረጋግጠው ንስጥሮስን አወገዙት።

ቅዱስ ቄርሎስ በጻፋቸው መጻሕፍት ስለ ምሥጢረ ተዋሕዶ አብራርቶና አስፋፍቶ ስለገለጸ፤ እነ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በአራተኛዋ የኬልቄዶን ጉባኤ ላይ ስለቀጥተኛዋ የተዋሕዶ እምነታችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር በማገናዘብ ለክርክራቸው መሠረት ያደረጉት የቅዱስ ቄርሎስን የመሠረተ ሃይማኖት ትምህርት ነበር።

እሱም የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን በትጋት ሲያስተዳድር፤ ሲያስተምርና የተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርት የያዙ መጻሕፍት ሲጽፍ



www.ethiopianorthodox.org

ቈይቶ በ444 ዓ.ም ዐረፈ።

5ኛ/ <u>ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ዘእስክንድርያ፦</u> ቅዱስ ዲዮስቆሮስ እስክንድርያ ውስጥ ተወልዶ መንፈሳዊ ትምህርት እየተማረ ከአደገ በኋላ በሊቀ ዲያቆንነት ሲያገለግል ቈየ።

በ444 ዓ.ም መምህሩ ቅዱስ ቄርሎስ ሲያርፍ ወዲያውኑ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ።

በቍስጥንጥንያው ንጉሥ በዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ትእዛዝ በዲዮስቆሮስ ሊቀ መንበርነት በ449 ዓ.ም የአውጣኪን ጉዳይ እንድትመለከት ኤፌሶን ውስጥ በተደረገችው በሁለተኛዪቱ ሲኖዶስ የሁለት ባሕርይ እምነት ደጋፊና የተዋሕዶ እምነት ተቃዋሚ የነበረውን የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ ፍላብያኖስን ወደ ግዞት እንዲላክ በማድረጉ፥ የፍላብያኖስ ተከታዮችና ደጋፊዎች በዲዮስቆሮስና በንጉሡ ላይ ቂም ይዘው ነበር። ሆኖም ዳግማዊ ቴዎዶስዮስ በ450 ዓ.ም ሲያርፍ በምትኩ በነገሠው በመርቅያን ትእዛዝ በ451 ዓ.ም በተደረገችው በአራተኛዪቱ በኬልቄዶን ጉባኤ ተገኝቶ ቀደም ሲል ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ያስተማረውን የተዋሕዶ እምነት አብራርቶ አስረዳ። የካቶሊክና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት " ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት" በማለት የሚያስተምሩትና መናፍቁ አውጣኪ "እግዚአብሔር ወልድ ከመቤታችን ከድንግል ማርያም ሰውነትን በነሣ ጊዜ አምላክነቱ ሰውነቱን ስለዋጠው ረቀቀ" ብሎ ያስተማረው የክሕደት ትምህርት መሆኑን አስረዳ። በዚህ አኳኋን ስለተዋሕዶ እምነት ሲያስረዳና ሲከራከር በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ ከተካፈሉት ጳጳሳት አብዛኞቹ የሁለት ባሕርይን እምነት የሚቀበሉ የልዮንና የፍላብያኖስ ደጋፊዎች ስለነበሩ ተቃወሙት። በክርክሩም ወቅት ከአንዳችም ስምምነት ላይ ለመድረስ ስላልተቻለ ዲዮስቆሮስ " ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት" በማለት የሮሙ ሊቀ ጳጳስ ቀዳማዊ ልዮን በጉባኤው ለተሰበሰቡት ጳጳሳት የላከው ጽሑፍ (የልዮን ቶም፥ ጦማር) ስሕተትና ኑፋቄ ነው ብሎ ልዮንን ከነተከታዮቹ አወገዘው። አንድ የነበሩት የክርስትና እምነት ተከታዮች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተዋሕዶን እምነት የሚቀበሉና የሁለት ባሕርይን እምነት የሚከተሉ ወገኖች ሁለት ላይ ተከፈሉ። ንጉሡ መርቅያን፥ ንግሥቲቱ ብርክልያና በጉባኤው ላይ ከተካፈሉት ጳጳሳት አብዛኞቹ ሁለት ባሕርይ የሚለውን ትምህርት



www.ethiopianorthodox.org

ደጋፊዎች ስለነበሩ በዲዮስቆሮስ ላይ በግፍ ተነሥተው እንዲጋዝ ወሰኑበት። እሱም በትንሿ እስያ በኤጅያን ባሕር በምትገኘው ጋንግራ በተባለች ደሴት ተግዞ በመሠቃየት ላይ ሳለ በ454 ዓ.ም ዐረፈ። ከመርቅያን ሞት በኋላ የነገሠው ባሲሊኩስ የቅዱስ ዲዮስቆሮስ አጽም ወደ እስክንድርያ እንዲላክ በፈቀደው መሠረት ተወስዶ ብዙ ካህናትና ምእመናን በተገኙበት ጸሎት ከተደረገ በኋላ አጽሙ እስክንድርያ በሚገኘው በቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በክብር ዐርፏል።

ባጠቃላይ በዚያን ወቅት የተፈጸመውን ሁኔታ ስንመለከት ቀደም ሲል በኒቅያ ጉባኤ በተወሰነው በመንበረ ፓትርያርኮች የክብር ደረጃ ተራ ውስጥ ያልነበረው የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ድንገት ተነሥቶ ከእስክንድርያው በክብር እበልጣለሁ ማለት ጀመረ ። በ449 ዓ.ም በተደረገችው በሁለተኛዪቱ የኤፌሶን ጉባኤ አውጣኪ ቀርቦ ሲጠየቅ እምነቱ ተዋሕዶ ነው በማለት ቃሉን በቃለ መሐላ አረጋገጠ ፤ በሲኖዶሱ አባላት ውሳኔ መሠረት ቅዱስ ዲዮስቆሮስ አውጣኪን ያንገላታውን የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ ፍላብያኖስን እንዲጋዝ አደረገ ። ሆኖም ተለዋዋጭ ጠባይ የነበረው አውጣኪ ለጉባኤው አባላት በመሐላ የሰጠውን ቃሉን አፍርሶ እንደገና የክሕደት ትምህርቱን መንዛት ቢጀምርም ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በአውጣኪ የኑፋቄ ትምህርት አልተስማማም ነበር። ስለዚህ ከዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባን ያ ሁሉ ውዝግብ የተፈጠረው ስለ ክርስቶስ ባሕርይ በተነሣው የእምነት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ፤ በዚያን ጊዜ ጠንካራ የነበረውን የእስክንድርያን መንበረ ፓትርያርክ ክብርና ደረጃ ዝቅ አድርገው የቍስጥንጥንያውን "የመናገሻ ከተማ መንበር ነው" በሚል ሽፋን ከፍ ለማድረግ ንጉሡ ፤ የሮም ፖፕና የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ዶልተው በኬልቄዶን ጉባኤ በሃያ ስምንተኛው አንቀጽ የወሰኑት ተንኮል ጭምር ነበር ።

በኬልቄዶን ጉባኤ ወቅት ከንጉሡ ጋር በማበር ቅዱስ ዲዮስቆሮስን በመወንጀሉ ተግባር አንድ የነበሩት የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክና የሮሙ ፖፕ ቈየት ብለው እኔ እበልጥ ፤ እኔ እበልጥ በሚል የሥልጣን ሽኩቻ (ሽሚያ) ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ በመፎካከር ተለያይተው ይኖራሉ ።

6ኛ/ <u>ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ</u> :- ሶርያ በምትገኘው አንጾኪያ ውስጥ በ347 ዓ.ም ተወለደ ። በሕፃንነቱ አባቱ ሲኩንዶስ ስለሞተ እናቱ አንሱሳ



www.ethiopianorthodox.org

ሊባንዮስ ወደተባለው አረማዊ መምህር ወስዳ የሕግና የንግግር ዘዴ (ሬቶሪክ) እንዲማር አደረገች ። እሱም ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ ጠበቃ በመሆን ጥቂት ጊዜ ሠራ ።

ቀጥሎም ተጠምቆ አንጾኪያ በነበረችው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ተማረ ። ከዚያም አባ ጳኩሚስ ቴቢያድ ውስጥ በመሠረተው ገዳም በብሕትውና ጥቂት ጊዜ ከቈየ በኋላ የዲቁና ፤ ቀጥሎም የቅስናን ማዕርግ ተቀብሎ ሕዝቡን በማስተማርና (በመስበክና) በሕመም ፤ በልዩ ልዩ ችግር ላይ የወደቁትን ድኆች ከሀብታሞች ገንዘብ እየሰበሰበ ይረዳቸው ጀመር ። ይህም የስብከትና የመመጽወት ሥራው ከአንጾኪያ ውጭ በሆኑ ሀገሮች ሁሉ ተሰማ ።

የቍስጥንጥንያው ንጉሠ ነገሥት አርቃዴዎስ የዮሐንስን ዝና ስለሰማ ያለውዴታው በ397 ዓ·ም ከአንጾኪያ ወደ ቍስጥንጥንያ ሄዶ እንዲያስተምር አደረገ ። የአንጾኪያ ሕዝብም መምህራቸውን ዮሐንስን አንሰድም በማለት ስለአወኩ ሀገረ ገዥው ሌሊት በድብቅ አውጥቶ ወደ ቍስጥንጥንያ ሰደደው ። እዚያም የቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሆኖ እንደ ቀድሞው ወንጌልን ማስተማር ፤ እውነትን መናገር ፤ ቀጥተኛ ፍርድን መፍረድና ለድኆች መመጽወቱን ስለቀጠለ በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅ አባት ሆነ ። ነገር ግን በእግዚአብሔር በማመን ማንንም ሳይፈራ በሰው ላይ ግፍ የሚሠሩትን ሰዎች ሁሉ ንግሥቲቱን አውዶቅስያን ሳይቀር ፤ እንዲሁም ሰነፍ የሆኑ ካህናትንም ገሠጻቸው ። በአጠቃላይ በልዩ ልዩ ወንጀልና ኃጢአት ከተዘፈቁት ምእመናንና ካህናት መካከል ምክሩን ተቀብለው በንስሐ ለመታረም ያልፈለጉት ዐይንህ ለአፈር ብለው በአንድነት እሱን ለማጥፋት ተነሡ ። ጠላቶቹ የነበሩ ጳጳሳት ከቍስጥንጥ ንያ ከተማ ወጣ ብላ በምትገኝ አክ በተባለች ቦታ ጉባኤ አድርገው በዮሐንስ ላይ የሐሰት ክሶችን በመደርደር ከመንበረ ፓትርያርኩ እንዲወ ርድ ወሰኑ ። ይህን ውሳኔና የራሳቸውን እኩይ ፍላጎት መነሻ በማድረግ በ403 ዓ·ም ንጉሡና ንግሥቲቱ የከተማው ሕዝብ አንለቅም በማለት እንዳያውካቸው ሰው ሳይሰማ በድብቅ ከከተማው ወጥቶ ወደ ጥቁር ባሕር አካባቢ እንዲሰደድ አዘዙ ። እሱም በስደት ላይ ሳለ በደረሰበት መንገላታትና ሥቃይ ምክንያት በ407 ዓ·ም ዐረፈ ። ዮሐንስ አፈወርቅ ከማስተማር ሥራው በስተቀር የክርስትናን ትምህርት የያዙ ብዙ



www.ethiopianorthodox.org

መጻሕፍት ጽፏል ። ለዮሐንስ "አፈወርቅ" የተባለው ስም የተሰጠው ከስብከቱ ጣዕም የተነሣ በዚያን ጊዜ ያዳምጥ ከነበረው ሕዝብ ነው ። አጽሙም በዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ትእዛዝ በ438 ዓ·ም ወደ ቍስጥንጥንያ ተወስዶ በሐዋርያት ስም በታነጸው ቤተ ክርስቲያን በክብር ዐርፏል ። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በስተቀር የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ቴዎፍሎስ ፡ የኢየሩሳሌም ጳጳስ ቄርሎስ ፣ የቀጳዶቅያው ጳጳስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ፣ የሶርያው ቅዱስ ኤፍሬም ፣ የሰላሚና ጳጳስ ኤጲፋንዮስና ሌሎችም የክርስትናን ትምህርት በሰፊው በማስተማርና መንፈሳዊ ትምህርት የያዙ መጻሕፍትን በመጻፍ ደክመዋል ።

## በ4ኛው መቶ ዘመን የነበሩት አምስቱ ሊቃነ ጳጳሳት (ፓትርያርኮች)

በመጀመሪያው በኒቅያ ጉባኤ አንቀጽ ስድስት የሊቃነ ጳጳሳቱ ማዕርግ ከዚህ በታች እንደተጻፈው ተወስኖ ነበር ።

1ኛ/ በቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር የሚቀመጠው የሮም ሊቀ ጳጳስ ።

2ኛ/ በቅዱስ ማርቆስ ወንበር የሚቀመጠው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ።

3ኛ/ በቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር የሚቀመጠው የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ ።

4ኛ/ በቅዱስ ዮሐንስ ወንበር የሚቀመጠው የኤፌሶን ሊቀ ጳጳስ ።

በኋላ ግን የኤፌሶን ወንበር ለቈስጠንጢኖስ ሲባል ወደ ቍስጥንጥንያ ተዛወረ ። ከነዚህም በታች ሆነው የሚሠሩ በብዙ ሀገሮች ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ተሹመው ነበር ።

የሮማውና የቍስጥንጥንያው የመናገሻ ከተማዎች ሊቃነ ጳጳሳት ስለነበሩ በመካከላቸው የነበረው የማዕርግ ፉክክር እንዲቆም በማለት በሥልጣን እኩል ሆነው በሽምግልናና በአክብሮት የሮሙ 1ኛ ፣ የቍስጥንጥንያው 2ኛ ፣ እንዲሆኑ በቍስጥንጥንያው ጉባኤ አንቀጽ ሦስትና በኬልቄዶን ጉባኤ አንቀጽ ሃያ ስምንት ተወሰነ ። እንዲሁም በኬልቄዶን ጉባኤ በኢየሩሳሌም ወንበር የሚቀመጠው ሊቀ ጳጳስ 5ኛ እንዲሆን ተወሰነ ።

በጉባኤው የተወሰነውን ባለማክበር የሮሙ ፖፕና የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ እኔ እበልጥ ፣ እኔ እበልጥ በመባባል እስከ ዛሬ ድረስ



www.ethiopianorthodox.org

ሲፎካከሩ ይታያሉ ። የቊስጥንጥንያውም ፓትርያርክ የዓለም ፓትርያርክ በሚል ስም ይጠራ ጀመር ።

## በኦርየንታል (በተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ ፣ በግሪክ ኦርቶዶክስ ፣ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ካሉት የሃይማኖትና የሥርዓት ልዩነቶች ጥቂቶቹ (ዋና ዋናዎቹ)

ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው በክሕደት ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን አባልነታቸው በጉባኤ ተወግዘው ከተወገዱት ከአርዮስ ፣ ከመቅዶንዮስ ፣ ከንስጥሮስና ከተከታዮቻቸው በስተቀር እስከ አራተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የእምነት ልዩነት አልነበረም ። ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ ግን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚከተሉት ልዩነቶች ተከስተዋል ። እነሱም:-

1ኛ/ የካቶሊክና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ለኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት ሲሉ ፣ የኦርየንታል (የተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ነው ይላሉ ።

2ኛ/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድም ሠረፀ ስትል ፣ የኦርየንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሠረፀ ይላሉ ።

3ኛ/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሰዎች ስለሠሩት ኃጢአት በመጸጸት ንስሐ ገብተው ሳይፈጽሙት በድንገት ሲሞቱ ፣ በመንግሥተ ሰማያትና በገሃነመ እሳት መካከል ልዩ የሆነ ቦታ (መካነ ንስሐ ፣ ፐርጋቶሪ) ስላለ ፣ ነፍሶቻቸው ወደዚያ ሄደው ከኃጢአታቸው እስኪነጹ ድረስ መከራ እየተቀበሉ ቈይተው ኋላ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ በማለት የምታስተምረውን ትምህርት የኦርየንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አይቀበሉትም ።

4ኛ/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሮም ፖፕ የክርስቶስ እንደራሴና የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በላይ ስለሆነ በመንበሩ ተቀምጦ (ተሠይሞ) በሚወስነው ሁሉ አይሳሳትም ብላ በ1870 ዓ·ም በቫቲካን አንድ ጉባኤ የወሰነችውን ፣ የኦርየንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጉባኤ ተሰብስበው በተገኙበት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተወሰነውና ለወደፊትም የሚወሰነው ውሳኔ (ድንጋጌ)



www.ethiopianorthodox.org

ነው የማይሳሳት በማለት የአንድ ሰው የፖፑን አለመሳሳት አይቀበሉም ። ፖፑ የሁሉ የበላይ ነው በማለት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውንም ይቃወማሉ ።

5ኛ/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሕፃናትን አጥምቃ ሜሮን የምትቀባቸው ነፍስ ካወቁ በኋላ ነው ። የኦርየንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ግን ሕፃናትን አጥምቀው ወዲያው ሜሮን ይቀቧቸዋል ።

6ኛ/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለቀዳስያን ካህናት ሥጋ ወደሙን ስትሰጥ ለምእመናን ሥጋውን ብቻ አቀብላ ደሙን አታቀብልም ነበር። ነገር ግን በቫቲካን ሁለት ጉባኤ ለምእመናንም ሥጋ ወደሙ እንዲሰጣቸው ተፈቅዷል ። የኦርየንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ግን ለካህናትና ለምእመናን ሥጋ ወደሙን ይሰጣሉ ። ከዚህም ጋር የተዋሕዶ ኦርቶዶክሳውያን የምንቀበለው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነፍስ የተለየው ፤ መለኮት የተዋሐደው ነው ስንል ፤ ካቶሊካውያን ግን ነፍስ ያለው መለኮት የተዋሐደው ነው ይላሉ ።

እንዲሁም በተለያዩ ሀገሮች የሚኖሩ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች እንደ ልደትና ፋሲካ የመሳሰሉትን በዓላት የምዕራብ ሀገሮች በሚያከብሩበት ቀን ሳይሆን የሚኖሩበት ሀገር ክርስቲያኖች በሚያከብሩበት ቀን አብረው እንዲያከብሩ ተፈቅዶላቸዋል ።

7ኛ/ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሕፃናት ቅዱስ ቍርባንን የሚቀበሉ ነፍስ ዐውቀው ሜሮን ከተቀቡ በኋላ ሲሆን ፤ በኦርየንታልና በግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ግን ከተጠመቁና ሜሮን ከተቀቡ በኋላ ወዲያው ይቈርባሉ ።

8ኛ/ በ306 ዓ·ም እስፖኝ ውስጥ በተደረገችው በኤልቪራ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካህናት በመላ ሚስት አያገቡም። የኦርየንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስ ካህናት ግን ከጳጳሳት በስተቀር ቀሳውስትና ዲያቆናት ከፈለጉ አንዳንድ ሚስት አግብተው ሥልጣነ ክህነት ተቀብለው ሊያገለግሉ ይችላሉ ።

9ኛ/ የካቶሊክ ካህናት ጽሕማቸውን ሲላጩ ፤ የኦርየንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስ ካህናት ግን ያሳድጉታል ።

10ኛ/ በካቶሊክ ቤተ ክርበቲያን አብዛኛውን ጊዜ ከሥዕል በተጨማሪ ለጌታ ፤ ለመቤታችን ፤ ለጻድቃንና ለሰማዕታት መታሰቢያ የድንጋይ ሐውልት ሲቀረፅላቸው ፤ በኦርየንታልና በግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያናት ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ በሥዕል ይጣላሉ ።

11ኛ/ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚፈጸሙት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ፣ በካህናት ልብስ ፣ በቋንቋና እነዚህን በመሳሰሉት ሁሉ የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ሥርዓት ይለያያል ።

12ኛ/ በ16ኛው መቶ ዘመን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተለዩት ፕሮቴስታንቶች የፖፑን የበላይነትና አይሳሳትም የሚለውን ትምህርት አይቀበሉም ። የፕሮቴስታንቶች ሃይማኖት መገኛ ብድሳ ስድስቱን መጻሕፍት የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ። ማንኛውም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ እንደመሰለው ሊተረጉም ይችላል ። በዚህም ዐይነት መንገድ ፕሮቴስታንቶች እያንዳንዳቸው መጽሐፍ ቅዱስን እንደ መሰላቸው ሲተረጉሙ በሐሳብ በመለያየታቸው ምክንያት በየጊዜው በእምነት እርስ በእርሳቸው ተለያዩ ።

ምንም እንኳ ማዕርገ ክህነት ከጌታ ለሐዋርያት የተሰጠ ፣ ከሐዋርያትም ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ መሆኑን በመቃወም እንደ ምሥጢር ባይቈጥሩትም ከሦስቱ ማዕርገ ክህነት ቅስናንና ዲቁናን ስሙን ብቻ ይቀበላሉ ። ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን ግብረ ገብነትን የተመረከዘ መልካም ኑሮ ከኖረና በቂ የመንፈሳዊ ትምህርት ዕውቀት ካለው በአንብሮተ እድ ባይሾምም የካህናትን ሥራ ሊሠራ ይችላል ይላሉ ።

ከፕሮቴስታንቶች የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሦስቱን ማዕርገ ክህነት እንደ ምሥጢር ቈጥራ ትቀበላለች ። ፕሮቴስታንቶች ከሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ጸጋ የሚሰጥ በጥምቀትና በቍርባን ብቻ ነው ይላሉ ። ካህኑ በሚጸልይበት ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ደመ አምላክ አይሆንም ይላሉ ። በወይኑም ውኃ አይጨምሩበትም ። ሕፃናትን አጥምቀው ቅዱስ ቍርባንን የሚሰጡአቸው ነፍስ ካወቁ በኋላ ነው ። ባፕቲስት የሚባሉት በሕፃንነት የሚፈጸመውን ጥምቀት ይቃወማሉ ። አናባፕቲስት የተባሉት ደግሞ የሕፃናትን ጥምቀት በመቃወም የተጠመቁትን እንደገና ያጠምቃሉ ። ከፕሮቴስታንቶች ጥቂቶቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ በስተቀር ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ የሏቸውም ።

ንስሐን እንደ ምሥጢር ሳይቈጥሩ የሰውን ጠባይ ያሻሽላል ፤ ሰዎችን ለማጽናናት ይችላል በማለት ቢቀበሉትም ቅሉ ፣ ኃጢአትን



www.ethiopianorthodox.org

ለንስሐ አባት መናገር አያስፈልግም አሉ ። ንስሐ ገብቶ ሳይፈጽመው ድንገት የሚሞተው ሰው ነፍሱ በንስሐ ቦታ ነጽታ ወደ መንግሥተ ሰማያት ትገባለች የሚለውን የካቶሊኮችን እምነት አይቀበሉትም ።

ከበዓላት ቀናችም እሑድን ፣ ልደትን ፣ ጥምቀትን ፣ ትንሣኤንና ዕርገትን ብቻ ተቀበሉ ።

ለጌታ ሁለት ባሕርያት አሉት ብለው ያምናሉ ። መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ሠረፀ ይላሉ ።

በተለይ ካልቪን እግዚአብሔር የተወሰኑ ነፍሳትን እንዲድኑ ፣ የቀሩት እንዲጠፉ ወስኗል ብሎ አስተማረ ። እዝቪንግልም ጾምን በፍጹም አስወገደ ። በየጊዜው የተነሡ የፕሮቴስታንት መሪዎች ከዚህ በላይ የተጠቀሱትንና እነዚህን የመሳሰሉ ትምህርቶችን አስተማሩ ።

በዚህ አኳኋን የሉተር ፣ የእዝቪንግልና የካልቪን ተከታዮች ከጥንት ጀምረው ክርስትናን የተቀበሉ የኦርየንታል (የተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ ፣ የግሪክ ኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ያመኑባቸውን እምነቶች ተቃወሙ ። ይኸውም የሃይማኖት ትምህርት መገኛዎች መጽሐፍ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፉአቸው መጻሕፍት ፣ በየጊዜው የተደረጉት ጉባኤዎች ድንጋጌ ሲሆኑ ፣ ፕሮቴስታንቶች ግን መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ተቀብለው የቀሩትን አልተቀበሉም ። ከነዚህም በስተቀር ምንዙስናን ፣ ማዕርገ ክህነትንና የጻድቃንን ማማለድ ተቃወሙ ። እንዲሁም የጻድቃንና የስዕላት ሥዕሎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳይገኙና የጸጋና የአክብሮት ስግደት እንዳይደረግላቸው ተቃወሙ ። በዚህ አኳኋን በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ጌጦችና ሥዕሎች እንዳይገኙ አደረጉ ። ከሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን አምስቱንና እነዚህን የመሳሰሉትን ትምህርቶች አልተቀበሉም ።

የኦርየንታል ፣ የግሪክ ኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ቄሱ በሚጸልይበት ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ደመ አምላክ ይሆናል ሲሉ ፣ ፕሮቴስታንቶች አይለወጥም ይላሉ ። እንዲሁም የኦርየንታል ፣ የግሪክ ኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ድኅነት የሚገኘው ከእምነትና ከደጋግ ሥራዎች ነው ሲሉ (ያዕ·2፡ 14–26፤ ማቴ·7፡21) ፣ ፕሮቴስታንቶች ግን ድኅነት የሚገኘው ከእምነት ብቻ ነው ይላሉ ።

<u>ማሳሰቢያ</u> ። ፕሮቴስታንቶች በየጊዜው እርስ በእርሳቸው በሃይማ



www.ethiopianorthodox.org

ኖት በመለያየታቸው ምክንያት የእምነታቸው ዐይነት ብዙ ነው ። በተለይ በአሜሪካን ሀገር ብቻ በእምነት ተለያይተው የየግል እምነታቸውን ይዘው የሚገኙት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት (ዴኖሚኔሽን) ቍጥር ከሁለት መቶ ስልሳ በላይ ነው ። ስለዚህ እላይ የተዘረዘሩት እምነት ነክ ትምህርቶች ቀደምትና ዋና ዋና በሆኑት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የሚሰጡ ትምህርቶች ናቸው እንጂ የሁሉንም አያጠቃልሉም ።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል ሁለት

## የኦርየንታል (የተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ

## ምዕራፍ ፩

### የእስክንድርያ (የግብጽ ፤ የኮፕት) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንመለከተው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ በሆኑ በቢዛንታይን (በቍስጥንጥንያ) ነገሥታትና የእስልምና እምነት ተከታይ በሆኑ ቅኝ ገዥዎች ቀንበር ሥር ለብዙ ዘመናት በመማቀቋ ምክንያት የምእመናኖቿ ቍጥር በጣም ተቀንሶና አንሶ የምትገኘው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በ451 ዓ·ም እስከተደረገችው እስከ ኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ ከሌሎች የዓለም አብያተ ክርስቲያናት በይበልጥ ለክርስትና መጠናከርና መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጋለች ። ይኸውም በቅዱስ ማርቆስ ተመሥርታ በክርስቲያኑ ዓለም መጀመሪያ የነበረችውን ዝነኛዋን የእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ከፍታ በማስተማር ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶችንና ሊቃውንትን አፍርታለች ።

ግብጽ ውስጥ ኒትራንና አስቄጥስ በተባሉት በዓባይ ወንዝ ዳር በሚገኙት በረሓማ ቦታዎች በነ አባ እንጦንስ ፤ ጳኵሚስ ፤ መቃርስና አሞንዮስ አማካይነት የብሕትውናን ኑሮ በመመሥረት በዓለም ለሚገኙ ገዳማት መመሪያ የሆነ መሠረት ጥላለች ።

የወንጌል መልእክተኞቿንም ወደ ኑብያ ፤ ኢትዮጵያ ፤ ፔንጻፖሊስ (ሊብያ) ፤ ዓረቢያ ፤ ሕንድ ወዘተ· ልካ በትጋት በመስበክና በማስተማር ለክርስትና መስፋፋት ጥራለች ። መናፍቃንም በተነሡ ቍጥር በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት መሠረት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ቀጥተኛ


www.ethiopianorthodox.org

እምነታችንን የወሰኑትን የኒቅያን ፣ የቍስጥንጥንያንና የኤፌሶንን ጉባኤዎች በሊቀ መንበርነት የመሩ የእስክንድርያ ፓትርያርኮች ናቸው ።

እላይ እንደተመለከትነው የግብጽ ክርስቲያኖች በቢዛንታይን ነገሥታት ፣ እስልምናን በሚከተሉ ዓረቦች ፣ ቱርኮች ወዘተ· የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር በመውደቅ ለዘመናት ከፍ ያለ መከራና ሥቃይ ቢቀበሉም ፣ የካህናቶቻቸውና የምእመናኖቻቸው ቍጥር እየቀነሰ ቢሄድም ቅሉ ፣ ካህናቱ ለዘመናት ቀጥተኛ እምነታቸውን በመጠበቅ ምእመናንን በትጋት ሲያስተምሩ ፣ ሲንከባከቡና ሲያጽናኑ ኖረዋል ። አሁንም በተጠናከረ ሁኔታ ምእመናንን በመንከባከብ ላይ ናቸው ። በሃያኛው መቶ ዘመን የተነሡ የግብጽ ገዥዎች በሀገሪቱ ለሚኖሩ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች መጠነኛ የአምልኮ ነጻነት ስለሰጡ ዛሬ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ኮሌጅና ማሠልጠኛዎችን ከፍታ ካህናትን በብዛትና በጥራት ታሠለጥናለች ። ሠልጥነው በሚወጡትም ምሁራን አማካይነት ምእመናንን በትጋት ስለምታስተምርና ስለምትንከባከብ የምእመናኖቿ ቍጥር በመጠኑም ቢሆን እየጨመረ መጥቷል ። በአጠቃላይ የኮፕቶች አንድነትና ህልውና ተጠብቆ የኖረውና ያለው በተዋሕዶ እምነታቸው በመጽናት በቤተ ክርስቲያናቸው መሪነት አምልኮአቸውን እየፈጸሙ በመኖራቸው ነው ።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ከሀገሯ ውጭ በሱዳን ፣ በኩዌት ፣ በደቡብ አፍሪካ ፣ በኬንያ ወዘተ· አብያተ ክርስቲያናት መሥርታ ወንጌልን ታስተምራለች ።

ከዚህ በታች ስለ እስክንድርያ (ኮፕት) ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጋር የተቈራኙትንና ሊወሱ የሚገባቸውን ዋና ዋና ነጥቦች (ክፍሎች) እንመለከታለን ። እነሱም ።

## ሀ) ቅዱስ ዮሴፍ ከሄሮድስ በመሸሽ እመቤታችንንና ጌታን ይዞ ወደ ግብጽ ያደረገው ስደት

ግብጽ ውስጥ ክርስትና በወንጌላዊው ማርቆስ ከመሰበኳ ብዙ ዓመታት ቀደም ብሎ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ቁጥር 13–15 በተጻፈው መሠረት ቅዱስ ዮሴፍ ጌታንና እመቤታችንን ይዞ ከሄሮድስ ግዛት ውጭ ወደነበረችው ወደ ግብጽ በተሰደደበት ወቅት የግብጽ


www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኖች ጥንታውያን አባቶቻቸውና እናቶቻቸው ጌታንና እመቤታች ንን ተቀብለው የማስተናገድ ዕድል ማግኘታቸውን እንደ ታላቅ ቡራኬ ይቈጥሩታል ። እንዲሁም ቅዱስ ዮሴፍ ፥ እመቤታችንና ጌታ በጉዞ ላይ ሳሉ ባረፉባቸውና ግብጽ ውስጥ በኖሩባቸው ቦታዎች ላይ የቅዱስ ሰርግዮስን ፥ የእመቤታችንን ወዘተ· አብያተ ክርስቲያናት በመሥራትና ገዳማት በመመሥረት ለነሱ ያላቸውን የአክብሮት ስሜት ገልጸዋል ። እመቤታችን ፥ ጌታና ዮሴፍ ግብጽ የሰነበቱበት (የተቀመጡበት) ካይሮ ውስጥ ማታሪሕ በሚባለው መንደር የሚገኘው የድንግል ማርያም ዛፍ በመባል የሚጠራው የሾላ (የሲካሞር) ዛፍ ባለበት አካባቢ ነው ይባላል ። ይህ የሲካሞር ዛፍ በዚያው ቦታ እስከዛሬ ድረስ አለ ። ዛፉ ይህን ያህል ዘመን ሊቈይ የቻለውም በየጊዜው ያረጀው ሲገረሰስ ከሥሩ ሌላ በመውጣት በመተካቱና ምእመናንም በሚያደርጉት እንክብካቤ ነው ይባላል ።

ቅዱስ ዮሴፍ ፥ ጌታና እመቤታችን ወደ ግብጽ ሲጓዙ በነበሩበት ወቅት በመንገዳቸው ከአጋጠሙአቸው የተለያዩ (ብዙ) አደጋዎች እንዴት እንደዳኑ የሚነገሩ አፈ ታሪኮች አሉ ። ከነሱም ሁለቱ የሚከተሉት ናቸው ። የመጀመሪያው አፈ ታሪክ ዮሴፍና እመቤታችን ሕፃኑን ጌታን ይዘው ሲጓዙ በመንገድ ቀማኞች ደርሰው ለመቀማት አቆሙአቸው ። ከቀማኞች አንዱ መንገደኞችን ገድሎ የያዟትን ጥሪት ለመውሰድ ሲከጅል ዲስማስ (ጥጦስ) የተባለው ቀማኛ ለሕፃኑ ለጌታ ሕይወት በመራራት በጌታም ላይ ሆነ በዮሴፍና በእመቤታችን በማርያም ላይ ቀማኞች እጃቸውን እንዳይሰነዝሩ ከልክሎ የሚበሉት ከሰጣቸው በኋላ መንገዳቸውን በሰላም እንዲቀጥሉ አደረጋቸው ። ይህም ዲስማስ የተባለው ቀማኛ ከጊዜ በኋላ በጌታ ቀኝ በኩል ተሰቅሎ ሳለ "ጌታ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ" (ሉቃ·23፥32) ብሎ በመለመን ከአዳም ቀድሞ መንግሥተ ሰማያት የገባው ነው ይባላል ። ሁለተኛው አፈ ታሪክ ደግሞ ዮሴፍ ፥ ጌታና እመቤታችን ሲጓዙ ውለው ስለደከሙና ስለመሸባቸው ሌሊቱን ለማሳለፍ ከአንድ ዋሻ ውስጥ ገብተው ዐረፉ ። ጊዜው ብርድ ስለነበር ቅዝቃዜው ሲያንቀጠቅጣቸው ነበር ። በተለይ የሕፃኑን በብርድ መኮራመት የተመለከተች ሸረሪት ትንሽ ሙቀት

www.ethiopianorthodox.org

ይሰጠዋል ብላ የዋሻውን መግቢያ በር በድሯ ዘጋችው ። ጌታን ይዘው ለመግደል በሄሮድስ ከታዘዙት ወታደሮች ጥቂቶቹ ይከታተሉአቸው ስለነበረ እነዮሴፍ ሲመሽባቸው ሌሊቱን ለማሳለፍ ከአንዱ ዋሻ ውስጥ ገብተው ዐርፈው እናገኛቸዋለን በማለት በአካባቢው የነበሩትን ዋሻዎች ሲያስሱ መንገደኞቹ ወደዐረፉበት ዋሻ ደርሰው አንዱ ወታደር ለመፈተሽ ዘው ብሎ ሊገባ ሲል ፣ ጓደኛው ሞኝ ነህ እንዴ! የዋሻው በር በሸረሪት ድር ተተብትቦ እያየኸው ለምን ትደክማለህ? በቅርብ ጊዜ ሰው ቢገባበት ኖሮ ድሩ ይበጣጠስ ነበረ ስላለው ፣ እውነቱን ነው እኮ ብሎ ሳይገባ ተመለሰ ። በዚህ አኳኋን በሸረሪቲቱ ድር ምክንያት የጌታ ሕይወት ከሞት ተረፈ ይባላል ።

ጌታ የግብጽን ምድር ከረገጠበት ጊዜ ጀምሮ በየመቅደሶቹ የነበሩት ጣዖታት ሊያመልካቸው በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት እየወደቁ ተሰባብረዋል ። በተለይ ሕፃኑ ኢየሱስ ሔሊዮ ፖሊስ እተባለው የአሕዛብ መቅደስ ሲገባ እመቅደሱ ውስጥ የነበሩት 365 ጣዖታት ሊያመልካቸው በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት በተአምር ተንኮታኩተው ሲሰባበሩ የተመለከተው ሕዝብ በክርስቶስ አምኖ ክርስትናን እንደተቀበለ ይተረካል ።

ከሄሮድስ ዕረፍት በኋላ የጌታ መልአክ በግብጽ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጾ ወደ እስራኤል እንዲመለሱ ነገረው ። በነቢያት ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ጌታ ናዝሬት በተባለች የገሊላ ከተማ ሄዶ ኖረ (ማቴ.2፥19—23) ።

ሦስቱ እንግዶች ግብጽ ውስጥ እስከ ሄሮድስ ሞት ድረስ መሰንበታቸው እንጂ ፣ የቈዩበት ጊዜ ልክ አልተገለጸም ። ሆኖም አንዳንድ ሊቃውንት ስድስት ወራት ቈዩ ሲሉ ፣ ሌሎች ደግሞ ከሁለት እስከ ስድስት ዓመት ቈይተዋል ይላሉ ። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ግን ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ቈዩ ይላሉ ።

## ለ) በእስክንድርያ የክርስትና አመሠራረት

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሥራች ፣ የመጀመሪያው ፓትርያርክና ሰማዕት ወንጌላዊው ማርቆስ ነው ። ቅዱስ ማርቆስ ከአይሁድ ወገን እግዚአብሔርን ከሚፈሩና ሀብታም ከነበሩ ከማርያምና ከአሪስቶቡሉስ ሰሜን አፍሪካ በጥንታዊቱ ፔንዳፖሊስ ፣ በዛሬዪቱ ሊቢያ ውስጥ


www.ethiopianorthodox.org

በነበረች ቀሬና በምትባለው ከተማ ተወለደ ። እነሱም እዚያ ሲኖሩ ሽፍቶች ከተማዋን ሲዘርፉ የነሱም ሀብት ስለተወሰደ በመደኸየታቸው ምክንያት ወደ ኢየሩሳሌም ተሰደው ኑሮአቸውን በዚያ አደረጉ ። ኢየሩሳሌም ሳሉ ልጃቸው ማርቆስ ከፍ ያለ ትምህርት እንዲቀስም አድርገዋል ። እሱም በእብራይስጥ (በአረማይስጥ) እዚያ ይሰጡ ከነበሩት ከፍተኛ ትምህርቶች በተጨማሪ የግሪክና የላቲን ቋንቋዎችንም በሚገባ አጥንቷል ። ለመጀመሪያ ጊዜ የክርስትናን ትምህርት የተማረ ከአጎቱ ከበርናባስ ነበር (ቆላ.4፡10) ። ከቅዱስ ጴጥሮስና ከቅዱስ ጳውሎስም ተምሯል ። ጌታ ሰባ ሁለቱን አርድእት ሲመርጥ ከተመረጡት አንዱ ማርቆስ ስለነበር ከጌታም ተምሯል (ሉቃ.10፡1–12) ። በስሙ የሚጠራውን ወንጌል የጻፈም ማርቆስ ነው ። ፓፒያስ የተባለው የኢራጳሊስ ጳጳስ (60–130 ዓ.ም) ማርቆስ ከቅዱስ ጴጥሮስ የሰማውን ፣ ቃል በቃል በወንጌሉ መጻፉን መስክሯል ።

ጌታ ከደቀመዛሙርቱ ጋር የፋሲካን ራት የበላበት ፤ ከጌታ ስቅለት በኋላ ሐዋርያት ተሰብስበው የተቀመጡበት ፣ ለጰንጠቆስጤ ዕለት ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ የወረደላቸው በዚሁ ከሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት አንዷ በነበረችው በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ነበር ። በዚህ አኳኋን የማርቆስ እናት ቤት ለጌታና ለሐዋርያት የመሰብሰቢያና የመጸለያ አዳራሽ (ቦታ) ስለነበር ሊቃውንት የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን ነበር ይላሉ (ማር.14፡13–15 ፤ ዮሐ.20፡19፡ የሐዋ.1፡13 ፤ 2፡1፤12፡12)።

ጌታ "...እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ፤ እነሆም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ.28፡18–20) ብሎ ባዘዛቸው መሠረት ሐዋርያት በዓለም ዙሪያ የወንጌልን መልእክት ማዳረስ እንደጀመሩ በመጀመሪያው የጳውሎስ የስብከት ጉዞ ወቅት ጳውሎስና በርናባስ ማርቆስን አስከትለው የማስተማር ተግባራቸውን ለማከናወን ሲጓዙ ማርቆስ ጵንፍልያ ላይ ጥሏቸው (ከድቶአቸው) ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ (የሐዋ. 12፡25፡13፡13)። እነሱም መጀመሪያውን የስብከት ጉዞ አከናውነው በ50 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ውስጥ ከተደረገችው የሐዋርያት ጉባኤ ፍጻሜ በኋላ (የሐዋ.15፡1 30) ሁለተኛውን ጉዞ ለመጀመር ሲነሡ በርናባስ

www.ethiopianorthodox.org

የእኅቱን ልጅ ማርቆስን እንዲያስከትሉ ቢጠይቀው ቀደም ሲል ጵንፍልያ ውስጥ ጥሏቸው ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ ስለነበር በዚያ ምክንያት የተቀየመው ጳውሎስ አናስከትለውም በማለቱ በርናባስና ጳውሎስ በመቀያየም ተለያይተው የስብከት ተግባራቸውን በየፊናቸው ቀጠሉ ። ይኸውም በርናባስ ምንም እንኳ ቀደም ሲል የወጣትነትና የወላጆቹ ናፍቆት ስሜት አስገድዶት ለስብከተ ወንጌል ባይተባበርም ለወደፊት እንደ እኛ በዕድሜ ሲበስልና መንፈስ ቅዱስ ሲመራው ለክርስትና መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችል ይሆናል ብሎ በማሰብ ማርቆስን አስከትሎ ወደ ቆጵሮስ ሲጓዝ ፤ ጳውሎስ ደግሞ ሲላስን አስከትሎ ወደ ሶርያና ቂልቅያ የስብከት ጉዞውን ቀጠለ (የሐዋ.15፡36–41) ።

ማርቆስም ቆጵሮስ ውስጥ ከበርናባስ ጋር ወንጌልን ሰበከ ። ቀጥሎም በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና ትእዛዝ ወደ ትውልድ ሀገሩ ወደ ፔንዳፖሊስ ሄዶ ሲሰብክ ከቈየ በኋላ በ55 ዓ.ም ግድም የአሕዛብና የአይሁድ ሊቃውንት መናኻሪያና የዕውቀት መፍለቂያ ፣ እንዲሁም ለሮማ ግዛት በታላቅነቱ ከሮም ቀጥላ ሁለተኛ ከተማ ወደነበረችው ወደ እስክንድርያ ሄደ ። እዚያም ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ የፈጸማቸው የማስተማርና የአገልግሎት ተግባሮች ታሪክ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው ።

ማርቆስ እስክንድርያ ከተማ ደርሶ ሲዘዋወር የጫማው ማሰሪያ ጠፍር ስለተበጠሰበት አንያኑ ወደተባለ አይሁዳዊ ጫማ ሰፊ ሱቅ ገብቶ እንዲሰፋለት ተነጋገረ ። ተሰፍቶ እስኪያልቅ ድረስ ተቀምጦ ሳለ አንያኑ የጫማውን ቆዳ በመስፌ ሲበሳ ወስፌው በድንገት እጁን ክፉኛ ስለወጋው ኤስታዎስ ብሎ ጮኸ ። ኤስታዎስም አንድ አምላክ ማለት ነው። ማርቆስም አንያኑ አንድ አምላክ በማለቱ ተደስቶ የአንያኑን ቁስል አፈር በምራቁ ለውሶ በመቀባት በተአምር አዳነለት ። ጫማውን ሰፍቶ እስኪጨርስ ድረስም ስለ እግዚአብሔር አብ ፣ ዓለምን (ሕዝቦችን) በደሙ ከኃጢአት ሊያነጻ ስለመጣው የባሕርይ ልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና በአጠቃላይ የክርስትናን ትምህርት አስተምሮ በክርስቶስ አሳመነው ። በዚህ አኳኋን አንያኑ በማርቆስ ስብከት እስክንድርያ ውስጥ ክርስትናን በመቀበል የመጀመሪያው ሰው ሆነ ። እሱም በማርቆስ ትምህርት ልቡ ስለተነካና ስለተደሰተ ወደ ቤቱ ወስዶ አብሮት እንዲሰነብት አደረገ ። እዚያም ሆኖ ማርቆስ የአንያኑን ቤተሰቦች አስተምሮ ሁሉንም አጠመቀ

www.ethiopianorthodox.org

ቸው ። በዚህ አኳኋን በታላቅ ትጋት ለአንያኑ ጐረቤቶችና በአጠቃላይ ለከተማዋ ኑአሪ ሕዝብ ወንጌልን እየሰበከ በክርስቶስ አሳምኖ በማጥመቁ ብዙዎች ክርስቲያኖች ሆኑ ። በነዚህም በማርቆስ ትጋት ወደ ክርስትና በተመለሱት ምእመናን የመጀመሪያዋ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች ። ነገር ግን የክርስቲያኖች ቍጥር በፍጥነት እያደገ (እየጨመረ) መሄዱን የተመለከቱ የጣዖት ካህናት ይህ ማርቆስ የተባለው የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ጣዖቶቻችንን ያለተከታይ (ያለአምላኪ) በማስቀረት አምልኮአችንንና መተዳደሪያችንን ቀስ በቀስ ሊያጠፋብን ነው በማለት እሱን ለመግደል በየስፍራው መዶለት ጀመሩ ። ማርቆስም ይህንኑ በሕይወቱ ላይ የተጠነሰሰውንና የተሸረበውን አድማ ከምእመናን እንደሰማ ለራሱ ሞት ምንም ሳይሰጋ ከራሱ ሕልፈት በኋላ ክርስቲያኖች ያለመንፈሳዊ አባት ፣ መሪና አጽናኝ ተበታትነው እንዳይቀሩ በማሰብ አንያኑን የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ አድርጎ ሾመው ። ከሥሩ ሆነው በማገልገል ለሚረዱትም ዐሥራ ሁለት ቀሳውስትና ሰባት ዲያቆናት ማዕርገ ክህነት በመስጠት ሾሞ የቤተ ክርስቲያኒቱን መሠረት አጠናከረ ። በዚህም ነቢዩ ኢሳይያስ በግብጻውያን ለጣዖት ይሰጥ የነበረው ክብር በማርቆስ ጥረት ለእግዚአብሔር የሚሰጥ መሆኑን በመግለጽ "በዚያን ቀን በግብጽ ምድር መካከል ለእግዚአብሔር መሠዊያ ፣ በዳርቻዋም ለእግዚአብሔር ዓምድ ይሆናል" (ኢሳ.19፡19) በማለት የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ ።

የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን ካጠናከረ በኋላ ቀደም ሲል የመሠረታትን የጴንጣፖሊስን ቤተ ክርስቲያን ለመጐብኘትና ምእመናንን ለማጽናናት ፣ እንዲሁም በሕይወቱ ላይ አደጋ ለማድረስ ከሚዶልቱት ዘንድም ቁጣቸው እስኪበርድ ድረስ ዘወር ብሎ እንዲቈይ ክርስቲያኖች በለመኑት መሠረት ወደ ፔንጻፖሊስ ሄዶ ያስተምር ጀመር ። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ (የሐዋ.13፡13) ከበርናባስና ከጳውሎስ ጋር በማስተማር ተግባር ላይ ተሰማርቶ ሳለ መከራውን በመሰቀቅና እናቱ ታደርግለት የነበረው እንክብካቤ ውል ስላለው ሳያሰናብቱት ከጵንፍልያ ሸልኮ ወደ ኢየሩሳሌም በመመለሱ በማርቆስ ላይ ቅሬታ አድሮበት የነበረው ጳውሎስ (የሐዋ.15፡38) ፣ ሮም በእስር ቤት ሳለ ማርቆስ በጋለ መንፈስ እስክንድርያና ፔንጻፖሊስ ውስጥ


www.ethiopianorthodox.org

ያከናወነውን የስብከተ ወንጌል ውጤት ሰማ ። ይህም የተከናወነው በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መሆኑን በመረዳቱ ፤ ለጥቂት ጊዜም ዘወር ብሎ ለመቆየት ከእስክንድርያ መውጣቱን ስለሰማ ያለፈ ቅሬታው አግባብ እንዳልነበር ተገንዝቦ ወደ ሮም ሄዶ እንዲረዳው ጠይቆት ነበር ። በዚህ መሠረት ማርቆስ ከፔንዳ ጶሊስ በ62 ዓ.ም ወደ ሮም ሄዶ ከቅዱስ ጳውሎስና ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በመሆን አስተምሯል ። ጳውሎስ በእስር ቤት ሳለም በሚገባ አገልግሎታል (ቆላ. 4፡10 ፤ 2ጢሞ. 4፡11፡ ፊልሞ. 1፡ 24፡ 1ጴጥ. 5፡13)። ለተወሰነ ጊዜ ሮም ከነጳውሎስና ጴጥሮስ ጋር ሲያስተምር በቈየበት ወቅት አቡነ አንያኑ ፤ ካህናቱና ዲያቆናቱ የእስክንድርያን ምእመናን ሲያስተምሩና ሲያገለግሉ ቈዩ ። ጳውሎስና ጴጥሮስ በሰማዕትነት ከዐረፉ በኋላ ማርቆስ ከሮም ተመልሶ እስክንድርያ ሲደርስ ቀደም ሲል የሾማቸው ካህናትና አስተምሮ ወደ ክርስትና የመለሳቸው ምእመናን እስክንድርያ ውስጥ በሜዲትራንያን (በታላቁ) ባሕር አጠገብ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ቈዩት ። ይህም ቤተ ክርስቲያን በአቡነ ክርስቶዱሎስ ፓትርያርክነት ዘመን በ1047 ዓ.ም የእስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክ ወደ ካይሮ እስኪተዛወረበት ጊዜ ድረስ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ሆኖ ኖሯል ።

ከሮም ወደ እስክንድርያ ከመመለሱ በፊት እላይ እንደተመለከት ነው ከጌታ ደቀ መዝሙር ከቅዱስ ጴጥሮስ ያገኘውን (የተማረውን) ትምህርት መሠረት በማድረግ በስሙ የሚጠራውን ወንጌል ከጴጥሮስ ዕረፍት በኋላ በ65 ዓ.ም ግድም ሮም ውስጥ ጽፎ እዚያው ለሚኖሩ ክርስቲያኖች የክርስቶስን አዳኝነት መረጃ ፤ ከደረሰባቸው ሥቃይና ስደት መጽናኛና የእምነት መመሪያ እንዲሆናቸው ሰጠ ። እሱም ወደ እስክንድ ርያ ሲመለስ የዚህኑ ወንጌል ቅጅ ይዞ እንደነበርና ዓለማቀፋዊ መግባቢያ በነበረው በጽርዕ ቋንቋ ስለተዘጋጀ እስክንድርያም ውስጥ ለማስተማሪያ እንደተጠቀመበት ይታመናል ። አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ ወንጌሉን እስክንድርያ ውስጥ ጽፎ ሮም ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ላከላቸው ይላሉ ።

ከሮም ወደ እስክንድርያ ከመመለሱ በፊትና ከተመለሰም በኋላ በማርቆስና በተከታዮቹ በነአቡነ አንያኑ ትጋት እስክንድርያ ውስጥ የክርስትና እምነት እየተስፋፋ ሄደ ። በክርስትና መስፋፋት ምክንያት


www.ethiopianorthodox.org

ልባቸው (አንጀታቸው) ያረረ ካህናተ ጣዖት ቀደም ሲል ማርቆስን ለማጥፋት የነበራቸው ፍላጎት እንደገና ስላገረሸባቸው እሱን ለመግደል ቈርጠው ተነሡ ። ይህንን ሕገወጥ ዓላማቸውን በተግባር ላይ ለማዋል በማሰብ ለጣዖት አምላኪው ሕዝብ በማርቆስ የሚመሩት ክርስቲያኖች ጣዖቶቻችንን (አምላኮቻችንን) በኃይል በማውደም የጣዖት አምልኮን ለማጥፋት ቈርጠው ተነሥተውብናል የሚል ወሬ ነዙ (አናፈሱ)። በሮም ቄሣር ተወክሎ የግብጽ ገዥ የነበረውም የጥፋት ተልእኮአቸውን (ዓላማቸውን) በመደገፍ ውስጥ ውስጡን አደፋፈራቸው ። ጣዖት አምላኪው ሕዝብም እንዳለፈው ጊዜ አሁንስ ዘወር በማለት አያመልጠንም ብሎ ማርቆስን በሕገ ወጥ መንገድ ለመግደል ሲያደባ እንደአጋጣሚ በ68 ዓ.ም ሴራፒስ የተባለው ጣዖትና የፋሲካ በዓላት በአንድ ቀን በዋሉበት ዕለት ክርስቲያኖች ባውካሊስ በተባለው ቦታ በነበረው ቤተ ክርስቲያናቸው የፋሲካን በዓል ሲያከብሩ የሴራፒስን በዓል የሚያከብረው ጣዖት አምላኪ ሕዝብ በድንገት ክርስቲያኖች ወደተሰበሰቡበት ቤተ ክርስቲያን ግልብጥ ብሎ በመሄድ ማርቆስን ያዘው ። ወዲያውም አንገቱን በገመድ አስረው በከተማይቱ (በእስክንድርያ ከተማ) መንገዶች በበሬ በመጐተት ካሠቃዩት በኋላ ነፍሱ ወጣች ። አሠቃይተው የገደሉት አላረካቸው ስላለ ወዲያው አስከሬኑን ለማቃጠል ሲሞክሩ (ሲዘጋጁ) ነጐድጓድና ዝናብ ያዘለ ከባድ አውሎ ነፋስ ተነሥቶ ስለወረወራቸው ጥቂቶች ሲሞቱ ብዙዎች በመቁሰላቸው የተረፉት ተደናግጠው እግሬ አውጭኝ በማለት ወደየቤታቸው ሸሹ ። በዚያን ጊዜ ክርስቲያኖች አስከሬኑን አንሥተው ባውካሊስ በነበረው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አሳረፉት ። በዚህ አኳኋን ወንጌላዊው ማርቆስ በቅዱስ ጴጥሮስ በመሾም የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን መሥርቶና የመጀመሪያው ፓትርያርክ ሆኖ በትጋት ሲያገለግል ከቈየ በኋላ በ68 ዓ.ም በሰማዕትነት ዐረፈ ። ወዲያው አቡነ አንያኑ በመንበሩ ተተክቶ የማርቆስን ፈለግ በመከተል የክርስትናን ትምህርት ማስፋፋቱን ቀጠለ ።

በዘጠንኛው መቶ ዘመን የቬኑስ ነጋዴዎች የቅዱስ ማርቆስን አጽም ሰርቀው ወስደው ቬኑስ በሚገኘው በማርቆስ ካቴድራል ውስጥ አስቀምጠውት ሲኖር በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ መሠረት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪ ፖፕ ጳውሎስ 6ኛ ለእስክንድርያው የኮፕት ፓትርያርክ ለአቡነ ቄርሎስ 6ኛ እንዲሰጥ አደረገ ። በእስክንድርያ ክርስትና


www.ethiopianorthodox.org

የተሰበከችበትና ወንጌላዊው ማርቆስ በሰማዕትነት ያረፈበት የአንድ ሺህ ዘጠኝ መቶኛው ዓመት በዓል ላይ ፕሬዚዳንት ናስር ፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፣ የኦርየንታል ፣ የግሪክ ኦርቶዶክስ ፣ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች በተገኙበት በ1968 ዓ.ም በድምቀት በተከበረበት ወቅት የቅዱስ ማርቆስ አጽም ወደ ግብጽ ተመልሶ ካይሮ ውስጥ በስሙ አዲስ በተሠራው ሃያ ሺህ ምእመናን ሊያስተናግድ በሚችለው በታላቁ ካቴድራል ውስጥ በክብር ዐርፏል ። በዚያው በ1968 ዓ.ም በሚያዝያ ወር በሕማማት መጀመሪያ ከሰኞ ዕለት ጀምሮ ዘይቱን በተባለው ካይሮ ውስጥ የድንግል ማርያም ዛፍ ከሚገኝበት ቦታ አካባቢ በሚገኘው በስሟ በሚጠራው ቤተ ክርስቲያን እመቤታችን ለአያሌ ጊዜ መሸት ሲል እየተገለጠች ለብዙ ሕዝብ ታይታለች ። ብዙ በሽተኞችም ተፈውሰዋል ።

ቅዱስ ማርቆስ ግብጽ ውስጥ ስላከናወነው የስብከተ ወንጌል ተግባር የኢትዮጵያ ሊቃውንት በትርጓሜ ወንጌል ውስጥ እንደሚከተለው ይተርካሉ "ማርቆስ በገጸ አንበሳ ይመሰላል ። አንበሳ ኑሮው ከሰው ርቆ በምድረ በዳ ነው ። ከዚያ ሆኖ ጣሕሩን ባሰማ ጊዜ እንስሳት ይገሠጻሉ ፤ አራዊት ይደነግጣሉ ። ማርቆስም ከትምህርት ምድረበዳ በምትሆን በግብጽ ቀዳሚሁ ለወንጌል እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ ባስተማረ ጊዜ ምእመናን ተገሥጸዋል ፤ አጋንንት ፣ መናፍቃን ደንግፀዋልና ፤ ዳግመኛም አንበሳ ለላህም ጌታው ነው ፤ ይሰብረዋል ። እሱም ከግብጽ አምልኮተ ላህምን አጥፍቷልና ። ከትምህርት ምድረበዳነቷንም ከዚህ ይናገራሉ ፣ ቀድሞ ሙሴ አሮን ኋላም እለ ኤርምያስ ወርደው ቢያስተም ሯት አልተቀበለችም ፤ ፍጹም ጥቅሟ በማርቆስ ነውና ።"

## ሐ) የስደት ዘመኖች (ዘመነ ሰማዕታት) በግብጽ ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስለ ቀጥተኛው እምነቷ የተጋደለችበት ዘመን

የሮማ መንግሥት ቀደም ሲል በግዛቱ ለሚኖሩ ለተለያዩ እምነት ተከታዮች የማምለክ ነጻነት ሰጥቶ ነበር ። በተለይ አይሁድ ኃይለኞችና አዋኪዎች ስለነበሩ ሙሉ የአምልኮ ነጻነት ነበራቸው ። ክርስትና የተጀመረች ከአይሁድ አምልኮ አካባቢ ነበር ። ሐዋርያትም በቤተ


www.ethiopianorthodox.org

መቅደስና በምኩራብ አምልኮአቸውን ይፈጽሙ ነበር ። ስለዚህ በዚያን ጊዜ (በመጀመሪያ) በክርስቲያኖች ላይ ከአይሁድም ሆነ ከአሕዛብ መሰናክል አልተፈጠረባቸውም ነበር ። ምክንያቱም አይሁድ በእምነት መሰሎቻችን ናቸው ፤ ሮማውያንም ክርስቲያኖች እቤተ መቅደስ አካባቢ የሚፈጽሙትን አምልኮ በማየት የአይሁድ እምነት ተከታዮች ናቸው ብለው ያምኑ ነበር ። በዚህ አኳኋን በመጀመሪያው ወቅት በአይሁድ ጥላ ሥር ክርስትና ሰላም አግኝታ ነበር ። ነገር ግን ጳውሎስና መሰሎቹ ክርስትና የአይሁድ እምነት ቅርንጫፍ አለመሆኗን በይፋ በማስተማራቸውና ከአሕዛብም ወገን ብዙዎችን ወደ ክርስትና በመመለስ ብዙ ተከታዮች በማግኘቷ ፤ እንዲሁም አይሁድ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ ነው ብለው እሱን በማምለካቸው ፤ አሕዛብ ደግሞ ክርስቲያኖች የአይሁድን እምነት ወይም ጣዖት አምልኮን ባለመከተላቸው ፤ አይሁድና ሮማውያን ክርስትናን ማሳደድ ጀመሩ ።

ቀደም ሲል የተመለከትነው በቅዱስ ማርቆስ ላይ የተፈጸመው ሕገ ወጥ ፤ ግፍን የተሞላና አሰቃቂ ድርጊት (እርምጃ) በሮማው ቄሣር (ንጉሠ ነገሥት) ተወክለው ግብጽን ያስተዳድሩ በነበሩት ገዥዎች ትእዛዝ አልነበረም ። ያ ሕገወጥ ድርጊት የተፈጸመው በክርስትና መስፋፋት ከፍ ያለ ጥላቻና ሥጋት ባደረባቸው ካህናተ ጣዖት አነሳሽነት በደም ፍላት በተነሣው ጣዖት አምላኪ ሕዝብ መሆኑ ግልጽ ነው ። ሆኖም ገዥዎችም ቢሆኑ የክርስቲያኖችን መደምሰስ ይሹ ስለነበር ያለመንግሥት ትእዛዝ በገዛ ፈቃዱ የግድያ ወንጀል በፈጸመው ሕዝብና ቅስቀሳ ባካሄዱት መሪዎቹ ላይ አንዳችም ሕጋዊ እርምጃ አልወሰዱም ።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ ማርቆስ ዕረፍት ጀምሮ በሮሙ ቄሣር በሴፕቲሚዮስ ሴቪሩስ የታወጀው ስደት እስከ ተጀመረበት ጊዜ ድረስ በነ አቡነ አንያኑ ፤ በቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ፤ በድሜጥሮስና በመሳሰሉት ካህናት ጥረት የክርስትናን ትምህርት ከሞላ ጐደል በሰላም ስታስፋፋ ቈይታለች ።

ከንጉሥ ዳክዮስ ቀደም ብሎ የተነሣው ንጉሥ አሌክሳንደር ለክርስቲያኖች በመራራት ከብዙ የሮማ አማልክት (ጣዖታት) መካከል ኢየሱስ የሚል ጣዖት አስቀምጦ እንደሌሎቹ ዜጎቹ ከሌሎች ጣዖታት ጋር አብራችሁ አምልኩት ቢላቸው ፤ የኛ አምላክ በሰው እጅ የተሠራ ጣዖት



www.ethiopianorthodox.org

ሳይሆን የሁሉ ፈጣሪ ሕያው አምላክ ነው ። አምልኮም የሚገባው እሱ ብቻ ነው በማለት አልተቀበሉትም ። የሮማ መንግሥት ምንም እንኳ ለዜጎቹ የእምነት ነጻነት የመስጠት ባህል ቢኖረውም ክርስቲያኖች ሌሎችን አማልክት አቃለው በመቃወማቸው በነሱ ላይ የተሰነዘረው ስደት እየከፋ ሄደ ።

በዚያን ጊዜ በየሀገሩ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ በገዥዎችና በጣዖት አምላኪው ሕዝብ ዘንድ እንደ ሃይማኖተ ቢስ (ሃይማኖት የለሽ)፣ ግብረ ገብነት እንደሌላቸው ፣ ሀገርን ፣ ሕዝብንና መንግሥትን እንደሚ ክዱ ሆነው ይቈጠሩ ነበር ። ይኸውም የሮም ነገሥታት አምልኩን ሲሉ ፣ ክርስቲያኖች የምናመልክ ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን ብቻ ነው ። ነገሥታቱ ግን ገዥዎቻችን ስለሆናችሁ ከልብ በመውደድ እናከብራችኋ ለን ፤ እንታዘዛችኋለንም ስላሉ እንደወንጀለኞች ተቈጠሩ ። ስለዚህ ነገሥታትንና ጣዖታትን አለማምለካቸው እንደ አደገኛ ወንጀለኞች አስቈጠራቸው ። ሰላማዊነታቸውንም ለማስረዳት ቢሞክሩ ሰሚ አጡ ። ጣዖት ጠራቢዎች ከፍ ያለ ገንዘብ የሚያጋብሱበት ሥራቸው እንዳይቋረ ጥባቸው በማሰብ (የሐዋ· 19 ፥ 21—41) ፤ የአይሁድም አለቆች ሕዝባቸው ወደ ክርስትና እምነት ጭልጥ ብሎ እንዳይሄድ በመፍራት ክርስቲያኖችን እንደ ደመኛ ጠላት ይመለከቷቸው ነበር ።

እንዲሁም በሮም ግዛት ውስጥ ረኃብ ፤ ቸነፈር ፣ የጎርፍ ማጥለቅለቅ፣ የመሬት መንቀጥቀጥና እነዚህን የመሳሰሉ አደጋዎች በተከሰቱ ቍጥር በከሐዲዎች ክርስቲያኖች ምክንያት አማልክቶቻችን ተቈጥተው ያወረዱ ብን መቅሰፍቶችና ቅጣቶች ናቸው ብለው በማመን ክርስቲያኖችን ለማጥፋት ከመሞከር ቸል አላሉም ነበር ።

በዚያን ወቅት ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት (አፖሎጂስቶች) ለክርስትና ጠበቃ በመሆን ከላይ የተጠቀሱት ክሶች (ወንጀሎች) ሁሉ መሠረተ ቢስ ውሸት መሆናቸውንና የክርስትናም ትምህርት የሕዝቡን ጠባይ የሚያርም መሆኑን ሽንጣቸውን ገትረው ለጣዖት አምላኪው ሕዝብ ፣ ለአስተዳዳሪዎችና ለነገሥታቱም ጭምር ቢያስረዱ ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት ሰምቶ የሚቀበላቸው ጠፋ ። ስለዚህ በዚያን ዘመን ዓለምን ይገዙ በነበሩት በሮማውያን ነገሥታት በሰፊው ግዛታቸው ውስጥ በሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ እንዲፈጸም የተላለፈው አሰቃቂ ስደትና



www.ethiopianorthodox.org

ጭፍጨፋ ከቅኝ ግዛታቸው አንዷ በነበረችው ግብጽ በሚኖሩት ክርስቲያኖች ላይም ተፈጽሟል ።

በግብጽ ክርስቲያኖች ላይ ከተፈጸሙት አሰቃቂ ስደቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ/ <u>በሴፕቲሚዮስ ሴቬሩስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (193 211 ዓ.ም)</u> ።

በዚሁ በሮም ንጉሠ ነገሥት በሴቪሩስ በ202 ዓ.ም በተላለፈው የስደት ዐዋጅ መሠረት እንደ ኔሮን የስደት ትእዛዝ ሮም ውስጥ በነበሩ ክርስቲያኖች ላይ ብቻ ሳይወሰን በሌሎች የሮማ ግዛቶች ውስጥ በሚኖሩትም ክርስቲያኖች ላይ ተፈጽሟል ። ሆኖም በሌሎች የሮም ግዛቶች ውስጥ ከተፈጸመው ሥቃይና ስደት ይልቅ በግብጽና በካርቴጅ (ሰሜን አፍሪካ) በነበሩ ክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው ሥቃይ ይበልጥ አሰቃቂ ነበር ። ይኸውም በንጉሡ ምስል ሥር ዕጣን በማጤስ እንዲያመልኩት ሲጠየቁ ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን ብቻ እንጂ ፍጡር የሆነ ሰውን አናመልክም ፤ ንጉሡ ግን ገዥያችንና አስተዳዳሪያችን በመሆኑ እናከብረዋለን ። ሃይማኖታችሁን ካዱ ከሚለው ትእዛዝ በስተቀር ትእዛዞቹን ሁሉ በታማኝነት በመፈጸም እንገዛለን አሉ ። ሆኖም ንጉሡን አናመልክም ፤ ለጣዖትም መሥዋዕት አናቀርብም ያሉት ክርስቲያኖች አንገታቸውን በመሰየፍ ደማቸው እንደጐርፍ ፈሰሰ ። እንዲሁም ከፊሎቹ ለተራቡ አውሬዎች በመጣል ፣ በመጋዝ በመሰንጠቅ ፣ በእሳት በመቃጠልና በተለያዩ አሰቃቂ ሥቃዮች በሰማዕትነት ዐረፉ ።

በዚሁ የስደት ወቅት ከግብጽ ውጭም በጎል (በፈረንሳይ) የልዮን ኤጲስ ቆጶስ ሔሬኒዮስ (ኢሪኔዎስ) በሰማዕትነት ዐርፏል ። እንዲሁም ንጉሡ በግዛቱ የሚኖር ማንኛውም ሰው ክርስትናን እንዳይቀበል (ክርስቲያን እንዳይሆን) በማለት የደነገገውን ሕግ ቸል በማለት የካርቴጅ ተወላጅ የነበሩት ፔርፔትዋና የሰንበት ትምህርት ቤት ጓደኞቿ ክርስትናን ተቀብለው ተጠመቁ ። የንጉሡ ወኪሎችም የመንግሥት ሕግን መጣሳቸውን ገልጸው ክርስቶስን እንዲክዱና ለጣዖት እንዲሰግዱ ቢጠይቋቸው አምላካችንን አንክድም ፤ በሰው እጅ ለተሠራ ጣዖትም አንሰግድም በማለት በቀጥተኛዋ የክርስትና እምነታቸው ስለጸኑ ፣ ይኸው እንደ ወንጀል ተቈጥሮባቸው በሰማዕትነት ዐረፉ ።

የሆነ ሆኖ ያ አሰቃቂ ስደት የክርስትናን እርምጃ በምንም መንገድ ለመግታትና ለመደምሰስ አልቻለም ። በተለያዩ የሮም ቅኝ ግዛት ሀገሮች



www.ethiopianorthodox.org

ውስጥ እንደሚኖሩት ክርስቲያኖች ሁሉ የእስክንድርያም ምእመናን ካህናት ቍጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዛ ሄደ ።

2ኛ/ <u>በዳክዮስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (249 — 251)</u> ።

፩ዳክዮስ ትእዛዝ በመላ የሮም ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ጣዖት እንዲያመልኩና ለማምለካቸውም የማስረጃ ሰርቲፊኬት ከየቀበሌ አቸው እንዲያመጡ ፤ ይህንን ያልፈጸሙ ግን እንዲፈጁ በማለት የታወጀው ስደት ግብጽም ውስጥ በተግባር ላይ ስለዋለ ብዙ ክርስቲያኖች ክርስቶስን አንክድም ፤ ለጣዖትም አንሠዋም ፤ ሠውተዋል የሚል ሰርቲፊኬትም አናወጣም በማለታቸው በሰማዕትነት ዐርፈዋል ። በዚያን ወቅት በሰማዕትነት ካረፉት መካከል የቀጸዶቅያው ተወላጅ ቅዱስ መርቆርዮስ በሮማ ጦር ሠራዊት ውስጥ በአዛዥነት ተመድቦ ሲያገለግል ከቆየ በኋላ ለአርጤምስ ጣዖት መሥዋዕት አላቀርብም ፤ የክርስትና እምነቴንም አልክድም በማለቱ በ250 ዓ·ም ቀጸዶቅያ በምትገኘው ቂሣርያ ውስጥ በመሰየፍ በሰማዕትነት ዐርፏል ። ቤተ ክርስቲያንም የቅዱስነት ማዕርግ ሰጥታ በስሙ ቤተ ክርስቲያን አሳንጻለታለች ።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ግን በፊታቸው ከተጋረጠው አሰቃቂ ሥቃይ ለማምለጥ ብቻ በማሰብ ለጣዖት በመሠዋት ክርስቶስን ክደዋል ። ሆኖም የስደቱ ጊዜ አልፎ በመካከሉ ጊዜአዊ ሰላም ሲሰፍን በሠሩት ስሕተት በመጸጸት ንስሐ ገብተው ወደ ቀድሞው የክርስትና እምነታቸው እንዲመለሱ የጠየቁትን ሁሉ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቀደም ሲል በሴፕቲሚዮስ ሴቬሩስ ዘመነ መንግሥት በተነሣው ስደት ወቅት ተሳስተው ለተጸጸቱት ይቅርታ እንዳደረገች ሁሉ አሁንም ዲዮናስዮስ የተባለው የእስክንድርያው ፓትርያርክ (246—264) ያለ ዳግም ጥምቀት (ጥምቀት አይደገምምና) ንስሐ በመስጠት ተቀብሏቸዋል (ሉቃ· 15 ፥ 11 — 31) ። ሆኖም እንደ ኖቫትያን ይህ የዲዮናስዮስ አቋም ትክክል አይደለም ብለው የቤተ ክርስቲያንን የቀና ድርጊት በመቃወም ከክርስቲ ያኖች አንድነት የተለዩ (የተገነጠሉት) ዶናቲስትና ሚሌቲያን ይባላሉ ።

3ኛ/ <u>በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት የተነሣው ስደት (284 — 305)</u> ።

ዲዮቅልጥያኖስ ለሁለት ዓመታት ያህል እያከታተለ ልዩ ልዩ የሆኑ ጥብቅ ዐዋጆችን በማወጅ ቅዱሳት መጻሕፍትንና አብያተ ክርስቲያናትን



www.ethiopianorthodox.org

አቃጠለ ። ለጣዖት መሥዋዕት አናቀርብም ያሉት ካህናትና ምእመናን ደም እንደ ጐርፍ ፈሰሰ ። ከአራዊት በማታገል ፣ ለተራቡ አውሬዎች በመጣል ፣ በመጋዝ በመሰንጠቅ ፣ በእሳት በማቃጠል ወዘተ· ክርስቲያኖችን አስፈጃቸው ።

እላይ በተጠቀሱት የስደት ዓመታት ግብጽ ውስጥ በሰማዕትነት ካረፉት መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

(1) <u>ቅድስት ካቴሪኒ ዘእስክንድርያ</u> ። ካቴሪኒ የዲዮቅልጥያኖስ ያንድ ክፍል ረዳት ገዥ በነበረው በማክሴንዲዮስ (በመክስምያኖስ) ዘመነ መንግሥት ለጣዖት ይቀርብ የነበረውን አምልኮ በመቃወሟና የክርስትና እምነቷን አልክድም በማለት ስለጸናች አንገቷን በሰይፍ በመቆረጥ በሰማዕትነት ዐርፋለች ። አስከሬኗ በመላእክት ተወስዶ ባረፈበት በሲና ተራራ ሙሴ የሚቃጠል ቁጥቋጦ ባየበትና ኋላም ዐሠርቱ ቃላትን ከተቀበለበት ቦታ ላይ በዩስጥንያኖስ ዘመነ መንግሥት በ530 ዓ·ም በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በስሟ የሚጠራ ታላቅ ገዳም ተሠርቷል ። ንጉሥ ዩስጥንያኖስ ይህንኑ ገዳም በ530 ዓ·ም ከማሠራቱ በፊት ከጥንት ጀምሮ መናንያን በዚሁ ቦታ ይኖሩ እንደነበረ ይተረካል ። በዚሁ ገዳም በሚገኘው ቤተ መጻሕፍት በጥንት ዘመን በእጅ በብራና የተጻፉ ከሦስት ሺህ ሦስት መቶ በላይ የሚሆኑ የቅዱሳት መጻሕፍት ቅጅዎች ይገኛሉ ። ቲሼንዶርፍ የተባለው ምሁር በብሪቲሽ ሙዚየም ያለውን ኮዴክስ ሲናይቲኩስ የተባለውን ጥንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ የእጅ ጽሑፍ በ1859 ዓ·ም ያገኘው እዚሁ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ነው ። በቤተ መጻሕፍቱ ከሚገኙት መጻሕፍት አብዛኞቹን የአሜሪካ ድርጅቶች በማይክሮ ፊልም ቀርጸዋቸዋል ። ይኸውም ተግባር ምናልባት በእሳት ቃጠሎና በመሳሰሉ ድንገተኛ አደጋዎች በመጻሕፍቱ ላይ ጉዳት ቢደርስ በማይክሮ ፊልም የተቀረጸው ለሚቀጥለው ትውልድ ሊተላለፍ ይችላል ። እንዲሁም ምርምር የሚያደርጉ ምሁራንም አሁንም ሆነ ለወደፊት እገዳሙ ድረስ በመጓዝ ሳይንገላቱ በማይክሮ ፊልሞች በመጠቀም የምርምር ተግባራቸውን በቀላሉ ሊያካሂዱ ይችላሉ ።

(2) <u>ግብጻዊው ቅዱስ ሚናስ</u>። የመርዩ ገዥ የነበረው ቅዱስ ሚናስ በዲዮቅልጥያኖስ በታወጀው የስደት ወቅት ለጣዖት አልሰግድም ፡



www.ethiopianorthodox.org

የክርስትና እምነቱን አልክድም በማለቱ በመሰየፍ በ303 ዓ·ም በሰማዕት ነት ዐረፈ ። የግብጽ ቤተ ክርስቲያንም ከታላላቆቹ ሰማዕታት እንደ አንዱ በመቍጠር በስሙ ቤተ ክርስቲያን አሳንጻለታለች ። ከእስክንድርያ ወጣ ብሎ የሚገኘው በስሙ የሚጠራው ገዳምም ከቅርብ ጊዜ በፊት እንደገና ተጠናክሮ ተግባሩን ያከናውናል ። በዚያን ዘመን ሸባዎችና በተለያዩ በሽታዎች የተለከፉ ሰዎች የቅዱስ ሚናስን መቃብር በመንካት ስለተፈ ወሱ ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በቅዱስ ሚናስ አማላጅነት ከአደረባቸው በሽታ ለመፈወስ ከተለያዩ ሀገሮች ብዙ ሰዎች ወደ ቅዱስ ሚናስ ገዳም ይሄዳሉ ። በቅዱስ ሚናስ መቃብር አጠገብ የፈለቀው ጠበል ከግብጽ ውስጥና ውጭ የሄዱ ብዙ ሕሙማንን መፈወሱ ይነገራል ።

(3) <u>የልዳው ቅዱስ ጊዮርጊስ</u>። በክርስቲያኑ ዓለም ታዋቂና ተወዳጅ የሆነው ቅዱስ ጊዮርጊስ ዲዮቅልጥያኖስ በክርስቲያኖች ላይ ያወጀውን ሕገወጥ ትእዛዝ ባለመቀበሉና በክርስትና እምነቱ በመጽናቱ ከግብጽ ውጭ ፍልስጥኤም በምትገኘው ልዳ ውስጥ በሰማዕትነት ዐረፈ ።

የአውሮጳ መንግሥታት ተባብረው ኢየሩሳሌምን ከእስላሞች ነጻ ለማውጣት ጦርነት ባካሄዱበት በመጀመሪያው የመስቀል ጦርነት ወቅት በ1098 ዓ·ም የመስቀል ጦረኞች ከእስላሞች ጋር አንጾኪያ ውስጥ በኃይል ይዋጉ በነበረበት ወቅት ቅዱስ ጊዮርጊስ ከጐናቸው ሆኖ ሲዋጋ ያዩት መሆናቸውን ይተርካሉ ። አባቶቻችን ኢትዮጵያውያን ከፋሽስት ኢጣ ሊያ ጋር አድዋ ሲዋጉ ቅዱስ ጊዮርጊስ በነጭ ፈረስ ተቀምጦ ከኢትዮጵያ ውያን ጐን በመሰለፍ ጣሊያኖችን የወጋ መሆኑ ይተረካል ። የቅዱስ ጊዮርጊስን ሰማዕትነት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተቀብለው በስሙ አብያተ ክርስቲያናት በማነጽ ቢያከብሩትም ቅሉ ፣ በተለይ የእንግሊዝና የአየርላንድ ሕዝብና መንግሥት "የሀገራችን ጠባቂ ነው" በማለት ከፍ ባለ ስሜትና ፍቅር ያከብሩታል ።

(4) <u>ዶሚአናና ጓደኞቿ</u> ። ስለ ክርስትና እምነታቸው ሰማዕትነት የተቀበሉ ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ፣ ብዙ ሴቶችም በሰማዕትነት ዐርፈዋል ። ከነሱም የጥቂቶቹ ገድል (ታሪክ) የሚከተለው ነው ።

ግብጽ የአልቦርሎስ ክፍለ ሀገር ገዥ የነበረው የሞርኮስ ብቸኛ ልጅ ግብጻዊቲቱ ልጃገረድ ዶሚአና በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ መሠረት አባቷ የክርስትና እምነቱን ክዶ ለጣዖት መስገዱንና መሥዋዕት ማቅረቡን



www.ethiopianorthodox.org

ስትሰማ በጣም አዘነች ። በማዘን ብቻ ሳትወሰን እያለቀሰች አባቷን ለዚህ ለኃላፊው ምድራዊ ሹመትና ክብር ብለህ ዘለዓለማዊውን ሕይወትና የእግዚአብሔርን ልጅነት ከማጣት ይልቅ ለሠራኸው ኃጢአት ንስሐ ገብተህ የሰማዕትነት አክሊል ብትቀበል ይሻላል ብላ መከረችው ። እሱም ምክሯን በጽሞና አዳምጦ በመቀበል ሕዝብ በብዛት ወደተሰበሰበበት አደባባይ ሄዶ በቀደመ ስሕተቱ የተጸጸተና በክርስትና እምነቱ የጸና መሆኑን ገለጸ ። ንጉሡም ይህንን ሲሰማ ተናዶ ወዲያው እንዲሰየፍ ስላዘዘ በሰማዕትነት ዐረፈ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሞርኮስ ወደ ክርስትና እምነቱ የተመለሰ በልጁ በዶሚአና ምክር መሆኑን ንጉሡ እንደሰማ ዶሚአና ተይዛ ለጣዖት ካልሰገደች እንደ አባቷ እንድትገደል አዘዘ ። የተላኩትም ወታደሮች እሷን ሲይዙ ፣ አብረዋት የነበሩትን አርባ ደናግል (ልጃገረዶች) ጓደኞቿን ስለ ክርስትና እምነታቸው ሰማዕትነት ለመቀበል ፈቃደኞች የሆኑ አብረዋት ስለ እምነታቸው እንዲመሰክሩ ጠየቀቻቸው ። እነሱም በአንድ ድምጽ (ሁሉም) በምንም ምክንያት እምነታችንን አንክድም አሏት ። በዚህ አኳኋን ሁሉም ለጣዖት ዕጣን አናጤስም ፣ አንሰግድም ስላሉ በመሰየፍ ከዶሚአና ጋር በሰማዕትነት ዐረፉ ።

ንግሥት እሌኒ ኢየሩሳሌም ደርሳ (ተሳልማ) በግብጽ በኩል ወደ ቍስጥንጥንያ ስትመለስ አርባ አንዱም ደናግል በተቀበሩበት ቦታ ላይ በዶሚአና ስም የሚጠራ ቤተ ክርስቲያን አሳንጻለች ። አሁንም ብዙ ክርስቲያኖች ግብጽ ውስጥ በስሟ ወደታነጸው ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ ይሳለማሉ ። የዓመት በዓሏንም በግንቦት ወር በደመቀ ሁኔታ ያከብራሉ ።

(5) <u>ዐሥራ ሰባተኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ አቡነ ጴጥሮስ።</u>

አቡነ ጴጥሮስ በዲዮቅልጥያኖስ ባለሟሎች የክርስትና እምነቱን ክዶ ለጣዖት እንዲሠዋና እንዲሰግድ ቢጠየቅ ፣ ስንኳን እራሱ ሊሠዋና ሊሰግድ ይቅርና ምእመናን ሁሉ ከቀጥተኛው የክርስትና እምነታቸው ዝንፍ እንዳይሉ በመንፈሳዊ አባትነቱ በትጋት ስላስተማረ አንገቱን በሰይፍ ተቈርጦ በሰማዕትነት ዐረፈ ። እሱም በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ በተነሣው እጅግ አሰቃቂ በነበረው ስደት የመጨረሻው ሰማዕት ስለሆነ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን "ተፍጻሜ ሰማዕት" ብላ የቅዱስነት ማዕርግ ሰጥታዋለች ።

ለእነዚህና እነዚህን ለመሳሰሉት በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ በየጊዜው ለክርስቲያኖች መልካም ጠባቂና አርአያ በመሆን በግምባር



www.ethiopianorthodox.org

ቀደምትነት ሰማዕትነት ከተቀበሉት ለጥቂቶቹ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የቅዱስነት ማዕርግ ሰጥታ በስማቸው አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት አሳንጻ በዓላቸውን በተለያዩ ቀናት ታከብራለች ።

ባጠቃላይ በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ በክርስቲያኖች ላይ በተነሣው አስከፊና አሰቃቂ የስደት ወቅት ላለቁት ሰማዕታት ሁሉ መታሰቢያ እንዲሆን በማሰብ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ዓመተ ምሕረትን ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ በመቊጠር ፈንታ ዲዮቅልጥያኖስ የሮም ንጉሠ ነገሥት ከሆነበት ከ284 ዓ·ም ጀምሮ ዓመተ ምሕረቷ እንዲቈጠር ወስናለች ። ይኸውም ጊዜ "ዘመነ ሰማዕታት" ተብሎ ተሰይሟል ።

ዲዮቅልጥያኖስና መሰሎቹ የአሕዛብ ነገሥታት ክርስትናን ለመደ ምሰስ በክርስቲያኖች ላይ ያወረዱት ስፍር ቊጥር የሌለው እልቂት ግቡን ሳይመታላቸው ከንቱ ድካም ሆኖ ቀረ ። በሌላው ወገን ግን የዘመነ ብሉይ አባቶች በእምነታቸው በመጽናት ፣ በታላቅ ተጋድሎ ከፍ ያለ መሥዋዕት ነት በመክፈል ታላላቅ ሥራዎችን እንደፈጸሙ ሁሉ (ዕብ· 11፥32–40) ፣ በዘመነ ሐዲስም በእግዚአብሔር መንፈስ በሚመሩና ፍጹም እምነት በነበራቸው የወንጌል መልእክተኞች የተሰበከችው ክርስትና አስደናቂ በሆነና በተፋጠነ ሁኔታ በየሀገሩ በመሰራጨት ብዙ አማኞችን አፈራች ። እንዲሁም የስደቱ ዘመን እንደተፈጸመ ክርስትና በታላቁ ቈስጠንጢኖስ ነጻነቷን ከተጎናጸፈች በኋላ አሕዛብን ማስተማር ብቻ ሳይሆን ማሳደድና መፍጀት ፣ እንደ ሰራፒስ የመሳሰሉ አብያተ ጣዖታትን ማፍረስና አንዳንዶችንም ወደ አብያተ ክርስቲያናትነት መለወጥ ጀመረች ። ዝነኛዋ የአሕዛብ የኒዎ ፕላቶን የፍልስፍና መምህር ሂፓትያ የተባለች ዪቱ እስክንድርያ ውስጥ በነበረው ሙሲዬም በተባለው የአሕዛብ የትምህርት ማዕከልና ቤተ መጻሕፍት አስተምራ ስትመለስ በ415 ዓ·ም መነኰሳትና ምዕመናን በድንጋይ ቀጥቅጠው ገደሏት ። ቈየት ብሎ ደግሞ በተለይም ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ አንዱ የክርስቲያን ወገን ሌላውን የክርስቲያን ወገን ማሳደድ ጀመረ ። ይህም በክርስቲያኖች መካከል የተጀመረው አስከፊ ፍጅት ለረጅም ዘመናት ቀጠለ ።

## መ) የእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ያፈራቻቸው መንፈሳውያን አባቶችና መምህራን

ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ እስክንድርያ ውስጥ ሙሲዬም



www.ethiopianorthodox.org

የተባለው ከፍተኛ የግሪክ (የአሕዛብ) ትምህርት ቤትና የአይሁድም ት/ቤቶች ስለነበሩ ይህችው ከተማ የአሕዛብና የአይሁድ ሊቃውንት (ፈላስፎች) መፍለቂያ ፣ መናሃሪያና የዕውቀት (የትምህርት) ማዕከል ነበረች ።

እስክንድርያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩት አይሁድ ቋንቋቸውን (ዕብራይስጥን) ስለረሱ ዳግማዊ ፕቶሎሚ (በጥሊሞስ) የተባለው የግብጽ ንጉሥ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ3ኛው መቶ ዘመን በሰባ የአይሁድ ሊቃውንት ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ በዚያን ጊዜ የዓለም ቋንቋ ወደ ነበረው ወደ ጽርዕ(ግሪክኛ) አስተረጐመላቸው ። ይኸውም የብሉይ ኪዳን ትርጒም ሴፕቱዋጀንት ይባላል ።

በዘመነ ክርስትናም የእስክንድርያ መንፈሳዊ ት/ቤት በቅዱስ ማርቆስ ተመሥርታ ከአይሁድና ከአሕዛብ ወገን ክርስትናን ለተቀበሉ መሃይምናንና በዓለማዊው ትምህርት ከፍተኛ ዕውቀት የነበራቸው ሰዎች(ንኡሰ ክርስቲያን) የክርስትናን መሠረተ እምነት በሚገባ ተረድ ተው እንዲጠመቁ የሚረዳ የሰንበት ትምህርት መስጫ(ማስተማሪያ) ሆና ቈየች ። በሁለተኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ላይ ግን በፓንጼኖስና በጓደኞቹ ተጠናክራ በመቋቋሟ በክርስቲያኑ ዓለም ከፍ ያለ ዝናን አትርፋ ነበር ። ይህቺው ትምህርት ቤት መንፈሳዊ ትምህርትን በከፍተኛ ደረጃ በማቅረብ የወንጌልን ትምህርት በዓለም ያሰራጩ ዝነኛ ሊቃውንትንና የቤተ ክርስቲያን አባቶችን በማፍራት ፣ ብዙ ምእመናንንም በማስተማር ለክርስትና መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጋለች። ስለዚህ ከአሕዛብና ከአይሁድ ወገን ክርስትናን ከተቀበሉት መካከል ከፊሎቹ በዕውቀት የበሰሉ ምሁራን ስለነበሩ የነሱን መንፈሳዊ ትምህርት ፍላጎት ለማርካት ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና የወንጌል መልእክተኞችን በከፍተኛ ደረጃ ለማሠልጠን በማቀድ የትምህርት አሰጣጡ ደረጃ ከፍ ከፍ እያለ በመሄዱ በክርስቲያኑ ዓለም መጀመሪያዋ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ለመሆን በቃች ። ሆኖም በዘመኑ ለንኡሰ ክርስቲያን የመሠረተ ሃይማኖት ትምህርት መስጫ የሆኑ ትምህርት ቤቶች ክርስትና በተሰበከችባቸው ሀገሮች ተከፍተው ነበር ። ነገር ግን ለወደፊት በሶርያ(በያዕቆባዊት) አርቶዶርስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ሰፋ አድርገን እንደምንመለከተው በከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት አሰጣጥ የእስክንድርያን ትምህርት



www.ethiopianorthodox.org

ቤት ልትወዳደር የቻለችው የቅዱሳት መጻሕፍትን የአንድምታ ትርጓሜ በመቃወም የነጠላ(የቃል በቃል) ትርጕምን የምትከተለው የአንጾኪያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ብቻ ነበረች ።

የእስክንድርያ ትምህርት ቤት ዋነኛ ዓላማዋ ከነበረው ከመንፈሳዊው ትምህርት በተጨማሪ እንደ ሎጂክስ ፣ ፊሎዞፊ ፣ ሪቶሪክ ፣ ታሪክ ፣ ሳይንስ ፣ አስትሮኖሚ ፣ ሒሳብ የመሳሰሉ ዓለማዊ ትምህርቶችንም ትሰጥ(ታስተምር) ነበር ። ምሥጢራቸው የረቀቁ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርቶች ፍች ለመረዳት የእስክንድርያ ትምህርት ቤት የቅዱሳት መጻሕፍት የነጠላ ትርጕም ከበስተጀርባው ምሥጢራዊ ፍች አለው በማለት አንድምታ(አሊጎሪክ ፣ ቲፖሎጂ) በተባለው የአተረጓጐም መንገድ(ስልት) ትጠቀም ነበር ። የአሊጎሪክ ትርጓሜ ስልት የተጀመረው በግሪክ ፈላስፎች ነበር ይባላል ።

ከአይሁድም ሊቃውንት መካከል ፊሊኦ ዘእስክንድርያና መሰሎቹ ብሉይ ኪዳንን በአሊጎሪክ መንገድ ተርጕመዋል ። ከክርስቲያኖችም ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያና የመሳሰሉት ቅዱሳት መጻሕፍትን በአሊጎሪክ ስልት ተርጕመዋል ። ሐዋርያው ጳውሎስም በመልእክታቱ አንዳንድ ቦታዎች ውስጥ በአሊጎሪክ አተረጓጐም ተጠቅሟል(ገላ·4፡24 ፤ 1 ቆሮ·9፡9)።

የእስክንድርያ ትምህርት ቤት ለክርስቲያኑ ዓለም እስከ አምስተኛው መቶ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ድረስ መንፈሳዊ ትምህርትን በስፋትና በጥልቀት ስትሰጥ ከቈየች በኋላ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ለመጀመሪያ ጊዜ በእምነት ምክንያት ለሁለት ከተከፈሉበት ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ እየተዳከመች ሄደች ። እንድትዳከምና እንድትጠፋ ያደረጉአትም ያን ጊዜ ግብጽን በቅኝ ገዥነት ያስተዳድሩ የነበሩት የሁለት ባሕርይ እምነት ተከታዮች የቢዛንታይን(የቊስጥንጥንያ) ነገሥታት ናቸው ። እነሱም የተዋሕዶ እምነት ተከታይ የነበሩ ኮፕቶችን ከማሳደድና ከመጨፍጨፍ ተግባራቸው በተጨማሪ ትምህርት ቤቷን ዘግተው በውስጧ የነበሩትን መጻሕፍት ዘርፈው ወደ ቊስጥንጥንያ ወሰዱ ። የኮፕት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ከዘረፋ የተረፉትን መጻሕፍት ሰብስበው ትምህርት ቤቷን ዋዲኤል ናትሩም በሚባለው በረሓማ ቦታ ወደሚገኘው የቅዱስ መቃርስ ገዳም በማዛወር መጠነኛ ትምህርት



www.ethiopianorthodox.org

እንድትሰጥ አድርገው ነበር ። ሆኖም እስከ ሰባተኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ውሱን በሆነ ሁኔታ መንፈሳዊ ትምህርትን ስትሰጥ ቈይታ በገዳሙ አካባቢ ከነበሩ ዘላኖች በመነኰሳቱ ላይ ይሰነዘር በነበረው ዝርፊያና ግድያ ምክንያት ቀስ በቀስ ደብዛዋ ጠፋ ።

እላይ እንደተመለከትነው እስክንድርያ ውስጥ ትምህርት ቤቷ ከተዘጋችበት ከአምስተኛው እስከ ዐሥራ ዘጠንኛው መቶ ዘመን ድረስ የግብጽ ካህናት መንፈሳዊ ዕውቀት ተዳክሞ ከቈየ(ከኖረ) በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድና እርዳታ በእስክንድርያው ፓትርያርክ በአቡነ ቄርሎስ አምስተኛ በ1893 ዓ·ም ትምህርት ቤቷ እንደገና በተጠናከረ ሁኔታ በመንፈሳዊ ኮሌጅ ደረጃ ካይሮ ውስጥ ተከፍታ ካህናትንና መምህራንን በማስተማርና በማሠልጠን ላይ ትገኛለች ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ይህች ትምህርት ቤት ከመዘጋቷ በፊት በመንፈሳዊ ትምህርት ካፈራቻቸው አያሌ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና መምህራን መካከል ቅዱስ አትናቴዎስ ፥ የእስክንድርያው ቀሌምንጦስና ቄርሎስ ፥ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ፥ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ወዘተ· ይገኙባቸዋል ።

ከመጀመሪያው የትምህርት ቤቷ መሥራች ከወንጌላዊው ማርቆስ ቀጥሎ አቴናጎራስ ፥ ጁስቱስ ፥ ኤውማኒኦስ ፥ ማርያኑስ ፥ ፓንጼኖስ ፥ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ፥ መናፍቁ አርጌንስ ፥ ቴዎግኖስቱስ ፥ ፒኤሪዮስ ፥ ዐይነ ስውሩ ዲዲሞስ ፥ ጴጥሮስ ወዘተ· በተከታታይ የትምህርት ቤቷ መሪና አስተማሪ በመሆን በትጋት አገልግለዋል ። ከነሱም መካከል ፓንጼኖስና ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ትምህርት ቤቷን ከመምራት ተግባራቸው በተጨማሪ በኅብረት ሂኤሮግሊፊክ የተባለውን ጥንታዊውን የግብጽ ሥዕል መሳይ ፊደል የተካ አዲስ ፊደል አዘጋጁ ። ይኸውም ሃያ ሁለት በሚሆኑ በግሪክ ፊደል በመጠቀም የሀገሬው ተወላጅ ሕዝብ የሚጠቀምበት ለጽሕፈትና ለንባብ የቀናና አመች የሆነ አዲስ የቅብጥ ቋንቋ ፊደል በማዘጋጀት ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ምትክ ያልተገኘላቸውን ሰባት ድምጽ ሰጭ የሆኑ የራሳቸውን ጥንታውያን ፊደላትም ከሃያ ሁለቱ የግሪክ ፊደላት ጋር ጨምረው አስገብተዋል ። እንዲሁም ብሉይና ሐዲስ ኪዳንን ካህናትና ምእመናን አንበው በቀላሉ ለመረዳት እንዲችሉ በማሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቅብጥ የተረጐሙ እነሱ ናቸው ። የቅብጥ ቋንቋ የተለያዩ ዲያሌክቶች(የ



www.ethiopianorthodox.org

ጎሣ ቋንቋዎች) አሉት ። ከእነሱም ዋናዎቹ ቦሔሪክ የተባለው የታሕታይ ግብጽ ዲያሌክትና ሳሂዲክ የተባለው የላዕላይ ግብጽ ዲያሌክት ናቸው ። መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጐመውም በነዚሁ በሁለቱ ዲያሌክቶች ነው ።

ግብጾች ለብዙ ዘመናት በቅብጥ ቋንቋ ሲነጋገሩ ፤ ሲጽፉና የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን ሲፈጽሙ ከኖሩ በኋላ ሀገራቸው በዐረቦች እጅ ስለወደቀች ከ706 ዓ.ም ጀምሮ ማንኛውም ዜጋ በዓረብኛ እንዲነጋገርና እንዲጽፍ ፤ የመንግሥት ሥራዎችም በዓረብኛ ብቻ እንዲከናወኑ ተደረገ።

ስለዚህ ቅብጥ ቀስ በቀስ እየተዳከመ በመሄዱ ከዐሥራ ሦስተኛው መቶ ዘመን ጀምሮ የሥርዓተ ቅዳሴ መፈጸሚያ ብቻ ሆኖ ቀረ ። ሕዝቡም በስፋት በዓረብኛ መናገር ፣ መማርና መጻፍ ስለጀመረ ከጊዜ በኋላ የቅብጥ ቋንቋ እየተረሳ ሄደ ። አሁንም በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ የሚፈጸመው ቦሔሪክ በተባለው የቅብጥ ዲያሌክት ነው ። ሆኖም የቤተ ክርስቲያኒቱን መገልገያ መጻሕፍት ይዘትና ፍች ምእመናን በቀላሉ ለመረዳት እንዲችሉ በማሰብ አብዛኛዎቹ በቅብጥና በዓረብኛ ጎን ለጎን ተጽፈው የተዘጋጁ ናቸው ። የሥርዓተ ቅዳሴው አፈጻጸምም በገዳማት ወደ ሦስት ሰዓት ያህል ሲፈጅ ፤ በከተማና በገጠር በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ግን የሚፈጀው አጠር ያለ ጊዜ ነው ።

## ሠ) የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ከሀገሯ ውጭ ክርስትናን ለማስፋፋት ያደረገችው የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ

ከታሪክ እንደምንመለከተው ክርስትና በጌታና በሐዋርያት ከተሰበከችበት ጊዜ ጀምሮ የወንጌል መልእክተኞች (ሐዋርያት) በመላ ዓለም በአደረጉትና አሁንም በሚያደርጉት ስብከት እየተስፋፋች የመጣች ሃይማኖት ናት ።

በወንጌላዊው ማርቆስ ስብከት ክርስትናን የተቀበሉ ኮፕቶችም ወዲያው በተራቸው (በበኩላቸው) የወንጌል መልእክተኞችን በመላክ ከግብጽ ውጭ ከሚኖረው ከሌላው ሀገር ሕዝብ ጥቂቱን በትጋት አስተምረው ወደ ክርስቶስ መልሰዋል ።

በሜዲትራንያን ባሕር ዳር የምትገኘው እስክንድርያ የጥንታዊው ዓለም ሕዝብ ማለት የአሕዛብና የአይሁድ መናሃሪያና መተላለፊያ የንግድ ማዕከል ስለነበረች የተለያዩ ሀገር ነጋዴዎች ይጐበኟት ነበር ። ቀደም



www.ethiopianorthodox.org

ሲል እንደተመለከትነው ከፍተኛ መንፈሳዊና ዓለማዊ ትምህርት ለመቅሰም ከተለያዩ ሀገሮች የሄዱ ደቀ መዛሙርትም እስክንድርያ ውስጥ በነበረችው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ተምረዋል ። እላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ሕዝብ ጋር ግንኙነት በማድረግ የወንጌል መልእክተኞቿን ወደተለያዩ ሀገሮች በመላክ ክርስትናን አስተምራለች ። ክርስትናን ከሰበከችባቸውም ሀገሮች አብዛኞቹ የሚከተሉት ናቸው ።

1) <u>ቀሬና (ፔንጳፖሊስ ፡ ሊብያ)</u> ።

በሐዋርያት ሥራ 2፡10 የቀሬና ተወላጅ የነበሩ አይሁድ የፋሲካን በዓል ለማክበር በመሄዳቸው ለጰንጠቆስጤ ዕለት ጴጥሮስ ሲያስተምር ኢየሩሳሌም እንደነበሩ ተገልጿል ። ሆኖም የክርስትና ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ የሮም ቅኝ ግዛት በነበረችው ቀሬና ውስጥ በይፋ የተሰበከችው በቅዱስ ማርቆስና በረዳቶቹ ግብጻውያን የወንጌል መልእክተኞች መሆኑ ይነገራል ። የቀሬናው ተወላጅ ሲኔሲዩስም (370 – 414) በእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በእስክንድርያ ፓትርያርክ በቴዎፍሎስ በ410 ዓ.ም የቀሬና ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ በመሾም በሀገሪቱ ክርስትናን አስፋፍቷል ። በ325 ዓ.ም በተደረገችው በመጀመሪያዋ የኒቅያ ጉባኤ ለመካፈል የተሰበሰቡት አባቶችም የቀሬና ሀገረ ስብከት በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሥር እንዲሆን ወስነዋል ። ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ታሪክና ውሳኔ የምንገነዘበው ከሰሜን አፍሪካ ሀገሮች ቀሬና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ስብከት ክርስትናን ስትቀበል ፣ እነ ጠርጥልያኖስን ፣ ቢፕሪያኖስንና አውግስጢኖስን ያፈራች ካርቴጅ (ሰሜን አፍሪካ) ግን ክርስትናን የተቀበለችው በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ስብከት መሆኑን ነው ። በ16ኛው መቶ ዘመን ቱርኮች ቀሬናን ከዓረቦች በጦር ኃይል ነጥቀው ይዘው እዚያ ይኖሩ ከነበሩ ኮፕቶች እስልምናን ያልተቀበሉትን ሁሉ እስከፈጇአቸው ድረስ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳትን እየሾመች ትልክ ነበር ። ሆኖም ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ትሪፖሊና ቤንጋዚ ውስጥ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ከፍታ እዚያ ለሚኖሩ ጥቂት ምእመናኖቿ መንፈሳዊ አገልግሎትን ታበረክታለች ።



www.ethiopianorthodox.org

2) <u>ኑብያ (ሱዳን) ።</u>

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በግብጽ ደቡባዊ ወሰን በኩል በምትገኘው በኑብያ የክርስትናን ትምህርት በማስተማር ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ መልሳለች ። ወደ ኑብያ ከተላኩትም አንዱና ከ551 ዓ.ም ጀምሮ በትጋቱ ያስተማረው አባ ዩልያኖስ ነበር ። እንዲሁም ከወንጌል መልእክተኞች ከፊሎቹ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ላይ በየጊዜው ከተነሡት ስደቶች እየሸሹ ኑብያ የገቡ ኮፕቶች እንደነበሩ ይተረካል ። በአባ እንጦንስ የተመሠረተውም የብሕትውና ኑሮ በአምስተኛው መቶ ዘመን ወደ ኑብያ ተዛምቶ ስለደረሰ ገዳማት ተመሥርተው ነበር።

የቢዛንታይን ንጉሥ ቀዳማዊ ዩስጢንያኖስም (527–565) በሥሩ በሚተዳደሩ የቅኝ ግዛቶች ውስጥ የሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ክርስትናን እንዲቀበሉ ያወጀው ትእዛዝ ኑብያም ውስጥ ከአሕዛብ ወገን ብዙዎቹ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረውን የክርስትና እምነት እንዲቀበሉ ረድቷል ። በኬልቄዶን ጉባኤ ከተደረገው መለያየት በኋላ በቍስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያንና በንጉሡ የሚደገፉት የሁለት ባሕርይን እምነት ተቀብለው እስክንድርያ የሚኖሩት መለካውያን (የቢዛንታይን ንጉሥ ታማኝ ደጋፊዎች) የተባሉት ክርስቲያኖች በኮፕት ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ተጽእኖ ያደርጉ ነበር ። ሆኖም የተዋሕዶን እምነት ተከታዮች በኀቡዕ ትደግፍ በነበረችው በእቴጌ ቴዎዶራ እርዳታና ድጋፍ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በኑብያ ለሚኖሩ የተዋሕዶ እምነት ተከታይ ክርስቲያኖች በ559 ዓ.ም ለዋናዋ ከተማ ለናፓታ ሎንጊኑስ ለተባለው ካህን የጵጵስና ማዕርግ በመስጠት ሾማለች ። እሱም ረዳቶቹ ከነበሩት ካህናት ጋር ኑብያ ውስጥ ክርስትናን በትጋት አስተምሯል ። ቀስ በቀስም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ታነጹ ፤ ገዳማትም ተመሠረቱ ፤ ከነዚህም አንዱ ታላቁ የቅዱስ ስምዖን ገዳም ነበር ። በዚህ አኳኋን የኑብያ ሕዝብ ክርስትናን ተቀብሎ ሲኖር ግብጽን ከወረሩአት የቱርክ እስላሞች ጋር እየተዋጋ ነጻነቱንና እምነቱን ጠብቆ ከቈየ በኋላ ሳላዲን በላከው የግብጽ ጦር በዐሥራ ሦስተኛው መቶ ዘመን ሰሜናዊው የሀገሪቱ ክፍል በእስላሞች እጅ ወደቀ ። የቀረው ክፍለ ሀገር ሕዝብ ግን በጀግንነት ሲከላከል ከቈየ በኋላ በዐሥራ አምስተኛው መቶ ዘመን በመሸነፋቸው የፖለቲካና የሃይማኖት ነጻነታቸውን ተገፈፉ ። ሆኖም ከቱርክ መንግሥት በክርስቲያኖች ላይ በወረደው ሥቃይና ጭፍጨፋ ምክንያት



www.ethiopianorthodox.org

ክርስትና ከምድረ ኑብያ ለጊዜው የጠፋች ብትመስልም አንድያውን እንደ ሊብያ ክርስቲያኖች አልተደመሰሰችም ። ለዚሁም ማስረጃ በዘመናችን የኮፕት ፡ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በሱዳን (በደቡብ ሱዳን) ውስጥ አብያተ ክርስቲያናትን መሥርተው ወንጌልን በስፋት በመስበክ ላይ ናቸው ።

3) ኢትዮጵያ ።

በታሪክ እንደምንመለከተው ዋና መናገሻ ከተማው አክሱም የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከክርስቶስ ልደት በፊት ሕገ ኦሪትን ተቀብሎ ሲኖር ፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ35 ዓ.ም ደግሞ ከፊልጶስ በተማረው የሕንደኬ ጃንደረባና (በጅሮንድና) በወንጌላዊው ማቴዎስ አማካይነት የክርስትናን ዜና ሰምቷል (የሐዋ.8፡26–40)። ሆኖም ከ35–330 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኦሪት እምነቱ ጋር ስለ ክርስትና ሰምቶና ጥምቀትን ተቀብሎ ከቈየ በኋላ የክርስትና እምነት በይፋና በስፋት ሊሰበክ የተቻለው በ330 ዓ.ም የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ ለፍሬምናጦስ (ለሰላማ ፡ ለከሣቴ ብርሃን) ማዕርገ ጵጵስና ሰጥቶ ወደኢትዮጵያ ከላከው በኋላ ነው ። በስብከትና አብያተ ክርስቲያናትን በመመሥረት የሚረዱት ግብጻውያን ካህናትም ከአቡነ ሰላማ ጋር አብሮ እንደላከ ይታመናል ።

ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞቿን ልካ በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ ባትካፈልም ፡ በቅዱስ ዲዮስቆሮስ የተወከለችው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበለውን ቀጥተኛውን የተዋሕዶ እምነት ተቀብላ በተግባር ላይ አውላለች ።

4) እስያ ።

የሮሙ ፖፕ ጎርጎርዮስ ዐሥራ ሦስተኛ በ1582 ዓ.ም የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን የምትከተለውን የቀን አቈጣጠር (መቍጠሪያ) ከማውጣቱ በፊት ፡ በኒቅያ ጉባኤ ጸድቆ መላ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ይጠቀሙበት የነበረውንና ዛሬም (አሁንም) የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት የሚጠቀሙበትን እንደ ፋሲካ ያሉትን በዓላት ለመወሰን የሚያስችል የቀን መቍጠሪያ የቀመረው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ቀዳማዊ ዲሜጥ



www.ethiopianorthodox.org

ሮስ ፓንዴኖስ የተባለውን ምሁር በ180 ዓ.ም ወደ ሕንድ በወንጌል መልእክተኛነት ላከው ። እሱም ቀደም ሲል በሐዋርያው ቶማስ የተጀመረውን የክርስትና ትምህርት ደቡብ ሕንድ ውስጥ አስተምሯል ። እንዲሁም የማቴዎስን ወንጌል ቅጅ አግኝቶ ይዞ መመለሱ ይነገራል ። የተላከበትን የሐዋርያነት ተግባር ፈጽሞ ሲመለስ እግረ መንገዱን ዓረቢያ ፌሊክስ (ሰሜን የመን) አርፎ ክርስትናን መስበኩ ይነገራል ።

በስድስተኛው መቶ ዘመን ወደ ሕንድ የተጓዘው ኮዝማስ ኢንዲኮፕ ሌውስቱስ የተባለው እስክንድርያዊ የጅኦግራፊ ምሁርና ነጋዴ ወደ ሕንድ በመርከብ በተጓዘበት ወቅት በፋርስ ባሕረ ሰላጤ ፣ በሶኮትራ ደሴቶች ወዘተ. ብዙ አብያተ ክርስቲያናትንና ምእመናንን የሚያገለግሉና የሚመሩ ጳጳሳት ማየቱን ገልጿል ። ሕንድም ውስጥ በሐዋርያው ቶማስ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑ ብዙ ክርስቲያኖችን ማየቱን ገልጿል ።

5) <u>አውሮጳ ።</u>

ምንም እንኳ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል መልእክተኞቿን በቀጥታ ልካ አውሮጳ ውስጥ ባታስተምርም ቅሉ ፣ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ በአርዮሳውያን ተጽእኖ በደረሰበት በሁለተኛው የስደቱ ወቅት ወደ ሮም ተሰዶ ከ339 እስከ 346 ዓ.ም ድረስ ከሮሙ ፖፕ ቀዳማዊ ጁልዮስ ዘንድ በእንግድነት በቈየበት ወቅት ፣ እንዲሁም ፈረንሳይ በምትገኝ ትሬቪን ከተባለች ከተማ በሰነበተበት ጊዜ በእነ አባ እንጦንስ ፣ አሞንዮስ ፣ መቃርስ ፣ ጳኵሚስ ወዘተ. ግብጽ ውስጥ የተመሠረተውን የብሕትውና (የምነና) ኑሮ ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አባላት አስረድቷል ። በዚሁ ትምህርት መሠረት በአውሮጳ የብሕትውና ኑሮ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሊስፋፋና ሥር ሊሰድ ቻለ ። ከአውሮጳ ወደ ግብጽ ሄደው የብሕትውናን ኑሮ ካጠኑና ከተለማመዱ በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ስለ ብሕትውና ኑሮና ሕግ ከጻፉትና ከመሠረቱት አንዱ ዮሐንስ ካሲያን (360–435) የተባለው መነኰሴ ነበር። እሱም ይህንኑ የብሕትውና ኑሮ የመሠረተ በትውልድ ሀገሩ በፈረንሳይ ውስጥ ማርሴይ አካባቢ ነበር ።

ከዲዮቅልጥያኖስ ረዳት ከንጉሥ መክስምያኖስ ሠራዊት ጋር በነርስነት ከሀገሯ ከግብጽ ወደ ስዊዘርላንድ የሄደችው (የዘመተችው)



www.ethiopianorthodox.org

ቬሬና በክርስቲያንነታቸው ምክንያት ብዙዎች ሲፈጁ ራሷን ከሞት ያተረፋትን አምላክ በማመስገን በቀሪው የሕይወት ዘመኗ እሱን ለማገል ገል ስለወሰነች ፡ መኖሪያዋን ጀኔቫ አካባቢ አድርጋ ሕዝቡን ስትረዳና ወንጌልን ስታስተምር ቄይታ ዙሪክ ከተማ ውስጥ ዐረፈች ። በተቀበረች በት ቦታ ላይም በስሟ ቤተ ክርስቲያን ታንጾላታል ። በእሷ የተረዱና ክርስትናን የተማሩ ሰዎች ዝርያዎች እስከ ዛሬ ድረስ ያከብሯታል ።

## ረ) የመነኰሳት ሕይወትና የገዳማት ሥርዓት

ምንም እንኳን የምንና ኑሮ ከክርስቶስ ልደት በፊት በተለያዩ እምነት ተከታዮች የተጀመረ ቢሆንም በክርስትና ትምህርት መሠረትነት የሚካሄደው የብሕትውና (የምነና) ኑሮ የተጀመረው (የተመሠረተው) በግብጻዊው በአባ እንጦንስ ነው ። ይኸው ግብጽ ውስጥ በአባ እንጦንስ የተጀመረው የብሕትውና ኑሮ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ለመላው የክርስቲያኑ ዓለም ያበረከተችው መንፈሳዊ ሥጦታ (በረከት) ነው ። የብሕትውና ኑሮ እንደማንኛውም ንቅናቄ ሁሉ በግብጽ በረሓዎችና ከግብጽም ውጭ ባሉ ሀገሮች እየተስፋፋ የሄደው ቀስ በቀስ ነው ።

የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ በጻፈው በአባ እንጦንስ የሕይወት ታሪክ መሠረት መጀመሪያው የምንኵስና መሥራ ችና አባት ቅዱስ እንጦንስ (251–356) ነው ። ምንም እንኳን የብሕትውና ኑሮ የተመሠረተው በአባ እንጦንስ ቢሆንም ትንሽ ቀደም ብሎ በንጉሥ ዳክዮስ ትእዛዝ በክርስቲያኖች ላይ በታወጀው ስደት ምክንያት ግብጻ ዊው መናኝ አባ ጳውሊና (ጳውሎስና) መሰሎቹ ዓለም በቃን በማለት በየጊዜው ወደ ግብጽ በረሓዎች እየተሰደዱ ከሰው ሳይገናኙ በተለያዩ ዋሻዎች ይኖሩ ነበር ። አባ እንጦንስ ምነና በጀመረበት ወቅት ግብጽ በረሓ ውስጥ ከአባ ጳውሊ ጋር ከተገናኙ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አባ ጳውሊ ማረፉ ይነገራል ።

የአባ እንጦንስ ዓላማ ከሰው ርቆ መንኵሶ በብሕትውና ለመኖር ቢሆንም ቅሉ ፥ ብዙ ታምራትን ስለሠራ አብዛኛው ሕዝብ እሱን አይቶ ለማድነቅና ከአደረበት በሽታ በእሱ ጸሎት ለመፈወስ ፤ ጥቂቱ ደግሞ በእሱ አካባቢ በብሕትውና ለመኖር በመሻት ወደነበረበት ቦታ ተከትለ ውት ስለሄዱ ከነአባ ጳውሊ የብቸኝነት ምነና ኑሮ የተለየና ለክርስቲያኑ


www.ethiopianorthodox.org

ዓለም ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደረገ ነው ። ሆኖም ከሰው ርቆ (ተገልሎ) ለብቻ ወደ አምላኩ እየጸለየ በምናኔ በመኖር የራሱንና የሰው ልጆችን ሁሉ ድኅነት ለማግኘት የመሠረተውን የብሕትውና ኑሮ ራሱ በተግባር የገለጸው የአባ እንጦንስ ታሪክ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው ።

አባ እንጦንስ ግብጽ ውስጥ በምትገኝ ቆማ በተባለች መንደር ውስጥ ደጋግ ከነበሩ ሀብታም ቤተ ሰቦች በ251 ዓ·ም ተወለደ ። ከወላጆቹም ዕረፍት በኋላ ዕድሜው 20 ዓመት ሲሆን አንድ ቀን እቤተ ክርስቲያን ለአምልኮ ሄዶ ሳለ በማቴዎስ 19፡21 የተጻፈው ሲነበብ ሰምቶ ልቡ ስለተነካና የንባቡ መልእክትም የወደፊት ሕይወቱን የሚመለከት ሆኖ ስላገኘው ወዲያው የነበረውን ሀብት ሸጦ ለድኾች ከመጸወተ በኋላ ዓለም በቃኝ ብሎ መነነ ። በግብጽ በረሓ በብሕትውና ተወስኖ ለሰማንያ አምስት ዓመታት በጾም ፣ በጸሎት ፣ አጋንንትን በመዋጋትና የተለያዩ ታምራትን በመፈጸም ፣ የእጅ ሥራዎችን በመሥራት ወዘተ· አምላኩን እያገለገለ ኖረ ። የሕይወት ታሪኩን የጻፈለት የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስም አባ እንጦንስ ወደነበረበት ገዳም ሄዶ ለተወሰነ ጊዜ አብሮት በመቈየት ሥርዓተ ምንኵስናን ተምሯል ። ታላቁ ቈስጠንጢኖስም በጸሎቱ እንዲያስበው ለአባ እንጦንስ የልመና ደብዳቤ መላኩ ይነገራል ።

አባ እንጦንስ የምነና ኑሮውን ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ዐረፈበት ጊዜ ድረስ በነበረው ወቅት ከሚኖርበት ዋሻ (ቦታ) ሁለት ጊዜ ወጥቶ ከምእመናን ጋር ለጥቂት ጊዜ እየቈየ ወደ በአቱ ተመልሷል ። ይኸውም መጀመሪያ የወጣው በንጉሥ መክስምያኖስ ትእዛዝ ስደትና ሥቃይ የደረሰባቸውን ክርስቲያኖች ለማጽናናት በ311 ዓ·ም ሲሆን ፤ ሁለተኛ ጊዜ የወጣው ደግሞ አርዮሳውያን በአትናቴዎስ ላይ በተነሡበት ወቅት ለአትናቴዎስና ለኒቅያ ጉባኤ ውሳኔዎች ያለውን ጽኑ ድጋፍ ለመግለጽ በ338 ዓ·ም ነበር ።

የቅዱስ እንጦንስን የብሕትውናና የብቃት ዝና ከሰሙ ክርስቲያኖች መካከል አንዳንዶቹ እሱ ወደሚኖርበት በረሓ ሄደው በአካባቢው በሚገኙ ዋሻዎች ውስጥ በየግላቸው የምነናን ኑሮ ይኖሩ ጀመር ። ምንም እንኳን ኑሮአቸው ለየግል ቢሆንም የአባ እንጦንስ ተከታይ የነበሩ ባሕታውያን ተራርቀው ከመኖር ይልቅ እሱ በሚኖርበት ዋሻ አካባቢ


www.ethiopianorthodox.org

ስብስብ ብለው መኖራቸው አልፎ አልፎ በአውሬዎችና በዘላን ዘራፊዎች በገዳማቱና በራሳቸው ላይ ከሚደርሱባቸው አደጋዎች በመከላከል ለመዳን አስችሏቸዋል ። ከመካከላቸውም አቅመ ደካማ የሆኑትን ፣ የታመሙትን ወዘተ. ለመርዳትና ለማስታመም ረድቷል ።

አባ እንጦንስ በራእይ በእግዚአብሔር መልአክ በታዘዘው መሠረት የመነኰሳቱ ልብስ ነጭ ፈረጅያና (ቀሚስና) ቆብ ፣ መታጠቂያቸው ከቆዳ የተሠራ ሰቅ እንዲሆን ወስኖ ሲሠራበት ኖሯል ። አሁን ግብጻውያን መነኰሳት የሚለብሱት ጥቁር ፈረጅያና (ቀሚስና) ቆብ ግን በ979 ዓ.ም በሱልጣን አልሐኪም ትእዛዝና ተጽእኖ በግዳጅ የተጀመረ ነው ይባላል ።

እንዲሁም መነኰሳቱ በየግላቸው ሆነው ሲጸልዩ ፣ ሲጾሙ ፣ ሲሠሩ ወዘተ. ከሰነበቱ በኋላ ከቅዳሜ እኩለ ሌሊት ጀምረው እስከ እሑድ ምሽት ድረስ ቅዱስ እንጦንስ ከሚኖርበት ዋሻ ዙሪያ ተሰብስበው ከሱ ጋር የማኅበር ጸሎትና አምልኮ ይፈጽሙ ነበር ።

ይህ ዓይነቱ የብሕትውና ኑሮ ምንም እንኳ የአባ እንጦንስ ደቀ መዝሙር አባ ጳኵሚስ ዘግየት ብሎ እንደመሠረተው ያለ የተሟላ የአንድነት (የማኅበራዊ) ኑሮ ባይሆንም ወደ አንድነቱ ኑሮ የተጠጋ ነበር።

ቀስ በቀስ የምነና ኑሮ ዛሬ የቅዱስ እንጦንስ ገዳም በሚገኝበት ቦታ አካባቢ እየተስፋፋ ሄደ ።

ሌላው የመነኰሳት የአንድነት ኑሮ የተመሠረተው የቅዱስ እንጦን ስና የአባ ፓላሞን (ጳላሞን) ደቀ መዝሙር በነበረው በአባ ጳኵሚስ (290–346) ነበር ። አባ ጳኵሚስ ግብጽ ውስጥ ኤስና በተባለች መንደር ከአረማውያን ወገን ከነበሩ ቤተሰቦች በ290 ዓ.ም ተወልዶ ካደገ በኋላ በቈስጠንጢኖስ ዘመን ለወታደርነት ተመልምሎ አገልግሏል ። በውትድ ርና አገልግሎት ላይ ሳለ በተመለከተው በክርስቲያኖች ጀግንነት ፣ ቸርነት ፣ እንግዳ ተቀባይነት ወዘተ. ተስቦ (ልቡ ተነክቶ) ስለነበር የአገልግሎት ግዳጁን እንደፈጸመ በ313 ዓ.ም ወደ ሲቪልነት ተመልሶ ሲኖር የክርስትናን ትምህርት ተቀብሎ ተጠመቀ ። ከዚያም በኋላ የአባ እንጦንስ ደቀ መዝሙር ወደነበረው አባ ፓላሞን ወደተባለው መናኝ ዘንድ ሄዶ ስለ ብሕትውና ኑሮና ሥርዓት ሲማር ከቈየ በኋላ በ320 ዓ.ም በዓባይ ወንዝ አጠገብ ከሚገኘው ታቤኒስ ከተባለው ቦታ ገዳም መሠ ረተ። በብሕትውና ለመኖር ወደ ገዳሙ ሄደው ለተሰበሰቡት መነኰሳት


www.ethiopianorthodox.org

በማኅበር እንዲኖሩ የሚረዱና መነኰሳት ሊመሩባቸው የሚገቡ ሕጎችን አወጣላቸው ። አባ ጳኵሚስ በመሠረተው ማኅበራዊ በሆነው የምንና ኑሮ ለመሳተፍ ብዙ ሰዎች ስለሄዱ በሕይወት ሳለ ዘጠኝ የወንድና ሁለት የሴት ገዳማት መሥርቶ ባዘጋጃቸው የመነኰሳት ሕጎች መሠረት ይተዳደሩ ነበር ። በዚህ አኳኋን አባ ጳኵሚስ በ346 ዓ·ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ብዙ ገዳማት ተመሥርተው በውስጣቸውም ቍጥራቸው የበዛ መነኰሳት በብሕትውና ይኖሩ ነበር ። አባ ጳኵሚስ የመሠረተው የማኅበራዊ የብሕትውና ኑሮ መንገድ ከታቤኒስ ወደ ሌሎች ገዳማት ተዛምቶ በተግባር ላይ ውሏል ። እንዲሁም ያዘጋጀው ሥርዓተ መነኰሳት በታላቁ ባስልዮስ ፣ በቤኔዲክትና በካስያን ጽሑፎች (ሥራዎች) ላይ ታላቅ ተጽእኖ አድርጓል ። የዚህም በአባ ጳኵሚስ የተዘጋጀው ሕግ ዋነኛ ቅጅ ሲጠፋ ወደ ላቲን የተተረጐመው እስከዛሬ ድረስ አለ ። በሕጉ ውስጥ ከተጠቀሱትም ዋና ዋናዎቹና ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

በማኅበራዊ ብሕትውና ኑሮ የሚኖረው እያንዳንዱ መነኵሴ በየዕለቱ ቀንና ሌሊት ሊሠራቸው (ሊፈጽማቸው) የሚገቡ ተግባሮች ተዘርዝረዋል ። ይኸውም መነኰሳት ጥዋትና ማታ አብረው እንዲጸልዩ ፣ በአንድነት እንዲሠሩ ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያጠኑና በቃል ጽሕፈት እንዲጽፉ ፣ ገቢና ወጪቸው አንድ ላይ እንዲሆን ፣ በአንድነት እንዲመገቡ ፣ ልብሳቸው አንድ ዐይነት እንዲሆንና እነዚህን የመሳሰሉትን ማኅበራዊ ኑሮ ነክ ሕጎች አወጣላቸው ። በዚህ አኳኋን መነኰሳቱ የዕለት ምግባቸውን የሚያገኙት እየሠሩ ነበር ። እነዚህን ሕጎች በመተላለፍ በማያከብሩ መነኰሳት ላይ የሚወሰዱት ለዘብ (ቀለል) ያሉ የቅጣት ዓይነቶችም ተዘጋጅተዋል ። እንዲሁም ማንኛውም እውነተኛ መነኵሴ ሊፈጽማቸው ከሚገቡ ተግባሮች ዋና ዋናዎቹ የድንግልና ኑሮ ፣ ንጽሕና ፣ እግዚአብሔርን በመላ ልብ ማፍቀርና ማምለክ ፣ ድህነት ፣ ታዛዥነት ወዘተ· ናቸው ።

ቀደም ሲል በአባ እንጦንስ ከተመሠረተው ከመጀመሪያው ከብቻኝነት የብሕትውና ኑሮ ይህ በአባ ጳኵሚስ የተዘጋጀው የማኅበራዊ የብሕትውና ኑሮ ያሳየው ታላቁ ለውጥ መነኰሳት ከዋናው ከአምልኮተ እግዚአብሔር ተግባራቸው በተጨማሪ የተለያዩ ሥራዎችን በትጋት እንዲሠሩና እንዲማሩ የሚያዝዘው ሕግ ነው ።


www.ethiopianorthodox.org

ማንኛውም ሰው በብሕትውና ለመኖር ወደ ገዳማቱ ሲሄድ እዚያ እንደደረሰ በአባልነት አይቀበሉትም ነበር ። ከአንድ እስከ ሦስት ዓመታት ለሚሆን ጊዜ የሰውየው ጠባይ ከተመረመረና ፈቃደኛነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ሥርዓተ ምንኵስና ተፈጽሞለት የገዳሙ አባል የመሆን እድል (ፈቃድ) ያገኛል ።

በገዳሙ አበምኔት (አስተዳዳሪ) ከሚሰጠው የዕለት ተዕለት የእጅ (የጉልበት) ሥራ በተጨማሪ ማንበብና መጻፍ እንዲማር ይደረጋል ። ከዳዊት መዝሙሮች አንዳንድ ክፍሎችንና በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙ መጻሕፍት ጥቂቶችን ክፍሎች በቃሉ እንዲያጠና ይደረጋል ። በዚህ አኳኋን አባ ጳኵሚስ በመሠረተው የማኅበራዊ የብሕትውና ኑሮ ውስጥ መሃይምነት ፈጽሞ ጠፍቶ ነበር ። እንዲሁም በየሀገሩ ከብዙ ዘመናት በፊት ለመነኰሳት ፣ ለምእመናንና ለልጆቻቸው ማስተማሪያ በገዳማት ከተመሠረቱት ትምህርት ቤቶች ቀስ በቀስ ጥቂቶቹ ዘመናዊ ዩኒቨርሲቲ ዎች ለመሆን በቅተዋል ።

እላይ እንደተመለከትነው ማንኛውም መናኝ መነኵሴ ዓለም በቃኝ ብሎ ሀገሩንና (ቀየውንና) ዘመድ አዝማዱን ትቶ ከመጣለት ከመንፈሳ ዊው ተግባሩ በተጨማሪ የሰው እጅ እንዳያይ የሚረዳውን የዕለት ጉርሱን የዓመት ልብሱን ለማግኘት ጠንክሮ መሥራትና አእምሮውንም በትምህ ርት ማነጽ የተቀደሰ ተግባሩና ግዴታው መሆኑ በአባ ጳኵሚስ የምንኵስና ሕግ (ሥርዓት) ውስጥ ተብራርቶ ተገልጿል ። በዚሁ መሠረት መነኰሳቱ ተሸጠው ለኑሮአቸው መደገፊያ የሚሆኑ ቅርጫት ፣ የሰሌን ምንጣፍ ፣ ገመድና ሌሎችንም የተለያዩ ዕቃዎችን ይሠሩ ነበር ። እንዲሁም እንደየሥጦታቸውና ችሎታቸው በግብርና ማለት ዓባይን እየጠለፉ በመስኖ ተግባር ላይ በማዋል ፤ የተለያዩ እህል ፣ አትክልትና ፍራፍሬ በማምረት ፣ እንስሳትን በማርባት ፣ በዳቦ ጋገራ ፣ በወጥ ሥራ ፣ በሸማ ሥራ፣ በስፌት ፣ በመፍጨት ፣ በግመል ነጅነት ፣ በአናጺነት ፣ በቤት ሥራ፣ በብረት ቅጥቀጣ ፣ የዘመኑ የሕትመት መሣሪያዎች ባልተፈለሰፉ በት ወቅት የተለያዩ መጻሕፍትን በብራና በቁም ጽሕፈት እየጻፉ በማራባት ወዘተ. ላይ ተሠማርተው በትጋት ይሠሩ ነበር ። ዛሬም በቅዱስ መቃርስ ገዳም መንፈሳዊ ነክ የሆኑ መጻሕፍትንና መጽሔቶችን የሚያ ትም ዘመናዊ ማተሚያ ቤት አላቸው ።


www.ethiopianorthodox.org

በገዳማቱ ክልል ውስጥ የመነኰሳቱ መኖሪያዎች ፣ የጸሎት ቤቶች ፣ የመሰብሰቢያ አዳራሾች ፣ የዕቃና የእህል ማስቀመጫ መጋዘኖች ፣ የምግብ ማዘጋጃ ማድ ቤቶች ፣ የመመገቢያ ቤቶች ፣ ሆስፒታሎች ፣ ወፍጮ ቤቶች፣ ዳቦ ቤቶች ፣ የአልባሳትና የቤተ ክርስቲያን መገልገያ ዕቃዎች (የንዋየ ቅድሳት) ማስቀመጫ ዕቃ ቤቶች ወዘተ· ይገኙ ነበር ። ከገዳሙ ውጭም የመቃብር ቦታዎች ፣ የውኃ ጉድጓዶች ፣ የአትክልትና የእርሻ ቦታዎች ወዘተ· ይገኙ ነበር ።

ለምነና የሄዱ መነኰሳት ጠባይ በሚገባ ተጠብቆ እንዲኖር ፣ ኑሮአቸው ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን ወዘተ· በማድረግ ገዳማቱን የሚያስተዳድሩ አበምኔቶች ከመነኰሳቱ መካከል ብቁ የሆኑት እየተመ ረጡ ያስተዳድሩ ነበር ። መነኰሳቱም በዓመት ሁለት ጊዜ አጠቃላይ ስብሰባ (ጉባኤ) እያደረጉ ሥነ ሥርዓት ፣ አስተዳደር ወዘተ. ነክ በሆኑና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ይወያዩና በገዳማቱ የተከናወኑትን ተግባሮች የሚገልጽ ዝርዝር ሪፖርትም ያዳምጡ ነበር ። በነዚህም ጉባኤዎች የተለያዩ ገምቢ የሆኑ ውሳኔዎች ይተላለፉ ነበር ። በመጨረሻም ሥጋ እንደመልበሳቸው መጠን በጥቂቶቹ መካከል አልፎ አልፎ ግጭት መፈጠሩ ስለማይቀር ከመነኰሳቱ የበደሉና የተበደሉ ይቅር ለእግዚአብ ሔር በመባባል በመካከላቸው የሰላም መንፈስን ካሰፈኑ በኋላ የጉባኤው ፍጻሜ ይሆን ነበር ።

በገዳማቱ ውስጥ በብዛት ይኖሩ ከነበሩት ግብጻውያን መነኰሳት በተጨማሪ ጥቂት ግሪካውያን ፣ ሮማውያን ፣ ቀጸዶቃውያን ፣ ሊብያው ያን፣ ሶርያውያን ፣ ኑብያውያን ፣ ኢትዮጵያውያን ወዘተ· መነኰሳት ነበሩ። ለምሳሌ አቡነ ጢሞቴዎስ ፓትርያርክ በነበረበት ወቅት ግብጽ ውስጥ ጌታውን በማወክ ስላስቸገረ ተባሮ በስርቆት ፣ በዝርፊያና በግድያ ተግባር ተሰማርቶ ኅብረተሰቡን ሲያውክ የነበረው ሙሴ ጸሊም አስከፊ ተግባሩን ርግፍ አድርጎ በመተው ወደ ገዳመ አስቄጥስ ሄዶ ከአባ መቃርስ እየተማረና የአበምኔትነት ተግባሩን እያከናወነ በብሕትውና ኖረ ። እሱም ገዳሙን ሊዘርፉና ሊያጠፉ በሄዱ ዘላኖች ከሰባት መነኰሳት ጋር በሰማዕትነት ስላረፈ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስነት ማዕርግ ሰጥታዋለች ። በዚህ አኳኋን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባቶች (መነኰሳት) በግብጽ በረሓ በሚገኙት ገዳማት ውስጥ ሥርዓተ ምንኵስ


www.ethiopianorthodox.org

ናን ራሳቸው ሊማሩና ገዳማትን በየሀገሮቻቸው ሊመሠርቱ ችለዋል ። ብዙ ምእመናንም በዋሻ የሚኖሩ የበቁ ባሕታውያን የሚፈጽሟቸውን ታምራት አይተው ለማድነቅና በጸሎታቸውም ካደረባቸው ደዌ ለመፈወስ ወደሚኖሩባቸው ገዳማት (ዋሻዎች) በብዛት ይጐርፉ ነበር ። በዚሁ የብሕትውና ኑሮ ለመሳተፍ ወደ ገዳማቱ ይሄድ የነበረው ተራው ምእመን ብቻ ሳይሆን ታላላቅ ሰዎችና የነገሥታትም ወገኖች ጭምር ነበሩ ። ለምሳሌ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ ከአባ እንጦንስ ዘንድ ለተወሰነ ጊዜ በመቈየት ሥርዓተ ምንኵስናን ተምሯል ። እንዲሁም የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቴቢያድ በተባለው አባ ጳኵሚስ በመሠረተው ገዳም ውስጥ ከ373 እስከ 381 ዓ·ም ድረስ በብሕትውና ቈይቷል ። ጀሮምና (342–420) ሩፊኖስ (345–410) ከኢጣልያ ወደ ግብጽ ሄደው ከገዳማቱ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ በብሕትውና ኖረዋል ።

ቅዱስ (ታላቁ) ባስልዮስ (330–379) በግብጽ ገዳማት በብሕትውና ከቈየ በኋላ ወደ ቍስጥንጥንያ ሄዶ በአባ ጳኵሚስ የብሕትውና ሕግ (ሥርዓት) መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ በቢዛንታይን ገዳማትን መሥርቷል። ይኸውም በግብጽ ገዳማት ውስጥ ከቈየ በኋላ ከ360 ዓ·ም ጀምሮ በታናሺ እስያ የምንናን ኑሮ በመመሥረት ያስፋፋው ቅዱስ ባስልዮስ በተለይ የግሪክና የሩሲያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የሚገለገሉበትን የገዳማት (የመነኰሳት) መተዳደሪያ ሕግ አዘጋጀላቸው ። ሕጉም መነኰሳት በየቀኑ ሊፈጽሟቸው ከሚገቡ አምልኮቶች ፣ የጉልበት ሥራዎች ወዘተ· በተጨማሪ የሙት ልጆችን ፣ በልዩ ልዩ በሽታ የሚሠቃዩ ሰዎችን ወዘተ· መነኰሳት እንዴት መርዳት እንደሚገባቸው ይገልጻል ።

እንዲሁም እላይ እንደተመለከትነው ዮሐንስ ካስያን (360–435) ቴቢያድና ኒትራን በሚገኙት ገዳማት ለሰባት ዓመታት ያህል በብሕትውና ከቈየ በኋላ ወደ ጎል (ፈረንሳይ) ተመልሶ በ415 ዓ·ም ጎል ውስጥ ማርሴ አጠገብ ሁለት ገዳማትን መሥርቷል ። ቀጥሎም ግብጽ በብሕትውና በቈየበት ወቅት የተመለከተውንና ያጠናውን መሠረት በማድረግ ሁለት የመነኰሳት መተዳደሪያ ሕጎችን (ሥርዓተ መነኰሳትን) የያዙ መጻሕፍት ጽፏል ።



www.ethiopianorthodox.org

ባጠቃላይ በማኅበራዊ ኑሮ ላይ ተመሥርቶ ጥራት ባለው መልክ ሳይከብድ ወይም ሳይቀል ለሁሉም እንደሚስማማ ሆኖ በአባ ጳኵሚስ የተዘጋጀው ሥርዓተ መነኰሳት በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነትን በማግኘቱ ብዙዎቹ ገዳማት እየመሠረቱ በዚሁ የመነኰሳት መተዳደሪያ ሕግ ተጠቅመውበታል ። አሁንም በመጠቀም ላይ ናቸው ።

ሆኖም በአባ ጳኵሚስ የተዘጋጀው ሥርዓተ መነኰሳት በተግባር ላይ በዋለበት ሀገር ግብጽ ውስጥ በአምስተኛው መቶ ዘመን በአትሪቢስ ገዳም አበምኔት በአባ ሲኖዳ (ሺኖዳ) ተለውጦ በጣም ከባድ የሆነ ሥርዓተ መነኰሳት (የገዳማት መተዳደሪያ ሕግ) ተዘጋጀ ። አባ ሺኖዳ በ370 ዓ.ም በአጎቱ በአባ ፕጐል በተመሠረተው ነጭ ገዳም (ጸአዳ ገዳም) ገብቶ በብሕትውና ከቈየ በኋላ በ388 ዓ.ም በአጎቱ እግር በመተካት የዚሁ ገዳም አበምኔት ሆኖ በውስጡ የሚኖሩ (የነበሩ) ቍጥራቸው የበዛ ወንድ መነኰሳትና ሴት መነኰሳይት ያስተዳድር ጀመር ።

በአባ ጳኵሚስ የተዘጋጀው ሥርዓተ መነኰሳት ሰብአዊ መብትን የሚጠብቅና ለዘብ ያለ በመሆኑ በመላው ዓለም ተቀባይነትን ሲያገኝ ፤ የአባ ሺኖዳ ሥርዓተ መነኰሳት (ሕግ) ግን በጣም ጥብቅና ጭካኔ የተሞላበት ስለነበርና ከሀገሪቱ ውጭም ተቀባይነትን ስላላገኘ ብሔራዊ የገዳማት ሕግ ሆኖ በግብጽ ውስጥ ብቻ ተወስኖ ቀረ ። ለምሳሌ ጥቃቅን ስሕተቶች የፈጸመ መነኵሴ በምክርና በተግሣጽ በመታለፍ ፈንታ በአባ ሺኖዳ ሥርዓተ መነኰሳት መሠረት ይገረፍና በጽኑ እስራት ይማቅቅ ነበር ። በብሕትውና ለመኖር ወደ ገዳሙ የሚሄዱትንም ከጊዜ በኋላ አንታዘዝም በማለት እንዳያውኩ በገዳሙ መተዳደሪያ ሕግ መሠረት ለመኖር በፈቃደኝነት ወደው የገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የግዴታ ውል በቅድሚያ እንዲፈርሙ ያደርጓቸው ነበር ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በእስክንድርያው ፓትርያርክ በአቡነ ቴዎፍሎስ አሳሳቢነት በንጉሥ ቴዎዶስዮስ ትእዛዝ ሴራፔውም በመባል የታወቀው የአሕዛብ ቤተ መቅደስ ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ሲለወጥ አባ ሺኖዳም ትእዛዙ ተፋጥኖ በተግባር ላይ እንዲውል ረድቷል። ዝነኛዋ አረማዊት መምህርት ሂፓትያ በ415 ዓ.ም በክርስቲያኖች ስትገደል አባ ሺኖዳም በገዳማቱ የሕንጻ ሸክላ ቀለም ዓይነት በተሰየሙት ነጭ ገዳምና ቀይ ገዳም በተባሉት ገዳማት በአበምኔትነት ያስተዳድራ



www.ethiopianorthodox.org

ቸው የነበሩትን መነኰሳት አስከትሎ ወደ ላዕላይ ግብጽ በመሄድ ብዙ የጥንት የአረማውያን ሐውልቶችንና ቤተ መቅደሶችን አውድሟል። እንዲሁም አባ ሺኖዳ የእስክንድርያውን ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስን በመከተል በ431 ዓ.ም ኤፌሶን ውስጥ በተደረገችዋ በሦስተኛዋ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ላይ ተካፍሎ የንስጥሮስን የኑፋቄ ትምህርት ተቃውሟል።

በ451 ዓ.ም በተደረገችው በኬልቄዶን ጉባኤ የእስክንድርያ (የኮፕት) ቤተ ክርስቲያን የካቶሊክንና የግሪክ ኦርቶዶክስን አብያተ ክርስቲያናት አውግዛ ከለየች በኋላ በግብጽ ገዳማት ውስጥ የብሕትውና ኑሮ ከዓለማቀፋዊነት ወደ ብሔራዊነት (ጠባብ ብሔርተኝነት) እየተለወጠ ሄደ።

የግብጽ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው በደረሱባት ችግሮችና ጭቆናዎች ሳትፈታ መንፈሰ ጠንካሮች በሆኑት መነኰሳቶቿ አጽናኝነት በተዋሕዶ እምነታቸው ጸንተው የኖሩትንና አሁንም ያሉትን ምእመናን በማገልገል ላይ ትገኛለች። ከገዳማቱም አብዛኞቹ ቢወድሙም ቀሉ እስከዛሬ ድረስ በምዕራባዊው በረሓማ ቦታ በኒትራን ሸለቆ አራት ገዳማት፣ በምሥራቃዊው በረሓማ ቦታ ደግሞ በመናኙ በአባ ጳውሊ ዘእስክንድርያና በአባ እንጦንስ ስም የሚጠሩ ሁለት ገዳማት አሉ። እንዲሁም በምዕራቡ በረሓማ ክፍል የእመቤታችን ገዳም ይገኛል። በእነዚህም ገዳማት በትምህርታቸው የገፉ ግብጻውያን መነኰሳት በብሕትውና ይኖራሉ።

ከሴቶችም ምንኵስናን የጀመረችና የሴት ገዳም በወንድሟ እንዲሠራ ያደረገች የአባ ጳኩሚስ እህት ማርያም ናት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሲያያዝ በመጣው መሠረት አሁን ካይሮ አካባቢ አምስት የሴት ገዳማት ይገኛሉ።

በዚህ አኳኋን በአባ እንጦንስና በተከታዮቹ የተመሠረተው የብሕትውና ኑሮ በግብጽና በመላው ዓለም በመካሄድ ለክርስትና መጠናከርና መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጓል፤ አሁንም በማድረግ ላይ ነው።

## ሰ)ከ325 እስከ 451 ዓ.ም ድረስ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤዎች (ሲኖዶሶች) በተደረጉባቸው ወቅቶች በአብያተ


www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያናት መካከል የተከሰቱ የማይታረቁ የሃይማኖት ልዩነ ቶች። እንዲሁም በሃያኛው መቶ ዘመን ይፋ (አፌሲል) ባልሆነ መንገድ ያደረጉአቸው ግንኙነቶች

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንመለከተው በዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባቶች (ጳጳሳት) ኅብረት ከፍተኛ የሆኑ የመሠረተ ሃይማ ኖት ትምህርቶች በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረትነት በጉባኤ የተወሰኑባ ቸው፤ መናፍቃን የተወገዙባቸው፤ በመጨረሻም አንድ የነበረችቱ ቤተ ክርስቲያን በእምነትና በፖለቲካ (በማዕርግ) ነክ ምክንያቶች በአሳዛኝ ሁኔታ እርስ በእርሷ ተወጋግዛ በሁለት ጎራ የተከፋፈለችበት ወቅት ከ325 እስከ 451 ዓ.ም ድረስ በነበረው ጊዜ ነው።

የቤተ ክርስቲያን አባላትና መሪዎች ከነበሩት ካህናት መካከል በጣም ጥቂቶቹ በየጊዜው ቅዱሳት መጻሕፍት ከሚያስምሩት ውጭ የሆኑ የኑፋቄ ትምህርቶችን በምእመናን ዘንድ ሲነዙ፣ ከአሳሳች ተግባሮቻቸው እንዲታቀቡ ከሐቀኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆችና መሪዎች የተሰጧቸውን ምክሮችና ማስጠንቀቂያዎች አንቀበልም በማለታቸው በ325 ዓ.ም በኒቅያ፤ በ381 ዓ.ም በቊስጥንጥንያ ፤ በ431 ዓ.ም በኤፌሶን በተደረጉት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤዎች ላይ የኑፋቄ ትምህርታቸው በተጨባጭ ማስረጃ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት የሚቃረኑ መሆና ቸው ከተረጋገጠ በኋላ አርዮስ፣ መቅዶንዮስ ፡ አቡሊናርዮስና ንስጥሮስ ከነግብረአበሮቻቸው እየተወገዙ ከቤተ ክርስቲያን አባልነታቸው ተወግ ደዋል።

የተዋሕዶ እምነትን የሚከተሉት አምስቱ የኦርየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ምንም እንኳ የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔዎች በጥብቅ በመቃወምና በማውገዝ ባይቀበሉም፡ በመናፍቁ በአውጣኪ ላይ በተላለፈው ውግዘት ላይ ብቻ ይስማማሉ። የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ ዎች የተቀበሉት ግሪኮችና ካቶሊኮች አምስቱ የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት የሚቀበሉት አውጣኪ "እግዚአብሔር ወልድ ከመቤታችን ከድንግል ማርያም ሰውነትን በነሣ ጊዜ አምላክነቱ ሰውነቱን ስለዋጠው ረቀቀ" በማለት ያስተማረውን የሞኖፊሲዝም ኑፋቄ ነው የሚሉትን ሐሰት የተሞላ ውንጀላ አይቀበሉትም። እላይ እንደተመለከትነው የእስክ ንድርያና መሰሎቿ የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት የአውጣኪን የኑፋቄ

www.ethiopianorthodox.org

ትምህርት አውግዘዋል። እነሱም የሚያምኑት "ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ መሆኑን፡ መለኮትና ትስብእትም ያለመለየት፣ ያለመቀላቀል፣ ያለመለወጥ ስለ ተዋሐዱ አንድ አካል ፣ አንድ ባሕርይ፣ አንድ ፈቃድ፣ አንድ ግብር ነው" ብለው ነው።

በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ጉባኤዎች የተወሰኑትን በመላ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተቀብለው ለእምነታቸው መሠረት በማድረግ እስከዛሬ ድረስ ይጠቀሙባቸዋል። በነዚህም ጉባኤዎች ላይ አብዛኛውን ጊዜ የመሪነቱን ቦታ ይዘው ከፍ ያለ ሚና የተጫወቱት እነ እለእስክንድሮስ፡ አትናቴዎስ፣ ቄርሎስ ዘእስክንድርያና የመሳሰሉት የእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ምሩቃንና የኮፕት ፓትርያርኮች ነበሩ። እንዲሁም በቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ በፍላብያኖስና በመናፍቁ በአውጣኪ መካከል የተነሣውን የእምነት ነክ ችግር እንዲመረምር በአውጣኪ ወዳጅ በንጉሡ ጃንደረባ በክሪሳፊዮስ ግፊት በዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ትእዛዝ በ449 ዓ.ም ኤፌሶን ውስጥ ለተደረገችዋ ጉባኤ ሊቀ መንበር ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ነበር።

ይህ ዓይነቱ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የፈጸሙት የተሳካ የመሪነት ተግባርና በመንፈሳዊ ትምህርትም የእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካህናት ያበረከተችው ታላቅ አስተዋጽኦ የግሪክ ኦርቶዶክስንና የካቶሊክን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ስላላስደሰተ (ስላስቀና) በአራተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ ከቢዛንታይን ንጉሥ ከመርቅያን ጋር በመመሳጠር የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በመንግስት ድጋፍ በእስክንድርያው ፓትርያርክ በቅዱስ ዲዮስቆሮስ ላይ በግፍ ተነሥተው አሠቃይተው ገደሉት። የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያንም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት" በማለት የሚያምኑትን ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት አውግዛ ለየቻቸው።

የቢዛንታይን ንጉሥ ሙሉ ድጋፍ በነበራቸው በኬልቄዶን ጉባኤ ተካፋዮች ሕገ-ወጥ ውሳኔ መሠረት ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በስደት በደሴተ ጋንግራ ተሠቃይቶ ከሞተ በኋላ የቢዛንታይን መንግሥት ደጋፊና በተፈጥሮው ፈሪና ድንጉጽ የነበረው አቡነ ፕሮቴሪዮስ (452-457) ያለ ኮፕት ካህናት ፈቃድ በንጉሡና በቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ


www.ethiopianorthodox.org

(ተጽእኖ) የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ። በተቃራኒው የተዋሕዶን እምነት የሚከተሉ የኮፕት ካህናትና ምእመናን ግን በተዋሕዶ እምነቱ የጸና ነው፤ በመንፈሳዊ አባትነት ይመራናል፤ ያስተምረናል፤ ወዘተ. ብለው ያመኑበትን የግብጽ ተወላጅ የነበረውን አቡነ ጢሞቴዎስ አኤሉሩስን ወዲያው መርጠው በንጉሡ ለተሾመው ለፕሮቴሪዮስ ተቃራኒ ፓትርያርክ አድርገው ሾሙ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእስክንድርያ (የግብጽ) ቤተ ክርስቲያን መለካውያን (የንጉሥ ደጋፊዎች ፣ ወገኖች) በተባሉ፣ የኬልቄዶንን ውሳኔ በሚከተሉ፣ ሥረ መሠረታቸው ቍስጥንጥንያ በሆነው የግሪክ ተወላጆችና የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ በመቃወም የተዋሕዶን እምነት በሚከተሉት የግብጽ ተወላጆች (ኮፕቶች) በሚመሩ በሁለት ፓትርያርኮች ተከፈለች።

ግብጽን በቅኝ ይገዙ የነበሩ የቢዛንታይን ነገሥታትም የሁለት ባሕርይን እምነት የሚከተሉትን መለካውያንን በመደገፍ፣ የተዋሕዶን እምነት የሚከተሉትን በኮፕት ካህናትና ምእመናን ተመርጠው የተሾሙትን እንደ ጴጥሮስ ሞንጎስ የመሳሰሉትን ፓትርያርኮች በመጨቆንና በማሠቃየት የኮፕትን መንበረ ፓትርያርክ ለመደምሰስ በየጊዜው የተደረገው ሕገ-ወጥ ሙከራ ካህናትና ምእመናን ባደረጉት ተጋድሎ ሳይሳካላቸው ቀርቷል። ስለዚህ የሁለት ባሕርይና የተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ሁለት መንበረ ፓትርያርኮች እስከ ዛሬ ድረስ ግብጽ ውስጥ የየራሳቸውን መንፈሳዊ ተግባሮች በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

የቢዛንታይን መንግሥት እላይ በተመለከትናቸው ዓይነት የተለያዩ ተጽእኖዎች የኮፕትን ካህናትና ምእመናን አስገድዶ ወደ ሁለት ባሕርይ እምነት ለመመለስ አልቻለም። ኮፕቶችም የጠባብ ብሔረተኝነት ስሜታቸው እየተጠናከረ ስለሄደ በቅኝ ገዣቸው በቢዛንታይን መንግሥት ፣ በግሪክ ኦርቶዶክስና በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ላይ የነበራቸው ጥላቻ እየከረረ ሄደ። እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናትና በመንግሥት መካከል እንደገና ሰላምን አስፍኖ ለመግዛት በማሰብ በቢዛንታይን ነገሥታት በንጉሥ ዜኖ (ዘይኑን)፣ በንጉሥ አናስታስዮስና በቀዳማዊ ዩስጢንያኖስ በተከታታይ የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ አሻሽሎ ሁለቱን በእምነት የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት አንድ የሚያደርጉ የዕርቅ ድርድሮችን ለማከናወን ሞክረው በኮፕቶች አለመስማማት ምክንያት

www.ethiopianorthodox.org

ሳይሳካላቸው ቀረ።

በሌላው ወገን ደግሞ የኬልቄዶን ጉባኤ እምነት ነክ ከሆኑ ጉዳዮች ባሻገር ፖለቲካ ነክ ለሆኑ ጥቅሞችም ማስከበሪያ ሆን ተብሎ የታቀደ ስለነበር በኒቅያ ጉባኤ በስድስተኛው አንቀጽ የአብያተ ክርስቲያናቱ መሪዎች የማዕርግ ተራ የሮም፣ የእስክንድርያ፣ የአንጾኪያ (የኢየሩሳሌም) የኤፌሶን የነበረው በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በንጉሡ በመርቅያን ተጽእኖ ተሽሮ፣ በኬልቄዶን ጉባኤ ጸድቆ በወጣው በሃያ ስምንተኛው ሕግ ላይ መናገሻ ከተማ ለሆነችው ለቊስጥንጥንያ (ለአዲሲቱ ሮም) ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የአንደኛነቱን ማዕርግ በመስጠት ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፖፕ ጋር አስተካክሎታል። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪ በሽምግልና ብቻ ከመቅደሙ በስተቀር የሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በማዕርግ (በክብር) እኩል መሆናቸው ተወስኗል። ሆኖም የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች "ሁለት ባሕርይ" በሚለው ኑፋቄና የእስክንድርያው (የኮፕት) ፓትርያርክ እንዲሠቃይ በማድረጉ ላይ በአንድ ልብ መካሪና በአንድ ቃል ተናጋሪ በመሆን ቢስማሙም ቅሉ፣ የክብር ጉዳይ ስለሆነ በሃያ ስምንተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ ላይ ግን አልተስማሙም። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በጥብቅ በመቃወም አልተቀበለችውም ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሮምና የቊስጥንጥንያ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች "እኔ እበልጣለሁ"፡ "የለም እኔ እንጂ አንተ አትበልጥም" በመባባል ሲፎካከሩ ኖረዋል። አሁንም ከቀደመ አቋማቸው ዝንፍ አላሉም ።

በዚህ አኳኋን የእስክንድርያ (የኮፕት) ቤተ ክርስቲያን በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ያን ጊዜ ግብጽንም ይገዙ ከነበሩት ከቢዛንታይን ነገሥታት በተደጋጋሚ በተሰነዘሩባት ጭቆናዎች ምክን ያት የቀደመ የመሪነትና የሁለተኛነት የማዕርግ ቦታዋን ከማጣቷም በላይ የምእመናኖቿ ቊጥር እየቀነሰ ሄደ ።

እላይ በተመለከትነው መሠረት የእስክንድርያና መሰሎቿ የኦርየን ታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የሚቀበሉት የመጀመሪያዎችን የሦስቱን ጉባኤዎች ውሳኔ ብቻ ሲሆን፣ የኬልቄዶንንና ከዚያም በኋላ በግሪክ ኦርቶዶክስና በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት በየጊዜው የተደረጉ ትን ጉባኤዎች ውሳኔ አይቀበሉም። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን

www.ethiopianorthodox.org

ከመጀመሪያዎቹ ከሦስቱ ጉባዔዎች በተጨማሪ የአራት ጉባኤዎችን በድምሩ የሰባት ጉባኤዎችን ውሳኔ ስትቀበል፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ከሰባቱ ጉባኤዎች በተጨማሪ ዐሥራ አራት ጉባኤዎችን በድምሩ የሃያ አንድ ጉባኤዎችን ውሳኔ ትቀበላለች።

ምንም እንኳ ሁለቱ ወገኖች በኬልቄዶን ጉባኤ ከተወጋገዙ በኋላ ለአያሌ ዘመናት የጎሪጥ እየተያዩ ቢኖሩም፣ አምስቱ የኦርየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ካህናት ከ1948 ዓ.ም ጀምሮ አባላት በሆኑበት በዓለም አብያተ ክርስተያናት ንቅናቄ የመቀራረብ (የመተባበር) መርሆ መሠረት በ1964 ዓ.ም ዴንማርክ፣ በ1967 ዓ.ም ኢንግላንድ፣ በ1970 ዓ.ም ስዊዘርላንድ፣ በ1971 ዓ. ም ኢትዮጵያ ውስጥ ይፋ (ኦፊሴል) ባልሆነ መንገድ እየተሰበሰቡ በመወያየት ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት በሚቀራረቡበት ሁኔታ ላይ ተነጋግረዋል።

እንዲሁም እንደ ዮሐንስ ሃያ ሦስተኛና ጳውሎስ ስድስተኛ የመሳሰሉት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፖፖች በክርስቲያኖች መካከል ለዘመናት ሰፍኖና ሥር ሰዶ የኖረው የጸብ ግድግዳ ፈርሶ፣ ክርስቲያኖች ሁሉ በሰላምና በወንድማማችነት መንፈስ የክርስትና ተግባራቸውን እየፈጸሙ እንዲኖሩ ያላቸውን ከልብ የመነጨ የዕርቅ ስሜትና እቅድ በ1963 ዓ.ም በተደረገው በሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤና በየጊዜው ገልጠዋል።

የኦርየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካህናት እላይ በተመለከትናቸው የመቀራረብ ዓላማዎች መሠረት ይፋ (ኦፊሴል) ባልሆነ መንገድ በ1971 ዓ.ም፣ በ1973 ዓ.ም ፣ በ1976 ዓ.ም፡ በ1978 ዓ.ም ፡ በ1989 ዓ.ም ቪየና ውስጥ እየተሰበሰቡ ተወያይተዋል።

የእግዚአብሔር እርዳታ ከተጨመረበት በቅርብ ጊዜ ውስጥ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በየጊዜው እየተፈጠረ በመካከላቸው የኖረውን አፍራሽ የጠብ መሰናክል አቃልለው፡ በክርስቶስ ያላቸውን የወንድማማችነት መንፈስ አጽንተውና ተባብረው መንፈሳዊ ተግባራቸውን በማከናወን በሰላምና በፍቅር ሊኖሩ እንደሚችሉ ይታመናል።

ወደፊት በስፋት እንደምንመለከተው ባለንበት በሃያኛው መቶ ዘመን ተጀምሮ በመካሄድ ላይ ያለው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

ንቅናቄ (ጉባኤ ) ዋና ዓላማም በክርስቲያኖች መካከል ዕርቀ ሰላም እንዲሰፍንና የወንጌልን ትምህርት በጋራ እየተረዳዱ በዓለም ለማዳረስ ነው ። የዚህ ጉባኤ አባል ካልሆኑት ጥቂት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ዋነኛዋ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሙሉ አባል እንደምትሆንና የጉባኤው ዓላማም ባፋጣኝ ግቡን እንደሚመታ ይታመናል ።

## ሸ) የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ አንቀበልም ያሉትን የኮፕትን (የግብጽን) ካህናትና ምእመናንን በማስገደድ ወደ ሁለት ባሕርይ የኑፋቄ እምነት ለመመለስ የተሳነው የቢዛንታይን መንግሥት፣ በሚከተሉት ለስለስ ባሉ የዕርቅ ሰነዶች (ፎርሙላ ዎች) አማካይነት ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት በእምነት አንድ ለማድረግ ሞክሮ ሳይሳካለት መቅረቱ

1) <u>በግሪክ ኦርቶዶክስና በኦርየንታል ( በተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ዕርቅና ሰላምን አስፍኖ በሰላም ለመግዛት እንዲያመች ፣ በቢዛንታይን ነገሥታት ጉትጎታ በተደጋጋሚ ተሞክሮ ሳይሳካ የቀረው ሄኖቲኮን (እንደገና አንድ የሚያደርግ ሰነድ) የተባለው ንቅናቄ።</u>

በኬልቄዶን ጉባኤ ወቅት ለሁለት የተከፈሉትን አብያተ ክርስቲያናት በሁለቱም ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው ፣ የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ ሽሮ ወይም አሻሽሎ ሊተካ በሚችል መሠረተ ሃይማኖት አስማምቶ ኮፕቶች አንገዛም በማለት የሚያነሡትን አመጽ በማስታገሥ በሰላም ለመግዛት ያቀደው የቢዛንታይን ንጉሥ ዜኖ (ዘይኑን) (474-491) ነበር። እሱም የሁለት ባሕርይ እምነት ተከታይ የነበረው የቊስጥንጥንያው ፓትርያርክ አካኪዮስና የተዋሕዶ እምነት ተከታይ የነበረው የእስክንድርያው ፓትርያርክ ጴጥሮስ ሞንጎስ ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት ሊያስማሙና ሰላምን ሊፈጥሩ የሚችሉ የመሠረተ ሃይማኖት ትምህርቶች (ፎርሙላዎች፡ ሰነዶች) እንዲያዘጋጁ ጠየቃቸው ። እነሱም በንጉሡ ጥያቄ (ዓላማ) በመስማማት በ482 ዓ.ም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ከኬልቄዶን ጉባኤ በፊት የነበራቸውን የአንድነት መንፈስ የሚያንጸባርቁና በሁለቱም ወገኖች ተቀባይነት ሊኖራቸው የሚችሉ


www.ethiopianorthodox.org

ትምህርቶችን አዘጋጅተው ለንጉሥ ዜኖ እንዲያጸድቀው አቀረቡለት ። የተዘጋጀውም ጽሑፍ ሄኖቲኮን ይባላል ። በዚህም ሰነድ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ የሦስቱ (የኒቅያ፣ የቊስጥንጥንያና የኤፌሶን) ጉባኤ ውሳኔዎች ቀጥተኛነትና ጠቃሚነት ተወስቷል ። መናፍቃኑ አርዮስ፣ ንስጥሮስና አውጣኪ ተወግዘዋል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ መሆኑ ተወስቷል ። ሆኖም ድኅረ ዓለም ከመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱ ቢወሳም በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ወይም ሁለት ባሕርይ የሚለው ወሳኝ የመሠረተ ሃይማኖት ቃል አልተወሳም። የኬልቄዶን ጉባኤም አልተወገዘችም ። በዚህ አኳኋን የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ያለፈውን ልዩነትና ጠብ ርግፍ አድርገው ትተው በዕርቅ ሰላምን አስፍነው መንፈሳዊ ተግባራቸውን እያከናወኑ ለመኖር በማሰብ ያደረጉት ውይይት የሮማ ካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን አላስደሰታትም ነበር ። ምንም እንኳን በሁለቱ ፓትርያርኮች የተዘጋጀው የዕርቅ ሰነድ በንጉሥ ዜኖ ቢጸድቅም ፣ በጽሑፉ ዝግጅት የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ካህናትና ምእመናን ተወካዮች ስላልተካፈሉበት በሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት ካህናትና ምእመናን ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም ። ምክንያቱም ግሪኮች የክርስትና እምነት በሦስቱ ጉባኤዎች ውሳኔ ብቻ መወሰኑ ለተዋሕዶዎች ያደላል ሲሉ ፣ ተዋሕዶዎች (ኮፕቶች) ደግሞ የኬልቄዶን ጉባኤ በይፋ ባለመወገዟ ለሁለት ባሕርይ እምነት ተከታዮች ያደላል በማለት በሁለቱም ፓትርያርኮች የተዘጋጀው ሰነድ ለሁለቱም ወገን ካህናትና ምእመናን አልተዋጠላቸውም ነበር ። እንዲሁም በዚሁ ዝግጅት የተከፋው የሮሙ ፖፕ ፊሊክስ በ484 ዓ.ም ሮም ውስጥ ሲኖዶስ ጠርቶ በኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ ግብር አበሩ የሆነችውን የቊስጥንጥንያን ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አካኪዮስን አወገዘው ። አካኪዮስም በበኩሉ የሮሙን ፖፕ ስም ከሥርዓተ ቅዳሴው መዝገብ እንዲፋቅ አደረገ ። በዚህ አኳኋን በካቶሊክና በግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሠላሳ አምስት ዓመት ያህል የፈጀ መለያየት ሰፍኖ ኖረ ። ይህም በካቶሊክ ታሪክ ጸሐፊዎች ዘንድ "በአካኪዮስ የተፈጸመ መለያየት" በመባል ይታወቃል ።

ሆኖም ከአካኪዮስ ፡ ከጴጥሮስ ሞንጉስና ከንጉሥ ዜኖ ዕረፍት በኋላም የሄኖቲኮን (የአንድነቱ) ንቅናቄ በቀዳማዊ አናስታሲዮስ (491-518) ስለ ቀጠለ ለቊስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው

www.ethiopianorthodox.org

የሚሾሙ ሁሉ ንጉሥ አናስታስዮስ እስከ ዐረፈበት እስከ 518 ዓ.ም ድረስ ይህንኑ የስምምነት ስነድ የተቀበሉና የሚደግፉ መሆናቸውን በፊርማቸው ያጸድቁ ነበር ።

በዚያን ወቅት የተነሣው የአንጾኪያው ፓትርያርክ አቡነ ሳዊሮስ (512-518) የተዋሕዶን መሠረተ ሃይማኖት በስብከቶቹና በጽሑፎቹ አብራርቶ አስተምሯል።

በቀዳማዊ ጀስቲን (518-527) ድጋፍ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስምምነቱ ለተዋሕዶ (ለኮፕት) ቤተ ክርስቲያን ያደላል በማለት የስምምነቱን ሰነድ ችላ ብላ በተዋሕዶዎች ላይ ስለተነሣች አቡነ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ በ518 ዓ.ም ወደ እምነት መሰሎቹ ወደ እስክንድርያ በመሰደድ ከሞት ተርፏል ። የግሪክ ኦርቶዶክሶች ተዋሕዶዎችን በመቃወም ብቻ ሳይወሰኑ በአካኪዮስ ጊዜ ከሮም ቤተ ክርስቲያን ጋር ተቋርጦ የነበረውን ግንኙነታቸውን እንደገና አደሱ። ይህንኑም ዕርቅ ያዘጋጀው ፖፕ ሖርሚስዳስ እንደ አርዮስ ፡ አውጣኪ ፡ ንስጥሮስ የመሳሰሉ መናፍቃንን፤ እንዲሁም የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ አካኪዮስን ፡ የእስክንድርያውን ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስን ሌሎችንም የተዋሕዶ እምነት ተከታዮችን የሚያወግዝ ጽሑፍ አዘጋጅቶ ለቍስጥንጥንያ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ልኳል ።

በቢዛንታይን መንግሥት (ኤምፓየር) ሥር ይተዳደር ለነበረው ሕዝብ ከፍተኛ ዋጋ ያለው የመተዳደሪያ ሕግ በመስጠቱና በመንፈሳዊ ትምህርት ችሎታው የታወቀው ቀዳማዊ ዩስጢንያኖስ (527-565) እንደነገሡ ዜጎቹ በሃይማኖት ልዩነት ምክንያት ሲያካሂዱት የቈዩትን ጠብ አስወግደው በመካከላቸው አንድነትን ፈጥረው በሰላም እንዲኖሩ ለማድረግ ሞክሮ ነበር ። ይህንንም ዕርቅና ሰላም በማስፈኑ ረገድ የግሉ እምነትና ፍላጎት በኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔዎች ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ከተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ጋርም ግጭትን ከመፍጠር ተቆጥቦ ነበር ። በተለይም ባለቤቱ እቴጌ ቴዎዶራ በይፋ ሳይሆን በኅቡዕ (ውስጥ ውስጡን) የተዋሕዶን እምነት ትከተልና ተዋሕዶዎችን ትደግፍ ስለነበር በዩስጢንያኖስ ዘመነ መንግሥት በተዋሕዶዎች ላይ የጎላ ችግር አልደረሰባቸውም ። በእቴጌይቱ ጉትጎታና ግፊት ንጉሥ ዩስጢንያኖስ በግሪክ ኦርቶዶክሶችና በተዋሕዶዎች መካከል ዕርቅን የሚያሰፍን ውይይት እንዲጀመር ስላዘዘ በቀዳማዊ ጀስቲን ዘመነ መንግሥት ወደ እስክንድርያ


www.ethiopianorthodox.org

ተሰዶ ይኖር የነበረው አቡነ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ በ533 ዓ.ም ከእስክንድ ርያ ቤተ ክርስቲያን የተወከሉትን ካህናት (ሊቃውንት) በመምራት ከግብጽ ወደ ቊስጥንጥንያ ሄዶ በውይይቱ ተካፍሏል። ሆኖም በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች መካከል የተካሄደው ውይይት አንዳችም ተጨባጭ ውጤት አላስገኘም። እንዲሁም ንጉሥ ዩስጢንያኖስ ተዋሕዶ ዎች ተደስተው ወደ ስምምነቱና ዕርቁ እንዲሳቡ በማሰብ በ544 ዓ.ም የንስጥሮስን ኑፋቄ ደጋፊ የነበሩትን ቴዎዶሬ ዘሞፕሱኤስትያን፣ ቴዎዶሬ ዘሲሩስንና ኢባስ ዘኤዴሳን ከነጽሑፎቻቸው የሚያወግዝ ውሳኔ እንዲተ ላለፍ አድርጓል። በዚህም ውግዘት ተዋሕዶዎች ወዲያውኑ ሲስማሙ ፡ ካቶሊኮችና የግሪክ ኦርቶዶክሶች በማቅማማት ውግዘቱን አልተቀበሉ ትም ። በዚህ አኳኋን ንጉሥ ዩስጢንያኖስ በግዛቱ የሚኖሩትን ካቶሊኮች ንና የግሪክ ኦርቶዶክሶችን የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ ከሚቃወሙት ከተዋሕዶዎች ጋር አስማምቶ በሰላም ለመግዛት የጀመረው እቅድ ግቡን ሳይመታለት ስለቀረ እስክንድርያ የሚኖሩትን መለካውያን (የግሪክ ኦርቶዶክሶችን) በመርዳት በኮፕቶች ላይ ተጽእኖ አደረገ።

ባጠቃላይ ንጉሥ ዩስጢንያኖስ ምንም እንኳ መለካውያንን በመደ ገፍ ኮፕቶችን መጫን ቢጀምርም በእቴጌ ቴዎዶራ እርዳታ በኮፕቶች (በተዋሕዶዎች) ላይ ከፍ ያለ ሥቃይ አላደረሰም ። እንዲሁም ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በእቴጌይቱ ድጋፍ በንጉሥ ዩስጢንያኖስ ዘመነ መንግሥት ኮፕቶች ኑብያ ውስጥ ያለመሰናከል ክርስትናን አስተምረ ዋል።

ከላይ እንደተመለከትነው ክርስቲያኖች በሚያሳዝን ሁኔታ በእም ነት ልዩነትና በማዕርግ ፍለጋ ምክንያት እርስ በእርሳቸው ሲፋጁና የቢዛንታይን ነገሥታትም ሰላም አስፍነው ሰፊውን ግዛታቸውን ለማስተ ዳደር በተሳናቸው ወቅት፡ ፋርሶችና በቢዛንታይን ግዛት ዙሪያ የነበሩ አረማውያን የቢዛንታይንን መንግሥት በኃይል ለመውረር አሰፍስፈው በታላቅ ዝግጅት ላይ ነበሩ።

2) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለው ኑፋቄ እንደተጠበቀ ሆኖ "አንድ ፈቃድ አለው" በሚል መሠረተ ሃይማኖት ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀው የዕርቅ ሰነድ።

ከዩስጢንያኖስ በኋላ ከነገሠው ከቢዛንታይን ንጉሥ ከሕርቃል


www.ethiopianorthodox.org

(575-641) ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በግብጽ የኮፕቶች ኑሮ የመረረ የሥቃይና የመከራ መቀበያ ሕይወት ሆኖ ነበር።

በተከታታይ በፋርሶችና በዓረቦች ጦር በመከበቡ ምክንያት የቢዛንታይን መንግሥት በተዳከመበት ወቅት በአፍሪካ ለነበረው የቢዛንታይን ግዛት ጦር አዛዥ ሕርቃል የሥልጣን ተቀናቃኞቹን ደምስሶ እንደነገሠ ፣ ፀሐይ አምላኪ በነበረው በቾስሮኤስ ፓርቪዝ የተመራው የፋርስ ጦር በእስያ የቢዛንታይን መንግሥት ቅኝ ግዛት ከነበሩት ሀገሮች በ613 ዓ·ም ሶርያን ፣ በ614 ዓ·ም ኢየሩሳሌምን ይዞ ጌታ የተሰቀለበትን ግማደ መስቀልና ሌሎችንም ንዋየ ቅድሳት ዘርፎ ወደ ሀገሩ ወሰደ ። የፋርስ ጦር ሶርያንና ፍልስጥኤምን በመያዝ ሳይወሰን በ619 ዓ·ም አንዱ ክፍል ጦር በቦስፈረስ የባሕር ሰርጽ በኩል የቍስጥንጥንያን አካባቢ ሲወጋ ፣ ሌላው ክፍለ ጦር ደግሞ የቢዛንታይን መንግሥት ቅኝ ግዛት የነበረችውን ግብጽን ወርሮ ለስድስት ዓመት ያህል በገዛበት ወቅት ክርስቲያኖችን ጨፈጨፈ ፣ አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን ደመሰሰ ። በዚያን ዘመን ኃያልና ሰፊ የነበረው የቢዛንታይን መንግሥት በዜጎቹ መካከል ሰላም ማስፈን ተስኖት በመዳከም ላይ በነበረበት ወቅት ልበ ሙሉ ጀግና የነበረው ንጉሥ ሕርቃል በፋርሶች ላይ ዘምቶ በ623 ዓ·ም ድል አደረጋቸው ። በምርኮ የወሰዱትንም ግማደ መስቀል ወደ ኢየሩሳሌም መልሶ በክብር ከነበረበት ከጌታ መቃብር ላይ እንዲያርፍ አደረገ ። ግብጽን ይዞ የነበረውንም የፋርስ ሠራዊት በ625 ዓ·ም ድል አድርጎ አባረረ ። በዚህም ጀግንነቱና ግማደ መስቀሉን በማስመለሱ የሕርቃል ዝና በቤተ ክርስቲያንና በዓለም ታሪክ ሲተረክ ይኖራል ። የዓቢይ ጾም መጀመሪያው ሳምንት "ጾመ ሕርቃል" ለሱ መታሰቢያ ተብሎ በቤተ ክርስቲያን የተደነገገ ነው ይባላል ። ሕርቃል በታላቅ ጀግንነት ፋርሶችን ድል በማድረግ የግዛቶቹን ነጻነት ካረጋገጠ በኋላ ቀደም ሲል በተነሡት ነገሥታት በሃይማኖት ልዩነት ሰበብ በዜጎቹ መካከል የተፈጠረው ክርክር ፣ ጥላቻና መከፋፈል ለጠላቶቹ ለፋርሶች የብርታት ፣ ለቢዛንታይን መንግሥት የውድቀት ምክንያት መሆኑን ተገነዘበ ። ሆኖም በሃይማኖት የተለያዩ ዜጎችን በሚያቀራርብ ፍትሕን በተከተለ መንገድ ለጠቡ እርማትና መፍትሔ በመሻት ፈንታ ከሱ በፊት የተነሡ ነገሥታት ከሞከሩት የከፋ ፍጅት የፈጠረ የዕርቅ ሰነድ አዘጋጀ ። ይኸውም ቀደም


www.ethiopianorthodox.org

ሲል በተመለከትነው እንዳችም ዕርቅና ሰላም ሊያወርድ ባለመቻሉ ሳይሳካ በቀረው "ሄኖቲኮን" በተባለው የስምምነት ሰነድ ምትክ ከቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ከአቡነ ሰርጌዮስ ጋር በመመካከር "ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ፈቃድ አለው(ሞኖቴሊትዝም)" የሚለውን መሠረተ ሃይማኖት የግሪክ ኦርቶዶክስና የኦርየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ሁሉ ተቀብለው በመስማማት ፣ አንድነታቸውን መሥርተውና አጽንተው ሀገራቸውን ከጠላት እየተከላከሉ በሰላም እንዲኖሩ በማለት በ622 ዓ·ም ዐወጀ ። ይህም ዐዋጅ የግሪክ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የሆኑ ነገሥታት በዜጎቻቸው መካከል ሰላምን አስፍነው ለመግዛት እንዲያመቻቸው ያወጁት ስለሆነ ፣ የአንድ ባሕርይን(የተዋሕዶን) መሠረተ ሃይማኖት ስላላነሣና የኬልቄዶንንም ጉባኤ ስላላወገዘ ለግሪክ ኦርቶዶክሶች በማድላት ተዋሕዶዎችን የሚጫን ነው በማለት በግብጽና በሶርያ ክፍላተ ሀገር ይኖሩ የነበሩ የተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ወዲያውኑ ተቃወሙት ። በተለይም በግብጽ የሚኖሩት ኮፕቶች የግሪኮችን ተንኮል ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ከነቅዱስ አትናቴዎስና ቄርሎስ የተማሩት ቀጥተኛ የተዋሕዶ ሃይማኖታቸው እንዳይፋለስባቸው በመስጋትና በመፍራት የዚህንኑ ሰነድ (ዐዋጅ) ዓላማ በጥብቅ ተቃውመዋል ። ሆኖም ይህንኑ ሰነድ የአንጾኪያው ፓትርያርክ አቡነ አትናቴዎስና(621–629) ፣ የሮሙ ፖፕ ቀዳማዊ ሖኖሪዮስ(625–638) ተቀብለውት ነበር ። ነገር ግን በሁለቱም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ ወዲያው ከካህናቶቻቸው ዘንድ ከፍ ያለ ተቃውሞ ደርሶባቸዋል ። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ትንሽ ቈየት ብላ በ680 ዓ·ም በተደረገችው በሁለተኛዋ የቍስጥንጥንያ ጉባኤ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ፈቃድ አሉት ብላ ወስናለች ። ንጉሥ ሕርቃል ያቀረበው የዕርቅ ሰነድ ተቀባይ ማጣቱን ቢገነዘብም ቅሉ ፣ በቢዛንታይን ግዛት ውስጥ በብዛት የስንዴና የተለያዩ እህሎች ማምረቻና ጎተራ በነበረችው ግብጽ የሚኖሩ ኮፕቶች በውድም ሆነ በግድ ስምምነቱን ተቀብለው በሰላም እንዲኖሩ ለማድረግ ቈርጦ ተነሣ ። ይህንንም ዓላማውን በጭካኔ መንገድ ከግቡ ሊያደርስለት የሚችል ቀራጥና ጨካኝ ካህን በጥቁር ባሕር አካባቢ የምትገኝ የፋሲስ ጳጳስ አቡነ ሲሩስ መሆኑን ተገነዘበ ። ስለዚህ ከመለካውያን(ከግሪክ ኦርቶዶክስ) እምነት ተከታዮች ጋር በመተባበር ቢፈቅዱ በውድ ፣ ባይፈቅዱ በግድ "አንድ ፈቃድ" በሚለው የዕርቅ



www.ethiopianorthodox.org

ሰነድ መሠረት የኬልቄዶንን የሁለት ባሕርይ እምነት ውሳኔ እንዲቀበሉ እንዲያደርግ በ630 ዓ.ም በእስክንድርያ የመለካውያን ፓትርያርክና በመላ ግብጽ የቢዛንታይን መንግሥት እንደራሴ አድርጎ ሾመው ። ይኸው ጨካኙና ምሕረተቢሱ አቡነ ሲሩስም ወደ እስክንድርያ ተጉዞ በ631 ዓ.ም ከደረሰ በኋላ በመንግሥት ሹማምንት ፣ በመለካውያን ካህናትና ምእመናን በመደገፍ በሰነዱ የሰፈረውን ተቀብለው ከመለካውያን ጋር አንድ እንዲሆኑ ኮፕቶችን ቢጠይቃቸው "ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ በመሆኑ መለኮትና ትስብእት ያለመለየት ፣ ያለመቀላቀል ፣ ያለመለወጥ ስለተዋሐዱ አንድ አካል ፣ አንድ ባሕርይ ፣ አንድ ፈቃድ ፣ አንድ ግብር" መሆኑን በምናምነው መሠረት አሁን ለክርስቶስ አንድ ፈቃድ አለው የሚለው ሰነድ ከመጀመሪያ ጀምሮ የተቀበልነው እምነት ቢሆንም ቅሉ ፣ ለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መለያየት ዋነኛ ምክንያት የሆነው ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ አለው የሚለው ኑፋቄ እስከ አልተወገዘ ድረስ ከቀጥተኛው የተዋሕዶ እምነታችን ዝንፍ አንልም ስላሉት ለዐሥር ዓመታት ያህል የኮፕቶችን ካህናትና ምእመናን በመግረፍ ፣ በማሰር ፣ በመግደል ወዘተ ከፍ ያለ አሰቃቂ ሥቃይ ፈጸመባቸው ። እንዲሁም የካህናቱ ፣ የምእመናን ሀብትና የአብያተ ክርስቲያናት ንዋያተ ቅድሳት ተዘረፉ ። በበረሓ በሚገኙ ገዳማት መንነው የሚኖሩ መነኰሳትም ሰነዱን አንቀበልም ስላሉ በግርፋትና በሞት እንዲቀጡ አደረገ ። በዚያን ወቅት ስለ ተዋሕዶ እምነታቸው ሲሉ ሰማዕትነት ከተቀበሉት በብዙ ሺህ ከሚቈጠሩት ካህናትና ምእመናን መካከል በእስክንድርያ የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የቀዳማዊ ብንያም ወንድም ሚናስና በምናና ላይ የነበረው ባሕታዊ ሳሙኤል ይገኙባቸዋል ። የኮፕቶች ፓትርያርክ ቀዳማዊ ብንያም(633-662) ግን የቢዛንታይን መንግሥት መውደቂያና የዓረቦች ድል አድራጊነት እስከተቃረበበት ወቅት ድረስ ቴቤያድ ወደ ነበረው ገዳም ተሰዶ በመግባት እዚያው በብሕትውና ቈየ ። ኮፕቶች በደረሱባቸው ከፍተኛ ሥቃዮች ምክንያት በቢዛንታይን መንግሥትና በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የነበራቸው ጥላቻና ቅራኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ የባሰውን እየከረረ ሄደ ። ስለዚህ ወዲያው የዓረብ ጦር የቢዛንታይንን መንግሥት በያለበት ከቦ ሲያስጨንቀው ኮፕቶች ቀደም ሲል በፋርሶች ወረራ ጊዜ ከግሪኮች ጎን በመሰለፍ ጠላትን ወግተው እንደመለሱ ሁሉ ፣ ዓረቦችንም ከግሪኮች ጎን ተሰልፈው ለመውጋት አልፈለጉም ። በቢዛንታ


www.ethiopianorthodox.org

ይን መንግሥትና በግሪክ ኦርቶዶክስ(በመለካውያን) ቤተ ክርስቲያን የተፈጸመባቸውን የሚያንገፈግፍ ጭፍጨፋ በማስታወስ በገለልተኝነት ከዳር ቁመው ጨቋኞቻቸው በነበሩት በቢዛንታይን መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰውን ጥፋት ተገቢ ነው በማለት ዓረቦች በንጉሥ ሕርቃል ወኪል በአቡነ ሲሩስ የሚተዳደረውን የቢዛንታይንን ግዛት ግብጽን ድል አድርገው ሲይዙ ድርጊቱን የተቀበሉት በታላቅ ደስታ ነበር። አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች አቡነ ሲሩስ በመንፈሳዊ ሹመቱ(በእስክ ንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክነቱ) ጸንቶ ለመቈየት በመሻት ውስጥ ውስጡን ከዓረብ መሪዎች ጋር በመመሳጠርና በመዋዋል ጠንካራ የነበረው የቢዛንታይን ሠራዊት በቀላሉ ተፍረክርኮ ግብጽ በዓረቦች እጅ እንድትወድቅ አስተዋጽኦ አድርጓል ይላሉ ።

ከብዙ ጦርነት በኋላ በ642 ዓ·ም ግብጽ በዓረቦች እጅ ወደቀች ። ሆኖም ለወደፊት እንደምንመለከተው ከዚያን ጊዜ በኋላም ቢሆን ኮፕቶች በገዥዎቻቸው ከመሠቃየት አልዳኑም ።

## ቀ) የመስቀል ጦርነቶች በተካሄዱበት ዘመን የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የነበረችበት ሁኔታ

ሳራካኖችና ቱርኮች በዐሥራ አንደኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ ፍልስጥኤምንና ሌሎችንም ሀገሮች በጦርነት ስለያዙ ፤ እዚያው የነበሩ ትን ክርስቲያኖች በማሠቃየት ብቻ ሳይወሰኑ ወደ ኢየሩሳሌም ለስግደት የሚሄዱትንም ክርስቲያኖች መዝረፍና መግደል ጀመሩ ። ይህንንም አሰቃቂ አድራጎት ዳግማዊ ኡርባን የተባለው የሮሙ ፖፕ ስለሰማ በ1095 ዓ·ም ክሌርሞንት ውስጥ ሲኖዶስ አድርጎ ፍልስጥኤምን ከእስላሞች እጅ ነጻ ለማውጣት ወሰነ ። በዚሁ ውሳኔ መሠረት ለዚህ ቅዱስ ዓላማ ለመዋጋት የአውሮፓ ነገሥታትና ሕዝብ ፈቃደኞች ሆኑ ። በዚሁ መሠረት የመስቀል ጦርነት በተካሄደበትና በዐሥራ አንደኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ላይ ኢየሩሳሌም ውስጥ የላቲን መንግሥት በተመሠረተ በት ወቅት ግብጽን ይገዙ የነበሩት የፋቲሚድ(የፋጡማ) ዳይናስቲ ዘሮች የሽያት እስልምና እምነት ተከታዮች እነ ዋዚር አል አፍዳል ነበሩ ። ከጨካኙና ከግፈኛው ከአል ሐኪም ዕረፍት በኋላ የተነሡ የፋቲሚድ ዘሮች ምንም እንኳ በኮፕቶች ላይ ከባድ ሥቃይ የማድረስ ፍላጎት ባይኖራቸውም ፤ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የነበረው የግብጽ ሕዝብ ከኮፕቶች ጥቂቶቹ በግብር(በታክስ) ሰብሳቢነትና በተለያዩ ሥራዎች ላይ


www.ethiopianorthodox.org

ተሠማርተው ብዙ ሀብት በማፍራታቸው ከፍተኛ ቅናትና ጥላቻ ስላደረ በት ፡ ሀብታቸውን በኃይል ለመዝረፍ ከመሞከር አልተቆጠበም ነበር ። ያንን ለጥፋት ያሰፈሰፈ ሕዝብ በክርስቲያኖች ላይ ለመፈጸም ከተነሣሣ ለት የዘረፋ ተግባር ለመግታት መሪዎቹ ስላልቻሉ ያንኑ ሕዝብ ለማስደ ሰት በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ይሠሩ የነበሩትን ኮፕቶች ያለምንም ጥፋት ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ አባረሩአቸው ።

በኮፕት ፓትርያርኮች ላይ የሚደርሰው እስራትና ሥቃይ ሁል ጊዜ ከእስላሞች በሚሰነዘረው ውንጀላ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ ከፍተኛ ምቀኝና ቅናት ከሰፈነባቸው ከኮፕት መነኰሳትና ጳጳሳት ለገዥዎች በሚቀርበው የሀሰት ውንጀላም ጭምር ነበር ። ለምሳሌ የማዕርግ እድገት ስለተከለከለ ኮሉቶስ የተባለው መነኵሴ በፓትርያርኩ በአቡነ ክርስቶዱ ሉስ(1047–1077) ላይ ባቀረበው የሀሰት ክስ ምክንያት ባለ ሥልጣኖች የክሱን ይዘት በሚገባ ሳያጣሩ "ሲሻኝ ጢስ ወጋኝ" እንዲሉ ፓትርያር ኩን አስረው የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብት ወሰዱ ።

እንዲሁም ቀደም ሲል በስምንተኛው መቶ ዘመን አባ ጴጥሮስ የተባለ መነኵሴ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቀዳማዊ ሚና ወርዶ እሱ እንዲሾም በመሻት ለደማስቆና ለግብጽ ገዥዎች ጉቦ በመስጠቱ እንዲወ ርድ የታዘዘው ፓትርያርክ በሕገ ወጥ መንገድ አልወርድም ስላለ ወደ እስር ቤት ተልኮ ለተወሰነ ጊዜ ሲሠቃይ ቆየ ። ሆኖም ለሥልጣን የጓጓው ትእግስተ ቢሱ አባ ጴጥሮስ ሹመቱን በአስቸኳይ ለማግኘት ባለመቻሉ ከግብጽ ገዥ ከአቡ አውን ጋር በመጋጨቱ በዚሁ ሁኔታ በመበሳጨት አቡ አውን የቀድሞ ትእዛዙን ቀይሮ አቡነ ሚና (ሚናስ) ከእስር ቤት ወጥቶ የፓትርያርክነት ተግባሩን እንዲቀጥልና አባ ጴጥሮስ ወደ ወኅኒ ቤት እንዲላክ አደረገ ። በተቃራኒው ደግሞ እንደ ዳግማዊ ማርቆስ ያሉ አንዳንድ መነኰሳት ለፓትርያርክነት ሲመረጡ የተግባሩን ከባድነት በማሰብ ለዚህ ከፍተኛ መንፈሳዊ ማዕርግ አንበቃም በማለት እየጠፉ ወደ ገዳም ይሄዱ ነበር ። ነገር ግን ይመራናል ብለው የመረጡአቸው ካህናትና ምእመናን አስረው በማምጣት ይሾሙአቸው ነበር ።

ከላይ እንደተመለከትነው ኮፕቶች ገደብ የለሽ ግብርና የነፍስ ወከፍ ታክስ በመክፈል ፡ አልፎ አልፎም የሚደርሱባቸውን ሥቃዮች በመቀ በል የሚያሳልፉት ኑሮ አንሶአቸው የመስቀል ጦርነት ሲጀመር እስላሞች ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ በተዋሕዶዎችና (በኮፕቶችና) በምዕራብ


www.ethiopianorthodox.org

አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተፈጠረውን የማይታረቅ ቅራኔና የከረረ ልዩነት ባለመገንዘብ ፤ ኮፕቶችን በክርስትና እምነት መሰሎቻቸው ለሆኑት ምዕራባውያን(ካቶሊኮች) የመስቀል ጦረኞች በማድላት ውስጥ ውስጡን ያግዛሉ ብለው በመጠራጠር በዓይነ መአት ይመለከቷቸው ነበር። ስለዚህ እስላሞች ጦርነቱ የመስቀል ጦርነት እስከሆነ ድረስ የካቶሊክም ሆኑ የግሪክ ኦርቶዶክስ ወይም የኮፕት ክርስቲያኖች መስቀ ልን ስለሚቀበሉ ሁሉንም እንደ ደመኛ ጠላት ይመለከቱ ጀመር ። በሌላው ወገን ደግሞ የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ የመስቀል ጦረኞች የተዋሕዶ እምነት ተከታይ ክርስቲያኖች ከሐዲዎች ናቸው ፤ የግሪክ ኦርቶዶክስ ተከታዮች ደግሞ ተገንጣዮች ናቸው በማለት እስላሞችን ድል እያደረጉ በያዙአቸው ሀገሮች በሚኖሩ የተዋሕዶና የግሪክ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ላይ ከፍ ያለ ሥቃይ ፤ የንብረት ጥፋትና ብዝበዛ አድርሰዋል ። ለምሳሌ በ1178 ዓ·ም ንጉሥ ባልድዊን ግብጽን በጦር ኃይል ይዞ ታላቅ ጥፋት ባደረሰ ጊዜ በእስላሞች ላይ ብቻ ሳይሆን በኮፕቶች ላይም ታላቅ ጉዳት ደርሶባቸዋል ። ባጠቃላይ የመስቀል ጦረኞችም ሆኑ የእስላም ገዥዎች አንዱ ወገን ሌላውን ወግቶ ባሸነፈ ቍጥር ሁለቱም ወገኖች ያለምንም ርህራሄ ኮፕቶችን ጨፍጭፈዋል ። ንብረታቸውንም አውድመዋል ።

በኮፕት ክርስቲያኖች ዘንድ የነበረው ሌላው ችግር ደግሞ አንድ ፓትርያርክ ከሞተ በኋላ ሌላ መርጦ ለመተካት ከገዥዎች ፈቃድ ሲጠየቅ የሚሰጠው ገደብ የለሽ ገንዘብ ከፍ ያለ ነበር ። ለምሳሌ የኮፕት ፓትርያርክ ዳግማዊ መቃርዮስ በ1128 ዓ·ም ከዐረፈ በኋላ ኮፕቶች አዲስ ፓትርያርክ መርጠው ለመሾም ፈቃድ ሲጠይቁ በቅድሚያ ስድስት ሺህ



www.ethiopianorthodox.org

ያህል ዲናር ለመንግሥት ግምጃ ቤት ክፈሉ ተባሉ ። ኮፕቶችም ለዓመት ግብርና ለነፍስ ወከፍ ታክስ ከሚከፍሉት በተጨማሪ እላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ መክፈሉ በጣም ከብዷቸው ሳለ የባሰውን ይባስ ብሎ አንዳንድ ነገር አመላላሽ ኮፕቶች ለቤተ ክርስቲያናቸው መተዳደሪያ ከምእመናን የሚሰበስቡትን ገንዘብ ለጠላቶቻችን ለፍራንኮች በድብቅ በመላክ ላይ ናቸው በማለት ስላሳበቁ ከሊፋዎች ጉዳዩን በሚገባ ሳያጣሩ ወዲያውኑ አብያተ ክርስቲያናቱ እንዲወረሱ በማዘዛቸው ያለ የሌለው ሀብት ሙጥጥ ተደርጎ ተወሰደ ። እንዲሁም ፓትርያርክ መርጦ የመሾም ዓላማቸው ተገትቶ ከቆዬ በኋላ በብዙ ደጅ ጥናት ዋዚር አሕመድ ስለፈቀደ ተፈላጊው ገንዘብ ተከፍሎ አቡነ ገብርኤል እብን ታሪክ (1131—1145) የእስክንድርያ (የኮፕት) ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ ።

የግብጽ ገዥ የነበረው የሱኒ እስልምና እምነት ተከታይ ሳላዲን የአስተዳደር ሥራውን እንደጀመረ ኮፕቶችን ከተለያዩ የሥራ ቦታዎች አባረረ ። ከሥራ ገበታቸው በማባረር ብቻ ሳይወሰን ክርስቲያኖችን ሁሉ የውርደት ምልክት ከሆነው ከጥቁር ልብስ በስተቀር ነጭና በተለያዩ ኅብረ ቀለማት ያጌጡ ልብሶችን እንዳይለብሱ ፣ ፈረስ እንዳይጋልቡና ከፍ ያለ መቀጫ ገንዘብ ለመንግሥት እንዲከፍሉ አዘዘ ። ኮፕቶችም በግፍ የተጣለባቸውን ገንዘብ ለመክፈል ያለ የሌለ ሀብታቸውን ሸጡ ፤ እርስታቸውንም ለእስላሞች በመሸጥ ርስት የለሽ ሆኑ ። አንዳንዶቹም የእስልምናን እምነት በመቀበል እላይ ከተጠቀሱት ጭቆናዎችና እዳዎች ነጻ ሆኑ ።

እላይ የተጠቀሰው ኮፕቶች ፈረስ እንዳይጋልቡ ፣ ጥቁር ልብስ ብቻ እንዲለብሱ ፣ ከፍ ያለ ገንዘብ እንዲከፍሉ የሚለው የጭቆና ሕግ በዐሥራ ሰባተኛው መቶ ዘመን ቱርኮች ግብጽን ይገዙ በነበረበት ወቅትም ለተወሰነ ጊዜ በተግባር ላይ ውሎ ነበር ።

እንዲሁም እስክንድርያ ውስጥ ባውካሊስ በተባለው ሥፍራ በግብጽ የመጀመሪያውና ጥንታዊው ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ በነበረበት ቦታ ላይ በእስክንድርያው ፓትርያርክ በአቡነ አጋሶስ (662–680) የተሠራው ታላቁ የቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ከሜዲትራንያን ባሕር ወደብ አጠገብ ስለሆነ ፣ የመስቀል ጦረኞች በመርከብ ተጉዘው ድንገት እስክንድርያን የያዙ እንደሆነ ምሽግ ያደርጉታል በሚል ሰበብ የሳላዲን ሹማምንት ለማፍረስ ከወሰኑ በኋላ ኮፕቶች ባለሥልጣኖችን በመለመንና ሁለት ሺህ


www.ethiopianorthodox.org

ዲናር በመክፈል ከመፍረስ አድነውታል ።

ሳላዲን በ1173 ዓ·ም ክርስቲያኑን የኑብያን መንግሥት የሚወር ሠራዊት ልኮ በኑብያ ኑአሪዎች ላይ ከባድ ጥፋት አደረገ ። ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት ፈረሱ ። የተዋሕዶ እምነት ተከታይ ከሆኑ ጳጳሳት ፣ ካህናትና ምእመናን ብዙዎቹ ታሰሩ ። አንዳንዶቹም ለዓረብ የባሪያ ገብያ ለሽያጭ ቀርበው ተቸበቸቡ ። ሆኖም በ1187 ዓ·ም ሳላዲን የመስቀል ጦረኞችን ድል አድርጎ ኢየሩሳሌምን ከያዘ በኋላ እሱና ተከታዮቹ በኮፕቶች ላይ የነበራቸውን ጥላቻ ትተው በደህና ዐይን ይመለከቷቸው ጀመር ። ይኸውም የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት እንዲሠሩ ፈቀዱ ። ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተባረሩ ኮፕቶች ሁሉ ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ፣ የፈለጉትን ዓይነት ልብስም እንዲለብሱ ወዘተ· ፈቀደላቸው ። ለጥቂቶችም የተወረሰ ሀብታቸው ተመለሰላቸው ።

በ14ኛው መቶ ዘመን የኮፕቶች መከራና ሥቃይ እንደገና እየጨመረና እየከፋ ሄደ ። ይኸውም በ1365 ዓ·ም እስክንድርያን የያዙ የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ የመስቀል ጦረኞችም ልዩነት ሳያደርጉ ታላቅ ጭካኔ በተሞላበት መንፈስ እስላሞችን ፣ ኮፕቶችንና መለካውያንን መዘበሩ ። በዓረቦች በባርነት እየተገዙ በውትድርና ያገለግሉ የነበሩት የቱርክ ፣ የሞንጐልያ ወዘተ· ተወላጅ እስላሞች ከፈረንሳይ የዘመተውን የመስቀል ጦረኛ ድል ካደረጉ በኋላ ኃይል ስላገኙ (ስለተሰማቸው) በዓረብ ተወላጆች ይገዛ የነበረውን ሕጋዊውን የግብጽ መንግሥት አይባክ በተባለው የጦር መሪያቸው በኃይል አስወግደው ግብጽን መግዛት የጀመሩት ማምሉኮች ክርስቲያኖችን ማሠቃየት ጀመሩ ። ይኸውም በጭካኔ የሚወጉንና የሚበዘብዙን የእምነት መሰሎቻችሁ የመስቀል ጦረኞች ስለሆኑ የደረሰብንን ጉዳት በእናንተ ላይ እንወጣለን በማለት የእስላም ባለሥልጣኖች በእስክንድርያ ፓትርያርኮች በአቡነ ማርቆስ አራተኛ (1350—1364) ፣ በአቡነ ዮሐንስ ዐሥረኛና (1364—1369) በኮፕቶች ላይ የግድያ ፣ የእስራት ፣ ከሥራ የማባረርና የመሳሰሉ ከፍ ያሉ ሥቃዮችን አድርሰዋል ። አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማትን አፍርሰዋል ። ከጥፋት የተረፈውን የመንበረ ፓትርያርኩንና የቤተ ክርስቲያኒቱንም ሀብት ወርሰዋል ። ሆኖም ከግብጽ ግዛት ውጭ ከአራት የሀገር መሪዎች ለግብጽ ገዥዎች በምልጃና በማስፈራራት መልክ


www.ethiopianorthodox.org

በቀረቡ ጥያቄዎች ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰላምና እፎይታን ልታገኝ ችላለች ። ምልጃዎችም የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ/ የቊስጥንጥንያ ንጉሥ ራሱ ከኦቶማን ቱርኮች ጋር በመዋጋት ላይ የነበረ ቢሆንም ፤ ግብጽ የሚኖሩትን መለካውያን እንዳያሠቃዩአቸው ለማምሉኮች ዳይናስቲ ያቀረበው ልመና ፤

2ኛ/ ከግብጽ መንግሥት ጋር መልካም ግንኙነት የነበረው የአራጐን ንጉሥ በግብጽና በኢየሩሳሌም የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናት ተከፍተው ለምእመናን መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን እንዲሰጡ በማለት ለማምሉኮች ያቀረበው ምልጃ ፤

3ኛ/ የኑብያው ንጉሥ የእስክንድርያውን ፓትርያርክ የአቡነ ማርቆስን በግፍ መታሰር እንደሰማ ወዲያው በሀገሩ የሚገኙትን እስላም ነጋዴዎች አስሮ ፓትርያርኩ ካልተፈታና በኮፕቶች ላይ የሚካሄደው ሥቃይ ካልቆመ ያሰራቸውን ሰዎች የማይፈታና ተጨማሪ ርምጃም የሚወስድ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ መላኩ ፤

4ኛ/ እላይ ከተጠቀሱት ከሦስቱም ጥያቄዎች ከበድ ያለው የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት በተዋሕዶ እምነት መሰሎቹ በሆኑት በኮፕቶች ላይ የሚፈጸመው ሥቃይ እንዲቆም ፤ የግብጽ እስላሞች በኮፕቶች ላይ የግፍ ተግባራቸውን የሚቀጥሉ ከሆነ እሱም የዓባይን ወንዝ አቅጣጫ በመለወጥና የተለያዩ ተጽእኖዎችን በማድረግ የሚበቀል መሆኑን በመግለጽ ከግብጽ ባለ ሥልጣኖች ጋር ያደረገው ድርድርና ያስተላለፈው መልእክት ነው ።

በ15ኛው መቶ ዘመን ፍሎሬንስ ውስጥ በተደረገችው የፌራራ ሲኖዶስ (1438—1439) የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከኮፕት ፣ ከኢትዮጵያ፣ ከግሪክ ኦርቶዶክስ ወዘተ· አብያተ ክርስቲያናት ጋር የዕርቅ ድርድር ለማድረግ ሞክራ ነበር ። ይኸውም ከተለያዩ የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የተወከሉ ካህናት ፤ እንዲሁም ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ እንጦንስ ገዳም አበምኔት አባ ዮሐንስና ኢየሩሳሌም ካለው የኢትዮጵያ ገዳም ኢትዮጵያዊው አባ ጴጥሮስ ተወክለው በጉባኤው ላይ በመገኘት ውይይቱ ተጀምሮ ሦስቱንም አብያተ ክርስቲያናት ከሮሙ ፖፕ ሥር ለማድረግ ከእስላሞች ወረራ እናድናችኋለን በሚል ሽፋን የታቀደ ደባ ስለነበር ግቡን ሳይመታ ቀረ ። የጉባኤው አለመሳካት ዋናው ምክንያት የካቶሊክ ፣ የግሪክ ኦርቶዶክስና የተዋሕዶ (የኦርየንታል)


www.ethiopianorthodox.org

አብያተ ክርስቲያናት ቀደም ሲል ተወጋግዘው የተለያዩባቸው የእምነት ልዩነቶች አስወግዶ የሚያስማማ በሦስቱም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል መፍትሔ ባለመገኘቱ ነበር ።

## በ) በአቡነ ቄርሎስ 4ኛና በአቡነ ቄርሎስ 5ኛ የፓትርያርክነት ዘመን ፣ ከዚያም በኋላ በኮፕት ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ዘንድ የተከሰተው መሻሻል (ተሐድሶ)

በኮፕቶች ዘንድ የተሐድሶ አባት በመባል የሚታወቀው ቄርሎስ 4ኛ (1854—1861) የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ እንደሆነ ፣ ዋነኛ ዓላማ አድርጎ የተነሣው ትምህርትን ማስፋፋት (ማሰራጨት) ስለነበረ በግብጽ ካህናት ዘንድ ሰፍኖ የነበረውን የትምህርት ጉድለት (ዝቅተኛነት) ለማሻሻል ካህናት ተግተው እንዲማሩ አደረገ ። ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትም ከፍቶ ዓለማዊና መንፈሳዊ ዕውቀት የነበራቸውን መምህራን በማሠማራት ፣ መጻሕፍትን በገፍ በማቅረብ ካህናትና ምእመናን የቅብጥ ፣ የዐረብኛ ፣ የእንግሊዝኛ ፣ የፈረንሳይኛ ፣ የኢጣልያንኛ ፣ የቱርክ ወዘተ· ቋንቋዎችና የተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርቶችን እንዲማሩ አደረገ ። በተጨማሪም ከካይሮ ወጣ ብሎ ሁለት የወንድ ትምህርት ቤቶችንና አንድ የልጃገረዶች ትምህርት ቤት ከፍቷል። እንዲሁም ያረጁ አብያተ ክርስቲያናትን አድሷል ። አዲሶችንም አሳንጿል ። ለካህናት መማሪያና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ መንፈሳዊ ነክ መጻሕፍት ማዘጋጃ የሕትመት መሣሪያ ከአውስትርያ ገዝቶ በማስመጣት አቋቁሞአል ። ይህም ካይሮ ከነበረው ከመንግሥቱ ማተሚያ ቤት ቀጥሎ ሁለተኛው የግል (የቤተ ክርስቲያን) ማተሚያ ቤት ነበር ።

ቀደም ሲል በዐሥራ አንደኛው መቶ ዘመን በአንድ ወቅት በድንገት የተለመደው የዐባይ ወንዝ ሙላት በጣም በመቀነሱ የተደናገጠውን የግብጽ ገዥ ከሊፋ አል ሙስታሊንን የእስክንድርያ ፓትርያርክ አቡነ ሚካኤል አራተኛ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የኢትዮጵያ መንግሥት በወንዙ ላይ ምንም መሰናክል አለማድረጉን በማስረዳት እንዳጽናናውና የሁለቱን ሀገሮች ወዳጅነት እንዳጠናከረ ሁሉ ፤ በዐሥራ ዘጠንኛው መቶ ዘመንም በግብጹ ገዥ በሰይድ ፓሻና በኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት በዐፄ ቴዎድሮስ መካከል የተነሣውን ጠብ በማስታረቅ ሰላምን ለማስፈን አቡነ


www.ethiopianorthodox.org

ቄርሎስ አራተኛ በ1856 ዓ·ም ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ነበር ። በዚያው ዘመን በዕውቀት በገፉ ፣ ለቤተ ክርስቲያናቸው በጎ አሳቢ በሆኑ የኮፕት ምእመናንና በወግ አጥባቂዎች ካህናት መካከል ከፍ ያለ ትግል (ሽኩቻ) ተጀምሮ ነበር ። አቡነ ቄርሎስ አራተኛ ከኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት በመሻት ከግሪክና ከአርመን ፓትርያርኮች ጋር ግንኙነት ፈጠረ ። ሆኖም በአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል የተጀመረው ግንኙነት በመንግሥቱ ላይ እንደታለመ አመጽ በመቈጠሩ የግብጹ ገዥ ሰይድ ፓሻ አቡነ ቄርሎስን በእጅ አዙር በመርዝ አስገደለው ።

ከአቡነ ቄርሎስ አራተኛ ዕረፍት በኋላ ቤተ ክርስቲያንን የማሻሻሉ ተግባር በምእመናን በተመረጡ ማዕርገ ክህነት በሌላቸው የሰበካ (የተሐድሶ) ጉባኤ አባላት ይካሄድ ጀመር ። ምንም እንኳ ወቅቱ ካህናት ዲሞክራሲን በተከተለ መንፈስ ከምእመናን ጋር እየተመካከሩ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር የማሻሻልና ስብከተ ወንጌልን የማስፋፊያ ዘመን ቢሆንም ፣ በ1874 ዓ·ም የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆኖ በመሾም ለ53 ዓመታት ያህል ቤተ ክርስቲያኒቱን ያስተዳደራት አቡነ ቄርሎስ 5ኛና (1874—1928) አንዳንድ መሰሎቹ ካህናት ወግ አጥባቂ ዎች ስለነበሩ ፣ ከምእመናን ጋር በእኩልነት መንፈስ ተቀምጠው እየተመካከሩ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ መሻሻል በጋራ እየተረዳዱ የመሥ ራቱ በአዲሱ ዘመን የተከሰተው የበጎ አሳቢነት መንፈስ የሰፈነበት ቀልጣፋና አመርቂ ውጤት የሚያስገኘው የአሠራር ዘዴ አልዋጥላቸውም አለ ። ስለዚህ ያለ የሌለ ኃይላቸውንና ሀብታቸውን መሥዋዕት በማድረግ ቤተ ክርስቲያኒቱ እንድትሻሻል (እንድታድግ) ለማድረግ በቀናና በጋለ መንፈስ ታጥቀው (ቆርጠው) ከተነሡት በጎ አሳቢ ምሁራንና ምእመናን ጋር በቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና የሥራ አመራር ወዘተ· ውስጥ አያገባችሁም በማለት ግብ ግብ ገጠሙ ። ሆኖም ከብዙ ትግልና ውጣ ውረድ በኋላ የምእመናኑ መንፈሳዊ (የሰበካ) ጉባኤ የመንግሥትን ድጋፍ ስላገኘ የወግ አጥባቂዎች ዓላማ ተዳከመ (ውድቅ ሆነ) ። ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምእመናን በማኅበር (በሰበካ ጉባኤ) እየተደራጁ ከካህናት ጋር በመተባበር ስለ እናት ቤተ ክርስቲያናቸው መሻሻልና ማደግ ከልብ በትጋት ይሠሩ ጀመር ። አሁንም በመሥራት ላይ ናቸው ።


www.ethiopianorthodox.org

አቡነ ቄርሎስ 5ኛ በወግ አጥባቂነቱ ሐሳበ ግትር ቢሆንም ቅሉ ፣ ብዙ ያረጁ አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን አሳድሶአል ። በመላ ግብጽ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትንም አሳንጿል ። የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤትም ከፍቷል ። ካይሮ ውስጥ መሐመሻ ከተባለው ቦታ ላይ የነበረውን ታላቅ ቤት ገዝቶ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ከፍቷል ።

ቀደም ሲል በጭቆና መልክ በክርስቲያኖች ላይ ከሕጋዊው ግብር በላይ ተጥሎ ይሠራበት የነበረው ተደራራቢ ግብር በሰይድ ፓሻ ተሽሮ ክርስቲያኖች እንደ እስላሞች እኩል ቀለል ያለ ሕጋዊ ግብር እንዲከፍሉ የተደረገው በአቡነ ቄርሎስ 5ኛ የፓትርያርክነት ዘመን ነበር ። ምንም እንኳ እስልምና የመንግሥቱ ሃይማኖት ቢሆንም ማንኛውንም እምነት የሚከተል የግብጽ ዜጋ ሁሉ እኩልነት በሕግ የተረጋገጠው በዚያው ዘመን ነው ።

ከላይ እንደተመለከትነው በጥንት ጊዜ በካህናትና በምእመናን ከየገዳማቱ ለፓትርያርክነት ከሚመረጡት መነኰሳት አንዳንዶቹ ከገዥዎች በኮፕቶች ላይ የሚሰነዘሩትን ሥቃዮች ከባድነት በማሰብ ለሹመቱ ብቁ አይደለንም በሚል ሰበብ ምርጫውን አንቀበልም ሲሉ ፣ በመራጮች ታስረው ከተወሰዱ በኋላ በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ሢመቱ እየተፈጸመላቸው ይሾሙ ነበር ። ከሃያኛው መቶ ዘመን ጀምሮ ግን በክርስቲያኖች ላይ ይሰነዘር የነበረው ሥቃይ በመቃለሉ በ1928 ዓ·ም ቄርሎስ 5ኛ ካረፈ በኋላ ከነበሩት ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት መካከል በአንዳንዶቹ ላይ ፓትርያርክ የመሆን ፍላጎት ስላደረባቸው በመካከላቸውም ውድድሩ እየጸና ሄደ ። ይህንኑ ጉዳይ ዝንባሌ ባጭሩ ለመቅጨት የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግ በሚያዝዘውና ከጥንት ጀምሮ ለፓትርያርክነት ይበቃል ተብሎ የታመነበት መነኵሴ ከገዳም እየተመረጠ እስክንድርያ በሚገኘው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ሢመቱ እየተፈጸመለት ይሾም በነበረው ባህል መሠረት በሃያኛው መቶ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን ከራሳቸው ጥቅምና ዝና በማስቀደም በቀና መንፈስ ያገለግላሉ ተብለው ከሚታመንባቸው መነኰሳት መካከል በካህናትና በምእመናን ብቁ የሆነው እየተመረጠ ካይሮ በሚገኘው በቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል እንዲሾም ተወሰነ ። ሆኖም ውሳኔው ለጥቂት ዓመታት (ለ29 ዓመታት) ተግባር ላይ ሳይውል ከቆየ


www.ethiopianorthodox.org

በኋላ ከጳጳሳት ሳይሆን ከመነኰሳት መካከል አቡነ ቄርሎስ ስድስተኛ (1959—1971) ለፓትርያርክነት ተመርጦ ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ በተግባር ላይ ውሏል ።

እንዲሁም ከዘጠንኛው መቶ ዘመን ጀምሮ አልፎ አልፎ ካህናትና ምእመናን ሁለት ወይም ሦስት ጳጳሳትን (ጳጳሳትንና መነኰሳትን) ለፓትርያርክነት በእጩነት ከመረጡ በኋላ ስሞቻቸው የተጻፈባቸው ዕጣዎች እቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከመንበሩ ላይ ተቀምጠው ከተቀደሰባቸው (ከተጸለየባቸው) በኋላ ሕፃን ልጅ ቀርቦ በምእመናን ፊት ዕጣውን ሲመዝ የወጣለት ካህን በመንፈስ ቅዱስ መመረጡ ታምኖ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖ ይሾማል (የሐዋ· 1 ፡ 23 — 26) ። በዚህ መንገድ ከተሾሙት መካከል አቡነ ዮሐንስ አራተኛ ፣ አቡነ አትናቴዎስ ሦስተኛ ፣ አቡነ ሺኖዳ ሦስተኛ ይገኛሉ ።

ለመላ የግብጽ ሕዝብ (ዜጋ) የሃይማኖት ነጻነት ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ የኮፕት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችንና የሰንበት (የእሑድ) ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት ፣ ሕፃናትን ፣ ወጣቶችን ፣ ምእመናንንና ካህናትን በትጋት አስተምራለች ። አሁንም በማስተማር ላይ ናት ። ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት የገበዩት ካህናትና ምእመናን ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ በማገልገል ላይ ናቸው ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ የተዋሕዶ እምነት ተከታይ ካልሆኑት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት እራሷን አግልላ ስትኖር በእኩልነት መንፈስ እርስ በእርስ ለመረዳዳትና ክርስትናን ለማጠናከር በሃያኛው መቶ ዘመን ለተጀመረው ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ንቅናቄ (ጉባኤ ፣ ማኅበር) እንደ ሌሎች የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት አባል በመሆን በየጊዜው በሚደረጉት ጉባኤዎች በመካፈል የተቻላትን አስተዋጽኦ ታደርጋለች ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ባደረገችው በሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ (1962—1965) ላይም በተመልካችነት ተገኝታለች ። እንዲሁም አዲስ አበባ ውስጥ እንደ ኢትዮጵያ አቈጣጠር በ1957 ዓ·ም በተደረገው የኦርየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ላይ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ተካፍላለች ። ይህም ጉባኤ በእምነት አንድ በሆኑት በአምስቱ የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት የተካሄደ ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ የመጀመሪያው መሆኑ ነው ።


www.ethiopianorthodox.org

## ተ) የእስክንድርያ (የኮፕት) ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርኮች

| ተራ ቁጥር | የፓትርያርኮች ስም | የተሾሙበት ዓ.ም | በፓትርያርክነት ያገለገሉበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | ወንጌላዊው ማርቆስ ። የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሥራች | 61 | 7 ዓመት ከ8 ወር |
| 2 | አባ አንያኑ | 64 | 22 ዓመት ከ7ወር |
| 3 | " ሜሊዮስ | 94 | 12 ዓመት ከ9 ወር |
| 4 | " ከርዶኖስ | 108 | 10 ዓመት ከ9 ወር |
| 5 | " ፕሪሙስ | 120 | 12 ዓመት ከ 1 ወር |
| 6 | " ዮስቱስ | 132 | 10 ዓመት ከ10 ወር |
| 7 | " አማኒዮስ | 143 | 11 ዓመት ከ3 ወር |
| 8 | " ማሪአኑስ | 154 | 9 ዓመት ከ2 ወር |
| 9 | " ክላዲአኑስ | 163 | 14 ዓመት ከ6 ወር |
| 10 | " አግሪፒኑስ | 177 | 11 ዓመት ከ7 ወር |
| 11 | " ዩሊአኑስ | 189 | 10 ዓመት ከ1 ወር |
| 12 | " ዲሜጥሮስ ተካሌ ወይን | 199 | 22ዓመት ከ7 ወር |
| 13 | " ሔራክላስ | 232 | 16 ዓመት ከ1 ወር |
| 14 | " ዲዮናሲዮስ | 249 | 19 ዓመት ከ9 ወር |
| 15 | " ማክሲሙስ | 270 | 12 ዓመት ከ7 ወር |
| 16 | " ቴኦናስ | 282 | 9 ዓመት ከ9 ወር |
| 17 | " ጴጥሮስ ተፍጻሜ ሰማዕት | 293 | 10 ዓመት ከ11 ወር |
| 18 | " አኪላስ | 303 | —— 6 ወር |
| 19 | " እለእስክንድሮስ (አንደኛ) | 303 | 22 ዓመት ከ10 ወር |
| 20 | " አትናቴዎስ ሐዋርያዊ | 326 | 46 ዓመት—— |
| 21 | " ጴጥሮስ (ሁለተኛ) | 372 | 5 ዓመት ከ9 ወር |
| 22 | " ጢሞቴዎስ (አንደኛ) | 378 | 6 ዓመት ከ5 ወር |
| 23 | " ቴዎፍሎስ | 384 | 27 ዓመት ከ2 ወር |
| 24 | " ቄርሎስ ዓምደ ሃይማኖት | 412 | 31 ዓመት ከ8 ወር |
| 25 | " ዲዮስቆሮስ (አንደኛ) | 443 | 14 ዓመት ከ2 ወር |


www.ethiopianorthodox.org

| | | | |
|---|---|---|---|
| 26 | ” ጢሞቴዎስ (ሁለተኛ) | 458 | 22 ዓመት ከ11 ወር |
| 27 | ” ጴጥሮስ (ሦስተኛ) | 480 | 8 ዓመት ከ3 ወር |
| 28 | ” አትናቴዎስ (ሁለተኛ) | 489 | 6 ዓመት ከ10 ወር |
| 29 | ” ዮሐንስ (አንደኛ) | 496 | 8 ዓመት ከ7 ወር |
| 30 | ” ዮሐንስ (ሁለተኛ) | 505 | 11 ዓመት ——— |
| 31 | ” ዲዮስቆሮስ (ሁለተኛ) | 516 | 2 ዓመት ከ4 ወር |
| 32 | ” ጢሞቴዎስ (ሦስተኛ) | 519 | 17 ዓመት ከ4 ወር |
| 33 | ” ቴዎዶሲዮስ (አንደኛ) | 536 | 31 ዓመት ከ4 ወር |
| 34 | ” ጴጥሮስ (አራተኛ) | 567 | 2 ዓመት ——— |
| 35 | ” ዳሚአኖስ | 570 | 35 ዓመት ከ11 ወር |
| 36 | ” አናስታሲዮስ | 606 | 12 ዓመት ከ6 ወር |
| 37 | ” አንድሮኒኩስ | 619 | 6 ዓመት ——— |
| 38 | ” ቤኒአሚን (አንደኛ) | 625 | 39 ዓመት ——— |
| 39 | ” አጋቶን | 664 | 16 ዓመት ከ9 ወር |
| 40 | ” ዮሐንስ (ሦስተኛ) | 681 | 8 ዓመት ከ1 ወር |
| 41 | ” ይስሐቅ | 689 | 2 ዓመት ከ11 ወር |
| 42 | ” ስምዖን (አንደኛ) | 692 | 7 ዓመት ከ8 ወር |
| 43 | ” እለእስክንድሮስ (ሁለተኛ) | 703 | 24 ዓመት ከ9 ወር |
| 44 | ” ኮዝማ (አንደኛ) | 728 | 1 ዓመት ከ4 ወር |
| 45 | ” ቴዎዶሩስ | 729 | 11 ዓመት ከ7 ወር |
| 46 | ” ሚካኤል (አንደኛ) | 743 | 23 ዓመት ከ6 ወር |
| 47 | ” ሜና (አንደኛ) | 766 | 8 ዓመት ከ10 ወር |
| 48 | ” ዮሐንስ (አራተኛ) | 776 | 22 ዓመት |
| 49 | ” ማርቆስ (ሁለተኛ) | 798 | 20 ዓመት ከ3 ወር |
| 50 | ” ያኮቡስ | 818 | 10 ዓመት ከ9 ወር |
| 51 | ” ስምዖን (ሁለተኛ) | 829 | 7 ወር |
| 52 | ” ዮሳብ (አንደኛ) | 831 | 17 ዓመት ከ11 ወር |
| 53 | ” ሚካኤል (ሁለተኛ) | 849 | 1 ዓመት ከ4 ወር |
| 54 | ” ኮዝማ (ሁለተኛ) | 850 | 7 ዓመት ከ7 ወር |
| 55 | ” ሺኖዳ (አንደኛ) | 858 | 11 ዓመት ከ3 ወር |
| 56 | ” ሚካኤል (ሦስተኛ) | 869 | 35 ዓመት ከ1 ወር |
| 57 | ” ገብርኤል (አንደኛ) | 908 | 11 ዓመት ——— |


www.ethiopianorthodox.org

| | | | |
|---|---|---|---|
| 58 | ” ኮዝማ (ሦስተኛ) | 919 | 12 ዓመት ——— |
| 59 | ” ማካሪ (አንደኛ) | 931 | 20 ዓመት ——— |
| 60 | ” ቴዎፋኒዮስ | 951 | 4 ዓመት ከ8 ወር |
| 61 | ” ሚና (ሁለተኛ) | 956 | 17 ዓመት ከ11 ወር |
| 62 | ” አብራም (አንደኛ) | 976 | 3 ዓመት ከ6 ወር |
| 63 | ” ፊሎቴዎስ (አንደኛ) | 979 | 24 ዓመት ከ7 ወር |
| 64 | ” ዘካርያ (አንደኛ) | 1004 | 27 ዓመት ከ11 ወር |
| 65 | ” ሺኖዳ (ሁለተኛ) | 1032 | 14 ዓመት ከ7 ወር |
| 66 | ” ክርስቶዱሎስ | 1047 | 22 ዓመት ከ8 ወር |
| 67 | ” ቄርሎስ (ሁለተኛ) | 1078 | 14 ዓመት ከ6 ወር |
| 68 | ” ሚካኤል (አራተኛ) | 1092 | 9 ዓመት ከ7 ወር |
| 69 | ” ማካሪ (ሁለተኛ) | 1102 | 27 ዓመት ከ1 ወር |
| 70 | ” ገብርኤል (ሁለተኛ) | 1130 | 14 ዓመት ከ3 ወር |
| 71 | ” ሚካኤል (አምስተኛ) | 1144 | —— 9 ወር |
| 72 | ” ዮሐንስ (አምስተኛ) | 1146 | 18 ዓመት ከ10 ወር |
| 73 | ” ማርቆስ (ሦስተኛ) | 1165 | 22 ዓመት ከ6 ወር |
| 74 | ” ዮሐንስ (ስድስተኛ) | 1188 | 26 ዓመት ከ11 ወር |
| 75 | ” ቄርሎስ (ሦስተኛ) | 1234 | 7 ዓመት ከ9 ወር |
| 76 | ” አትናቴዎስ (ሦስተኛ) | 1250 | 11 ዓመት ከ1 ወር |
| 77 | ” ገብርኤል (ሦስተኛ) | 1269 | 2 ዓመት ከ2 ወር |
| 78 | ” ዮሐንስ (ሰባተኛ) | 1271 | 23 ዓመት ——— |
| 79 | ” ቴዎዶሲዮስ (ሁለተኛ) | 1294 | 6 ዓመት ከ7 ወር |
| 80 | ” ዮሐንስ (ስምንተኛ) | 1300 | 20 ዓመት ——— |
| 81 | ” ዮሐንስ (ዘጠንኛ) | 1320 | 6 ዓመት ከ5 ወር |
| 82 | ” ቢኒያሚን (ሁለተኛ) | 1327 | 11 ዓመት ከ8 ወር |
| 83 | ” ጴጥሮስ (አምስተኛ) | 1340 | 8 ዓመት ከ6 ወር |
| 84 | ” ማርቆስ (አራተኛ) | 1350 | 14 ዓመት ከ5 ወር |
| 85 | ” ዮሐንስ (ዐሥረኛ) | 1364 | 6 ዓመት ከ2 ወር |
| 86 | ” ገብርኤል (አራተኛ) | 1370 | 8 ዓመት ከ3 ወር |
| 87 | ” ማቴዎስ (አንደኛ) | 1378 | 30 ዓመት ከ5 በወር |
| 88 | ” ገብርኤል (አምስተኛ) | 1409 | 19 ዓመት ከ8 ወር |
| 89 | ” ዮሐንስ (ዐሥራ አንደኛ) | 1428 | 24 ዓመት ከ11 ወር |



www.ethiopianorthodox.org

| | | | |
|---|---|---|---|
| 90 | ” ማቴዎስ (ሁለተኛ) | 1453 | 13 ዓመት ——— |
| 91 | ” ገብርኤል (ስድስተኛ) | 1466 | 8 ዓመት ከ10 ወር |
| 92 | ” ሚካኤል (ስድስተኛ) | 1477 | 1 ዓመት —— |
| 93 | ” ዮሐንስ (ዐሥራ ሁለተኛ) | 1480 | 3 ዓመት ከ4 ወር |
| 94 | ” ዮሐንስ (ዐሥራ ሦስተኛ) | 1483 | 40 ዓመት ከ10 ወር |
| 95 | ” ገብርኤል (ሰባተኛ) | 1526 | 43 ዓመት——— |
| 96 | ” ዮሐንስ (ዐሥራ አራተኛ) | 1573 | 15 ዓመት ከ4 ወር |
| 97 | ” ገብርኤል (ስምንተኛ) | 1590 | 11 ዓመት——— |
| 98 | ” ማርቆስ (አምስተኛ) | 1610 | 10 ዓመት——— |
| 99 | ” ዮሐንስ (ዐሥራአምስተኛ) | 1621 | 10 ዓመት——— |
| 100 | ” ማቴዎስ (ሦስተኛ) | 1631 | 10 ዓመት——— |
| 101 | ” ማርቆስ (ስድስተኛ) | 1650 | 10 ዓመት——— |
| 102 | ” ማቴዎስ (አራተኛ) | 1660 | 14 ዓመት ከ8 ወር |
| 103 | ” ዮሐንስ (አሥራ ስድስተኛ) | 1676 | 42 ዓመት ከ3 ወር |
| 104 | ” ጴጥሮስ (ስድስተኛ) | 1718 | 7 ዓመት ከ6 ወር |
| 105 | ” ዮሐንስ (ዐሥራ ሰባተኛ) | 1727 | 18 ዓመት ከ3 ወር |
| 106 | ” ማርቆስ (ሰባተኛ) | 1745 | 24 ዓመት——— |
| 107 | ” ዮሐንስ (ዐሥራ ስምንተኛ) | 1770 | 6 ዓመት ከ7 ወር |
| 108 | ” ማርቆስ(ስምንተኛ) | 1797 | 13 ዓመት ከ2 ወር |
| 109 | ” ጴጥሮስ (ሰባተኛ) | 1810 | 42 ዓመት ከ3 ወር |
| 110 | ” ቄርሎስ (አራተኛ) | 1854 | 6 ዓመት ከ8 ወር |
| 111 | ” ዲሜጥሮስ (ሁለተኛ) | 1862 | 7 ዓመት ከ7 ወር |
| 112 | ” ቄርሎስ (አምስተኛ) | 1874 | 53 ዓመት ከ 9 ወር |
| 113 | ” ዮሐንስ (ዐሥራ ዘጠነኛ) | 1929 | 13 ዓመት ከ6 ወር |
| 114 | ” ማካሪ (ሦስተኛ) | 1944 | 1 ዓመት ከ6 ወር |
| 115 | ” ዮሳብ (ሁለተኛ) | 1946 | 10 ዓመት ከ5 ወር |
| 116 | ” ቄርሎስ (ስድስተኛ) | 1959 | 11 ዓመት ከ10 ወር |
| 117 | ” ሺኖዳ (ሦስተኛ) | 1971 | አሁን የእስክንድርያ ን ቤተ ክርስቲያን በመ ምራት ላይ ያሉት ፓት ርያርክ ናቸው። |



www.ethiopianorthodox.org

<u>ማሳሰቢያ</u>

(1) አባ አንያኑ የተሾመው ወንጌላዊው ማርቆስ በሕይወት ሳለ ሲሆን፣ ሌሎች ግን የተሾሙት በየጊዜው ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩት ፓትርያርኮች ፈንታ እየተመረጡ ነበር። አልፎ አልፎ ምርጫዎች በተለያዩ ምክንያቶች በዘገዩ ቊጥር መንበረ ፓትርያርኩ በተጠባባቂ አባቶች ሲመራ የቆየባቸው ጊዜዎች ነበሩ።

(2) ከዚህ በላይ የተጻፈውን የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርኮች ስም ዝርዝር ያገኘሁት የኮፕቶች ታሪክ በሚል ርእስ በኢሪስ ሀቢብ ኤል ማስሪ በእንግሊዝኛ በ1978 ዓ.ም ከተጻፈው መጽሐፍ ከገጽ 563 -566 ነው።

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፪

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

### የክርስትና ዜናና እምነት ወደ ኢትዮጵያ መግባት ።

ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመላ ክርስትናን የተቀበለ በ4ኛው መቶ ዘመን ቢሆንም ቀደም ሲል በ35 ዓ·ም የክርስትናን እምነት ኢትዮጵያ ተቀብላ ነበር ። ይኸውም በ35 ዓ·ም የኢትዮጵያ ንግሥት የህንደኬ በጅሮንድ (ጃንደረባ) ኢየሩሳሌም ደርሶ በኦሪቱ ልማድ በዓለ ፋሲካን አክብሮ ወደ ጋዛ በምትወስደው መንገድ በኩል አድርጎ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ፡ ፊልጶስ አግኝቶ ስለ ጌታ ወደዚህ ዓለም መምጣት ፡ ስለሞቱ ፡ ስለ ትንሣኤውና ስለ ሥርዓተ ጥምቀት አስረድቶና በክርስቶስ አሳምኖ አጠመቀው ። ጃንደረባውም ከፊልጶስ የተማረውን የክርስትና ትምህርት ዜና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሰማ ። ስለዚህ ከ35 ዓ·ም እስከ 330 ዓ·ም ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኦሪት እምነቱ ጋር ጥምቀትን ተቀብሎ ቈየ ።

እስከ ዛሬ ድረስ በክርስቲያኖች ዘንድ የሚፈጸሙት ከሕገ ኦሪት የተወረሱት እንደ ታቦት ፡ ግዝረት ፡ የአሣማ ሥጋ አለመብላትና የመሳሰሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኦሪት ወደ ክርስትና እምነት ሲሸጋገር የጠበቃቸው ናቸው ።

ከ4ኛው መቶ ዘመን አጋማሽ እስከ 5ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ድረስ የኖረው ሩፊኑስ የተባለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ስለ ክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ መግባት የሚከተለውን ጽፏል ።

በ4ኛው መቶ ዘመን አብርሃና አጽብሐ(ክርስትናን ከመቀበላቸው በፊት ኢዛና ሳይዛና ይባሉ ነበር) የተባሉ ወንድማማቾች አክሱም ንግሠው ሳለ ፡ ከአንቱ ከፈላስፋው ከመሮፒዎስ ጋር ህንድን ለመጎብኘት ሲጓዝ መርከባቸው ስለሰመጠች ፡ ከወንድሙ ከሲድራኮስ ጋር ከሞት ተርፎ ምጽዋ አጠገብ የተገኘው ፡ የጢሮስ ተወላጅ ግሪካዊው ፍሬምና ጦስ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ወንጌልን እየተማረ ያደገ ስለነበረ ፡ ከኦሪቱ ሊቀ ካህናት ከእንበረም ጋር ተመካክሮ የሚያስተምር ፡ የሚያጠምቅና



www.ethiopianorthodox.org

የሚያቈርብ ጳጳስ ከእስክንድርያ ለማምጣት ተላከ ። ወደ እስክንድርያ የተላከ በኢትዮጵያዊነቱ እንጂ በግሪክነቱ አልነበረም ። የእስክንድርያው ፓትርያርክ አትናቴዎስም የኢትዮጵያን ቋንቋና ልማድ ስለምታውቅ አንተው ጳጳስና ሐዋርያ ሁን ብሎ ሰላማ በሚል ስም ማዕርገ ጵጵስና ሰጥቶ በ330 ዓ·ም ወደ ኢትዮጵያ ሰደደው ይላል ።

እሱም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መንበረ ጵጵስናውን አክሱም ላይ አድርጎ በሀገራችን የወንጌልን ብርሃን በሰፊው ስለገለጸ ከሣቴ ብርሃን ተባለ ። ከዚያም በኋላ በፊት የብሉይ ሊቀ ካህናት የነበረውን ኢትዮጵያዊ ውን እንበረምን ሕዝበ ቀድስ የሚል ስም ሰጥቶ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾመው ።

እንዲሁም በ4ኛው መቶ ዘመን አጋማሽ ላይ የትልቁ ቈስጠንጢኖስ ልጅ ኮንስታንቲዮስ (ቊንስጣ) የተባለው አርዮሳዊ ንግሥ ሳለ የአርዮስን ትምህርት ተቀዋሚ የነበረውን ቅዱስ አትናቴዎስን ወደ ግዞት ልኮ በምትኩ አባ ጊዮርጊስ የተባለውን አርዮሳዊ የእስክንድርያ ፓትርያርክ አድርጎ ሾመው ። ከዚያ በኋላ ኮንስታንቲዮስ በቅዱስ አትናቴዎስ እጅ የጵጵስና ማዕርግ የተቀበለው አቡነ ሰላማ ወደ እስክንድርያ ሄዶ በአቡነ ጊዮርጊስ አማካይነት የአርዮስን እምነት እንዲቀበል የሚጠይቅ ደብዳቤ ቴዎፍሎስ በተባለ ቄስ እጅ ለኢትዮጵያ ነገሥታት ለአብርሃና ለአጽብሐ ልኮ ነበር ። ነገር ግን ነገሥታቱም ሆኑ አባ ሰላማ ያን የተሳሳተ መልእክት ሳይቀበሉት ቀሩ ። ስለዚህ አባ ሰላማ ቅዱስ አትናቴዎስ ያስተማረውን በኒቅያ ጉባኤ የተወሰነውን ቀጥተኛ እምነት በኢትዮጵያ ማስፋፋቱን ቀጠለ ።

አባ ሰላማ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጳጳስ በመሆን አክሱም ውስጥ ባለ 13 መቅደስ በጽዮን ማርያም ስም የሚጠራና በየቦታውም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሠራ ። ለቀሳውስትና ለዲያቆናትም ማዕርገ ክህነት ሰጠ ። እንዲሁም የክርስትና እምነት እንዲስፋፋ ከማድረጉም ሌላ ሐዲስ ኪዳንን ከግሪክ (ከዮናኒ ፡ ከጽርዕ) ወደ ግዕዝ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጋር ተርጒሞአል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለአቡነ ሰላማ የቅዱስነት ማዕርግ ሰጥታ በዓሉን ሐምሌ 26 ቀን ታከብራለች ።

በዚህ አኳኋን ፊት በወንጌላዊው ማቴዎስና በሕንደኬ ጃንደረባ ተሰብካ የነበረች ክርስትና በኢትዮጵያ ተስፋፋች ። ከዚህም ጊዜ ጀምሮ



www.ethiopianorthodox.org

እስከ 20ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ከግብጻውያን ብቻ ጳጳሳት ሲሾሙ ቈይተዋል ። ይሁን እንጂ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጳጳስ ፡ አቡነ ፊልጶስ ኤጲስ ቆጶስ ሆነው እንደተሾሙ ታሪክ ይናገራል ።

ተስዓቱ ቅዱሳን ። ከአቡነ ሰላማ ቀጥለው ሚናስ የተባሉት ግብጻዊ ጳጳስ ተሹመው መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ቢቀጥሉም ቅሉ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ጐልቶ የሚነገረው በ5ኛው መቶ ዘመን ላይ በዚያን ጊዜ የሮማ ግዛት ከነበሩት ከሶርያ ፡ ከቍስጥንጥንያና ከልዩ ልዩ ሀገሮች የዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ነው ።

የስም ዝርዝራቸውም የሚከተለው ነው።

1ኛ/ አባ አሌፍ
2ኛ/ ” ጽሕማ
3ኛ/ ” ዐረጋዊ(ዘሚካኤል)
4ኛ/ ” አፍጼ
5ኛ/ ” ገሪማ(ይስሐቅ)
6ኛ/ ” ጳንጠሌዎን
7ኛ/ ” ሊቃኖስ
8ኛ/ ” ይምዓታ
9ኛ/ ” ጉባ

እነዚህ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ዋናው ምክንያት የሚከተለው ነው ።

የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በኬልቄዶን ጉባኤ የአንድ ባሕርይን እምነት በመደገፉ ምክንያት በንጉሡ በመርቅያንና በንግሥቲቱ በብርክልያ ትእዛዝ በደሴተ ጋንግራ ውስጥ ታሥሮ በመሠቃየት ላይ ሳለ ከዐረፈ በኋላ ፡ እነዚህ ቅዱሳን የአንድ ባሕርይን እምነት በመከተላቸውና በማስተማራቸው ምክንያት የሁለት ባሕርይን እምነት የሚከተሉትን ወገኖች የሚደግፈው የሮማ ንጉሥ ከፍ ያለ ሥቃይ ስላደረሰባቸው በእምነት መሰሎቻቸው የሆኑ ክርስቲያኖች ወደሚኖሩባት ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው መጡ ። በሰሜን ክፍለ ሀገር (በትግራይ) በአት መሥርተው ፡ ገዳም አቅንተው ኖረዋል ።

በገዳመ አስቄጥስ የተጀመረውን (የተመሠረተውን) ሥርዓት ምንኵስና ወደ ኢትዮጵያ ያመጡና ያስፋፉ ተስዓቱ ቅዱሳን ናቸው ። በተለይ አባ ዐረጋዊ የአባ ጳኵሚስ ተከታይ የነበረው የአባ ቴዎድሮስ ደቀ


www.ethiopianorthodox.org

መዝሙር ስለነበር በገዳመ አስቄጥስ የተመሠረተውን ሥርዓት ምንኩስና ጠንቅቆ ያውቅ ነበር ። ስለዚህ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን የምንኩስናን ሥርዓት ደብረ ዳሞ ገዳም በሚገባ አቋቋሙ ።

ቀደም ሲል ከባቢሎን ምርኮ ጀምሮ በተለይም በ70 ዓ·ም ጥጦስ ኢየሩሳሌምን ባጠፋበት ጊዜ ተሰደው ደቡብ ዓረብ (የመን) የገቡ አይሁድ ድሁኖቫስ (ፊንሐስ) በተባለው ሰው እየተመሩ በ6ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሀገረ ናግራን በነበሩ ክርስቲያኖች ላይ ከፍ ያለ መከራና ሥቃይ አደረሱባቸው ። ይኸው ዜና እንደተሰማ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዐፄ ካሌብ መሪነት በአዶሊስ ወደብ በኩል ዘምቶ የድሁኖቫስን ሠራዊት በመውጋት አሸንፎ ደቡብ ዓረብን ያዘ ። በስደት ላይ የነበሩ ክርስቲያኖች ወደ ቀድሞ ሰፍራቸው እንዲመለሱ ፣ በግዴታ እምነታቸውን የለወጡ ወደ ክርስትና እምነታቸው እንዲመለሱ ታወጀ ።

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አባ ጢሞቴዎስ 3ኛ እና የቍስጥንጥንያው ንጉሥ ዩስጢንያኖስ በክርስቲያኖች ጠላት ላይ የኢትዮጵያ ሠራዊት ስለተቀዳጀው ድል የተሰማቸውን ደስታ ለዐፄ ካሌብ ገልጸዋል ። ከዚያ በኋላ በደቡብ ዓረብ የካሌብ እንደራሴ በመሆን ተሹሞ ያስተዳድር የነበረው አብርሃም ሳና ውስጥና በየቦታው ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንጾ ነበር ። እንዲሁም እስልምና በደቡብ ዓረብ ከመጀመሩ በፊት አካባ (ከሰማይ የወረደ ድንጋይ ፣ ከሰማይ የወረደ ድንጋይ ያለበት ሰፍራ) የተባለውን የጣዖት መቅደስ ለማፍረስ ወደ መካ ዘምቶ ሳይሳካለት መቅረቱ ይነገራል ። ከጊዜ በኋላ ግን ደቡብ ዓረብን ፋርሶች ወረው ኢትዮጵያውያንን ስለፈጅዋቸው ግዛቱ ተቋረጠ ።

በ6ኛው መቶ ዘመን በኢትዮጵያና በቍስጥንጥንያ መንግሥታት መካከል የጠበቀ ወዳጅነት ተመሥርቶ ስለነበር የአንድ ባሕርይን ወገኖች ትደግፍ በነበረችው በዩስጢንያኖስ ሚስት በእቴጌ ቴዎዶራ ድጋፍ ከኢትዮጵያ ለሚሄዱ ምእመናንና መነኰሳት ማረፊያ የሚሆኑ ቦታዎች ግብጽና ኢየሩሳሌም ውስጥ ተገዝተው ነበር ።

በዚሁ ዘመን አክሱማዊው ቅዱስ ያሬድ የተባለው ባለዜማ (ማኅሌታይ) ተነሣ ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት ጀምራ የምትገለገልባቸውን ልዩ ልዩ ጽዋትወ ዜማዎች ግዕዝ ፣ እዝል ፣ አራራይ በሚል ስልት ከአማረ ጣዕመ ዜማና ጥልቅ ምሥጢር ጋር ደርሶአል ። ከጊዜ በኋላ ግን አንዳንድ የዜማ መምህራን ለያሬድ ዜማ ልዩ ልዩ ስልትና ሕግ


www.ethiopianorthodox.org

ስላወጡለት የቆማ ፡ የቤተልሔም ፡ አጫብር ፡ ወንጨሬ ፡ ተጕለቴ ፡ ዋድሌ በተባሉ ክፍሎች ተከፍሎ ይጠራል ።

ቅዱስ ያሬድ የጣዕመ ዜማ ሊቅ ብቻ ሳይሆን ምሥጢረ ሃይማኖትን፥ ሥነ ምግባርን በጥልቅ የመረመረና እንደ አንቀጸ ብርሃን ፡ ድጓ ፡ ዝማሬና መዋሥዕት የመሳሰሉትን መጻሕፍት የደረሰ ታላቅ ሊቅ ነው ። የአቡነ ዐረጋዊ ደቀ መዝሙር ስለነበረ በተሰዓቱ ቅዱሳን ትምህርት ተመርቶ በመመነን ስሜን ወደሚገኝ ከፍተኛ ተራራ ላይ ወጥቶ የመጨረሻዎቹን ዘመኑን በምንኵስና እንዳሳለፋቸው ይነገራል ።

ከግራኝ ወረራ በኋላ የያሬድ ድጓ ጠፍቶ ሳለ ተፈልጎ ቤተ ልሔም ስለተገኘ ፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቤተ ልሔም የድጓ ማስመስከሪያ ሆናለች ።

ከ7ኛው እስከ 9ኛው መቶ ዘመን በነበሩት ጊዜዎች የዓረቦች መነሣትና የእስልምና መስፋፋት በኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ችግር አስከተለ ። ይኸውም መሐመድ ካረፈ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የክርስትና ትምህርት መፍለቂያ የነበሩትን ኢየሩሳሌምንና ግብጽን ዓረቦች (እስላሞች) በጦር ኃይል ያዙ ። ቀጥለውም የኢትዮጵያን የባሕር በር ቀይ ባሕርን ያዙ ።

ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ጳጳሳት ያለ ብዙ ችግር በቀላሉ ታስመጣ ነበር ። ግብጽ በዓረቦች እጅ ከወደቀች በኋላ ግን በልዩ ልዩ ምክንያቶች ጳጳሳትን እንደልብ ለማስመጣት ስላልቻለች አልፎ አልፎ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ችግር ይደርስ ነበር ። በነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ታደርገው የነበረው ግንኙነት ከሞላ ጎደል ተቋረጠ ። ከ650 እስከ 1270 ዓ·ም ድረስ የነበረው ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የጨለማ ዘመን ተብሎ ይጠራል ።

በ10ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሚናስና ፊቂጦር የተባሉ ምግባራቸው የከፋ አታላይ ግብጻውያን መነኰሳት ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ከቆዝሞስ(ከኮዝማ ሦስተኛ) ሚናስ ጳጳስ ፥ ፊቂጦር የጳጳሱ ረዳት ሆነው ተሹመዋል የሚል የሹመት ደብዳቤ ይዘናል ብለው ኢትዮጵያ ገቡ ። እነሱም የለየላቸው አጭበርባሪዎች ስለነበሩ ንጉሡንና ካህናቱን ለማታለል በመቻላቸው በሕጋዊ መንገድ የተሾሙት አቡነ ጴጥሮስ ተሽረው ሚናስ ተሾመ ። ፓትርያርኩም ይህንኑ ሕገ ወጥ ሹመት እንደሰሙ ሚናስን አውግዘው ከግብጽ ለኢትዮጵያ ጳጳስ እንዳይላክላት



www.ethiopianorthodox.org

ወሰኑ ። ይህንኑ ውሳኔ ከቆዝሞስ ቀጥለው የተነሡ አራት ፓትርያርኮች በሥራ ላይ አዋሉት ። በዚህ አኳኋን የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ሥልጣነ ክህነት የሚሰጥ ጳጳስ ሳያገኝ ለ60 ዓመታት ያህል በመቸገር ከቈየ በኋላ ፊላታዎስ (ፊሎቴዎስ) የተባሉት ፓትርያርክ ለኢትዮጵያ ጳጳስ በመላካቸው ችግሩ ተቃለለ ።

ቀደም ሲል ከቅድስት ሀገር የመጡት እስራኤላውያን ከኢትዮጵያ ውያን ጋር በጋብቻ ተቀላቅለው የኦሪትን እምነት ተከትለው ሲኖሩ ፣ በ4ኛው መቶ ዘመን ሊቀ ካህናቱ እንበረምና ብዙዎቹ ሰዎች ክርስትናን ተቀበሉ ። ጥቂቶች ግን በኦሪት እምነታቸው በመጽናት ክርስትናን አንቀበልም ስላሉ ከክርስቲያኖች ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ምክን ያት አክሱምን እየለቀቁ በሰሜንና በወገራ ፣ በወልቃይትና በላስታ ዙሪያ ባሉት ሀገሮች ተበትነው ስለኖሩና ከቅድስት ሀገርም ፈልሰው ስለመጡ ፈላሾች ተባሉ ። እንዲሁም በየጊዜው ከቅድስት ሀገር እየተሰደዱ የመጡ አይሁድ ቀድሞ ከነበሩት ጋር ተደባለቁ ። ስለዚህ ቊጥራቸውና ኃይላቸው እየበዛና እየጠነከረ ስለሄደ በ10ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ በዮዲት መሪነት አክሱም ውስጥ በክርስቲያኖች ላይ ተነሡ ። የክርስትናን ሃይማኖት አጥፍተው የአይሁድን እምነት ለመተካት ስለፈ ለጉ በተለይ በትግራይ ክፍለ ሀገር የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናትና መጻሕፍት አቃጠሉ ። ካህናትንና ክርስቲያኖችንም ገደሉ ። በአብርሃና በአጽብሐ ዘመን የተሠራውን የመጀመሪያውንና ታላቁን የአክሱም ጽዮንን ቤተ ክርስቲያን ፣ በአካባቢው ከነበሩት ሐውልቶችና መታሰቢያ ዎች አብዛኞችን አወደሙ ። ጽላተ ሙሴን ግን ይዘዋት ስለተሰደዱ ሊያገኟት አልቻሉም ። በዚህ አኳኋን ለ40 ዓመታት ያህል ክርስቲያኑን ሕዝብ ሲያሠቃዩ ቈይተው በክርስቲያኖች ድል ስለተመቱ መከራው ተግ አለ ።

በ12ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ በቅዱስ ሀርቤ ዘመነ መንግሥት ቤተ ክርስቲያናችን ከሊቃውንቶቿ መካከል ሰባት መነኰሳት መርጣ ጳጳሳት ለመሾም በመሻት ለእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያ ርክ ለአቡነ ገብርኤል ሁለተኛ ጥያቄ አቅርባ ነበር ። ነገር ግን ክርስትናን ለማስፋፋት ስትል በቀና መንፈስ በመመራት ያቀረበችውን ጥያቄ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን መሪ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ የነበራቸው ሥልጣንና በየጊዜው የሚላክላቸው ገጸ በረከት እንዳይቀርባቸው (እንዳይ



www.ethiopianorthodox.org

ቋረጥባቸው) በማሰብ ስላልተቀበሉት ፍጻሜ ሳያገኝ ቀረ ። ለወደፊቱም የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከሥራቸው ለማቄየት በማሰብ አቡነ ገብርኤል በፍትሐ ነገሥት ውስጥ "የኢትዮጵያ ሰዎች ከዐዋቂዎቻቸው ጳጳሳትን እንዳይሾሙ በኒቂያ ጉባኤ ተወስኖአል" የሚል የሐሰት ጽሑፍ አስገብተው አብርሃም ቀሲስ በተባለው ሰው እጅ ወደ ኢትዮጵያ ላኩ ይባላል ።

በ12ኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ላይ ቅዱስ ላሊበላ ላስታ ውስጥ ገዳመ (ደብረ) ሮሐ ከተባለው ስፍራ እንደ ዋሻ ከአለት ድንጋይ አስፈልፍሎ በልዩ ልዩ ቅርፆች ያጌጡ ፡ በርና መስኮት ፡ ጣራና ግድግዳ ያላቸው ዐሥራ አንድ አብያተ ክርስቲያናት በሃያ ዓመት ውስጥ አሠርቷል ። ከነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ ከተፈለፈሉበት ቋጥኝ ተለይተው የተወሰነ ቅርፅ ሲኖራቸው ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከተፈለፈሉበት ቋጥኝ በውጭ በኩል ባይለያዩም ቅሉ የውስጥ ቅርፃቸው በሚገባ ተሠርቷል ። አንዳንዶቹ አብያተ ክርስቲያናት ከውጭ ሲታዩ ዋሻ ይመስላሉ ። ከውስጥ ሲታዩ ግን ቅርፃቸው በሚገባ የተሠራ ነው ።

ዐሥራ አንዱ አብያተ ክርስቲያናት የተሠሩት በአንድ አካባቢ በሚገኙ በተለያዩ ሦስት ስፍራዎች ላይ ነው ።

በአንደኛው ስፍራ ላይ ከቋጥኝ በመፈልፈል የተሠሩት፡

1ኛ/ ቤተ መድኃኔ ዓለም። 2ኛ/ ቤተ ማርያም ።
3ኛ/ ቤተ ደናግል ። 4ኛ/ ቤተ መስቀል ።
5ኛ/ ቤተ ቅዱስ ሚካኤል ። 6ኛ/ ቤተ ጎልጎታ ናቸው ።

በሁለተኛው ስፍራ ላይ ከድንጋይ እየተፈለፈሉ የተሠሩት ደግሞ፡

1ኛ ቤተ አማኑኤል ። 2ኛ/ ቤተ ገብርኤል ።
3ኛ/ ቤተ አባ ሊባኖስ ። 4ኛ/ ቤተ መርቆሬዎስ ናቸው።

በሦስተኛው ስፍራ ከድንጋይ ተፈልፍሎ በመስቀል ቅርፅ የተሠራው ቤተ ክርስቲያን ቤተ ጊዮርጊስ ብቻ ነው ።

እላይ ከተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት መካከል በትልቅነትም ሆነ በውበት የአንደኛነትን ደረጃ ይዞ የሚገኘው የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ነው ።

ከነዚሁ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ላሊበላ ያሠራቸው ዐሥሩን ብቻ ሲሆን ፣ ቤተ አባ ሊባኖስን ግን ያሠራች ባለቤቱ እቴጌ መስቀል



www.ethiopianorthodox.org

ክብራ ናት ይባላል ። በነዚህ አብያተ ክርስቲያናት አጠገብ የሚያልፈው ትንሽ ወንዝ ጌታ በተጠመቀበት በዮርዳኖስ ስም ተሰይሞአል ። ቅዱስ ላሊበላ ሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት በላስታ ዙሪያ አሳንፆአል ።

አብያተ ክርስቲያናቱ የተሠሩበትን ቦታ ቅዱስነት እንደ ኢየሩሳሌም በመቍጠርና ገድሉም እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት የተሳለመ ኢየሩሳሌም ያሉትን ቅዱሳት መካናት እንደተሳለመ ይቈጠርለታል ስለሚል በመላ ኢትዮጵያ በተለይ በጎጃም ፥ በጎንደርና በትግራይ ክፍላተ ሀገር ከሚኖሩት ክርስቲያኖች ብዙዎቹ በያመቱ በልደት ሰሞን ወደ ላስታ እየሄዱ ጸሎታቸውንና አምልኮታቸውን ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ። በዓሉ በልደት ዕለት ደምቆ የሚከበረው ዐሥራ አንዱ ታቦቶች የልደት ዕለት ተባርከው ስለገቡና ቅዱስ ላሊበላም የልደት ዕለት ስለተወለደ ነው ይባላል ።

የውጭ ሀገር ቱሪስቶችም ስለነዚህ አብያተ ክርስቲያናት አስደናቂ ሥራ ከመጻሕፍት ያነበቡትን በዓይናቸው ለማየት ወደ ላስታ በብዛት ይጎርፋሉ ። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በዓለም ከሚገኙት እንደ ግብጽ ፒራሚዶች ከመሳሰሉት ታላላቅ ሥራዎች ጋር የሚወዳደሩ ናቸው ። ለሁሉም የጥንት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ታላቅ ፡ አስደናቂና አኩሪ ሥራዎች ከልብ ለማድነቅ የምንችለው ከመጻሕፍት በማንበብ ብቻ ሳይሆን ወደላስታ ሄደን የአብያተ ክርስቲያናቱን ሥራና ቅርፅ በዓይናችን በመመልከት ጭምር ነው ።

በ13ኛው መቶ ዘመን የተነሡት የአባ ኢየሱስ ሞዓ ደቀ መዝሙር የነበሩት አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሽዋ ክፍለ ሀገር ውስጥ በሚገኙ ልዩ ልዩ አውራጃዎችና በተለይም በዳሞት(በወላይታ) አውራጃ እየዞሩ በትጋት ወንጌልን በማስተማር ብዙ አረማውያንን ወደ ክርስትና እምነት መልሰዋል ። እንዲሁም ፈጠጋር ውስጥ የዶስክ (እንደቃልቻ ፥ ዛር ያለ) አምልኮ ተስፋፍቶ ስለ ነበር ይህንኑ ባዕድ አምልኮ ለማጥፋት ደክመዋል።

በሽዋ ክፍለ ሀገር የሚገኘው ቀደም ሲል ደብረ አስቦ ይባል የነበረው የደብረ ሊባኖስ ገዳም የተገደመው በእርሳቸው ነው ። ደብረ ሊባኖስ ተብሎ የተሰየመው በ15ኛው መቶ ዘመን በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ መሆኑ ይነገራል ። የመጀመሪያው እጨጌም እርሳቸው ነበሩ ። የግብጻዊው ጳጳስ ተግባር ሥልጣነ ክህነት መስጠት ሲሆን ፥ የደብረ ሊባኖሱ ኢትዮጵያዊው እጨጌ ተግባር ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር



www.ethiopianorthodox.org

ማከናወን ነበር ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ጳጳሳት የመሾም መብቷን ከተጎናጸፈች በኋላ ግን ፓትርያርኩ የእጨጌነቱን ሥራ ደርበው ይዘውት ነበር ።

ግብጻዊው ጳጳስ አባ ጌርሎስ(ቄርሎስ) ከዐረፉ በኋላ በመስቀል ጦርነት ፣ እንዲሁም ሳራካን የተባሉት እስላሞች በምድረ ግብጽ ባነሡት ጦርነት ምክንያት ግብጽንና ኢትዮጵያን የሚያገናኘው መንገድ ስለተ ዘጋ፣ከግብጽ ጳጳስ ለማስመጣት ባለመቻሉ አባ ተክለሃይማኖት በምግባር የቀኑ በዕውቀት የበሰሉ ስለነበሩ የኢትዮጵያ ካህናት በጉባኤ ተሰብስበው መርጠው ጳጳስ አድርገው እንደሾሙአቸው ይነገራል ።

በዚሁ ዘመን አባ ኤዎስጣቴዎስ የተባሉ መነኩሴ በተወለዱበት በትግራይ አካባቢ የክርስትናን ትምህርት በሰፊው አስተምረዋል ። ከእርሳቸው ዕረፍት በኋላ ደቀ መዛሙርቶቻቸው ኤርትራ እንደሚገኘው እንደ ደብረ ቢዘን ያሉ ገዳማትን አሠርተዋል ። ክርስትናንም አስፋፍተ ዋል ።

በኢትዮጵያ የመነኰሳት ስያሜ መሠረት የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዛሙርት ቤተ ተክለ ሃይማኖት ሲባሉ ፣ የአባ ኤዎስጣቴዎስ ደቀ መዛሙርት (ተከታዮች) ደግሞ ቤተ ኤዎስጣቴዎስ ይባላሉ ።

በ14ኛው መቶ ዘመን በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ከኢየሩሳሌም ምእመናንና ካህናት በስጦታ ለኢትዮጵያ መንግሥት የተላኩት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰቀል የቀኝ እጁ ያረፈበት ግማደ መስቀልና ልዩ ልዩ ንዋያተ ቅድሳት መስከረም 10 ቀን ኢትዮጵያ ደረሱ ። ግማደ መስቀሉ ደብረ ከርቤ ገዳም በሚገኘው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ካሠራው እግዚአብሔር አብ ከተባለው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀመጠ ። ስለዚህ ቀደም ሲል ክረምት በሚወጣበት መስከረም 25 ቀን ይከበር የነበረው የተቀጸል ጽጌ (የአበባ በዓል) ጌታ የተሰቀለበት ግማደ መስቀል ኢትዮጵያ የገባበትን ቀን ለማስታወሻ እንዲሆን መስከረም 10 ቀን እንዲከበር ተወሰነ ።

ምንጭ እንኳ ክርስቶስ ለተሰቀለበት መስቀል በሀገራችን ክብር መስጠት የተጀመረው ከ4ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ ቢሆንም ቅሉ ከዚህ ጊዜና በተለይም ከ15ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ በሕዝቡ ዘንድ እየተወደደ ስለ ሄደ ምእመናን በእጃቸው ፣ በግንባራቸው ፣ በጌጦቻቸውና በልብሶቻ ቸው ላይ በብዛት የመስቀል ምልክት ማድረግ ጀመሩ ።



www.ethiopianorthodox.org

በ14ኛው መቶ ዘመን በምዕራብ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝና በጣና ሐይቅ አካባቢ ሰባቱ ከዋክብት በተባሉት አበው አማካይነት የክርስትና ትምህርት በሰፊው ተሰበከ ። ብዙ ገዳማትም ተሠርተዋል ።

እንዲሁም እጨጌ ፊልጶስ ከግብጻዊው ጳጳስ ከአቡነ ያዕቆብ የኤጲስ ቆጶስነት ማዕርግ ከተቀበሉ በኋላ የዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት አርአያ በመከተል እርሳቸው እንደ ሊቀ ሐዋርያው እንደ ጴጥሮስ ሆነው ከደብረ ሊባኖስ ዐሥራ አንድ መምህራን (ንቡራነእድ) ልከው በሸዋ ክፍለ ሀገርና በአካባቢው የወንጌል ትምህርት በሰፊው እንዲሰበክና ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሠሩ አድርገዋል ።

ውዳሴ ማርያም ፡ መጽሐፈ ግንዘት ፡ ገድለ ሰማዕታትና የመሳሰሉት መጻሕፍት ከዐረብኛ ወደ ግዕዝ የተተረጐሙ በዚሁ ዘመን መሆኑ ይነገራል ።

በ15ኛው መቶ ዘመን በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ትእዛዝ ልዩ ልዩ የጣዖታት (የዶስክና የዲኖ) አምልኮቶች እንዲቀሩ ተደርጓል ። እንዲሁም ምእመናን ቅዳሜንና እሑድን እኩል በማክበር በነዚሁ ቀኖች ቤተ ክርስቲያን እየተገኙ የክርስትናን ትምህርት እንዲማሩ ፡ ካህናትና ዲያቆናትም ተግተው እንዲያስተምሩ ሥርዓት ተሠርቶ ነበር ።

ከቤተ ክርስቲያን ራቅ ባለ መንገድ አልፈው የሚሄዱ መንገደኞችም ለመስገድ(ለመሳለም) እንዲችሉ የሚረዳና የሚያስታውስ በቤተ ክርስቲያኑ አቅጣጫ መሳለሚያ መስቀል መትከል የተጀመረው በዘርዓ ያዕቆብ ትእዛዝ ነበር ።

ደቂቀ እስጢፋ (የእስጢፋኖስ ተከታዮች ፥ ልጆች) የተባሉት ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ፡ ለቅዱሳንና ለጌታ መስቀል መስገድ አይገባም ብለው የክሕደት ትምህርት ስላስተማሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተወግዘዋል ። በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብም ትእዛዝ የሞት ቅጣት ተፈጽሞባቸዋል ።

የነዚህ ሰዎች ትምህርት ዘግየት ብለው በ16ኛው መቶ ዘመን አውሮፓ ውስጥ ከተነሡት ከፕሮቴስታንቶች እምነት ይመሳሰላል። ይኸው ትምህርታቸው የአይሁድ እምነትም ጠባይ አለው። በዚሁ ዘመን መንፈሳዊ ትምህርት የያዙ ብዙ መጻሕፍት ተደርሰዋል። ተተርጕመዋልም። ለምሳሌ መጽሐፈ ብርሃንና



www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፈ ምእላድ በዐዌ ዘርዓ ያዕቆብ፣ መጽሐፈ ምሥጢር፣ ሰዓታትና አርጋኖን በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ተደርሰዋል። ተአምረ ማርያምም ከዐረብኛ ወደ ግዕዝ የተተረጐመ በዚሁ ዘመን ነው።

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለመጀመሪያ ጊዜ አባ ሚካኤል ፡ አባ ገብርኤልና አባ ዮሐንስ የተባሉ ሦስት ግብጻውያን ጳጳሳት በአንድ ጊዜ ሊያስመጡ ችለዋል ።

በዚሁ ዘመን በሮሙ ፖፕ በኤውጌንዮስ 4ኛ ሰብሳቢነት ፍሎሬንስ ውስጥ በተደረገው የፌራራ ጉባኤ ኢየሩሳሌም ባለው የኢትዮጵያ ገዳም የነበረው አባ ጴጥሮስ የተባለው መነኵሴ በገዳሙ መምህር በአባ ኒቆዲሞስ ተልኮ በጉባኤው ተገኝቶ ነበር ። ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያ ንም የቅዱስ እንጦንስ ገዳም አበምኔት አባ ዮሐንስ በዚሁ ጉባኤ ተካፋይ ሆኖ ነበር ። የጉባኤው ዓላማ የግሪክ ኦርቶዶክስ ፡ የካቶሊክና የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት በመካከላቸው ሰላምን መሥር ተው በእምነት አንድ በመሆን የቱርክን መንግሥት (የእስላሞችን) ኃይል በኅብረት ለመቋቋም እንዲችሉ ለመገፋፋትና ሁሉንም በሮሙ ፖፕ ሥር ለማድረግ የታሰበ ነበር ። ይህንኑ የፖፑን የበላይነት ፍላጎት በመገንዘብ ከግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች አብዛኞቹ የጉባኤውን ሐሳብ ተቃወሙት ። የጉባኤውን ውሳኔ ተቀብለናል ካሉትም መካከል ቍስጥንጥንያ እንደገቡ የቀድሞ ሐሳባቸውን ለውጠው ውሳኔውን የሚቃ ወሙ መሆናቸውን ገለጹ ። አባ ጴጥሮስም በጉባኤው ሐሳብ ሳይስማማ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ ።

በ16ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ ገንኖ በነበረው በቱርክ መንግሥት አነሳሽነትና ድጋፍ በምሥራቅ ኢትዮጵያ በኩል በግራኝ መሐመድ መሪነት ኢትዮጵያን ለመውረር የተሰነዘረውን ሙከራ ለነጻ ነቱ፣ ለሃይማኖቱ ቀናኢ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፖርቱጋሎች ያገኘውን መጠነኛ እርዳታ ከራሱ የተፈጥሮ ወኔ ጋር አቀናጅቶ 15 ዓመታት ያህል ባደረገው መራራ ጦርነት ጠላቱን ድል ነሥቶ ሀገራችንን ነጻ አወጣ ። በወራሪዎች የተደመሰሱት አብያተ ክርስቲያናትም እንደገና ተሠሩ ። እንዲሁም ፖርቱጋሎች ባደረጉት እርዳታ ምክንያት የካቶሊክ እምነት በኢትዮጵያ ሊሰበክና ሊስፋፋ ቻለ ።

በ17ኛው መቶ ዘመን የተነሡት ቅባቶችና ጸጎች ከተዋሕዶዎች ጋር



www.ethiopianorthodox.org

ክርክርን ያዘወትሩ ነበር ። ይኸው ክርክር እስከ 19ኛው መቶ ዘመን መቀጠሉ ይነገራል ። ነገር ግን ዐፄ ቴዎድሮስ ማንኛውም ክርስቲያን የተዋሕዶን እምነት እንዲከተል ፡ የቅባቶችና የጸጎች ትምህርት እንዳይሰበክ ጥብቅ ስለከለከሉ ክርክሩ ቀስ በቀስ እየተዳከመ በመሄዱ ቆመ ።

ከሱስንዮስ በፊት በ16ኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ላይ በነበረው በዘድንግል ዘመነ መንግሥት ክርስቶስ ነኝ የሚል ሐሳዊ መሢሕ ተነሥቶ 12 ሐዋርያት ፡ 72 አርድእትና 36 ቅዱሳት አንስት መርጦ በማስከተል ሲሰብክ ተይዞ ማን እንደሆነ ቢጠየቅ ክርስቶስ ነኝ በማለቱ ስለጸና እርሱና ተከታዮቹ ተገደሉ ።

በ19ኛው መቶ ዘመን ወሎ ክፍለ ሀገር ቦሩ ሜዳ በተደረገው ጉባኤ "ሦስት ልደት" የሚለውን የተሳሳተ እምነት ያስተምሩ የነበሩ ካህናት ተወገዙ ።

ሥልጣነ ክህነት ለመቀበል ግብጻዊው ጳጳስ ወደሚኖርበት መናገሻ ከተማ ከሩቅ ክፍላተ ሀገር በእግር በመጓዝ የሚሠቃየውን ሕዝብ ችግር ለማቃለልና ወንጌልም በሰፊው እንዲሰበክ በማሰብ ዐፄ ዮሐንስ ለእስክንድርያው ፓትርያርክ ለአቡነ ቄርሎስ 5ኛ እንደተለመደው አንድ ሊቀ ጳጳስ ብቻ ሳይሆን ከሊቀ ጳጳሱ ጋር ሌሎች ሦስት ጳጳሳት ጭምር እንዲልኩላቸው ጥብቅ የሆነ መልእክት ላኩላቸው ። ፓትርያርኩም አንድ ጳጳስ ብቻ ይበቃችኋል በማለት ጥያቄውን ባልቀበል በሃይማኖት መሰሎቻችን በሆኑት በአርመኖችና በሶርያውያን እጅ ኢትዮጵያውያን ከራሳቸው ሊቃውንት ጳጳሳት ይሾሙ ይሆናል ብለው በማሰብ በጥያቄው መሠረት አራት ግብጻውያን ጳጳሳትን ወደ ኢትዮጵያ ላኩ ። እነሱም ፡ 1ኛ/ አቡነ ጴጥሮስ የትግራይ ጳጳስ ፡ 2ኛ/ አቡነ ማቴዎስ የሸዋ ጳጳስ ፡ 3ኛ/ አቡነ ሉቃስ የጐጃም ጳጳስ ፡ 4ኛ/ አቡነ ማርቆስ የስሜንና የቤገምድር ጳጳስ ነበሩ ። ሆኖም አቡነ ማርቆስ ወዲያው ስላረፉ ለምእመናን ያበረክታሉ ተብሎ የታሰበው መንፈሳዊ ተግባር ተቋረጠ ።

በ18ኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ላይና በ19ኛው መቶ ዘመን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በነአቡነ ጦቢያስ ገብረ እግዚአብሔርና በነ አባ ያዕቆብ መሪነት ብዙ ሚስዮናውያንን ወደ ኢትዮጵያ ልካ ነበር ። በተለይ በ20ኛው መቶ ዘመን ፋሽስት ኢጣልያ በግፍ ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ ፕሮቴስታንቶችን ከኢትዮጵያ ስላስወጣቻቸው የካቶሊክ ሚስዮናውያን እምነታቸውን እንደልብ ለማስተማርና ለመስበክ ችለው ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

ምንም እንኳ ጀርመናዊው ጴጥሮስ ሄይሊንግ በ17ኛው መቶ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በጎንደር የፕሮቴስታንትን እምነት ቢሰብክም ቅሉ ፕሮቴስታንቶች በብዛት ወደ ኢትዮጵያ መግባት የጀመሩት በ19ኛው መቶ ዘመን ነው ። ለምሳሌ በዚሁ ዘመን "ዘ ቸርች ሚሽኔሪ ሶሳይቲ" የተባለው የፕሮቴስታንት ሚስዮን አባላት የሆኑ ሳሙኤል ጐባትና ክርስቲያን ኩግለር ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው እምነታቸውን ማስተማር ጀምረው ነበር ። የስዊድን ሚስዮን አባላትም ኩናማ ውስጥ ያስተምሩ ነበር ። እንዲሁም የፕሬዝቢቴርያን ቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑ ሚስዮናውያን በ20ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ወንጌልን ይሰብኩ ነበር ። በዚህ አኳኋን ከኢጣልያ ወረራ በፊትና በኋላ ብዙ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ወንጌልን ለማስተማር ኢትዮጵያ ገብተዋል ። የውጭ ሀገር ሚስዮናውያን አረማውያንን እያስተማሩ እንዲያጠምቁ ፣ ለሕዝቡ የትምህርትና የሕክምና አገልግሎት በመስጠት እርዳታቸውን እንዲያበረክቱ ሲፈቀድላቸው ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑትን ወደነሱ እምነት እንዳይለውጡ የሚከለክል ሕግ በ1936 ዓ.ም ወጥቶ ነበር ። ሆኖም ሕጉ አስፈጻሚ ስላጣ እምብዛም በተግባር ላይ አልዋለም ።

ከዐረብኛ ወደ ግዕዝ በተተረጐመው ፍትሐ ነገሥት ውስጥ "ኢትዮጵያውያን ከወገኖቻቸው (ከዐዋቂዎቻቸው) ጳጳሳት እንዳይሾሙ 318ቱ አበው በኒቅያ ጉባኤ ወስነዋል" የሚለው ዘግይቶ በግብጻውያን የተጨመረው የሀሰት ጽሑፍ የኒቅያ ጉባኤ ተካፋዮች በነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ቋንቋዎች በጽርዕና በላቲን በተጻፉት በኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ ዎች ውስጥ ፈጽሞ አልተጻፈም ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ በተጨባጭ ማስረጃ ለእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስረድታ ለች ። ስለዚህ በአለንበት በ20ኛው መቶ ዘመን ራሷን ለመቻል ሙሉ ችሎታ ያላትና ቁርጣ የተነሣች መሆኗን ለእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አስታወቀች ። የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያንም በጥያቄው ስለተስማማች ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በየጊዜው ግብጻውያን ጳጳሳትን ማስመጣ ቷን ትታ ከኢትዮጵያውያን ካህናት መካከል እየመረጠች የመሾም መብቷን ተጐናጸፈች ።

ይህ መብት ሙሉ በሙሉ ከመሰጠቱ በፊት በ1921 ዓ.ም ካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት



www.ethiopianorthodox.org

በፓትርያርኩ በአቡነ ዮሐንስ 19ኛ እጅ ተቀብተው ተሾሙ ። እነሱም 1ኛ/ አቡነ አብርሃም የጐጃምና የጎንደር ጳጳስ ። 2ኛ/ አቡነ ይስሐቅ የትግራይና የስሜን ጳጳስ ። 3ኛ አቡነ ጴጥሮስ የወሎና የላስታ ጳጳስ ። 4ኛ/ አቡነ ሚካኤል የምሥራቅ ኢትዮጵያ ጳጳስ ናቸው ። በዚሁ ጊዜ ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ በሊቀ ጳጳስነት ማዕርግ ለአራቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት የበላይ ሆነው ተሾሙ ።

የእስክንድርያው ፓትርያርክ ኢትዮጵያ መጥተው ስለነበር በጤና መታወክ ምክንያት ግብጽ ሄደው ለመሾም ላልቻሉት ለእጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሳዊሮስ በሚል ስም የጵጵስና ማዕርግ ሰጧቸው ። እነዚህ ጳጳሳት ከወገኖቻቸው ከኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳትም ሆነ ጳጳሳት እንዳይሾሙ ፓትርያርኩ በሲኖዶስ አስወስነው ከልክለዋቸው ነበር ።

እላይ ከተጠቀሱት ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የኢትዮጵያን ሕዝብ በመንፈሳዊው ተግባር በማገልገል ብቻ ሳይወሰኑ በ1928 ዓ.ም የኢጣልያ ፋሽስት ሀገራችንን በግፍ ለመውረር በመጣበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ዘምተው ሠራዊቱን ያደፋፍሩ ነበር ። ፋሽስቶች በአውሮፕላንና በመርዝ ጢስ በመጠቀም ሕዝቡን ስለጨረሱት ከሞት ከተረፈው ጋር ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ ። ከዚያም አርበኞችን ለማበረታታት በማሰብ ደብረ ሊባኖስ ሄደው ሰላሌ ከነበሩት አርበኞች ጋር ተቀላቀሉ ። አርበኞቹ ወደ አዲስ አበባ ዘልቀው በመግባት ጠላትን በወጉበት ወቅት አቡነ ጴጥሮስም አብረዋቸው ስለነበሩ ተማርከው ወደ ግራዚያኒ ቀረቡ ። እሱም ለኢጣልያ ንጉሥ ተገዥ ነኝ እንዲሉ በማስፈራራት ቢጠይቃቸው ፡ ንጉሤ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ኢትዮጵያም የኢትዮጵያውያን ናት እንጂ ለፋሽስቶች አትሆንም በማለት ስለመለሱለት ተቀጥቶ በጥይት እንዲደበደቡ አዘዘ ። እርሳቸውም በሚገደሉበት ስፍራ ሲደርሱ አራቱን ማዕዘን በመስቀላቸው ባርከው በዙሪያቸው ለተሰበሰበው ሕዝብ ፋሽስቶች የሀገራችንን አርበኞች ሽፍታ ቢሏቸው እውነት አይምሰላችሁ ። ሽፍታ ማለት ያለ ሀገሩ መጥቶ የሰውን ርስትና ሀብት የሚቀማ ፡ አብያተ ክርስቲያናትን የሚያቃጥል ፡ የሕዝብ ደም የሚያፈስ ፡ ይህ በመካከላችሁ የቆመው አረመኔው የኢጣልያ ፋሽስት ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሱ እንዳይገዛ ውጉዝ ነው ። የኢትዮጵያም መሬት እንዳትቀበለው የተገዘተች ትሁን በማለት ተናግረው ሲጨርሱ በመትረየስ ተገደሉ ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ለሀገራችን ነጻነት ሲሉ



www.ethiopianorthodox.org

ራሳቸውን ለመሥዋዕትነት አሳልፈው ለሰጡት ከፍ ላለው ውለታቸው መታሰቢያ እንዲሆን በተገደሉበት አካባቢ ሐውልታቸውን አቁሞ ሲያስታውሳቸው ይኖራል ።

ግብጻዊው ሊ.ቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ግን ኢትዮጵያ ድል ስትሆን በመንፈሳዊ አባትነታቸው ሕዝቡን በማጽናናትና አብረው ከምእመናን ጋር የመጣውን ሥቃይ በመቀበል ፈንታ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያላቸውን መንፈሳዊ ሹመት (ሥልጣን) የኢጣልያ መንግሥት እንዲያጸድቅላቸው ለመጠየቅ ከአዲስ አበባ ተነሥተው ወደ ሮም ሄዱ ። የኢጣልያ መንግሥትም የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እንዲያስተዳድሩ የምንፈቅድልዎ ቤተ ክርስቲያኗ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን እንድትለይ (እንድትገነጠል) የረዱን እንደሆነ ብቻ ነው ስላላቸው ተስፋ ቈርጠው ወደ ግብጽ ሄደው ቀሩ ።

ቀደም ሲል ከተሾሙት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት አብዛኞቹ በመሞታቸውና ግብጻዊው ሊ.ቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስም ግብጽ ሄደው ስለቀሩ በምእመናን ላይ ችግርና የሞራል ውድቀት እንዳይደርስ በማሰብ ፤ የኢትዮጵያ ሊቃውንት አዲስ አበባ ውስጥ ጉባኤ አድርገው ኅዳር 21 ቀን 1930 ዓ.ም ቀደም ሲል በአቡነ ዮሐንስ 19ኛ እጅ ጵጵስና የተቀበሉትን አቡነ አብርሃምን ሊ.ቀ ጳጳስ እንዲሆኑ ወስነው በተጨማሪ አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳትና አንድ ኤጲ.ስ ቆጶስ ተመርጠው በአቡነ አብርሃም እጅ ተሾሙ ። እነሱም 1ኛ አቡነ ዮሐንስ የሸዋ ጳጳስና እጨጌ ። 2ኛ/ አቡነ ማርቆስ የኤርትራ ጳጳስ ። 3ኛ/ አቡነ ሰላማ የሐረር ጳጳስ ። 4ኛ/ አቡነ ማቴዎስ የወሎ ጳጳስ ። 5ኛ አቡነ ገብርኤል የጎንደር ጳጳስ ። 6ኛ/ አቡነ ሉቃስ የወለጋ ኤጲ.ስ ቆጶስ ነበሩ ።

ሐምሌ 14 ቀን 1931 ዓ.ም ሊ.ቀ ጳጳሱ አቡነ አብርሃምስላረፉ መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ.ም አቡነ ዮሐንስ ሊ.ቀ ጳጳስ ሆነው ተሾሙ ። እርሳቸውም በዚያው ዕለት የሚከተሉትን ጳጳሳትና ኤጲ.ስ ቆጶሳት ሾሙ ።

1ኛ አቡነ ፊልጶስ ኤጲ.ስ ቆጶስና የሊ.ቀ ጳጳሱ ጸሐፊ

2ኛ አቡነ ጎርጎርዮስ የወሎ ጳጳስ

3ኛ/ አቡነ ማትያስ የሸዋ ጳጳስ

4ኛ/ አቡነ አትናቴዎስ የጐጃም ጳጳስ

5ኛ/ አቡነ ቄርሎስ የኤርትራ ኤጲ.ስ ቆጶስ

እንዲሁም ካምስት ወራት በኋላ አቡነ ዘካርያስን የኢየሩሳሌም



www.ethiopianorthodox.org

ኤጲስ ቆጶስ አድርገው ሾመዋል ።

የኢትዮጵያ ካህናትና ሊቃውንት የሕዝቡን ችግር፣ ሥቃይና መከራ በማጽናናትና በመምከር ለማቃለል እንዲቻል በማሰብ እንዲሾሙ ያደረጉ አቸውን ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ያለኔ ፈቃድ ነው የተሾሙ በማለት የእስክንድርያው ፓትርያርክ አወገዟቸው ። ሆኖም አዲስ የተሾሙት ጳጳሳት መንፈሳዊ ሥራቸውን ሲያከናውኑ ቈዩ ። የኢትዮጵያ ነጻነት ከተመለሰ በኋላ ግን በእስክንድርያው ፓትርያርክ ግዝት መሠረት በጠላት ጊዜ የተሾሙት ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ሥልጣን ታገደ ። ቈየት ብሎም ግዝቱ ተነሥቶ የጵጵስናውን ማዕርግ ከመቀበላቸው በፊት ወደ ነበሩበት ሥራ እንዲመለሱ ተፈቀደላቸው ። ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ሥራቸውን ቀጠሉ ።

የኢትዮጵያ ምእመናን መንፈሳዊ ፍላጎት በአንድ ጳጳስ ብቻ ሊረካ ስለማይችል ከነጻነት በኋላ ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ·ም አምስት ጳጳሳት ካይሮ በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በአቡነ ዮሳብ 2ኛ እጅ ተቀብተው ተሾሙ ።

እነሱም ፤ 1ኛ/ አቡነ ባስልዮስ የሸዋ ጳጳስ ።

2ኛ/ አቡነ ሚካኤል የጎንደር ጳጳስ ።

3ኛ/ አቡነ ቴዎፍሎስ የሐረር ጳጳስ ።

4ኛ/ አቡነ ያዕቆብ የወለጋ ጳጳስ ።

5ኛ/ አቡነ ጢሞቴዎስ የሲዳሞ ጳጳስ ናቸው ።

የመጨረሻውና 110ኛው ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ካረፉ በኋላ ጥር 6 ቀን 1943 ዓ·ም አቡነ ባስልዮስ ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ከአቡነ ዮሳብ 2ኛ ካይሮ ውስጥ የሊቀ ጵጵስና ማዕርግ ተቀበሉ ። ይኸውም 111ኛው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ መሆናቸው ነው ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ነጻ ወጥታ እራሷን ችላ ከሊቃውንቶቿ መካከል ጳጳሳትን የመሾም መብት ስለተቀዳጀች በዚያው ዓመት አቡነ ባስልዮስ የሚከተሉትን ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ሾሙ ።

1ኛ/ አቡነ ታዴዎስ የኢሉባቦር (የጎሬ) ጳጳስ ።

2ኛ/ አቡነ ገብርኤል የወሎ ጳጳስ ።

3ኛ/ አቡነ ፊልጶስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ጳጳስ ።



www.ethiopianorthodox.org

4ኛ/ አቡነ ማርቆስ የኤርትራ ጳጳስ ።

5ኛ/ አቡነ ጎርጎርዮስ የጂማ ጳጳስ ።

ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም በእስክንድርያው ፓትርያርክ በአቡነ ቄርሎስ 6ኛ እጅ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ ።

አስፈላጊነቱ በቅዱስ ሲኖዶስ እየተጠና በተወሰነው መሠረት እስከ አሁን ድረስ አምስት ፓትርያርኮች ፥ ብዙ ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ተሹመዋል ። አምስቱ ፓትርያርኮችም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፥ ሰማዕቱ ቅዱስ ቴዎፍሎስ ፥ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፥ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፥ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ናቸው ።

በዚህ አኳኋን ኢትዮጵያውያን ከኤጲስ ቆጶስነት እስከ ፓትርያርክነት ያለውን ማዕርገ ክህነት ተቀዳጅተው በአሁኑ ጊዜ በመላ ኢትዮጵያ ሐዋርያት የሰበኳትን የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ እምነታችንን በማስተማር ላይ ይገኛሉ ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት ያህል በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሞግዚትነት ቁይታ ባገኘችው ታላቅ የነጻነት ዕድል ባህሏንና ቋንቋዋን በሚያውቁ በገዛ ልጆቿ መሪነትና መምህርነት በመተዳደር ከፍ ያለ ፍሬ የምታስገኝ መሆኗ ግልጽ ነው ።

በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉ የአፍሪቃ ሀገሮች የወንጌልን ትምህርት ሳይቀበሉ ፥ ከብዙ ዘመናት በፊት ጀምራ ክርስትናን የተቀበለች ሀገራችን ኢትዮጵያ ብቻ ስለሆነች የክርስቲያን ደሴት ተብላ ትጠራለች ።

በኢትዮጵያ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ቊጥር ከ15ሺህ እስከ 20ሺህ መሆኑ ሲገመት ፥ የካህናት ቊጥር ደግሞ ከ200 ሺህ እስከ 300 ሺህ ይሆናል ይባላል ። እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት የሚገለገሉባቸው ኢየሩሳሌም ፥ ጃማይካ ፥ ጂቡቲ ፥ ሱዳን ፥ ኒዮርክ ፥ ወዘተ. ውስጥ ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት አሏት ።

ምንም እንኳ ባሲሊካ ተብሎ በሚጠራው በአራት ማዕዘን ቅርፅ የተሠሩ ጥቂት አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም በኢትዮጵያ የሚገኙት ያብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ቅርፅ (ሥራ) ክብ ነው ። ውስጡም መቅደስ ፥ ቅድስትና ቅኔ ማኅሌት በተባሉ ሦስት ክፍሎች ይከፈላል ። ከመቅደሱ ውስጥ የታቦተ ጽዮን ምሳሌ የሆነው ታቦት በመንበሩ ላይ ይቀመጣል ። ታቦት በሌለበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥርዓተ ቅዳሴ



www.ethiopianorthodox.org

ሊከናወን አይችልም ። መቅደስ ሊገቡ የሚችሉ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ብቻ ናቸው ። ከቅድስቱ ውስጥ ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉ ሰዎች ይቆማሉ። ከቅኔ ማኅሌቱ ውስጥ በአንድ ወገን ደብተሮች ይዘምራሉ ፤ በአንድ ወገንም ቀሳውስት ሰዓታት ይቆማሉ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወንዶችና ሴቶች በተወሰነላቸው ስፍራዎች ቆመው ሥርዓተ ቅዳሴውን ይከታተላሉ ። ንጽሕና ይጐድለናል ብለው የሚያስቡና ቅዳሴ ከገቡ በኋላ ዘግይተው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያኑ ውጭ ቆመው ያስቀድሳሉ ። ጸሎተ ቅዳሴውን ለመፈጸም በትንሹ ሁለት ቀሳውስትና ሦስት ዲያቆናት መኖር አለባቸው ።

የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በሦስት መደቦች ይከፈላሉ ። እነሱም 1ኛ/ ገዳም ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ የፈጸመውን ተግባር በመቀበል ፍለጋውን ተከትለው አባትና እናታቸውን፣ ሚስትና ልጆቻቸውን ፤ ሀብትና ንብረታቸውን ፤ ባጠቃላይ ዓለሙን ንቀው ወደ ገዳም የሄዱ መናንያን መነኰሳት በጾም በጸሎት ተጠምደው የሚኖሩበት ቦታ ገዳም ይባላል ። እንዲሁም ባሕታውያን የነቢዩ ኤልያስንና የመጥምቁ ዮሐንስን አርአያ ተከትለው በተግባር ላይ ያውላሉ።

በገዳም የሚኖሩ መነኰሳትና መነኰሳይያት ብቻ ሲሆኑ ፤ የወንዶችና የሴቶች ገዳም የተለያየ ነው ። ገዳም የገባ ሰው ገዳሙ የሚያዝዘውን መፈጸም እንጂ በራሱም ሆነ በንብረቱ ሊያዝዝ ከቶ አይችልም ።

የገዳሙ መምህር (አበምኔት ፤ አስተዳዳሪ) በዕድሜ ፤ በመልካም ጠባይ ፤ በገድል ፤ በትሩፋትና በመሳሰሉት የተሻለው ከመነኰሳቱ መካከል ተመርጦ አባት (መምህር) ተብሎ ይሾማል ። እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ 11፡37 የጻፈውን መሠረት በማድረግ ሽካራ በርኖስ ፤ የፍየል ሌጦ ፤ የበግ አጐዛ በመልበስ ፤ የሰሌን ቆብ በመድፋት ለሥጋዊው ምቾታቸው ሳያስቡ የሚኖሩ በመሆናቸው አስተዳዳሪያቸው የአጐዛ መምህር ይባላል ። የመምህሩ ረዳቶች አፈ መምህር ፤ መጋቢ ፤ ሊቀ ረድእ ፤ ሊቀ ዲያቆን ወዘተ ይባላሉ ።

አብዛኞቹ የኢትዮጵያ መነኰሳት በማኅበር እየሠሩ ፤ እየተመገቡ ፤ እየጸለዩ ፤ አንድ ዓይነት ልብስ እየለበሱ እንዲኖሩ የሚያዝዘውን አባ ጳኵሚስ ያዘጋጀውን ሥርዓተ ምንኵስና የሚከተሉ ናቸው ።

2ኛ/ ደብር ። ትምህርቱን ለማዳመጥ የተሰበሰበው ሕዝብ በሚገባ



www.ethiopianorthodox.org

አዳምጦ በቀላሉ ለመረዳት እንዲችል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስ ተምርበት ስፍራ የብስ ሲሆን ከተራራ ( ከኮረብታ) ፡ ባሕር ዳር ሲሆን ከመርከብ ላይ ሆኖ ይሰብክ ነበር ። አምላክነቱንም ለደቀ መዛሙርቱ የገለጸ በደብረ ታቦር ላይ ነው ። ስለዚህ በተራራ (በኮረብታ) በመመሰል የእግዚአብሔር ቃል ለምእመናን ሁሉ የሚሰጥባቸውና ምእመናንም አምልኮአቸውን የሚፈጽሙባቸው አብያተ ክርስቲያናት አድባራት ይባላሉ ። እንዲሁም አድባራት የሚባሉት ከዓመት እስከ ዓመት ስብሐተ ነግህ ፡ መዝሙር የሚቆምባቸው ፡ ዘወትር ቅዳሴ የሚቀደስባቸው ወዘተ ናቸው ። በደብር ውስጥ (አካባቢ) ማንኛውም ሰው ይኖራል ።

የደብር አስተዳዳሪ አለቃ ይባላል ። የሚመረጠውም እንደ አድባ ራቱ ሥርዓት ከደናግል (ከመነኰሳት) ፡ ከሕጋውያንና ከመምህራን ነው ። ምንም እንኳ ሥራቸው ያው እልቅና ቢሆንም ቅሉ ያንዳንድ አድባራት አስተዳዳሪዎች ንቡረ ዕድ ፡ ሊቀ ሥልጣናት ፡ ሊቀ ሊቃውንት ፡ መልአከ ሰላም ፡ መልአከ ነገት ፡ መልአከ ፀሐይ ወዘተ በተባሉ ስሞች ይጠራሉ ። የሥራ ረዳቶቻቸውም ሊቀ ጠበብት ፡ አፈ ሊቀ ሊቃውንት ፡ ሊቀ መዘምራን ወዘተ ይባላሉ ።

3ኛ <u>ገጠር</u> ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ዙሪያና በፍልስጥኤም ውስጥ በሚገኙ ገጠሮች (መንደሮች) እየተዘዋወረ ሲያስተ ምር አምስት ገበያ የሚያህሉ ሰዎች ተከትለውት ነበር የሚለውን መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ በየገጠሩ በብዛት የተተከሉ (የተሠሩ) አብያተ ክርስቲያናት ገጠር ይባላሉ ። እንዲሁም ገጠር የሚባሉት ዘወትር ስብሐተ ነግህ ፡ መዝሙር የማይደረስባቸው ፡ በየሳምንቱ እሑድና በወር በዓላት ብቻ የሚቀደስባቸው ናቸው ። የገጠር ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ እንደ ችሎታው አለቃ ፡ መሪጌታ ወይም ገበዝ ይባላል ።

በ20ኛው መቶ ዘመን መንግሥት ትምህርት ቤቶችን እየከፈተ በምዕራባውያን የትምህርት አሰጣጥ መንገድ ዓለማዊውን ትምህርት ማስተማር ከመጀመሩና ከማስፋፋቱ በፊት ለብዙ ዘመናት ማንኛውም ትምህርት ይሰጥ የነበረው እላይ እንደተጠቀሱት ባሉት ገዳማት ፡ አድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ (ውስጥ) ነበር ። በነዚሁ ስፍራዎች በሰፊው ይሰጥ የነበረውና አሁንም በዘመናዊው ትምህርት መስፋፋት ምክንያት ስለ ተዳከመ በመጠኑ በመሰጠት ላይ ያለው አብዛኛው ትምህርት መንፈሳዊ መሆኑ ግልጽ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

የትምህርቱም ደረጃ የንባብ ፡ የዜማ ፡ የቅኔና የትርጓሜ ትምህርት በመባል በአራት ክፍሎች ተከፍሎ በመካሄድ ላይ ነው ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ዘጠኝ ዐበይት በዓላት ፡ ዘጠኝ ንዑሳን በዓላትና ሰባት አጽዋማት አሉ ። እነሱም፡ ዘጠኙ ዐበይት በዓላት ትስብእት ፡ ልደት (ገና) ፡ ጥምቀት ፡ ደብረ ታቦር ፡ ሆሣዕና ፡ ስቅለት ፡ ትንሣኤ ፡ ዕርገትና ጰራቅሊጦስ ሲሆኑ ፡ ዘጠኙ ንዑሳን በዓላትም መስቀል ፡ ስብከት ፡ ብርሃን ፡ ኖላዊ ፡ ግዝረት ፡ ልደት ስምዖን ፡ ቃና ዘገሊላ ፡ ደብረ ዘይትና መጋቢት 10 ቀን የሚውለው መስቀል ናቸው ። ሰባቱ አጽዋማት ደግሞ ዓቢይ ጾም ፡ ጾመ ሐዋርያት ፡ ጾመ ፍልሰታ ፡ ጾመ ነቢያት ፡ ገሃድ ፡ ጾመ ነነዌና ዓርብና ረቡዕ ናቸው ።

ማሳሰቢያ፡– 1ኛ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሰፊው ለመረዳት በግዕዝ ፡ በአማርኛና በውጭ ሀገር ቋንቋዎች በብዛት የተጻፉትን መጻሕፍት ማጥናት ያሻል ።

2ኛ/ በመግቢያው እንደተገለጸው ከዚህ በላይ በምዕ ራፍ ፱ ውስጥ የተጻፈው ዓመተ ምሕረት ሁሉ እንደ ኢትዮጵያ አቈጣጠር ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፫

## የሶርያ (የአንጾኪያ ፣ ያዕቆባዊት) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በቅዱስ ጴጥሮስ ፣ ቀጥሎም በነቅዱስ አግናጥዮስ የተመሠረተችው የሶርያ ቤተ ክርስቲያን የኬልቄዶንን የሁለት ባሕርይ ውሳኔ የተቃወመው የአንጾኪያው መንበረ ፓትርያርክ ተከታይ ናት ። የዚች ቤተ ክርስቲያን እምነት ከእስክንድርያ ፣ ከኢትዮጵያ ፣ ከአርመንና ከሕንድ ተዋሕዶ (ኦርየንታል) አብያተ ክርስቲያናት ጋር አንድ ነው ።

አንጾኪያ በዚያን ዘመን ገኖ ከነበረው የሮማ ንጉሠ ነገሥት (ቄሣር) ግዛት ከሮምና ከእስክንድርያ ቀጥላ ሦስተኛዋ ታላቅ ከተማ ነበረች ። በሐዋርያት ሥራ እንደምንመለከተው ክርስትና ለአሕዛብ በመጀመሪያ ጊዜ የተሰበከችው አይሁድ በ34 ዓ·ም እስጢፋኖስን በግፍ በመግደል በክርስቲያኖች ላይ በአስነሡት ስደት ምክንያት ወደ ሶርያ በተሰደዱት በነፊልጶስ እዋና ከተማዋ አንጾኪያ ውስጥ ነበር (የሐዋ·11፡19–27፤ 14፡21 ፤ 14፡26 ፤ 15፡22–23 ፤ 15፡30–35 ፤ 18፡22) ። ለሐዋርያትም "ክርስቲያን" የሚለው ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣላቸው አንጾኪያ ውስጥ ነው (የሐዋ· 11፡26) ።

በዚያን ጊዜ ይህችው ቤተ ክርስቲያን የተጠናከረች ስለነበረች በቀላውዴዎስ ቄሣር ዘመነ መንግሥት በተነሣው አስከፊ ረሀብ ለተሠቃዩት በይሁዳ ለነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን እርዳታ ልካለች (የሐዋ· 11፡29) ።

የዚችው ቤተ ክርስቲያን የባህል መዲና የነበረችው የኤዴሳ ንጉሥ አብጋርም ካደረበት ደዌ በሐዋርያው ታዴዎስ አማካይነት እንደዳነ እንደተፈወሰና ክርስትናን እንደተቀበለ አውሳብዮስ ይተርካል ። ይኸው አውሳብዮስ (ኤቭሲቢዮስ) የተባለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ የአንጾኪያን ቤተ ክርስቲያን የመሠረተ ቅዱስ ጴጥሮስ መሆኑን ገልጿል። ወደ ሮምም እስኪሄድ ድረስ የመጀመሪያው ጳጳስ በመሆን (34 40) ክርስትናን አስተምሯል ፣ ኋላም በምትኩ ቅዱስ ኤውዲዮስን ማዕርገ



www.ethiopianorthodox.org

ጵጵስና ሰጥቶ ከሾመ በኋላ ወደ ሮም ሄደ ይላል ። ኤውዲዮስም መንፈሳዊ ተግባሩን በማከናወን ላይ ሳለ በኔሮን ትእዛዝ (54–68) በተነሣው ስደት በሰማዕትነት ሰላረፈ ከቅዱስ ጴጥሮስ ማዕርገ ጵጵስና ተቀብሎ የነበረው ቅዱስ አግናጥዮስ ጳጳስ ሆኖ ተሾመ ። እሱም በትራይአኖስ ትእዛዝ (98–117) በተነሣው ስደት ሮም ውስጥ ለአንበሶች በመጣል በሰማዕትነት ዐረፈ ። ይኸውም አግናጥዮስ ቀጥተኛ የሆነውን የክርስትና እምነቱን አልክድም በማለቱና ምእመናንም በክርስትና እምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ ተግቶ በማስተማሩ ምክንያት ንጉሡ ራሱ አግናጥዮስን የክርስትና እምነቱን እንዲክድ ቢጠይቀው አልክድም በማለት በእምነቱ ስለጸና ፤ በንጉሡ ትእዛዝ ከአንጾኪያ በወታደሮች ተይዞና ታጅቦ ወደሮም ሲጓዝ ምንም እንኳ ያጀቡት ወታደሮች አልፎ አልፎ ቢያጉላሉትም ቅሉ፤ የንግግር ነጻነቱን ስላልተገፈፈ በመንገዱ ላገኛቸው ክርስቲያኖች ሁሉ የወንጌልን ቃል በመስበክ በክርስትና እምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ የአባትነት ምክሩን ለግሷቸዋል ። እዝሚርንም ሲደርስ ቅዱስ ፖሊካርፕና የኤፌሶኑ ጳጳስ አቡነ አኔሲሙስ ተቀብለው አስተናግደውታል ። ሮምም እንደደረሰ የተቀበሉት ክርስቲያኖች በቅርቡ የሚቀበለውን ሥቃይ በማሰብ ልባቸው በኃዘን ተውጦ ስላያቸው ስለ ክርስትና እምነት የሚቀበለው ሰማዕትነት ተገቢ መሆኑን በማስረዳት አጽናንቷቸዋል ። አግናጥዮስ በሰማዕትነት ከማረፉ አስቀድሞ ለኤፌሶን ፤ ለፊላደልፊያና ለእዝሚርን ወዘተ ክርስቲያኖች መልእክታት ጽፎ ልኮላቸዋል ። እነዚህም መልእክታት ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከጻፉአቸው መንፈሳዊ ነክ መጻሕፍት ጋር ተጠርዘው ይገኛሉ ።

የአንጾኪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርኮች ለቤተ ክርስቲያናቸው አባት ለቅዱስ አግናጥዮስ ያላቸውን አክብሮትና ፍቅር ለመግለጽ ከ1293 ዓ·ም ጀምሮ በየጊዜው ከተሾሙት አብዛኞቹ "አግናጥዮስ" በሚል ስም ይጠራሉ ። እንዲሁም የእያንዳንዱ ክፍለ ሀገር ጳጳስ ስም አስቀድሞ ስለተወሰነ አንዱ ሞቶ ሌላ ሲጸድስ የሚሰጠው ስም አዲስ ሳይሆን ያው የተወሰነው ነው ። ለምሳሌ የአንጾኪያው ፓትርያርክ ስም አግናጥዮስ፡ የኢየሩሳሌም ጳጳስ ስም ጎርጎርዮስ ወዘተ ነው። ከሐዋርያው ጴጥሮስ ጀምሮ አሁን ቤተ ክርስቲያኒቱን በመም ።ት ላይ እስካሉት እስከ ማር አግናጥዮስ ያዕቆብ ሦስተኛ ድረስ አንድ መቶ ሃያ አንድ ፓትርያርኮች ቤተ ክርስቲያኒቱን መርተዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

በኒቅያ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ እንደ ቅዱስ አትናቴዎስ የአርዮስን የክሕደት ትምህርት በጥብቅ የተቃወመው ቅዱስ ኤዎስጣቴዎስ የአንጾኪያ ጳጳስ ነበር ። በኒቅያ ጉባኤ የሶርያ ፣ የፍልስጥኤም ፣ የቆጵሮስ ፣ የዓረቢያ ፣ የሜሶፖታሚያ ፣ የፋርስና የሕንድ አብያተ ክርስቲያናት በአንጾኪያ መንበረ ፓትርያርክ ሥር እንዲተዳደሩ ተወስኖ ነበር ። የቂሣርያ ፣ የኤዴሳ ፣ የሴሌውቂያና የማላባር (የደቡብ ሕንድ) አብያተ ክርስቲያናትም መንፈሳዊ አመራርን የሚቀበሉት ከአንጾኪያው መንበረ ፓትርያርክ ነበር ።

እንዲሁም የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ በጥብቅ በመቃወም ስለ ተዋሕዶ እምነት አብራርቶ የጻፈው ቅዱስ ሳዊሮስ (465–538) የአንጾኪያ ፓትርያርክ ነበር ። አሕዛብ ስለ ክርስቲያኖች አምልኮ የነበራቸው አመለካከት ፍጹም ስሕተት መሆኑን አብራርተው ካስረዱት የክርስትና አፖሎጂስቶች (ጠበቆች) አንዱ በሁለተኛው መቶ ዘመን የተነሣው የአንጾኪያው ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ነበር ።

ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ እስክንድርያ እንደተፈጸመው ሁሉ የግሪክ ተወላጆችና በእምነት መሰሎቻቸው የሆኑ የሶርያ ተወላጆች መለካውያን ሶርያ ውስጥ የራሳቸውን መንበረ ፓትርያርክ ሲያቋቁሙ ፣ የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ በመቃወም በተዋሕዶ እምነታቸው የጸኑት ሶርያውያን (ያዕቆባውያን) ደግሞ ቀድሞ የነበረውን የራሳቸውን መንበረ ፓትርያርክ አጸኑ ።

እላይ ከተጠቀሱት ቅዱሳን አባቶች በስተቀር ከሐዲው ጳውሎስ ሳምሳጢስም ከ260–270 ዓ.ም ድረስ የአንጾኪያ ጳጳስ ሆኖ ነበር ።

አንድ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን በአራተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ ተወጋግዛ በእምነት ሁለት ላይ ስትከፈል ፣ ቀድሞ ከነበሩት ፓትርያርኮች የማዕርግ ተራ ያልገባቸቱ የቍስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን በንጉሡ በመርቅያን ተጽእኖና ግፊት በጉባኤው በተደነገገው በ28ኛው ሕግ (አንቀጽ) መሠረት "አዲሲቱ ሮም" በመባል የቍስጥንጥንያ መንበረ ፓትርያርክ ከሮማው ፖፕ ጋር በማዕርግ ትክክል ፡ በሽምግልና ግን ሁለተኛ ሆነ ። በዚህ አኳኋን በኒቅያ ጉባኤ በተወሰነው መሠረት ሁለተኛና ሦስተኛ የነበሩት የእስክንድርያና የአንጾኪያ መንበረ ፓትርያርኮች ማዕርግ ችላ ተባለ ። ለቍስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን ማዕርግ የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ሳይሆኑ የሮሙ ፖፕም



www.ethiopianorthodox.org

አልተቀበለውም ።

ቀደም ሲል በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደተመለከትነው የቢዛንታይን ንጉሠ ነገሥት ዜኖና (474–491) መሰሎቹ በኬልቄዶን ጉባኤ በመወጋገዝ ተለያይተው በግዛቱ የሚኖሩትን አብያተ ክርስቲያናት በእምነት አስማምቶ አንድ በማድረግ ሰላምን ለማስፈንና መንግሥታቸውን ለማጽናት ጥረው ነበር ። ሆኖም ይህ የሁለት ባሕርይና የአንድ ባሕርይ እምነት ተከታዮችን በእምነት አስማምቶ አንድ የማድረጉ ዓላማ ግቡን ሳይመታ ከሽፎ ቀረ ።

ከቢዛንታይን መንግሥት ሥር ትገዛ የነበረችው የአንጾኪያ ያዕቆባዊት ቤተ ክርስቲያንም እንደ እስክንድርያ (ኮፕት) ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ ተንኰል ያዘለ የዕርቅ (የስምምነት) ንቅናቄ በመቃወም የተዋሕዶ እምነቷንና የራሷን መንበረ ፓትርያርክ አጽንታ እስከ ዛሬ ድረስ መንፈሳዊ ተግባሯን በማከናወን ላይ ናት ።

የቊስጥንጥንያው (የቢዛንታይኑ) ንጉሥ ዩስጢንያኖስ በግዛቱ የነበሩትን ክርስቲያኖች በሃይማኖት አንድ ለማድረግና የግዛቱን አንድነት ለማጽናት በማሰብ የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ ከተቀበሉት ጋር አንታረቅም ያሉትን የተዋሕዶ እምነት ተከታዮችን በጸጥታ ጠባቂዎች ያስርና ያሠቃያቸው ነበር ። አብዛኞቹ የሶርያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት በመታሰራቸውና ምእመናንን የሚያስተምሩና የሚያጽናኑ ካህናት ባለመገኘታቸው የሶርያ ያዕቆባዊት ቤተ ክርስቲያን ወደ መጥፋቱ ተቃርባ ነበር ። በዚያ ቀውጢ ጊዜ የሶርያው ተወላጅ ያዕቆብ ባራዲውስ (ያዕቆብ ዘአልበረዲ 500 578) የተባለው መንፈሳዊ አባት ተነሥቶ ቤተ ክርስቲያኒቱን ከጥፋት አዳናት ። ያዕቆብንና መሰሎቹን የአንድ ባሕርይን እምነት ተከታዮች በምሥጢር ትደግፍ የነበረችው የሶርያዊ ቄስ ልጅ እቴጌ ቴዎዶራም የተዋሕዶ እምነት እንዳይደመሰስ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጋለች ።

ኒሲቢ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ትምህርቱን ያጠናቀቀው ያዕቆብ ዘአልበረዲ ለማስተማር ተግባሩ መቃናት የረዱትን የግሪክ ፣ የሱርስትና የዓረብኛ ቋንቋዎችን ጠንቅቆ ያውቅ ነበር ። እሱም ከ542 ዓ·ም ጀምሮ በቢዛንታይን መንግሥት ወታደሮች ተይዞ እንዳይታሰርና የማስተማሩ ተግባር እንዳይቋረጥበት በማሰብ ቡትቶ ለብሶ ለማኝ በመምሰል በሶርያ ፣



www.ethiopianorthodox.org

በአርመን ፣ በቀጰዶቅያ ፣ በጵምፍልያ ፣ በቆጵሮስ ፣ በግብጽ ወዘተ· በአጠቃላይ ከግብጽ እስከ ኤፍራጥስ በሚገኙ ሀገሮች ፣ በተለይ በሶርያ ውስጥ የሕይወት ዘመኑን ሙሉ በማስተማር (በመስበክ) ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን መሥርቷል ። በታሰሩትና በተገደሉት ካህናት ምትክ አብያተ ክርስቲያናትን ለሚያገለግሉ ሰዎችም ማዕርገ ክህነት ሰጥቷል ። ይኸውም የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናትን ለሚያገለግሉ ለ27 ጳጳሳት ፣ ለ100,000 ቀሳውስትና ዲያቆናት ማዕርገ ክህነት ሰጥቷል ። የተዋሕዶን እምነት የሚከተሉ ምእመናንንም ከመናፍቃን ለመለየት ተከታዮቹ የሆኑ ምእመናን በአንገታቸው ማተብ እንዲያስሩ ሕግ የሠራ እሱው ነው ። ምንም እንኳ እራሱ የኤዴሳ ጳጳስ እንጂ ፓትርያርክ ባይሆንም ሰርግዮስ ዘአንጾኪያንና (542–562) ፣ ጳውሎስ ጸሊምን (564–581) የአንጾኪያ ፓትርያርክ አድርጎ ሾሞአቸዋል ። ያዕቆብ ማዕርገ ጵጵስና የተቀበለው በተዋሕዶ እምነታቸው ምክንያት በቢዛንታይን መንግሥት ወኀኒ ቤት ተጥለው ይማቅቁ የነበሩ ፓትርያርክና ጳጳሳትን ለመጠየቅ በሄደበት እስር ቤቱ ውስጥ በ542 ዓ·ም በነሱ በመሾም ነበር ።

በ6ኛው መቶ ዘመን ላይ ይህችን ቤተ ክርስቲያን ባጠናከራት (ባስፋፋት) በኤዴሳው ጳጳስ በቅዱስ ያዕቆብ ዘእልበረዲ ስም ቤተ ክርስቲያኒቱ ያዕቆባዊት ፣ አባላቷ ያዕቆባውያን በሚል ስም በምዕራባውያን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች ይጠራሉ ።

አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች ይህችን ቤተ ክርስቲያን ከንስጥሮሳውያን ቤተ ክርስቲያን ለመለየት የንስጥሮስን "የምሥራቅ ሶርያ ቤተ ክርስቲያን" ሲሉ ፣ ይህችን የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ "የምዕራብ ሶርያ ቤተ ክርስቲያን" ይሏታል ።

ምንም እንኳ አብዛኞቹ የሶርያ መነኰሳት እስከዛሬ ድረስ የነአባ እንጦንስንና ጳኵሚስን ዱካ በመከተል በገዳሞቻቸው የአንድነት (የማኅበር) ኑሮን ቢኖሩም ቅሉ ፣ ከ4ኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ አንዳንድ የሶርያ መነኰሳት እንደነ አባ እንጦንስ መንኖ በገዳም ከመኖር በተጨማሪ በቋሚ ኮሎን (አንድ ወጥ ረጅም ድንጋይ) ላይ ያረፈ መደገፊያ ግድግዳ እንጂ ጣራ የሌለው ማማ የመሰለ ደርብ ሠርተው የሌሊቱ ቁር የቀኑ ሐሩር ሳይበግራቸው እዚያ ላይ ሆነው በመጾም ፣ በመጸለይ ፣ በመስበክ ፣ በማስተማር ወዘተ· የብሕትውና ኑሮን ይኖሩ ነበር ። መናኙ



www.ethiopianorthodox.org

እታች (እመሬት) ከሚኖሩት መነኰሳትና ትምህርቱን ለመስማት ፣ ካደረባቸው ደዌ ለመፈወስ ወዘተ ወደእሱ ከሚሄዱት ምእመናን ጋር የሚገናኘው በመሰላል አማካይነት ነበር ። ይህንን መንኖ በማማ ላይ የመኖርን ዘዴ የጀመረውና ያስፋፋው ሶርያዊው ቅዱስ ስምዖን ዘዐምድ (389-459) ነው ። እሱም በምንና ከኖረባቸው አምሳ ስድስት ዓመታት ውስጥ ሠላሳ ሰባቱን ያሳለፋቸው በማማ ላይ ሆኖ ሳይወርድ በመጾም ፣ በመጸለይ ፣ በማስተማር ፣ ታምራት በመሥራት ፣ ድውያንን በመፈወስ ወዘተ ነበር ። ይህ ዓይነቱ የቅዱስ ስምዖን የምንና ዘዴ ወደ ሌሎች አገሮች በስፋት አልተዛመተም ። ሆኖም ግብጽና ግሪክ ውስጥ ጥቂት ባሕታውያን እንደተጠቀሙበት ይተረካል ። አንዳንዶች መነኰሳትም በገላቸው ላይ ሀብል ያጠልቁ ነበር ። የቢዛንታይን ንጉሥ ዜኖ ለቅዱስ ስምዖን መታሰቢያ ጳድቁ በጸለየበት ዐምድ አካባቢ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን አሠርቶለታል ።

ዓረቦች (እስላሞች) ሶርያን በኃይል ከመውረራቸው በፊት የቅኝ ገዥ የነበረው የቢዛንታይን መንግሥት አንጾኪያ በነበረው የግሪክ (የመለካዊት) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሥር ለነበሩት ክርስቲያኖች ሙሉ ነጻነት ሲሰጥ ፣ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በሶርያዊው (በያዕቆባዊው) ፓትርያርክ ሥር የነበሩትን ክርስቲያኖችና በንስጥሮሳዊው ፓትርያርክ ሥር የነበሩትን (ንስጥሮሳውያንን) በጥብቅ ያሳድድ ነበር ። በተለይ የንስጥሮስ ተከታዮች ሥቃዩ ስለበዛባቸው ወደ ፋርስ ተሰደው በመሄድ እዚያ በሰላም ይኖሩ ነበር ።

ዓረቦች በ638 ዓ.ም ሶርያን ከያዙ በኋላ ግን በሦስቱም የክርስትና ተከታዮች (በመለካውያን ፣ በያዕቆባውያንና በንስጥሮሳውያን) መካከል ልዩነት ሳያደርጉና ጭቆናውንም ሳያከብዱ የመስቀል ጦረኞች ኢየሩሳሌምን በጦር ኃይል እስከያዙበትና የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮችንም እስከወጉበት ወቅት ድረስ ክርስቲያኖችን በደህና ዐይን ይመለከቷቸው ነበር። በዚያን ወቅት የዓረቦች ዓላማና ፍላጎት ክርስቲያኖች በሙሉ እስላም ከሆኑት ዜጎቻቸው የበለጠ ከፍ ያለ ግብር እንዲሰጡአቸው ስለ ነበር፣ የግብሩ ሁኔታ በጣም አንገፍጋፊ ነበር ። የመስቀል ጦረኞች ከተነሡ በኋላ ግን በሥራቸው ከነበሩት ክርስቲያኖች ጋር በምሥጢር ተባብረው ይወጉናል በሚል ሐሳብና ስጋት ተነሥተው (ተመርተው)



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኖችን ማሠቃየት ጀመሩ ። በዚህ አኳኋን ከቢዛንታይን መንግሥት ጭቆና ተገላግለን የእምነትና የአስተዳደር ሻል ያለ ነጻነት እናገኛለን በሚል ተስፋ የዓረቦችን ድል ማድረግ በደስታ የተቀበሉት የሶርያ ክርስቲያኖች እላይ በተጠቀሰውና በተለያዩ ምክንያቶች ከእስላሞች በተሰነዘሩባቸው ጭቆናዎች በሀገሪቱ ቀደም ሲል ተስፋፍታ የነበረች ክርስትና እየተዳከመች ሄደች ። በተለይ በ10ኛው ፣ በ11ኛውና በ12ኛው መቶ ዘመን የሶርያ ክርስቲያኖች ቊጥር እየመነመነ ሄደ ።

በ13ኛው መቶ ዘመን ሶርያን ወረው ከገዙ ሞንጎሎች (ታርታሮች) እንደ ሁላጉ የመሳሰሉት መሪዎች (ካሃኖች) ክርስቲያኖችን ሳይቃወሙ ከቆዩ በኋላ ከ1295 ዓ.ም ጀምሮ በመሪያቸው በግሐዛን እስልምናን ተቀብለው የመንግሥቱ ሃይማኖት ካደረጉ በኋላ ግን ክርስቲያኖችን እያሳደዱ በመግደል ፣ አብያተ ክርስቲያናትን በማቃጠል፣ ገዳማትን በማፍረስ ባደረሱት ጥፋት ምክንያት የክርስቲያኖች ቊጥር በጣም ቀንሶ ነበር ።

እንዲሁም በ19ኛውና በ20ኛው መቶ ዘመን በተከታታይ በተነሡት በሳልጁክና በኦቶማን ቱርኮች እጅ ብዙ የሶርያ ክርስቲያኖች በሰማዕትነት አልቀዋል ። የቱርክ ገዥዎችም ከሞት ከተረፉት ክርስቲያኖች ላይ ገንዘብ ማጋበሱን ሥራችን ብለው ተያይዘውት ነበር ። ለምሳሌ ፓትርያርክነት ሊሾም የሚችለው ካህን ከምርጫ ተወዳዳሪዎቹ (ተቀናቃኞቹ) ለቱርክ መንግሥት የበለጠ ገንዘብ ለመስጠት የሚችለው ነበር ። ሆኖም ለዘመናት አብዛኛውን ጊዜ በቅድስናቸው ፣ በምሁርነታቸው ወዘተ. ከተመሠከረላቸው መነኰሳት መካከል በመምረጥ ፓትርያርክ ይሾማሉ ። እነሱም ቤተ ክርስቲያኒቱ ካፈራቻቸው ካህናት ጋር ምእመናንን በመምከር ፣ በማስተማር ፣ በማገልገል ይንከባከባሉ ። ከምእመናንም በንግድ ሥራ ላይ ተሠማርተው ከፍ ያለ ሀብት ካፈሩት ጥቂቶቹ ለአብያተ ክርስቲያናትና ለገዳማት ማሠሪያ በመለገሥ ለሶርያ ቤተ ክርስቲያን መጠናከር ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ለብዙ ጊዜ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር ከቈየ በኋላ የሶርያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ አሁን የሚገኘው ሶርያ ደማስቆ ውስጥ ነው ።

በሁለተኛው መቶ ዘመን ሜሶፖታሚያዊው ታትያን የተባለው የወንጌል መልእክተኛ በጤግሮስና ኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ በምትገኝ ኤዴሳ ውስጥ ወንጌልን በማስተማሩ የሀገሪቱ ነዋሪዎች ክርስትናን



www.ethiopianorthodox.org

ተቀብለው አብያተ ክርስቲያናትን በብዛት ሠሩ። በ200 ዓ.ም የሐዲስ ኪዳንን መጽሐፍ ወደ ቋንቋቸው (ሱርስት) ተረጐመው ። ይኸውም የሶርያው ሐዲስ ኪዳን በመባል ይጠራል ። በዚህ አኳኋን በሶርያ ካህናት ጥረት (ትጋት) በየጊዜው በሱርስት የተተረጐሙትና የተደረሱት መንፈሳዊ መጻሕፍት በፋርስ ፣ በሕንድ ፣ በቻይና ባሕር አካባቢ ለነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ከፍ ያለ አገልግሎት በመስጠት ለክርስትና መስፋፋት ጠቃሚ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ከጥንታውያን የእጅ ጽሑፎች ጥቂቶቹ በቫቲካን ፣ በለንደን ፣ በፓሪስ ወዘተ. አብያተ መጻሕፍት ውስጥ ይገኛሉ ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይናገርበትና ያስተምርበት ከነበረው ከአረማይስጥ (ከእብራይስጥ) ጋር ተመሳሳይ በሆነው በሱርስት ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን የተረጐሙና መንፈሳዊ ነክ የሆኑ የተለያዩ መጻሕፍትን የደረሱ እንደነ ያዕቆብ ዘስሩግ (451-521)፣ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ (306-376)፣ ያዕቆብ ዘእልበረዲ ወዘተ .የመሳሰሉ ብዙ መንፈሳውያን ደራሲያንን (ሊቃውንትን) አፍርታለች።

ምንም እንኳ ከ13ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ ዓረብኛ በመንግሥቱ ድጋፍ እየተስፋፋ በመሄዱ የሕዝቡ መግባቢያ ቋንቋ ቢሆንም ቅሉ፣ ሥርዓተ ቅዳሴው የሚፈጸመው በሱርስት ነው።

የሶርያ ቤተ ክርስቲያን በያመቱ ከምታከብራቸው ዐበይት በዓላት መካከል የቅድስት ድንግል ማርያም መቀነት ክብረ በዓል ይገኛል ። ይኸውም በነሐሴ ወር ሖምስ በተባለው ቦታ ባለው በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በብዛት በሚገኙበት ካህናት መቀነቷን ይዘው (ተሸክመው) ዑደት በማድረግ በድምቀት ያከብሩታል ።

የሶርያ ቤተ ክርስቲያን ከሀገሯ ውጭ ሊባኖስ፣ ዮርዳኖስ፣ ደቡብ ሕንድ፣ ኢራቅ፣ ቱርክ ፣ ግብጽ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ ካናዳ ወዘተ. የሚኖሩ ምእመናኖቿን የሚያገለግሉ ካህናትና አብያተ ክርስቲያናት አሏት ። እንዲሁም አሁን ካህናትን የምታሰለጥንበት ሊባኖስ ውስጥ አንድ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አላት። በሦስተኛው መቶ ዘመን አንጾኪያ ውስጥ ተመሥርታ ለክርስቲያኑ ዓለም ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ስላደረገችው ስለ ዝነኛዋ የአንጾኪያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ከዚህ በታች ባጭሩ እንመለከታለን።



www.ethiopianorthodox.org

# የአንጾኪያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት

ቀሲስ ሉሲያን ዘሳሞስታ በ312 ዓ.ም ይህችን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አንጾኪያ ውስጥ መሠረተ።

ቀደም ሲል በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደተመለከትነው የእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ቅዱሳት መጻሕፍትን በአንድምታ (በአሊጎሪክ) ትርጓሜ ስትተረጉም ፣ የአንጾኪያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ደግሞ በተቃራኒው የቅዱሳት መጻሕፍትን ታሪካዊ አመጣጥ ፣ የተጻፉባቸውን ቋንቋዎችና የቃላትን አገባብ በማጥናት (በመመርመር) ቃል በቃል (በነጠላ ትርጓሜ) ቀለል ባለ ዘዴ ትተረጉም ነበር ። በዚህ አኳኋን በእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የአሊጎሪክ አተረጓጎም ዘዴ የፕላቶን ሐሳባዊነት ፍልስፍና ተጽእኖ ሲታይበት ፣ በአንጾኪያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የቃል በቃል ትርጓሜ ደግሞ የአሪስቶትል ሪያሊስትነት ፍልስፍና ተጽእኖ አለበት (ያንጸባርቃል) ይባላል። ስለዚህ የሁለቱ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች የአተረጓጎም ዘዴ (መንገድ ፣ ስልት) የተለያየ ነበር።

የአንጾኪያ ትምህርት ቤት መሥራቾች ምንም እንኳ በጣም ጥልቅ ዕውቀት የነበራቸው ባይሆኑም ቅሉ ትምህርት ቤቷ ቀስ በቀስ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ መሠረት (መፍለቂያ) ሆነች ። በተለይ በአራተኛው መቶ ዘመን በዲአዶሩስ ዘጠርሴስ ትመራ በነበረችበት ወቅት ከፍ ያለ ዝና አትርፋ ነበር ። ትምህርት ቤቲቱ ካፈራቻቸው ዝነኛ ሊቃውንትም (የቤተ ክርስቲያን አባቶችም) መካከል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቴዎዶሬ ዘሞፕሱኤስቲያ ወዘተ. ይገኙበታል ። ትምህርት ቤቷ ምክንያቶችን እየደረደሩ ቃል በቃል በመተርጐም የምትከተለው የአተረጓጐም ዘዴ(መንገድ) ለብዙ መናፍቃን መከሰት መንገድ ከፍቷል ። ለምሳሌ የትምህርት ቤቷ መሥራች ሉሲያን የአርዮስ መምህር ነበር ። እንዲሁም የአርዮስ የቅርብ ጓደኛና ውስጥ ውስጡን (በኅቡዕ) የክሕደቱ ደጋፊ የነረበው አቡነ አውሳብዮስ ዘኒቆሚዲያ ከአርዮስ ጋር የተማረ በዚችው ትምህርት ቤት ነበር።

የእስክንድርያና የአንጾኪያ ትምህርት ቤቶች በሚከተሉት የተለያየ የትርጓሜ ስልት (መንገድ) ምክንያት ከእስክንድርያ ትምህርት ቤት ሊቃውንት ጥቂቶቹ ወደ ክርስቶስ የአምላክነት ባሕርይ ሲያዘነብሉ፣



www.ethiopianorthodox.org

ከአንጾኪያ ትምህርት ቤት መምህራን ደግሞ ጥቂቶቹ ወደ ክርስቶስ የሰውነት ባሕርይ ያዘነብሉ (ያደሉ) ነበር ይባላል።

## ምዕራፍ ፬

### በደቡብ ሕንድ የሐዋርያው ቶማስ (የማላባር፡ የኬራላ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ሐዋርያው ቶማስ እግረ መንገዱን በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ በሳኮትራና በመሳሰሉት ደሴቶች የነበሩትን ሕዝቦች እያስተማረ (እየሰበከ) በ52 ዓ.ም ምዕራብ ሕንድ ክራንጋኖሬ ከተባለው ቦታ ደርሶ፡ በስደት ሄደው እዚያ ይኖሩ ለነበሩ አይሁድና ለሕንዳውያን ወንጌልን አስተምሮ ከሁለቱም ወገኖች ብዙዎችን ወደ ክርስትና መለሰ ። ወደ ደቡብ የክራንጋኖሬ ክፍል ተጉዞ በወደቡ አካባቢ በሰባት ቦታ ላይ ሰባት አብያተ ክርስቲያናትን መሥርቷል ። ከእነዚህም በአራቱ ቦታዎች እስከ ዛሬ ድረስ የሶርያ (የማላባር) ያዕቆባዊትን እምነት ተከታዮች አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ። ቀጥሎም ለመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት ለሚያበረክቱ ከብራሕማኖች ወገን ለነበሩ ሕንዳውያን ክርስቲያኖች ለነቀሲስ ሲሮርና ለነዲያቆን ዜኖፋስ ማዕርገ ክህነት ከሰጠ በኋላ ወደ ምሥራቃዊው የሕንድ ክፍል ተጉዞ ማድራስ አካባቢ አስተምሯል። ከዚያም ወደ ደቡብ ሕንድ ሄዶ ኬራላ ውስጥ ወንጌል ከሰበከ በኋላ ተመልሶ ማድራስ ውስጥ ሲያስተምር ትምህርቱን የሚቃወሙ ብራሕማኖች ባስነሡት ሁከት ረብሻ በጦር ተወግቶ በ72 ዓ.ም በሰማዕትነት ዐረፈ። ቶዳውን ገፈው ሽልቻ በማድረግ አሠቃይተው እንደገደሉትም ይተረካል። ክርስቲያኖችም በመምህራቸው መገደል አዝነው ከቀበሩት በኋላ አንድ ሶርያዊ ነጋዴ በድብቅ የቶማስን አስከሬን ሶርያ ውስጥ ወደአለችው ወደ ኤዴሳ ወስዶ በክብር እንዲያርፍ አደረገ ። የቶማስን አስከሬን መወሰድ ያላወቀው የዚያ አካባቢ ንጉሥ የቶማስን አጽም በማስነካት በጸና የታመመ ልጁን ለማስፈወስ መቃብሩን ቢያስከፍተው አስከሬኑን አጣው። በአስከሬኑ መሰረቅ አዝኖ አስከሬኑ ያረፈበትን አፈር ልጁን ቢያስነካው ከበሽታው ተፈወሰለት ። በዚሁም ታምር በመደነቅና በመደሰት ንጉሡና ንጉሣውያን ቤተሰቦች ሁሉ ክርስትናን ተቀበሉ ይባላል። የሶርያው ቅዱስ ኤፍሬምም የሐዋርያው ቶማስ አጽም



www.ethiopianorthodox.org

በሶርያ ነጋዴዎች ወደ ኤዴሳ ተወስዶ በክብር ስለማረፉ፥ ሕንድ ውስጥም ስለአደረገው ስብከትና ስለተቀበለው ሰማዕትነት፥ በኤዴሳም ቤተ ክርስ ቲያን ስለተፈጸሙ ታምራቶች በመዝሙር ጽሑፎቹ ገልጿል።

ይህንኑም የቶማስን ሕንድ ሲያስተምር በሰማዕትነት ማረፍ ከጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች ከነኮዝማስና ከነቅዱስ ኤፍሬም በተጨማሪ በዘመና ችን ደቡብ ሕንድ ኬሬላ ውስጥ የምትገኘው የቶማስ (የማላባር) ቤተ ክርስቲያን መሥራቿ ሐዋርያው ቶማስ መሆኑን ታረጋግጣለች ። እንዲሁም አውሳብዮስ በቤተ ክርስቲያን ታሪኩ ሐዋርያው በርተሎሚዎ ስም በሕንድ ምዕራባዊ ክፍል ክርስትናን አስተምሯል ይላል ።

የቶማስ ሥራ በተባለው አዋልድ መጽሐፍ ውስጥ ሐዋርያው ቶማስ ወደ ሕንድ እንዴት እንደሄደና እንዳስተማረ እንደሚከተለው ተጽፏል ። "ሐዋርያት የሚያስተምሩባቸውን ሀገሮች በዕጣ ሲካፈሉ ለቶማስ ሕንድ ደረሰው ። ቶማስ ግን አቅመ ደካማ ስለሆንሁ ወደ ሌላ ቀረብ ያለ ሀገር እንጂ ወደ ሕንድ አልሄድም በማለት ወስኖ ተቀመጠ ። ጌታም ሄዶ እንዲያስተምር ቢነግረው አሳበግትር በመሆን አሻፈረኝ ስላለ ከአንድ የሕንድ ነጋዴ ጋር ወደ ሕንድ ሄዶ እንዲያስተምር አደረገው ። ታሪኩም እንደሚከተለው ነው ። ጎንዶፋሬስ የተባለው የሕንድ ንጉሥ አባኔስ የተባለውን ወደ ሶርያና አካባቢ ሀገሮች አዘውትሮ የሚመላለሰውን ነጋዴ ታላቅ ቤተ መንግሥት ለማነጽ የሚችል ከፍተኛ ዕውቀት ያለው መሐንዲስ እንዲፈልግለት አዘዘው ። አባኔስም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እየተመራ ኢየሩሳሌም ወደነበረው ገበያ ደርሶ የንግድ ተግባሩን ሲያከናውን ቶማስን አግኝቶ የንጉሡን ቤተ መንግሥት እንዲያንጽ ተስማሙ ። ቶማስም ከአባኔስ ጋር በመርከብ ወደ ሕንድ ሄዶ ንጉሡ የሚሻውን ዓይነት ቤተ መንግሥት በተለመደው የቤት መሥሪያ ጊዜ በበጋው ወራት ሳይሆን በክረምቱ ወራት የሚያንጽለት መሆኑን ገልጾ ለማሠሪያ ከተመደበው ገንዘብ በቅድሚያ ቀብድ ተቀበለ ። የቶማስም ዓላማ የንጉሡን ሰማያዊ መኖሪያ ለማዘጋጀት (ለማነጽ) እንጂ ምድራዊ ቤተ መንግሥት ለማነጽ አልነበረም ። በዚሁ ዓላማው መሠረት ከንጉሡ ለማሠሪያ የተሰጠውን ገንዘብ ድኾች (ችግረኞች) በችጋር አለንጋ እየተገረፉ (እየተሠቃዩ) ወደሚኖሩባቸው ቦታዎች እየዞረ ሲመጸውት ፥


www.ethiopianorthodox.org

ለሰዎች ወንጌልን ሲሰብክና ድውያንን ሲፈውስ ወዘተ· ያዩ ለንጉሡ ስለነገሩት ቶማስን አስይዞ የሠራህልኝ ቤተ መንግሥት የት ነው ? ብሎ ቢጠይቀው ፤ ቶማስ ንጉሥ ሆይ ! የሠራሁልህን ቤተ መንግሥት የምታየውና የምትረከበው አሁን በሕይወት ሳለህ ሳይሆን ፡ ከሞትህ በኋላ ነው አለው ። ንጉሡም ተቆጥቶ የባከነው ገንዘብ የደረሰበት ተመርምሮ ሲያልቅ ይገደላሉ በማለት ቶማስንና ያመጣውን አባኔስን ወኅኒ ቤት ጨመራቸው ። በንጉሡ የታቀደው የሞት ፍርድ በሁለቱም ላይ ከመፈጸሙ ትንሽ ቀደም ብሎ ጋድ የተባለው የንጉሡ ወንድም ሞቶ ከተቀበረ በኋላ አፈሩ ወደ ጉድጓዱ ከመመለሱ በፊት በተአምር ከሞት ተነሥቶ በቶማስ አማካኝነት ለንጉሡ በመንግሥተ ሰማያት (በሰማይ) ስለተዘጋጀለት እጹብ ድንቅ የሆነ ቤተ መንግሥት ያየውንና ከመላእክት የሰማውን ሁሉ አብራርቶ ገለጸ ። ወዲያው ንጉሡና ወንድሙ ቶማስንና አባኔስን ከእስር ቤት አስወጥተው ከቶማስ በመማር ከብዙ ዜጎቻቸው ጋር ክርስትናን ተቀብለው ተጠመቁ” ይላል ።

በሁለተኛው መቶ ዘመን ማለቂያ ላይ የእስቶይክስን ፍልስፍናና የክርስትናን ትምህርት ጠንቅቆ ያውቅ የነበረው ግብጻዊው ምሁር

ፓንጼኖስ ወንጌልን ለመስበክ በእስክንድርያው ፓትርያርክ በአቡነ ዲሜጥሮስ ወደ ምሥራቅ ሀገሮች ሲላክ ሕንድም ለብራሕማኖችና ለሕንድ ፈላስፎች አስተምሯል ። ፓንጼኖስ ሕንድ በነበረበት ወቅት ቀደም ሲል ሐዋርያው በርተሎሜዎስ ለማስተማሪያ ከኢየሩሳሌም ሕንድ የወሰደውን በእብራይስጥ የተዘጋጀውን የማቴዎስ ወንጌል ቅጅ ማግኘቱ ይተረካል ።

በ525 ዓ·ም በዓረብ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ በመርከብ ጉዞ ያደረገው ፡ ቀደም ሲል የጅኦግራፊ ምሁርና ነጋዴ የነበረው ፡ ኋላም መነኩሴ የሆነው ኮዝማስ የተባለው እስክንድርያዊው ሰው የክርስትና ትምህርት ከጥንት ጀምሮ በሲሎን (በሲሪላንካ) ፡ በሕንድ ፡ በፋርስ ፡ በሶኮትራ ፡ በየመንና በዓረቢያ (በዓረብ ሀገሮች) ተስፋፍቶ እንደነበር ገልጿል ። በጉዞው ወቅትም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ፡ ካህናትንና ክርስቲያኖችን እንዳገኘ ይተርካል ።

የኤዴሳ ጳጳሳትና ነገሥታት የኬራላን (የደቡብ ሕንድን) አብያተ ክርስቲያናት ለማጠናከር በየጊዜው ብዙ ሶርያውያን ካህናትና ምሁራን



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኖችን ለስብከተ ወንጌል ወደ ክራንጋኖሬ መላካቸውን ታሪክ ጸሐፊዎች ይተርካሉ ።

እንዲሁም በዳግማዊ ሻፑር ዘመነ መንግሥት (309–379) በክርስቲያኖች ላይ በተነሣው ሥቃይ ምክንያት ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች ጋር የንግድ መናሃሪያ ወደነበረችው የሕንድ የባሕር ወደብ ወደ ማላባር በ345 ዓ·ም ተሰደው የገቡት ወደ አራት መቶ የሚጠጋ ቤተሰብ የነበራቸው ሰባ ሁለት አባወራዎችን ያካተተ የሶርያ ክርስቲያኖች አብረዋቸው ከሄዱት ካህናት ጋር ሕንድ ውስጥ ለክርስትና መስፋፋት ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። ሆኖም እነዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ በቶማስ ዘቃና መሪነት ተሰደው ሕንድ የገቡ ክርስቲያኖች ክርስትናን ከማስፋፋታቸው ባሻገር ለክርስትና ትምህርት ተቃራኒ የሆነውን የዘር ልዩነት በመፍጠር የሕንድ ቤተ ክርስቲያን እንድትከፋፈል አድረገዋል ። በተዋሕዶ እምነት አንድ ቢሆኑም ቅሉ ጥቂቶቹ ከሕንዳውያን ክርስቲያኖች ጋር አይጋቡም ነበር ።

እንዲሁም በ823 ዓ·ም ለሁለተኛ ጊዜ ፋርስ ከምትገኘው የሶርያ ያዕቆባዊት ቤተ ክርስቲያን አባላት ሁለት ጳጳሳትና ብዙ ምዕመናን ደቡብ ሕንድ ወደሚገኘው ኲሎን ወደተባለው ቦታ በስደት ሄደው ክርስትናን አስፋፍተዋል ።

ከላይ ከተጠቀሱት ስደቶች በተጨማሪ ከእስላሞች የተሰነዘረባቸው ሥቃይ ያንገፈገፋቸው ጥቂት የሶርያ ክርስቲያኖች በተለያዩ ጊዜዎች ሕንድ በስደት ገብተው ክርስትናን አስተምረዋል ።

እንዲሁም ወደ ሕንድ ከተሰደዱት ሶርያውያን መካከል ከያዕቆባውያኑ በስተቀር ንስጥሮሳውያንም ተሰደው ሄደው የራሳቸውን እምነት አስፋፍተዋል ። ከያዕቆባዊት ቤተ ክርስቲያን በስተቀር ሕንድ ውስጥ የንስጥሮሳውያን ፡ የካቶሊክ (የዩኒአታ) ፡ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ።

የሕንድ ቤተ ክርስቲያን በ6ኛው መቶ ዘመን ፋርስ ግዛት ውስጥ በነበረች የሶርያ ቤተ ክርስቲያን ተጽእኖ ፤ በ17ኛው መቶ ዘመን ሕንድን በቅኝ ግዛት በያዚት የካቶሊክን እምነት አራማጅ በነበሩት በፖርቱጋሎች፣ ኋላም በዳቾች ተጽእኖ ፤ ከዚያም በኋላ የእንግሊዝን መንግሥት ድጋፍ ባገኘችው በሶርያ ቤተ ክርስቲያን ተጽእኖ ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ራሷን በራሷ የመምራት መብትን ተገፋ ከቈየች በኋላ በ1912 ዓ·ም



www.ethiopianorthodox.org

በሶርያ ቤተ ክርስቲያን ሥር ከመተዳደር ነጻ ወጥታ ጥንት የነበራትን የኦቶኖሞስ (ራስን በራስ የማስተዳደር) ሥልጣን እንደገና ያደሰች (ያቋቋመች) መሆኗን ገለጸች ። ይህንንም የራሷን ካቶሊኮስና (ፓትርያር ክና) ጳጳሳት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ እየሾመች ራሷን በራሷ እንድት መራ በፊርማ አጽድቆ የፈቀደላት ሶርያን ይገዛ በነበረው በቱርክ መንግሥት በግዞት ላይ የነበረው የሶርያ ፓትርያርክ አቡነ አብዱል መሢሕ በክርስቲያኖች ተጋብዞ ሕንድ ሄዶ በነበረበት ወቅት ነው ። በዚሁ ፈቃድ መሠረት ሕንዳዊው አቡነ ኢቫንዮስ አቡነ ባስልዮስ በሚል ስም የመጀመሪያው ካቶሊኮስ ሆኖ ተሾመ ። ነገር ግን እራሳቸው ሕንዳውያን ጳጳሳትና ካህናት የአቡነ አብዱል መሢሕ ድርጊት ሕገ ወጥ ነው ፤ አይደለም ፤ በመባባል ከሁለት ላይ ተከፍለው አንዱ ወገን በአንጾኪያው ፓትርያርክ ሥር ሲመራ ፤ ሌላው ወገን ደግሞ በካቶሊኮሱ ሥር ይመራ ነበር ። በእምነትና በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሁለቱም ወገኖች አንዳችም ልዩነት አልነበራቸውም ። በዚህ አኳኋን በሕጋዊው የሶርያ ፓትርያርክና በሕንዳዊው ካቶሊኮስ ደጋፊዎች መካከል አምሳ ዓመት የፈጀ ውዝግብ ተነሥቶ ከቈየ በኋላ በ1958 ዓ·ም የሕንድ መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤተ ክርስቲያኒቱን ነጻነት ስላጸደቀና የሶርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አግናጥዮስ ያዕቆብ ሣልሳዊ ወዲያው የሕንድን (የያዕቆባዊትን) ቤተ ክርስቲያን ነጻ መሆን በጽሑፍ ስላጸደቀ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሙሉ ነጻነቷን ተጐናጸፈች ። ሆኖም ይህችው ቤተ ክርስቲያን አቶኖሞስ ሆና ጳጳሳትን ከሶርያ በማስመጣት ፈንታ ከራሷ አባላት ከሕንዳውያን ካህናት በመምረጥ እየሾመች ራሷን ለማስተዳደር ብትበቃና መሪዋም ካቶሊኮስ በሚል ስያሜ ቢጠራም ቅሉ ፤ የሶርያ ያዕቆባዊት ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክን የመንፈሳዊ አባትነት ትቀበላ ለች ። ይኸውም ካቶሊኮሱ ሲሞትና አዲስ ሲመረጥ ለሶርያ ፓትርያርክ የማስታወቅ ግዴታ አለባት ። በካቶሊኮሱ የሹመት ወቅት ተገኝቶ ተካፋይ ከሆነም ሥርዓተ ሢመቱን መምራት የሚገባው የሶርያው ፓትርያርክ ነው ።

ሆኖም ቊጥራቸው አነስ ያለ የሶርያን ቤተ ክርስቲያን ፍጹም የበላይነት በመደገፍ የነጻነቱን ውሳኔ የሚቃወሙ ሕንዳውያን ጳጳሳት ፤ ካህናትና ምዕመናን መኖራቸው ይነገራል ።

ይህቺው የኬራላ (ያዕቆባዊት) ቤተ ክርስቲያን ለካህናቶቿ ማሠል ጠኛ አንድ መንፈሳዊ ሴሚናሪ አላት ።


www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፲

## የአርመን (ጎርጎርዮሳዊት) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎችና የአርመን ቤተ ክርስቲያን አባቶች አርመን ውስጥ ክርስትና በሐዋርያው ታዴዎስና (ልብድዮስና ፣ ይሁዳና) በርተሎሜዎስ በ43 ዓ·ም ተሰብካ ነበር ፤ የመጀመሪያው ፓትርያርክም ታዴዎስ ነበር ሲሉ ፣ አብዛኞቹ ግን አርመኖች ቀደም ሲል ለአበረከተው የማስተማር (የስብከት) አገልግሎት በንጉሡ ፣ በካህናትና በሕዝቡ ፈቃድ ቀጰዶቅያ በምትገኘው ቂሣርያ ውስጥ ከሌዎንዲዮስ ዘቂሣርያ በ301 ዓ·ም የጵጵስና ማዕርግ በተቀበለው በቅዱስ ጎርጎርዮስ ከሣቴ ብርሃን ስብከት የክርስትናን እምነት ተቀበሉ ይላሉ ።

አውሳብዮስ ዘቂሣርያም ከጎርጎርዮስ ከሣቴ ብርሃን ቀደም ሲል ክርስትና አርመን ውስጥ ተሰብካ እንደነበረ ባዘጋጀው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ያወሳል ።

በዘመነ ብሉይ የኖኅ መርከብ ያረፈችበት አራራት የተባለው ተራራ የሚገኘው አርመን ውስጥ ነው ። አርመኖች የኖኅ መርከብ ጉራጅ ኢትቺሚአድዚን እተባለው ቦታ በሚገኝ ገዳም ውስጥ ተቀምጧል ይላሉ።

አቡነ ጎርጎርዮስ ከሣቴ ብርሃን (300- 325) ቀጰዶቅያ በምትገኘው ቂሣርያ ውስጥ ክርስትናን ከተቀበለና የክርስትና ትምህርቱን ካከናወነ በኋላ ወደ ሀገሩ ወደ አርመን ተመልሶ መንበረ ጵጵስናውን ኤትቺሚአድዚን በተባለ አራራት ተራራ አጠገብ በሚገኝ ቦታ መሥርቶ በሀገሪቱ ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ አደረገ ።

የነገሥታት ዝርያ የሆነው አቡነ ጎርጎርዮስ ከሣቴ ብርሃን ያገባ (ሕጋዊ) ነበር ። የመሞቻው ጊዜ እንደተቃረበ አሪስታኪስ ለተባለው ልጁ ማዕርገ ክህነት ሰጥቶ መንበረ ጵጵስናውን እንዲወርስ አደረገ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለተወሰነ ወቅት የአርመን ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ እንደ አይሁድ ሥርዓት እንደ አሮን ዘሮች ከዘር ወደ ዘር



www.ethiopianorthodox.org

ሲተላለፍ ቈይቶ ነበር ።

ኤትቺሚአድዚን የሚለው ቃል ፍች የእግዚአብሔር አብ አንድያ ልጅ እግዚአብሔር ወልድ ወደ መሬት ወረደ ማለት ነው ። ይኸውም ክርስቶስ ክብ በሆነ ብርሃን ሆኖ ከሰማይ ወርዶ ፥ በራእይ የመዶሻ ቅርጽ ባለው የእሳት ነበልባል እየጠቆመ ቤተ ክርስቲያኑ የሚሠራበትን የተቀደሰ ስፍራ አሳየው ። አቡነ ጎርጎርዮስም ባየው ራእይ መሠረት በእግዚአብሔር አብ አንድያ ልጅ በክርስቶስ ስም የሚጠራ ካቴድራል በ303 ዓ·ም ኤትቺሚአድዚን ውስጥ አሠራ ይላሉ ። እንዲሁም በዚሁ ራእዩ ጥቋቁር ፍየሎች የጠራ ወንዝ እንደተሻገሩ ወደ ነጫጭ የበግ ጠቦትነት ተለወጡና በዙ ። እነሱንም ድቦች ለመብላት ሲሞክሩ ፥ ጠቦቶች እየተጋደሉ ሳይሸነፉ መቅረታቸውን አየ ። ይህም ራእይ የአርመንን ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ታሪክ ይገልጻል ። ይኸውም በጥቋቁር ፍየሎች የተመሰሉት ክርስትናን ከመቀበላቸው በፊት ፥ በነጫጭ የበግ ጠቦቶች የተመሰሉት ደግሞ ክርስትናን ከተቀበሉ በኋላ የነበሩት አርመኖች ናቸው።

እንዲሁም አርመን ውስጥ ክርስትና እ'ሔት እንደተሰበከች ፥ በድብ በተመሰሉ ክርስቲያን ባልሆኑ ጠላቶቿ (ቅኝ ገዥዎቿ) በየጊዜው የተሰነዘሩባትን ስደቶች (መከራዎች) በጌታ እርዳታ በመቋቋምና በማሳለፍ ማሸነፏን ይገልጻል ።

በአቡነ ጎርጎርዮስ ትጋት የክርስትና አሳዳጅ የነበረው የአርመን ንጉሥ ግልሳዊ ትርዳት (261–317) በ301 ዓ·ም ክርስትናን ስለተቀበለ ፥ ትልቁ ቈስጠንጢኖስ ለሮማ መንግሥት ግዛቱ ለክርስትና ነጻነትን ከማወጁ ትንሽ ቀደም ብሎ በንጉሥ ትርዳት ትእዛዝ በአርመን መንግሥት ግዛት ውስጥ ክርስትናን የመንግሥት ሃይማኖት በማድረግ አርመን ከዓለም የመጀመሪያዪቱ ሀገር ናት ።በዚያን ጊዜ ብዙ የጣዖት መቅደሶች እንዲፈርሱ ሲደረግ ፥ አንዳንዶቹ ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ተለወጡ ።

በ365 ዓ·ም በአቡነ ኔርሴስ የተጠራችዋ ሲኖዶስ በምእመናን መካከል ሥር ሰደው የነበሩት በልቅሶ ወቅት ፊት መንጨት ፥ ደረት መድቃት ፥ አጋንንት መሳብ ፥ የተለያዩ ድግምቶች የተጻፉበት ክታብ በአንገት ማሰርና የመሳሰሉትን የአሕዛብ ባህልና የባዕድ አምልኮ ርዝራዦች ከክርስቲያኖች መካከል ለማስወገድ ውሳኔ ተደርጎ ፥ በካህናት



www.ethiopianorthodox.org

ጥረት ምእመናን እነዚህን የክርስትና ትምህርት ተቃራኒ የሆኑ ባህሎችና ባዕድ አምልኮዎች ከመካከላቸው እንዲያስወግዱ ተደርጓል ። እንዲሁም ለሕሙማን መታከሚያ፣ ለሙት ልጆች ማሳደጊያ፣ ለድኩማን መጦሪያ፣ ለመንገደኞች ማረፊያ የሚሆኑ ቤቶች፣ መነኰሳት በኅብረት የሚኖሩባቸው ገዳማት በምእመናን ድጋፍ እንዲሠሩ ተወስኖ በተግባር ላይ ውሏል።

መንፈሳውያን አባቶቻቸው ሥልጣነ ክህነት ከሐዋርያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መሆኑንና ቤተ ክርስቲያናቸውም ከማንም ሥር ሳትሆን ራሷን በመቻል ምእመናኖቿን መጠበቅ (መንከባከብ) እንደሚገባት በማመን በ374 ዓ.ም አርመኖች የቂሣርያን ቤተ ክርስቲያን የበላይ ነኝ ባይነት ሰርዘው ራሷን የቻለች ነጻ ቤተ ክርስቲያን አደረጓት ። ይህም የሆነው ንጉሥ ፓፕ ከአቡነ ኔርሴስ ዕረፍት በኋላ አቡነ ዩሴክ ዳግማዊ ቂሣርያ ሳይሄድ እዚያው አርመን ውስጥ በአርመናውያን ጳጳሳት ሥርዓተ ሢመቱ እንዲፈጸም ባዘዘው መሠረት በመፈጸሙ የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ተቋርጦ የአርመን ቤተ ክርስቲያን በራሷ ልጆች የምትተዳደር ነጻ ቤተ ክርስቲያን ሆነች ።

የግሪክና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች አቡነ ጎርጎርዮስ ከሣቴ ብርሃን በ301 ዓ.ም ከቂሣርያው ጳጳስ ማዕርገ ጵጵስና ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ የአርመን ቤተ ክርስቲያን በቂሣርያ ቤተ ክርስቲያን ሥር ቆይታ በ374 ዓ.ም ነጻ ወጥታ ራሷን በመቻል ትተዳደር ጀመር በማለት የሚተርኩትን የአርመን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አይቀበሉትም ። አርመኖች አቡነ ጎርጎርዮስ ቂሣርያ ውስጥ ስለተማረ በፈቃዱ በጓደኞቹ እጅ ማዕርገ ጵጵስናን ቢቀበልም ቅሉ፣ የአርመን ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ከተመሠረተችበት ወቅት ጀምሮ ከማንም ቤተ ክርስቲያን ሥር ሳትሆን ራሷን ችላ መንፈሳዊ ተግባራትን ስታከናውን ኖራለች ይላሉ ።

በ5ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ የአርመን ፓትርያርክ (ካቶሊኮስ) ታላቁ ቀዳማዊ ይስሐቅና (387-439) ቆሞስ ሜስሮፕ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አንዳንድ የሥርዓት መሻሻል አደረጉ ። ይኸውም ቀደም ሲል የአርመን ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ ፊደል እንኳ ስላልነበራት የምትገለገለው በሱርስትና በግሪክኛ በተጻፉ መጻሕፍት ነበር ። ሆኖም በቅዱስ ሜስሮፕ ትጋትና በእግዚአብሔር እርዳታ



www.ethiopianorthodox.org

የአርመን ሊቃውንት በ400 ዓ.ም ገደማ ተዘጋጅተው ከተጠናቀቁ በኋላ አንድ መቶ የሚሆኑ ምሁራን ለትርጓሜ ሥራ የጽርዕንና የሱርስትን ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ጠንቅቀው ያውቁ በነበሩት በአርመን ፓትርያርክ በቅዱስ ይስሐቅና በቅዋስ ሜስሮፕ አስተማሪነት ሰልጥነው መጽሐፍ ቅዱስን ፣ ሃይማኖተ አበውን ፣ የቅዱስ ባስልዮስን ቅዳሴ ወዘተ ከ404 እስከ 433 ዓ.ም ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ ከሱርስትና ከግሪክኛ ወደ አርመን ቋንቋ ተርጉመው በአገልግሎት ላይ አዋሉ ። ብሉይ ኪዳንን የተረጐሙት ከእብራይስጥ ሳይሆን በጽርዕ ከተዘጋጀው ከሴፕቱአጀንት ነው ። ፔሽታ በተባለው በሱርስት ቋንቋ በተዘጋጀው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍም ለትርጉም ሥራቸው ተጠቅመዋል ።

ብሔራዊ ነጻነታቸውንና የክርስትና እምነታቸውን ለመጠበቅ በ451 ዓ.ም ሀገራቸው የዞሮአስትርን እምነት ይከተሉ ከነበሩ ከፋርሶች ጋር ታካሂደው በነበረው ከባድ የሞት ሽረት ጦርነት ምክንያት የአርመን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ ተገኝተው ተካፋይ ለመሆን ባይችሉም ቅሉ ፣ በአርመን ፓትርያርክ በአቡነ ባብጉኤን ሰብሳቢነት በ506 ዓ.ም ድዊን በተባለች ከተማ በተደረገችው ጉባኤ ላይ የተገኙት የቤተ ክርስቲያን አባቶች የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ ወደ ንስጥሮስ የክሕደት ትምህርት ያዘነበለ መሆኑን በመገንዘብ ፣ የእስክንድር ያው ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ ስለ ክርስቶስ ባሕርይ (ስለተዋሕዶ) ያስተማረውን በመከተል ፣ ሁለት ባሕርይ የሚለውን ውሳኔ በመቃወም ከተዋሕዶዎች ጋር በእምነት ያላቸውን አንድነት አረጋገጡ ።

ቀደም ሲል በእስክንድርያና በሶርያ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ እንደተመለከትነው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና የቢዛንታይን ነገሥታት በሥራቸው ይተዳደሩ የነበሩትን የተዋሕዶ እምነት ተከታዮች በበስተጀርባው "ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት" የሚለውን የኬልቄ ዶን ጉባኤ ኑፋቄ ባዘለው "ክርስቶስ አንድ ፈቃድ አለው" በሚለው ሄኖቲኮን በተባለው የዕርቅ ሰነድ መሠረት የአርመን ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ግሪክ ኦርቶዶክስ እምነት ለመመለስ ሞክረው ሳይሳካላ ቸው ቀረ ። ሆኖም የአርመን አጕራባች በሆነችው በጆርጅያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በአቡነ ኩሪአን አማካይነት የጆርጅያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰባተኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ ወደ ግሪክ



www.ethiopianorthodox.org

ኦርቶዶክስ እምነት ተመልሳለች ። ይህችው የጆርጅያ ቤተ ክርስቲያን በ1811 ዓ·ም በአስተዳደር ከሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ ሁና ከቆየች በኋላ ከ1917 ዓ·ም ጀምሮ እንደ ገና ራሷን ችላ በራሷ ትመራለች ።

ከቻይና ጠረፍ እስከ ሶርያ የነበሩትን ሀገሮች በኃይል ይዞ ይገዛ የነበረው የፋርስ ንጉሥ ያዝዴጊርት በሥሩ የሚተዳደሩ ሕዝቦች ሁሉ በብሔራዊው በዞሮአስትር እምነት መሠረት ፀሐይን ፣ ከዋክብትን ፣ እሳትን ፣ ንጉሡን እንዲያመልኩ በ449 ዓ·ም ዐወጀ ። የንጉሡ እንደራሴ በመሆን አርመንን ያስተዳድር የነበረው አርመናዊውና ክርስቲያኑ ወታደር ቫርታን በዚያ ሕገ ወጥ በሆነው ዐዋጅ እጅግ አዘነ ። እርሱም የአርመን ጳጳሳት በአርታሻት ከተማ ውስጥ ሲኖዶስ አድርገው በዐዋጁ ይዘት ላይ እንዲመከሩበት ከአደረገ በኋላ አርመኖች ለንጉሡ ፍጹም ታማኞችና ታዛዦች መሆናቸውን በመግለጽ የሚያስረዱና የክርስትና እምነታቸውን ግን በምንም መንገድ የማይክዱ መሆናቸውን በመግለጽ አስታውቀው ዐዋጁ በክርስቲያኖች ላይ እንዳይጸና የሚለምኑ ከጳጳሳትና ከምእመናን መርጦ መልእክተኞች ላከ ። ንጉሡም አቤቱታቸውን ተቀብሎ በመፈጸም ፋንታ በመናደድና የፋርስ ነገሥታት ዐዋጅ ፈጽሞ አይለወጥም በማለት ዐዋጁን በኃይል በተግባር ላይ የሚያውሉ ወታደሮ ችን ላከ ። ቫርታንና የአርመን ክርስቲያኖችም የክርስትና እምነታችንን አንክድም በማለት ዱርቢንድ ውስጥ ከንጉሡ ወታደሮች ጋር ከፍ ያለ ጦርነት አካሂደው በሰማዕትነት ዐረፉ ። ቅዱስ ቫርታንና ተከታዮቹ በአርመን ቤተ ክርስቲያን የዱርቢንድ ሰማዕታት ተብለዋል ። ሆኖም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ንጉሥ ያዝዴርጊት ሲሞት ፣ ተጥሎ የነገሠው የፋርስ ንጉሥ ሙሻካን ለአርመኖች የሃይማኖት ነጻነት በመስጠት የክርስትና አምልኮታቸውን በሰላም እንዲፈጽሙ ፈቀደላቸው ።

ቀደም ሲል በፋርስና በቢዛንታይን የቅኝ ገዥ መንግሥታት ለሁለት ተከፍላ ትገዛ የነበረችይቱን አርመንን በሰባተኛው መቶ ዘመን ዓረቦች ሁለቱንም መንግሥታት ድል አድርገው ከያዟት በኋላ የአርመን ቤተ ክርስቲያን የሁለት ባሕርይን እምነት ከሚከተለው ከቢዛንታይን መንግሥት ይሰነዘርባት የነበረው የሃይማኖት ተጽእኖ ስለተወገደላት የአንድ ባሕርይን (የተዋሕዶን) እምነት ያለ ተጽእኖ ታስተምር ጀመር ።


www.ethiopianorthodox.org

ሆኖም ዓረቦች በአርመን ሕዝብ ላይ ከጣሉት ከፍተኛ ግብር በተጨማሪ ማንኛውም የክርስቲያን ሀገር በዓረብ የጦር ኃይል ከመያዙ በፊት ከተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት በስተቀር አዳዲስ እንዳይሠሩ፣ የፈረሱትም እንዳያድሱ በሚያዝዘው "የአማር ቃል ኪዳን" መሠረት አርመኖች ቀደም ሲል በተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት ከመጠቀም በስተቀር ሌላ አዲስ እንዳይሠሩ ተከልክለው ነበር ። አልፎ አልፎ ሕግ አስፈጻሚዎች ላላ በሚሉበት ወቅት ጥቂት አብያተ ክርስቲያናትን እንዲሠሩ ተፈቅዶላቸዋል ። በአርመን ክርስቲያኖችና በካህናቱ ላይም አልፎ አልፎ መጠነኛ የሆነ ሥቃይና ግፍ ይፈጸምባቸው ነበር ።

በዐሥራ አንደኛው መቶ ዘመን ዓረቦችን ድል አድርገው አርመንን የያዙት እስልምናን የሚከተሉ የሳልጁክ ቱርኮች ቋሚ መኖሪያቸውን አርመን ውስጥ በማድረግ በአርመን ክርስቲያኖች ላይ ግደብ የለሽ ከፍ ያለ ጥፋትና ሥቃይ ስለፈጸሙባቸው ከአርመኖች አብዛኞቹ እንደ ኤዴሳ ወደ መሳሰሉ የጐረቤት ሀገሮች ተሰደው ይኖሩ ነበር ።

የአርመን አርበኞች ሲሊሲያ (ሲሊቅያ፣ ሊባኖስ) አካባቢ የነበረውን የቢዛንታይን መንግሥት ሠራዊት ወግተው በማባረር በ1080 ዓ.ም "ትንሿ አርመን" በሚል ስያሜ በሚጠራው የሀገራቸው ክፍል ነጻ መንግሥት መሥርተው እስከ 1375 ዓ.ም ድረስ በነጻነት ኖሩ ። የመንግሥቱ ዋና ከተማም ሲስ (ሲሊቅያ) ነበረች ።

በዙሪያዋ ከነበሩት የቱርክ እስላሞችና የቢዛንታይን ቅኝ ገዥዎች ጋር እየተዋጉ በትንሿ አርመን ውስጥ ነጻነታቸውን ጠብቀው ከቈዩ ከጥቂት ዓመታት በኋላ በሮም ቤተ ክርስቲያን አነሳሽነት የመስቀል ጦርነት ስለተጀመረ፣ የጋራ ጠላት የሆኑትን ቱርኮችን በመዋጋት የጦር መሣሪያ በመለገሥ ይረዱናል በሚል ዓላማ በአርመን ንጉሥ በሌቮንና በፓትርያርክ ጎርጎርዮስ አራተኛ (1185) አነሳሽነት የትንሿ አርመን መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ከመስቀል ጦረኞችና ከሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጋር የቀረበ ግንኙነት ፈጠሩ ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና በሷ ግፊት የዘመቱት ምእመናኖቿ የሆኑ የመስቀል ጦረኞች መሪዎች ዓላማ ግን በተቃራኒው አርመኖችን ከቱርኮች በመላ ነጻ በማውጣቱ ተግባር ተሠማርቶ ለመርዳት ሳይሆን የተዋሕዶ እምነትን የምትከተለው የአርመን ቤተ ክርስቲያን የሁለት ባሕርይን እምነት ተቀብላ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥር እንድትሆን ለማድረግ ነበር ። በግራኝ መሐመድ



www.ethiopianorthodox.org

ወረራ ወቅት በፖርቱጋሎች እርዳታ ሰበብ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ከሥሯ ለማድረግ ሞክራ ሳይሳካላት እንደቀረ ሁሉ ፤ በመስቀል ጦረኞች አማካይነትም የአርመንን ቤተ ክርስቲያን ከሥሯ ለማድረግ ያደረገችው ተገቢ ያልሆነ ሙከራ ሁሉ ከሸፎ ቀረ ።

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ሲል በመስቀል ጦረኞች አማካይነት የአርመንን ቤተ ክርስቲያን ከሥሯ ለማድረግ ያደረገችው ሙከራ በመክሸፉ ተስፋ ሳትቆርጥ እንደገና በዐሥራ ስምንተኛውና በዐሥራ ዘጠንኛው መቶ ዘመን ሚሲዮኖቿን አርመኖች በብዛት ወደሚኖሩባቸው ወደ ቍስጥንጥንያ ፤ ወደ ሊባኖስ ወዘተ· በመላክ ከአርመን ቤተ ክርስቲያን አባላት ጥቂቶችን ወደ ካቶሊክ እምነት መለሰች ። እነሱም የራሳቸውን ቋንቋ ፤ ሥርዓተ ቅዳሴ ፤ ሕገ ቤተ ክርስቲያን እንደጠበቁ ከኦርየንታል (ከተዋሕዶ) ኦርቶዶክስና ከምሥራቅ (ከግሪክ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አባላት በተለያዩ ዘዴዎች የካቶሊክን እምነት በመቀበል "ዩኒአታ" በሚል ስያሜ ከሚጠሩት የካቶሊክ ክፍሎች ናቸው። ኢክርስቲያናዊ በሆነ መንገድ የኦርየንታልንና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አባላትን ወደ እምነታቸው የለወጡ ካቶሊኮች ብቻ ሳይሆኑ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ሚስዮናውያንም ክርስቲያን ያልሆኑትን አስተምረው በመመለስ ፈንታ ያለ ብዙ ድካምና ውጣ ውረድ የኦርየንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተከታዮችን ወደእምነቶቻቸው ለውጠዋል ። አሁንም ይህንኑ ሕገ ወጥ ተግባር በማካሄድ ላይ ናቸው ።

በዐሥራ ስምንተኛው መቶ ዘመን የሩሲያ መንግሥት በወሰኑ እየኖሩ በቱርክ መንግሥት አገዛዝ ሥር ወድቀው ይሠቃዩ የነበሩትን አርመኖች ከኛ ጋር ብትቀላቀሉ በእኩልነት ፤ በሰላምና በነጻነት ትኖራላችሁ በማለት በሰጣቸው ተስፋ የአርመን ፓትርያርክ ተስማማ ። በስምምነቱ መሠረት ፓትርያርኩ ምእመናኑን ስላስተባበራቸው ከፊሉ ከሩሲያ ጋር ተደባልቆ የሚገኘውን የአርመን ክፍል የሩሲያ ጦር ሠራዊት በአርመኖች በመረዳት በ1828 ዓ·ም በጦር ኃይል ከኦቶማን ቱርኮች አስለቅቆ ስለያዘ መንበረ ፓትርያርካቸውን ከዋናዋ ከተማ ከየሬቫን እምሳ ማይል ርቃ በምትገኘው በኢትቺሚአዲዚን ውስጥ መሥርተው እንደማንኛውም የሩሲያ ዜጋ በነጻነትና በሰላም ኖሩ ። በጥር ወር 1992 ዓ·ም



www.ethiopianorthodox.org

የሶቪየት ሶሻሊስት ሪፐብሊክ መንግሥት ፈርሶ በሥሩ የነበሩት ራስ ገዝ ሀገሮች የየራሳቸውን ነጻነት ስለተጐናጸፉ የአርመን ክርስቲያኖችም በነጻይቱ የአርመን መንግሥት ውስጥ በሰላም አምልኮአቸውን እየፈጸሙ ይኖራሉ ።

የአርመን መንበረ ፓትርያርክ በሰላም እጦት ምክንያት ቀደም ሲል ከተመሠረተበት ከዋናው ቦታ ከኢትቺሚአዲዚን ድዊን ፣ ቫን ፡ ሲስ ወዘተ· ወደተባሉ ከተሞች ከ901–1441 ዓ·ም ለ540 ዓመታት ሲዘዋወር ከኖረ በኋላ በ15ኛው መቶ ዘመን እንደገና ከሲስ ወደ ኢትቺሚአዲዚን ተመልሶ እስከ ዛሬ ድረስ እዚያው ይገኛል ።

በ14ኛው መቶ ዘመን ኢየሩሳሌም ፤ በ15ኛው መቶ ዘመን ቍስጥንጥንያ የተቋቋሙት የአርመን መንበረ ፓትርያርኮች ኢትቺሚአዲዚን ከሚገኘው ከመላው የአርመን ፓትርያርክ ሥር ናቸው ። ይኸው በኢትቺሚአዲዚን የሚገኘው የአርመን መንበረ ፓትርያርክ ከሀገሩ ውጭ በአውሮጳ ፣ በአሜሪካ ፣ በካናዳ ወዘተ· ውስጥ በሥሩ የሚተዳደሩ አብያተ ክርስቲያናት አሉ ።

ቀደም ሲል ሲስ (ሲሊቅያ) የነበረው ፤ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ወደ ሊባኖስ ተዛውሮ አንቴሊያስ ከተባለው ቦታ የሚገኘው የአርመን ካቶሊኮስ ሩሲያ (አርመን) ውስጥ ኢትቺሚአዲዚን ከሚገኘው ፓትርያርክ (ካቶሊኮስ) ጋር በማዕርግ እኩል ነን ባይ ነው ።

በቱርክ ግዛት ሥር በከፊል በቀረው የአርመን ሀገር በሚኖሩ አርመኖች ላይ በየጊዜው በቱርኮች በተሰነዘሩባቸው አስከፊ መከራዎችና ጭፍጨፋዎች ሲሠቃዩ ኖረዋል ። በስደት ይኖሩ የነበሩትና በሀገር ውስጥ የነበሩ የአርመን ወጣቶች ተደራጅተው ሀገራቸውን ከቱርክ ነጻ ለማውጣት ያደረጉትን ከፍተኛ እንቅስቃሴ በመፍራት ከ19ሥራ ዘጠንኛው መቶ ዘመን መጨረሻ (1895) ጀምሮ በተለይ አንደኛው የዓለም ጦርነት ይካሄድ በነበረበት ወቅት በቱርክ መንግሥት ሱልጣን በታላትፓሻ አነሳሽነት በ1915 ዓ·ም ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ አርመኖች በግፍ ተጨፍጭፈዋል ። ወደ ተለያዩ ሀገሮችም ተሰደዋል ።

በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊው ኑሮአቸው በዓለም ተበትነው የሚኖሩ አርመኖች አንድነታቸውን አጽንተው የኖሩ ፣ ያሉና የሚኖሩ በቤተ ክርስቲያናቸው ጥላ ሥር በመሰብሰብ ነው ። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ መንፈሳዊ ነክ የሆኑ ተግባሮች በካህናት ሲከና



www.ethiopianorthodox.org

ወኑ፡ አስተዳደር ነክ የሆኑ ተግባሮች ደግሞ የሚያከናውኑት በምእመናን ነው ።

ባጠቃላይ የአርመን ቤተ ክርስቲያንና ሕዝብ አንድነት የጠበቀ ስለሆነ ተደጋግፈው እንደኖሩ ሁሉ ለወደፊትም የሚኖሩ መሆናቸው ግልጽ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል ሦስት

## የምሥራቅ (የግሪክና የእስላቮኒክ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ

### የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ታሪክ

ክርስትና በክርስቶስ ፣ በሐዋርያትና በየጊዜው በተነሡ የወንጌል መልእክተኞች ተሰብካ ፣ ከአሕዛብና ከአይሁድ የደረሱባትን መከራዎችና ስደቶች በትእግሥት ተቀብላ በመቋቋም በዓለም ተስፋፋች ። በተለይ ትልቁ ቈስጠንጢኖስ ነጻነቷን አጐናጽፎ የመንግሥቱ ሃይማኖት ካደረጋት በኋላ ያላንዳች ተቃውሞ በይፋ ትሰበክ ጀመር ።

በዚያን ዘመን ዋና መናገሻ ከተማ የነበረችው ሮም በጣዖት ቤተ መቅደሶችና በባዕድ አምልኮ ተጥለቅልቃ ነበር ። እንዲሁም ለጥ ባለ ሜዳ ላይ በመመሥረቷ በየጊዜው ከጠላት ለሚሠነዘሩ አደጋዎች ሁሉ የተጋለጠች ነበረች ። በነዚህና በመሳሰሉ ምክንያቶች ቈስጠንጢኖስ ለአውሮጳና ለእስያ አማካይና መገናኛ ወደነበረችውና ጠላትንም ለመከላከል በተፈጥሮ ምቹ እስትራቴጂካዊ አቀማመጥ ወደ ነበራት ቢዛንታይን ወደተባለችው የግሪክ ከተማ በ330 ዓ.ም መናገሻ ከተማውን አዛውሮ እዚያው ሆኖ ምዕራቡንና መሥራቁን የሮማ መንግሥት (ኤምፓየር) ይገዛ ነበር ። ይህችው አዲሲቱ መናገሻ ከተማ ለቈስጠንጢኖስ ክብር ሲባል ቢዛንታይን የተባለው ስሟ ተለውጦ ቍስጥንጥንያ ተባለች ። በዚችው ከተማ ውስጥ ጣዖት አምልኮ እንዳይፈጸም ቈስጠንጢኖስ ከለከለ ። በ1453 ዓ.ም የቢዛንታይንን መንግሥት በጦር ኃይል ድል አድርጎ ሀገሪቱን በሚያስተዳድራት በቱርክ መንግሥት ይህች ከተማ እስታንቡል ተብላ ተሰየመች ።

ቈስጠንጢኖስ በዚችው ከተማ ዝነኛ የሆነችውን የቅድስት ሶፊያ



www.ethiopianorthodox.org

ንና ሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት አሠራ ። መጀመሪያ የተሠራችው የቅድስት ሶፊያ ቤተ ክርስቲያን በእሳት ስለተቃጠለች ንጉሥ ዩስጢንያኖስ ከ532 እስከ 537 ዓ·ም በነበረው ጊዜ በዓለም ከነበሩት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ወደር የማይገኝላት አድርጎ አሠራት ። ሆኖም የቢዛንታይን መንግሥት በቱርኮች እጅ ከወደቀበት ከ1453 ዓ·ም ጀምሮ የቅድስት ሶፊያ ቤተ ክርስቲያን የእስላሞች መስጊድ ሆና ከቈየች በኋላ ከ1934 ዓ·ም ጀምሮ ሙዚየም እንድትሆን ተደረገ ። የቅድስት ሶፊያ ቤተ ክርስቲያን ወደ መስጊድነት ከተለወጠች በኋላ በ1603 ዓ·ም የቍስጥንጥንያው መንበረ ፓትርያርክ ብዙ ግሪኮች በሚኖሩበት ፋናር በተባለው የከተማው ክፍል ወደሚገኘው ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ተዛወረ ። እስከ ዛሬ ድረስ መንበረ ፓትርያርኩ የሚገኘው በዚሁ ፋናር በተባለው ቦታ ነው ።

በተለያዩ ሀገሮች የሚገኙት የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ሁሉ በአስተዳደር ሳይሆን በሃይማኖት አባትነት አክብረው የበላይነቱን (የመንፈሳዊ አባትነቱን) የሚቀበሉት የቍስጥንጥንያ (የአዲሲቱ ፥ የዳግማዊት ሮም) የዓለም ፓትርያርክ በዚችው ከተማ ተቋቋመ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪ የፖፑ መንበር ሮም ውስጥ ሲሆን ፥ የግሪክ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መሪ መንበረ ፓትርያርክ ደግሞ ቍስጥንጥንያ ውስጥ ሆነ ። ለቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ የዓለም ፓትርያርክ የሚለው ከፍተኛ ማዕርግ የተሰጠው በአቡነ ዮሐንስ ዘመን በ595 ዓ·ም ነው ።

በአምስተኛው ፥ በስድስተኛውና በሰባተኛው መቶ ዘመን የምዕራቡ ክፍል አልፎ አልፎ በአሕዛብ ነገዶች ሲወረር ወዲያው እንደ ቀዳማዊ ዩስጢንያኖስ (535—562) በመሳሰሉት የቢዛንታይን ነገሥታት ነጻ እየወጣ በቢዛንታይን መንግሥት ሥር ሲተዳደር ከቈየ በኋላ በስምንተኛው መቶ ዘመን አጋማሽ ላይ የፍራንኮች ንጉሥ ፔፒን ሎምባርዶችንና በአካባቢው የነበሩትን ገዥዎች ደምስሶ በመካከለኛው ኢጣልያ "የተቀደሰው የሮማ ኤምፓየር (ግዛት)" የተባለውን መንግሥት መሠረተ ። ይኸውም መንግሥት ተከፋፍለው የነበሩት የኢጣልያ ክፍሎች እስከተዋሐዱበት ጊዜ ድረስ ለ1000 ዓመታት ያህል ቈይቷል ። ስለዚህ አንድ ሆኖ የቈየው መንግሥት የምሥራቅና የምዕራብ መንግሥታት በመባል ሁለት



www.ethiopianorthodox.org

ላይ ስለተከፈለ የሁለቱም ክፍል አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ነገሥታት የየራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን መሪ ክብር (ማዕርግ) ይደግፉ ጀመር ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቍስጥንጥንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥታት ጋር በመተባበር የእስላሞች ሐዋርያት በመባል የሚጠሩትን የወንጌል መልእክተኞቿን እንቅዱስ ቄርሎስንና ሜቶዲዮስን በምሥራቁ ክፍል በማሠማራት ክርስትናን ስታስፋፋና መንፈሳዊ ተግባሯን ስታከናውን ፣ የካቶሊክ (የምዕራብ) ቤተ ክርስቲያን ግን ልታከናውነው ከሚገባት መንፈሳዊ ተግባር በተጨማሪ በነገሥታቱ ላይ ተጽእኖ ታደርግ ነበር ። አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር ተባብራ ብትሠራም ቅሉ የነገሥታቱ ታዛዥ ነበረች ይላሉ ። ሐቁ ግን ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ተባብረው ቢሠሩም የመንግሥት ተግባር የሕዝቡን ደኅንነት በመጠበቅ ማስተዳደር ሲሆን ፣ የቤተ ክርስቲያን ተግባር ደግሞ ምእመናንን እያስተማሩና እያጽናኑ በመንፈሳዊው መንገድ መምራት ነበር ። ሆኖም አልፎ አልፎ በአንዳንድ ሕገ ወጥ ነገሥታት በቤተ ክህነቱ ላይ ከተፈጸሙት ጣልቃ ገብነቶች በስተቀር በአጠቃላይ የቢዛንታይን መንግሥት በቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ ተግባር ውስጥ ጣልቃ በመግባት ተጽእኖ አያደርግም ነበር ። ለምሳሌ በ8ኛውና በ9ኛው መቶ ዘመን ላይ ነገሥታቱ እነ ልዮን ሦስተኛ ፣ ቈስጠንጢኖስ አምስተኛና ደጋፊዎቻቸው የሆኑ አንዳንድ ካህናት ከአይሁድና ከእስልምና እምነት ተከታዮች ወደ ክርስትና ለመመለስ ለሥዕል የሚደረገው ስግደት መሰናክል ስለሆነና ባዕድ አምልኮም መስሎ ስለታያቸው የጸጋ (የአክብሮት) ስግደት ማድረግ አይገባም ሲሉ ፤ በተቃራኒው ከቤተ ክህነት እንቅዱስ ዮሐንስ ደማስቂኖስ (ዮሐንስ ዘደማስቆ) ፣ ቅዱስ ቴዎዶሬ ፣ ፓትርያርክ ኒኪፎሮስ ፣ የሮሙ ፖፕ ሣልሳዊ ጎርጎርዮስ ወዘተ· በተለያዩ ቀለማት አምሮ የተዘጋጀውን ሥዕል ለማምለክ ሳይሆን ፤ ጌታን ፣ እመቤታችንን ፣ ጻድቃንንና ሰማዕታትን በማሰብ ፤ ጌታ ኃጢአታችንን ይቅር እንዲለን ፤ ጻድቃን ፣ ሰማዕታትና መላእክት እንዲያማልዱን የጸጋ ስግደት መደረግ መገባቱን ደግፈው ተነሡ ። በሁለቱ ክፍሎች መካከል እያሌ ጊዜ የፈጀ ብዙ ፍጅትና ውጣ ውረድ ከተካሄደ በኋላ በ787 ዓ·ም ኒቅያ ውስጥ በተደረገችው በሰባተኛዋ ጉባኤ ላይ የተገኙት ጳጳሳት ለጌታ ፣ ለጻድቃን ፣ ለሰማዕታትና ለመላእክት



www.ethiopianorthodox.org

ሥዕል የጸጋ ስግደት መደረግ መገባቱን ወስነው አጸደቁ ። ይኸው ተግባር እስከ ዛሬ ድረስ በግሪክ ኦርቶዶክስ ፣ በኦርየንታል ኦርቶዶክስና በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ይፈጸማል ።

ቀደም ሲል በኒቅያ ፣ በቍስጥንጥንያና በኤፌሶን የተደረጉት ጉባኤዎች በቤተ ክርስቲያን ጥያቄ መሠረት በነገሥታቱ ቢጠሩም ቅሉ ውሳኔዎችን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ያስተላለፉ በጉባኤዎቹ ላይ የተገኙ (የተካፈሉ) ጳጳሳት ነበሩ ። ሆኖም በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ ግን የቍስጥንጥንያ ንጉሥ መርቅያን ጣልቃ በመግባት ቅዱስ ዲዮስቆሮስ እንዲሠቃይ አድርጓል ። የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ ፍርደ ገምድልና ሕገ ወጥ በመሆኑ የኦርየንታል (የተዋሕዶ) አብያተ ክርስቲያናት አይቀበሉትም ። የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት የሚቀበሉት የመጀመሪያዎቹን የሦስቱን ጉባኤዎች ውሳኔ ብቻ ነው ። የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በነዚህ በሦስቱ ላይ አራት ጉባኤዎች በመጨመር የሰባት ጉባኤ ውሳኔዎችን ይቀበላሉ ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በሰባቱ ላይ ዐሥራ አራት ጉባኤዎች በመጨመር የሃያ አንድ ጉባኤ ውሳኔዎችን ትቀበላለች ።

የሮሙ ፖፕ ልዮን ሣልሳዊ በ800 ዓ·ም ታላቁ ቻርልስን (ቻርሌማኝን) የተቀደሰችዋ የሮማ መንግሥት ንጉሠ ነገሥት እንዲሆን ቀብቶ በማንገሡ ቀደም ሲል በምሥራቁና በምዕራቡ ክፍል የተፈጠረውን መለያየት አባባሰው ።

እንዲሁም በኒቅያና በቍስጥንጥንያ ጉባኤዎች በተወሰነው በጸሎተ ሃይማኖትና በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለውን የሮም ቤተ ክርስቲያን በ1014 ዓ·ም "መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሳይሆን ከወልድም ተገኘ" ብላ በመወሰን አዲስ ትምህርት በማስተማሯ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በጥብቅ ተቃውማለች ። በተጨማሪም በኬልቄዶን ጉባኤ በ28ኛው አንቀጽ የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ ከሮሙ ፖፕ ጋር በማዕርግ በማስተካከል የተወሰነውን በመጣስ በ1870 ዓ·ም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያው የቫቲካን ጉባኤ በተወሰነው መሠረት የሮሙ ፖፕ ?የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበላይ ነኝ ሲል ፣ የቍስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ክብር እኩል ነው በማለታቸው ስለጸኑ በመካከላቸው የማይታረቅ ቅራኔ ተፈጥሮ ንትርክ ተጀመረ ። ስለዚህ የበላይ ነኝ ፣ አይደለህም ፣ በመባባል በሁለቱ አብያተ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያናት መካከል የተፈጠረው የማዕርግ ንትርክ በ863 ዓ·ም በቍስጥ ንጥንያው ፓትርያርክ በፎትዮስና በሮሙ ፖፕ በቀዳማዊ ኒኮላዎስ ተጀምሮ ጥቂት ዘመን ከቈየ በኋላ በ1054 ዓ·ም ከሮሙ ፖፕ ከልዮን 9ኛ ተልከው ወደ ቍስጥንጥንያ የሄዱት መልእክተኞች እነ ካርዲናል ሑምበርት የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ሚካኤል ኪሩላሪዎስ የፖፑን የበላይነት ሥልጣን ስላልተቀበለ አወገዙት ። እሱም በዚያው ዓመተ ምሕረት የሮሙን ፖፕ አወገዘው ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ተለያይተው የጐሪጥ እየተያዩ ለዘመናት ኖሩ ።

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የቢዛንታይን ነገሥታት ኀይል ጠንካራ በነበረበት ዘመን ድምጿን አጥፍታ ቈይታ በዚህ ወቅት የቍስጥንጥንያን ፓትርያርክ ለማውገዝ በሙሉ ልብ ቈርጣ የተነሣችበት ምክንያት በ800 ዓ·ም ሮም ከተማ ውስጥ በፖፑ ሥርዓቱ ንግሡ ተፈጽሞለት በምዕራብ አውሮጳ ክፍል የተመሠረተው "የተቀደሰው የሮማ ኤምፓየር" ንጉሠ ነገሥት ሆኖ ዘውድ ከጫነውና ከቢዛንታይን መንግሥት ካፈነገጠው ፤ የቢዛንታይንንም ዙፋን ደምስሶ የበላይ ለመሆን ይሻ ከነበረው የፍራን ኮች ነገሥታት ዘር ከሆነው ከንጉሥ ቻርልስ ፖፑ ባገኘው ሙሉ ድጋፍ በመረዳት ነበር ።

እንዲሁም እላይ እንደተመለከትነው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን "መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሳይሆን ከወልድም ተገኘ" የሚለውን ኑፋቄ ቀደም ብላ ለአርባ ዓመታት ያህል ስታስተምር የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት ምንም ዓይነት ተቃውሞ ሳታቀርብ ቈይታ ፤ በ9ኛው መቶ ዘመን የማዕርጉ ንትርክ ሲፋፋም የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ለመቃወም በማቀድ እንደ ዋና ምክንያት አድርጋ አቀረበች ።

በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አነሳሽነት ኢየሩሳሌምን ከእስላሞች ነጻ ለማውጣት በተደጋጋሚ ከዘመቱት የመስቀል ጦረኞች በአራተኛው ዙር በ1202 ዓ·ም በቬንቲያን መርከቦች ተሳፍረው በግብጽ በኩል አድርገው ወደ ፍልስጥኤም ለመጓዝ የተንቀሳቀሱት ካቶሊካውያን የመስቀል ጦረ ኞች፥ በሮሙ ፖፕ በታቀደው የጥፋት ዓላማ መሠረት የተሰለፉለትን ቅዱስ ተግባር ትተው የክርስትና መዲና የሆነችውን ቍስጥንጥንያን በ1203 ዓ·ም ወረሩ ። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናትንና ምእመናንን በመጨፍጨፍ ፤ በከተማይቱ የነበረውን ሀብት በመዝረፍ



www.ethiopianorthodox.org

የቢዛንታይንን መንግሥት በኃይል አስወግደው በ1204 ዓ·ም የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆነ የላቲን መንግሥት አቋቋሙ ። በፖፕ ኢኖሴንት ሦስተኛ ትእዛዝ ቶማስ ሞሮሲኒ የተባለው ካቶሊካዊ ካህን የቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሆኖ በመሾም በቍስጥንጥንያ አርቶዶክስ መንበረ ፓትርያርክ ላይ ተቀመጠ ። ይህ ዐይነቱ ሕገ ወጥ ድርጊት ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት በማቀራረብ ፈንታ ግሪኮች በካቶሊኮች ላይ የነበራቸውን ጥላቻ እያባባሰው ሄደ ። ሆኖም ከጥቂት ጊዜ በኋላ የግሪክ አርቶዶክስ እምነት ተከታይ የነበረው ግሪካዊው ንጉሥ ሚካኤል ስምንተኛ (1259 1282) ላቲኖችን በ1261 ዓ·ም ድል አድርጎ የቢዛንታይንን መንግሥት እንደገና አቋቋመ ።

ፖፖች ከቱርክ እስላሞች ጋር በመዋጋት ክርስትናን ይንከባከብ የነበረውን የቢዛንታይን መንግሥት በመርዳት ማጠናከር ሲገባቸው ፡ በመስቀል ጦረኞች በማስወረር አዳከሙት ። የቢዛንታይን ነገሥታትም ተስፋ ሳይቈርጡ እየተከላከሉ ቱርኮችን ለመቋቋም የሚያስችል የጦር እርዳታ ፖፖችና የካቶሊክ እምነት ተከታይ ነገሥታት እንዲለግሱአቸው ሲጠይቁ ፡ የፖፖች ምላሽ መጀመሪያ የካቶሊክን እምነት ተቀብላችሁ ከሥራችን ሁኑና እንርዳችሁ የሚል ነበር ። አንዳንድ ነገሥታት ሐሳቡን ቢቀበሉም እንኳ የአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእምነታቸው ፈቀቅ ባለማለታቸው ፡ እንዲሁም በፌራራና በፍሎሬንስ (1438—1439) በተደረገው ጉባኤም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የአርቶዶክስን ቤተ ክርስቲያን ከሥሯ ለማድረግ ያደረገችው ጥረት ሙሉ በሙሉ ተቀባይነትን ባለማግኘቱ የጦር እርዳታው ጥያቄ ከሽፎ ቀረ ። በዚህ አኳኋን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ንትርኩን በማፋፋሟና የአውሮጳ ነገሥታት የጦር እርዳታ እንዲለግሡ ለማግባባት ፈቃደኛ ባለመሆኗ ቍስጥንጥንያ በ1453 ዓ·ም በቀላሉ በቱርኮች እጅ እንድትወድቅና ባጠቃላይ ክርስትናም እንድትዳከም አፍራሽ ተጽእኖ አድርጋለች ። ቍስጥንጥንያን በ1453 ዓ·ም በጦር ኃይል የያዘው የቱርኮች መሪ ዳግማዊ መሐመድ የአርቶዶክስ ካህናትና ምእመናን ከኃያላኑ ምዕራባውያን ነገሥታትና ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር ግንኙነት አድርገው እንዳያምጹበት በማሰብ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ጥላቻ የነበረው ጌናዲዮስ አስኮላሪስ የተባለው ካህን የቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሆኖ እንዲሾም ፈቀደ ። ፓትርያርኩም በ1472



www.ethiopianorthodox.org

ጉም ቍስጥንጥንያ ውስጥ ጉባኤ ጠርቶ በቴዎሪ ደረጃ አለ ይባል የነበረውን በፍሎሬንስ ጉባኤ የተወሰነውን የአንድነት ስምምነት በይፋ በመሠረዝ ውድቅ አድርጎ ግንኙነቱን አቋረጠ ። የፓትርያርኩም ተጠሪነት ለቱርክ ሡልጣን ሆኖ በቱርክ መንግሥት ሥር በሚገኙ በተለያዩ ሀገሮች ለሚኖሩ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ክርስቲያኖች ሁሉ የመንፈሳዊና የዓለማዊ መሪነት ሥልጣን ተሰጠው ። ፓትርያርኩና ጳጳሳት ከቀረጥ (ከግብር) ነጻ እንዲሆኑ ተደረገ ። ሆኖም ይህ ዓይነቱ የይስሙላ ሥልጣን ለፓትርያርኩ ቢሰጥም በቱርክ በተያዙ በተለያዩ ሀገሮች የነበሩ ምእመናን በታላቅ ተጋድሎ ነጻነታቸውን እስከተቀዳጁ በት ጊዜ ድረስ ለአራት መቶ ዓመታት ያህል በቱርኮች ብዙ ጭቆናዎች ተፈጽመውባቸዋል ። ። ከጭቆናዎችም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ/ ክርስቲያኖች የወንጌል መልእክተኛነትን ተግባር እንዳያከና ውኑ ተከለከሉ ። የክርስትናን ትምህርት በቱርክ ግዛት ውስጥ ሲሰብክ የተገኘ ሁሉ ተግባሩ እንደ ፖለቲካ ወንጀል ተቈጥሮ ከፍ ያለ ቅጣት ይደርስበት ነበር ። ሆኖም ቀደም ሲል በቍስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ሲካሄድ የቈየውን የስብከተ ወንጌል ተግባር ለማራመድ (ለማስፋፋት) የቻለችው ነጻዋ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነበረች ።

እንዲሁም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለ400 ዓመታት በቱርክ መንግሥት ቀንበር ሥር በቈየችበት ወቅት ትምህርት ቤቶች ከፍታ ካህናትን እንዳታሰለጥን ፡ ለካህናትና ለምእመናን የሚያገለግሉ መጻሕ ፍት እንዳታሳትም ወዘተ ታግዳ ነበር ። በነዚሁ ምክንያቶች የካህናቶቹ የመንፈሳዊ ትምህርት ችሎታም (ዕውቀትም) ተቀንሶ ነበር ። ሆኖም በግላቸው ጥረትና ትጋት የተለያዩ መጻሕፍትን እየዘውትረው በማጥናት ፡ ምዕራብ አውሮጳ በሚገኙ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት መንፈሳዊ ትምህ ርት ቤቶች በመማር ከፍ ያለ ዕውቀት የገበዩ አንዳንድ ኦርቶዶክሳውያን ሊታወንት ነበሩ ። እነሱም ምዕራብ አውሮጳ ውስጥ ከካቶሊክና ከፕሮቴስታንት መምህራን መንፈሳዊ ትምህርቶች በቀሰሙበት ወቅት በጥቂቶቹ ላይ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት እምነት መጠነኛ ተጽእኖ አሳርፎባቸው ነበር ።

2ኛ ፓትርያርክ በተመረጠና በተሾመ ቍጥር ለቱርክ መንግሥት ከፍ ያለ ገንዘብ መክፈል ግዴታ ነበር ። ጳጳሳትም ሲሾሙ እንደ አቅማቸው መጠነኛ ገንዘብ ለቱርክ መንግሥት የመክፈል ግዴታ



www.ethiopianorthodox.org

ነበረባቸው ።

3ኛ/ የቍስጥንጥንያ ፓትርያርኮች የበላይነት ሥልጣናቸውን በማፅከላዊነት አሰባስበው ለማጠናከር በማሰብ ፡ የቡልጋርያንና የሰርቢያን ፓትርያርኮች ሥልጣን ዝቅ በማድረግ የሀገሬውን ተወላጅ እየሻሩ የግሪክ ተወላጅ ካህናት በመሾም ከመንፈሳዊ መረና አባት የማይጠበቅ አሳዛኝና የዘረኝነት ተግባር ፈጽመዋል ። ይህም ተግባራቸው የየሀገሩን ተወላጅ ምእመናን አስቆጥቶ በየሀገሩ የብሔርተኝነት ስሜት ቀሰቀሰ ። ቀስ በቀስም የግሪክ ተወላጅ የሆኑ ጳጳሳትን በማስወገድ የየራሳቸውን የፓትርያርክነት ማዕርግ በማስመለስ ቤተ ክርስቲያናቸው በየሀገራቸው ተወላጅ ፓትርያርኮችና ጳጳሳት እንድትመራ አደረጉ ። ይህ ዓይነቱ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የእርስ በእርስ የመንፈሳዊ ሹመት ሽኩቻ (ጠብ ፡ ንትርክ) በተመልካች ዘንድ አሳፋሪና አሳዛኝ እንደነበረ ግልጽ ነው ።

ምንም እንኳ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበራት ግንኙነት የቈየ ቢሆንም ከፕሮቴስታንት ሊቃውንት ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ግንኙነት ያደረገችው በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ላይ ነበር ። ይኸውም ከ1573—1574 ዓ·ም በነበረው ጊዜ ውስጥ ቱቢንጌን የነበሩ ሉተራውያን ምሁራን ለቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ለዳግማዊ ኤርምያስ የአውግስበርግን መሠረተ ሃይማኖት የግሪክኛ ቅጅ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት አንጻር አስተያየት እንዲሰጥበት በመጠየቅ ላኩለት ። ፓትርያርኩም ከግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ጋር የጽሑፉን ይዞታ በሚገባ ካጠናና ከመረመረ በኋላ በዚሁ ጽሑፍ ላይ ብቻ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያላትን የጠነከረ የተቃውሞ ሂስ ወዳጅነትን በተከተለ መንፈስ ጽፎ ላከላቸው ።

ከዚህ በሁለቱ ወገን ምሁራን መካከል ከተደረገው የመጻጻፍ ግንኙነት አንዳችም ተጨባጭ ውጤት አልተገኘም ። ሆኖም በዐሥራ ሰባተኛው መቶ ዘመን በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አደገኛ የሆነ እምነት ነክ ችግር ተፈጥሮ ነበር ። ይኸውም በ1620 ዓ·ም የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ቄርሎስ ሉካሪስ በቱርክ (በቍስጥንጥንያ) የዳች አምባሳደር ከነበረው ከፕሮቴስታንቱ ከቆርኔሊዎስ ሐጋ ጋር የጠበቀ ግንኙነት መሥርቶ ስለነበር ፡ እንዲሁም ቀደም ሲል አውሮጳ ይማር በነበረበት ወቅት በሉተራንና በካልቪኒስቶች ትምህርት ተስቦ ስለነበር በቆርኔሌዎስ



www.ethiopianorthodox.org

ግፊትና ትብብር አቡነ ሉካሪስ የካልቪንን እምነት የሚከተል መሠረተ ሃይማኖት በላቲን ቋንቋ አዘጋጅቶ ጄኔቭ ውስጥ አሳትሞ አወጣ ። በመጽሐፉም ውስጥ የእምነታችን መሠረትና መገኛ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ፡ ፕሮቴስታንቶች ከሚቀበሏቸው ከስድሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በስተቀር ሌሎቹ አዋልድ ናቸው ፡ ቅዱስ ቍርባንም ለማስታወሻ የሚፈጸም እንጂ ኅብስቱና ወይኑ ካህኑ በሚጸልይበት ጊዜ ወደ ጌታ ሥጋና ደም አይለወጥም ፡ መላእክት ፡ ጻድቃንና ሰማዕታት አያማልዱም ፡ ለጌታ ፡ ለእመቤታችን ፡ ለጻድቃንና ለሰማዕታት ሥዕሎች የአክብሮት ስግደት ማድረግ አይገባም አለ ። ባጠቃላይ እነዚህንና የመሳሰሉትን የፕሮቴስታንት እምነቶች ጻፈ ።

ዋናው የአቡነ ሉካሪስ ዓላማ እስላሞችን አስተምሮ ወደ ክርስትና መመለስ ሲሳናቸው በኦርቶዶክስ ምእመናን መካከል ተሰግስገው ኦርቶዶክሶችን በብዛት ወደ ካቶሊክ እምነት ይመልሱ የነበሩትን የካቶሊክ ሚስዮናውያን ለመቃወም በማሰብ ነበር ይባላል ። ሆኖም ከካልቪን ተከታዮች ጋር የጀመረው የቅርብ ግንኙነት ወደ ፕሮቴስታንት እምነት ጭልጥ ብሎ እንዲገባ አደረገው ። ፕሮቴስታንቶችም በፓትርያርኩ በተዘጋጀው መሠረተ ሃይማኖት አማካይነት የኦርቶዶክስን ምእመናን በቀላሉ ወደ ፕሮቴስታንት እምነት የሚመልሱ መስሏቸው በመደስት ወዲያውኑ መጽሐፉን በፈረንሳይ ፡ በእንግሊዝ ፡ በጀርመን ወዘተ. ቋንቋዎች ተርጕመው ጄኔቫ ውስጥ አሳትመው በዓለም አሰራጩት ። በዚያን ወቅት በድርጊቱ እጅግ ያዘኑና የተቆጡ ካቶሊኮች ቍስጥንጥንያ በነበሩት በፈረንሳይና በኦውስትርያ አምባሳደሮቻቸው አማካይነት ለኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት የማቴሪያልና የፖለቲካ ድጋፍ በመለገስና በማደፋፈር ሉካሪስን በከሐዲነት አስወግደው ከመንበረ ፓትርያርኩ እንዲወርድ አደረጉ ። አምባሳደሮቹ በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ ሉካሪስ ከሩሲያ መንግሥት ጋር ቱርክን ለማስወጋት ዶልቷል ብለው በመወንጀላቸው በቱርክ መንግሥት ተገደለ ። ወዲያው በ1638 ዓ.ም በቍስጥንጥንያ ፡ በ1640 ዓ.ም በኪየቭ ፡ በ1642 ዓ.ም በጃስየ ፡ በ1672 ዓ.ም በኢየሩሳሌም፡ በተደረጉ ሲኖዶሶች የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሉካሪስንና መጽሐፉን አውግዛለች ። እንዲሁም ቀደም ሲል ሉካሪስ በእስክንድርያ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በነበረበት ወቅት



www.ethiopianorthodox.org

በአምስተኛው መቶ ዘመን በግሪክኛ የተጻፈውን ኮዴክስ አሌክሳንድሪኑስ የተባለውን መጽሐፍ ቅዱስ ለእንግሊዝ ንጉሥ ለቀዳማዊ ቻርለስ በስጦታ መልክ ስላበረከተው ለንደን በሚገኘው በብሪተሽ ሙዚየም ተቀምጧል ።

ባጠቃላይ የቀውስጥንጥንያው ፓትርያርክ የሉካሪስ ተግባር ለጥቂት ዓመታት በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ጥቁር ነጥብ ጥሎ ከቄየ በኋላ የኪየቭ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ ሞግሒላ በ1640 ዓ·ም· የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናትን መንፈሳዊ ዕውቀት ከፍ ለማድረግ በማሰብ የካህናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ከፈተ ። ማተሚያ ቤትም አቋቁሞ መንፈሳዊ ነክ መጻሕፍትን እያሳተመ ማሠራጨት ጀመረ ። በቤተ ክርስቲያኒቱ እምነት ላይ ሉካሪስ የጣለውን ጥቁር ነጥብ ለመፋቅ በማሰብ የኦርቶዶክስን እምነት አብራርቶ የሚገልጽ መሠረተ ሃይማኖት አዘጋጅቶ አሳተመ ። ይህንኑ መጽሐፍ የኪየቭ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወዲያው በይፋ ተቀብላ በማስተማሪያነት ላይ አዋለችው ። እንዲሁም ጥቂት እርማቶች ከተደረጉለት በኋላ በሙሉ የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ ከሩሲያ ቋንቋ ወደ ግሪክኛ ተተርጕሞ በሰፊው በአገልግሎት ላይ ዋለ ።

ከጴጥሮስ ሞግሒላ ቀጥሎ የኦርቶዶክስን እምነት ከሞግሒላ ሻል ባለ መልክ የሚያብራራ የመሠረተ ሃይማኖት ትምህርት ያዘጋጀ በ1669 ዓ·ም የኢየሩሳሌም ፓትርያርክ አቡነ ዶሲቴዎስ ነበር ። እሱም የሉካሪስን መጽሐፍ ይዘት በመቃወም የግሪክ ኦርቶዶክስን እምነት በዝርዝርና በግልጽ የሚያብራራ መሠረተ ሃይማኖት በማዘጋጀት አሳትሞ ለካህናትና ለምእመናን የሃይማኖት መመሪያና ማጽኛ እንዲሆን አበረከተ ። በዚህም መጽሐፉ ውስጥ የካልቪንን የኑፋቄ ትምህርት የሚያንጸባርቀውን የሉካሪስን ጽሑፍ በመቃወም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት መሠረትና መገኛ መጽሐፍ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፉአቸው መጻሕፍት መሆናቸውን ፡ ማዕርገ ክህነት ከጌታና ከሐዋርያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መሆኑን ፡ ካህኑ በሚጸልይበት ወቅት ኅብስቱና ወይኑ ወደ ጌታ ሥጋና ደም እንደሚለወጥ ፡ መላእክት ፡ ጻድቃንና ሰማዕታት የሚያማልዱ ስለመሆናቸው ፡ ለጌታ ፡ ለእመቤታችን ፡ ለጻድቃንና ለሰማዕታት ሥዕሎች የአምልኮ ሳይሆን የክብር ስግደት ማድረግ ስለመገባቱ ወዘተ· በማብራራት ጽፏል። በዚህ አኳኋን እውነተኞች የኦርቶዶክስ ቤተ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ልጆችና መሪዎች የኦርቶዶክስን እምነት የሚያብራሩ የመሠረተ ሃይማኖት መጻሕፍት አዘጋጅተው ለካህናትና ለምእመናን የሃይማኖት መመሪያና ማጽኛ እንዲሆኑ ስላበረከቱ ውለታቸው በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ለዘለዓለም ሲታወስ ይኖራል ። እንዲሁም በታላቁ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ገዳም በአግዮን ኦሮስ (ማውንት አቶስ) ውስጥ በብሕትውና ይኖር የነበረው ቅዱስ ኒቆዲሞስ (1748–1809) ከቆሮንቶስ ሊቀጳጳስ ከአቡነ መቃርዮስ ጋር በመተባበር ጸሎት ነክና የመሳሰሉ መንፈሳዊ ትምህርቶችን የያዘ ከጥንታውያን የግሪክ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ጽሑፍ (ሥራ) በማውጣጣት ፊሎካልያ በሚል ርእስ ለካህናትና ለባሕታውያን መንፈሳዊ ተግባር መመሪያ የሚሆን ጠቃሚ መጽሐፍ አዘጋጅቶ በ1782 ዓ·ም ቬኒስ ውስጥ አሳትሞ አወጣ ። ከመጽሐፉ ጠቃሚነት የተነሣ ወዲያው በእስላቮኒክ ፡ በራሽያ ፡ በሩማንያና በሌሎችም ቋንቋዎች ተተርጕሞ ተሰራጨ ። ይህና ሌሎቹም የኒቆዲሞስ ጽሑፎች ለኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት መንፈሳዊ ተግባር መቃናትና ተሐድሶ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኒቆዲሞስ በብሕትውና ያሳለፋቸውን የቅድስና ኑሮ ፡ ለቤተክርስቲያን ያበረከታቸውን አገልግሎቶች ወዘተ· በመመልከት በ1954 ዓ·ም የቅዱስነት ማዕርግ ሰጥታዋለች ።

በ19ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ የግሪክና የምሥራቅ አውሮጳ ሀገሮች በቅኝ ገዥያቸው በቱርክ መንግሥት ላይ አምጸው ባካሄዱት ጦርነት ነጻነታቸውን ከተቀዳጁበት ጊዜ ጀምሮ በየሀገሮቻቸው መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችን በመክፈትና ካህናትን በማሠልጠን በቱርክ መንግሥት ተጽእኖ ተዳክማ የነበረችዌቱ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንድትጠናከር አድርገዋል ።

እንዲሁም ከካቶሊክና ከፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ጋር የነበራቸውን የከረረ ቅራኔ አለዝበው በእኩልነትና በፍቅር ላይ በተመሠረተ መንፈስ ተቀራርበው መሥራት ጀምረዋል ። ይኸውም ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና ከአንዳንድ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በስተቀር የግሪክ ኦርቶዶክስን ፡ የኦርየንታልንና የፕሮቴስታንትን አብያተ ክርስቲያናት ላቀፈው ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ንቅናቄ (ማኅበር፡ ድርጅት) አባላት በመሆን ይሠራሉ ። ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ጋር በመሪዎቻቸው አማካይነት አልፎ አልፎ ግንኙነት በማድረግ



www.ethiopianorthodox.org

ይወያያሉ። ለምሳሌ እላይ እንደተመለከትነው ለብዙ ዘመናት ተወጋግዘው የኖሩት የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የሮሙ ፖፕ ጳውሎስ 6ኛና የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ አቴናጎራስ በ1964 ዓ.ም. በልደት ሰሞን ኢየሩሳሌም ውስጥ ተገናኝተው ፍቅርን በተሞላ የወንድማማችነት መንፈስ በመነጋገር (በመወያየት) በመካከላቸው ስላሉት ልዩነቶች መወገድ የሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት ካህናት ለወደፊት እንዲወስኑት በማለት ተስማምተዋል ።

ጸረ ሃይማኖት የሆነው የኮሚንስት ሥርዓት ከቅርብ ጊዜ በፊት በመንኮታኮቱ በሩሲያና በምሥራቅ አውሮጳ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያ ናት ሁሉ የእምነት ነጻነታቸውን ተጐናጽፈዋል ።

በእምነት አንድ ስለሆኑት ፣ የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ ክብርና የበላይነት ስለሚቀበሉት ፣ በአስተዳደር ግን ራሳቸውን ችለው የኦርቶዶክስን እምነት በየሀገሮቻቸው በማጠናከርና ምእመናንን በመንከባከብ ላይ ስለሚገኙት የግሪክና የእስላቮኒክ ቋንቋ ተናጋሪ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ከዚህ በታች አጠር አጠር አድርገን እንመለከታለን።

## ምዕራፍ ፩

### የቍስጥንጥንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

በዘመነ ሐዋርያት ሐዋርያው እንድርያስ ቍስጥንጥንያ (ቢዛንታይን) ውስጥ ወንጌልን ማስተማሩ ይተረካል ። ቈስጠንጢኖስ ቤተ መንግሥቱን ከሮም ወደ ቍስጥንጥንያ ካዛወረ በኋላ በሁለተኛው የቍስጥንጥንያና በአራተኛው የኬልቄዶን ጉባኤዎች ላይ የተሰበሰቡት ጳጳሳት የቍስጥንጥንያ ፓትርያርክና የሮም ፖፕ በማዕርግ (በሥልጣን) እኩል ሆነው፣ በሽምግልናና በአክብሮት የሮሙ አንደኛ የቍስጥንጥን ያው ሁለተኛ እንዲሆኑ ወሰኑ ። ይሁን እንጂ ይህንን የእኩልነት ውሳኔ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ወዲየውኑ ብትቃወመውም ቅሉ ፣ የቍስጥንጥ ንያና የመላ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት እስከ ዛሬ ድረስ እኩል ናቸው በሚለው ውሳኔ እንደጸኑ ናቸው ።

በ1922 ዓ.ም. በግሪክና በቱርክ መንግሥታት መካከል በተደረገው ጦርነት ምክንያት የኦርቶዶክስን እምነት የሚከተሉ ብዙ ግሪኮች ቍስጥንጥንያን ለቀው ስለተሰደዱ በቱርክ ግዛት የኦርቶዶክስ እምነት



www.ethiopianorthodox.org

ተከታዮች ቍጥር እየቀነሰ ሄደ ። ይህንኑ በመመልከት የግሪክ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ከቱርክ አገዛዝ ነጻ ወጥተው በግሪክ መንግሥት ግዛት ሥር በሆኑት እንደ ቀርጤስ ፣ ፍጥሞ ወዘተ· በመሳሰሉ ደሴቶች የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በመንፈሳዊው ተግባር እንደቀድሞው በቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ሥር እንዲተዳደሩ አድርገዋል ። እላይ ከተጠቀሱት በስተቀር በመንፈሳዊው ተግባር በቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ሥር የሚተዳደሩ በምዕራብ አውሮጳ ፣ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ ፣ በኒውዚላንድ ፣ በፊንላንድ ወዘተ· የሚገኙ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አሉ ።

መላ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች (ፓትርያርኮች ፣ ሊቃነ ጳጳሳት ፣ ጳጳሳት) የቍስጥንጥንያውን የዓለም ፓትርያርክ በመንፈሳዊ ተግባር የበላይነት ስለሚቀበሉ አንዳንድ ውሳኔዎችን ሲያደርጉና ችግሮችም ሲያጋጥሟቸው ለቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ያስታውቃሉ (ያመለክታሉ) ። በሌላው ወገን ደግሞ የማይሆን መስሎ ከታያቸው የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ ውሳኔ አይቀበሉም ። ለምሳሌ በ1922 ዓ·ም ሚሌቲዮስ አራተኛ የተባለው የቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን ማዕርገ ክህነት ሕጋዊነት ሲቀበል ፣ የሩሲያ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎችም በመቃወም አልተቀበሉም ።

በዓለም ዝነኛ የሆነው በግሪክ ግዛት ውስጥ የሚገኘው በአሁኑ ጊዜ የግሪክ ፣ የሩሲያ ፣ የሰርቢያ ፣ የቡልጋርያ ወዘተ· ገዳማት ያሉበት የአቶስ ተራራ (አግዮን ኦሮስ ፣ ቅዱስ ተራራ) የተባለው የወንድ ገዳም የሚተዳደረው በቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሥር ነው ። እገዳሙ ውስጥም ለመነኰሳት ማሠልጠኛ የሚሆን መንፈሳዊ ትምህርት ቤትም በ1749 ዓ·ም ተከፍቷል።

የቍስጥንጥንያ መንበረ ፓትርያርክ ከግሪክ ኦርቶዶክስና ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የሚላኩ ደቀ መዛሙርትን እየተቀበለ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰጥበት በ1844 ዓ·ም የተመሠረተ ሐልኪ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የተባለ አለው ።

ለወደፊት እንደምንመለከተው በተለያዩ ሀገሮች ከሚገኙት የግሪክ ኦርቶዶክስን እምነት ከሚከተሉት አብያተ ክርስቲያናት አብዛኞቹ ለብዙ ዘመናት በቍስጥንጥንያው መንበረ ፓትርያርክ ሥር ሲተዳደሩ ከቆዩ



www.ethiopianorthodox.org

በኋላ በየጊዜው የየራሳቸውን ፓትርያርክ በመሰየም እራሳቸውን በራሳ ቸው በማስተዳደር ላይ ይገኛሉ ።

በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚፈጸመውም አገልግሎት ምእመናን በሚረዱአቸው በየሀገሮቻቸው ቋንቋ ነው ። ካህናትንም የሚያሠለጥኑባቸው በየሀገሮቻቸው መንፈሳዊ ሴሚናሪዎችና (ኮሌጆችና) ፋካልቲዎች አሏቸው ።

ራሳቸውን ችለው የሚተዳደሩት የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ከእርስ በእርሳቸው ራሳቸውን አግልለው በመኖር ፈንታ ተቀራርበው በኅብረት ሊሠሩ በሚችሉባቸው መንገዶች ላይ ለመወያየት በቊስጥንጥንያው ፓትርያርክ አሳሳቢነት ሮድስ ደሴት በ1961 ፣ በ1963 ፣ በ1964 ዓ.ም፤ ቤልግሬድ በ1966 ዓ.ም ፣ ጄኔቫ በ1968 ዓ.ም በተደረጉት "የመላ ኦርቶዶክስ ኮንፈራንሶች" ላይ ተገኝተው በሰፊው ተወያይተዋል ።

## ምዕራፍ ፪

### የእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ወንጌላዊው ማርቆስ ከሮም ቀጥሎ ሁለተኛ ከተማ በነበረችው እስክንድርያ ውስጥ ክርስትናን አስተምሮ እዚያው በሰማዕትነት ከዐረፈበት ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው በተነሡት እንደነ ቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ፣ አትናቴዎስ፣ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ወዘተ. በመሳሰሉት አባቶች ትጋት የክርስትና እምነት በግብጽና በአካባቢ ሀገሮች ተስፋፋች።

በአራተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ ላይ የተካፈሉት ጳጳሳት "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት" ብለው በመወሰናቸው የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ይህ ዓይነቱ እምነት ስሕተት መሆኑን ገልጾ አወገዛቸው። እስከዚያ ጊዜ ድረስ በእምነትና በአስተዳደር አንድ የነበረችይቱ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ከዚያን ወቅት ጀምሮ በእምነት ሁለት ላይ ተከፈለች። ይኸውም ቀደም ሲል በክፍል ሁለት እንደተመለከትነው በግብጽ ከነበሩት ክርስቲያኖች አብዛኞቹ የሀገሪቱ ተወላጆች የነበሩት ኮፕቶች ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ያስተማረውን ቀጥተኛ የተዋሕዶ (የአንድ ባሕርይ) እምነት በመከተል በኮፕቱ የእስክንድርያ ፓትርያርክ አመራር ሥር ቀጥተኛ እምነታቸውን በመፈጸምና በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ



www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያንም የምትከተለው የቅዱስ ዲዮስቆሮስን ትምህርት ነው። በተቃራኒው ደግሞ ያን ጊዜ ግብጽን ጭምር ይገዛ በነበረው በቍስጥንጥንያው ንጉሥ እየተረዱ የኬልቄዶንን ውሳኔ የተቀበሉ የግሪክ ተወላጅ የነበሩ መለካውያን (የንጉሥ ወገኖች) የተባሉት እስክንድርያ ቅዱስ ሳባ ገዳም ውስጥ የራሳቸውን መንበረ ፓትርያርክ መሥርተው የሁለት ባሕርይ እምነትን በመከተል ላይ ናቸው። ከግብጽ ውጭ በዚሁ መንበረ ፓትርያርክ ሥር የሚተዳደሩ ትሪፖሊ ፣ አዲስ አበባ፣ ጆሐንስ በርግ፣ ካርቱም፣ ቱኒዝ፣ አክራ፣ ማዕከላዊ አፍሪካ፣ ኡጋንዳ፣ኬንያ ወዘተ. ውስጥ አብያተ ክርስቲያናት አሉ።

# ምዕራፍ ፫

## የአንጾኪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

በሮማ መንግሥት ግዛት ውስጥ አንጾኪያ ከሮምና ከእስክንድርያ ቀጥላ ሦስተኛዋ ታላቅ ከተማ ነበረች። አሁን ግን አንጾኪያ ቱርክ ግዛት ውስጥ የምትገኝ ትንሽ መንደር ናት።

በሐዋርያት ሥራ 11፡26 እንደምንመለከተው የክርስቶስ ተከታዮች ለመጀመሪያ ጊዜ በአሕዛብ "ክርስቲያን" የሚል ስም የወጣላቸው በዚችው ከተማ ውስጥ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ጴጥሮስ በአንጾኪያና በአካባቢዋ በሚገኙ ሀገሮች ወንጌልን አስተምረዋል። የአንጾኪያ የመጀመሪያው ጳጳስ ቅዱስ ጴጥሮስ ነበር። ቅዱስ አግናጥዮስም የዚችው ከተማ ጳጳስ በመሆን ክርስትናን አስተምሯል።

በ4ኛው መቶ ዘመን የአንጾኪያ ፓትርያርክ ከእስክንድርያው ፓትርያርክ ቀጥሎ የሦስተኛነት ማዕርግ ተሰጥቶት ነበር። ዓረቦች ሶርያን በ636 ዓ.ም. በጦር ኃይል ከያዙ ጀምሮ የኦርቶዶክስ ምእመናን ቍጥር እየመነመነ ሄደ። አሁን መንበረ ፓትርያርኩ የሚገኘው በሶርያ ዋና ከተማ ደማስቆ ውስጥ ነው። በሥሩም ሶርያና ሊባኖስ የሚኖሩ ዓረብኛ ተናጋሪ የሆኑ ምእመናን አሉ። ኢራቅና አሜሪካም ውስጥ በአንጾኪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥር የሚተዳደሩ አብያተ ክርስቲያናት አሉ።

ለብዙ ጊዜ (1724–1898) የግሪክ ተወላጅ የሆኑ ጳጳሳት በተከታታይ የፓትርያርክነቱን ማዕርግ ይዘው ከኖሩ በኋላ ከ1898 ዓ.ም. ወዲህ የፓትርያርክነቱን ማዕርግ የዓረብ ተወላጅ የሆኑ ኦርቶዶክሶች ተረክበው



www.ethiopianorthodox.org

ታል። በ1898 ዓ.ም. የተሾመው መጀመሪያው የሶርያ ተወላጅ ፓትርያርክ አቡነ ሚሌትዮስ ዱማኒ ነው።

ከ1941 ዓ.ም. ጀምሮ በመንበረ ፓትርያርኩ ሥር ተግባሩን የሚያከናውነው " የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር " ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ነው። የዚህም ማኅበር አባላት በሰንበት ትምህርት ቤቶች በማስተማር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በማከሄድ ፣ መንፈሳዊ ነክ የሆኑ መጽሔቶችን በዓረብኛ ቋንቋ በማዘጋጀት፣ ድኾችን በመርዳት ወዘተ. ለቤተ ክርስቲያናቸው ከፍ ያለ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ናቸው።

ቀደም ሲል በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደተመለከት ነው ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ ይህች ቤተ ክርስቲያንም በመለካውያንና በተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ለሁለት ስለተከፈለች ከግሪክ ኦርቶዶክስ (ከመለካውያን) መንበረ ፓትርያርክ በተጨማሪ የተዋሕዶን እምነት የሚከተሉት የሶርያ ኦርቶዶክስ (ያዕቆባዊት) ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክም የሚገኘው ሶርያ ደማስቆ ውስጥ ነው።

## ምዕራፍ ፬

## የኢየሩሳሌም ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

የሮማ መንግሥት ዓለምን ይገዛ በነበረበት ወቅት ኢየሩሳሌም (ፓሌስታይን፣ ቅድስት ሀገር) በሥሩ ትተዳደር ነበር። በዚያን ጊዜ የክርስትና እምነት መሥራች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ልሔም ተወለደ። ሐዋርያትንና ሰባ ሁለቱን አርድእት መርጦ በማስከተል በኢየሩሳሌምና ዐውራያዋ(በይሁዳ፣ በናዝሬት፣ በሰማርያ) ወንጌልን ካስተማረ በኋላ የሰው ልጆችን ከወደቅንበት ኃጢአት ለማዳን መከራ ተቀበለ፣ ተሰቀለ፣ ሞተ፣ በሦስተኛውም ቀን ተነሣ፣ ከአርባ ቀን በኋላ ሲያርግ ደቀ መዛሙርቱ በዓለም እየዞሩ እንዲያስተምሩ አዘዛቸው። ከሙታን በተነሣ በአምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ከላከላቸው በኋላ በዓለም ተሰማርተው በማስተማር ላይ ሳሉ አብዛኞቹ በሰማዕትነት ዐረፉ።

ሐዋርያት ወንጌልን ለማስተማር ሲሰማሩ ሐዋርያው ያዕቆብ ኢየሩሳሌም ውስጥ ለተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ሆኖ ወንጌልን በትጋት ማስተማሩ በአይሁድ ዘንድ እንደወንጀል ስለተቈጠረበት፣



www.ethiopianorthodox.org

በሄሮድስ አግሪጳ ትእዛዝ አንገቱን በሰይፍ ተቈርጦ በሰማዕትነት ዐረፈ።

በ4ኛው መቶ ዘመን የቈስጠንጢኖስ እናት ንግሥት እሌኒ ኢየሩሳሌም ውስጥ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሠራች(አሳነፀች)።

የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን እስከ 5ኛው መቶ ዘመን ድረስ በቂሣርያ መንበረ ጵጵስና ሥር ትተዳደር ነበር። ነገር ግን በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን ጉባኤ የተሰበሰቡት ጳጳሳት ለኢየሩሳሌሙ ጳጳስ የፓትርያርክነት ማዕርግ ሰጡ። በ1672 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም ውስጥ ሲኖዶስ ጠርቶ የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ የቄርሎስ ሉካሪስን የፕሮቴስታንት እምነት የሚያንጸባርቅ ጽሑፍ ያወገዘና የግሪክ ኦርቶዶክስን እምነት የሚያብራራ መሠረተ ሃይማኖት የጻፈ የኢየሩሳሌም ፓትርያርክ ዶሲቴዎስ ነው።

የግሪክ ኦርቶዶክስን እምነት ከሚከተሉት ክርስቲያኖች በስተቀር በዓለም ያሉ በእምነት የተለያዩ ክርስቲያኖችም በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ በሚገኙ ቅዱሳት መካናት የየራሳቸውን ገዳማት መሥርተውና አብያተ ክርስቲያናት ሠርተው አምላካችንን በማገልገልና በማመስገን ላይ ይገኛሉ። ቀደም ሲል ወደ ኢየሩሳሌም ካህናት ልከው ገዳማትን ከመሠረቱት ክርስቲያኖች መካከል አንዷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት።

# ምዕራፍ ፳

## የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

እስላቮች ክርስትናን በተቀበሉበት ዘመን እነቅዱስ ቄርሎስ(ቈስጠንጢኖስ)፣ ሜቶዲዮስና ረዳቶቻቸው የቢዛንታይን የወንጌል መልእክተኞች በ864 ዓ.ም. በቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ በፎቲዮስ ወደ ሩሲያ ተልከው ለሕዝቡ ወንጌልን በትጋት አስተምረው በ955 ዓ.ም. ልዕልት ኦልጋን ፣ በ988 ዓ.ም የልዕልት ኦልጋን የልጅ ልጅ ንጉሥ ቭላድሚርን እዋና ከተማይቱ ኪኤቭ ውስጥ ከብዙ ሕዝብ ጋር ወደ ክርስትና መልሰው ሊያጠምቁ ቻሉ። እንዲሁም ንጉሥ ቭላድሚር ከመጠመቁ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ በ987 ዓ.ም. የቢዛንታይንን ንጉሥ እኅት ልዕልት አንን በማግባቱ የሁለቱ መንግሥታት ግንኙነት እየጠበቀ ሄደ። የግሪክ ጳጳሳትና ካህናት በብዛት ወደ ሩሲያ ተልከው ክርስትናን አስተማሩ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን እስከ 1589 ዓ.ም. ድረስ



www.ethiopianorthodox.org

በቍስጥንጥንያ መንበረ ፓትርያርክ ሥር ስትተዳደር ቈየች። ሕዝቡ ያመልካቸው የነበሩ ፔሩን የተባለውና ሌሎችም ጣዖታት ተንኮታኩተው እንዲወድቁ ተደረጉ። በቦታቸውም ላይ አብያተ ክርስቲያናት ታነጹ። የሩሲያ ዋና ከተማ በነበረችው በኪየቭ አካባቢ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክርስትና የመንግሥቱ ሃይማኖት ሆነች።

የንጉሥ ቭላድሚር ልጅ ያሮስላቭ(1036–1054) ቍስጥንጥንያ ባለው በቅድስት ሶፊያ ቤተ ክርስቲያን ዓይነት ቅድስት ሶፊያ ተብሎ የሚጠራ ትልቅ ካቴድራል አሳንጾ ውስጡን ከቍስጥንጥንያ በሄዱ ዝነኛ አርቲስቶች አሣለው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተሠሩ። ትንሽ ቀደም ሲል ለቡልጋርያና ለሞራቪያ(ለቸኮዝሎቫኪያ) እስላቮች መገልገያ እንዲሆን ታስቦ በቅዱስ ቄርሎስና በቅዱስ ሜቶዲዮስ ከጽርዕ ወደ ጥንታዊው የእስላቭ ቋንቋ የተተረጐሙት መጽሐፍ ቅዱስና የቅዳሴ መጻሕፍት ለሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል።

በ1051 ዓ·ም· ከአቶስ ገዳም በሄደው እንጦንስ በተባለው ሩሲያዊ መነኵሴ ኪየቭ አጠገብ የተመሠረተው የብሕትውና ኑሮ በደቀ መዝሙሩ በቅዱስ ቴዎዶስዮስ፡ ቈየት ብሎም በ14ኛው መቶ ዘመን በተነሣው በሩሲያዊው በቅዱስ ሰርጊዮስ ትጋት በሀገሪቱ ውስጥ በብዛት እየተስፋፋ ሄደ ። ገዳማቱም የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት ስጦታና ችሎታ የነበራቸው ጳጳሳትንና ካህናትን አፍርተዋል።

ሞንጎሎች (ታርታሮች) መጀመሪያ ኪኤቭን ፡ ቀጥሎ መላ ሩሲያን ወረው ከ1237 1480 ዓ·ም በገዙበት ዘመን ቤተ ክርስቲያኒቱ ሕዝቡ አንድነቱን አጠናክሮና ሞራሉን ከፍ አድርጎ ጠላቶቹን እንዲደመስስ በማበረታታት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጋለች ። ጥንታዊቷ የሩሲያ ከተማ ኪኤቭ በሞንጎሎች በተደጋጋሚ በመወረሯ ከፍ ያለ ጥፋት ስለደረሰባት በ14ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ጵጵስና በአቡነ ጴጥሮስ (1308–1326) ዘመን ከኪኤቭ ወደ ሞስኮ ተዛወረ ።

የዓለምን አብያተ ክርስቲያናት እንደገና አንድ ለማድረግ ታስቦ ፍሎሬንስ ውስጥ ከ1439 1440 በተደረገው ጉባኤ ላይ ከተካፈሉት የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞች እንደ ኤፌሶኑ ጳጳስ



www.ethiopianorthodox.org

እንደ አሁን ማርቆስ የመሳሰሉት ጥቂት ጳጳሳት የጉባኤው ውሳኔ የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ዓላማ የሚያንጸባርቅ ነው በማለት ወዲያው ሲቃወሙት ፣ የግሪክ ተወላጅ የነበረው የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ኢሲዶር ውሳኔውን በመቀበሉና ወደ ሩሲያም ተመልሶ በይፋ ማስተጋባት ስለጀመረ ፣ የሩሲያ ካህናትና ታላቁ ዱክ ባስልዮስ የተባለው የሀገሪቱ ገዥ ውሳኔውን ውድቅ በማድረግ አቡነ ኢሲዶርን ከመንበረ ጵጵስናው አውርደው በ1448 ዓ.ም ዮናስን የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ አድርገው ሾሙ ።

የኪኤቭ መንበረ ጵጵስና እስከ 15ኛው መቶ ዘመን ድረስ በቍስጥንጥንያ መንበረ ፓትርያርክ ሥር ሆኖ ከቈየ በኋላ በ16ኛው መቶ ዘመን የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ከቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ጋር በመስማማት ራሷን ችላ ሞስኮ ውስጥ መንበረ ፓትርያርኳን መሠረተች ። ይኸውም የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ዳግማዊ ኤርምያስ በ1589 ዓ.ም የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ለመጐብኘት ሄዶ ሳለ ኢዮብ የተባለውን ካህን የመጀመሪያው የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አድርጎ ሾመው።

የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ከሀገሯ ውጭ ቻይና ፣ ጃፓንና ኮርያ ውስጥ ክርስትናን አስተምራለች ። ምንም እንኳ የምእመናኖቻቸው ቍጥር ጥቂት ቢሆንም ፣ የቻይናና የጃፓን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ (አውቶኖሞስ ናቸው) ። የኮርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ግን የምትተዳደረው ሰሜን አሜሪካ ባለችው የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥር ነው ።

የቍስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን የቢዛንታይን መንግሥት በቱርክ እጅ ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ ሚስዮናውያንን ወደ ውጭ ሀገር በመላክ ወንጌልን ማስተማር ስታቋርጥ ፣ የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ከሀገሯ ውጭ ስታስተምር ቈይታ ከቦልሼቢኩ ሪቮሉሽን በኋላ አቋረጠች ። በዚህ አኳኋን የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከሀገራቸው ውጭ የወንጌል መልእክተኞች በመላክ የማስተማሩን ተግባር አቁመዋል ።

መጀመሪያዋ ሮም በአሕዛብ እጅ በመውደቋ ቍስጥንጥንያ ሁለተኛዋ ሮም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መዲና ሆነች ። በ15ኛው መቶ ዘመን ቍስጥንጥንያና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የነበሩ የምሥራቅ አውሮጳ መንግሥታት ሁሉ በየተራ በቱርክ እጅ ሲወድቁ የቱርክን


www.ethiopianorthodox.org

ሠራዊት በጀግንነት ተዋግቶ ያባረረና ነጻነቱን ጠብቆ የኖረ የሩሲያ መንግሥት ብቻ ነው ።

ከጥንት ሮማውያን ነገሥታት የነበራቸውን የዘር ሐረግ ቈጥረው የሩሲያ ነገሥታት ዛር (ቄሣር) በሚለው ማዕርግ እንዲጠሩ ወስነው የቢዛንታይን ነገሥታት ምትኮች መሆናቸውን ገለጹ ። ስለዚህ በቢዛንታይን ንጉሥ ፈንታ የሩሲያ ዛር የኦርቶዶክስ እምነት ጠባቂ ነው በማለት ሩሲያ ሦስተኛዋ ሮም እንድትባል የሚል ሐሳብ ፊሎቴዎስ በተባለ መነኵሴና በሌሎችም ሊቃውንት ቀርቦ ተወስኖ ነበር ። እንዲሁም የሩሲያና የቊስጥንጥንያ መንግሥታት በሩሲያው ንጉሥ በኢቫን ሦስተኛና በፓሌዎሎጎስ ልጅ በልዕልት ሶፊያ ጋብቻ ተሳስረው ስለነበር ሩሲያ የቊስጥንጥንያ ወራሽ "ሦስተኛዋ ሮም ናት" ለሚለው አስተሳሰብ ድጋፍ ሰጥቷል ። ቤተ ክርስቲያኒቱ ግን በይፋ የቊስጥንጥንያው መንበረ ፓትርያርክ ማዕርግ ይገባኛል አላለችም ። ይህን ዓይነቱን አዲስ አስተሳሰብ የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ወዲያው ተቃውመውታል ። የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ማዕርግ ሁልጊዜም ከኢየሩሳሌም ፓትርያርክ ቀጥሎ አምስተኛ ነው ።

በ፲፮ኛው መቶ ዘመን የሩሲያ ኦርቶዶክስ ካህናት ቤተ ክርስቲያን ለኅብረተሰቡ ማበርከት በሚገባት ተግባሮች ላይ በሁለት ተቃራኒ ሐሳቦች ተከፍለው የተለያየ አቋም በመያዝ ይፋጁ ነበር ። ይኸውም በቮሎትስኪው በአባ ዮሴፍ የሚመራው ቤተ ክርስቲያን ሀብት እንዲኖራት ደጋፊው ክፍል የሩሲያ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በጥብቅ ተባብረው በመደጋገፍ እንዲሠሩ ያሻል ። አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማትም ባላቸው ከፍተኛ ሀብት በመንግሥት እየተረዱ የበጎ አድራጎትን ፡ የትምህርትንና የማኅበራዊ ኑሮ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ሲል ፤ በአባ ኒል ሶርስኪጂ የተመራው ቤተ ክርስቲያን ሀብት አልባ ትሁን ባዩ ክፍል ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ተጽእኖ ነጻ ሁና የመጸለይ ፣ የማስተማር ወዘተ መንፈሳዊ ተግባሯን ብቻ ማከናወን ይገባታል ። የበጎ አድራጎት (የመመጽወት) ፡ የማኅበራዊ ኑሮ እንቅስቃሴዎችን የማስፋፋት ወዘተ ተግባር ግን በምእመናን መከናወን አለበት የሚል ነበር ። ምንም እንኳ በሁለቱም ክፍሎች አስተሳሰብ ውስጥ መጠነኛ እውነት ቢኖርም በዚያን ወቅት የመጀመሪያው ክፍል የመንግሥትን ፡ የብዙ ካህናትንና ምእመናንን ድጋፍ ስላገኘ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር


www.ethiopianorthodox.org

ተባብራ ሠርታለች ። በኒልና በተከታዮቹ ላይም ከመንግሥት ከፍ ያለ ሥቃይ ተሰንዝሮባቸዋል ። ሆኖም የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ለሁለቱም የቅዱስነት ማዕርግ ሰጥታቸዋለች ።

በብሕትውና ተግባሩ ዝነኛ የነበረው ቅዱስ ሰራፊም (1759–1833) በ19 ዓመቱ ሳሮቭ ከተባለው ገዳም ገብቶ ለብዙ ዓመታት በጾምና በጸሎት ተወስኖ ከቈየ በኋላ ከሕማማቸው ለመፈወስ ፣ ምክር ለመቀበል ወዘተ· ወደነበረበት ገዳም የሚሄዱትን ቊጥራቸው የበዛ ምእመናን እየተቀበለ መንፈሳዊ አገልግሎትን ይለግሳቸው ነበር ።

በ17ኛው መቶ ዘመን የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አቡነ ኒኮን (1605–1681) ሥልጣኑን ለማጠናከር በመሻት ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓተ ቅዳሴ አንዳንዶቹን ክፍሎች ለማሻሻል (ለመለወጥ) ሲሞክር ፣ አቫኩም በተባለው ካህን የተመሩት አሮጌ አማኞች የተባሉት ለውጡን በመቃወማቸው ምክንያት በመወገዛቸው በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ መለያየት ተፈጥሮ ነበር ። መሪያቸው አቫኩምና ጥቂት ጓደኞቹ በዛሩ ትእዛዝ በእሳት ተቃጥለው ሲሞቱ ፣ በብዙዎቹ ላይ የተለያዩ ሥቃዮች ደርሰውባቸዋል ።

እንዲሁም አቡነ ኒኮን የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት መሪዎች እንደ ቢዛንታይን መንግሥትና የቊስጥንጥንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ተደጋግፈው በኩልነት ሲሠሩ የቈዩበትን ባህል ውድቅ አድርጎ ፣ የቤተ ክህነት ሥልጣን ከቤተ መንግሥት ሥልጣን ይበልጣል ብሎ በመነሣት በሲቪል አስተዳደር ጣልቃ ለመግባት ሞከረ ። ይኸው የፓትርያርኩ የኒኮን ዓላማ በዛር አሌክሲ ተቀባይነትን አግኝቶ ለጥቂት ጊዜ ሲሠራበት ከቈየ በኋላ ፣ ይህንኑና የመሳሰሉትን ተግባሮች በመቃወም የሩሲያ ንጉሥ ትልቁ ጴጥሮስ (1676–1725) ቤተ ክርስቲያኒቱን ከሥልጣኑ ሥር ለማድረግ በመሻት አድርያን የተባለው ፓትርያርክ ከዐረፈ በኋላ ሌላ ፓትርያርክ እንዳይመረጥ አገደ ። እገዳውም ሃያ አንድ ዓመት ከቈየ በኋላ በ1721 ዓ·ም ራሱ በፈለገው ጊዜ ሊሽራቸው የሚችላቸው ዐሥራ ሁለት አባላት ባሉት በቅዱስ ሲኖዶስ እንድትመራ አደረገ ። በዚህም ሁኔታ ቤተ ክርስቲያኒቱ እስከ 1917 ዓ·ም ድረስ በሲኖዶስ ስትመራ ኖረች (1721–1917) ። ከአባላቱም ሦስቱ ጳጳሳት ሲሆኑ የቀሩት ከገዳማትና ከአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የተመረጡ



www.ethiopianorthodox.org

ነበሩ ። ሆኖም መብቷ ተቀንሶ በነበረበት ዘመን ቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ ተግባሯን ከማከናወን ቸል አላለችም ።

በተለይም በቆሞስ መቃርዮስ (1792–1847) ፣ በአቡነ ኢኖሴንት (1797–1879) ወዘተ. ትጋት በሩሲያ ውስጥ በተለያዩ ክፍላተ ሀገርና ጥንት የሩሲያ ግዛት እስከነበረችው እስከ አላስካ ድረስ ወንጌልን በሰፊው በማስተማር ብዙዎችን ወደ ክርስትና እምነት መልሳለች ። በ1868 ዓ.ም በሩሲያ መንግሥት ለአሜሪካ በመሸጥ የአሜሪካ ክፍለ ሀገር በሆነችው በአላስካ የሚኖሩ ኤስኪሞዎች ፣ ቀይ ሕንዳውያንና በመላ አሜሪካ የሚኖሩ ሩሳውያን ኦርቶዶክሶች አቡነ ኢኖሴንትን (ጆን ቬኒአሚኖቭን) እንደ ሐዋርያ አድርገው ይቈጥሩታል ። ቆሞስ መቃርዮስ ከስብከተ ወንጌል ተግባሩ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ራሻኛ ተርጕሟል ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የኪኤቭ ሊቀ ጳጳስ ጴጥሮስ ሞግሒላ በ1640 ዓ.ም የፕሮቴስታንትን እምነት የሚያንጸባርቀውን የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ የቄርሎስ ሉካሪስን ጽሑፍ የሚቃወምና ቀጥተኛውን የኦርቶዶክስ እምነት የሚያብራራ መሠረተ ሃይማኖት ጽፏል ።

በ15ኛውና በ16ኛው መቶ ዘመን የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስን ተረጐሙ ። እንዲሁም ብዙ ሃይማኖት ነክ የሆኑ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚጠቅሙ የትዳሴና የመሳሰሉ መጻሕፍትን በራሻ ቋንቋ ተርጕመው አዘጋጁ ። ፔሲይ ቬሊችኮቭስኪ (1722–1794) የተባለው ሩሲያዊ የአቶስ ገዳም መነኵሴ ከጓደኞቹ ጋር በመረዳዳት የግሪክ ቤተ ክርስቲያን አባቶች የደረሱአቸውን መጻሕፍት ከግሪክኛ ወደ እስላቮኒክ ቋንቋ ተረጐመ ።

ፊሎካሊያ (ከቤተ ክርስቲያን አባቶች ጽሑፍ የተውጣጣ ትንብር) የተባለውን መጽሐፍም አቡነ ቴዎፋን (1815–1894) ከጽርዕ ወደ ራሻ ቋንቋ ተረጐመ ።

ከጊዜ በኋላ ሩሲያ ውስጥ በተቀጣጠለው አብዮት ምክንያት ዳግማዊ ኒኮላ ከዙፋኑ ወርዶ ሀገሪቱ በጊዜአዊ መንግሥት ትመራ በነበረበት ወቅት ፣ በጊዜአዊው መንግሥት መሪ በኬሬንስኪ ፈቃድ በ1917–1918 ዓ.ም ጳጳሳት ፣ ካህናትና ምእመናን ሞስኮ ውስጥ ጉባኤ አድርገው በትልቁ ጴጥሮስና ከሱ ቀጥለው በተነሡ ነገሥታት የተሜነባቱን የተዛባ ሕገ ወጥ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር አሻሽለው ጊዜአዊው


www.ethiopianorthodox.org

መንግሥት በቦልሸቪኮች ከተወገደ ከጥቂት ቀናት በኋላ ጥቅምት 13 ቀን 1917 ዓ.ም የሞስኮ ሊቀጳጳስ የነበሩትን አቡነ ቲኮንን ፓትርያርክ አድርገው ሾሙ ።

በ1917 ዓ.ም በሩሲያ የፈነዳው የሶሻሊስት አብዮት አቴይስት መሪዎች(የእግዚአብሔርን ህልውና ክሐዲዎች) ጥር 20 ቀን 1918 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያኒቱ ከመንግሥት ጋር የነበራትን የጠበቀ ግንኙነት ሰርዘው ከካህናቷ ጥቂቶችን ገድለውና አስረው ፤ ሀብቷን ወርሰው ፣ አብያተ ክርስቲያናትን ፣ ገዳማትንና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችን ዘግተው ፤ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሃይማኖት ትምህርት እንዳይሰጥ አደረጉ። የወረሱአቸውን አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ወደ ሙዚየም ፣ እስር ቤት ፣ ሲኒማ ቤት ወዘተ· ለወጡአቸው ።

እንዲሁም የኮሚኒስቱ መንግሥት ያቋቋመው አንዳንድ ስግብግብ ፣ መሠርይ ካህናትንና ምእመናንን ያቀፈው የታደሰችዋ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ (የተሐድሶ ጉባኤ) አባላት የቤተክርስቲያኒቱ ጊዜአዊ መሪ እኛ ነን በማለት የኮሚኒስቶችን ዓላማ ለማስፈጸም እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድረስ ካህናትንና ምእመናንን ያተራምሱና ያሠቃዩ ነበር ። በሀገሪቱ ለሚኖሩ የተለያዩ እምነት ተከታዮች ሁሉ በሰጡት ውሱንና የይስሙላ የእምልኮ መብት መሠረት የሰው ልጆች በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት አዳክሞ ለመደምሰስ በየጊዜው በአቴይስቶች (ኮሙኒስቶች ፣ ሶሻሊስቶች) የሚሰነዘሩባትን አፍራሽ ፕሮፓጋንዳዎችና መሰናክሎች ቤተ ክርስቲያን በትእግሥት በማሳለፍና ሰላምን እንዲያወርድላት ወደ አምላኳ ተግታ በመጸለይ ፣ ምእመናንን በማስተማርና በመንከባከብ ተግታ ሠርታለች ። መንግሥት በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የወሰደውን ከባድ ርምጃ መሪዎቿ እነ ፓትርያርክ ቲኮን በይፋ ተቃውመው ነበር ። ነገር ግን በፓትርያርኩ ፣ በካህናትና በምእመናን ላይ የሚፈጸሙ እስራቶችና ሥቃዮች ስለጸኑባቸው ፣ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኒቱን ከመደምሰስ ለማዳን በማሰብ የቀድሞ ተቃውሞአቸውን (ግዝታቸውን) አንሥተው ለሀገራቸውና ለመንግሥት ያላቸውን ዕርን አዘል ድጋፍ በጽሑፍ በይፋ ገልጸዋል።

ይህ ዓይነቱ ጭቆናና ሥቃይ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና በተለያዩ እምነት ተከታዮች ላይ ሩሲያ ውስጥ ብቻ የተፈጸመ ሳይሆን ፣ የሶሻሊስትን ርዮተዓለም በተቀበሉ ሀገሮችም ከሞላ ጐደል በአብዛኛዎቹ



www.ethiopianorthodox.org

ውስጥ ተፈጽሟል ። በሀገራችን በኢትዮጵያም የኮሚኒስት ርዮተዓለም አራማጅ የነበረው ፣ ከሐዲውና አረመኔው ፋሽስቱ የደርግ መንግሥት በሰማዕቱ በቅዱስ ቴዎፍሎስና ቍጥራቸው እጅግ ብዙ በሆኑ ኢትዮጵያ ውያን ላይ የሚዘገንኑ ሥቃዮችን ፈጽሟል ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ናዚ ጀርመን በ1941 ዓ·ም ሩሲያን በወረረችበት ጊዜ በያዘቻቸው ክፍላተ ሀገር ለሚኖሩ ክርስቲያ ኖች በሰጠቻቸው ጊዜያዊ የሃይማኖት ነጻነት ሳይደለሉ ፣ ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው በሀገር ወዳድነታ ቸው የታወቁት የሩሲያ ካህናትና ምእመናን ዓላማቸው ከሁሉም አስቀ ድሞ ሀገራቸውን ከደረሰባት ወረራ ነጻ ማውጣት ስለሆነ እነ አቡነ ሰርግዮስ ፣ ሌሎችም ጳጳሳት ፣ ካህናትና ምእመናን ከመንግሥት ጐን ተሰልፈው ለእናት ሀገራቸው ነጻነት እንዲዋጉ አስተማሩ ። ራሳቸውም ተካፋይ ሆኑ ። በዚያ ቀውጢ ወቅት ቤተ ክርስቲያኒቱ በሀገር ፍቅር ስሜት ተነሣሥታ ባደረገችው የሀገርን ነጻነት ማዳን ተጋድሎና በተለያዩ ምክንያቶች ኮሚኒስቶች በሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚኑ ትን ጭቆና ቀለል በማድረግ መጠነኛ ነጻነት ሰጧት ። ይኸውም በእስታሊን የሚመራው የኮሚኒስት መንግሥት ቤተ ክርስቲያኒቱ ፓትር ያርኳን መርጣ እንድትሾም በፈቀደው መሠረት በ1943 ዓ·ም አቡነ ሰርግዮስ ተመርጠው የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆኑ። እሳቸውም በተሾሙ በስድስት ወራቸው ስላረፉ በ1944 ዓ·ም አቡነ አሌክሲ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ ። ቀስ በቀስም የሩሲያ ኮሚኒስት መንግሥት ዕድሜአቸው ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑ ምእመናን የሃይማኖት ትምህርት እንድትሰጥ ፣ ለካህናት ማሰልጠኛ የሚሆኑ የተወሰኑ ሴሚናሪ ዎች እንድትከፍት ፣ የተወሰኑ ገዳማት ተከፍተው መንፈሳዊ ተግባራቸ ውን እንዲያከናውኑ ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትም በተወሰነ ቅጅ እንዲታተሙ ወዘተ· ፈቀደ ። እንዲሁም በሩሲያ መንግሥት ሕግ መሠረት ከ18 ዓመት በታች ሕፃናትና ወጣቶች በየትምህርት ቤቶች የኮሚኒዝምን እግዚአብሔ ርን የሚያስክድ ፕሮፓጋንዳ ቢማሩም ፣ በየቤታቸው እናቶቻቸው የክርስትናን ትምህርት አብራርተው ስላስተማሩአቸው ብዙዎች በኦርቶ ዶክስ እምነታቸው ጸንተው ኖሩ ። በዚህ አኳኋን እቤተ ክርስቲያን እንዳይሄዱና የሃይማኖት ትምህርት እንዳይማሩ የተከለከሉትን ልጆች እናቶቻቸውና አያቶቻቸው በማስተማር ለኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org

ጸንታ መኖር ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

በሥራ ገበታ ላይ የተሠማሩ ወንዶች እቤተ ክርስቲያን ሄደው ፈጣሪያቸውን ሲያመልኩ ከታዩ የሥራና የደመወዝ እድገት ስለሚነፈጋቸው ፣ የስም ማጥፋት ዘመቻም ስለሚካሄድባቸው ወዘተ ብዙዎቹ ወደ ቤተ ክርስቲያን አይሄዱም ነበር ። በየእሑዱና በበዓላት ቀናት አብያተ ክርስቲያናትን ሞልተው ሲያመልኩ የሚታዩ በዕድሜ የገፉ ወንዶችና ሴቶች ነበሩ ። ብዙ ወጣት እናቶችም ጸሎተ ቅዳሴውን ይከታተሉ ነበር ።

ሆኖም ከሰባ ዓመታት ያህል በኋላ በፕሬዝዳንት ጎርባቾብ ዘመነ መንግሥት ለኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችና ለሶቪየት ዜጎች ሁሉ ተገቢው የእምነትና የአምልኮ ነጻነት ተሰጥቷል ። ቀደም ሲል ከተወሰዱባት አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት አብዛኞቹ ተመልሰውላታል ።

ክርስትና ሬሻ የገባበት አንድ ሺህኛ ዓመት ከሰኔ 5–16,1988 ዓ·ም ከፍተኛ የመንግሥቱ ተወካዮችና ጥሪ የተደረገላቸው የውጭ ሀገር ፓትርያርኮች ፣ ካርዲናሎች ፣ ሊቃነ ጳጳሳት ፣ ቀሳውስት ፣ ቡዲሂስቶች ወዘተ በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል ። በዚሁ በዓል ወቅት መንግሥት ሞስኮ ከተማ ውስጥ ለአዲስ ቤተ ክርስቲያን መሥሪያ የሚሆን ሰፊ ቦታ ሰጥቷል። በዚህ አኳኋን ለዓመታት የተጫነባት ጭቆና ስለተነሣላት ቤተ ክርስቲያኒቱ በሰላም ተግታ በማስተማርና በመሥራት ለኦርቶዶክስ እምነት መጠናከር ፣ ለሀገሪቱ ብልጽግና ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንደምታደርግ ይታመናል ።

# ምዕራፍ ፺

## የሩማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

የሩማንያ ሕዝቦች የሮማውያን ዝርያ ያላቸውና በላቲን ቋንቋ የሚናገሩ ናቸው ። ለመጀመሪያ ጊዜም ክርስትና ሩማንያ ውስጥ የተሰበከች በሮማ የቅኝ ግዥ ክርስቲያን ወታደሮች በ4ኛው መቶ ዘመን መሆኑ ይነገራል ። አውሳብዮስ ግን ሐዋርያው እንድርያስ በመጀመሪያው መቶ ዘመን ሩማንያ አካባቢ ክርስትናን ማስተማሩን ጽፏል ።

ሀገሪቱ በቡልጋርያ መንግሥት ትግዛ በነበረችበት ወቅት በላቲን ቋንቋ ትገለገልባቸው የነበሩትን የጸሎት መጻሕፍት ትታ በ10ኛው መቶ ዘመን ወደ እስላቮኒክ ቋንቋ በመተርጐም ለወጠች ። ሆኖም ብዙ የላቲን



www.ethiopianorthodox.org

ቃላት በጸሎት መጻሕፍቶቿ ውስጥ ይገኛሉ ። በየጊዜው ከቍስጥንጥንያ መንበረ ፓትርያርክ ጋር በተፈጠረው የቅርብ ግንኙነት መሠረት ብዙ የግሪክ ጳጳሳት ሩማንያ ውስጥ በመንፈሳዊው ተግባር ተካፋይ በመሆን ከፍ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል ። በነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች የሩማንያ ቤተ ክርስቲያን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሆነች ።

የሩማንያ ቤተ ክርስቲያን በ1865 ዓ·ም ራሷን ችላ የምትተዳደር (አውቶኬፋሎስ) መሆኗን ብትወስንም ፣ ይኸው ውሳኔዋ ለሃያ ዓመታት ያህል በቍስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ተቀባይነት ሳያገኝ ቈይቶ በ1885 ዓ·ም በቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ በኢዮአቄም አራተኛ ተቀባይነትን አግኝቶ ስለጸደቀ ራሷን ችላ ትተዳደር ጀመር ። በ1925 ዓ·ም ደግሞ የፓትርያርክነት ማዕርግ ተጎናጸፈች ።

በሶሻሊስት ሀገሮች ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት የተለየች በመሆኗ የአብያተ ክርስቲያናት መተዳደሪያ የሚገኘው በምእመናን ከሚደረገው መዋጮ ነበር ። የሩማንያ ሶሻሊስት መንግሥት ግን የካህናትን ቀለብ ይከፍል ነበር። በቤተ ክርቲያኒቱ ሥር የሚተዳደሩትን መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች ወጭም ይደጉም ነበር። ሆኖም ከኮሚኒስት ሥርዓት ውድቀት በፊት በሌሎች የሶሻሊስት ሀገሮች እንደሚደረገው ሁሉ ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናትና ወጣቶች የሃይማኖት ትምህርት በይፋ አይሰጥም ነበር። አልፎ አልፎ አንዳንድ ካህናት እስር ቤት ተጨምረዋል።

የሩማንያ ቤተ ክርስቲያን ከኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በምእመናን ብዛት ከሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀጥላ ሁለተኛውን ደረጃ የያዘች ናት ። እሷም ምእመናንን የሚያገለግሉ ካህናት የሚሰለጥኑባቸው ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችና መንፈሳዊ ነክ የሆኑ ጽሑፎችን የምታወጣባቸው መጽሔቶች አሏት።

## ምዕራፍ ፲

## የሰርቢያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

የሜቶዲዮስ ደቀ መዛሙርት በነበሩት በቢዛንታይን የወንጌል መልእክተኞች ትጋት ክርስትና ሰርቢያ ውስጥ በ9ኛው መቶ ዘመን በተሰበከችበት ወቅት ልዑል ሙቲሚርና (860 891) ብዙ ሰዎች


www.ethiopianorthodox.org

በክርስቶስ አምነው ስለተጠመቁ ክርስትና የመንግሥቱ ሃይማኖት ሆነች።

በ1220 ዓ.ም በአቶስ ገዳም በብሕትውና ይኖር የነበረው ቅዱስ ሳቫስ በወንድሙ በዳግማዊ እስጢፋኖስ ድጋፍ በቊስጥንጥንያው ፓትር ያርክ ኒቅያ በተባለች ቦታ ውስጥ የመጀመሪያው የሰርቢያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቱ ራሷን የቻለች (አውቶኬፋሎስ) ሆነች ። በቱርክ መንግሥት ይገዙ በነበሩ ሀገሮች የሚኖሩ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በቊስጥንጥንያው ፓትርያርክ ሥር እንዲተዳደሩ በ1766 ዓ.ም በወጣው የመንግሥቱ ትእዛዝ መሠረት የሰርቢያ ኦርቶዶ ክስ ቤተ ክርስቲያንም በቊስጥንጥንያው ፓትርያርክ ስትተዳደር ቈይታ በ1879 ዓ. ም ሰርቢያ ነጻነቷን ስትጎናጸፍ ቤተ ክርስቲያኒቱም እንደ በፊቱ ራሷን በራሷ ትመራ ጀመር ።

በ1346 ዓ.ም የሰርቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪ በቤተ ክርስቲያኒቱ ጳጳሳት ውሳኔ መሠረት የፓትርያርክነት ማዕርግ ቢጎናጸፍም ይኸው ማዕርግ በቊስጥንጥንያ ፓትርያርክ በአቡነ ሜሌትዮስ አራተኛ ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘው በ1922 ዓ.ም ነው።

የናዚ ጀርመን መንግሥት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዩጎዝላቪ ያን በኃይል በወረረበት ቀውጢ ጊዜ ካህናቱ በሀገር ፍቅር ስሜት ከነጻ አውጭ አርበኞች ጎን ስለተሰለፉ ጀርመኖች ብዙ ጳጳሳትንና ካህናትን ገድለዋል። ፓትርያርኩ አቡነ ገብርኤልም ጀርመኖችን በመቃወሙ በናዚዎች እስር ቤት አራት ዓመት ማቋል ። ይህ ዓይነቱ በሀገር ፍቅር ምክንያት የተደረገው ተጋድሎ በዩጎዝላቪያ መንግሥትና ሕዝብ ዘንድ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ከፍ ያለ አክብሮትን አትርፎላታል ። በፕሬዝዳንት ቲቶ የኮሚኒስት አገዛዝ መርሆ መሠረት ቤተ ክርስቲያኒቱ ከመንግሥት የተለየች ብትሆንም ፣ በሥሩአ ባሉት መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች ካህናትን እያሰለጠነች ለምእምናኖቿ መንፈሳዊ አገልግሎቷን ታበረክታ ለች ። በቅርቡ የኮሚኒስት ሥርዓት ከመውደቁ በፊት በሌሎች የኮሚኒስት (የሶሻሊስት) ሀገሮች ለሕፃናትና ለወጣቶች በትምህርት ቤቶች የሃይማ ኖት ትምህርት መስጠት ሲከለከል ፣ የሰርቢያ ቤተ ክርስቲያን ግን የማስተማር ነጻነት ነበራት። በዚሁ ነፃነት መሠረት ቤተ ክርስቲያኒቱ ሕፃናትንና ወጣቶችን በግብረገብነት ትምህርት አንጻ ታሳድጋለች ።


www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፰

## የቡልጋርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ምንም እንኳ ወንጌል በባልካን ሀገሮች አካባቢ በመጀመሪያው መቶ ዘመን የተሰበከች መሆኑ ቢታመንም፤ ክርስትና በቡልጋርያ ውስጥ በይፋ የተሰበከችው በ9ኛው መቶ ዘመን ከቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ ከፎትዮስ በተላኩ የቢዛንታይን የወንጌል መልእክተኞች ትጋት ነው ። በ865 ዓ.ም የቡልጋርያ ንጉሥ ቀዳማዊ ቦሪስና ብዙ ሕዝብ በክርስቶስ አምነው በመጠመቃቸው የኦርቶዶክስ እምነት የመንግሥቱ ሃይማኖት ሆነች ።

በዚያን ጊዜ ቡልጋርያ ውስጥ ያስተምሩ የነበሩ የካቶሊክ እምነት ተከታይ የጀርመን ሚስዮናውያን የቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ ለቡልጋርያ ቤተ ክርስቲያን የነፈጋትን ራስን በራስ የማስተዳደር (የኦቶኖሚ) መብት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትሰጣታለች በማለት ንጉሥ ቦሪስን አግባቡት። ንጉሡም ለጊዜው እውነት መስሎት እሱና መሰሎቹ የካቶሊክን ሃይማኖት ተቀብለው ነበር ። ሆኖም ቀስ በቀስ ተንኮላቸውን በመረዳቱና የካቶሊክ ሚስዮናውያንን ከሀገሩ በማባረሩ ዓላማቸው ከሽፎ የቡልጋርያ ሕዝብ በኦርቶዶክስ እምነቱ ጸንቶ ኖረ። ይህ በፖፕ ኒኮላዎስ አንደኛ አደፋፋሪነት የተፈጸመው የጀርመን (የፍራንኮች) ሚስዮናውያን ሕገ ወጥ ሙከራ ለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መራራቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ከላይ እንደተጠቀሰው በ9ኛው መቶ ዘመን የእስላቮች ሐዋርያት የተባሉት የተሰሎንቄ ተወላጅ የነበሩ ወንድማማቾች ቅዱስ ቄርሎስና (ቈስጠንጢኖስና) ሜቶዲዮስ በቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ በፎትዮስ ወደ ቡልጋርያ ተልከው አስተማሩ። እንዲሁም ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በተወለዱበት አካባቢ ከሚኖሩት እስላቮች የእስላቭን ቋንቋ ተምረው ስለነበር የእስላቮኒክ ቋንቋ ፊደሎች አዘጋጅተው ከደቀመዛሙርቶቻቸው ጋር በመረዳዳት መጽሐፍ ቅዱስን ፤ የቅዳሴ መጻሕፍትንና ብዙ መንፈሳዊ ነክ የሆኑ መጻሕፍትን ከጽርዕ ያን ጊዜ ሕዝቡ ወደሚረዳው ወደ እስላቮኒክ ቋንቋ ተርጒመው አዘጋጁ ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን አሳነጹ ። በምሥራቅ አውሮጳ ያሉ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የተጠቀሙበት እነዚህ የወንጌል መልእክተኞች በእስላቮኒክ ቋንቋ ባዘጋጁአቸው መንፈሳዊ ነክ መጻሕፍት ነው። እስከ ዛሬ ድረስም ሥርዓተ ቅዳሴ የሚፈጽሙ በነዚሁ መጻሕፍት ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ሀገሪቱ በቢዛንታይን መንግሥት ሥር ትተዳደር (ትገዛ) በነበረች በት ወቅት በ1018 ዓ.ም ዳግማዊ ባስልዮስ የተባለው የቢዛንታይን ንጉሥ ለቡልጋርያ ቤተ ክርስቲያን ራስን ችሎ የመተዳደር (አውቶኬፋሎስ) መብት ሰጥቶ ነበር ።

በ1235 ዓ.ም የቡልጋርያ ቤተ ክርስቲያን በቍስጥንጥንያው ፓትር ያርክ በዳግማዊ ጀርመኖስ የፓትርያርክነት ማዕርግ ተሰጣት ። ሆኖም ሀገሪቱ በኦቶማን ቱርኮች እጅ በወደቀችበት ጊዜ በ1393 ዓ.ም በገዥዎች ትዕዛዝ የቤተ ክርስቲያኒቱ የፓትርያርክነት ማዕርግ ተገፎ በቍስጥንጥ ንያ መንበረ ፓትርያርክ ሥር ሆና የግሪክ ተወላጅ በሆኑ ጳጳሳት ስትተዳደር ቈየች ። በ1870 ዓ.ም ያለቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ ስምምነት (ፈቃድ) የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ቡልጋራውያን ሆኑ ። ቤተ ክርስቲያናቸውም ራሷን ችላ የምትተዳደር ሆናለች ፤ በማንኛውም ሀገር የሚኖሩ ቡልጋራውያን ምእመናንም በዚችው ቤተ ክርስቲያን ሥር ይተዳደራሉ ብለው ወሰኑ ። ይህንኑም ውሳኔ የኦቶማን ሱልጣን አጸደ ቀው። የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ አንሲሞስ ስድስተኛ ግን ከሱ ጋር ሳይማከሩ በጠባብ ብሔርተኝነት ስሜት ተነሣሥተው የወሰኑትን ራስን ችሎ በሊቀ ጳጳስ ማዕርግ የመተዳደርን ሹመት ፤ እንዲሁም ከቡልጋርያ ግዛት ውጭ ያሉትን ምእመናን ማስተዳደር መሻትን ወዘተ. በመቃወም በ1872 ዓ.ም በጠራው ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት አወገዘ ። ይኸውም ውግዘት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል መቃቃርን በመፍጠር ለሰባ ሦስት ዓመታት ያህል ሳይነሣ ቈይቶ በቡልጋርያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ በአቡነ እስጢፋኖስና በቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ በቀዳማዊ ብንያም መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት በ1945 ዓ.ም ተነሣ።

በ1953 ዓ.ም ደግሞ ያለቍስጥንጥንያ መንበረ ፓትርያርክ ስምምነ ትና ፈቃድ ለቡልጋርያ ቤተ ክርስቲያን አቡነ ቄርሎስ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ ። ይህም ሹመት የቡልጋርያ ሶሻሊስት መንግሥትን ድጋፍ አግኝቷል ። ሆኖም ይህንኑ የፓትርያርክነት ማዕርግ የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ አቲናጎራስ ለስምንት ዓመት ያህል ሳይቀበለው ቈይቶ በ1961 ዓ.ም ተስማምቶ አጸደቀው ።

የቡልጋርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናኖቿን የሚያገለ ግሉ ካህናትን የምታሠለጥንበት ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትና መንፈሳዊ ነክ የሆኑ ጽሑፎችን የምታሳትምባቸው መጽሔቶች አሏት ።



www.ethiopianorthodox.org

ከኮሚኒዝም ሥርዓት ውድቀት በፊት በሶሻሊስት ሀገሮች እንደነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከመንግሥት የተለየች ነበረች ። በትምህርት ቤቶችም የሃይማኖት ትምህርት እንዳይሰጥ ተከልክሎ ነበር ። የምትተዳደረውም ከምእመናን በሚሰበሰብ መዋጮ ነው። ከሀገሯ ውጭ አሜሪካ ፣ ካናዳ ፣ አውስትራሊያ ፣ እስታንቡል፣ ቡዳፔስት ፣ ቪየናና ቡካሬስት ውስጥ በቡልጋርያ መንበረ ፓትርያርክ ሥር የሚተዳደሩ አብያተ ክርስቲያናት አሉ ።

## ምዕራፍ ፱

### የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ሐዋርያው ጳውሎስ ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር አቴናና እንደ ቆሮንቶስ በመሳሰሉት በተለያዩ የግሪክ ከተሞችና ክፍላተ ሀገር በመጀመሪያው መቶ ዘመን ክርስትናን በትጋት መስበኩ (ማስተማሩ) በሐዋርያት ሥራና በጳውሎስ መልእክታት ውስጥ በሰፊው ተጽፎ ይገኛል ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በ8ኛውና በ9ኛው መቶ ዘመን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የሆኑ አንዳንድ ነገሥታትና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለጌታ ፣ ለጻድቃንና ለሰማዕታት ሥዕሎች የጸጋ (የአክብሮት) ስግደት ማድረግ አይገባም ብለው በተነሡ ጊዜ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የጸጋ ስግደት ተገቢ መሆኑን ተከራክረው በማስረዳት እንዲቀጥል አድርገዋል ።

በ1456 ዓ.ም የቱርክ ሠራዊት ግሪክን ይዞ በቍስጥንጥንያ የምትገኘውን የቅድስት ሶፊያን ቤተ ክርስቲያን ወደ መስጊድነት እንደለወጠ ሁሉ፣ ጥንታዊ በሆነው በፓርሲኖን ሕንጻ የነበረውን የቅድስት ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ወደ መስጊድነት ለውጦት ነበር ።

ሀገሪቱ በቱርኮች እጅ በወደቀችበት ወቅት ካህናቱ ሕዝቡን ይመሩና ያጽናኑ ነበር ። በ1821 ዓ.ም የግሪክ ሕዝብ በቱርክ መንግሥት ላይ እንዲያምጽ ከአነሣሡት አርበኞች አንዱ የፓትራ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጀርመኖስ ነበር ።

ግሪኮች ከቱርክ መንግሥት ጋር ላደረጉት የነጻነት ትግል ረድተሃል በመባል የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ጎርጎርዮስ አምስተኛ በ1821 ዓ.ም በቱርኮች በስቅላት ተገድሏል ። እንዲሁም ከ1940 ዓ.ም.ጀምሮ



www.ethiopianorthodox.org

በግሪክ ሕዝብ ላይ ከናዚ ጀርመን ፣ ከፋሽስት ኢጣልያ ፣ ከቡልጋርያ ፣ ከኮሚኒስት ሰርጎ ገቦች በተከታታይ ጦርነቶች በተሰነዘሩበት ወቅት ሁሉ ካህናቱ የግሪክ ሕዝብ የመጡበትን ጠላቶች በጀግንነት በመቋቋም ነጻነቱን ጠብቆ እንዲኖር በማበረታታት የመከራው ተካፋዮች ሆነዋል ።

የግሪክ ቤተ ክርስቲያን የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ በሃይማኖት አባትነቱ በማክበር የበላይነቱን ብትቀበልም እንኳ ግሪክ ከቱርክ ነጻ ከወጣችበት ከ1833 ዓ.ም ጀምሮ በአስተዳደር የነበራትን ግንኙነት አቋርጣ ራሷን የቻለች(አውቶኬፋሎስ) ሆነች ። ይህንንም ያደረገችው የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ በቱርክ መንግሥት ግፊት በምታካሂደው ተግባር ላይ እንቅፋት (ተጽእኖ) እንዳይፈጥርባት በመሥጋት ነበር ። የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ለዐሥራ ሰባት ዓመታት ድርጊቱ ትክክል አይደለም ሲል ከቈየ በኋላ ይህንኑ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ውሳኔ በ1850 ዓ.ም አጽድቆታል ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትተዳደረው በአቴናው ሊቀ ጳጳስ ፕሬዝዳንትነት በሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ነው ።

በዘመናችን ከኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሙሉ በሙሉ የመንግሥት ሃይማኖት ሆና የምትገኝ ይህች ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት ።

የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርትንና ስብከተ ወንጌልን በሰፊው የምታካሂደው በሀገሯ ውስጥ ነው ። በ1911 ዓ. ም በቆሞስ ኤቭሴቢዮስ ማቴዎፑሎስ የተመሠረተው "ዞይ(ሕይወት)" የተባለው መንፈሳዊ ትምህርት ባላቸው መምህራንና ምእመናን በግል የሚተዳደረው መንፈሳዊ ድርጅት፤ እንዲሁም በ1930 ዓ.ም ተመሥርቶ በቤተ ክርስቲያኒቱ ሥር የሚተዳደረው "አፖስቶሊኪ ዲያኮንያ (ሐዋርያዊ አገልግሎት)" የተባለውና ሌሎችም ድርጅቶች በሀገሪቱ ውስጥ ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ፣ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ፣ በትምህርት ቤቶችና በሰንበት ትምህርት ቤቶች ለማስተማሪያነት የሚጠቅሙ መጻሕፍትን አዘጋጅተው በብዛት በማሳተም፣ የወጣቶችን መንፈሳዊ ንቅናቄ በማበረታታት ወዘተ. በትጋት ይሠራሉ ።

በመንፈሳዊ ተግባር የሚሠማሩትን ካህናት የምታሰለጥንባቸው በአቴናና በተሰሎንቄ ዩኒቨርሲቲዎች ሁለት መንፈሳዊ ፋካልቲዎች አሏት ። በተጨማሪም ስብከተ ወንጌል የሚሠማሩና በየትምህርት ቤቶች



www.ethiopianorthodox.org

የሃይማኖት ትምህርት የሚያስተምሩ ካህናትና መምህራን በብዛት የሚማሩባቸው (የሚሠለጥኑባቸው) በመለስተኛ መንፈሳዊ ኮሌጅ ደረጃ የሁለት ዓመት ኮርስ የሚሰጡ ወደ ዐሥራ ሁለት የሚጠጉ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች አሏት ።

በዘመናችን በየሀገሩ ከሚገኙት የኦርቶዶክስን እምነት ከሚከተሉ አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ በሙሉ የራሷ እምነት ተከታይ የሆነ የመንግሥት ድጋፍ ያላት የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ስለሆነች የኦርቶዶክስን እምነት ለማጠናከር ፣ ወንጌልን በሀገሯና ከሀገሯ ውጭም ለማዳረስ የምትችል እሷ መሆኗን ሊቃውንት በተስፋ ይገምታሉ።

# ምዕራፍ ፲

## የቆጵሮስ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 13 እንደተጻፈው በቆጵሮስ ደሴት ውስጥ ክርስትና የተሰበከችው በመጀመሪያው መቶ ዘመን በጳውሎስና በበርናባስ ነበር ። በ4ኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ላይ ተነሥተው ክርስትናን ካስፋፉት የቤተ ክርስቲያን አባቶች አንዱ በደሴቲቱ ውስጥ የምትገኘው የሰላሚና ጳጳስ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ነበር ።

በ431 ዓ·ም በተደረገችው በኤፌሶን ጉባኤ የቆጵሮስ ቤተ ክርስቲያን ከአንጾኪያ መንበረ ፓትርያርክ አስተዳደር ሥር ነጻ እንድትወጣ ስለተወሰነና ውሳኔውም በንጉሥ ዜኖ በተግባር ላይ እንዲውል ስለተደረገ ከ488 ዓ·ም ጀምሮ ራሷን ችላ ትተዳደር ጀመር ። ሆኖም ደሴቲቱ በተለያዩ ጊዜያት በቢዛንታይን መንግሥት ፣ በዓረቦች ፣ በመስቀል ጦረኞች ፣ በቱርኮችና በእንግሊዞች እየተያዘች ስለተገዛች ሕዝቦቿ ከፍ ያለ ሥቃይ ደርሶባቸዋል ። ያ ሁሉ ሥቃይ ቢደርስባቸውም ቅሉ የቆጵሮስ ምእመናን ከኦርቶዶክስ እምነታቸው ዝንፍ አላሉም ።

ቱርኮች አብዛኛውን ጊዜ አንድ ሀገርን በኃይል ከያዙ በኋላ ከመንፈሳዊ አመራሩ በተጨማሪ የሲቪል አመራሩን የሀገሪቱን ቤተ ክርስቲያንመሪ ለነሱ ተጠሪ አድርገው የመሾም ልምድ ስለነበራቸው ፣ የቆጵሮስ ሊቀ ጳጳስም ከመንፈሳዊው ተግባሩ በተጨማሪ የቱርክን መንግሥት በመወከል የደሴቲቱም መሪ ነበር ።

በ1821 ዓ·ም ግሪኮች ከቱርክ አገዛዝ ነጻ ለመውጣት የትጥቅ ትግል


www.ethiopianorthodox.org

በጀመሩበት ወቅት የዚሁ አመጽ ደጋፊ በመሆን እርዳታ በመለገሳቸው የደሴቲቱ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ሲፕሪያኖስ ፣ ሦስት ጳጳሳት ፣ ብዙ ካህናትና ምእመናን በቱርክ ባለሥልጣኖች ተገድለዋል ።

የእንግሊዝ መንግሥት ደሴቲቱን በያዘበት ወቅትም የደሴቲቱ መንፈሳዊና ብሔራዊ መሪ ሊቀ ጳጳሱ ነበር ። የቆጵሮስ ደሴት ከእንግሊዞች አገዛዝ ነጻ ወጥታ ከግሪክ መንግሥት ጋር እንድትቀላቀል የደከመው አቡነ መቃርዮስ ቀደም ሲል በ1950 ዓ.ም በቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዱስ ሲኖዶስ በመመረጥ ከነበረው ከደሴቲቱ የሊቀ ጵጵስና ማዕርግ በተጨማሪ በ1960 ዓ.ም ነጻነቷን ለተጐናጸፈችው ለቆጵሮስ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት ሆኖ በመሾም አገልግሏል ። ጥጥራቸው አናሳ በሆነው በቱርክ ቆጵሮሳውያን ተቃውሞ ምክንያት ደሴቲቱን ከግሪክ ሀገር ጋር አንድ ለማድረግ በግሪክ ቆጵሮሳውያንና በግሪክ መንግሥት በየጊዜው የተደረገው ሙከራ እስከ አሁን ድረስ አልተሳካም ።

ቆጵሮስ በሚገኘው ኪኮስ በተባለው ገዳም ታምራትን የሚያደርግ የእመቤታችን ሥዕል መኖሩ ይነገራል ።

የቆጵሮስ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደረው በቅዱስ ሲኖዶስ ነው ።

እላይ ታሪካቸው በአጭሩ ከተዘረዘረው አብያተ ክርስቲያናት በስተቀር ራሳቸውን ችለው (አውቶኬፋሎስ ሆነው) የሚተዳደሩ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጆርጅያ ፣ ፖላንድ ፣ ቼኮዝሎቫኪያ (ጭራቪያ) ፣ አልቤንያ ፣ ሲና ተራራ ወዘተ. ናቸው ። ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር (አውቶኖሞስ) መብት ኖሮአቸው ሙሉ በሙሉ ነጻ (አውቶኬፋሎስ) ያልሆኑ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ፊንላንድ ፣ ቻይና ፣ ጃፓን ወዘተ. ውስጥ ይገኛሉ ።

እንዲሁም ቀደም ብለን እንደተመለከትነው በቍስጥንጥንያ ፣ በእስክንድርያ ፣ በአንጾኪያ ፣ በሩሲያ ፣ በሰርቢያ ፣ በሩማንያ ፣ በቡልጋርያ ፓትርያርኮች ሥር የሚተዳደሩ ከየሀገሮቻቸው በስደት ፣ በሥራና በተለያዩ ምክንያቶች በየጊዜው የወጡ ምእመናን ያቋቋሟቸው የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በሚገንና ደቡብ አሜሪካ ፣ ካናዳ ፣ እንግሊዝ ፣ ፈረንሳይ ፣ ቪየና ፣ ኢትዮጵያ ፣ ኡጋንዳ ፣ ኬንያ ወዘተ. ውስጥ አሉ ። ለእነዚህ ከትውልድ ሀገሮቻቸው ውጭ ለሚኖሩ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን የሚያገለግሉ ካህናት የሚያሰለጥኑባቸው ሴሚናሪዎች በሚገን


www.ethiopianorthodox.org

አሜሪካና ፈረንሳይ ውስጥ አሏቸው ። መንፈሳዊ ነክ መጽሔቶችንና መጻሕፍትን በእንግሊዝኛና በተለያዩ ቋንቋዎች እያተሙ ያወጣሉ ።

ባጠቃላይ እላይ እንደተመለከትነው በተለያዩ ሀገሮች የሚገኙ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የሚተዳደሩት እንደ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ማዕከል ሥር ሳይሆን ፤ ብዙዎቹ ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ ። ሆኖም በእምነት (በሃይማኖት) አንድ በመሆናቸው በዜግነት ፤ በዘር ፤ በቋንቋ ወዘተ· ልዩነት ምክንያት ሳይለያዩ የአንዲት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልጆች (ተከታዮች) አንድ ቤተሰብ መሆናቸውን በዘመናት ሁሉ በተግባር እየገለጹ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል አራት

## የምዕራብ (የካቶሊክና የፕሮቴስታንት) አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ

በዚህ ክፍል የካቶሊክንና የፕሮቴስታንትን አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ በሁለት ምዕራፍ ከፍለን በአጭሩ እንመለከታለን ።

## ምዕራፍ ፩

### የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

### ሀ) ከመጀመሪያው እስከ ስምንተኛው መቶ ዘመን ያለው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ሐዋርያው ጴጥሮስና ጳውሎስ ሮም ውስጥ ክርስትናን ሲያስተምሩ በኔሮን ትእዛዝ በክርስቲያኖች ላይ በተነሣው ስደት በ64 ዓ·ም በሰማዕትነት ዐርፈው ጴጥሮስ በቫቲካን ኮረብታ ፡ ጳውሎስ በኦስትያ መንገድ ተቀበሩ ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስ የሮም ቤተ ክርስቲያን መሥራችና የመጀመሪያው ጳጳስ (ፖፕ) መሆኑን ታስተምራለች ። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስን "... አንተ ጴጥሮስ ነህ፡ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም ። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ ፡



www.ethiopianorthodox.org

በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል ፡ በምድር የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል ። …" (ማቴ· 16፡18-19)። "… ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን … በጎቼን አሠማራ አለው" (ዮሐ·21፡15-16) ሲል የተናገረውን መሠረት በማድረግ የሮም ቤተ ክርስቲያን በሊቀ ሐዋርያው በጴጥሮስ ስለተመሠረተች የሱ ተከታይ የሆኑ ፖፖች የክርስቶስ እንደራሴዎችና የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበላይነት ሥልጣን ያላቸው መሪዎች ናቸው በማለት ያስተምራሉ ። በተጨማሪም ሐዋርያው ዮሐንስ ኤፌሶን እያለ የሮሙ ፖፕ ቀዳማዊ ቀሌምንጦስ በ96 ዓ·ም ቆሮንቶስ በነበሩ ካህናትና ምእመናን መካከል የተፈጠረው አለመግባባት እንዲበርድ ፡ ከሥልጣናቸው የተወገዱ ካህናትም ወደ ቀደመ ሥልጣናቸው እንዲመለሱ የሚል መልእክት ጽፎ መላኩ ፖፑ በመላ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ያለውን ሥልጣን ይገልጻል ይላሉ ። ቀዳማዊ ጁልዮስ (337-352) ፖፕ በነበረበት ወቅት ቅዱስ አትናቴዎስን ለመደገፍና አርዮሳውያንን ለማውገዝ በ343 ዓ·ም ምዕራባውያን ጳጳሳት ብቻ በተገኙበት ሰርዲካ ውስጥ የተደረገችዋ ጉባኤ ለመጀመሪያ ጊዜ የሮሙን ፖፕ የበላይነት ሥልጣን አጸደቀች ። እንዲሁም በሰባተኛው መቶ ዘመን በሴቪሌ ሊቀ ጳጳስ በኢሲዶሬ በተሰበሰበው "የኢሲዶሬ የሐሰት ዶኩሜንቶች" በሚል ስያሜ በሚጠራው ጽሑፍ ውስጥ የሮሙ ፖፕ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበላይ ነው የሚል ክፍል አለ ። በዚሁ ጽሑፍ በመደገፍ እንደነቀዳማዊ ኒኮላ የመሳሰሉ ፖፖች በአብያተ ክርስቲያናት ላይ የነበራቸውን ፍጹማዊ ሥልጣን በተግባር ላይ ለማዋል ተጠቅመውበታል። ሆኖም በ16ኛው መቶ ዘመን የተነሡ ሊቃውንት ጽሑፉን በሚገባ ከመረመሩ በኋላ ከተሰበሰቡት ዶኩሜንቶች የአብዛኞቹ ይዘት ሐሰት ሆኖ ስለተገኘ ውድቅ አድርገውታል ። የፖፑ የበላይነት በተለይ በይፋ የተሰበከው በሮሙ ፖፕ በቀዳማዊ ልዮን (440-461) ነበር ። የሮም ንጉሠ ነገሥት ሣልሳዊ ቫሌንታይን ሐሳቡን በመደገፍ በግዛቱ የሚኖሩ ጳጳሳት ሁሉ የፖፑን የሁሉ በላይነት ሥልጣን ተቀብለው በተግባር እንዲያውሉት አዝዞ ነበር ። ይህንኑ ሐሳብ የአርዮንታልና (የተዋሕዶና) የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በአንድ ድምጽ ተቃውመውታል ። በኬልቄዶን ጉባኤም የፖፑና የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ሥልጣንና ክብር እኩል መሆኑ ተወስኗል ።

በ4ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ ክርስትና በታላቁ ቈስጠንጢ



www.ethiopianorthodox.org

ኖስ ነጻ ከወጣች በኋላ የወንጌል ትምህርት በሰፊው ይሰጥ ጀመረ ። ለዚሁ የተቀደሰ ተግባር ማከናወኛ ለቤተ ክርስቲያን ከንጉሡ የማቴሪያል ድጋፍ ይሰጣት ነበር ። ቈስጠንጢኖስ ለፖፖች መኖሪያ እንዲሆን ላቴራን የተባለውን ቤተ መንግሥት ሰጠ ። እንዲሁም ፖፖች የሮማን ከተማና አካባቢዋን እንዲገዙ (እንዲያስተዳድሩ) ፈቀደላቸው ። እነሱም እስከ 1308 ዓ.ም ድረስ በዚያው ቤተ መንግሥት ኖሩ ። በቅዱስ ጴጥሮስ መቃብር ላይ የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያንም አሠራ ። ክርስቶስ ከሙታን የተነሣበት ቀን እሑድ ክርስቲያኖች እየተሰበሰቡ በአንድነት አምላካቸውን የሚያመልኩበት ቀን ስለነበረች በዐዋጅ የዕረፍት ቀን ሆነች ። በዚህ አኳኋን ቈስጠንጢኖስ በየጊዜው ባደረጋቸው ጦርነቶች የመንግሥቱን (የግዛቱን) አንድነት ሲያጸና ፣ የክርስትና እምነት አንድ ነት ደግሞ እንደ ኒቅያ በመሳሰሉ የጉባኤ ውሳኔዎች በመመራት እንዲጠበቅ ረድቷል ። ሆኖም በኒቅያ ጉባኤ የተወገዘው የአርዮስ የክሕደት ትምህርት በመጥፋት ፈንታ ቀስ በቀስ ደጋፊዎችን በማግኘት እያንሠራራ ሄደ ። በተለይ የታላቁ ቈስጠንጢኖስ ልጅ ዳግማዊ ቍንስጣ የኦርቶዶክስ እምነቱን ትቶ የአርዮሳውያን እምነት ተከታይ ስለሆነ ጳጳሳትና ምእመናን የአርዮስን ኑፋቄ እንዲቀበሉ ማስገደድ ጀመረ ። ይህንኑ የተሳሳተ ዓላማውን የተቃወሙትን እንደ እስክንድርያው ፓትርያ ርክ ቅዱስ አትናቴዎስ የመሳሰሉትን ወደ ስደት ቦታዎች መላክ የተለመደ ተግባሩ ሆነ ።

አርዮሳውያን ጳጳሳት በንጉሡ ድጋፍ በ335 ዓ.ም ጢሮስ ውስጥ ባደረጉት ጉባኤ ቅዱስ አትናቴዎስን ካወገዙ በኋላ የሮሙ ፖፕ ቀዳማዊ ጁሊዮስ ውሳኔአቸውን በመደገፍ እንዲያጸድቅላቸው ጠየቁት ። እሱም በ343 ዓ.ም ሰርዲካ ውስጥ ጉባኤ አድርጎ የኦርቶዶክስ እምነት አጋርና መሪ የሆነውን ቅዱስ አትናቴዎስን በመደገፍ አርዮሳውያንን አወገዘ ። ቀደም ሲል በ339 ዓ.ም ቅዱስ አትናቴዎስ ከእስክንድርያ ተሰዶ ሮም ሲገባ ፖፑ በክብር ተቀብሎ አስተናግዶታል ።

በኦርቶዶክስ እምነቱ የጸናው ቀዳማዊ ቴዎዶስዮስ (379–395) የአሕዛብንና የአርዮሳውያንን እምነት በጥብቅ ይቃወም ነበር ። በ381 ዓ.ም የተደረገችው የቍስጥንጥንያ ጉባኤም በተሳካ አኳኋን እንድትካሄድ ረድቷል ።

በ390 ዓ.ም የተሰሎንቄ ገዥ በመገደሉ ምክንያት ቴዎዶስዮስ



www.ethiopianorthodox.org

በደም ፍላት ተገፋፍቶ በችኮላ ያለምንም ፍርድ የብዙ ንጹሐን ሰዎችን ደም በከንቱ በማፍሰሱ የሚላኑ ጳጳስ አምብሮስዮስ ያላንዳች ፍርሃትና ይሉኝታ በመገሠጽ ንስሐ እንዲገባ አዘዘው ። ንጉሡም ትእዛዙን በመቀበል ንስሐ ገባ ። በዚህ አኳኋን አንዳንድ ቈራጥ የሆኑ ጳጳሳት (ካህናት) እንደነቢዩ ናታን (2ሳሙ. 12፡1–15) መንፈሳዊ ተግባራቸውን ያለምንም ፍርሃት ሲያከናውኑ ፤ በፍርሃት የተዋጡና በጥቅም የታሠሩ ካህናት ደግሞ አንዳንድ ገዥዎች በመንፈሳዊ ተግባር ጣልቃ ሲገቡ አሜን ብለው ይቀበሉ ነበር ።

የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መሪዎች በወኪሎቻቸው አማካይነት በአራተኛው መቶ ዘመን ኒቅያና ቍስጥንጥንያ በተደረጉት ጉባኤዎች ላይ በመገኘት የከሐዲዎችን ትምህርት እንደተቃወሙ ሁሉ ፤ በአምስተኛው መቶ ዘመን በተደረጉት በኤፌሶንና በኬልቄዶን ጉባኤዎች ላይም ተካፋይ ሆነዋል ።

ዓለምን ለብዙ ዘመናት ሲገዛ የቈየው የሮማ መንግሥት የምዕራቡ (የላቲኑ) ክፍል ገዥ የነበረው ንጉሥ ቫሌንታይን ሦስተኛ የጦር አዛዡን አኤቲዮስን በመግደሉ የተቆጩ የአኤቲዮስ ደጋፊዎች ንጉሡን በመግደላቸው በተፈጠረው ሽኩቻ ምክንያት የሮማ መንግሥት ተዳክሞ ጠንካራ መሪ (ንጉሥ) ባልነበረበት ወቅት ፡ ሁንስ የተባሉት ሞንጎላውያን አሕዛብ ነገድ መሪ አቲላ በ425 ዓ.ም ሮምን ከቦ ለማጥፋት ወደፊት ሲገሠግሥ ፡ የሮሙ ፖፕ ቀዳማዊ ልዮን (440–461) ለሕይወቱ ሳይሳሳ በድፍረት ወደ አቲላ ሄዶ ሕዝቡንና ከተማይቱን ከማጥፋት እንዲቆጠብ በመማጠን ከጥፋት አድኗል ። እንዲሁም በ452 ዓ.ም በጋይሴሪክ የተመሩ ቫንዳልስ የተባሉት አረማውያን የሮምን ከተማ ለማጥፋት በከበቡአት ወቅት ፤ ፖፑ ከተማዋን እንዳያቃጥሉና ሕዝቡንም እንዳይጨፈጭፉ ስለተማጠናቸው በኑአሪዎች ሕይወት ላይ ከባድ ጥፋት ሳያደርሱ ከተማዋን ዘርፈው ወደ ሰሜን አፍሪካ ሄደዋል ።

የሮምን መንግሥት በየጊዜው ከወረሩት አረማውያን አብዛኞቹ የአርዮስን ትምህርት የሚከተሉ ክርስቲያኖች ስለነበሩ በሮም ግዛት ውስጥ የነበሩት ክርስቲያኖች በብዛት ከመጨፍጨፍና አብያተ ክርስቲያናትም በብዛት ከመቃጠል ድነዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

በ451 ዓ·ም በተደረገችው የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የልዮንን ትምህርት የሚከተሉ የካቶሊክና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት ሲሉ ፡ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መሪና አባት ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ለኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባሕርይ አለው በማለቱ አንድ የነበረችቱ ቤተ ክርስቲያን ተወጋግዛ ሁለት ላይ ተከፈለች ። እንዲሁም በኬልቄዶን ጉባኤ በ28ኛው አንቀጽ የመናገሻ ከተማዋ የቊስጥንጥንያ ፓትርያርክና የሮሙ ፖፕ በክብር እኩል ናቸው የሚለውን ድንጋጌ የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተቀብለው በተግባር ላይ ሲያውሉት ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አልተቀበለችውም ። በተጨማሪም የሮሙ ፖፕ በግሪክ ቤተ ክርስቲያን ላይ የበላይነትን መንፈስ ስላሳየ ፡ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ያለው መንፈስ ሕገ ወጥ ነው ስትል በጥብቅ ተቃውማለች ። በዚህ አኳኋን የበላይ ነኝ ፡ አይደለህም ፡ በመባባል በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች መካከል የተፈጠረው የሹመት ንትርክ በ863 ዓ·ም በቊስጥንጥንያው ፓትርያርክ በፎቴዎስና በሮሙ ፖፕ በቀዳማዊ ኒኮላዎስ ተጀምሮ ጥቂት ዘመን ከቈየ በኋላ በ1054 ዓ·ም ከፖፕ ልዮን ዘጠንኛ ተልከው ወደ ቊስጥንጥንያ የሄዱት መልእክተኞች እነ ካርዲናል ሑምበርት የቊስጥንጥንያው ፓትርያርክ ሚካኤል ኪሩላሪዎስ የፖፑን የበላይነት ሥልጣን ስላልተቀበለ አወገዙት ። እሱም በዚያው ዓመት የሮሙን ፖፕ አወገዘው ። ፓትርያርኩም ባደረገው ውግዘት ኢየሩሳሌም ፡ አንጾኪያ ፡ እስክንድርያ የነበሩ የግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትርያርኮች ተስማሙ ። ለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መለያየት ምክንያት የሆነው እላይ እንደ ተመለከትነው የሮሙ ፖፕ የበላይነትን ፈልጓል በማለት ብቻ ሳይሆን ፡ በኒቅያና በሁለተኛው በቊስጥንጥንያ ጉባኤዎች በተወሰነው በጸሎተ ሃይማኖትና በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለውን የሮም ቤተ ክርስቲያን በ1014 ዓ·ም "መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሳይሆን ከወልድም ተገኘ" ብላ በመወሰን አዲስ ትምህርት አስተምራለች በማለት ጭምር ነው ። ይህ ትምህርት በዚያን ዘመን ተጠናክረው የነበሩ የቪሲጎትስ ነገድ የሆኑትን አርዮሳውያንን ለመቃወሚያ ያመቻል ተብሎ እስጳኝ ውስጥ በ589 ዓ·ም በተደረገችው በሦስተኛዋ በቶሌዶ ጉባኤ ተወስኖ ሲሠራበት ከቈየ በኋላ ዘግየት ብሎ በዐሥራ አንደኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሮም ውስጥም ተቀባይነት አገኘ ይባላል ። ይህንን



www.ethiopianorthodox.org

ትምህርት የምትቃወም የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳትሆን እምስቱ የኦርየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናትም ናቸው። በመጀመሪያው በኒቅያና በሁለተኛው በቊስጥንጥንያ ጉባኤዎች በተወሰነው በጸሎተ ሃይማኖት "ከአብ የሠረፀ" የሚለውንና በዮሐ· 15፥ 26 የተጻፈውን መሠረት በማድረግ የግሪክ ኦርቶዶክስና የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚያምኑት "ከአብ የሠረፀ" ብለው ነው ።

በ1274 ዓ·ም በተደረገችው በልዮን ጉባኤና በ1439 ዓ·ም በተደረገችው በፍሎሬንስ ጉባኤ የካቶሊክን ፥ የግሪክ ኦርቶዶክስንና ሌሎችንም አብያተ ክርስቲያናት አንድ ለማድረግ የተሞከረው ጥረት ከንቱ ሆኖ ቀረ። ምክንያቱም የጉባኤው ዓላማ በግሪክ ኦርቶዶክስ ፥ በካቶሊክና በኦርየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሰላም ተመሥርቶ በእምነት አንድ በመሆን የቱርክን መንግሥት (የእስላሞችን) ኃይል በኅብረት ለመቋቋም እንዲችሉ ለመገፋፋትና ሁሉንም ከሮሙ ፖፕ ሥልጣን ሥር ለማድረግ የታሰበ ስለነበር ነው ። ይህንኑ የፖፑን የበላይነት ፍላጎት በመገንዘብ ከግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች አብዛኞቹ የጉባኤዎችን ሐሳብ ተቃወሙ ። የጉባኤዎችን ውሳኔ ተቀብለናል ካሉትም መካከል ቊስጥንጥንያ እንደገቡ የቀድሞ ሐሳባቸውን ለውጠው ውሳኔውን የሚቃወሙ መሆናቸውን ገለጹ ።

በጉባኤዎች ላይ የተካፈሉት የኦርየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮችም በውሳኔው አልተስማሙም ። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ ከሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ ወዲህ በየጊዜው በአብያተ ክርስቲያናት መካከል በመደረግ ላይ ያሉት ውይይቶች የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን በእኩልነት መንፈስ በተመሠረተ አንድነት ያስተሳስሩአቸው ይሆናል ተብሎ ይታመናል ።

የሮማ መንግሥት የምዕራቡ (የላቲኑ) ክፍል ነገሥታት ቀስ በቀስ እየተዳከሙ ስለሄዱ በኦዶሴር የተመራው የአረማውያን ጦር የሮማን ንጉሠ ነገሥት በ476 ዓ·ም· አስወግዶ የመንግሥቱን ሥልጣን ያዘ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በምዕራቡ ክፍል የባላባቶችንና የምእመናንን ድጋፍ በማግኘት የፖፑ ሥልጣን እየተጠናከረ ቢሄድም ቅሉ ፥ ፖፑ እየተጠናከረና በሕዝቡ እየታቀፈ ሲሄድ ሙሉ ነጻነት ተሰምቶት በመንግሥቱ ላይ አመጽ እንዳያስነሣበት በማሰብ ኦዶሴር አዲስ የሚመረጠው ፖፕ ሹመት



www.ethiopianorthodox.org

በቍስጥንጥንያ መንግሥት መጽደቅ ያለበት መሆኑን ወስኖ አስታወቀ ። ፖፖችም ይህንኑ ውሳኔ ለተወሰነ ጊዜ በተግባር ላይ ቢያውሉትም እንኳ ፣ እምነት ነክ በሆኑ ጉዳዮች አልፎ አልፎ ከቍስጥንጥንያ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ጋር ተጋጭተዋል ። አንድ የነበረው የምዕራቡ ክፍል ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በብዙ ትናንሽ ሀገሮች ተከፋፍሎ እርስ በእርሳቸው ተጻራሪ (ተፎካካሪ) በሆኑ የአረማውያን ገዥዎች (ነገሥታት) ይተዳደር ጀመር ። በነዚህ በተከፋፈሉት ሀገሮች ውስጥም ካቶሊኮች ፣ አርዮሳውያንና አሕዛብ በኅብረት ይኖሩ ጀመር ። ቀስ በቀስ ከአሕዛብ አብዛኞቹ የካቶሊክን እምነት ተቀበሉ ። ይኸውም በ496 ዓ·ም የፍራንኮች (የፈረንሳዮች) ንጉሥ ክሎቪስ ካቶሊካዊቲቱን ልዕልት ክሎቲልዳን አግብቶ ከሦስት ሺህ ወታደሮቹ ጋር የልደት (የገና) ዕለት በአቡነ ሬምል ተጠምቆ ክርስትናን በመቀበል ከአሕዛብ ወገን የመጀመሪያው ካቶሊካዊ ልዑል ሆነ ። ክሎቪስ ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ የሚሆናት መሬትና የመሳሰሉ እርዳታዎችን በመለገሥ ሲረዳ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ደግሞ ምእመናን በቀና ልቦና በመታዘዝ እንዲገዙለት በማስተማር ግዛቱ የተቃና እንዲሆንለት ትረዳ ነበር ። በዚህም አኳኋን በመካከለኛው የታሪክ ዘመን ሰፊው የካሮላይን መንግሥት (ኤምፓየር) ተመሠረተ ። የፖፖችም ምድራዊ ግዛትና ክብር ከፍ ከፍ እያለ መሄድ ጀመረ ። ክርስትናም እየተስፋፋች መሄድ ጀመረች ።

በስድስተኛው መቶ ዘመን የምዕራቡን (የሮማን) ግዛት በጦር ኃይል በያዘው ቴዎዶሪክ በተባለው አስትሮጎታዊ የአርዮስ ትምህርት ተከታይ ንጉሥ (493—526) መሪነት በምዕራቡ ክፍል ለጥቂት ጊዜ ፖፖችና የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ሲጨቆኑ ከቈዩ በኋላ የቢዛንታይን ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ዩስጢንያኖስ የምዕራቡን ግዛት ክፍል በወረሩት በአስትሮጎቶች መሪ በቶቲላ ላይ ዘምቶ ባደረገው ረጅም ጊዜ የፈጀ ጦርነት (535—562) ወራሪዎችን ድል ነሥቶ የምዕራቡን ክፍል ከምሥራቁ ጋር በአንድነት ሲገዛ ቈየ ። ሆኖም ከእሱ ረፍት በኋላ በ568 ዓ·ም ሎምባርዶች የኢጣልያንን ግማሽ ከቢዛንታይን ነገሥታት በጦርነት አስለቅቀው ያዙ ። ከዚህ በኋላ ኢጣሊያ በሎምባርዶችና በቢዛንታይን ተወካዮች ትገዛ ጀመር ። በዚያን ወቅት የቢዛንታይን መንግሥት ተወካዮች በሥራቸው የሚኖረውን ሕዝብ በሚገባ ማስተዳደር ባለመቻላ



www.ethiopianorthodox.org

ቸው ሕዝቡ የሎምባርዶችን አስጊ የሆነ አደጋ ለመከላከል በየጊዜው የተነሡትን ፖፖች መሪነት ተማጠነ ። በዚሁ መሠረት የሮሙ ፖፕ ቀዳማዊ ጎርጎርዮስ (540—604) በሮም ከተማና በቢዛንታይን መንግሥት ተወካይ ሥር ይተዳደሩ የነበሩት ክፍለ ሀገሮች በየጊዜው በሎምባርዶች ይሰነዘሩባቸው ከነበሩት ወረራዎች ከመሪዎቹ ጋር ባደረጋቸው የሰላም ድርድሮችና በተለያዩ ዘዴዎች ሊያድናቸው ችሏል ።

እንዲሁም በየጊዜው የነበሩት የሲቪል ገዥዎች ለሚያስተዳድሩት ሕዝብ ተገቢውን አመራር መስጠት ተስኖአቸው ስለነበር ፤ ቀዳማዊ ጎርጎርዮስ ከመንፈሳዊው አገልግሎቱ በተጨማሪ የማዕከላዊ ኢጣልያ ገዥ በመሆን አገልግሏል ። በዚህም የፖፖች የወደፊት ምድራዊ (ዓለማዊ) ግዛት መንገድ ጠራጊ ሆነ ።

ከቤተ ክህነቱ መሬት በግብር መልክ የተሰበሰበውንም ገንዘብ በድህነት ቀንበር ሥር ወድቀው ይማቅቁ ለነበሩት ሮማውያን መርጃ እንዲውል አድርጓል ። እንዲሁም ሰባኪዎችን (ሚስዮናውያንን) በመመደብ በአካባቢው የነበሩት አረመኔዎችና አርዮሳውያን ወደ ካቶሊክ እምነት እንዲመለሱ አድርጓል ። ከኢጣልያ ውጭም በ597 ዓ.ም ወደ እንግሊዝ ሀገር ሄደው ክርስትናን እንዲያስተምሩ በአውግስጢኖስ መሪነት አርባ ቤኔዲክታውያን መነኰሳት ልኳል ። እነሱም ዘገየት ብሎ በሀገሪቱ የክርስትና መዲና በሆነችው በካንተርበሪ አካባቢ በትጋት አስተምረው ብዙዎችን ወደ ክርስትና እምነት መልሰዋል ። ኢቴልበርት የተባለውን የኬንት ንጉሥም አጠመቁ ። ባጠቃላይ ክርስትናን በማስፋፋቱ የተቀደሰ ተግባር ላይ ተሰማርተው ዋነኛውን ሚና የተጫወቱት በየገጠሩ በተለያዩ የአሕዛብ ነገዶች መካከል ገዳማትን መሥርተው ይኖሩ የነበሩ ካቶሊካውያን መነኰሳት ናቸው ። ጎርጎርዮስ ሲሲሊ ውስጥ ስድስት ፤ ሮም ውስጥ አንድ በጠቅላላው ሰባት ገዳማት መሥርቷል ።

በ588 ዓ.ም ዮሐንስ የተባለው የቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ በፓትርያርክነቱ ማዕርግ ላይ "የዓለም ፓትርያርክ" የሚለውን የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበላይነት ማዕርግ በመጨመሩ የሮሙ ፖፕ ቀዳማዊ ጎርጎርዮስ ይህንኑ አዲስ ማዕርግ በቀጥታ ተቃውሟል ።

በሰባተኛው መቶ ዘመን በምዕራቡ ክፍል የነበሩት የቢዛንታይን መንግሥት ወኪሎች ሕዝቡን የማስተዳደር ችሎታ ስላልነበራቸው ፤



www.ethiopianorthodox.org

የቢዛንታይን መንግሥት ዜጎች የነበሩት ፖፖች ከመንፈሳዊው ተግባራቸው በተጨማሪ ሕዝቡን ከወራሪዎች በመጠበቅ ይንከባከቡት ነበር ። በዚህ አኳኋን ለመንግሥቱ ከፍ ያለ አገልግሎት ቢያበረክቱም ቅሉ ነገሥታቱ በቤተ ክርስቲያኒቱ የእምነት ጉዳይ ጣልቃ እየገቡ ያውኩ ነበር። ለምሳሌ በ653 ዓ.ም ዳግማዊ ቍንስጣ (642—668) ቀዳማዊ ማርቲን የተባለውን ፖፕ "ለክርስቶስ አንድ ፈቃድ አለው" የሚለውን የመሠረተ ሃይማኖት ትምህርት እንዲቀበል ቢጠይቀው አልቀበልም ስላለ ፤ ቴዎዶሩ ካሊፖስ በተባለው ወኪሉ አስይዞ ቍስጥንጥንያ በመውሰድ በስደት (በግዞት) ተንገላቶ እንዲሞት አድርጓል ።

ቀጥለን እንደምንመለከተው የፍራንኮች ንጉሥ ፔፒን ሎምባርዶችን ድል ካደረገ በኋላ የፖፑን ግዛት መሥርቶ የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ራሷን በማስቻል ከቢዛንታይን መንግሥት ጣልቃ ገብነት ነጻ አወጣት ። የሮም ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ከፔፒንና ከልጁ ከቻርልስ (ከካሮላይን) መንግሥት ጋር በመተባበር የክርስትናን ትምህርት እያስፋፉ ለብዙ ጊዜ (ዘመናት) በሰላም ኖሩ ።

## ለ) ከስምንተኛው መቶ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ እስከ ዐሥራ አንደኛው መቶ ዘመን ድረስ (751—1048) የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስተምረው ከጣዖት አምላኪነት ወደ ክርስትና ከመለሱአቸው ነገሥታት ጋር በመተባበር እንደ ሠሩ

<u>የፍራንኮችና የፖፖች ተባብሮ መሥራት ፡</u>

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በፈረንሳይ ይኖሩ የነበሩ የፍራንኮች ንጉሥ ክሎቪስ (481—511) በ496 ዓ.ም ከሦስት ሺህ ሰዎች ጋር የካቶሊክን ሃይማኖት ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው የተነሡ ፖፖች የፍራንኮችን ነገሥታት ይደግፉ ነበር ። በክሎቪስ የተቋቋመው ጠንካራው የፍራንኮች መንግሥት ለሁለት መቶ ዓመታት ያህል በሱ ዘሮች ሲተዳደር ከቈየ በኋላ በ732 ዓ.ም ሳራካን የተባሉት እስላሞች አውሮጳን ለመውረር ደቡብ ፈረንሳይ ቱርስ በተባለ ቦታ ላይ ያደረጉትን ከባድ ጦርነት ድል በመንሳት ያሸነፈውና ምዕራብ አውሮጳንም በእስላሞች ከመወረር ያዳነ ነገዱ ጀርመናዊ ፤ መኖሪያው ፈረንሳይ (ጎል) የነበረው



www.ethiopianorthodox.org

የቤተ መንግሥቱ ከንቲባ (የግቢ ሚኒስትር) የቻርልስ ማርቴል ልጅ ፔፒን ከአባቱ እረፍት በኋላ በእርሱ እግር በ741 ዓ.ም የቤተ መንግሥቱ ከንቲባ ሆኖ ሲሠራ ቈየ። በዚያን ዘመን የነበሩት ነገሥታት ለይስሙላ በዙፋኑ ላይ ይቀመጡ ነበር እንጂ ፡ ማንኛውንም የመንግሥት ተግባር የሚያከናውነው ሙሉ ሥልጣን የነበረው የቤተ መንግሥቱ ከንቲባ ነበር። ዘካርያስ ከተባለው ፖፕ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለይስሙላ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ የነበረውን ደካማ ንጉሥ በ751 ዓ.ም አስወግዶ መጀመሪያው የካሮላይን ሥርወ መንግሥት (ዝርያ) ንጉሥ ሆነ።

የሎምባርዶች ንጉሥ ኤስቱልፍ ዳግማዊ እስጢፋኖስ ከተባለው ፖፕ ጋር ያደረገውን የሰላም ውል (ስምምነት) አፍርሶ የሮምን ከተማ ለመውረር በከበበበት ወቅት ፖፑ ከቢዛንታይን መንግሥት ወኪሎች ርዳታ ለማግኘት ባለመቻሉ የአልፕስን ተራራ አቋርጦ ተጉዞ በደቡባዊ ፈረንሳይ ክፍለ ግዛት ከፔፒን ጋር ተገናኝቶ የደረሰበትን አደጋ (ችግር) በመግለጽ እርዳታውን ጠየቀ ። ፔፒንም ቀደም ሲል ፖፕ ዘካርያስ ያደረገለትን የሞራል ድጋፍ ውለታ ለመመለስ ከፈረንሳይ ወደ ኢጣልያ ዘምቶ በ755 ዓ.ም ሎምባርዶችን በማዕከላዊ ኢጣልያ በጦር ድል ነሥቶ ቀደም ሲል ታላቁ ቈስጠንጢኖስ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ባደረገው ስጦታ መሠረት በ756 ዓ.ም ከሎምባርዶች የነጠቀውን ግዛት ለፖፑ አስረከበ ። ይህም "ለቅዱስ ጴጥሮስ የተለገሰ ስጦታ" በሚል ስያሜ ይጠራል ። ይህ የፔፒን ስጦታ የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች (ፖፖች) ለተከታዮቹ አንድ ሺህ ዓመታት ያህል በሮም ከተማና በመካከለኛው ኢጣልያ ክፍለ ግዛት ላይ የምድራዊ (የዓለማዊ) ገዥነት መብትን አጐናጽፎ ነጻ መንግሥት እንዲያስተዳድሩ አደረጋቸው ። ይህ ዓይነቱ ስጦታ የተጀመረው ታላቁ ቈስጠንጢኖስ ቀዳማዊ ሲልቬስተር (314–335) ለተባለው ፖፕ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበላይነት ማዕርግ ፡ ሮማንና በአካባቢዋ የሚገኙትን ክፍለ ሀገሮች ወዘተ. እንዲያስተዳድር ፈቅዶለት ነበር ከሚለው ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው ። ሆኖም ይህ "የቈስጠንጢኖስ ስጦታ" በሚል ርእስ የሚተረከው ታሪክ በስምንተኛውና በዘጠንኛው መቶ ዘመን አውሮጳ ውስጥ ገነው በነበሩት በፍራንኮች ነገሥታት የተፈጠረና ከእውነት የራቀ መሆኑ በዐሥራ ስምንተኛው መቶ ዘመን ሊታወቅ ችሏል ።



www.ethiopianorthodox.org

ከፔፒን ዕረፍት በኋላ ሎምባርዶች የፖፑን ግዛት በጦርነት ለመውሰድ ሲሞክሩ ቀዳማዊ ሐድርያን በተባለው ፖፕ የእርዳታ ጥያቄ መሠረት የፔፒን ልጅና አልጋ ወራሽ ታላቁ ቻርልስ በ774 ዓ.ም ድል አድርጎ የቀደመ ግዛታቸውን መለሰላቸው ። ከዚያን ጊዜ አንሥቶ በየጊዜው የተነሡት ፖፖች ከቍስጥንጥንያው ንጉሠ ነገሥት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አቋርጠው ከፍራንኮች ጋር በመተባበር ይሠሩ ጀመር ።

የተከፋፈሉት የኢጣልያ ግዛቶች በንጉሥ ቪክቶሪዮ ኤማኑኤል ጥረት ሲዋሐዱ ፣ የፖፖች ግዛትም በመላ ኢጣሊያ መንግሥት ሥር እስከተቀላቀለበት እስከ 1870 ዓ.ም ድረስ ቈየ ።

በስምንተኛው መቶ ዘመን በተነሣው በታላቁ ቻርልስ (742—814) ዘመነ መንግሥት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና የመንግሥቱ ግንኙነት እየጠበቀ ሄደ ። ቻርልስ የምዕራብ አውሮጳን ሀገሮች ማለት ጀርመንን ፣ ፈረንሳይን ፣ ኔዘርላንድን ፣ ስዊዘርላንድን ፣ አውስትርያን ፣ ሀንጋሪን ፣ በልጅግን ፣ እስጳኝንና ኢጣልያን በኃይል ይዞ ይገዛ ነበር ። ለቤተ ክርስቲያንም ቀናተኛ ፣ ጠባቂና ደጋፊ ነበር ።

ግልሳዊ ልዮን የተባለው ፖፕ በ795 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተመርጦ ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግል ከቈየ በኋላ በ799 ዓ.ም የቅዱስ ማርቆስ በዓል በሚከበርበት ወቅት ፣ ቀደም ሲል ቂም በቀል ይዘውበት የነበሩ ሰዎች ከበዓሉ ሥፍራ በኃይል ይዘው አንገላቱት ። እሱም ከደረሰበት ጉዳት ካገገመ በኋላ ወደ ፍራንኮች ንጉሥ ወደ ቻርልስ ሄዶ ስለተፈጸመ በት ግፍ አስረዳ ። ንጉሡም ጉዳዩን እራሱ ሮም ተገኝቶ እስኪያጣራ ድረስ ፖፑን ከአጀቢዎች ጋር መልሶ ወደ ሮም ላከው ። ቻርልስ በ800 ዓ.ም ሮም ሄዶ የጠቡን (የረብሻውን) መንስኤ ካጣራ በኋላ ፖፑ ያለምንም ጥፋት መበደሉን በቃለ መሐላ ስላረጋገጠ ፣ በተንኮል ተነሣሥተው ያንገላቱት ሰዎች ለሕገ ወጥ ተግባራቸው ተገቢውን ቅጣት ተቀበሉ ።

ንጉሡ እላይ በተጠቀሰው ምክንያት ሮም ሄዶ ሳለ የገና በዓል ዕለት እቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተንበርክኮ በሚጸልይበት ጊዜ ያለምንም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ፖፑ በራሱ ላይ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ደፋለት ። በቤተ ክርስቲያኒቱ ቅጽር ግቢ የነበሩት ካህናትና ምእመናንም "ቻርልስ አውጉስቶስ የሮማ ንጉሠ ነገሥት" እያሉ በዉኽት አስተጋቡ ። ይህ ተግባር የሚገልጸው በኅብረት የሕዝቡን



www.ethiopianorthodox.org

ደጎንነት የሚጠብቁና የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያስፋፉ በአውሮጳ አንድ መንግሥትና አንድ ቤተ ክርስቲያን መኖራቸውን ነበር ። እንዲሁም በአንድነት በአንድ ንጉሠ ነገሥት ይተዳደር የነበረው የምሥራቁና የምዕራቡ የሮማ መንግሥት መለያየቱንና በሁለት ተቀናቃኝ ነገሥታት መገዛት መጀመሩን ይገልጻል ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ቅርጾች እስከ ናፖልዮን ዘመን ድረስ የቈየው በአውሮጳ የተቀደሰው የሮማ ኤምፓየር ተመሠረተ ። ፖፖች ታላቁ ቻርልስን ቀብቶ በማንገሥ የኃያላኑን የሮማውያንንና የቢዛንታይንን ነገሥታት ክብር አጐናጸፍነው ይላሉ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቻርልስ የፖፑ ተግባር ለሕዝቡና ለመንግሥቱ አዘውትሮ መጸለይ ብቻ መሆኑን በይፋ ገልጾ ፤ ቤተ ክርስቲያንን መንከባከብና የክርስትና ትምህርትም በመላ ግዛቱ የሚስፋፋበትን መንገድ መቀየስ ዋና ተግባሩ ሆነ ። እንዲሁም ጳጳሳትንና የአድባራት አለቆችን ይሾም ፤ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ የሚመለከቱ ጉባኤዎችን ይጠራ ነበር ። የቤተ ክህነት ሰዎችም በመንግሥቱ የአስተዳደር ሥራ ላይ ተሠማርተው እንዲሠሩ አድርጓል ። የመንግሥቱንና የቤተ ክህነቱን አስተዳደር አጣምሮ በራሱ መሪነት እንዲካሄድ ቢያደርግም ቅሉ ፤ ከመንግሥቱ አስተዳደር ይልቅ በጣም የሚያተኩረው በቤተ ክህነቱ አስተዳደር መቃናት ላይ ነበር ። የቤተ ክህነቱን የአስተዳደር ሥልጣን ከመንግሥቱ ሥልጣን ጋር ደርቦ በመያዝ በፖፖቹ (በቤተ ክርስቲያኒቱ) ላይ የነበረውን የበላይነት ስለገለጸ በዘመኑ የነበሩት ፖፖች በሁኔታው አልተደሰቱም ነበር ።

ታላቁ ቻርልስና ደጋፊዎቹ የነበሩ ካህናት በ794 ዓ.ም ፍራንክፈርት ውስጥ ጉባኤ አድርገው ቀደም ሲል በ787 ዓ.ም በተደረገችው በሁለተኛዋ የኒቅያ ጉባኤ ለጌታ ፤ ለጻድቃንና ለሰማዕታት ሥዕሎች የአምልኮ ሳይሆን የአክብሮት ስግደት ሊደረግላቸው ይገባል በማለት የተወሰነውን በመቃወም ሐድርያን የተባለውን ፖፕ ይህንኑ የተቃውሞ ውሳኔአቸውን እንዲያጸድቅ ንጉሡ ጠይቆት ነበር ። ፖፑ ግን ሃይማኖት ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ሁሉ መወሰን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተግባር መሆኑንና በሁለተኛዋ የኒቅያ ጉባኤ የተወሰነውም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተስማማችበትና ቀድሞም በቤተ ክርስቲያን ሲፈጸም የነበረ ቀጥተኛ እምነት መሆኑን ገልጾ የፍራንክፈርትን ውሳኔ ውድቅ አደረገው ። በዚህ



www.ethiopianorthodox.org

አኳኋን እምነት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ነገሥታት ጣልቃ ለመግባት ሲሞክሩ አንዳንድ አድርባይ ያልሆኑ ፖፖች በግልጽ ይቃወሙ ነበር ።

በ814 ዓ.ም ታላቁ ቻርልስ ከዐረፈ በኋላ ፖፖች ከወራሾቹ ላይ የቤተ ክህነት አስተዳደር ሥልጣናቸውን (መብታቸውን) አስመልሰው ያዙ ። ለምሳሌ እስጢፋኖስ አምስተኛ (816–817) እና ፓስካል (818–824) የተባሉት ፖፖች ምርጫ የተከናወነው በቤተ ክርስቲያኒቱ የምርጫ ሥርዓት መሠረት ያለ ነገሥታቱ ጣልቃ ገብነት ነበር ። ሆኖም የፖፖቹ ሕጋዊ የምርጫ ሥርዓት አልፎ አልፎ ይጣስ ነበር ። እንዲሁም ከቻርልስ ዕረፍት በኋላ ፖፖች በነገሥታቱ ላይ የነበራቸው (ቤተ ክርስቲያን በቤተ መንግሥት ላይ የነበራት) የበላይነት እየተጠናከረ ሄደ ። ይኸውም ቀዳማዊ ኒኮላ የተባለው ፖፕ (858–867) ንጉሡን ቀብቶ ዘውድ ከጫነለት በኋላ የቤተ ክርስቲያኒቱ ጠባቂ መሆኑን የሚገልጽ ሰይፍ ሰጥቶት ነበር ። ዮሐንስ ስምንተኛ የተባለው ፖፕ (872–882) ደግሞ የሚነግሠውን ልዑል እየመረጠ ዘውድ በመጫን ያነግሥ ነበር ።

ከቻርልስ ዕረፍት በኋላ መንግሥቱን ለሦስት (ጀርመን ፡ ፈረንሳይና ኢጣልያ) ተካፍለው ያስተዳድሩ የነበሩት ሦስቱ የልጅ ልጆቹ እራሳቸው ተስማምተው ሕዝቡን በሰላም በማስተዳደር ፈንታ እርስ በእርሳቸው መዋጋትን የዘወትር ተግባራቸው አድርገው ስለያዙት ሰላም ጠፍቶ ብጥብጥ (ሁከት) ሰፍኖ ነበር ። በዚህ አኳኋን በቻርልስ የተመሠረተው "የተቀደሰው የሮማ ኤምፓየር" በ1806 ዓ.ም በቀዳማዊ ናፖሌዎን (ናፖሌዎን ቦናፓርት) በይፋ እስከተሰረዘበት ጊዜ ድረስ በቴዎሪ ደረጃ ለ1000 ዓመታት ያህል ቢቈይም እንኳ ፡ በተግባር ግን ከሱ ዕረፍት በኋላ በወራሾቹ ያስተዳደርና ዘራፊዎችን (ወራሪዎችን) የመቈጣጠር ችሎታ ማነስ ፡ በተለይም እርስ በእርስ በመዋጋት ወዘተ. ምክንያት ኃያልና ስመጥር የነበረው መንግሥት እየተዳከመ ስለሄደ አውሮጳ ውስጥ በራይን ወንዝ አካባቢ ብቻ ተወስኖ ቀረ ። በጀርመን ግዛት ውስጥ ከሚገኙት ክፍለ ሀገሮች አብዛኞቹ ራሳቸውን በራሳቸው ነጻ እያወጡ እርስ በእርሳቸው መዋጋትን የዕለት ከዕለት ተግባራቸው አድርገው ያዙት ። ሆኖም እነዚሁ ራሳቸውን ነጻ ያወጡ የትናንሽ ሀገር የፊውዳል ባላባቶችና (መሳፍንትና) ጳጳሳት ንጉሠ ነገሥቱን መርጦ የመሾም ፡ ሳያስፈልግም የመሻር መብት እያላቸው ለይስሙላ ያህል በንጉሠ ነገሥቱ ሥር መሆናቸውን ያምኑ ነበር ። ንጉሠ ነገሥቱ በአውሮጳ ክርስቲያኖች



www.ethiopianorthodox.org

ዘንድ በስም ብቻ የበላይነቱ ተቀባይነት ነበረው ። ለምሳሌ በፈረንሳይ ፡ በእንግሊዝና በእስካንዲናቪያን ሀገሮች ንጉሡ ይከበር ነበር ። ትእዛዙ ግን ተቀባይነት አልነበረውም ።

እላይ እንደተመለከትነው የታላቁ ቻርልስ መንግሥት መዳከም በፖፖች ላይ ከባድ ሽክምን አስከተለ ። ይኸውም ቀደም ሲል በሮም ፖፖች በቀዳማዊ ልዮንና በቀዳማዊ ጎርጎርዮስ ዘመን ጽጽስና እንደተፈጸመው ሁሉ በዚህም ዘመን የተነሡት ፖፖች የራሳቸውን ፡ የአብያተ ክርስቲያናትንና የሮማን ሕዝብ ሕይወት ከአደጋ የመከላከል (የመጠበቅ) ኃላፊነት በጫንቃቸው ላይ ወደቀ ። በዚህ መሠረት ልዮን አራተኛ (847–855) የተባለው ፖፕ በዘመኑ ከተነሡት ሳራካን ከተባሉት እስላሞች ለመከላከያ የሚሆን በቫቲካን ከተማ ዙሪያ ታላቅ ቅጽር አስገነባ ። ይህም ስፍራ የልዮን ከተማ ይባላል ። ከዚህም በተጨማሪ መርከበኞችንና እግረኛ ወታደሮችን አዘጋጅቶ በ849 ዓ.ም ሮምን ሊወሩ አስፍስፈው የነበሩትን እስላሞች ከነመርከቦቻቸው እንዲመለሱ አድርጓል ። ዮሐንስ ስምንተኛ (872–882) የተባለው ፖፕ ግን ራሱ አቅም በማጣቱና የሚረዳውም ንጉሥ ባለማግኘቱ የሮማን ከተማ ለማጥፋት በመቃረብ ላይ የነበሩትን እስላሞች በየዓመቱ የተወሰነ ግብር የሚከፍላቸው መሆኑን በስምምነት አረጋግጦ በሰላም እንዲመለሱ አድርጓል ።

ከ880–1000 በነበሩት ዓመታት ኢጣልያ ውስጥ አናርኪ (ሥርዓተ አልበኝነት) ሰፍና ስለነበር ፥ የቅዱስ ጴጥሮስ መንበረ ጵጵስናም ከ880–1050 በነበሩት ዓመታት ውስጥ አልፎ አልፎ በዐሥራ ስምንት ዓመት ዕድሜው የፖፕነት ማዕርግ እንደተሾናጸፈው እንደ ዮሐንስ ዐሥራ ሁለተኛ (955–964) ያሉ መንፈሳዊ ትምህርትና ቅድስና የጐደላቸው ፖፖች ፡ ግብረ ገብነት በተለያቸው የፊውዳል ባላባቶችና እንደ ታላቁ ኦቶ በመሳሰሉ ንጉሥታት እየተመረጡ በመሾማቸውና ሲያስፈልግም በመሻራቸው (በመባረራቸው) የፖፖችን ሥልጣን (ክብር) ዝቅ አድርገውት ነበር። በቤተ ክርስቲያኒቱም ታሪክ ላይ ጥቁር ነጥብ ትተው አልፈዋል ። ይህን ለመሳሰለው ድክመት ሁሉ ጎርጎርዮስ ሰባተኛ በተባለው ፖፕ ተገቢው እርማት መደረጉን ቀጥለን እንመለከታለን ። ሆኖም አንዳንድ ችግሮች ቢከሰቱም ቅሉ ፡ ከ800–1073 በነበሩት ዓመታት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያንን ወደ ኖርዌ ፡ አይስላንድ ፡ ግሪንላንድ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ቦሔምያ ፡ ሀንጋሪ ፡ ፖላንድ ወዘተ. በመላክ የክርስትናን ትምህርት አስፋፍታለች ።

## ሐ) ከ1048–1198 ዓ.ም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተደረገው ተሐድሶ (ለውጥ ፡ መሻሻል)

ከላይ በተጠቀሱት ዓመታት በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተደረገው መሻሻል (ተሐድሶ) በሚገባ የተካሄደው በፖፕ ጎርጎርዮስ ሰባተኛ (በሒልዴብራንድ) ቢሆንም ቅሉ ፡ የተሐድሶው ተግባር የተጀመረው ቀደም ሲል በፖፕ ልዮን ዘጠንኛ(1048—1054) ነበር። ይኸውም በ1048 ዓ.ም ልዮን በንጉሥ ሄንሪ ሣስተኛ (1039–1056) ሲሠየም ሹመቱን እንደ ቀደሙት ፖፖች ከንጉሡ በኋ በመቀበል ፈንታ የሮም ቤተ ክርስቲያን ካህናት ሳያጸድቁት ማዕርገ ክህነት በሌለው ንጉሥ የተሰጠውን ማዕርግ አልቀበልም በማለቱ ፖፖች ከነገሥታቱ ተጽእኖ ሥር ነጻ ለመውጣት ያደረጉት ትግል ተጀመረ ። ሹመቱም በካህናት ተደግፎ ከጸደቀ በኋላ ልዮን በመላ አውሮጳ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት እየዞረ በመጎብኘት ፡ በየክፍለ ሀገሩ የሚገኙትን ካህናት በጉባኤ እየሰበሰበ ከተወያየ በኋላ ቤተ ክርስቲያን የምትሻሻልበትን ማለት ካህናት ከጋብቻ የሚርቁበትን ፡ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችም በጉቦ (በመተያያ) ከመሾም ወዘተ. የሚወገዱበትን ትእዛዝ ሰጠ ። ትእዛዙንም እየተከታተሉ በተግባር ላይ የሚያውሉ የቤተ ክህነት ፍርድ ቤቶችን አቋቋመ ።

ዳግማዊ ኒኮላ (1058–1061) የተባለው ፖፕ በ1059 ዓ.ም በጽሑፍ ለካህናት ባስተላለፈው ትእዛዝ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፖፖች መመረጥ የሚገባቸው በባላባቶች ፡ በነገሥታትና በምእመናን ዘንድ ሐሜትን በሚያስከትሉ የተለያዩ መንገዶች መሆኑ ቀርቶ በካርዲናሎች የሚፈጸም መሆኑን ገለጸ ። ምርጫውም ከ1271 ዓ.ም ጀምሮ የሚፈጸመው ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው ኮንክሌቭ (በዝግ ቤት) ውስጥ ካርዲናሎች ተሰብስበው ከጸለዩ በኋላ በሚያካሂዱት ምርጫ ሁለት ሣስተኛውን ድምጽ ያገኘውን ፖፕ አድርገው በመሾም ነው ። በ1800 ዓ.ም ቬኒስ ከተከናወነው በስተቀር ፡ ከዐሥራ ስድስተኛው መቶ ዘመን ጀምሮ የፖፖች ምርጫ በየጊዜው የተከናወነው ቫቲካን ውስጥ ባለው ሲስቲን በተባለው ሥዕል



www.ethiopianorthodox.org

(ጸሎት) ቤት ውስጥ ነው ።

በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተደረጉት መሻሻሎች (ለውጦች) አብዛኛዎችንና ዋና ዋናዎችን በታላቅ ተጋድሎ በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደረጋቸው ጎርጎርዮስ ሰባተኛ (1073 1085) የተባለው ፖፕ ነበር ። እሱም ቀደም ሲል ስለ ቤተክርስቲያኒቱ እንዲደረጉ የታቀዱት ለውጦች (መሻሻሎች) እንዲሠምሩ ለደከሙት ለፖፕ ልዮንና ኒኮላ አማካሪ ስለነበር ችግሮችን ሁሉ ጠንቅቆ ለማወቅ ዕድል አግኝቶ ነበር ። እንዲሁም ጎርጎርዮስ ቀደም ሲል ካርዲናል ሑምበርት ቤተ ክርስቲያንን ከተጽእኖአቸው ሥር አድርገው የነበሩ ፊውዳል ባላባቶችንና ነገሥታትን በመቃወም ያስተማረውንና የጻፈውን መሠረት በማድረግ የቀደመ ክብሯን እንድታገኝ ትግሉን ጀመረ ። ይኸውም ቤተ ክህነት ከቤተ መንግሥት ተጽእኖ ነጻ እንድትሆን ፤ ምእመናን መንፈሳዊ አባቶቻቸው የሆኑ ካህናትን እንዲያከብሩና እንዲታዘዙ ፤ ካህናትን የሚመለከት ክስ ሁሉ በቤተ ክህነት መንፈሳዊ ፍርድ ቤት እንዲታይ ፤ ካህናት በጉቦና በዘመድ እንዳይሾሙ ፤ በቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ተደንግጎ ሙሉ በሙሉ በተግባር ላይ ያልዋለውን የካህናት ሁሉ በድንግልና መኖር በተግባር እንዲውል አደረገ ። በተለይ ልዑላንና ነገሥታት በፖፖች አማካይነት የምእመናንን ድጋፍ ለማግኘት ፤ የተትረፈረፈውን የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብት ለማጋበስ ይረዳናል (ይጠቅመናል) ብለው ያመኑበትን ካህን ለሊቀ ጳጳስነትና ለፖፕነት እየመረጡ በሹመ ቍጥር የታዛዥነት ምልክት የሆኑትን አርዌ ብርትና (መቋሚያና) ቀለበት በመሸለም የንጉሡ ደጋፊነታቸውን በቃለ መሐላ እንዲያረጋግጡ ያደርጉ ነበር ። ይህም ጳጳሳትና ፖፖች የነገሥታቱ ተቀጣሪዎችና የበታች መሆናቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳይ ነበር ። እንዲሁም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት ካህናት በመላ ስለማያገቡ እንደ ዓለማውያኑ መኳንንት ሹመታችን ለልጆቻችን ይተላለፍልን በማለት ስለማያስቸግሩ ከነሱ ሕልፈት በኋላ ንጉሡ ሹመቱን መንግሥቱን ይደግፍልኛል ብሎ ለሚያምነው ሰው በቀላሉ ለመስጠት ይችላል ። በዚህ ምክንያት ነገሥታት ለጳጳሳት ከመንፈሳዊው ተግባራቸው በተጨማሪ የሀገር አስተዳደር ሥልጣንም ይሰጡ ነበር ። ጎርጎርዮስ መንፈሳዊ ሹመት ማዕርገ ክህነት በሌላቸው ባላባቶችና ነገሥታት ምርጫ መሰጠቱ ሕገ ወጥ ድርጊት ነው በማለት ቀቀዋሚ ሕግ በ1075 ዓ·ም በማውጣቱ ሕጉ ጥቅማቸውን ከነካባቸው



www.ethiopianorthodox.org

መኳንንት ፣ ባላባቶችና ነገሥታት ዘንድ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ከፍ ያለ ተቃውሞ ደርሶባታል ። እንዲሁም በጉቦና በዘመድ ማዕርገ ክህነት የሚሰጡ ጳጳሳት ከመንበረ ጵጵስናቸው እንዲወገዱ ፤ የቤተ ክርስቲያን ልቅና ወዘተ· በጉቦ ያገኙ ሁሉ እንዲሻሩ በ1074 ዓ·ም ሮም ውስጥ በተደረገ ጉባኤ (ሲኖዶስ) አስወሰነ ።

ቤተ ክርስቲያን ለምታካሂደው ተሐድሶ ደንታ ያልነበረው የጀርመን ንጉሥና የተቀደሰው የሮማ ኤምፓየር ንጉሠ ነገሥት ሄንሪ አራተኛ እንደለመደው እንዳሻው የሚያዝዘውን ቴዳላ የተባለውን ካህን መርጦ የሚላን ጳጳስ አድርጎ ለመሾም ሲዘጋጅ ፣ ጎርጎርዮስ በበኩሉ ይህንኑ ምርጫ በመቃወም እራሱ ቀጥተኛና ለቦታው ተገቢ የሆነ ሌላ ካህን መረጠ ። በዚህ ምክንያት በንጉሡና በፖፑ መካከል ከፍ ያለ ግጭት ተፈጠረ ። ንጉሡም ጀርመን የነበሩ ታዛዦቹ የሆኑ ጳጳሳትን በ1076 ዓ·ም· ወርምስ እተባለ ቦታ ሰብስቦ በጉባኤ ፖፑን አስወግዞ ከመንበሩ እንዲወርድ አስወሰነ ። ፖፑም በበኩሉ ወዲያው የዚህኑ አጸፋ ለመመለስ ንጉሡንና በወርምስ ጉባኤ የተካፈሉትን ጳጳሳት አውግዞ ንጉሡ ከዙፋኑ የወረደ ስለሆነ ምእመናን እንዳይታዘዙት ወሰነ ። ቀደም ሲል በንጉሡ ላይ ለማመጽ ተነሣሥተው የነበሩት የሳክሶን ባላባቶች በፖፑ ውግዘት በመጠቀም ሕዝቡን በንጉሡ ላይ አስነሡበት ። ንጉሡም ከዙፋኑ ላለመውረድ የሚረዳ ሌላ አማራጭ ስላጣ ባለቤቱንና ልጁን አስከትሎ በ1077 ዓ·ም በክረምት ወራት የአልፕስን ተራራ አቋርጦ ሰሜን ኢጣልያ ውስጥ ወደሚገኘው ፖፑ ለተወሰነ ጊዜ ወዳረፈበት ካኖሳ ወደተባለው የፖፑ ማረፊያ ሄደ ። እዚያም ሲደርስ በበረዶ ላይ በባዶ እግሩ ቆሞ ፣ ቡትቶ ለብሶ ባደረገው ጥፋት ተጸጽቶ ንስሐ መግባቱን ገለጸ ። ጎርጎርዮስም ከሦስት ቀን በኋላ ተቀብሎ ለሠራው ስሕተት ይቅርታ አደረገለት ። ከዚያም በኋላ ሕዝቡ በሰላም ስለተገዛለት ያለፈ ቂሙን ባለመርሳት ንጉሡ በጎርጎርዮስ ላይ ዘምቶ ከሮም አባረረው ። በሕጋዊ መንገድ የተሾመው ጎርጎርዮስ በሕይወት እያለ ሣልሳዊ ቀሌምንጦስ የተባለውን በሕገ ወጥ መንገድ ፖፕ (ተጻራሪ ፖፕ ፣ አንቲ ፖፕ) አድርጎ በምትኩ ሾመ ።

ጎርጎርዮስ በስደት ላይ ሳለ "ጽድቅን ወድጄ ፣ አመጽን በመጥላቴ ምክንያት በስደት ላይ እንዳለሁ እሞታለሁ" ብሎ ከተናገረ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በ1085 ዓ·ም ዐረፈ ። ምንም እንኳ በስደት ላይ በመንገላታት


www.ethiopianorthodox.org

ቢያርፍም የጎርጎርዮስ የተሐድሶ ሥራዎች ወድቆ (ዝቅ ብሎ) የነበረውን የካህናት ሞራል ከፍ አድርገውታል ። በሥልጣን ላይ ሳለ ያወጣቸው መመሪያዎች ሁሉ ከሱ ቀጥለው በተነሡት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተቀባይነትን አግኝተዋል ።

ጎርጎርዮስ የተጋደለለት ቀጥተኛ ዓላማ ዘግየት ብሎ በሮሙ ፖፕ በዳግማዊ ካሌስቱስ (1119–1124) ጥረት ሙሉ በሙሉ ግቡን መታ ። ይኸውም በ1122 ዓ·ም በዳግማዊ ካሌስቱስና በንጉሥ ሄንሪ አምስተኛ መካከል በተደረገው የስምምነት ውል መሠረት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ካህናት (የአድባራትና የገዳማት አለቆች ፡ ጳጳሳትና ፖፖች) በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግ መሠረት ያለምንም የውጭ ባለሥልጣን ተጽእኖ እየተመረጡ እንዲሾሙ የሚል ነበር ። ይህም ውል "የወርምስ ስምም ነት" በሚል ስም ይታወቃል ። ይኸው ስምምነት ሮም በሚገኘው ላተራን በተባለው የፖፑ ቤተ መንግሥት ውስጥ በ1123 ዓ·ም· በተደረ ገው በመጀመሪያው የላተራን ጉባኤ ጸድቋል ።

እንዲሁም ጎርጎርዮስ ሰባተኛ በምድር የክርስቶስ እንደራሴ የሆኑት የፖፖች ሥልጣን ከልዑላንና ከነገሥታት ሥልጣን በላይ ነው በማለት ያስተማረውን ኢኖሴንት ሦስተኛ (1198 –1216) ፡ ኢኖሴት አራተኛ (1243–1254) ፡ ቦኔፌስ ስምንተኛ (1234 – 1303) ወዘተ· በስፋት ሲያራምዱት ከቈዩ በኋላ ልዮን ዐሥራ ሦስተኛ (1810–1903) የተባለው ፖፕ በ1885 ዓ·ም ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን ተልእኮ በሰላም ማከናወን እንጂ አንዱ ወገን የሌላው የበላይ አለመሆኑን ገልጿል ። ምንም እንኳን እስከ ጎርጎርዮስ ዘመን ድረስ በቴዎሪ ደረጃ ቢቆይም የፖፖች ሥልጣን ከነገሥታቱ ሥልጣን ይበልጣል የሚለው ትምህርት የተጀመ ረው በአውግስጢኖስ ነው ያባላል ።

## መ) በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አነሳሽነት የተካሄ ደው የመስቀል ጦርነት

ዳግማዊ ኡርባን (1088 – 1099) የተባለው በ1088 ዓ·ም ፖፕ ሆኖ ሲመረጥ ጎርጎርዮስ የጀመረውን የተሐድሶ ፈር የሚከተልና የፖፑን የበላይነት የሚያጠናክር መሆኑን ገለጸ ። ቀጥሎም በሕገ ወጥ መንገድ በቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ላይ ተቀምጦ የነበረውን ተጻራሪ ፖፕ (አንቲ



www.ethiopianorthodox.org

ፖፕ) ግልሳዊ ቀሌምንጦስን አስወግዶ ቦታውን ከያዘ በኋላ ማዕርገ ክህነት በጉቦ እንዳይሸጥ ፡ ክህነት የሌላቸው ባላባቶችና ነገሥታት መግሪያ ሊያደርጓቸው የሚፈልጓቸውን ካህናት እየመረጡ በመሾም በየታላላቁ አድባራትና ገዳማት የማስቀመጥ ተግባራቸው እንዲገታ ፡ ሹመት የሚገባቸው ካህናት ሁሉ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲሾሙ ፡ ካህናት ሁሉ በድንግልና እንዲኖሩ ወዘተ ለማድረግ በሰፊው ደከሟል ።

እንዲሁም ይኸው የፈረንሳዩ ተወላጅ ዳግማዊ ኡርባን የተባለው ፖፕ በ1095 ዓ.ም ፈረንሳይ ውስጥ በምትገኝ ክሌርሞንት በተባለች ቦታ በራሱ ሊቀ መንበርነት በተካሄደው ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ወደ ቅድስት ሀገር ለስግደት የሚሄዱ ምእመናን ፍልስጥኤምን ይገዙ በነበሩ ቱርኮች ከሚደርስባቸው ዝርፊያ ፡ መጉላላት ፡ ግድያ ወዘተ ኢየሩሳሌምን ነጻ በማውጣት ለማዳን የሮሙን ፖፕ ዝና ከፍ ያደረገውን የመጀመሪያውን ከምዕራብ አውሮጳ ሀገሮች በተለይ ከፈረንሳይ ፡ ከሎሬንና ከደቡብ ኢጣልያ የተውጣጣውን የመስቀል ጦረኛ ሠራዊት አዘመተ ።

በ11ኛው መቶ ዘመን በሮም ቤተ ክርስቲያን አቀነባባሪነት ተጀምሮ ወደ ስምንት የሚጠጉ ተከታታይ ዘመቻዎችን በማካሄድ ረጅም ጊዜ የፈጀው (1095 – 1272) የመስቀል ጦርነት በሚከተለው አኳኋን ተካሄደ ።

ዳግማዊ ኡርባን በመስቀል ጦርነቱ ላይ የሚካፈሉት ምእመናን የሠሩት ኃጢአት ሁሉ እንደሚሠረይላቸው ፡ በጦርነቱ ላይ የሚወድቁትም የዘለዓለም ሕይወትን እንደሚወርሱ ፡ በጦርነቱም ላይ ጌታ በተለያዩ ታምራት እንደሚረዳቸው ፡ በመንግሥት የሚያስጠይቅ ወንጀል የሠሩም እንደሚማሩ ፡ በዘመቻ ላይ በሚቴዩበት ወቅት ለቤተ ሰቦቻቸውና ለንብረታቸው ተገቢው እንክብካቤና ጥበቃ እንደሚደረግ ወዘተ ቃል በመግባት አረጋገጠላቸው ።

የመጀመሪያው የመስቀል ጦር ዝግጅት ከመጠናቀቁ በፊት ጴጥሮስ የተባለ ባሕታዊ መነኵሴ በየሀገሩ እየዞረ እስላሞችን ተዋግተን በተአምር በማሸነፍ የክርስትና መዲና የሆነችውን ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ነጻ እናወጣለን ተከተሉኝ ብሎ ሲሰብክ ወጣቱ ፡ ሽማግሌው ፡ ገበሬውና ከተሜው አካለ ጉደሎዎች ሳይቀሩ በአጠቃላይ ከ40,000 በላይ የሚሆን የፈረንሳይ ፡ የፍሌምንግስ ፡ የኢጣልያ ፡ የጀርመን ወዘተ ሕዝብ የስንቅና የትጥቅ ዝግጅት ሳያደርግ በጊዜአዊ ስሜት ተፈንቅሎ በመነማማት



www.ethiopianorthodox.org

ተከተለው ። ጴጥሮስም ያንን ያህል ሕዝብ እየመራ ሲጓዝ ግማሹ በራብና በብርድ ሲያልቅ ፡ የተረፈው ደግሞ በቱርክ እስላሞች ተገደለ ። አንዳንድ ከሞት የተረፉም ተማርከው ለባርነት ተወሰዱ ።

ከምዕራብ አውሮጳ ሀገሮች 275.000 የሚሆኑ ጦረኞች (ተዋጊዎች) ከተሰበሰቡ በኋላ በቀኝ ክንዳቸው ከቀይ ጨርቅ የመስቀል ምልክት ተሰፍቶላቸው አስፈላጊው ዝግጅት እንደተጠናቀቀ በጐድፍሬይ ፡ በወንድሙ በባልድዊን ፡ በሬይሞንድ ፡ በቦሔሞንድና በመሳሰሉ ልዑላን የጦር አዝማችነት የመጀመሪያው የመስቀል ጦርነት ዘመቻ (1095 – 1099) በ1096 ዓ·ም ተንቀሳቀሰ ። ፖፑን በመወከል የፑዩ ሊቀ ጳጳስ አቡነ አድሔማር ደ· ሞንቴል አብሮ ዘመተ ። በዘመቻውም ወቅት በአንዳንድ መሪዎች መካከል የዲሲፕሊን ጉድለት በመፈጠሩ ፤ በቅናት እርስ በእርሳቸው በመጣላታቸው ፤ ከዘማቹ ሠራዊትም መካከል አንዳንድ ዱርየዎችና ዘራፊዎች በመኖራቸው ፤ እንዲሁም ከሠራዊቱ ከፊሉ በብርድ በማለቁ ወዘተ· ምክንያቶች ዘመቻው ቢዳከምም ቅሉ ፡ አብዛኞቹ አዝማቾችና ዘማቾች መንፈስ ጠንካሮችና ልበሙሉዎች በመሆናቸው በፊታቸው ያገኙትን የጠላት (የቱርክ) ጦር እየደመሰሱ ወደፊት በመገፋት በ1096 ዓ·ም· ቊስጥንጥንያ ደረሱ ። ጉዞአቸውን በመቀጠል በ1098 ዓ·ም በከባድ ተጋድሎ አንጾኪያን ያዙ ። ወዲያውም እዚያ የነበረውን የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አንሥተው በቦታው ላቲን (ካቶሊካዊ) ፓትርያርክ ሾሙ ። ይህም ሕገ ወጥ ተግባራቸው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባላትን እጅግ አድርጎ አሳዝኖአል ። በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረውን መለያየት እያሰፋውና እያባባሰው ሄዷል ። ከአንጾኪያም ተጉዘው በ1099 ዓ·ም የኢየሩሳሌምን ከተማና ፍልስጥኤምን (ቅድስት ሀገርን) በቊጥጥራቸው ሥር አደረጉ ። ወዲያውም ኢየሩሳሌምንና አካባቢዋን እንደ አንድ የክርስቲያን መንግሥት በመቊጠር ጐድፍሬይን የቅድስት ሀገር ገዥ አድርገው ሾሙት ። ከእሱ ዕረፍት በኋላም ወንድሙ ባልድዊን መጀመሪያው ላቲናዊ የኢየሩሳሌም ንጉሥ ተብሎ ተሾመ ። በኢየሩሳሌም የተቋቋመው የላቲን መንግሥት በዙሪያው ያሰፈሰፉትን እስላሞች የሚቋቋም በቂ ሠራዊት መቅጠሪያ ገንዘብ ስላጣ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር ክብር ሲሉ ( መሥዋዕትነት ለመስጠት ፈቃደኞች የሆኑ በ1118 ዓ·ም ቴምፕላርስ ፡



www.ethiopianorthodox.org

በ1120 ዓ·ም ሆስፒታለርስ የተባሉ ያለደመወዝ የሚሠሩ ሁለት ወታደራዊ የመነኰሳት ድርጅቶች ተመሥርተው የመንግሥቱን ጸጥታ በመጠበቅና ወደ ኢየሩሳሌም ለስግደት የሚሄዱ ምእመናን በሰላም ደርሰው እንዲመለሱ በመርዳት ከፍ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል ። ሆኖም የኢየሩሳሌም የላቲን መንግሥት ከሥሩ ከነበሩት ከፍልስጥኤም ዋና ዋና ከተሞችና ከባሕር በኩል በስተቀር ዙሪያውን በእስላሞች ግዛት የተከበበና ከአውሮጳም የራቀ ስለነበረ ፣ በየጊዜው ከሚደርሱበት ጥቃቶች እየተከላከለ እስከ 1187 ዓ·ም· ድረስ ከቈየ በኋላ እንደገና በቱርኮች መሪ በሳላዲን እጅ ወደቀ ።

እላይ እንደተመለከትነው ክርስቲያኑ የኢየሩሳሌም መንግሥት በዡርዱ ተወላጅ በሳላዲን በሚመራው ጦር ድል ከመመታቱ በፊት የቱርክ ጦር አንዳንድ እንደ ኤዴሳ ፣ ሲዶን ፣ ናዝሬት ወዘተ· ያሉ የቅድስት ሀገር ክፍለ ሀገሮችን መያዙ አውሮጳ ውስጥ ስለተሰማ ሣልሳዊ ኤውጌንዮስ የተባለው ፖፕና ቤርናርድ የተባለው ካህን የአውሮጳ ነገሥታትና ሕዝብ ቅድስት ሀገርን ከጥፋት እንዲያድኗት ስለሰበኩና ስለተማጸኑ ፣ በፈረንሳይ ንጉሥ በሉዊስ ሰባተኛና በጀርመኑ የተቀደሰው የሮማ ኤምፓየር ንጉሠ ነገሥት በሣልሳዊ ኰንራድ የተመራው ሁለተኛው የመስቀል ጦር (1147–1149) በ1147 ዓ·ም ዘምቶ በመንገዱ የገጠመውን የጠላት ጦር ድል እየነሣ ኢየሩሳሌም ከተማ ደረሰ ። በቱርኮች እጅ የወደቁትን ክፍለ ሀገሮች ግን ለማስለቀቅ አልቻለም ። ሆኖም የኢየሩሳሌም መንግሥት የውድቀት ጊዜ እስከ 1187 ዓ·ም ድረስ ሊያራዝም ቻለ ።

በ1187 ዓ·ም የኢየሩሳሌም ከተማ በሳላዲን በሚመራው ጦር ስለወደቀች በኢየሩሳሌም የተቋቋመው የላቲን መንግሥት አከተመ ። ይህ የኢየሩሳሌም ውድቀት በአውሮጳ እንደተሰማ በፖፕ ቀሌምንጦስ ሦስተኛ አነሣሽነት በጀርመኑ የተቀደሰው የሮም ኤምፓየር ንጉሠ ነገሥት በፍሬደሪክ ባርባሮሳ (ቀዳማዊ ፍሬደሪክ) ፣ በፈረንሳዩ ንጉሥ በፊልጶስ አውግስቶስና በእንግሊዙ ንጉሥ በቀዳማዊ ሪቻርድ የተመራው ሦስተኛው የመስቀል ጦር (1189–1192) ወደ ፍልስጥኤም ዘመተ ። በጉዞው ላይ ፍሬደሪክን ውሃ ሙላት ወሰደው ። ሁለቱ ነገሥታት ደግሞ ቀደም ሲል በመካከላቸው ተፈጥሮ የነበረው ቂም አገርሽቶ ስለተጣሉ ፊልጶስ ከነሠራዊቱ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ። ሪቻርድ ግን ከሀገሩ የወጣለትን ዓላማ ብቻውን ከግቡ ለማድረስ ሞክሮ የማይሳካለት መሆኑን በመገንዘብ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኖች ለስግደት ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ በእስላሞች ሳይጉላሉ አምልኮታቸውን በሰላም እንዲፈጽሙ የሚያስችል ውል ከሳላዲን ጋር ተዋውሎ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ።

ለመጀመሪያ ጊዜ "የክርስቶስ እንደራሴ" የሚል የክብር ስም በተሰጠው በሮሙ ፖፕ በሣልሳዊ ኢኖሴንት (1160-1216) የተዘጋጀው አራተኛው የመስቀል ጦር (1201-1204) በመጀመሪያ ግብጽን ይዞ ከሰፈረ በኋላ ከዚያ እየተነሣ በመዋጋት ፍልስጥኤምን እንዲይዝ ታቅዶ ነበር ። ነገር ግን የታቀደለትን ግብ ካለመምታቱም ሌላ በቢዛንታይን መንግሥትና በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አስከት ሏል። ይኸውም የመስቀል ጦረኞች ዘመቻውን በግብጽ አድርገው ወደ ቅድስት ሀገር በመቀጠል ፈንታ የቬኒስ ነጋዴዎች በንግድ ሥራ ተቀናቃኞቻቸው የነበሩት ነጋዴዎች የሚኖሩባትን ዛሬ የተባለችውን የክርስቲያኖች ከተማና ቊስጥንጥንያን ካላወደማችሁ በማለት መርከብ አናቀርብላችሁም አሉን በሚል ሽፋን (ሰበብ) መጀመሪያ ዛራን አውድ መው ያገኙትን ሁሉ ዘረፉ ። ቀጥሎም የክርስቲያን መንግሥት የነበረች ውን ቊስጥንጥንያን በ1203 ዓ.ም ወግተው ከያዙና ከዘረፉ በኋላ በ1204 ዓ.ም የራሳቸውን የላቲን መንግሥትና ፓትርያርክ አቋቋሙ ። ኢኖሴንት ሣልሰኛ የተባለው ፖፕም በግፍ ቊስጥንጥንያ የተቋቋመውን የላቲን መንግሥት የካቶሊክንና የኦርቶዶክስን አብያተ ክርስቲያናት አንድ ለማድረግ ይረዳል በሚል አጉል ምኞት ደግፎት ነበር ። ሆኖም በኒቅያ አካባቢ መሽጉ ይኖር በነበረው በንጉሥ ሚካኤል ስምንተኛ በተመራው በቢዛንታይን ጦር በ1261 ዓ.ም ድል ሆነው እስከተባረሩበት ጊዜ ድረስ በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተጽእኖ በማድረግና ሀገሪቱንም በመበዝበዝ ስላዳከሚት ቱየት ብሎ በ1453 ዓ.ም የኦቶማን ቱርኮች በቀላሉ እንዲይዟት መንገድ አመቻችላቸው ። ይኸውም ድርጊት በግሪክ ኦርቶዶክስና በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በ1054 ዓ.ም የተደረገውን መለያየት ይበልጠውን አባባሰው ። በአጠቃላይ አራተኛው የመስቀል ጦርነት ዓላማውን የሳተ ፡ የዝርፊያና የጥፋት ጦርነት ነበር ።

የመስቀል ጦረኞችን ያዘምቱ ከነበሩት መሪዎች የጥቂቶቹን አስተሳ ሰብ ከንቱነት የሚገልጸው፡ ቀደም ሲል ጴጥሮስ በተባለው ባሕታዊ ስብከት ያለቅድሚያ ዝግጅት በስሜት በዘመተው ሕዝብ ላይ እንደተፈጸ መው እልቂት የመሰለ ፡ ውጤቱ በጣም አሳዛኝ የነበረው ደግሞ በ1212


www.ethiopianorthodox.org

ዓ·ም የተደረገው እድሚእቸው ከዐሥራ ሁለት ዓመት በታች የሆነ የታዳጊ ሕፃናት የመስቀል ጦርነት የተባለው ነው ። የመስቀል ጦርነቱ ግቡን ሊመታ ያልቻለበት ምክንያት ምናልባት መጣሪያ በታጠቁ ዘማቾች በንጹሐን ስምት ላይ የተፈጸመው ዝርፊያና ግድያ እግዚአብሔርን አስቀይሞት ይሆናል ። ስለዚህ ልበ ንጹሐን የሆኑ ሕፃናት ቢዘምቱ ቅድስት ሀገርን በአምላክ እርዳታ በተአምር ነጻ ያወጣሉ በሚል እምነት ከፈረንሳይና ከጀርመን በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ወንድና ሴት ታዳጊ ሕፃናት እስጢፋኖስ በተባለው ፈረንሳዊ የበግ እረኛና በጀርመናዊው የዐሥር ዓመት ሕፃን በኒኮላ መሪነት ዘመቻው ተጀመረ ። ከዘመቱት ሕፃናት አብዛኞቹ በየቦታው ተበታትነው የትም ባዝነው ሲያልቁ ፤ ከፊሉን ደግሞ ባለመርከቦች ወደ እስክንድርያና አልጀርያ ወስደው ሸጧቸው ይባላል ።

የጀርመን ንጉሥ ዳግማዊ ፍሬደሪክ የመስቀል ጦረኞችን ወደ ፍልስጥኤም በማዝመት አምስተኛው የመስቀል ጦርነት በ1229 ዓ·ም· ተደረገ ። ፍሬደሪክ ቅድስት ሀገርን ከያዙት እስላሞች ጋር በሰላማዊ መንገድ ድርድር በማድረግ ኢየሩሳሌም ፤ ጃፋ ፤ ቤተልሔም ፤ ፤ ናዝሬትና የባሕር በሩ ለክርስቲያኖች እንዲመለሱ አደረገ ። ፍሬደሪክ ቀደም ሲል ጎርጎርዮስ ዘጠንኛ በተባለው ፖፕ ተወግዞ ስለነበር ቀብቶ የሚያነግሠው ጳጳስ በማጣቱ እራሱ በራሱ ላይ ዘውድ ደፍቶ የኢየሩሳሌም ንጉሥ ተባለ። ይህም "የኢየሩሳሌም ንጉሥ" የሚለው ማዕርግ ከሱ ቀጥለው የተነሡ የጀርመን ነገሥታት ፤ ኋላም የአውስትርያ ነገሥታት እስከ 1835 ዓ·ም ድረስ ሲጠሩበት ኖሩ ። ሆኖም በፖፑና በንጉሡ ጠብ ምክንያት የመስቀል ጦርነቱ ስለከሸፈ በ1244 ዓ·ም ኢየሩሳሌም እንደገና በእስላሞች እጅ ወደቀች ።

የመስቀል ጦርነቱ ካከተመ ከብዙ ዘመን በኋላ በጄኔራል አለንባይ የተመራው የእንግሊዝ ጦር በ1917 ዓ·ም ቅድስት ሀገርን ከቱርኮች አስለቅቆ እስከያዘበት ጊዜ ድረስ በእስላሞች ሥር ስትተዳደር ቈየች ። ቀጥሎም በ1948 ዓ·ም በዴቪድ ቤንጎርዮን የሚመራ የእስራኤል ሪፑብሊክ ተመሠረተ ።

የፈረንሳይ ንጉሥ ልዊስ ዘጠንኛ ስድስተኛውን የመስቀል ጦርነት (1248–1254) በመምራት በግብጽ በኩል ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ ዳሚኤታ የተባለችውን የግብጽ የባሕር ወደብ ይዞ በመዋጋት ላይ ሳለ



www.ethiopianorthodox.org

ድል ሆኖ በእስላሞች ተማረከ ። በብዙ ገንዘብ ክፍያ ነጻ ከወጣ በኋላ ወደ ፍልስጥኤም ሄዶ እዚያ ቈየ ። ኋላም በ1254 ዓ·ም ወደ ፈረንሳይ ተመለሰ።

ሰባተኛው የመስቀል ጦር (1270—1272) የተመራው በፈረንሳዊው በቅዱስ ልዊስና በእንግሊዛዊው ልዑል ኤድዋርድ ነበር ። ዘማቾችም በአፍሪካ በኩል አድርገው ሲጓዙ ቅዱስ ልዊስ በኮሌራ በሽታ ቱኒስ ውስጥ ዐረፈ ። ልዑል ኤድዋርድም ለመንገሥ ወደ እንግሊዝ ሀገር ተመለሰ ። በዚህ አኳኋን የተጀመረው ዘመቻ ፍሬ አልባ ሆኖ ቀረ ።

በዚያን ዘመን እስያንና ማዕከላዊ አውሮጳን የወረሩት የጌንጊስ ካሐን (1162—1227) ተከታዮች ሞንጐላውያን እስላሞችን እየደመሰሱ በ1258 ዓ·ም ባግዳድን ፣ በ1260 ዓ·ም ሶርያን ወዘተ· ይዘው ነበር ። እነሱም የንስጥሮስ ተከታዮች (ክርስቲያኖች) በነበሩ ሞንጐላውያን መነኰሳት አማካይነት የአውሮጳ ክርስቲየኖች በጦር ጓደኝነት እንዲተባበሩአቸውና እስላሞችን እንዲደመስሱ ቢጠይቋቸው ፣ አውሮጳውያን ቸል በማለታቸው ምክንያት የእስላሞች ኃይል ቀስ በቀስ እየተጠናከረ ስለሄደ በ1291 ዓ·ም ፍልስጥኤምን (ቅድስት ሀገርን) በጦር ኃይል እንደገና ሙሉ በሙሉ ያዙ ።

እላይ ከተጠቀሱት በስተቀር ታሪካቸው ጐልቶ ያልተነገረላቸው ትናንሽ የመስቀል ጦርነቶች ተካሂደዋል ። በተለይ ከ1272 ዓ·ም ወዲህ በቤተ ክርስቲያን መሪነት የተደረጉ ጥቃቅን ጦርነቶች ፣ በክርስቲያን ሀገሮች ውስጥ ቀጥተኛው እምነት ተከታዮች ነን ባዮች እምነታቸው የተዛባውን (ከሐዲዎችን) ለመቅጣት ያደረጉት ጊዜአዊ ግጭት ሁሉ "የመስቀል ጦርነት" በሚል ስም ይጠራል ።

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በየጊዜው በተደረጉት የመስቀል ጦርነቶች ቅድስት ሀገርን ነጻ ለማውጣት አልተቻለም ። ዘመቻዎች ግባቸውን እንዳይመቱ ከአደረጉት ምክንያቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

1) ሠራዊቱን እንዲያዘምቱ ተመርጠው የተመደቡት ልዑላን ፣ ነገሥታትና ባላባቶች በኅብረትና በቀና መንፈስ ተዋጊውን ሕዝብ እያበረታቱ በጦርነቱ ቦታ ላይ በማዋል ፈንታ የአንዱ መሪ ዝና ከሌላው እንዳይበልጥ በመቀናናትና በመሳሰሉት ምክንያቶች እርስ በርሳቸው በመጣላታቸው ፣



www.ethiopianorthodox.org

2) ቅድስት ሀገር ከአውሮጳ የራቀች በመሆኗ በቀላሉ ግንኙነት በማድረግ ማንኛውንም እርዳታ በተፈለገበት ጊዜ ለማቅረብ ባለመቻሉ ፡

3) የመስቀል ጦረኞች ነጻ ሊያወጡት የሄዱለትን ክርስቲያን ሕዝብ በመመዝበራቸውና ምሽጐችን እንደ ባሪያ ሌት ከቀን በማሠራታቸው ፡

4) እስላሞች ከሚጭኑበት ሸክም ይልቅ ክርስቲያን ነኝ ባዩ መንግሥት የጫነበት ሸክም አመዝኖ (በልጦ) ስለነበር ወዘተ· ሕዝቡ ጠልቶአቸው ነበር ።

የመስቀል ጦረኞች ቅድስት ሀገርን ነጻ አውጥተው ቋሚ የሆነ የክርስቲያን መንግሥት ለማቋቋም ባይችሉም ቅሉ ፡ ለአውሮጳና ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን አስገኝተዋል ። ይኸውም ቀደም ሲል በሰባተኛው መቶ ዘመን ፍልስጥኤምን የያዙ ዓረቦች ለዘብተኞች ስለነበሩ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም የሚሄዱት ምእመናን በሰላም ደርሰው ይመለሱ ነበር ። ነገር ግን ፋናቲክነት ያጠቃቸው ቱርኮች ቅድስት ሀገርን በ1071 ዓ·ም በጦር ኃይል ከያዙ በኋላ ለስግደት የሚሄዱትን ክርስቲያኖች መዝረፍ ፡ ማጉላላትና መግደልን ሥራዬ ብለው ተያይዘውት ስነበር በመስቀል ጦርነቱ ምክንያት በተደረገው ስምምነት መሠረት ኢየሩሳሌምን ለመሳለም የሚሄዱ ምዕመናን ሁሉ በሰላም ደርሶ የመመለስ መብታቸው በቱርክ መንግሥት ተጠበቀላቸው ። ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱት ምእመናን በሚለግሡት ገንዘብ ምክንያት እዚያ የነበሩት ካህናትና ምእመናን ኑሮ እየተሻሻለ ሄደ ። በጦርነቱ ምክንያት የአውሮጳ ነገሥታት የእስላሞችን ኃይል ከባድነት ጠንቅቀው ስለተረዱ በሀገሮቻቸው ላይ በድንገት ሊሰነዘሩ ከሚችሉት አደገኛ የእስላም ጥቃት ለመከላከል ተዘጋጁ ። ለምሳሌ በ1492 ዓ·ም እስጳኞች እስላሞችን ከሀገራቸው ወግተው አባረሩ ። ፖላንድና አውስትርያም በ1683 ዓ·ም ቪየና ደርሶ የነበረውን የቱርክ ጦር በጀግንነት ተዋግተው ድል ነሥተው መለሱት ። ይህም በኋላ ቀ መሥዋዕትነት የተገኘው ድል የቱርክን መንግሥት እየተዳከመ መሄድ አበሰረ ። እንዲሁም በመስቀል ጦርነቱ ምክንያት የብዙ መንግሥታት መሪዎች ፡ የጦር አዛዦችና ተራው ዘማች በቅርብ ተገናኝቶ ለመተዋወቅና ለወደፊትም በማንኛውም ጉዳይ እየተረዳዱ ለመኖር እንዲችሉ አደረገ (ረዳ) ። በተጨማሪም በምሥራቅና በምዕራብ ሀገሮች መካከል የንግድ ሥራ እየተስፋፋ ስለሄደ ብዙዎቹ በለጸጉ ። እንዲሁም የመስቀል ጦረኞች


www.ethiopianorthodox.org

ከዓረቦች ጋር ባደረጉት የባህል ግንኙነት ዓረቦች ከግሪኮች ያገኙትን ዕውቀት ሊቀስሙ ቻሉ ። በዚህም ሳቢያ አውሮጳ ውስጥ የትምህርት (የዕውቀት) ፍላጐት መስፋፋት ጀመረ ።

የመስቀል ጦርነቱ እንዲካሄድ ሕዝቡን በመቀስቀስ የጀመሩት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለሆኑ ፖፖች በነገሥታት ፥ በልዑላንና በመሳፍንት ላይ ከፍ ያለ ሥልጣን አገኙ። ቤተ ክርስቲያን በግዥና በስጦታ ብዙ መሬትና ሀብት አፈራች ። ሆኖም ቤተ ክርስቲያን የተቀዳጀችውን ከፍተኛ ሥልጣንና ከልክ ያለፈ ሀብት በተገቢው ቦታና መንገድ ላይ በማዋል ስላልተጠቀመችበት ፥ በምእመናንም ዘንድ ጥላቻን ስላተረፈች ቀስ በቀስ በማርቲን ሉተር ፍጻሜ ያገኘው የፕሮቴስታንቶች መለየት ተከሰተ ።

እላይ ከተጠቀሰው (ከተመለከትነው) በተጨማሪ የፖፖችን ሥልጣንና ኃይል ከአጠናከሩአቸው ምክንያቶች አንዱ መናፍቃንን መክሮና አስተምሮ እሽ ቢሉ በንስሐ ለመመለስ ፤ አንመለስም ያሉትን ደግሞ በቅጣት ለመደምሰስ ታስቦ በዳግማዊ ፍሬደሪክ ትእዛዝና ጎርጎርዮስ ዘጠንኛ በተባለው ፖፕ(1227—1241) ትብብር የተመሠረተው ኢንኩዚሽን የተባለው የቤተ ክርስቲያን ፍርድ ቤት ነበር ። ይኸውም ፍርድ ቤት የተጀመረው ሕዝቡን በሰላም ለመንግሥት ሊያስገዛ ይችላል ፥ ለቤተ ክርስቲያንም መናፍቃንን አስተምሮ በመመለስ ፥ የማይመለሱትንም በመደምሰስ ፥ ምእመናንን በእምነት አንድ አድርጎ ያኖራል ተብሎ ተገምቶ ነበር ።

ይኸው ፍርድ ቤት በ1232 ዓ·ም ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው በፈረንሳይ ደቡባዊ ክፍልና በሰሜናዊ ኢጣልያ ክፍል የተነሡትን አልቢጀንሲያን የተባሉትን መናፍቃን ለመደምሰስ ታስቦ ነበር ። ማንኛውም መናፍቅ ሆኖ የተገኘ ሰው በንስሐ የማይመለስ ሲሆን ፥ ለዚሁ ተግባር ከዶሚኒካን ፥ ከፍራንሲስካን መነኰሳትና ከምእመናን ተመርጠው የተሰየሙት ዳኞችና ጳጳሳት ስለሰውየው መናፍቅነት የቀረቡትን ማስረጃዎች አጣርተው ከተስማሙ በኋላ ተገቢውን ቅጣት እንዲቀበል ወደ ሲቪል አስተዳዳሪዎች ይልኩት ነበር ። ከ1252 ዓ·ም ጀምሮ ግን መናፍቅነቱ በፍርድ ቤቱ ተረጋግጦ በንስሐ አልመለስም ሲል የግርፋት ፥ ሀብቱን የመወረስ ወይም የሞት ቅጣት እንዲፈጸምበት ኢኖሴንት አራተኛ በተባለው ፖፕ ተወሰነ ። በእሳት ተቃጥሎ ወዘተ· እንዲሞት



www.ethiopianorthodox.org

የተፈረደበት መናፍቅ ቅጣቱ የሚጸናበት ወደ ሲቪል አስተዳዳሪዎች ከተላለፈ በኋላ ነበር ።

በእስፓኝ ንጉሥ በፌርዲናንድ አምስተኛና በባለቤቱ በኢዛቤላ ፣ በፖፑም ፈቃድ በ1479 ዓ·ም የተቋቋመው የእስጳኝ ኢንኩዚሽን በመባል የታወቀው መጀመሪያ ያተኰረው በአይሁድና ሙርስ ከተባሉት እስላሞች መካከል በግዳጅ ክርስትናን ተቀብለው በነበሩት ማራኖስና ማሪስኮስ በተባሉት ነገዶች ላይ የጠላት ሰላዮች ናችሁ በመባል ሲሆን ፣ ቈየት ብሎ ደግሞ በፕሮቴስታንቶች ላይ በስፋት ተካሄደ ። ይኸውም ከሁለት ሺህ ሰዎች በላይ በሞት ቅጣት ያስፈጀው ፍርድ ቤት (ኢንኩዚሽን) በ1808 ዓ·ም በጆሴፍ ቦናፓርት ታግዶ ከቈየ በኋላ ፣ በ1814 ዓ·ም የተለመደ የጭካኔ ተግባሩን ቀጥሎ ፥ በ1820 ዓ·ም ለመጨረሻ ጊዜ እንዲቆም ተደረገ ።

## ሠ) የፖፖች ፈላጭ ቆራጭነት አገዛዝ ውድቀት (1303—1447)

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ከፖፕ ጎርጎርዮስ ሰባተኛ (1073—1085) እስከ ፖፕ ቦኔፌስ ስምንተኛ (1234—1303) ድረስ የሮም ፖፖች በአብያተ ክርስቲያናትና በነገሥታት ዘንድ ተሰሚነትንና የበላይነትን አትርፈው ነበር ። ሆኖም በኔፌስ ስምንተኛ የሮም ፖፕ ከነበረበት ዘመን ጀምሮ በአውሮጳ መንግሥታት ዘንድ የብሔርተኝነት (ጠንካራ ብሔራዊ መንግሥት የማቋቋም) ስሜት እየጸና ሄደ ። ስለዚህ የየሀገሩ ነገሥታትና ሕዝብ ለቤተ ክርስቲያን የነበራቸው ታማኝነትና ፍጹም ታዛዥነት እየቀዘቀዘ በመሄዱና በምትኩ በነገሥታት አመራር ሥር አንድነታቸውን እያጸኑ ስለሄዱ ገኖ የነበረው የፖፖች ሥልጣን እየተዳከመ ሄደ ።

ቦኔፌስ ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ፖፖች ነገሥታት ምክሩን እንዲቀበሉ ጥብቅ ትእዛዝ ቢሰጥም ቅሉ ፣ ሁሉም ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት የሚቀበለው ጠፋ ። ለምሳሌ የእንግሊዝ ንጉሥ ቀዳማዊ ኤድዋርድ ከካህናትና ከቤተ ክርስቲያን ሀብት ከፍተኛ ታክስ (ግብር) እንዳይሰበስብ ፖፑ ከልክሎት ነበር ። ንጉሡ ግን ትእዛዙን ከጉዳይ ሳይጽፍ ለመንግሥቱ ማስተዳደሪያ ወጭ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከካህናትና ከቤተ ክርስቲያን ሀብት በታክስ መልክ መሰብሰቡን ቀጠለ ። ፖፑም የትእዛዙን ተደማጭነት ማጣት ተገንዝቦ ንጉሡ የሚያስፈልገውን ያህል እንዲሰበስብ በመፍቀድ ተስማማ ። በጣም የከፋው ጠብ (ግጭት) የተካሄደው ግን



www.ethiopianorthodox.org

በፖፑና ከፍተኛ የብሔርተኝነትና የሥልጣን ጥም ባደረበት በፈረንሳይ ንጉሥ በፊልጶስ አራተኛ መካከል ነበር ። በፈረንሳይና በእንግሊዝ መካከል ይካሄድ የነበረውን ጦርነት ለማቆም እንዲቻል በማሰብ ፖፑ ያለሱ የቅድሚያ ስምምነት ከካህናትና ከቤተ ክርስቲያን ሀብት ላይ ከፍ ያለ ታክስ እንዳይሰበስብ ፊልጶስን ከለከለው ። ንጉሡም ወዲያው ፖፑ በመንግሥት ሥልጣን ጣልቃ የመግባት መብትና ሥልጣን እንደሌለው ገልጾ በየጊዜው ከፈረንሳይ አብያተ ክርስቲያናት ለፖፑ ወደ ሮም የሚጉርፈውን ወርቅና የተለያዩ የከበሩ ዕቃዎችን አገደ ። ፖፑም በዚህ በመደናገጥ ንጉሡ በቸገረው ጊዜ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ያህል ያለምንም የቅድሚያ ፈቃድና ጥያቄ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብት ላይ ግብር እንዲሰበስብ ስለፈቀደለት ለጥቂት ጊዜ ሰላም ሰፍኖ ቈየ ።

በ1301 ዓ·ም ፊልጶስ የፖፑ ተወካይ የነበረውን አቡነ ቤርናርድን አስሮ ጉዳዩ በቅድሚያ በቤተ ክህነቱ ፍርድ ቤት መታየት ሲገባው ለዓለማዊው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በማድረጉ ንጉሡ ሮም ሄዶ ፍርዱን እንዲቀበል ቦኒፋስ አዘዘ። ንጉሡም ትእዛዙን በመቃወሙ ፖፑ በንጉሡ ላይ የሚያስተላልፈውን ግዝት በማዘጋጀት ላይ ሳለ ፣ ንጉሡ ኖጋሬት በተባለው የጦር አዛዥ የሚመሩ ወታደሮች በድንገት ይዘው እንዲያስሩት ወደ ኢጣልያ ልኮ ፖፑ አናግኒ እተባለ ቦታ ሳለ አስያዘው ። ምንም እንኳ የኢጣልያ ወታደሮች ከሦስት ቀን በኋላ ቢያስጥሉትም የሰማንያ አምስት ዓመቱ ሽማግሌ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ከአንድ ወር በኋላ በ1303 ዓ·ም ዐረፈ ። ወዲያው የፈረንሳዩን ተወላጅ ፖፕ ቀሌምንጦስ አምስተኛን በ1305 ዓ·ም ሊዮን ውስጥ አስመርጦና አሹሞ በቍጥጥሩ ሥር በማድረግ የፈረንሳይን ጥቅም እንዲያስጠብቅ ፈረንሳይ ውስጥ ወደምትገኝ አቪኞን ወደተባለች ከተማ ተዛውሮ የፖፑን መንበር እዚያው መሥርቶ እንዲኖር አደረገ ።

በዚህ አኳኋን ፖፕ ቦኒፋስ በፊልጶስ በመሸነፉ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሠራ አንደኛው ክፍለ ዘመን ጀምራ የተያያዘችው የተሐድሶ ፕሮግራም (ተግባር) ስለተደናቀፈ የድቀቷ ዘመን ተጀመረ ።

ረ) ፖፖች ከሮም ውጭ አቪኞን ውስጥ ለሰባ ዓመታት ያህል የተቀመጡበት ጊዜ (1305—1378) ። ወዲያውም


www.ethiopianorthodox.org

## በተከታታይ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አርባ ዓመት ያህል የፈጀው መለያየት (1378—1417)

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ከ1305 ዓ·ም ጀምሮ በፈረንሳይ መንግሥት ጥያቄ (ትእዛዝ) የፈረንሳዩ ተወላጅ ፖፕ ቀሌምንጦስ አምስተኛ (1305—1314) ለፖፕነት የሚያስፈልገው የምርጫና የጸሎተ ሢመቱ ሥነ ሥርዓት ሊዮን ውስጥ ከተፈጸመለት በኋላ ሮም ሄዶ በመቀመጥ ፈንታ በፈረንሳይ ንጉሥ ተጽእኖ በ1305 ዓ·ም በደቡብ ፈረንሳይ ወደምትገኝ አቪኞን ወደምትባል ከተማ ተዛውሮ በጊዜያዊነት እንዲኖር ተደረገ ። እንዲሁም ኢጣልያ ውስጥ በፖለቲካ ተከፋፍለው ለየብቻ ይኖሩ በነበሩት ክፍለ ሀገሮች መካከል የተነሣው ብጥብጥ (የእርስ በእርስ ጦርነት) ወደ ሮም ለመመለስ ስላላስቻለ የፖፑ መንበር በቋሚነት አቪኞን ውስጥ ተቋቋመ ። የአቪኞን ፖፖች የኢጣልያ ጸጥታ እስኪረጋጋ ድረስ የምንቈየው በጊዜአዊነት መልክ ነው በማለት ቢያስቡም ቅሉ ጸጥታው ስላልተረጋጋ በ1348 ዓ·ም በቀሌምንጦስ ስድስተኛ የአቪኞን ከተማ ተገዝቶ የፖፖች ቤተ መንግሥት ተሠራ ። ከተማውም የፖፖች ግዛት ሆነ ። ሰባ ዓመታት ያህል የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፖፖች በፈረንሳይ ነገሥታት ተጽእኖ ሥር በሚካሄድ ምርጫ እየተመረጡ በመሾማቸው የመንግሥቱ ፍጹም ታዛዥና መጠቀሚያ መሣሪያዎች ሆነው ቈዩ ። በዚህ አኳኋን ቀደም ሲል በአውሮጳ ነገሥታት ላይ የነበራቸው የበላይነት ሥልጣን ስለተቋረጠ ክብራቸው ዝቅ እያለ ሄደ ። ታሪክ ጸሐፊዎች ይህንን ጊዜ አይሁድ በናቡከደነፆር ተማርከው ወደ ባቢሎን ተወስደው ሰባ ዓመት በሥቃይ ከቈዩበት ጋር በማነጻጸር "የቤተ ክርስቲያን የባቢሎን ምርኮ ዘመን" ይሉታል (2 ነገ· 24፡14 - 16 ፡ 25 ፡ 11፡ዕዝ· 2፡ ነሀ· 1፡ ኤር· 25፡11) ።

ፊልጶስ አራተኛ የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን ሲጋፋና ሀብቷን ሲመዘብር ፖፕ ቀሌምንጦስ አምስተኛ ድርጊቱ ሕገ ወጥ መሆኑን አስረድቶና መክሮ ከስሕተቱ እንዲታረም በማድረግ ፈንታ የንጉሡ ፍጹም ታዛዥ ሆኖ መኖርን መርጦ ነበር ። በተጨማሪም ከንጉሡ ጋር በመመሳጠር የፈረንሣይ ዜጋ የሆኑ ካርዲናሎችን በብዛት በመሾም በየጊዜው በድምጽ ብልጫ የሚመረጠው ፖፕ የፈረንሣይ ዜጋ እንዲሆን አድርጓል ። ለምሳሌ በሰባቱ የአቪኞን ፖፖች ከተሾሙት 134 ካርዲና



www.ethiopianorthodox.org

ሎች 113ቱ የፈረንሳይ ተወላጆች ነበሩ ።

በፈረንሳይና በእንግሊዝ መንግሥታት መካከል መቶ ዓመት በፈጀው ጦርነት ወቅት ፖፖች የሁለቱም ወገኖች መንፈሳዊ አባት እንደመሆናቸው ገለልተኛ ሆነው ሁለቱን መንግሥታት ገላግሎና አስታርቆ ሰላምን በማስፈን ፈንታ ፤ ለትውልድ ሀገራቸው በማድላትና በአድርባይነት ስሜት እየተመሩ ከፈረንሳይ መንግሥት ጐን በመቆማቸው በእንግሊዝ መንግሥትና ሕዝብ ዘንድ ጥላቻን አትርፈዋል ። እንዲሁም የሥልጣን ሱስ ለተጸናወተው ለፈረንሳይ መንግሥት መሣሪያና ጥቅም ጠባቂ በመሆን የጀርመንን መንግሥት በመቃወማቸው ከጀርመን መንግሥትና ሕዝብም ጥላቻን አትርፈዋል ። ለምሳሌ ፖፕ ዮሐንስ ሃያ ሁለተኛ (1314—1347) ሉዊስ ዘባቫርያን የተባለውን የጀርመን ንጉሥ በ1323 ዓ·ም በቂ ባልሆነ ምክንያት ከሥልጣኑ እንዲወርድ አድርጓል ። ንጉሡም የፖፑን ውሳኔ (ፍርድ) አሜን ብሎ በመቀበል ፈንታ ለቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ጉባኤ ይግባኝ በማለት ዮሐንስን ከሰሰ። ከፈረንሳይ ወደ ጀርመን ተሰደው ይኖሩ የነበሩት የፖፑ ጠላቶችም ከንጉሡ ጋር በማበር ፖፑን ከሰሱ ። ከከሳሾችም መካከል የፓሪስ ዩኒቨርሲቲ ሊቃውንት የነበሩ ማርሲሊዮስና ዮሐንስ የተባሉ ይገኙበታል ። የፖፑን የበላይነት ሥልጣን ክደው (ተቃውመው) ከመላ አብያተ ክርስቲያናት የተወከሉ ካህናትና ምእመናን ለሚካፈሉበት ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ተገዥ መሆን አለበት ። ጉባኤውም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው (መናፍቅ ወዘተ· ሆኖ ሲያገኘው) ፖፑን ከመንበሩ ሊያወርደው ይችላል አሉ ። ይህ ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሥልጣን ከፖፑ ሥልጣን በላይ ነው የሚለው ቲዎሪ ኮንሲሊያሪዝም ይባላል ። ይህንኑ መሠረት በማድረግ ብዙዎች በየጊዜው የፖፑን የበላይነት ሥልጣን በመቃወም ተነሣሥተዋል ።

በአቪኞን ፖፖች ላይ ከካህናትና ከምእመናን ይሰነዘር የነበረው የተቃውሞ ትችት እየተባባሰ ስለሄደ የሲየናይቱ ቅድስት ካቴሪኔ ፤ ስዊድናዊቱ ቅድስት ብሪድጊት ወዘተ· ፖፑ ወደ ሮም እንዲመለስ ስለተማጸኑ ፤ ኢጣልያን የነበረውም የፖፑ ግዛት እየተዳከመ ስለሄደ ጎርጎርዮስ ዐሥራ አንደኛ የተባለው ፖፕ በ1377 ዓ·ም ወደ ሮም ተመልሶ እዚያው ተቀመጠ ። እሱም በ1378 ዓ·ም ዐረፈ ። ወዲያው ተተኪውን ፖፕ የሚመርጡት ዐሥራ ስድስት ካርዲናሎች ለምርጫ ሲዘጋጁ ከነሱም መካከል ዐሥራ አንዱ የፈረንሳይ ተወላጆች ስለነበሩ ፤ በድምጽ ብልጫ



www.ethiopianorthodox.org

የፈረንሣይ ተወላጅ ይመርጡና እንደ ልማዱ ወደ ትውልድ ሀገሩ ሊጓዝ ይችላል ። በዚህም ምክንያት የፖፑን ቡራኬ ለመቀበል ፣ የተቀደሱ ቦታዎችን ለመጐብኘት ወዘተ· በየጊዜው ከዓለም ከሚጐርፉ ምእመናንና ቱሪስቶች የሚገኘውን ከፍተኛ ገንዘብ በማጣት ሮም (የሮም ኑአሪዎች ይሠቃያሉ) ትሠቃያለች በማለት የታጠቁ ሮማውያን ምእመናን ካርዲና ሎች ለመምረጥ ከተሰበሰቡበት (ኮንክሌቭ) ጥሰው ገብተው የሮም ከተማ ተወላጅ እንዲመርጡ በማስፈራራት ጠየቁአቸው ። ሕዝቡም ከውጭ ሆኖ ሮማዊ ምረጡልን እያለ ይጮህ ነበር ። ካርዲናሎችም ጥያቄውን ቢቃወሙ በሚፈጠረው ትርምስ ምክንያት የሰው ሕይወት እንዳያልፍና ምርጫውም እንዳይሰናከል በማለት በ1378 ዓ·ም የሮም ከተማ ተወላጅ ሳይሆን የኢጣልያ ተወላጅ የነበረውን ኡርባን ስድስተኛን መረጡ ። በዓለ ሢመቱ ከተፈጸመ ከሦስት ወር በኋላ ዐሥራ አንዱ ፈረንሳውያን ካርዲናሎች ወደ አቪኞን ተመልሰው የኡርባንን ምርጫ የፈጸምነው በወታደር ኃይል ተገደን ስለሆነ በኛ በኩል ውድቅ አድርገነዋል በማለት ፣ በ1378 ዓ·ም በሕገ ወጥ መንገድ ቀሌምንጦስ ሰባተኛን (1378—1394) መርጠው ተቃራኒ ፖፕ (አንቲ ፖፕ) አድርገው በመሾም በአቪኞን የፖፑ ቤተ መንግሥት እንዲቀመጥ ሆነ ። በዚህም የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን በማተራመስ አርባ ዓመት የፈጀው መለያየት ተጀመረ ።

በዚህ አኳኋን በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ፖፖች ስለተሾሙ ምእመናን ግራ ተጋቡ ፣ ጳጳሳት ፣ የአድርባራት አለቆች ፣ መነኰሳት ወዘተ· ጐራ ለይተው ይነታረኩ ጀመር ። በፖለቲካው አኳያ የካቶሊክን እምነት የሚከተሉ ሀገሮች የፈረንሳይ ፣ የእስኮትላንድ ፣ የናፕልስ ፣ የአውስትርያ ወዘተ· መንግሥታት ቀሌምንጦስን ሲደግፉ ፣ የእንግሊዝ ፣ የመላ ጀርመን ፣ የእስካንዲናቪያ ሀገሮች ፣ የሰሜናዊና የማዕከላዊ ኢጣልያ፣ የአየርላድ ፣ የፖላንድ ፣ የፖርቱጋል ወዘተ· መንግሥታት ኡርባንን ይደግፉ ነበር ። ከፖፖችም አንደኛው እኔ ነኝ ሕጋዊው የቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ወራሽ ሲል ፣ ሌላው ደግሞ ሕጋዊው እኔ ነኝ እንጂ አንተማ መናፍቅ ነህ በመባባል ይወጋገዙ ነበር ። በሥልጣን ላይ የነበሩ ፖፖች በሞት ሲለዩ የሁለቱም ወገን ካርዲናሎች በየፊናቸው ምርጫውን ያከናውኑ ስለነበር መለያየቱ ቀጠለ ።

በ1394 ዓ·ም የፓሪስ ዩኒቨርሲቲ መምህራን (ምሁራን) መከፋፈሉን ያቆማሉ በሚል እምነት ሁለቱም ፖፖች በፈቃዳቸው ከሥልጣና


www.ethiopianorthodox.org

ቸው እንዲወርዱ ፡ ወይም ከሁለቱም ወገኖች በሚመረጡ ገላጋይ ሽማግሌዎች የሚሰጠውን ውሳኔ እንዲቀበሉ ፡ ወይም አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የሚሰጠውን ውሳኔ እንዲቀበሉ የሚሉ ሦስት አማራጮች አቅርበው ተቀባይ ስላጣ ለረጅም ጊዜ በሰላማዊ መንገድ አንድነትን ለማስፈን የተደረገው ድካም ሁሉ ውጤት አልባ ሆነ ። ስለዚህ ለቤተ ክርስቲያኒቱ አንድነት የሚቆረቆሩ ከሁለቱም ፖፖች ወገን የተውጣጡ ሠላሳ አራት ካርዲናሎች መፍትሔው ሊገኝ የሚችለው በቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ጉባኤ ውሳኔ ብቻ መሆኑን በማመን ከመሪዎቻቸው ሥልጣንና ትእዛዝ ውጭ በ1409 ዓ.ም ፒሳ ውስጥ ጉባኤ አደረጉ ። በጉባኤውም ላይ አንድ መቶ ጳጳሳት ፡ አንድ መቶ የጳጳሳት ተወካዮች ፡ ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ የገዳማትና የአድባራት አለቆች ፡ የዩኒቨርሲቲ ምሁራን ወዘተ. ተገኝተዋል ። እነሱም በችግሩ ላይ በሰፊው ከተወያዩ በኋላ መፍትሔው ሁለቱን ፖፖች ማውረድና አንድ አዲስ መሾም መስሎ ስለታያቸው ሁለቱም ፖፖች እንዲወርዱ ወስነው አሌክሳንደር አምስተኛ የተባለውን መርጠው ሾሙ። ይሁን እንጂ የሮሙ ፖፕ ጎርጎርዮስ ዐሥራ ሁለተኛና ተቃራኒው የአቪኞን ፖፕ ቤኔዲክት ዐሥራ ሦስተኛ ጉባኤው በፖፕ ስላልተከፈተና በፖፕ ሊቀ መንበርነትም ስላልተመራ ውሳኔው ዋጋ ቢስ ነው ። ከፖፕ በላይ ሥልጣን ያለው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የለም በማለት አንወርድም በማለታቸው የፖፖቹ ቍጥር ከሁለት ወደ ሦስት ከፍ አለ ። ፒሳ ውስጥ ይኖር የነበረው አሌክሳንደር በ1410 ዓ.ም ስላረፈ እዚያው በምትኩ የተሾመው ዮሐንስ ሃያ ሦስተኛ የተባለው ፖፕ በሐሳበ ግትርነቱና በሞገደኛነቱ የታወቀ ነበር። ሁለቱ ፖፖች በፒሳ ጉባኤ እንዲወርዱ በመወሰኑ ምክንያት የተከታዮቻቸው ቍጥር ዝቅ ሲል ፡ የዮሐንስ ተከታዮች ግን እየበዙ ሄዱ ።

የጀርመን ንጉሥና የሮማ ኤምፖየር ንጉሠ ነገሥት የነበረው ሲግስሙንድ (1410—1437) በቤተ ክርስቲያን ዘንድ የተፈጠረውን መለያየት አጥፍቶ አንድነትን ለማስፈን ፖፕ ዮሐንስን ማቅረቡ የተሻለ መስሎ ታየው ። በዮሐንስ አማካይነት ኮንስታንስ በምትባል ጀርመን በምትገኝ ከተማ ውስጥ ጉባኤ በማድረግ መለያየቱ ጠፍቶ አንድነት የሚሰፍንበትን መንገድ ለመሻት ወሰነ ። ዮሐንስም በሲግስሙንድ ጥሪ መሠረት ከብዙ የኢጣልያ ጳጳሳት ጋር ወደ ኮንስታንስ ሄደ ። ሁለቱ ፖፖችም ወኪሎቻቸውን ላኩ ። ሠላሳ ሦስት ካርዲናሎች ፡ አምስት መቶ



www.ethiopianorthodox.org

ጳጳሳት ፣ ቍጥራቸው ብዙ የሆነ የዩኒቨርሲቲ አባላት ፣ ቀሳውስት ልዑላንና ምእመናን ለመካፈል በተገኙበት በ1414 ዓ·ም የኮንስታንስ ጉባኤ ተከፈተ ።

ዮሐንስም ወደ ኮንስታንስ የሄደው የጉባኤው ተካፋዮች የሁለቱን ፖፖች መውረድ አጽድቀው የኔን ብቸኛ ፖፕነት ያጸድቁልኛል በሚል ምኞትና ተስፋ ነበር ። ነገር ግን በጉባኤው ላይ የተገኙት አንድነት ሊገኝ የሚችለው ሦስቱም ወርደው አዲስ ፖፕ ተመርጦ ሲሾም ብቻ ነው ከሚል ውሳኔ ላይ ደረሱ ። የኢጣልያ ተወላጅ የሆኑት ጳጳሳት ብዛት ስለነበራቸው በድምጽ ብልጫ ዮሐንስን እንዳይመርጡ በመፍራት ቍጥራቸው ትንሽ የነበረው የፈረንሳይ ፣ የጀርመን ፣ የእንግሊዝና የእስጳኝ ተወላጅ የሆኑት ጳጳሳት ምርጫው በነፍስ ወከፍ መሆኑ ቀርቶ በብሔር እንዲሆን ተስማሙ ። በዚህ አኳኋን ለመምረጥ መብት የነበራቸው የኢጣልያ ፣ የፈረንሳይ ፣ የጀርመን ፣ የእንግሊዝና የእስጳኝ ሀገሮች ነበሩ ። እያንዳንዱ ብሔር አንድ ድምጽ እንዲኖረው ፣ ፖፕ የመምረጥ ሥልጣን የነበራቸው ካርዲናሎችም አንድ ድምጽ እንዲኖራ ቸው ተወሰነ ። ይህ ዓይነቱ የምርጫ ዘዴ የኢጣልያኖችንና የዮሐንስን ተስፋ ባጭሩ ስለቀጨው ፣ ዮሐንስ ራቅ ካለ ቦታ ሆኖ የጉባኤውን ሂደት ለማደናቀፍ እንዲመቸው በማሰብ በ1415 ዓ·ም በምሥጢር ከኮንስታንስ ጠፍቶ ወደ አውስትርያው ዱክ (መስፍን) ግዛት ኮበለለ ። ከዚያም ሆኖ ጉባኤው እንዲበተን መልፈፍ ጀመረ ። በዮሐንስ ለፈፋ ምክንያት የጉባኤው ተካፋዮች ተስፋ ቈርጠው ከአንዳች ውሳኔ ሳይደርሱ ለመበተን በተነሣሡበት ወቅት ሲግስሙንድ ያለ ፖፑ ሊቀመንበርነትም ቢሆን ጉባኤው ቀጥሎ ለዚች ለተከፋፈለች እናት ቤተ ክርስቲያናችን አንድነት ከሚያስገኝ ውጤት ላይ መደረስ አለበት ብሎ ስላጽናናቸው ጉባኤው ሥራውን በረጋ መንፈስ ቀጠለ ። ሆኖም ዮሐንስ ሸሽቶ ከተቀመጠበት ቦታ ሆኖ ጉባኤውን ለመበተን በማሰብ አጉል ፕሮፖጋንዳውን ስለቀጠለ የጉባኤው አባላት የአጠቃላዩ ጉባኤ ሥልጣን ከፖፑ በላይ መሆኑን በመግለጽ ለፖፕ ዮሐንስ "…ይህ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በሕጋዊ መንገድ የተጀመረ ፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በመወከል በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የሚሠራ ፣ ሥልጣንም የተቀበለው በቀጥታ ከእግዚአብሔር ስለሆነ ማንኛውም ክርስቲያን ፖፑም ጭምር ይህ ጉባኤ መከፋፈልን አስወግዶ አንድነትንና እምነትን ለማጽናት ለሚያወጣው



www.ethiopianorthodox.org

እምነት ነክ ውሳኔ ሁሉ ታዛዥ መሆን ይገባዋል …" በማለት መልስ ሰጡት ። ይህ "አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ከፖፑ ሥልጣን በላይ ስለሆነ ሲያስፈልግ ካህናትና ምእመናን ለዚሁ ጉባኤ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ ። …" የሚለው ኮንሲሊያሪዝም የተባለው በብሔርተኝነት ላይ የተመሠረተው አስተሳሰብ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ለብዙ ዘመናት ሲያወዛግብ የኖረ ነው ። ዘግየት ብሎ የተነሣው ዳግማዊ ፒዮስ የተባለው ፖፕ በ1460 ዓ·ም ኮንሲሊያሪዝም ሕጋዊውን የፖፖች የበላይነት ሥልጣን ለመደምሰስ የተወጠነ ነው በማለት አውግዞታል ። ሆኖም በውግዘቱ ምክንያት ብዙ ምሁራን ቴዎሪውን በተግባር ላይ ከማዋል ወደ ኋላ አላሉም ። ለምሳሌ ሉተር ያስተማረው ትምህርት በፖፑ ከተወገዘ በኋላ ለአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ይግባኝ ብሏል ። በዚህ አኳኋን ኮንሲሊያሪዝም በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ዘመን ለፕሮቴስታንቶች መነሣት እስተዋጽኦ በማድረግ መንገድ ከፍቷል ።

እላይ እንደተመለከትነው ፖፕ ዮሐንስም መቀመጫውን ቡርጉንዲ ውስጥ አድርጎ ከዚያ ሆኖ ጉባኤውን ለመረበሽ በማሳብ መንገድ እንደጀመረ ሲግስሙንድ በድንገት አስይዞ በኮንስታንስ ጉባኤ ለተቀመጡት አባቶች ለፍርድ ካቀረበው በኋላ ከሥልጣኑ እንዲወርድ ተደረገ ። ወዲያው የሮሙ ፖፕ ጎርጎርዮስ ዐሥራ ሁለተኛ ስለ ሰላምና አንድነት ሲል በፈቃዱ በክብር ከሥልጣን መልቀቁን ሲያስታውቅ ፣ የአቪኞኑ ፖፕ ቤኒዲክት ዐሥራ ሦስተኛ በፈቃዱ ከሥልጣኑ እንዲወርድ ሲግስሙንድ ቢያግባባው አሻፈረኝ ስላለ ፣ በጉባኤው የተሰበሰቡት አባቶች በሌለበት በ1417 ዓ·ም ከሥልጣኑ እንዲወርድ በመወሰናቸው ሳይወድ ተገዶ ወረደ። ከዚያ በኋላ ከአምስቱ ብሔሮች ከያንዳንዱ ስድስት ስድስት መራጮችና ሃያ ስድስት ካርዲናሎች በአጠቃላይ አምሳ ስድስት መራጮች ለምርጫ ተሰብስበው በ1417 ዓ·ም ማርቲን አምስተኛን መርጠው ሾሙ ። ሲግስሙንድ አዲስ የተመረጠው ፖፕ ጀርመን ውስጥ እንዲኖር ፣ ፈረንሳዮች ደግሞ አቪኞን ሄዶ እንዲቀመጥ ቢያግባቡት የቅዱስ ጴጥሮስ መቃብር በሚገኝበት በሮም መቀመጥን በመምረጥ የእርስ በእርስ ጦርነት ወደ ሚካሄድባት ወደ ኢጣልያ ተጓዘ ። እዚያም እንደ ደረሰ በጦርነት ፈራርሳ የነበረችውን የሮም ከተማ አሳደሰ ። ሕዝቡም በሚገባ የሚመራ አባት በማግኘቱ ተደሰተ ። በዚህ አኳኋን አርባ ዓመታት ያህል የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ከፋፍሎ ሲያተራምስ የቈየው መለያየት



www.ethiopianorthodox.org

አከትሞ አንድነትና ሰላም ሰፈነ ። አዲስ የተመረጠውም ፖፕ የኮንስታንስን ጉባኤ በ1418 ዓ·ም በጸሎት ዘጋ። በዚህ አኳኋን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ መከፋፈልን አስወግዳ አንድነቷን ለማጽናት ስትችል ፤ በውስጧ ይፈጸሙ የነበሩትን የተለያዩ እንደ ኃጢአት ማስተስረያ ጽሑፎች (ኢንዶልጀንስ) ፣ የሞራል ጉድለቶች ወዘተ· የመሳሰሉትን ለማረም ባለመቻሏ ከአባላቷ በየጊዜው እንደነ ሑስ፣ ሉተር ወዘተ· ያሉ ምሁራን ተነሥተው አተራመሷት (ወነጀሏት) ። ይኸውም የፖፑን ሥልጣን በመቃወም ፤ የድኅነት መገኛ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ፣ መጽሐፍ ቅዱስም ምእመናን በሚረዱት ቋንቋ ተተርጉሞ መቅረብ አለበት ፤ ቤተ ክርስቲያንም ከፍተኛ መሻሻል ማድረግ ያስፈልጋታል ወዘተ· በማለት ያስተማሩት የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ዮሐንስ ዊክሊፍ (1330—1384) ፣ የፕራግ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ዮሐንስ ሑስ (1370—1415) መናፍቃን ናቸው በማለት በኮንስታንስ ጉባኤ የተሰበሰቡት አባቶች የዊክሊፍ አጽም ከመቃብር ወጥቶ በእሳት እንዲቃጠል ፤ ሑስም በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ስለወሰኑ ውሳኔው በ1415 ዓ·ም በተግባር ላይ ዋለ ። በዚህ አኳኋን ሁለቱ ምሁራን (ካህናት) ያስተማሩት ትምህርት በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ዘመን ለተነሡት ለነሉተርና ለነካልቪን መንገድ ጠርጎላቸዋል (አመቻችቶላቸዋል) ።

በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ለውጦችን (መሻሻሎችን) ለማድረግ ታቅዶ በፖፕ ኤውጌኒዮስ አራተኛ (1431—1447) በ1431 ዓ·ም ከኢጣልያ ውጭ በተከፈተው በባሴል አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ላይ ከተካፈሉት አባቶች መካከል አብዛኞቹ ከፖፑ የጉባኤው ሥልጣን ስለሚበልጥ ጉባኤውን እኛ እንመራለን በማለት ተነሡ ። ፖፑም ዓላማቸውን በጥብቅ በመቃወሙ ባሴል ውስጥ የተጀመረው ጉባኤ ፌራራ ፣ ከዚያም ፍሎሬንስ ውስጥ እንዲካሄድ አደረገ። ወደ ፌራራ ያልሄዱ ጥቂት የባሴል ጉባኤ ተካፋዮች በዓላማቸው በመጽናት ፖፑን በድምጽ ብልጫ በ1439 ዓ·ም ሽረው ፊልክስ አምስተኛ የተባለውን ተጻራሪ ፖፕ (አንቲ ፖፕ) በሕገ ወጥ መንገድ ፖፕ አድርገው በመሾማቸው እላይ የተመለከትነው ዐይነት መከፋፈል በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ተጀምሮ ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

ሆኖም ቀስ በቀስ የኤውጌንዮስ አራተኛ ዓላማ ደጋፊዎች እየበዙ በመሄዳቸውና ፊልክስም በ1449 ዓ.ም. በፈቃዱ ከሥልጣኑ በመውረዱ ፣ በንጉሥ ፍሬደሪክና በጀርመን ልዑላን ትእዛዝ የባሴል አጠቃላይ ጉባኤ በመቋረጡ ፣ ከኤውጌንዮስ ቀጥሎ በሕጋዊ መንገድ ተሹሞ ፖፕ የነበረው ኒኮላኦስ አምስተኛ (1447–1455) የፖፑን ሥልጣን አጠቃሎ ያዘ ። ስለዚህ ተስፈንጣሪ በነበሩ በባሴል ጉባኤ አባላት የተካሄደው የኮንሲሊያሪዝም ግፊት ያስከተለው የመለያየት ጠንቅ አንድያውን አከተመ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የፖፑ ሥልጣን ከአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በለይ መሆኑ ተረጋገጠ ።

እላይ የተመለከትነው በ1431 ዓ.ም በኤውጌንዮስ አራተኛ ባሴል ውስጥ የተጀመረው አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በተከታታይ እንደገና በ1438 ዓ.ም. ኢጣልያ በምትገኘው ፌራራ ውስጥ ቀጥሎ ሳለ ፣ በካቶሊክና በግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንድነት ለመፍጠርና ከቱርክ መንግሥት አደጋ መከላከያ የሚሆን የጦር እርዳታ ለመጠየቅ የቍስጥንጥንያው (የቢዛንታይን) ንጉሥ ዮሐንስ ፓሌዎሎጉስ አምስተኛ ፣ ፓትርያርኩ ዳግማዊ ዮሴፍ ፣ ሌሎችም የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርኮች ተወካዮች በጉባኤው ላይ ተገኝተው ነበር ። ፌራራ ውስጥም የወረርሽኝ በሽታ ስለተነሣና የገንዘብ እጥረትም ስለተፈጠረ ወዘተ. በ1439 ዓ.ም ጉባኤው ወደ ፍሎሬንስ ተዛውሮ ሥራውን ቀጠለ ። ለጊዜው በአንዳንድ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች ገፋፊነት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንድነት ተመሥርቶ ነበር ። ነገር ግን ወዲያው ስምምነቱ በግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነትን ስላጣ ውድቅ ሆነ ። የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መለያየትም እስከ ዛሬ ድረስ እንደቀጠለ ነው ።

የምዕራብ አውሮጳ መንግሥታትም በቸልተኝነትና በግድየለሽነት በተለያዩ ምክንያቶች የጦር እርዳታ ስላልላኩ ፣ የምሥራቅ አውሮጳ ክፍል የቢዛንታይን ንጉሥ ኮንስታንታይን (ቈስጠንጢኖስ) ዐሥራ አንደኛ በ1453 ዓ.ም በዳግማዊ መሐመድ በተመራው የቱርክ ጦር ድል ስለተመታና ራሱም በጦር ሜዳ ላይ ስላረፈ የቢዛንታይን መንግሥት በቱርኮች እጅ ወደቀ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ሰ) ከፕሮቴስታንቶች መለየት በኋላ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል መልእክተኞቿን (ሚስዮኖቿን) በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በማሠማራት (በመላክ) እምነቷን ያስፋፋችበት ዘመን

የክርስትና መሥራች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ዓለምን ዞረው ወንጌልን እንዲሰብኩ ባዘዘው መሠረት (ማቴ. 28፡18–20 ፤ ሉቃ. 24፡47፤ ዮሐ.17፡18፤ 20፡21፤የሐዋ. 1፡8) ቤተ ክርስቲያን የወንጌልን ትምህርት በየጊዜው ለዓለም ሕዝቦች አዳርሳለች ። ሆኖም በእስልምና መስፋፋት ፣ በግሪክ ኦርቶዶክስና በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት መለያየት ወዘተ. ምክንያት ወንጌልን በዓለም የማዳረሱ ተግባር በመጠኑ ተገትቶ ነበር ።

በ16ኛው መቶ ዘመን አውሮጳ ውስጥ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ከነበረው ሕዝብ መካከል ከፊሉ ተለይቶ የፕሮቴስታንትን አብያተ ክርስቲያናት ሲመሠርት ፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች በደቡብ አውሮጳ ውስጥ በኢጣልያ ፣ በእስጳኝ ፣ በፖርቱጋል ወዘተ. የነበሩ በእምነታቸው ጸንተው ቀሩ ። ከዚህ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ቊጥር እየቀነሰ ከሄደበት ዘመን ትንሽ ቀደም ብሎና በዚሁ ዘመን የካቶሊክ እምነት ደጋፊዎች የነበሩት የእስጳኝና የፖርቱጋል መንግሥታት መርከቦቻቸውን ወደተለያዩ አቅጣጫዎች በመላክ የላቲን (የመካከለኛና የደቡብ) አሜሪካን ሀገሮች ፣ ከእስያና ከአፍሪካም አንዳንድ ሀገሮችን በቅኝ ግዛትና በንግድ ስምምነት ስም ያዙ ። በዚያን ጊዜ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ፍራንሲስካውያን ፣ ዶሚኒካውያን ፣ ኢየሱሳውያን ወዘተ. ከወታደሮችና ከነጋዴዎች ጋር በመርከብ በመጓዝ ክርስትናን በላቲን አሜሪካ ሀገሮች በብራዚል ፣ በፔሩ ፣ በቺሊ ፣ በኮሎምቢያ ፣ በኤኳዶር ፣ በሜክሲኮ፣ በአርጀንቲና ፣ በቦሊቪያ ፣ በቬኔዙኤላ ፣ በጓቴማላ ፣ በኮስታሪካ ፣ በሔቲ ፣ በሆንዱራስ ወዘተ. ውስጥ በማስተማር ሕዝቡን ወደ ክርስትና በመመለስ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን አባላት ቊጥር ከፍ ለማድረግ ቻሉ ። እንዲሁም የካቶሊክ ሚስዮናውያን የፖርቱጋል ቅኝ ገዥዎችን በመከተል በ17ኛው መቶ ዘመን እንደ ሞዛምቢክ ፣ ኮንጐ ፣ ወዘተ. በመሳሰሉት የአፍሪካ ሀገሮች የክርስትናን ትምህርት አስተምረዋል ። ዘግየት ብሎም የቅኝ ግዛቶቻቸው በአመጽ



www.ethiopianorthodox.org

ነጻነታቸውን በመቀዳጀታቸውና በተለያዩ ምክንያቶች የእስጳኝና የፖርቱ ጋል መንግሥታት በተዳከሙበት ወቅትም በ19ኛው መቶ ዘመን የፈረን ሳይ ፣ የቤልጅግ ወዘተ. መንግሥታት አፍሪካ ፣ ካናዳ ፣ ሰሜን አሜሪካና እስያ በነበሩት የቅኝ ግዛቶቻቸው የካቶሊክ እምነት እንዲስፋፋ ረድተ ዋል ።

ከእስጳኝ ፣ ከፖርቱጋል ወዘተ. የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር በአመጽ የፖለቲካ ነጻነታቸውን የተቀዳጁት ሀገሮች ወዲያው ከቫቲካን ጋር የዲፕሎማቲክ ግንኙነት መሥርተው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባልነታ ቸውን በማጽናት እምነታቸውን በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ ።

ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል መልእክተኞች መካከል ዝነኛ የነበረው የእስጳኙ ተወላጅ ኢየሱሳዊው የወንጌል መልእክተኛ ፍራንሲስ ሐቪየር (1506–1552) በፖርቱጋል መንግሥት ሥር በነበሩት በሕንድ ፣ በኢንዶኒስያ ፣ በጃፓን ውስጥ በሚገኙ ክፍለ ሀገሮች ወንጌልን በትጋት አስተምሮ ወደ ቻይና በመጓዝ ላይ ሳለ ሳንሲያን (የቅዱስ ዮሐንስ ደሴት) እተባለችው ደሴት ውስጥ በ1552 ዓ.ም ዐረፈ ። አስከሬኑም የስብከተ ወንጌል ተግባሩ ማዘጋጃና መኖሪያው ወደነበረችው ወደ ጐአ ተወስዶ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ በክብር ዐረፈ ። የፖርቱጋልን ንጉሥና የፖፑን ሙሉ ድጋፍ አግኝቶ በትጋት በማስተማሩ ምክንያት ቊጥራቸው እጅግ ከፍ ያለ ሰዎችን ወደ ክርስትና መልሶ ነበር ። ለዚህም ላበረከተው ታላቅ ተግባር የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በ1622 ዓ.ም የቅዱስነት ማዕርግ ሰጥታዋለች ።

በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥር የሚከናወነውን የስብከተ ወንጌል ተግባር በፖፑ ሥልጣን ሥር በማዕከላዊነት የሚያቀነባብርና አስፈላጊ ውን ድጋፍ የሚያደርግ "ፕሮፓጋንዳ ፊዴ" በመባል የታወቀው መንፈሳዊ ድርጅት ጎርጎርዮስ ዐሥራ አምስተኛ በተባለው ፖፕ በ1622 ዓ.ም ተመሥርቶ ተግባሩን ያከናውን ጀመር ። ይኸው ድርጅት ለካቶሊክ እምነት መስፋፋት ታላቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል ።

ኢየሱሳዊው የወንጌል መልእክተኛ ሮበርት ዴ. ኖቢሊ (1577–1656) ደቡብ ሕንድ ውስጥ ብራሕማኖችን በመምሰል ፤ በብራሕማኖች ዝቅተኛ ነገዶች ናቸው በመባል እንደ እርኩስ ነገር በመታየት የማይነኩ ትን ሰዎች በመራቅ ፤ እንደ ብራሕማኖች የምንና (የብሕትውና) ኑሮን በመኖር ፣ ባህሎቻቸውን በመፈጸምና መስሎ እየኖረ ተግቶ በማስተማር



www.ethiopianorthodox.org

በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ሰዎችን አጥምቋል ። በብራሕማኖች ባህል መሠረት እንደ ርኩስ በመቈጠር የማይነኩ ለተባሉትም ዝቅተኛ ነገዶች በሌላ አስተማሪ የሚመሩ የወንጌል መልእክተኞች እንዲላክላቸው ሐሳብ አቅርቧል ። ሳንስክሪት በተባለው ቋንቋም የትምህርተ ሃይማኖት መጻሕፍት ጽፎላቸዋል ። የተጠመቁት ምእመናንም የአሕዛብን መንፈስ ያልተከተሉ ሕንዳዊ ባህሎቻቸውን ከክርስትና እምነታቸው ጋር ጐን ለጐን እንዲፈጽሙ ፈቅዶላቸው ነበር ። ይህ ዐይነቱ መስሎ የማስተማሩ ዘዴ በ1623 ዓ.ም ጎርጎርዮስ ዐሥራ አምስተኛ በተባለው ፖፕ ተደግፎ ሲሠራበት ከቈየ በኋላ ፤ ቤኔዲክት ዐሥራ አራተኛ የተባለው ፖፕ ይህንኑ ዘዴ በመቃወም ስላወገዘው ከ1742 ዓ.ም ጀምሮ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሰባክያን በሕንድ ያፋፋሙት የወንጌል ትምህርት ለተወሰነ ጊዜ ተዳክሞ ከቈየ በኋላ ከ19ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ ሕንድ ውስጥ ክርስትና በመስፋፋት ላይ ናት ።

እንዲሁም ኢየሱሳዊው የወንጌል መልእክተኛ ማቴዎስ ሪኪ (1552–1610) ቻይና ውስጥ ሀገሬውን መስሎ በመኖርና በኮንፉሲዩስ ትምህርት መሠረት የሞቱ ዘመዶቻቸውን ማምለክ የመሳሰሉትን ባህሎቻቸውን እንዲፈጽሙ በመፍቀድ ፤ እራሱም እየፈጸመ በቻይንኛ ቋንቋ ስላስተማረ ብዙዎችን ወደ ክርስትና እምነት መለሰ ። እንዲሁም የሰዓትና የካርታ ሥራ ችሎታው በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅ አደረገው ። የንጉሡም የቅርብ አማካሪ ለመሆን ስለቻለ ቻይና ውስጥ ክርስትና በይፋ እንድትሰበክ ለማድረግ ችሎ ነበር ።

ከማቴዎስ ሪኪ ዕረፍት በኋላ ረዳቱ አዳም ሸል ቮን ቤል (1592–1666) ቻይናዎችን መስሎ ባህሎቻቸውን እየፈጸመ በመኖር ወንጌልን አስተማረ ። በመንግሥቱም ዘንድ ከፍ ያለ ክብርና የሚኒስትርነት ማዕርግ ተሰጥቶት ነበር ። ፔኪንግ ውስጥ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንጾ ክርስቲያኖች ያለምንም ተጽእኖ በሰላም አምልኮአቸውን ለማከናወን ችለው ነበር ። እንደ አሕዛብ የጣዖት አምልኮ እስካልተለወጠ ድረስ የቻይና ክርስቲያኖች የሞቱ ዘመዶቻቸውን በአክብሮት ስሜት በማሰብ የሚያደርጉትን የማምለክ ልምዳቸውን (ባህላቸውን) እንዲፈጽሙ ኢየሱሳውያን ሰባኪዎች ፈቅደው ነበር ። ሆኖም ከ1630 ዓ.ም ጀምሮ ቻይና ውስጥ ማስተማር የጀመሩት ዶሚኒካውያንና ፍራንሲስካውያን የወንጌል መልእክተኞች የሀገሬውን ባህል እየፈጸሙ ማስተማሩ ከክርስትና ትምህ



www.ethiopianorthodox.org

ርት ውጭ ነው በማለት በኢየሱሳውያን ላይ ክስ ስላቀረቡ ኢኖሴንት ዐሥረኛ የተባለው ፖፕ በ1645 ዓ.ም የየሀገሩን ተወላጅ መስሎና ባህሉን እየፈጸሙ ማስተማርን ከለከለ ። በ1704 ዓ.ም. ቀሌምንጦስ ዐሥራ አንደኛ ይህንኑ እገዳ ስላጸናው የቻይና ንጉሥ ካንግሕሲ በተለይ የሞቱ ዘመዶችን ማምለክ መከልከሉ ስላስቆጣው ክርስቲያኖች የሀገሬን ባህል ይቃወማሉ በማለት ክርስትና በግዛቱ እንዳትሰበክ ከልክሎ በክርስቲያኖች ላይ ስደትን በማወጁ በእስያ የተጀመረው የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ ባጭሩ ተቀጨ ።

- በሃያኛው መቶ ዘመን የካቶሊክ ሚስዮናውያን እንደገና ቻይና ውስጥ ቀስ በቀስ ወንጌልን አስተምረው ለአጠመቋቸው ክርስቲያኖች በ1946 ዓ.ም. ቻይናዊውን ቲየንን ካርዲናል አድርገው በሾሙ በሦስተኛው ዓመት ማኦ ሴቱንግ ባካሄደው የኮሙኒስት አብዮት የሀገሪቱን የመሪነት ሥልጣን ከያዘ በኋላ ክርስቲያኖች ተደመሰሱ ።

እላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በእስያ ያሰማራቻቸው ሚስዮናውያን ድካም አጥጋቢ ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም ።

የእስጳኝ ተወላጆች በነበሩ አውግስቲናውያን የወንጌል መልእክተኞች ትጋት ከ1565 ዓ.ም ጀምሮ ሩቅ ምሥራቅ በሚገኙት ፊሊፒንስ ደሴቶች ውስጥ ወንጌልን አስተምረው ብዙዎችን ወደ ክርስትና እምነት መለሱ ። ከ1595 ዓ.ም ጀምሮ ኢየሱሳውያን ፊሊፒንስ ውስጥ ብዙ ትምህርት ቤቶች ከፍተው አስተምረዋል ። በዚህ አኳኋን በእስያ ከሚገኙት ሀገሮች መካከል የካቶሊክ እምነት ሥር ሰዶና ተስፋፍቶ የሚገኘው ፊሊፒንስ ውስጥ ነው ። በዘመናችን ከፊሊፒንስ ሕዝብ ከመቶ ሰማንያው እጅ የካቶሊክ እምነት ተከታይ መሆኑ ይነገራል ።

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከ19ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ አፍሪካ ውስጥም ኡጋንዳ ፣ ዛየር ፣ ሩአንዳ ፣ ቡሩንዲ ፣ ኬንያ ፣ ታንዛንያ ፣ ሞዛምቢክ ፣ አንጐላ ወዘተ. ክርስትናን በሰፊው በማስተማርና በማስፋፋት ላይ ናት ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ከላቲን አሜሪካ ፣ ከእስያና ከአፍሪካ ሀገሮች በከፊል በጦር ኃይል በቅኝ ግዛትነት ይዘው ያስተዳድሩ የነበሩ የእስጳኝና የፖርቱጋል መንግሥታት በተዳከሙበት ወቅት ከ17ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ ተጠናክረው የተነሡት የዳች ፣ የእንግሊዝ ፣



www.ethiopianorthodox.org

የፈረንሳይ ወዘተ. መንግሥታት በእስጳኝና በፖርቱጋል እጅ ከነበሩት ቅኝ ግዛቶች ከፊሎችንና ሌሎችንም ሀገሮች በቅኝ ግዛትነት ይዘው ያስተዳድሩ ጀመር ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የካቶሊክ ሚስዮናውያን ብቻ ሳይሆኑ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያንም እምነታቸውን በሚከተሉ በእንግሊዝ ፣ በጀርመን ፣ በዳች ፣ በስዊን አሜሪካ ወዘተ. መንግሥታት ድጋፍ የየራሳቸውን እምነት በዓለም አዳረሱ ። ከዚህ ላይ ልንረዳው የሚገባን የፖርቱጋል ፣ የፈረንሳይና የእስጳኝ ቅኝ ገዥዎች በያዙአቸው ሀገሮች የካቶሊክ እምነት እንዲስፋፋ ሲጥሩ ፣ የዳች ፣ የጀርመን ፣ የስዊን አሜሪካ ወዘተ. መንግሥታት ደግሞ ለፕሮቴስታንት እምነት መስፋፋት ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። የእንግሊዝ መንግሥት ፖሊሲ ግን ቅኝ ግዛትን ማብዛትንና ንግድን ማስፋፋት እንጂ ለሃይማኖት መስፋፋት ደንታ ስላልነበረው ሕዝቡ የራሱን እምነትና ባህል ጠብቆ እንዲኖር ይፈቅድ ነበር ። ሆኖም የካቶሊክና የተለያዩ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ጐን ለጐን በሚያስተምሩበት ወቅት ተባብረው በማስተማር ለምእመናን መልካም ምሳሌ በመሆን ፈንታ አንዳንዶቹ አፍራሽ የሆነ ውድድርን በመከተል አንዱ ወገን አስተምሮ ያጠመቀውን ፣ ሌላው ወገን ፊት ከሌሎቹ የተማርኸው ስሕተት ነው በማለት እንደገና ያጠምቅ ነበር ። እንዲሁም አረመኔዎችንና ክርስትናን ያልተቀበሉትን ወገኖች አስተምሮ በማጥመቅ ፈንታ ኢክርስቲያናዊ በሆነ መንገድ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችን ሁለቱም ወገኖች ወደየራሳቸው እምነት በመመለስ ወዘተ ምእመናንን ግራ አጋብተው ነበር ። ዛሬም ቢሆን ጥቂቶቹ ሚስዮናውያን ክርስትናን ያልተቀበሉትን አስተምሮ የመመለስ የተቀደሰ ዓላማቸውን ስተው ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንን ግራ በማጋባት ላይ ናቸው ።

በመጨረሻ ሁላችንም ልንገነዘበው የሚገባን የካቶሊክም ሆኑ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን የስብከተ ወንጌል ተልእኮአቸውን ለማከና ወን የቻሉት ፤ ዛሬም በማከናወን ላይ ያሉት በበጎ አድራጊ ድርጅቶችና ምእመናን በየጊዜው ያለማቋረጥ እንደየችሎታቸው በሚለግሡት ገንዘብ (ሙዳየ ምጽዋት) ድጋፍ መሆኑን ነው ። ከበጎ አድራጊዎች የሚሰበሰበው ገንዘብም በመዝረክረክ በማንም ሳይመነተፍና ሳይባክን በታላቅ ጥንቃቄ ተሰብስቦና ተቀምጦ በቤተ ክርስቲያን ሃላፊዎችና ከምእመናን በተመ ረጡ ሽማግሌዎች በተዘጋጀ ፕሮግራም መሠረት በተግባር ላይ ይውላል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ሸ) የፖፖችን ሥልጣን በመጋፋት ከ1648–1789 ዓ.ም ድረስ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተነሡ ንቅናቄዎች

ከዌስትፋልያው ስምምነት እስከ ፈረንሳይ ሪቮሉሽን ድረስ ፖፖች ተቀባይነትና ተሰሚነት የነበራቸው የካቶሊክን እምነት በሚከተሉ ሀገሮች ዘንድ ብቻ ነበር ።

በትሬንት ጉባኤ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በፖፑ መሪነት በውስጧ የተከሰቱትን ስሕተቶች ካረመች በኋላ ለወደፊትም በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚከሰቱትን ስሕተቶች ፖፖች በየጊዜው እየተከታተሉ እንዲያርሙ ሥልጣን ተሰጥቷቸው ነበር ። እነሱም በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ብዙ ገንቢ ለውጦች እንዲፈጸሙ አድርገዋል ። በተጨማሪም በአምባሳደር ማዕርግ የቤተ ክርስቲያኒቱን ጉዳይ የሚያከናውኑ መልእክተኞች በፖፑ እየተመረጡ ወደ ፈረንሳይና ወደ ሌሎችም ሀገሮች እየተላኩ ተግባራቸውን ያከናውኑ ነበር ።

ሆኖም አንዳንድ የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ ነገሥታትና ጳጳሳት በማዕከላዊነት የሚሠራውን የፖፑን የበላይነት ሥልጣን እንደ ጣልቃ ገብነት በመቍጠር መቃወም ጀመሩ ። በተቃውሞአቸውም ምክንያት የፖፖች ሥልጣን እየተዳከመ ሄደ ። ከተቃዋሚዎችም አብዛኞቹ የተነሡት ፈረንሳይ ውስጥ ነበር ። እነሱም ፡

1ኛ) በዐሥራ ሰባተኛውና በዐሥራ ስምንተኛው መቶ ዘመን የተካሄደው ጋሊካኒዝም (ጋሊካዊ) የተባለው ንቅናቄ ፈረንሳይ በነበረችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ላይ የነበረውን የፖፑን የመንፈሳዊ አስተዳደር ሥልጣን ለንጉሡ ለሉዊስ ዐሥራ አራተኛ (1643–1715) ለማጉናጸፍ የተተለመ ነበር ። ይህ በብሔርተኝነት ስሜት የተጀመረው ንቅናቄ ፖፑ የውጭ ሀገር ተወላጅ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያኒቱ በንጉሡ በሚመረጡ የፈረንሳይ ዜጎች በሆኑ ካህናት መተዳደር አለባት በሚል ዓላማ የተነሣ ነበር ። ይህ ዓይነቱ ቤተ ክርስቲያንን ከነገሥታት በታችና ታዛዥ ለማድረግ የተሞከረው ንቅናቄ በፈረንሳይ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሌሎች የአውሮጳ ሀገሮችም ተንጸባርቋል ።

ንጉሥ ሉዊስ በ1682 ዓ·ም የፈረንሳይ ካህናት የተካፈሉበት ጉባኤ ጠርቶ ይህንኑ ንቅናቄ እንዲያጸድቁ አደረገ ። በዚሁ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የፈረንሳይ ንጉሥ የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ አስተዳዳሪ መሆን ፡



www.ethiopianorthodox.org

የአብያተ ክርስቲያናት ሃላፊዎች የተገኙበት አጠቃላይ ጉባኤ ከፖፑ ሥልጣን በላይ መሆኑ ፤ ፖፑ እምነት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ ሥልጣን እንዲኖረው ወዘተ፡ ተብሎ ተወሰነ ። በተጨማሪም እላይ የተጠቀሱትን ውሳኔዎች የያዙ በአቡነ ቦሱኤትና በፓሪስ ዩኒቨርሲቲ መንፈሳውያን መምህራን የተዘጋጁት ይህንኑ ንቅናቄ የሚደግፉት (ሀ) ፖለቲካ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ነገሥታት ከቤተ ክርስቲያን ሥልጣን በታች ስላለመሆናቸው ፤ (ለ) ለየት ያሉት የፈረንሳይ ቤተ ክርስቲያን መብቶች ሊለወጡ የማይችሉ ስለመሆናቸው ፡ (ሐ) አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች (ሲኖዶሶች) ከፖፖች ሥልጣን በላይ ስለመሆናቸው ፡ (መ) የፖፑ ውሳኔ (ብያኔ) ሊጸና የሚችለው በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሲጸድቅ ብቻ ስለመሆኑ የሚገልጹት አራቱ አርቲክሎች በዩኒቨርሲቲዎችና በመንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች በትምህርት መልክ እንዲሰጡ ተወሰነ። በዚሁ ትምህርት አማካይነት ንቅናቄው የካቶሊክ እምነት ተከታይ ወደሆኑ ሀገሮች ተዛመተ ። ይህንኑ የንጉሡን ሕገ ወጥ ተግባር ኢኖሴንት ዐሥራ አንደኛ የተባለው ፖፕ ወዲያውኑ አወገዘው ። ሆኖም ከሁለት መቶ ዓመታት በኋላ በተደረገው በመጀመሪያው የቫቲካን ጉባኤ (1869–1870) ቀደም ሲል በጥብቅ የተቃወሙት የፖፑ አለመሳሳት (አይሳሳትም የሚለው) ስለጸደቀ የጋሊካኒዝም ንቅናቄ ደብዛው ጠፋ ። በተጨማሪም ፖፕ ኢኖሴንት ዐሥራ አንደኛ የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ መንግሥታትን አስተባብሮ ቪየናን የከበቡ ቱርኮችን በጦር ኃይል እንዲባረሩ ሲያደርግ ፡ ሉዊስ ዐሥራ አራተኛ ግን ቱርኮችን ይረዳ ነበር ።

2ኛ) ጃንሴኒዝም (ጃንሴናዊ) የዚህ ንቅናቄ መሪ ቆርኔሌዎስ ጃንሴን የተባለው ጳጳስ የተወሰኑ ሰዎች ለድኅነት ፡ የተወሰኑ ደግሞ ለመጥፋት ተመድበዋል የሚለውን ፕሬዴስቲኔሽን በሚል ስያሜ የሚታወቀውን የካልቪንን ትምህርት ስላስተማረ በኢየሱሳውያን ተከሶ ኢኖሴንት ዐሥረኛ በተባለው ፖፕ በ1653 ዓ·ም ሮም ውስጥ ተፈረደበት ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሮም ፖፕና በጃንሴኒያውያን መካከል የነበረው አለመግባባት በመሻሻል ፈንታ እየከረረ ስለሄደ ከጋሊካውያን ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጥረው ፖፖችን ይቃወሙ ነበር ። ቀጥሎም የሮሙ ፖፕ አይሳሳትም የሚለውን ውሳኔ ስለተቃወሙና ባጠቃላይ በፖፖቹ ላይ የተጠናከረ የፖለቲካ ትግል (ዘመቻ) ማካሄድ ስለጀመሩ በ1710 ዓ·ም በንጉሥ ሉዊስ ዐሥራ አራተኛ ከፈረንሳይ ስለተባረሩ ወደ ሖላንድ ሄደው



www.ethiopianorthodox.org

ተቀመጡ ። ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም በይፋ (በኦፊሴል) አልተገነጠሉም ።

3ኛ) ፌብሮኒአኒዝም (ፌብሮናዊ) ። ይህ ንቅናቄ በ18ኛው መቶ ዘመን ብዙ የጀርመን ጳጳሳት ፖፑ በመላ የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ያለውን ፍጹም የሆነ ሥልጣን በመቃወም የአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሥልጣን ከፖፑ በላይ መሆኑን አረጋገጠ ። ፖፑ በመጠኑ በእምነት ነክ ጉዳዮች ብቻ የበላይ ጠባቂ ሆኖ ፡ በየሀገሩ ያሉት የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት አቶኖሞስ ሆነው ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ በማለት ወሰነ ። ባጠቃላይ የዚህ ንቅናቄ ዋና ዓላማ የፖፑን ፍጹማዊ የሆነ ሥልጣን ለመቃወም ነበር ። በዚህ አኳኋን ከአውሮጳ ካህናትና ሕዝብ መካከል አብዛኞች ፖፑ በማዕከላዊነት ስለተጐናጸፈው ፍጹም የሆነ ሥልጣን የነበራቸው ድጋፍ እየተቀነሰ ሄደ። ሆኖም ይህ ንቅናቄ በዓላማ መሰሉ እንደነበረው እንደ ጋሊካኒዝም በመጀመሪያው የቫቲካን ጉባኤ የፖፑ አለመሳሳት ስለጸደቀ ደብዛው ጠፋ።

4ኛ) ጆሴፊዝም (ዮሴፋዊ) የኦውስትርያ ንጉሥ ዳግማዊ ዮሴፍ (1765 1790) ከናቱ ከማርያ ትሬዛ ጋራ ሀገሪቱን ይገዛ በነበረበት ወቅት በግዛቱ የነበረችውን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ከአስተዳደሩ ሥር አደረጋት ። በገዳማቱ ላይም ከፍ ያለ ተጽእኖ አደረገ ። ይህንኑ ሕገ ወጥ ድርጊት በሰላማዊ መንገድ ለማርገብ በማሰብ ፒዮስ ስድስተኛ (1775 1799) የተባለው ፖፕ በጉብኝት ስም ቪየና ቢሄድ ተገቢ አቀባበል ስላልተደረገለት አዝኖ ወደ ሮም ተመለሰ ። ሆኖም ከንጉሡ ዕረፍት በኋላ የንቅናቄው ደብዛ ጠፋ ።

የፖፖች ቀኝ እጅና ጠንካራ ደጋፊ የነበሩት ኢየሱሳውያን በጃንሴኒዝምና በጋሊካኒዝም ላይ ያደረጉት ተቃውሞ ያላስደሰታቸው የፖርቱጋል፡ የፈረንሳይ ፡ የእስጳኝና የሲሲሊ መንግሥታት የተለያዩ ወንጀሎችን ሠርተዋል የሚል የሐሰት ክስ መሥርተው ሀብታቸውን እየወረሱ አባረሩአቸው ። ፖፖችም በኢየሱሳውያን ላይ የተፈጸመው ግፍ ሕገ ወጥ መሆኑን በመግለጽ ስደቱ እንዲገታ ለመንግሥታቱ ጥያቄ ቢያቀርቡም ሰሚ አጡ ።

እላይ የተጠቀሱት መንግሥታት መሪዎች ተጽእኖ ስላበዙበት ፡ ጥያቄአቸውንም ቢቃረን ወደ ፕሮቴስታንት እምነት ያዘነብላሉ ብሎ



www.ethiopianorthodox.org

ስለፈራ ቀሌምንጦስ ዐሥራ አራተኛ የተባለው ፖፕ በ1773 ዓ·ም የደጋፊዎቹን የኢየሱሳውያን ድርጅት እንዲፈርስ በይፋ ዐዋጀ ። ይህና የመሳሰሉት ድርጊቶች የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ መንግሥታት በቤተ ክርስቲያን ላይ የነበራቸውን ተጽእኖና የፖፖችን እየተዳከሙ መሄድ ይገልጸል ። ሆኖም የካቶሊክን እምነት የሚከተሉ መሪዎች ከሚገዙአቸው ሀገሮች የተባረሩት ኢየሱሳውያን የፖፑን ትእዛዝ በማይ ቀበሉት አውስትርያ ፣ ራሽያና ፕሩሲያ ውስጥ መጠጊያ አገኙ ። ከጊዜ በኋላ ግን የኢየሱሳውያን ድርጅት በአጠቃላይ ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እድገት ጠቃሚ መሆኑ ስለታመነበት በ1814 ዓ·ም በፒዮስ ሰባተኛ እንደገና ተቋቁሞ ተግባሩን ያከናውናል ።

## ቀ) ከፈረንሳይ አብዮት (ሪቮሉሽን) እስከ አንደኛው የዓለም ጦርነት ድረስ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (1789–1918)

### (1) የፈረንሳይ አብዮት በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያስከተለው ጥፋት

ፍትሕን ፣ እኩልነትንና አንድነትን ለፈረንሳይ ሕዝብ ለማጐናጸፍ በ1789 ዓ·ም የተነሣው የፈረንሳይ አብዮት ሲጀመር በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥም ፍትሕ የሰፈነበት የአስተዳደር ፣ የተስተካከለ የደመወዝ አከፋፈል ወዘተ· ለውጥ (መሻሻል) እንዲደረግ የሚሹ ካህናት ደግፈውት ነበር ። በዚሁ ምክንያት በመጀመሪያ ሪቮሉሽኑ ቤተ ክርስቲያንን አልተቃወመም ነበር ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን አብዮታዊው መንግሥት ለተያያዘው ተግባር ማስፈጸሚያ እንዲረዳውና ክርስትናንም ቀስ በቀስ አዳክሞ ለማጥፋት በማሰብ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብት ወረሰ ። ለሮም ቤተ ክርስቲያንም በገጸ በረከት መልክ ይላክ የነበረው ገንዘብ ታገደ ። ከቤተ ክርስቲያኒቱም መሪዎች አብዛኞቹ ውርሱን በጥብቅ መቃወማ ቸው መንግሥቱን ስላስቆጣው በ1790 ዓ·ም ገዳማት እንዲዘጉ ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱም ከሮም ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላትን የአስተዳደር ግንኙነት አቋርጣ በመንግሥቱ ሥር እንድትተዳደር ፣ ከፈረንሳይ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሮም የሚላከው ገንዘብ እንዲቋረጥ ፣ ቀሳውስትና ጳጳሳትም ያለፖፑ ጣልቃ ገብነት (ፈቃድ) በመንግሥቱ ባለሥልጣኖችና በምእመናን



www.ethiopianorthodox.org

እየተመረጡ በመሾም ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ ፤ ባጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን በማገልገል ላይ ያሉ ካህናት ለአብዮታዊው መንግሥት ቃለ መሐላ እንዲያደርጉ ታዘዙ ። በነአቡነ ታሌይራንድ ቀስቃሽነት ጥቂት ካህናት ቃለ መሐላውን ፈጸሙ ። ሆኖም ከካህናቱ መካከል ቃለ መሐላውን ሁለት ሦስተኛው እጅ ስለተቃወመው ብዙ ካህናት ታሰሩ ። ጥቂቶችም ተገደሉ ። እንዲሁም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሕግ የማይፈቀደውን ጋብቻ እንዲፈጽሙ ከተገደዱት ካህናት መካከል ጥቂቶቹ አገቡ ።

ፒዮስ ስድስተኛ የተባለው ፖፕ ለመንግሥቱ ቃለ መሐላ አናደርግም ያሉትን ካህናት በመደገፍ በ1791 ዓ·ም የመንግሥቱን ትእዛዝና ቃለ መሐላ የፈጸሙትን ካህናት አወገዘ ። በዚህ ምክንያት የ1801 ዓ·ም ስምምነት (ኮንኮርዳንት) እስከ ተደረገ ድረስ በሮም ቤተ ክርስቲያንና በፈረንሳይ መንግሥት ዘንድ የነበረው ግንኙነት እንደሻከረ ቈየ ።

## (2) በናፖልዮን ቦናፓርትና በሮም (በካቶሊክ) ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል የተደረገው ስምምነትና ግጭት

ወጣቱ ጀኔራል ናፖልዮን ቦናፓርት በሥልጣን ላይ የነበረውን መንግሥት በመፈንቅለ መንግሥት ገልብጦ የመጨረሻውን ሥልጣን ከጨበጠ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፈረንሳይ ውስጥ በሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ ይካሄድ የነበረው ሥቃይ አከተመ ።

በ1798 ዓ·ም ናፖልዮን ወታደሮቹን በጄኔራል ቤርቲየር አዝማችነት ወደ ሮም ልኮ ከተማዋ ከተያዘች በኋላ ፒዮስ ስድስተኛ የተባለው የሰማንያ አንድ ዓመቱ ፖፕ ፈረንሳይ ውስጥ ወደምትገኘው ቫሌንስ ወደተባለች ቦታ ተወስዶ በእስር ሲኖር በ1799 ዓ·ም እዚያው ዐረፈ ። ሮምና ኢጣልያ በናፖልዮን ሠራዊት ተይዘው ስለነበር የፈረንሳይ ገዥዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እየያዙ ያስሩና ከሀገርም ውጭ ያባርሩ ነበረ ። በዚህ ምክንያት ተይዘው እንዳይታሰሩ የሰጉ ካርዲናሎች ወደ ውጭ ሀገር ተሰደው ይኖሩ ጀመር ። ፖፕ ፒዮስ ስድስተኛም በካርዲናሎች ላይ የሚደርሰውን መታሰርና ስደት አስቀድሞ ስለተረዳ ከእርሱ ዕረፍት በኋላ የሚተካውን ፖፕ የሚመርጥ ጠፋ በሚል ሰበብ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ችግር እንዳይደርስ በማሰብ ከካርዲናሎች አብዛኞቹ ተሰደው በሚኖሩበት ሀገር ውስጥ ምርጫው ቫቲካን ውስጥ በሚፈጸምበት መንገድ ተገቢውን ፖፕ እንዲመርጡ ቀደም ሲል ፈቅዶ



www.ethiopianorthodox.org

ነበር ። ከፖፑ ዕረፍት በኋላ የፈረንሳይ መንግሥት ጠላት የነበረው የአውስትርያው ንጉሥ ዳግማዊ ፍራንሲስ ቬኒስ እቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም ውስጥ ኮንክሌቭ የተባለውን የምርጫ ቦታ ስላዘጋጀላቸው እዚያ ሀገር በብዛት በስደት ይኖሩ የነበሩት አርባ ስድስት ካርዲናሎች በ1800 ዓ·ም ተሰብስበው በሕጋዊ መንገድ ፒዮስ ሰባተኛን ለፖፕነት መርጠው ሾሙ። እሱም በዚያው ዓመት ወደ ሮም ሲመለስ ሕዝቡ የጋለ አቀባበል አደረገለት ።

ናፖልዮን የፈረንሳይ ሕዝብ በሃይማኖት ምክንያት እየተነታረከ ተከፋፍሎ መኖር የሚያስከትለው ውጤት ድክመት መሆኑን ተረዳ ። የአውሮጳንም ሀገሮች በጦር ኃይል ድል አድርጎ ለመያዝ በቅድሚያ የሕዝቡ አንድነት መጠበቅ መገባቱን በመገንዘብ በ1801 ዓ·ም በናፖል ዮን አነሳሽነት በፖፕ ፒዮስ ሰባተኛና በፈረንሳይ ሪፑብሊክ መካከል የተፈረመው ስምምነት (ኮንኮርዳንት) በሀገሪቱ ውስጥ አንድነትና ሰላም እንዲሰፍን ረዳ ። የፖፑን ግዛቶች ይዘው የነበሩት የፈረንሳይ ወታደሮ ችም ለቀው ወጡ ። በስምምነቱም ውስጥ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሀገሪቱ ውስጥ መንፈሳዊ ተግባሯን በሰላምና በነጻነት እንድታስፋፋ ፣ ፖፑም በ1790 ዓ·ም የተወረሰው የቤተ ክርስቲያን ሀብት እንዲመለስ ላይጠይቅ ፣ ካህናትም ከመንግሥት ደመወዝ የሚሰጣቸው መሆኑ ፣ በሥልጣን ላይ ያሉት ጳጳሳት ወርደው አዲሶች ከተመረጡ በኋላ በፖፑ ትእዛዝ በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግ መሠረት እንዲሾሙ ፣ የካቶሊክ እምነት የመንግሥቱ ሃይማኖት ሳይሆን ፣ በሀገሪቱ ውስጥ የብዙኃኑ ሃይማኖት መሆኑ ፣ የአምልኮው ሥርዓት የሚፈጸመውም የሀገሪቱ ጸጥታ አስከባሪ ዎች ለማንኛውም ዜጋ በሚፈቅዱት መሠረት መሆኑ ወዘተ· ተገልጾ ነበር።

ምንም እንኳ ይህ ስምምነት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን መብት በመጠኑ የሚቀንስ ቢሆንም ቅሉ ፣ ካህናትና ምእመናን አምልኮታቸውን ያለምንም ሥጋት በነጻነት እንዲፈጽሙ አስችሏቸዋል ።

ይህም ፖፑ በቀጥታ ከአንድ መንግሥት ጋር ያደረገው የመጀመሪ ያው ኮንኮርዳት በአዲሱ የቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ውስጥ ከዚያን ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

ጀምሮ ከሌሎች መንግሥታት ጋር በየጊዜው ለተደረጉት ተመሳሳይ ስምምነቶች ሞዴል ፡ መሠረትና መንገድ ጠራጊ ሆነ ። ሆኖም በ1801 ዓ·ም ለተደረገው ስምምነት ማሻሻያና ማብራሪያ ነው በማለት ናፖልዮን ፖፑን ሳያማክር በ1802 ዓ·ም የጋሊካኒዝምን ተከታዮች የሚደግፈውን ኦርጋኒክ አርቲክልስ የተባለውን ሕግ አወጣ ። ይኸውም ሕግ ማንኛውም የፖፑ ትእዛዝና የአጠቃላይ ሲኖዶስ ውሳኔዎች ሁሉ ሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት ለመንግሥት ቀርበው መጽደቅ አለባቸው ፤ በቅድሚያ የመንግሥት ፈቃድ ያልተሰጠው ማንኛውም የፖፑ ተወካይ ፈረንሳይ ውስጥ ሊሠራ አይችልም ፤ ፈረንሳይ ውስጥ ያሉ ጳጳሳትም ያለመንግሥት ፈቃድ መንበረ ጵጵስናቸውን ትተው የትም ሊሄዱ አይችሉም ፤ ያለመንግሥት ፈቃድ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችን ሊከፍቱ አይችሉም ፤ ወዘተ· የሚል ነበር ።

ይህን ቤተ ክርስቲያንን እንደገና ከመንግሥት ቊጥጥር ሥር ያደረገውን ሕግ በመቃወም ፖፕ ፒዮስ ሰባተኛ የተቃውሞ ድምጹን ቢያሰማም ተቀባይ አጣ ። ምንም እንኳ ሕጉ ሙሉ በሙሉ ተግባር ላይ ባይውልም በ1905 ዓ·ም ቤተ ክርስቲያኒቱ ከመንግሥት እስከተለየችበት ጊዜ ድረስ በከፊል ሲሠራበት ኖሮአል ። በተጨማሪም ናፖልዮን ያለ ፖፑ ፈቃድ ለራሱ መንፈሳዊ ክብር በመሻት በያመቱ ነሐሴ 16 ቀን የቅዱስ ናፖልዮን በዓል ተብሎ እንዲከበር ወሰነ ። እንዲሁም ምእመናን እንዲወዱት ፤ እንዲያከብሩት ፤ ያለማመንታት እንዲታዘዙት ወዘተ· የሚረዳና የሚያብራራ የካቴኪዝም (የሰንበት ትምህርት) መጽሐፍ እንዲዘጋጅ አድርጎ በተግባር ላይ አዋለ ።

አብዛኛውን የፈረንሳይ ሕዝብና ካህናት ከሪፐብሊኩ ይልቅ የነገሥታት አስተዳደር የሚያስደስታቸው መሆኑን በመገንዘብ ፤ እንዲሁም ግዛቱን ለማስፋፋት የሚያደርገው ጥረት የሕዝቡን ሙሉ ድጋፍ ሊያገኝ የሚችለው ንጉሠ ነገሥት ሆኖ በመንገሥ ብቻ መሆኑን ስለተገነዘበ ፤ ናፖልዮን በ1804 ዓ·ም· በራሱ ሥልጣን የፈረንሳይ ንጉሠ ነገሥት እንዲሆን ወሰነ ። ነገር ግን ሹመቱ በፈረንሳይ ሕዝብ ዘንድ ሕጋዊ እንዲሆን ስለፈለገ ፓሪስ በሚገኘው በኖትርዳም ቤተ ክርስቲያን ፖፑ ተገኝቶ ሥርዓተ ንግሡን እንዲፈጽምለት ጠየቀው ። ፖፑም ጥያቄውን አልቀበልም ቢል በራሱና በፈረንሳይ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሊደርስ



www.ethiopianorthodox.org

የሚችለውን ጥፋት በመገንዘብ ጥያቄውን ተቀብሎ ወደ ፓሪስ ሄደ ። እዚያም እንደደረሰ እቴጌ ጆሴፊን ከናፖልዮን ጋር ያደረገችው ጋብቻ በቤተ ክርስቲያን ስላልተፈጸመ ባሰኘው ጊዜ ፈትቶ እንዳያባርራት በመስጋት ጋብቻቸው በተክሊል ያልተፈጸመ መሆኑን ለፖፑ ገለጸች ለት። በፖፑም ተጽእኖ ሥርዓተ ንግሡ ከመፈጸሙ በፊት ሥርዓተ ተክሊሉ ተፈጸመላቸው ። ሆኖም ከጥቂት ዓመታት በኋላ ጆሴፊኒን ፈትቶ አውስትርያዊቱን እቴጌ ማርያ ሉዊስን ኖትርዳም ቤተ ክርስቲያን በተክሊል አገባ ። በሕገ ወጡ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ላይ ባልተገኙ ካርዲናሎች ላይም ከፍ ያለ ቅጣት ተፈጽሞባቸዋል ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ሻልሳዊ ልዮን የተባለው ፖፕ በቻርልስ እራስ ላይ ዘውድ ጭኖ በማንገሡ ምክንያት ዘግየት ብለው የተነሡት ጎርጎርዮስ ሰባተኛ፣ ኢኖሴንት ሦስተኛ ወዘተ ከንጉሡ ቀብቶ ያነገሠው ፖፕ ይበልጣል ያሉት አስተሳሰብና እምነት እንዳይደገም በቅድሚያ በተስማሙት መሠረት ፖፑ ጸሎተ ንግሡን ፈጽሞ ከቀባው በኋላ ናፖልዮን እራሱ ዘውዱን በእጁ አንሥቶ በራሱ ላይ በመድፋት ነገሠ ። በዚሁ በዓል ምክንያት ፖፑ ፓሪስ ውስጥ ያደረገው ጉብኝት ለምእመናን ከፍ ያለ የመንፈስ እርካታ ሰጥቷል ።

ናፖልዮን በየጊዜው ድልን እየተቀዳጀ በሄደ ቍጥር ሀገሮችን በጦር ኃይል እያሸነፈ የመግዛቱ ሱስ እየባሰበት ስለሄደ ፣ ፖፑ የሱ ተባባሪ በመሆን በእንግሊዝ ላይ የሚያካሂደውን ዘመቻ እንዲደግፍና በፖፑ ግዛት ውስጥ ባሉ ወደቦች የእንግሊዝ መርከቦች እንዳይገለገሉ ጠየቀው ። ፖፑም አልስማማም ስላለና በፈረንሳይ መንግሥት የተወሰዱበት ግዛቶቹ እንዲመለሱለት ስለጠየቀ በ1809 ዓ·ም· የሮም ከተማና በጠቅላላ የፖፑ ግዛት በጦር ኃይል ተይዞ ከፈረንሳይ ግዛት ጋር እንዲቀላቀል አዘዘ ። ፖፑም ግዛቱን ያስወረረውን ናፖልዮንንና ተባባሪ ባለሥልጣኖችን ወዲያው በይፋ አወገዘ ። በዚህ አኳኋን ፖፑ የሀገር አገዛዝ ሥልጣኑን አለቅም ፣ ውግዘቱንም አላነሳም ስላለ ወዲያው ተይዞ መጀመሪያ ወደ ግሬኖብል ፣ ቀጥሎ ወደ ሳቮና ተወስዶ በስደትና በእስር መልክ ተቀመጠ።

ፖፑ በስደት በነበረበት ወቅት ጳጳሳት ላልነበራቸው ሀገረ ስብከ ቶች አዳዲስ ጳጳሳት እንዲሾም ፣ ግዛቱንም በፈቃደኝነት የለቀቀ መሆኑን በይፋ እንዲገልጽ ደጋግሞ ቢጠይቀው ስላልተቀበለውና እንግሊዞችም ከሳቮና ነጥቀው እንዳይወስዱት በማለት በ1812 ዓ·ም· ፖፑ ፓሪስ


www.ethiopianorthodox.org

አጠገብ ወደምትገኘው ወደ ፎንቴንብሌው ተዛውሮ በእስር እንዲቀመጥ አዝዞ ወደ ሩሲያ ለጦርነት ዘመተ ። ከሩሲያም ድል ሆኖ ከተመለሰ በኋላ በበሽታ ይማቅቅ የነበረውን ፖፕ ክፍት ለሆኑት ሀገረ ስብከቶች ጳጳሳት እንዲሾምለት አዘውትሮ ስለነዘነዘው በስድስት ወራት ውስጥ ጳጳሳት የሚሾም መሆኑን በመግለጽ ፈረመለት ። ይኸውም ፊርማ በምሥጢር የሚቀመጥ መሆኑን ለፖፑ ቃል ገብቶለት ነበር ። ናፖልዮን ግን የገባውን ቃል ኪዳን ወዲያው በማፍረስ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥቱ መካከል ሻክሮ የቈየው ግንኙነት ተሻሻለ በማለት የፖፑ ፊርማ የሠፈረበትን ጽሑፍ አሳትሞ አወጣው ። በምሥጢር ይቀመጣል የተባለው ጽሑፍ በግልጽ ታትሞ መውጣቱን ፖፑ ቢቃወምም ቅሉ ፣ ከማንም ሰው ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ ስለተከለከለ ተቃውሞው በሕዝብ ዘንድ ሊታወቅ አልቻለም ።

ናፖልዮን በ1813 ዓ·ም ተባብረው በተነሡበት መንግሥታት በማያዳግም ሁኔታ ከፋኛ ድል ከተመታ በኋላ በእስር ይማቅቅ የነበረውን ፖፕ ፈታው ። ፖፑም ከአምስት ዓመት በእስር መጉላላት በኋላ በሳቮና በኩል ተጉዞ በ1814 ዓ·ም ሮም ሲገባ ከሕዝቡ ታላቅ አቀባበል ተደረገለት ።

ፓሪስም በ1814 ዓ·ም ናፖልዮንን በጋራ ድል በአደረጉት በእንግሊዝ ፣ በሩሲያ ፣ በፕሩሲያና በአውስትርያ የጦር ኃይሎች በመያዟ የናፖልዮን መንግሥት አከተመ ። ድል አድራጊዎች መንግሥታትም ቪየና ውስጥ በ1814–1815 ዓ·ም ተሰብስበው የፈረንሳይ አብዮት ተወግዶ በፈረንሳይ የጥንቱ የነገሥታት አገዛዝ እንዲቀጥል ፣ ፖፑም በግዛቱ ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዲኖረው ወሰኑ ።

## በ) ሰፊው የፖፖች ምድራዊ ግዛት መዳከም

የኢጣልያ ማዕከላዊ ክፍልና ፈረንሳይ ውስጥም አቪኞን የተባለችው ከተማ የሮም ፓፖች ምድራዊ ግዛት እንደነበሩ ቀደም ሲል ተመልክተናል።

የኢጣልያ ሕዝብ ብሔራዊ አንድነቱን ለመመሥረት ስለተነሣ በኅቡዕ ድርጅቶቹ አማካይነት የፖፖችን የፈላጭ ቆራጭነት አገዛዝ የሚቃወም ንቅናቄ ጀመረ ። ከናፖልዮን ድቀት በኋላ ቪየና ውስጥ



www.ethiopianorthodox.org

በተሰበሰቡት የጦር ጓዶች ውሳኔ መሠረት ተመልሶ የተሰጠው የፖፑ ግዛት ዕድሜ ማክተሚያ እየተቃረበ ሄደ ። ፈረንሳይ ውስጥ የነበረው የፖፑ ግዛት ግን በ1791 ዓ·ም በአዲሱ የፈረንሳይ ሪፑብሊክ እንደተወሰደ ቀርቷል ።

ፒዮስ ዘጠነኛ (1846–1874) የተባለው ፖፕ የተራማጆችን (የሊብራሎችን) ሐሳብ በመደገፍ በ1848 ዓ·ም በግዛቱ የሚኖሩ ዜጐች የመንግሥቱ አስተዳደር ተካፋይ እንዲሆኑ የሚያስችልና ሌሎችም ነገሥታት የሱን ምሳሌ በመከተል ሕዝባቸውን በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንዲያስተዳድሩ የሚረዳ የዲሞክራሲን ሥርዓት የተከተለ ሕገ መንግሥት ስላወጣ ሕዝቡ በደስታ ተቀበለው ። ነገር ግን በተስፈንጣሪ (በራዲካል) ሪቮሉሽናሪዎች ፔሌግሪኖ ሮሲ የተባለው የፖፑ ግዛት ጠቅላይ ሚኒስትር በ1848 ዓ·ም ሲገደል የተመለከቱ የበላይ ባለሥልጣኖች ድርጊቱን በመደገፍ ያሳዩት የግድየለሽነት አቋምና በቦታው ከተገኘው ሕዝብ አብዛኛው ያሳየው ፌስታ (ደስታ) ስላስቆጣው ፒዮስ የሰጠውን የተሻሻለ ሕገ መንግሥት ሰረዘው ። በዚህ ምክንያት የፖፑና የሊብራል ሪቮሉሽናሪስቶች ግንኙነት በመቋረጡ ወዲያው ሮም ውስጥ ሪቮሉሽን ስለተጀመረ (ስለተቀጣጠለ) ፖፑ በ1848 ዓ·ም ናፕልስ ወደምትገኝ ጋኤታ ወደ ተባለች ከተማ ሸሽቶ አመለጠ ። በካህናት ላይ ከፍተኛ ጥላቻ የነበራቸው ሊብራሎች የሪቮሎሽኑ መሪዎች ማዚኒ ፣ ጋሪባልዲ ወዘተ· የጦር ሠፈራቸውን ቱሪናል እተባለው እፖፑ ቤተ መንግሥት አድርገው በ1849 ዓ·ም ሮም ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ በማቋቋም የፖፑ ግዛት ማክተሙን በዓዋጅ ገለጹ ። ፖፑም ከግዛቱ ያስወጡትን በጦር ኃይል ደምስሰው ግዛቱን እንዲያስመልሱለት በመማጸን ለፈረንሳይና ለአውስትርያ መንግሥታት ጥያቄ አቀረበ ። በፖፑ ጥያቄ መሠረት በፈረንሳይ ፕሬዚዳንት በሉዊስ ናፖልዮን (ሣልሳዊ ናፖልዮን) የተላከው ሠራዊት ሮምን ሲይዝ ፣ በአውስትርያ መንግሥት የተላከው ሠራዊት ደግሞ ሌላውን የፖፑን ግዛት ያዘ ። ፖፑም በፈረንሳይ ወታደሮች እርዳታ በ1850 ዓ·ም ወደ ሮም ተመልሶ በግዛቱ ላይ የፈላጭ ቆራጭነት አስተዳደር ቀንበር ጫነበት ። ይህ ዓይነቱ አስተዳደር የተቃዋሚዎቹን የጥላቻ ስሜት ስላባባሰው በሰርዲኒያ ፒኤድሞንት ንጉሥ በዳግማዊ ቪክቶር ኢማኑኤል (1849–1878) መሪነት በፖፑ ፣ በአውስትርያና በፈረንሳይ መንግሥታት ፣ በተለያዩ የሀገሪቱ መሳፍንት



www.ethiopianorthodox.org

ተገነጣጥለው ይገዙ የነበሩትን የኢጣልያ ክፍላተ ሀገር በጦር ኃይል አንድ አድርጎ ለማስተዳደር ቱሪን ውስጥ የተነሣው ንቅናቄ እንደ እሳተ ገሞራ ሊታገድ የማይቻል ሆነ ። የፖፑ ግዛት እንዲያከትምና የኢጣልያ ብሔራዊ አንድነት እንዲሰፍን ከደከሙት መሪዎች ዋነኛው የንጉሥ ቪክቶር ኢማኑኤል ግዛት የነበረችው የሳርዲኒያ ፒኤድሞንት ጠቅላይ ሚኒስትር ካሚሎ ካቡር (1852–1861) ነበር ። እሱም እንደነ ጋሪባልዲ ምድራዊ ግዛታቸውን እንዳያጡ በማሰብ የኢጣልያንን አንድ መሆንና ነጻ መውጣት የሚቃወሙትን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ባለ ሥልጣኖችን በጣም ይጠላ ነበር ። እንዲሁም እነ ጋሪባልዲ ሮምን በያዙበት ወቅት እንዳደረጉት ሁሉ ካቡርም ሳርዲኒያ ፒኤድሞንት ውስጥ በቤተ ክርስቲያኒቱ ይካሄድ የነበረው ትምህርትና ፍርድ ቤት ተቋርጦ በመንግሥት ቊጥጥር ሥር ሆኖ በዓለማውያን ምሁራን እንዲካሄድ አድርጓል ። ከአንዳንድ በበጎ አድራጎት ተግባር ላይ ከተሰማሩ ገዳማት በስተቀር ሌሎቹ እንዲዘጉ ፤ ሊብራሎችም በመንግሥቱ ጋዜጦች ቤተ ክርስቲያንን በመወንጀል እንዲጽፉ ወዘተ· አድርጓል ።

ዳግማዊ ቪክቶር ኢማኑኤል በፖፑ ሥር ይተዳደሩ የነበሩትን ግዛቶች በጦር ኃይል እያስለቀቀ የኢጣልያንን ብሔራዊ አንድነት ከመሠረተ በኋላ በ1861 ዓ·ም ፍሎሬንስ ውስጥ የኢጣልያ ንጉሥ መሆኑን በዐዋጅ ገለጸ ። ሆኖም ሮም በሣልሳዊ ናፖልዮን ትእዛዝ ፖፑን ለመርዳት በተሠማራ የፈረንሳይ ሠራዊት ትጠበቅ ስለነበር ከተማዋን ከኢጣልያ ግዛት ጋር ለመቀላቀል ያደረገው ሙከራ ሳይሳካለት ከቈየ በኋላ ፤ ፈረንሳይ ከፕሩሲያ ጋር ከ1870–1871 ዓ·ም ባካሄደችው ጦርነት ላይ ለማሠማራት ወታደሮቿን በ1870 ዓ·ም ከሮም ስታስወጣ ወዲያው የቪክቶር ኢማኑኤል ወታደሮች ሮምን ያዙ ። በዚህ አኳኋን ከአንድ ሺህ ዓመት በላይ ዕድሜ የነበረው ሰፊው የፖፖች ምድራዊ ግዛት አከተመ ። ፖፑም ሮም ውስጥ ከቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በምትገኘው ቫቲካን በተባለች ከተማ ተወስኖ ተቀመጠ ።

ቪክቶር ኢማኑኤልም በ1871 ዓ·ም ቤተ መንግሥቱን ሮም ውስጥ በነበረው ኲሪናል እተባለው እፖፑ ቤተ መንግሥት ውስጥ አደረገ ። ሮም የአዲሱ የኢጣልያ መንግሥት መናገሻ ከተማ መሆኗ በዐዋጅ ተገለጸ ።

ፖፑ ቫቲካን ውስጥ ሆኖ ያሳለፈው የተቃውሞ ውግዘት ተቀባይ


www.ethiopianorthodox.org

ሊያገኝ አልቻለም ነበር ። ንጉሡም ለፖፑ የተወሰነ ገንዘብ የሚሰጥ መሆኑን ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ያለምንም መሰናክል መንፈሳዊ ተግባሯን ለማከናወን የምትችል መሆኗን ፤ የፖፖችም ክብር በሕግ የተጠበቀ መሆኑን ወዘተ· የሚያረጋግጥ ሕግ በማውጣት እንዲስማሙ ቢጠይቀው ፤ ፖፑ ሲሾም ከቤተ ክርስቲያኒቱ ግዛት አንዳችም ክፍል አሳልፎ ላይሰጥ በገባው ቃለ መሐላ መሠረት አሻፈረኝ በማለት የአዲሱን የኢጣልያ መንግሥት ሕጋዊነት ሳይቀበል ቫቲካን ውስጥ እንደ እስረኛ ሆኖ መኖርን መረጠ ። ፖፑ ካቶሊኮች በአዲሱ የኢጣልያ መንግሥት እንደመምረጥና መመረጥ ወዘተ· በመሳሰሉ ተግባራት ላይ እንዳይሳተፉ በ1874 ዓ·ም ስለከለከለ ፤ ለፖፑ ታማኝ የነበሩ ምእመናን እገዳው በፖፕ ቤኔዲክት ዐሥራ አምስተኛ በ1919 ዓ·ም እስከ ተነሣበት ጊዜ ድረስ በገዛ ፈቃዳቸው ከመንግሥቱ የዕለት ከዕለት የተግባር እንቅስቃሴ መካፈሉን አቋረጡ ። በተቃራኒው ወገን ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚ የነበሩት ራዲካሎች ያለምንም ተቀናቃኝ የኢጣልያ ሕዝብና መንግሥት በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ጥላቻን እንዲያሰፍን ለመቀስቀስና ለመገፋፋት አጋጣሚ ዕድል አገኙ ። ሆኖም ከፒዮስ ዘጠንኛ ቀጥለው የተነሡት (የተሾሙት) ሦስት ፖፖች ከመንግሥቱ ጋር አንዳችም ስምምነት ላይ ሳይደርሱ ለ59 ዓመታት ከቈዩ በኋላ በሙሶሊኒ የተመሩት ፋሽስቶችና የራሻን መንግሥት ዱካ የተከተሉ ኮሚኒስቶች በኢጣሊያ ፓርላማ ውስጥ ሚና ለይተው ይፋጁ ነበር ። ሙሶሊኒም ኮሙኒስቶችን ድል ነሥቶ ሙሉ ሥልጣን ለመጨበጥ የሚችለው ከፖፑ ጋር ሲተባበር ብቻ መሆኑን ስለተረዳ ፤ ፖፑም ከኮሙኒስቶች ጋር ከመስማማት ይልቅ የአቴይስትነት ዝንባሌ ከነበረው ከሙሶሊኒ ጋር መስማማቱ በመጠኑም ቢሆን የተሻለ መስሎ ስለታየው ፤ ፒዮስ ዐሥራ አንደኛ (1922–1939) የተባለው ፖፕ በ1929 ዓ·ም ከሙሶሊኒ ጋር የላቴራንን ስምምነት (ኮንኮርዳት) በማድረግ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና በአዲሱ የኢጣልያ መንግሥት መካከል ከሮ የቈየው አለመግባባት ሰላማዊ መፍትሔ አገኘ ። በዚህ ስምምነት መሠረት ፖፕ ፒዮስ ቀደም ሲል ለዘመናት በፖፖች ሲተዳደር የነበረውን ማዕከላዊ ኢጣልያንና የሮማን ከተማ ግዛት ማክተም አረጋገጠ ። የቫቲካን ከተማ ነጻ ግዛት ሆና በፖፖች ሥልጣን ሥር እንድትተዳደር ሆነ ። ከቫቲካን ውጭም የላቴራን ቤተ መንግሥት ፤ የካስቴል ጋንዶልፎ ቪላ ፤



www.ethiopianorthodox.org

የቅድስት ማርያም ማጅአሬ ፣ የቅዱስ ጳውሎስ ወዘተ· ካቴድራሎችና አንዳንድ ታላላቅ ሕንጻዎች በፖፑ ሥር እንዲተዳደሩ ፤ የግል ዘቦችም ለማቋቋም መቻሉ ተወሰነ ። የቫቲካን ነጻ መንግሥት ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ መንግሥታት አምባሳደሮች በመላክ ግንኙነታቸውን መሥርተዋል ። እንዲሁም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እምነት ብቸኛ የመንግሥቱ ሃይማኖት መሆኑን ፤ በትምህርት ቤቶችም የሃይማኖት ትምህርት የሚሰጥ መሆኑ ወዘተ· በኮንኮርዳንት ጸደቀ ። ሆኖም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና በኢጣልያ መንግሥት መካከል በ1929 ዓ·ም ጸድቆና ተፈርሞ ሲሠራበት የቈየው ስምምነት በ1984 ዓ·ም ተሻሽሎ የካቶሊክ እምነት የመንግሥቱ ሃይማኖት መሆኑ መቅረቱ ፤ በየትምህርት ቤቶችም የሃይማኖት ትምህርት ፈቃደኞች ለሆኑት ብቻ እንጂ በግዴታ ለሁሉም እንዳይሰጥ ወዘተ· የሚያደርግ ኮንኮርዳት (ስምምነት) በቫቲካንና በኢጣልያ መንግሥት መካከል ተፈርሟል ።

## ተ) መጀመሪያው የቫቲካን (ሃያኛው አጠቃላይ) ጉባኤ (1869–1870)

ፒዮስ ዘጠንኛ በእምነትና በአስተዳደር የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተነጋግሮ ውሳኔ የሚሰጥ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ለመጥራት ማሰቡን በ1867 ዓ·ም የቅዱስ ጴጥሮስንና የቅዱስ ጳውሎስን አንድ ሺህ ስምንት መቶኛ ዓመት የሰማዕትነት መታሰቢያ በዓል ለማክበር ሮም ውስጥ ተሰብስበው ለነበሩት ሃያ አንድ ካርዲናሎችና ጳጳሳት ገለጸላቸው ። ከነሱም አብዛኞቹ ሐሳቡን በመደገፍ ስለተስማሙ በዓለም ለሚገኙ የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በ1869 ዓ·ም ቫቲካን በሚከፈተው አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ተካፋይ እንዲሆኑ የጥሪ ደብዳቤ ላከ ። ከ700 በላይ የሆኑ ጳጳሳት በተገኙበት በፒዮስ ሊቀ መንበርነት በ1869 ዓ·ም መጀመሪያው የቫቲካን ጉባኤ ተከፈተ ። በጉባኤው ላይ በመሠረተ ሃይማኖት ፣ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና በሕገ ቤተ ክርስቲያን ፤ ሊብራሊዝም ባስከተላቸው ክሕደቶችና በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ተነጋገሩ ። ወዲያውም የሮም ከተማ በቪክቶር ኢማኑኤል ሠራዊት መያዝ የጉባኤውን ሂደት እንዳያደናቅፍ በማሰብ በ1870 ዓ·ም የፖፑ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበላይ መሆኑንና


www.ethiopianorthodox.org

በመንበሩ ላይ ተቀምጦ እምነትና ሞራል ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሲወስን (ሲናገር) የማይሳሳት መሆኑን የሚገልጹትን ውሳኔዎች አንዳንድ ሊብራሎች ቢቃወሙም ቅሉ ፥ በአብዛኞዎቹ የጉባኤው አባላት ስለ ተደገፉ ዶግማ (መሠረተ ሃይማኖት) ሆነው ከጸደቁ በኋላ ጉባኤው ተፈጸመ ።

በዚህ አኳኋን ፖፑ ምድራዊ ግዛቶቹን በጦር ኃይል ቢገፈፍም ቅሉ በመንፈሳዊው ወገን (በኩል) በቫቲካን ጉባኤ ውሳኔ መሠረት እጅግ ድርብ ክብርን ተጐናጸፈ ።

አብዛኞቹ የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ምእመናን የቫቲካንን ጉባኤ ውሳኔ ሲቀበሉ ፥ ጀርመንና አውስትርያ ውስጥ ብቻ ጥቂት ተቀዋሚዎች ተነሥተው ነበር ። እነሱም ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተለይተው "ጥንታውያን (አሮጌ) ካቶሊኮች" በሚል ስም ይጠራሉ ።

## ቸ) ጥንታዊት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን

ከላይ እንደተመለከትነው የቫቲካን ጉባኤ ውሳኔ ተቃዋሚዎች ንቅናቄ በጀርመን ውስጥ እየተጠናከረ ስለሄደ በ1870 ዓ·ም የቦን ዩኒቨርሲቲ የቴዎሎጂ መምህራን ኮንግስዊንተር ፥ ኑሬምበርግ ወዘተ· በተባሉ ከተሞች ስብሰባ አድርገው ብዙ ሊቃውንትና ካህናት በተገኙበት ከተወያዩ በኋላ የቫቲካንን ጉባኤ ውሳኔዎች በጥብቅ መቃወማቸውን ገለጹ ። ይህንኑ ተቃውሞ የብሬስላው ፥ የሙኒክና የብራውንስበርግ ዩኒቨርሲቲዎች መንፈሳውያን መምህራን ደገፉ ።

ይኸው ንቅናቄ እየገፋ ሄዶ በ1871 ዓ·ም ሙኒክ ውስጥ የተሰበሰበው የመጀመሪያው ኮንግሬስ ካህናትና ምእመናን የሚከተሏት "ጥንታዊት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን" እንድትባል ወስኖ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለመጨረሻ ጊዜ መለየቱን በይፋ ገለጸ ። በ1874 ዓ·ም ሪንኬንስ የተባለው የብሬስላው ዩኒቨርሲቲ የቴዎሎጂ መምህር ተመርጦ ሄካምፕ በተባለው ጃንሴንስታዊ የኡትሬቼት ጳጳስ ተቀብቶ የመጀመሪያው የጥንታዊት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ሆነ ።

ይህች ቤተ ክርስቲያን እንደ ግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያዎቹ ሰባቱ ጠቅላላ የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤዎች የተወሰኑትንና በ1054 ዓ·ም የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከመለየቷ በፊት የተወሰኑትን የሃይማኖት ትምህርቶች ትቀበላለች ። ካህናቶቿም እንዲያገቡ ትፈቅዳለች ። በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸ



www.ethiopianorthodox.org

መው ሥርዓተ ቅዳሴም ሕዝቡ በሚረዳው ቋንቋ ነው ። እንዲሁም የዚች ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን ማዕርገ ክህነት ሕጋዊነት በ1925 ዓ·ም ተቀብለው ከቈዩ በኋላ ፣ በ1932 ዓ·ም ቦን ውስጥ በተደረገው ስምምነት መሠረት ከእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ጋር በእም ነት ሙሉ ግንኙነት አድርገዋል ።

ተከፋፍለው የነበሩትን የጀርመን ክፍለ ሀገሮች በ1871 ዓ·ም ከትውልድ ሀገሩ ከፕሩሲያ ጋር በጦር ኃይል አንድ ያደረገው የፕሮቴስታ ንት እምነት ተከታይ የነበረው መጀመሪያው የጀርመን ኤምፓየር ቻንስለር ቢስማርክ ጥንታዊት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን በመደገፍ ከሮም ፖፕ ተጽእኖ ነጻ የሆነች ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን መሥርቶ ፣ በዚችው ቤተ ክርስቲያን ድጋፍ የተከፋፈሉትን የጀርመን ግዛቶች አንድ ለማድረግና እቅዶቹን ከግባቸው ለማድረስ በማሰብ ሙሉ ድጋፍ አደረገ ላት ። ነገር ግን በጀርመን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች የሚኖሩባቸው ክፍላተ ሀገር በማዕከላዊ ፓርቲያቸው አማካይነት ጥቅማ ቸውን ለማስጠበቅ በፓርላማ ውስጥ ቢስማርክን መቃወም ጀመሩ ። ይኸው ተቃውሞ ስላስቆጣውና የጀርመን ካቶሊኮች የፖፑን ትእዛዝ እስከተቀበሉ ድረስ በሕዝቡ ዘንድ የብሔርተኝነት ስሜት በቀላሉ ሊሰፍን የማይችል መስሎ ስለታየው ከ1872 ዓ·ም ጀምሮ በጀርመን የምትገኘዋን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለማዳከም መጨቆን ጀመረ ። ይኸውም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ቍጥጥር ሥር እንድት ሆን ፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች ይሰጥ የነበረው የሃይማኖት ትምህርት በመንግሥቱ ቍጥጥር ሥር እንዲውል ፣ ጋብቻም በቤተ ክርስቲያን መፈጸሙ ቀርቶ በማዘጋጃ ቤት እንዲፈጸም ወዘተ· አደረገ ። ኢየሱሳውያንንም ከሀገር አባረረ ። በቫቲካንና በጀርመን መንግሥት መካከል የነበረውን የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ሠረዘ ። ሆኖም እላይ የተጠቀሱት ትእዛዞች በሮሙ ፖፕ በፒዮስ ዘጠንኛ በ1875 ዓ·ም ተወገዙ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናንም በኅብረት ተነሣሥተው ትእዛዞችን በተግባር ላይ አናውልም በማለታቸው ፣ ከሶሻሊስቶችና ከማዕከላዊው ፓርቲ አባላትም ዘንድ ፓርላማ ውስጥ ተቀዋሚ ስለበዛበት ቢስማርክ ልዮን ዐሥራ ሦስተኛ (1878–1903) ከተባለው ፖፕ ጋር ባደረገው የዕርቅ ስምምነት መሠረት በ1886 ዓ·ም


www.ethiopianorthodox.org

ትእዛዞቹን እነሣ ።

ጥንታዊት ካቶሊካዊት (የአሮጌ ካቶሊኮች) ቤተ ክርስቲያን ስዊዘር ላንድ ፣ አውስትርያ ፣ አሜሪካ ወዘተ· ውስጥ ተከታዮች አሏት ።

## ጎ) ሁለተኛው የቫቲካን (ሃያ አንደኛው አጠቃላይ) ጉባኤ (1962–1965)

ዮሐንስ ሃያ ሦስተኛ የተባለው ፓፕ (1958–1963) በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የቤተ ክርስቲያኒቱ የትምህርት አሰጣጥ ፣ የዲሲፕሊን ፣ የአስተዳደር ፣ የሶሻል ሂደት ወዘተ· ተገቢው መሻሻል እየተደረገለት በአፋጣኝ በሥልጣኔ ከተራቀቀውና የተለያዩ የሶሻል ፣ የፖለቲካ ወዘተ· ለውጦችን ካስከተለው ከአዲሱ ዘመን ሁኔታ ጋር በማስተካከል (በማዛመድ) ቤተ ክርስቲያን ከዘመኑ ጋር አብራ ለመራመድ እንድትችል የሚረዳ ፤ እንዲሁም በምዕራብና በምሥራቅ ካሉት የፕሮቴስታንትና የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በውይይት (በዲያሎግ) ቀስ በቀስ አንድነት ሊመሠረት የሚቻልበትን መንገድ የሚቀይስ አጠቃላይ ጉባኤ የሚጠራ መሆኑን በ1959 ዓ·ም በጥንታዊው በቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ አስታወቀ ። በሦስት ዓመት ውስጥ ቅድመ ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ በ1962 ዓ·ም ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከየሀገሩ የሄዱ ከ2500 በላይ ካቶሊካውያን ጳጳሳት (አባቶች) በተገኙበት ተከፈተ ። በተመልካችነት እንዲገኙ የተጋበዙ የአርየንታል ፣ የግሪክ ኦርቶዶክስና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮችም በጉባኤው ላይ ተገኝተዋል ።

ጉባኤው ከመደረጉ ቀደም ሲል በአንዳንድ ሀገሮች ሥርዓተ ቅዳሴው ሕዝቡ በሚረዳው በራሱ ቋንቋ መፈጸም ቢጀመርም እንኳ ፣ በጉባኤው ላይ የተሰበሰቡት ጳጳሳት ግልጽ የሆነ ውሳኔ እንዲሰጡበት ሥርዓተ ቅዳሴው በላቲን ብቻ መፈጸሙ ቀርቶ ሕዝቡ ወደሚረዳቸው ዘመናዊ ቋንቋዎች ተተርጉሞ እንዲቀርብ ፤ መጽሐፍ ቅዱስ በካህናት ብቻ ሳይሆን በምእመናንም በሰፊው እንዲጠና ፤ ቅዱስ ቊርባንም ቢቻል ሁልጊዜ ያለበለዚያ በበዓላት ቀናትና የጋብቻ ተክሊል በሚፈጸምበት ጊዜ በሁለቱም በኅብስትና በወይን እንዲቀርብ ወዘተ· የሚሉ ሐሳቦች ቀረቡ ። በነዚሁ ሐሳቦች ላይ በወግ አጥባቂዎችና በተራማጆች መካከል



www.ethiopianorthodox.org

ሰፊ ውይይት ከተደረገ በኋላ የጀርመን ፡ የቪየና ፡ የቤልጅግ ፡ የቶኪዮ ፡ የችካጐ ፡ የፈረንሳይ ፡ የሰሜን ኢጣልያ ፡ የላቲን አሜሪካ ፡ የአፍሪካ ወዘተ· ጳጳሳት ስለደገፉት ሐሳቡ በተግባር እንዲተረጐም ተወሰነ ።

ጉባኤው ተግባሩን በማካሄድ ላይ እንዳለ በ1963 ዓ·ም ፖፕ ዮሐንስ ስላረፈ ወዲያው ጳውሎስ ስድስተኛ የተባለው ፖፕ (1963–1978) ተመርጦ ጉባኤው ቀጠለ ። እሱም ፖፕ ዮሐንስ ስለ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ፤ ስለ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት በውይይት መቀራረብና አንድ መሆን ወዘተ· የተለመውን ፈለግ በመከተል ጉባኤው የታቀደለትን ግብ እንዲመታ የሚደክም መሆኑን ገለጸ ። በጉባኤውም ላይ ከምእመናን ወንዶችና ሴቶች በተመልካችነት እንዲካፈሉ ተደርጓል ።

እንዲሁም በጉባኤው የሩቅ ጊዜ ዓላማ (እቅድ) መሠረት ፖፕ ጳውሎስ ስድስተኛ በ1964 ዓ·ም ከግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪ ከዓለም ፓትርያርክ ከአቲናጐራስ ጋር ተገናኝቶ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተፈጠረው አሳዛኝ መለያየት ቀስ በቀስ ተወግዶ አንድነት በሚመሠረትበት መንገድ ላይ ለመወያየት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ። እዚያም የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ተገናኝተው ያለፈው ጥል ተረስቶ ለወደፊት ሰላምና አንድነት ስለሚመሠረትበት መንገድ ከተወያዩ በኋላ ወደ ቫቲካን ተመልሶ ጉባኤው ሥራውን ቀጠለ ።

የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ተገናኝተው አንድነት ስለሚፈጠርበት መንገድ ያደረጉት ውይይት ከፍሎሬንስ ጉባኤ ወዲህ የመጀመሪያ ጊዜ መሆኑ ነው ።

ፖፕ ጳውሎስ ስድስተኛ በ1971 ዓ·ም ጀኔቭ ያለውን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ቋሚ ጽሕፈት ቤት ጐብኝቶ እዚያው ከሚኖሩት የፕሮቴስታንት ፡ የግሪክ ኦርቶዶክስና የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ጋር ጸልዮአል ።

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሃያኛው መቶ ዘመን በፕሮቴስታንት ፡ በግሪክ ኦርቶዶክስና በኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ከተጀመረው ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ንቅናቄ (ጉባኤ ፡ ማኅበር) ጋር በሙሉ አባልነት ሳይሆን በአንዳንድ መስኮች ተባብራ እንድትሠራ በዚሁ በሁለተኛው በቫቲካን ጉባኤ ተፈቅዷል ።

በጉባኤው ላይ ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን ስለሚያደርጉት እስተ



www.ethiopianorthodox.org

ዋጽኦና ስለ ክርስትና መስፋፋት የሚጫወቱት ሚና ፤ ቤተ ክርስቲያን አዲሱን ትውልድ እንዴት ማገልገል እንደሚገባት ፤ ስለ ካህናት አሰለጣጠንና አኗኗር ፤ ስለ ሚስዮናውያን ተግባራት ፤ የክርስትና ትምህርት በሰፊው ስለሚሰጥበት መንገድ ፤ ስለ ኢኩሜኒዝም ፤ ለያንዳንዱ ዜጋ የእምነት ነጻነት ስለመስጠት ፤ ምእመናን ሁሉ በየጊዜው በሚደረገው ጸሎተ ቅዳሴ በፍላጎት ተካፋይ እንዲሆኑ ስለሚያስችለው (ስለሚረዳው) በ1909 ዓ·ም ስለተጀመረው ሊተርጅካል ሙቭሜንት ወዘተ· ውሳኔዎች ተሰጡ ።

እንዲሁም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ አባላት ከሆኑ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች (ወኪሎች) ጋር በውይይት የሚያቀራርብ ጽ/ቤት መሥርታ በየጊዜው በክርስቲያኖች መካከል ሊኖር ስለሚገባው መቀራረብና አንድ መሆን ውይይት ታደርጋ ለች ። በዚህ ጉባኤ በዘመናችን ለክርስትና መስፋፋት ጠቃሚ የሆኑ ውሳኔዎች ሲተላለፉ ፤ ጐላ ያለ መሠረተ ሃይማኖት (ዶግማ) አልተወሰ ነም ። ፓፑ የክርስቶስ እንደራሴና የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በላይ ስለሆነ በመንበሩ ላይ ተቀምጦ እምነትና ሞራል ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በሚወስነው ሁሉ አይሳሳትም በማለት በመጀመሪያው የቫቲካን ጉባኤ የጸደቀው በሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ አልተሻሻለም ።

ፓፕ ጳውሎስና ፓትርያርክ አቴናጐራስ በ1054 ዓ·ም በሁለቱ አብያተ ክርስቲያኖቻቸው መካከል የተፈጸመው ውግዘትና መለያየት ያሳዘናቸው መሆኑን በመግለጽ ከ1965 ዓ·ም ጀምሮ ጥንት የተላለፈው ውግዘት የተነሣ መሆኑን የሚገልጸው የስምምነት ሰነድ ከተነበበ በኋላ አራት ዓመት ያህል የፈጀው የቫቲካን ሁለተኛ አጠቃላይ ጉባኤ ተግባሩን አጠናቆ ተዘጋ ።

## ምዕራፍ ፪

## የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ

ሀ) በአስተዳደርና በእምነት (በዶግማ ፡ በዶክትሪን) ነክ ትምህርቶች ባለመስማማት ምክንያት በ16ኛው መቶ ዘመን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለተለዩት ፕሮቴስታን



www.ethiopianorthodox.org

## የች መንገድ ጠራጊዎች የነበሩት የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት

እነ ማርቲን ሉተር የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ፣ የኃጢአት ማስተስረያ ጽሑፍና አንዳንድ እምነት ነክ ትምህርቶችን በመቃወም ታላቅ ለውጥ ለማድረግ ከመነሣታቸው ቀደም ብሎ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት የነበሩ ቅጥ ያጣው የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደርና አንዳንዶቹ የእምነት ትምህርቶች ይታረሙ በማለት የተቃውሞ እንቅስቃሴ አድርገው ነበር ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ) <u>አልቢጀንሴስ (ንጹሐን)</u> የተባሉት በዐሥራ ሁለተኛው መቶ ዘመን በደቡብ ፈረንሳይ ፣ በሰሜን እስጳኝና በሰሜን ኢጣልያ ተነሥተው በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለጻድቃን ምስልና ሥዕል የሚደረገውን የአክብሮት ስግደት ፣ የመካነ ንስሐን (የፐርጋቶሪን) ትምህርት ፣ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያንን ፣ ትንሣኤ ሙታንን ወዘተ· ተቃወሙ ። አኗኗራቸውም ከፍ ባለ ሞራል ላይ የተደገፈ የብሕትውና ኑሮ ነበር ። በ1167 ዓ·ም ከደቡብ ፈረንሳይ ብዙ ሕዝብ ትምህርታቸውን ተቀብሎ ተከተላቸው ። በ1200 ዓ·ም ደግሞ ከሰሜን ኢጣልያ ብዙ ሕዝብ ተከተላቸው ። ይህንኑ በመመልከት ሣልሳዊ ኤኖሴንት የተባለው ፖፕ ሚስዮናውያንን በመላክ አስተምሮ ለመመለስ ያደረገው ጥረት ሁሉ ስላልተሳካለት በ1208 ዓ·ም የመስቀል ጦረኞችን ልኮ አስጨፈጨፋቸው። ከሞት የተረፉትም ዘግየት ብሎ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በተቋቋመው ኢንኩዚሽን በተባለው ፍርድ ቤት ትእዛዝ እየታደኑ በእሳት ስለተቃጠሉ ደብዛቸው ከምድረ ገጽ ጠፋ ።

2ኛ) <u>ዋልዴንሴስ</u> የተባለው ንቅናቄ ጴጥሮስ ዋልዶ በተባለው የልዮን ነጋዴ በ1176 ዓ·ም ደቡብ ፈረንሳይ ውስጥ ተጀመረ ። ይህ ንቅናቄ እላይ ከተመለከትነው ከአልቢጀንሴስ ንቅናቄ ጋር አንዳንድ ተመሳሳይ ነጥቦች ቢኖሩትም ቅሉ በአብዛኛው ፈጽሞ የተለየ ነው ። ዋልዶ ጌታ በማቴዎስ 19፡21 ያስተማረውን በመከተል የነበረውን ሀብት ለድሆች መጽውቶ የክርስትና ትምህርት መገኛና መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ፣ ጸሎተ ቅዳሴና ለሙታን የሚደረገው ጸሎተ ፍትሐት አያስፈልግም፣ ቅዱሳት መጻሕፍትም ምእመናን በሚረዱአቸው ቋንቋ ዎች ተተርጕመው መቅረብ አለባቸው ፣ ሥልጣነ ክህነት የሌላቸው


www.ethiopianorthodox.org

ወንድና ሴት ምእመናንም የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ አለባቸው ወዘተ· በማለት የስብከት ተግባሩን ቀጠለ ። ወዲያውም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተወሰኑ ክፍሎችን ምእመናን በሚረዱአቸው ቋንቋዎች ተርጉሞ አቀረበ ። ማዕርገ ክህነት ያልነበራቸው ምእመናንም እንዲሰብኩ አደረገ። ቀስ በቀስም የጌታን ምሳሌ በመከተል ሕዝቡ ንስሐ ገብቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እየፈጸመ እንዲኖር የሚያስተምሩ (የሚሰብኩ) ሰባ ደቀመዛሙርት መርጦ ወደ ደቡብ ፈረንሳይ ፥ ኢጣልያ ፥ እስጳኝ ፥ ጀርመንና ቦሔሚያ ላከ። ብዙ ሕዝብም ትምህርታቸውን ስለተቀበለ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪ ፖፕ ሉሲዮስ ሦስተኛ በ1184 ዓ·ም ዋልዶን ከነተከታዮቹ አወገዛቸው ። ቀጥሎም ወደ ቀደመ እምነታቸው እንመለስም ያሉት ኢንኩዚሽን በተባለው ፍርድ ቤት አማካይነት ቀስ በቀስ ተፈጁ ።

ሆኖም ኢጣልያ ውስጥ በአልፕስ ሸለቆዎች ቱሪን አካባቢ ቍጥራቸው ወደ ሃያ ሺህ የሚጠጉ የዋልዶ ተከታዮች ከተሰነዘረባቸው ጭፍጨፋ ተርፈው እስከ አሁን ድረስ አሉ ። እነሱም ዛሬ ኢጣልያ ውስጥ ከሚገኙት ፕሮቴስታንቶች የቀደምትነትን ቦታ ይዘው ይገኛሉ ።

3ኛ) የኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰርና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካህን የነበረው ዮሐንስ ዊክሊፍ (1330–1384) ፖፑ አይሳሳትም የሚለውንና የፖፑን ፍጹማዊ ሥልጣን ተቃወመ ። የቤተ ክርስቲያን መሪና እራስም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፤ እንደ ጴጥሮስ ያለ ቅዱስ መሪ ከተገኘ ግን የቤተ ክርስቲያን መሪነቱ ተቀባይነት ሊኖረው ይቻላል ። የድኅነት መገኛም መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እንጂ በቤተ ክርስቲያን አባቶች የተዘጋጁት መጻሕፍት አይደሉም ። ኅብስቱና ወይኑ ወደ ጌታ ሥጋና ደም አይለወጥም ። ወደ ተቀደሱ ገዳማት ለስግደት መሄድ አያስፈልግም ። በሽያጭ መልክ ለምእመናን የሚታደለው የኃጢአት ማስተስረያ ጽሑፍ (ኢንዶልጀንስ) ዋጋ ቢስ ስለሆነ እንዲቋረጥ ወዘተ· በማለት አስተማረ ። መጽሐፍ ቅዱስን ቩልጌት ከተባለው ከላቲኑ መጽሐፍ ሕዝቡ ወደሚረዳው ወደ እንግሊዝኛ መተርጐም ጀምሮ የሐዲስ ኪዳኑን ክፍል ጨርሶ ብሉይ ኪዳንን በመተርጐም ላይ ሳለ ስለሞተ ፡ የትርጐም ሥራው በደቀመዛሙርቱ በሒርፎርድና በፑርቬይ ተፈጽሞ በአገልግሎት ላይ ዋለ ። ይኸውም የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም ለእንግሊዝኛ ቋንቋ መሻሻል አስተዋጾኦ አድርጓል ። በተጨማሪም ከምእመናን ላይ በግብር የሚሰበሰ



www.ethiopianorthodox.org

በው የቤተ ክርስቲያን ሀብት ከምችት ያለአግባብ መባከንን በመቃወም ሀብቷን መንግሥት እንዲያስተዳድረው ፤ ካህናት ግን ከጌታ የተጣለባቸ ውን መንፈሳዊ አገልግሎት ለምእመናን እንዲያዳርሱ ይገባል ወዘተ· በማለት አስተማረ ። እላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በ1377 ዓ·ም ጎርጎርዮስ ዐሥራ አንደኛ የተባለው ፖፕ ቢያወግዘውም ቅሉ ፣ የእንግሊዝን ፓርላማ ድጋፍ ስላገኘ ከምእመናን መካከል ለስብከት ከአዘጋጃቸው ወንጌላውያን ጋር እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ማስተማሩን ቀጠለ ።

እንዲሁም ሎላርድስ የተባሉት የዊክሊፍ ተከታዮች የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖትና አስተዳደር በጥብቅ በመቃወም ሲያመቻቸው በግልጽ ፤ ስደት ሲነሣባቸው በሕቡእ ተግተው በመስበክ የፈለጉትን ለውጥ በራሳቸው ጥረት ለማስገኘት ባይችሉም ቅሉ በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ለተደረገው ለውጥ ታላቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

4ኛ) ቦሔምያ (ቼኮዝሎቫኪያ) ውስጥ የተነሣው ዮሐንስ ሑስ (1370–1415) የተባለው ካህንና የፕራግ ዩኒቨርሲቲ የፊሎዞፊ ፕሮፌሰር የፖፑን ሥልጣን፣ የኃጢአት ማስተስረያ ነው ተብሎ ለምእመናን በሽያጭ የሚሰጠውን ጽሑፍ ፤ በኃላፊነት ላይ ያሉ ካህናት የሚቀበሉትን የመተያያ (የጉቦ) ገንዘብ ወዘተ· በመቃወም አስተማረ ። እንደ ዊክሊፍ የቤተ ክርስቲያን ራስ ክርስቶስ እንጂ ፖፑ አለመሆኑን አብራርቶ አስተማረ ። በ1411 ዓ·ም ዮሐንስ ሃያ ሦስተኛ በተባለው ፖፕ ተወግዞ በስደት ላይ ሲኖር ፣ ንጉሥ ሲግስሙንድ በሰላም ደርሶ ለመመለስ የሚያስችል መተማመኛ ሰጥቶ ኮንስታንስ ወደ ተባለች የስዊስ ሀገር ከተማ ሄዶ ስለተወገዘበት ሁናቴ ያለውን ሐሳብ እዚያ ለተሰበሰበው ጉባኤ እንዲያስረዳ አዘዘው ። እሱም በጉባኤው በተሰበሰቡት ጳጳሳት ፊት በግንባር ቀርቤ እውነቱን ፍርጥርጥ አድርጌ በማስረዳት አሳምናለሁ በሚል ዓላማ በ1414 ዓ·ም ወደ ኮንስታንስ ሄደ ። በጉባኤው የተሰበሰቡት ያስተማረው ትምህርትና የጻፋቸው ጽሑፎች በክሕደት የተሞሉ ስለሆኑ በማረም እንዲያስተባብል (ሐሳቡን እንዲለውጥ) ቢጠይቁት ያስተማርሁትና የጻፍሑት ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ ቀጥተኛ ነው ብሎ አቋሙን በዝርዝር አስረድቶ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለቱ ስለጸና በ1415 ዓ·ም በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት ተፈረደበት ። ንጉሡም ከቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ጋር የሚያስከትለውን ግጭት ለማስወገድ በመሻት



www.ethiopianorthodox.org

ሉሑስ የሰጠውን ከኮንስታንስ በሰላም ደርሶ የመመለስ ተስፋ በተግባር ላይ አላዋለውም ። የዊክሊፍም አጽም ከተቀበረበት ወጥቶ እንዲቃጠል በዚሁ ጉባኤ ተወሰነ ። ሁለቱም ውሳኔዎች ወዲያውኑ በተግባር ላይ ዋሉ። ምንም እንኳ ሑስ በእሳት ተቃጥሎ ቢሞትም ተከታዮቹ ሊጠፉ አልቻሉም ። እስከ ዛሬ ድረስ ያሉ የሑስ ተከታዮች የሞራቪያን ወንድማማቾች በሚል ስያሜ ይጠራሉ ።

5ኛ/ ጊሮላሞ ሳቮናሮላ (1452–1498) የተባለው ኢጣልያዊ የዶሚኒካን ኦርደር (ክፍል) መነኩሴና የፍሎሬንስ ሰባኪ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሻሻል (ተሐድሶ) እንዲደረግ ይጥር ነበር ።

በ1482 ዓ·ም ፍሎሬንስ ባለው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምእመናንና ካህናት ከሚገኙበት የሞራል ውድቀት በንስሐ እንዲመለሱ በማስተማሩ ብዙ ተከታዮችን አገኘ ። ቈየት ብሎም የቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን አለቃ ሆኖ ካገለገለ በኋላ በ1494 ዓ·ም· የፍሎሬንስ ከተማ አስተዳዳሪ ሆነ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሕዝቡ ንስሐ ገብቶ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ ፤ ካህናትና ፖፑም ጭምር ከተሳሳተ የአስተዳደርና የአኗኗር ጉድለታቸው ታርመው እግዚአብሔር ባዘዘው መንገድ ምእመናንን እንዲያገለግሉ አስተማረ ።

ይህ ዐይነቱን ሐቀኛ ሰባኪ በአጭሩ ለመቅጨት በማሰብ አሌክሳንደር ስድስተኛ የተባለው ፖፕ በ1495 ዓ·ም ሳቮናሮላን ሮም ሄዶ ለሚቀርብበት ክስ መልስ እንዲሰጥ አዘዘዉ ። እሱም የፖፑን ትእዛዝ በመቃረን የተለመደ ስብከቱን ስለቀጠለ ፖፑ አወገዘው ። ሳቮናሮላም ፖፑ በሕገ ወጥ መንገድ በጉቦ የተሾመና ወንጀለኛ ስለሆነ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ተጠርቶ እዚያ ላይ እፋረደዋለሁ በማለት ውግዘቱን አልቀበልም አለ ። የፍራንሲስካን ኦርደር መነኰሳት እንዲነሡበት ውስጥ ውስጡን ግፊት ስለተደረገና ፖፑም የሳቮናሮላን ተከታዮች እገዝታችኋለሁ በማለት ስላስፈራራቸው ቀደም ሲል ይደግፈው ከነበረው ሕዝብና ካህናት አብዛኛው ተነሣበት ። ወዲያው ይዘው ለፍርድ አቅርበው በማሰር ከአሠቃዩት በኋላ መናፍቅ ነው በማለት ፍሎሬንስ በሚገኘው ገበያ ሰቀሉት ። ሬሳውንም አቃጠሉት ። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚፈጸመው ስሕተት እንዲታረም በጥብቅ ያስተማረው ካህን በግፍ እንደወንጀለኛ ተሠቃይቶ እንዲሞት ተደረገ ።


www.ethiopianorthodox.org

በዚህ አኳኋን በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይፈጸሙ የነበሩት የእምነት ፣ የሞራል ፣ የኢኮኖሚ ፣ የአስተዳደር ፣ ወዘተ· ጉድለቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲታረሙ የጠቆሙት ( ያስተማሩት) እንደ ጥፋተ ኞች በመቁጠር የሞት ቅጣት ተፈጸመባቸው ። ሆኖም በ16ኛው መቶ ዘመን ለተነሡት ፕሮቴስታንቶች መንገድ ጠራጊዎች በነበሩት ሰዎች በየጊዜው እንዲታረም የተጠቆመው ሁሉ ለጊዜው ተድበስብሶ ቢታለ ፍም "አለባብሶ ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" እንዲሉ ትንሽ ዘግየት ብለው በተነሡት በሉተር ፣ በዝዊንግልና በካልቪን መሪነት ስሕተት ነው የተባለው በይፋ ለምእመናን ሊገለጽና የለውጡም ተግባር ተከናውኖ ለካቶሊክ ፣ ለግሪክ ኦርቶዶክስና ለኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት እምነት ተቃራኒ የሆነው የፕሮቴስታንት እምነት ሊከሰት ቻለ ።

## ለ) በ16ኛው መቶ ዘመን በፕሮቴስታንቶች የተካሄደው የአስተ ዳደርና አንዳንድ የመሠረተ ሃይማኖት ለውጥ እንቅስቃሴ እንዲጀመርና ግቡን እንዲመታ አስተዋጽኦ ከአደረጉት ቀደምት ምክንያቶች ጥቂቶቹ

1ኛ/ በ15ኛው መቶ ዘመን ኢጣልያ ውስጥ ተጀምሮ ቀስ በቀስ ወደ ጀርመን ፣ እንግሊዝ ፣ ፈረንሳይ ወዘተ· በተዛመተው ሬኔሳንስ (የዕውቀት ዳግም ልደት) በተባለው ንቅናቄ ቀደም ሲል ሮም በአሕዛብ ከተወረረች በት ወቅት ጀምሮ ተዳፍኖ የነበረው ዕውቀት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በአውሮጳ የሥነ ጽሑፍ (የሊትሬቸር) ፣ የሥነ ጥበብ ፣ የሳይንስ ወዘተ· ዕውቀት እየተስፋፋ ሄደ ። በመካከለኛው ዘመን ሊቃውንቱ የቤተ ክህነት ሰዎች ብቻ ስለነበሩ ትምህርታቸውና ጽሑፎቻቸው ሁሉ በሃይማኖትና በፍልስ ፍና ላይ ያተኮሩ ነበሩ ። ከሬኔሳንስ ንቅናቄ ጊዜ ጀምሮ ግን ሊቃውንቱ ካህናት ብቻ መሆናቸው ቀርቶ ከምእመናንም ሆኑ ። በዚህ ጊዜ የተነሡት ሊቃውንት የሃይማኖት ተቀዋሚዎች አልነበሩም ። የሊቃውንቱ ንቃተ ኅሊና ከፍ እያለ ስለሄደ መጽሐፍ ቅዱስን ከላቲኑ ትርጉም ሳይሆን መጀመሪያ በተጻፈባቸው ቋንቋዎች በእብራይስጥና በግሪክ መመርመርና ማጥናት ጀመሩ ። የምርምራቸውም ውጤት አብዛኛውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውጭ የሆነውን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ



www.ethiopianorthodox.org

ሃይማኖት (ዶግማ) እያቃለሉ እንዲሄዱ ስለገፋፋቸው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እምነት መሠረት ወደ መናጋቱ ተቃረበ ።

በ1453 ዓ·ም ቍስጥንጥንያ በቱርኮች እጅ ስትወድቅ ብዙ ሊቃውንት የግሪክን የሥነ ጽሑፍ መጻሕፍት ይዘው ወደ ምዕራብ አውሮጳ ስለገቡ ፣ በአውሮጳ ለተጀመረው የሬኔሳንስ ንቅናቄ ታላቅ አስተዋጽኦ አደረጉ ።

ኤራዝመስ (1466–1536) የተባለው የሆላንድ ተወላጅ ሂውማኒስት ሊቅ በፈረንሳይ ፣ በእንግሊዝ ፣ በስዊዘርላንድ ፣ በኢጣልያ ወዘተ· እየተዘዋወረ እዚያ የነበሩትን ሥነ ጽሑፎች ከመረመረና ካጠና በኋላ በ1516 ዓ·ም ሐዲስ ኪዳንን መጀመሪያ በተጻፈበት በጽርዕ (በግሪክኛ) አዘጋጅቶ አሳተመ ። በተጨማሪም በየጊዜው ባሳተማቸው ጽሑፎቹ የሮማን ቤተ ክርስቲያን ቅጥ ያጣ አስተዳደርና ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጭ የሆኑትን አንዳንድ የተንዛዙ የመሠረተ ሃይማኖት ትምህርቶች ፊት ለፊት በመጋፈጥ ሳይሆን ፣ ገደም ባለ በፌዝ (ባሽሙር) መልክ በመቃወም ተገቢው እርማት (መስተካከል) እንዲደረግ ይገልጽ ስለነበር እሱና መሰሎቹ በሉተር ለተካሄደው ለውጥ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። በሌላው ወገን ደግሞ የፕሮቴስታንቶች ተስፈንጣሪ ሂደት ስላላስደሰተው እነሱንም በመቃወም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባልነቱን እንደጠበቀ ኖሮ በ1536 ዓ·ም ዐረፈ ።

2ኛ/ በ1455 ዓ·ም ዮሐንስ ጉቴንበርግ በተባለው ጀርመናዊ የተፈለሰፈው ማተሚያ የፕሮቴስታንቶችን የመነሻ ጊዜ አቃረበው (አፋጠነው) ። ይህ ማተሚያ ከመፈልሰፉ በፊት መጻሕፍት በብዙ ድካምና ወጭ በእጅ በቁም ጽሕፈት ይጻፉ ስለነበር ፣ ከቍጥራቸው ማነስ የተነሣ ለሊቃውንትና ለምእመናን ሊዳረሱ አልቻሉም ነበር ።

በዚያን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ተፈላጊ ስለነበር አዲስ በተፈለሰፈው ማተሚያ የታተመው መጀመሪያው ጽሑፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር ። በዚህ አኳኋን መጽሐፍ ቅዱስ ሕዝቡ በሚረዳቸው የተለያዩ ቋንቋዎች እየተተረጐመና በብዛት እየታተመ ለምእመናን እንዲዳረስ ተደረገ ። ሐዲስ ኪዳንን በቋንቋቸው እያነበቡ የተመራመሩ ካህናትና ምእመናን በፖፖቹ ፈላጭ ቆራጭነት የምትመራዋ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ዘመን ከነበረችው ከጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ሁናቴ



www.ethiopianorthodox.org

nationalism

የራቀችና የተሳሳተ መንገድ የምትከተል መሆኗን ስለተረዱ ፤ የአስተዳደርና የእምነት ለውጦች መካሄድ መገባቱን አምነው የለውጡን ጀማሪና መሪ ይጠባበቁ ነበር ። እነሉተርም ከተነሡ በኋላ ትምህርታቸውን በብዙ ሚሊዮን ቅጅ እያሳተሙ በመላ አውሮጳ ለሚገኙ ካህናትና ምእመናን ለማዳረስ የቻሉት ማተሚያ በመፈልሰፉ መሆኑ ግልጽ ነው ።

3ኛ/ በዚሁ ዘመን በአውሮጳ መንግሥታት መሪዎችና ሕዝብ ዘንድ <u>የብሔርተኛነት ስሜት</u> ገኖ ነበር ። ቀደም ሲል በመካከለኛው ዘመን የነበሩት የተቀደሰው የሮማ ነገሥታትና ፖፖች አልፎ አልፎ ቢጋጩም ቅሉ ፤ በመካከላቸው የብሔርተኛነት ስሜት ጐልቶ አይታይም ነበር ። ከዚህ ዘመን ጀምሮ ግን አዲስ ኃይል በማግኘት የተነሡት የየሀገሩ ማለት የእንግሊዝ ፤ የፈረንሳይ ፤ የእስጳኝ ፡ የጀርመን ወዘተ ነገሥታት ፡ ካህናትና ምእመናን የፖፑን የበላይነት ፍላጎት በመቃወም ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያናችን ባዕድ በሆነ ፖፕ አትገዛም (አትተዳደርም) ፤ የየሀገራቸው ተወላጆች የሆኑ አስተዳዳሪዎቿ ጳጳሳት ፡ የደብርና የገዳማት አለቆች በፖፑ ተመርጠው አይሾሙም ፡ ለሮም ቤተ ክርስቲያንም ግብር አንከፍልም ፡ በሀገራችን የሚገኘውም ከፍ ያለ የቤተ ክርስቲያን ርስትና ተንቀሳቃሽ ሀብት በመንግሥት ሥር እንዲተዳደር ወዘተ በማለት ተነሣሥተው ውሳኔአቸውን በተግባር ላይ ማዋል ጀመሩ ። ይህ ዐይነቱ በሮም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ የተሰነዘረው የጥላቻ መንፈስ ለፕሮቴስታንቶች ንቅናቄ መጠናከር ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል ። ለምሳሌ የፈረንሳይ ንጉሥ ቀዳማዊ ፍራንሲስ በብሔርተኛነት ስሜት በመነሣሣት ልዮን ዐሥረኛ የተባለውን ፖፕ አስገድዶ በ1516 ዓ.ም ቦሎኒያ ውስጥ በተደረገው ስምምነት ንጉሡ በግዛቱ ውስጥ ጳጳሳትን ፡ የገዳማትና የአድባራት አለቆችን የመምረጥና የመሾም መብትን ተረከበ ። በዚህ አኳኋን ፖፖች የፈረንሳይ ተወላጅ የሆኑትን ካህናት የመሾምና በቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብት የመጠቀም መብታቸውን ተገፈፉ ።

4ኛ/ <u>ቱርኮች</u> ምዕራብ አውሮጳን በጦር ኃይል ለመያዝ ስለተነሡ የካቶሊክ እምነት ተከታይና ደጋፊ የነበሩት ነገሥታት ከእስላሞች ጋር በየጊዜው ከባድ ጦርነት ያካሂዱ ነበር ። ይህ ዓይነቱ ጦርነት ካቶሊካውያን ነገሥታት የሉተር ደጋፊ በነበሩ ልዑላን ላይ ተጽእኖ ለማድረግ ስላላስቻላቸው ለፕሮቴስታንቶች መጠናከር ረድቷል ።



www.ethiopianorthodox.org

እላይ በተመለከትናቸውና በመሳሰሉ ምክንያቶች የአውሮጳ ሕዝብ፡ ካህናትና ነገሥታት ንቃተ ኅሊና ከፍ በማለቱ ለውጥንና ነጻነትን ስለፈለጉ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ልታዳፍነው ያልቻለችው ለውጥ በዊተንበርግ ፕሮፌሰር በማርቲን ሉተር ግምባር ቀደምትነት በ1517 ዓ.ም ጀርመን ውስጥ ተከሰተ ።

## ሐ) በ16ኛው መቶ ዘመን በማርቲን ሉተር መሪነት ጀርመን ውስጥ የተካሄደው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና የመሠረተ ሃይማኖት ለውጥ

ቀደም ሲል የተመለከትናቸው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባላት ቤተ ክርስቲያኒቱ በወቅቱ ተገቢ የሆኑ ለውጦችን እንድታደርግ ቢጥሩ ሰሚ አጥተው ሲኖሩ በሉተር ፣ በዝዊንግል ፣ በካልቪን ወዘተ. ቆራጥ መሪነት ፕሮቴስታንቶች ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተለይተው የየራሳቸ ውን አብያተ ክርስቲያናትና አስተዳደር መሠረቱ ። የየራሳቸው የሆነ የተለያየ መሠረተ ሃይማኖት ወሰኑ።

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ስትከተላቸው የቈዩትን የአስተዳደር ጉድለቶች ወደፊት እንደምንመለከተው በትሬንት ጉባኤ ውሳኔዎች መሠረት ከሞላ ጐደል በማረም ለማስተካከል ችላለች ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትከተላቸው ከነበሩት የአስተዳደር ጉድለቶች እንድትታረም ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውጭ የሆኑ መሠረተ ሃይማኖቶችንም እንድታስወግድ (እንድትሰርዝ) በመጠየቅ የተነሣው ማርቲን ሉተር (1483 1546) በ1483 ዓ.ም በማዕድን ማውጣት ሥራ ላይ ከተሰማራው አባቱ ከሐንስና ከእናቱ ከማርጋሬት ሉድሄር ጀርመን በምትገኝ አይስሌ በን ውስጥ ተወለደ ። ማንስፈልትና አይስሌበን ይሰጥ የነበረውን ትምህርት ካጠናቀቀ በኋላ በ1501 ዓ.ም ኤርፉርት ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ተማረ ። ከዚያም በፍርድ ቀን (በዳግም ምጽአት) እንዴት እሆናለሁ? በማለት የኃጢአተኛነት ስሜት አእምሮውን እያስጨነቀውና እየጸናበት ስለሄደ የነፍሱን ድኅነት ለማግኘት በማሰብ በ1505 ዓ.ም ኤርፉርት ከነበረው አውግስቲንያን ገዳም ገባ ። እዚያም የአውግስቲንን ጽሑፎች አጠና ። የገዳሙ አበምኔት ስታውፕትዝ ሉተር ከደረሰበት የኃጢአተኛ



www.ethiopianorthodox.org

ነት ስሜትና ጭንቀት ሊገላገል የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት መሆኑን ገልጾ ባበረታታው መሠረት ሉተር በጳውሎስ የተጻፈችውን የሮሜን መልእክት ሲያጠና "ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና" (ሮሜ 1፡17) ከሚለው ሲደርስ ማንኛውም ክርስቲያን በክርስቶስ ላይ ባለው ሐቀኛ (ከልብ የመነጨ) እምነት ብቻ በእግዚአብሔር ጸጋ የሚድን (የነፍሱን ድኅነት የሚያገኝ) መሆኑን በመገንዘብ የሰው ልጆች ሊድኑ የሚችሉት በእምነታቸው ብቻ እንጂ በደጋግ ሥራዎቻቸው አለመሆኑን ተረዳሁ አለና በዚሁ እምነት ገፋበት ።

አንዳንዶቹ ስለ ሉተር ገዳም መግባት ሲተርኩ አንድ ቀን ማንስፌልት የነበሩ ወላጆቹን ጠይቆ ወደ ኤርፉርት ሲመለስ ከመንገድ ላይ አደገኛ አውሎ ነፋስ ሲያንገላታው በዚህ አውሎ ነፋስ ከመሞት ብታተርፊኝ ቀሪ ሕይወቴን አምላኬን በምንኵስና አገለግላለሁ ብሎ ለቅድስት ሐና ቃል ኪዳን ስለገባ ነበር ይላሉ ።

እንዲሁም የገዳሙን ጉዳይ ለማስፈጸም በ1510 ዓ.ም ወደ ሮም ተልኮ እዚያ በቈየበት ጊዜ ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች በሚኖሩበት ከተማ ይፈጸም የነበረውን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መዛባት በመመልከት በጣም አዝኖ ወደ ዊተንበርግ ተመለሰ ። በ1512 ዓ.ም. ከዊተንበርግ ዩኒቨርስቲ በመንፈሳዊ ትምህርት በዶክተርነት ማዕርግ ተመርቆ እዚያው በመምህርነት በመመደብ የቅዱሳት መጻሕፍትን (የመዝሙረ ዳዊትን ፡ የሮሜንና የገላትያን መልእክታት) ትርጓሜ ያስተምር ጀመር ።

ልዮን ዐሥረኛ (1513–1521) የተባለው ፖፕ በሮም ከተማ ለሚገኘው ለታላቁ የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን የእድሳት ሥራ ማስፈጸሚያ የሚሆን ገንዘብ ስለፈለገ ፣ በጀርመን የሜንዝ ሊቀ ጳጳስ አልበርት ቀደም ሲል በሦስት ሀገረ ስብከቶች ላይ ሲሾም ሹመቱን ለሰጠው (ለሾመው) ለሮሙ ፖፕ በግብርና በገጸ በረከት መልክ አውግስበርግ ከነበረው ፉገር ከተባለው የገንዘብ ድርጅት በአራጣ ተበድሮ ሰጥቶ ነበር። ስለዚህ ለፖፑ ተበድሮ ለላከው የገንዘብ ዕዳ የሚከፍለው ስለፈለገ፣ ዮሐንስ ቴትዝል የተባለው የዶሚኒካን ገዳም መነኵሴ "ኢንዱልጀንስ" የተባለውን የኀጢአት ማስተስርያ ጽሑፍ በመሸጥ እላይ ለተጠቀሰው ዕዳ



www.ethiopianorthodox.org

የሚከፈል ገንዘብ ከምእመናን እንዲሰበስብ ታዘዘ ። በዚሁ የገንዘብ ስብሰባ ተግባር የተካነው (ኤክስፐርት የሆነው) ቴትዝልም በ1517 ዓ.ም ዊተንበርግ አካባቢ ይህንኑ ከፖፑ የተላከ የኃጢአት ማስተስርያ ጽሑፍ በመግዛት ዋጋውን በሙዳየ ምጽዋቱ ውስጥ ስትጥሉ የሞተ (የሞተች) ዘመዳችሁ (ወዳጃችሁ) የተኰነነች ነፍስ በቅጽበት ከፐርጋቶሪ (ከመካነ ንስሐ) ወዲያው ነጻ ሆና ወደ መንግሥተ ሰማያት ትገባለች ። የራሳችሁም ነፍስ ትማራለች በማለት እየሰበከ የየዋሐን ምእመናንን ገንዘብ ሲያጋብስና ምእመናንም በዚህ በገዛነው ጽሑፍ አማካይነት የሞቱ ዘመዶቻችን ነፍሳት ይድናሉ ። የራሳችንም ነፍስ ድኅነት ስለምታገኝ ከእንግዲህ ኑዛዜ አያስፈልገንም ሲሉ ሉተር ሰምቶና ተመልክቶ ከተሰማው ከፍተኛ ኃዘን የተነሣ መንፈሱ ተረበሸ ። ወዲያው በመላ ቅዱሳን ስም በታነጸውና በፍሬደሪክ ትጋት የተሰበሰበው የቅዱሳን አጽም ለምእመናን በሚታይ በት ቤተክርስቲያን የቅዱሳን የዓመት በዓል በሚከበርበት ዋዜማ ዕለት ምእመናን በተሰበሰቡበት ተቃውሞውን ገለጸ ። ይኸውም ይህ የኃጢአት ማስተስርያ ነው በመባል የሚሸጠው ፡ ምእመናንን በመደለል ገንዘብ ለመሰብሰቢያ (ለማጋበሻ) የሚያገለግል እንጅ በምንም ዓይነት መንገድ በሕይወት ያሉትንም ሆነ የሞቱትን ሰዎች ኃጢአት ፈጽሞ የማያስተሰርይ መሆኑን ፤ ኃጢአት ሊሰረይ የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ፡ በእግዚአብሔር አምኖ ንስሐ በመግባት ብቻ መሆኑን ወዘተ. የሚገልጹ ዘጠና አምስት ማስረጃዎችን (የክርክር ዐረፍተ ነገሮችን) የያዘ ጽሑፍ አዘጋጅቶና በላቲን ቋንቋ ጽፎ ምእመናን እንዲያነቡት ዊተንበርግ በነበረው ቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ላይ ለጠፈው ። ይህ በላቲን የተዘጋጀው በሉተር ደጋፊዎች ወዲያው ወደ ጀርመን ቋንቋ ተተርጉሞ ከታተመ በኋላ በመላ ጀርመን ተበተነ ። በዚህ አኳኋን ፕሮቴስታንቶችን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የለየው ጸብ ተጀመረ ።

ሉተር ይህንኑ ተቃውሞ ሲያዘጋጅ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ይፈጸሙ የነበሩትን ስሕተቶች በአስቸኳይ እንዲያርሙ ለማሳሰብ ነበር እንጅ ለመገንጠል በመሻት አልነበረም ። ፖፕ ልዮን ዐሥረኛ ይህንኑ ተቃውሞ ከአቡነ አልበርት ሪፖርት ሲሰማ በአውግስቲንያንና በዶሚኒካን ገዳማት መነኰሳት መካከል አልፎ አልፎ ይከሰት የነበረው ንትርክ የተቀሰቀሰ ስለመሰለው የገዳሙ አበምኔት ሉተርን



www.ethiopianorthodox.org

በተግሣጽ እንዲያስታግሰው ትእዛዝ አስተላለፈ ። ቁየት ብሎ ግን በፖፑ የተቋቋመውን "ኢንደልጀንስ" የተባለውን የኃጢአት ማስተስርያ ጽሑፍ መቃወም በቀጥታ የፖፑን ፍጹማዊ ሥልጣን መቃወም መሆኑ ን የጉዳዩንም አሳሳቢነት ስለተገነዘበው በ1518 ዓ.ም ሉተር ወደ ሮም ተጠራ ። ትእዛዙን ተቀብሎ ቢሄድ እንደነ ሑስ በግፍ እንደሚገደል ስለሚያውቀው አልሄድም አለ ። የኢጣልያ ተወላጅ የሆኑ ፖፖችን ጣልቃ ገብነት በሚጠላው በሉተር ደጋፊ በጀርመናዊው በሳክሶኒው መስፍን በጠቢቡ ፍሬደሪክ ጥያቄ መሠረት ፖፑ ጉዳዩ ጀርመን በነበረው ተወካዩ በካርዲናል ካያታን እንዲታይ አዘዘ ። ዶሚኒካዊው ካያታንም በትእዛዙ መሠረት ሉተርን ወደ አግስቡርግ አስጠርቶ ባዘጋጃቸው ጽሑፎች ውስጥ በፖፑ አማላጅነት ኃጢአት አይሠረይም የሚለውና የመሳሰሉት ስሕተቶች መሆናቸውን አምኖ በይፋ እራሱን እንዲያጋልጥና በመናፍቅነት ከሚያደርስበት የሞት ቅጣት እንዲድን ቢጠይቀው ፤ እምነቴን ለውጬ ከመዳን ይልቅ ሞትን እመርጣለሁ በማለት አሻፈረኝ ብሎ ወደ ዊተንበርግ ተመለሰ ። በ1518 ዓ.ም ዊተንበርግ ሆኖ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ተጠርቶ ጉዳዩ እንዲታይለት ለፖፑ አመለከተ ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ሉተር የፖፑን የበላይነት ሥልጣን አልተቃወመም ነበር ። የልዑል ፍሬደሪክ እርዳታ ባይታከልበት ኖሮ ሉተር መናፍቅ ነው በመባል በእሳት ተቃጥሎ ይሞት ነበር ።

ከዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባን ይህ ዓይነቱ የኃጢአት ማስተስርያ ጽሑፍ በሉተር ዘመን አዲስ የተጀመረ ሳይሆን ፣ ከዐሥራ አንደኛው መቶ ዘመን ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፈቃድ (ትእዛዝ) ለመስቀል ጦረኞች ማዝመቻ ፣ ለአብያተ ክርስቲያናት ማሳነጫ ፣ ለሆስፒታሎች ማሠሪያ ወዘተ የሚሆን ገንዘብ ሲሰበሰብበት መቈየቱን ነው ።

በ1519 ዓ.ም ሊፕዚግ ውስጥ በሉተር ደጋፊ በካርልስታድና በፖፑ ደጋፊ በዮሐንስ ኤክ መካከል ክርክር በተካሄደበት ወቅት ሉተር የፖፑ የአብያተ ክርስቲያናት የበላይነት ሥልጣንና አለመሳሳት በቅዱሳት መጻሕፍት ያልተደገፈና ከ400 ዓመታት በፊት የተጀመረ ሰው ሠራሽ ስለሆነ ይህንኑ ሥልጣን በመደገፍ የወሰኑ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ተሳስተዋል ። በክርስትና ሃይማኖት የመጨረሻ ሥልጣን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው አለ ። እንዲሁም ሉተር ካህናት እንዲያገቡ ፤ ለሙታን



www.ethiopianorthodox.org

የሚደረገው ጸሎተ ፍትሐት አስፈላጊ ስላልሆነ እንዲቀር ፤ የያንዳንዱ ሰበካ ምእመናን የየቤተ ክርስቲያናቸውን አገልጋይ (ፓስተር ፤ ካህን) እንዲመርጡና አስተዳደሩንም በኃላፊነት እንዲያካሂዱ ፤ ማንኛውም ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል የሚያስችል መንፈሳዊ ዕውቀት ካለውና ግብረ ገብነትን የተከተለ ኑሮን ከኖረ በካህንነት ሊያገለግል የሚችል መሆኑን ወዘተ አስተማረ ። ከሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያንም ቅዱስ ቍርባንንና ጥምቀትን ቢቀበልም ቅሉ ፤ ካህኑ በሚጸልይበት ጊዜ የኅብስቱና የወይኑ ወደ ጌታ ሥጋና ደም መለወጡን ካደ ። ቀጥሎ ሲል የፖፑን የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበላይነት ሥልጣንና የኃጢአት ማስተስርያ የተባለውን ጽሑፍ ወዘተ በመቃወሙ በሑስ ላይ የፈረደው የኮንስታንስ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤም ተሳስቷል አለ ። በዚህ የፖፑን የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበላይነት ሥልጣንና የአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤን አለመሳሳት በመቃወም በራሱ ሕይወት ላይ ሞትን የጋበዘ መሆኑን ቢረዳም ቅሉ ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከፖፑ ፤ ከአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ውሳኔዎች ነጻ ሆኖ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ብቻ ተገዥ መሆኑን አምኖ ተቀበለ ። ሉተር ሊፕዚግ በነበረበት ጊዜ የሉተራውያንን ቴዎሎጂ አብራርቶ የጻፈው ፤ ከዕረፍቱም በኋላ መሪነቱን ተረክቦ ሥራውን ያከናወነው ፤ የዊተንበርግ የግሪክኛ መምህር የነበረውና የቅርብ ጓደኛው ፊልጶስ ማላንክቶን አብሮት ነበር ።

ከጀርመን ሕዝብም አብዛኛው በሉተር ምክንያት ለወደፊት የእምነቱን ነጻነት ብቻ ሳይሆን የሀገሩንም ነጻነት የሚጐናጸፍ መሆኑን ተገንዝቦ ተከተለው ። እሱም የምእመናንን ድጋፍ መከታ አድርጎ የሚከተለውን እምነት በማብራራት ፤ በየጊዜው የሚሰብካቸውን ስብከቶች ፤ የተለያዩ ፓምፍሌቶችንና ጽሑፎችን አዘጋጅቶ በማሳተም ለምእመናን እንዲዳረሱ አደረገ ። ልዑላኑም ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ኃላፊነት የፖፑን ሥልጣን አስወግደው በጀርመን አብያተ ክርስቲያናት ለምእመናን የሚበጅ ለውጥ እንዲያካሂዱ ጥሪ አድርጓል ።

ሉተር ከተነሣበት ዓላማ ፍንክች የማይል መሆኑን በመረዳት በ1520 ዓ.ም ፖፑ አወገዘው ። መጻሕፍቱም ከተሰራጩበት ቦታ እየተሰበሰቡ እንዲቃጠሉ አዘዘ ። ሉተርም ውግዘቱን የያዘው ጽሑፍ እንደደረሰው ዊተንበርግ አካባቢ ምእመናን በተሰበሰቡበት ይህንኑ



www.ethiopianorthodox.org

ጽሑፍና የቤተ ክርስቲያኒቱን የሕግ መጽሐፍ (ካኖን ሎው) በማቃጠል ከፖፑ ለተሰነዘረበት ውግዘት መልስ በመስጠት እሱና ተከታዮቹ ከሮም ቤተ ክርስቲያን መለየታቸውን አበሰረ ፡፡

ከአውሮጳና ከአሜሪካ አብዛኛውን ክፍል ይገዛ የነበረው ታላቁ የእስጳኝ ንጉሥ ቻርልስ አምስተኛ (1500–1558) የካቶሊክ እምነት ተከታይና ደጋፊ ነበር ፡፡ የእሱም ምኞትና ዓላማ ክርስቲያኖችን ሁሉ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥር ፤ ሀገሮችንም በአንድ ንጉሠ ነገሥት ሥር አድርጎ ለማስተዳደር ነበር ፡፡ እሱም የፕሮቴስታንቶችን ንቅናቄ ወዲያው በአጭሩ የመቅጨት ችሎታ እየነበረው ይህንኑ በተግባር ላይ ከማዋል የተቆጠበባቸው ምክንያቶች በወቅቱ ከደመኛ ጠላቱ ከፈረንሳይ ንጉሥ ከቀዳማዊ ፍራንሲስ ጋር በጦርነት ላይ ስለነበረ ፤ እንዲሁም ቱርኮች አውሮጳን ለመውረር ወደዳንዩብ ሸለቆ ተቃርበው ስለነበር በጀርመን ግዛቱ ውስጥ ከሥሩ (በሥልጣኑ ሥር) የነበሩ የሉተርን ትምህርትና እምነት የሚከተሉ ልዑላን (መሳፍንት) በሁለቱም ጦርነቶች እንዲረዱት በማሰብ ነበር ፡፡

ቻርልስ በ1521 ዓ.ም ወርምስ ከተባለች ከተማ ውስጥ ልዑላን ፤ ሀገረ ገዥዎች ፤ ካህናት ወዘተ. የተካፈሉበት ጉባኤ ጠርቶ ሉተር በጉባኤው ተገኝቶ አቋሙን እንዲያስረዳ አዘዘው ፡፡ በጉባኤው ላይ ለተሰበሰቡት ሐሳቡን ገልጾ ወደ መኖሪያ ቦታው ተመልሶ እስኪደርስ ድረስ ምንም ዓይነት ጉዳት የማይደርስበት መሆኑንም የሚገልጽ መተማመኛ ሰጠው ፡፡ ሉተር ለመሄድ ሲዘጋጅ ወዳጆቹ የዮሐንስ ሑስ ዕጣ ይደርስበታል ብለው በመፍራት እንዳይሄድ ቢያግባቡትና ቢመክሩት የሚደርስብኝን መከራ ሁሉ እቀበላለሁ እንጂ ንጉሠ ነገሥቱ በጠራው ጉባኤ ላይ ተገኝቼ እምነቴን እገልጻለሁ ብሎ ሄደ ፡፡ እዚያም እንደደረሰ በንጉሡ ሊቀ መንበርነት በሚመራው ጉባኤ ላይ የተገኙት ለሉተር ብዙ ጥያቄዎች ካቀረቡለትና መልሱን ከሰጣቸው በኋላ እስከዚያን ጊዜ ድረስ በፈጸመው ስሕተት ተጸጽቶ ንስሐ እንዲገባ ቢጠየቅ ፤ ያስተማርሁትና የጻፍሁት ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እስካልተቃረነ ድረስ በጀመርሁት ትምህርት እገፋበታለሁ እንጂ በምንም መንገድ ወደ ኋላ አልልም ፤ የመጨረሻ አቋሜም ይህ ነው በማለት መለሰላቸው ፡፡ ከጉባኤው እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ ቀደም ሲል ንጉሡ በገባለት ቃል



www.ethiopianorthodox.org

መሠረት ያለምንም ጉዳት ወደ ቦታው እንዲሄድ ሆነ ። ከመኖሪያ ቦታው ከደረሰ በኋላ ግን በማንኛውም ጊዜ ተይዞ ፍርዱን እንዲቀበል በንጉሡና በመሰሎቹ ተወሰነ ።

ልዑል ፍሬደሪክ በንጉሡና በአብዛኞቹ የጉባኤው አባላት መናፍቅ ነው ተብሎ ሞት የተወሰነበትን ሰው በግልጽ ለማዳን መሞከር የማያዋጣ መሆኑን በመገንዘብ ወታደሮቹ ሉተርን በመንገድ ላይ አድፍጠው አፍነው ወደ ዋርትቡርግ እንዲወስዱት ለማድረግ ወሰነ ። ይህንኑም እቅድ ቀደም ብሎ ለሉተር በምሥጢር ገልጾለት ነበር ። ሉተር ወደ ዊተንበርግ በሰረገላ በመጓዝ ላይ ሳለ በወዳጁና በደጋፊው በልዑል ፍሬደሪክ በምሥጢር የታዘዙ ፈረሰኛ ወታደሮች ከመንገድ አጠገብ እነበረ ጫካ ውስጥ አድፍጠው በመያዝ ወደ ዋርትቡርግ ምሽግ ወሰዱት። አብረውት የነበሩ ጓደኞቹ በመደናገጥ ሊገድሉት ወሰዱት በማለት ሲያዝኑ ፤ ተይዞ ሲወሰድ የተመለከቱ ጠላቶቹ የነበሩ ሰዎች ደግሞ አለቀለት (ተገደለ) ብለው በደስታ አወሩ ። በዚህ አኳኋን ሉተር ከአደጋ ተጠብቆ ዋርትቡርግ በነበረበት የአንድ ዓመት ያህል ጊዜ ማንነቱ በጠላቶቹ እንዳይታወቅ ጆርጅ በሚል ስም እየተጠራና ወታደሮችን መስሎ በመኖር ፣ ቀደም ሲል በዘመነ ሬኔሳንስ በተነሣው በዝነኛው ምሁር በኤራዝመስ በግሪክኛ የተዘጋጀውን ሐዲስ ኪዳን ምእመናን ወደሚረዱት ወደ ጀርመንኛ ቋንቋ ተረጐመ ። ይኸውም ለፕሮቴስታንት እምነት መስፋፋትና ለጀርመንኛ ቋንቋ እድገት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጓል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት መገልገያ የሚሆኑ መዝሙሮችንና የጸሎት መጻሕፍትን ቀለል ባለ መንገድና ሕዝቡ በሚረዳው በጀርመን ቋንቋ አዘጋጀ ።

ዋርትቡርግ በነበረበት ወቅት ካርልስታድ ፣ አስቶርችና ከዙዊኩ የሄዱ ፋናቲኮች (ራዲካሎች) የለውጡን ሂደት ለማፋጠን በመሻት ሥልጣነ ክህነትን ፣ የጻድቃንን ሥዕሎች ፣ ለካህን የሚነገረውን ኑዛዜ ፣ ጾምን ፣ የብሕትውና ኑሮን ፣ ጸሎተ ፍትሐትን ፣ የሕፃናትን ጥምቀት ወዘተ. ተቃውመው በመስበክ በዊተንበርግ ምእመናን ዘንድ ከፍ ያለ ችግር መፍጠራቸው ተነገረው ። እሱም ለጀመረው የቤተ ክርስቲያን መታደስ እንቅፋት እንዳይሆን በመፍራት ከተደበቀበት ቦታ ባስቸኳይ ወደ ዊተንበርግ ሄዶ በመምከርና በማስተማር ተፋፍሞ የነበረውን



www.ethiopianorthodox.org

ብጥብጥ በሳምንት ውስጥ አብርዶ ከጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያገናዘበ ቀስ በቀስ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትለውን ሐሳብ እያብራራ የማስተማር ተግባሩን ቀጠለ ። እላይ በተጠቀሱት በአብዛኞቹ ትምህርቶች ሉተር ቢስማማም ቅሉ ፣ እሱ የተቃወመው ያለዘዴና ያለወቅቱ በችኮላና በደመፍሉነት በመስበካቸው ዜጎቻቸውን በሰላም ለመግዛት ከሚሹ ከገዥዎቻቸውና ከምእመናን በሚሰነዘረው ተቃውሞ የለውጡ ሂደት ባጭሩ ይቀጫል ብሎ በመፍራት ነበር ። ይህም የሰላም ማስፈን ተግባሩ በገዥዎች ዘንድ ተወዳጅነትንና አክብሮትን አተረፈለት።

በገዥዎች የተጫነበት የሶሻልና የኢኮኖሚ በደል ያንገፈገፈው የጀርመን ገበሬ በ1525 ዓ.ም በመንግሥቱ ላይ አምጾ በተነሣበት ወቅት ፣ ሉተር ለተበደሉት ገበሬዎች ደጋፊ ሆኖ በመቆም ፈንታ ልዑላኑን በመደገፍ ገበሬው የማያርፍ ከሆነ በሰይፍ ቆራርጡት ብሎ በይፋ በማስተማሩና እንዲፈጁ በመስማማቱ ከፍ ያለ ነቀፋ ደርሶበታል ። ትምህርቱን ተቀብለው ይከተሉት ከነበሩት ገበሬዎችም አብዛኞቹ ገሸሽ ብለው በመሪነት አብሮአቸው የተጋፈጠውን የቶማስ ሙንዜርን የአናባፕቲስት (ዳግም አጥማቆች) እምነት ተከተሉ ።

ቻርልስ አምስተኛ ደመኛ ጠላቱን የፈረንሳይን ንጉሥ ቀዳማዊ ፍራንሲስን ድል ካደረገ በኋላ የሉተርን ተከታዮች ለማጥፋት በማሰብ መጀመሪያውን የእስፒር ጉባኤ በ1526 ዓ.ም ጠራ ። እንደ አጋጣሚ የቱርኮች ጦር በሐንጋሪ በኩል እየገፋ ስለመጣ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የሆኑ መሪዎች በኅብረት ቱርኮችን ለመቋቋም እንዲችሉ በማሰብ በጉባኤው ላይ የተገኙት ሉተርንና ተከታዮቹን በማውገዝ ፈንታ ሕዝቡ እያንዳንዱ የጀርመን ክፍለ ሀገር (ራስ ገዝ) የሚያስተዳድረው ልዑል (መስፍን) የሚቀበለውን እምነት እንዲከተል የሚያጐናጽፍ የሃይማኖት ነጻነት ወሰኑ ። ይህንኑ ውሳኔ መሠረት በማድረግ የሉተር ትምህርት እየተስፋፋ ሄደ ። በሉተራውያን ግዛት የነበሩ የካቶሊክ ጳጳሳትና ካህናት ተባረሩ ። የገዳማት ሀብት ተወርሶ ከፊሉ ለአብያተ ክርስቲያናት ማስተዳደሪያና ለትምህርት ቤቶች ማካሄጃ ሲሆን ፣ ከፊሉ ደግሞ ወደ ልዑላኑ ካዝና ገባ ።

በአጠቃላይ ምንም እንኳ በአውሮጳ የአንደኛነትን ደረጃ ይዞ



www.ethiopianorthodox.org

የነበረው የእስጳኙ ንጉሥ ቻርልስ ቢሆንም ፣ በየጊዜው ከፈረንሳይ ነገሥታት ጋር ያደረገው የፖለቲካ ግጭት (ጦርነት) ፕሮቴስታንቶች ያለ ንጉሥ ቻርልስ ተጽእኖ እምነታቸውን በነጻ እንዲያስፋፉ ፋታ በመስጠት ረድቷል ።

በ1529 ዓ.ም በተደረገው በሁለተኛው የእስፒር ጉባኤ ላይ ከተሰበሰቡት ብዙኃኑ የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ስለነበሩ የሚከተለውን ወሰኑ። ሉተራውያን በብዛት በማይኖሩባቸው ክፍላተ ሀገር የሉተር ትምህርት እንዳይሰጥ ፣ የሉተር ተከታዮች በብዛት በሚኖሩባቸው ክፍላተ ሀገር ውስጥ ደግሞ ካቶሊኮች እምነታቸውን በነጻ እንዲያከናውኑ በማለት በድምጽ ብልጫ በመወሰኑ ምክንያት ፣ ይህንኑ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ውድቅ ለማድረግ ያልቻሉ የሉተርን ትምህርት የሚከተሉ ልዑላን ግልጽ ተቃውሞአቸውን (ፕሮቴስታቸውን) ስላቀረቡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፕሮቴስታንት (ተከራካሪ) የሚል ስም ወጣላቸው ።

ጀርመን ውስጥ ካቶሊኮች በብዛት የሚኖሩበትን የደቡቡን ክፍል ያስተዳድሩ የነበሩት ካቶሊካውያን ልዑላንና መሳፍንት በንጉሥ ቻርልስ ድጋፍ በሰሜኑ ክፍል በብዛት የሚኖሩትን ፕሮቴስታንቶች ለማጥፋትና የካቶሊክን እምነት በመላ ጀርመን ለማስፋፋት በመካከላቸው የጦር ኅደኝነት መሠረቱ ። የሉተር ደጋፊ የነበረው የሳክሶን ክፍለ ሀገር ገዥ ልዑል ፍሬደሪክና ሌሎችም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይና ደጋፊ የነበሩ ልዑላን ከካቶሊኮች ሊሰነዘርባቸው የታቀደውን አደጋ ለመቋቋም የፕሮቴስታንት ሊግ (አንድነት) መሠረቱ ። ከዚህ ላይ መገንዘብ የሚያሻ የካቶሊክን እምነት ደጋፊዎችም ሆኑ የፕሮቴስታንትን እምነት ደጋፊ ዎች ያካሄዱት ትግል ፣ የሚከተሉትን የየራሳቸውን ሃይማኖት ለመደገፍ ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት ስም ግዛታቸውንም ለማጠናከር መሆኑን ነው ።

ካቶሊካውያን ልዑላን የፕሮቴስታንትን እምነት ተከታዮች በጦር ኃይል ለመደምሰስ ባሰፈሰፉበት ወቅት ሉተርና ዝዊንግል ስለ ቅዱስ ቊርባን በነበራቸው የተለያየ አመለካከት (አተረጓጐም) ምክንያት በመካከላቸው ስምምነት ሊገኝ ስላልተቻለ በ1529 ዓ.ም የሔሱ ልዑል ፊልጶስ ሁለቱ ወገኖች ማርበርግ ምሽግ ውስጥ ተገናኝተው በመካከላቸው ያለውን የእምነት ልዩነት በውይይት አስወግደው አንድነት እንዲመሠርቱ ያደረገው ሙከራ ሳይሳካ ቀረ ። ይኸውም ሉተር ስለ ቊርባን



www.ethiopianorthodox.org

ከነበረው የወግ አጥባቂነት እምነት በተጨማሪ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት የጌታ መስቀል ፣ ሻማ ማብራት ፣ በቅዳሴ ጊዜ የካህናት አልባሳት ወዘተ. እንዲሠራባቸው አድርጓል ። በዚህም ከዝዊንግልና ከካልቪን ወቀሳ ተሰንዝሮበታል።

ሉተር ከሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን ቍርባንንና ጥምቀትን ቢቀበልም ቅሉ ስለቍርባን የነበረው እምነት ከዝዊንግልና ከካልቪን ለየት ያለ ነው ። ሉተር የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በሲቪል አስተዳዳሪ ዎች እጅ እንዲገባ አድርጓል ። በዚያን ወቅት ከምእመናን ቤተ ክርስቲያንን የሚያስተዳድር ኮሚቴ የሚሾሙ የሲቪል አስተዳዳሪዎች ስለነበሩ በጀርመን የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ለብዙ ጊዜ በመንፈሳዊው ተግባር ድክመት ይታይ ነበር ። ካህናትም እንዲያገቡ ፤ ከምእመናንም መካከል ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ብቃትና ችሎታ ያላቸው በካህንነት እንዲያገለግሉ ተደረገ ። ሉተር በጀርመንኛ ከተረጐ መው መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ ለምእመናንና ለወጣቶች መማሪያ የሚያገለግል አጠር ያለ ፣ ለካህናትና ለምሁራን የሚያገለግል ደግሞ ሰፋ ያለ ሁለት የሰንበት ትምህርት ማስተማሪያ (ካቲኪዝም) መጻሕፍትና የጸሎት መጻሕፍት አዘጋጅቷል ።

ከጀርመን ውጭ የሉተር ትምህርት በዴንማርክ ፣ በኖርዌ ፣ በስዊድን ወዘተ. ተሰብኮ በምእመናን ተቀባይነትን አገኘ ። የሉተርን ትምህርት የተቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት "ሉተራውያን" በሚል ስም ይጠራሉ ።

ሉተር በዐረፈ በዓመቱ በ1546 ዓ.ም ሁለቱ ወገኖች ጦርነት ገጥመው ለጊዜው ካቶሊኮች ድል ማድረግ ጀምረው ነበር ። ቀስ በቀስ ግን የፕሮቴስታንቶች ጦር የካቶሊኮችን ሠራዊት ስላሸነፈ በ1555 ዓ.ም አግስቡርግ ውስጥ በተደረገው ጉባኤ ጦርነቱ እንዲቆም ፤ የካቶሊክና የሉተራን እምነቶች አውሮጳ ውስጥ ሕጋዊ ሃይማኖቶች መሆናቸው ተወሰነ ። እንዲሁም ከ1552 ዓ.ም በፊት በሉተራውያን እጅ የነበሩ መሬቶች (ርስቶች) ሕጋዊ ሀብታቸው መሆናቸው ፤ ምእመናንም የየክፍለ ሀገራቸው ገዥ የተቀበለውን እምነት እንዲከተሉ ፤ ለመከተል ፈቃደኞች ያልሆኑት ግን በእነሱ እምነት ተከታይ ገዥ ወደሚተዳደረው ክፍለ ሀገር (ራዝ ገዝ) ሄደው በሰላም እንዲኖሩ ወዘተ. ተወሰነ ። የሉተራን እምነት



www.ethiopianorthodox.org

መሠረትም በ1530 ዓ.ም በማላንክቶን የተዘጋጀው "የአግስቡርግ የሃይማኖት መግለጫ" የተባለው መሆኑ ተገለጸ ። ይህ የአግስቡርግ የሰላም ስምምነት በካቶሊኮችና በፕሮቴስታንቶች መካከል ለሠላሳ ዓመታት የተካሄደው ጦርነት እስከተጀመረበት እስከ 1618 ዓ.ም ድረስ ከሞላ ጐደል ጸንቶ ሲሠራበት ስለቈየ ፕሮቴስታንቶች በሰላም እምነታቸውን ለማስፋፋት ቻሉ ።

የሉተርና የካልቪን ተከታዮች ከግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር በእምነት አንድነት ለመመሥረት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀርቷል ። ይኸውም ማላንክቶን በ1559 ዓ.ም ለቊስጥንጥንያው ፓትርያርክ ለዳግማዊ ዮሳፋት "የአግስቡርግ የሃይማኖት መግለጫ" የተባለውን መሠረተ ሃይማኖት በግሪክኛ አስተርጒሞ ቢልክለት ሳይቀበለው ቀረ ። ትንሽ ዘግየት ብሎ ደግሞ የቱቢንገን መንፈሳውያን መምህራን ለቊስጥንጥንያው ፓትርያርክ ለዳግማዊ ኤርምያስ በሉተራውያን ሃይማኖት ትምህርት መሠረት ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት አንድ ሊሆኑ የሚችሉበት መንገድ እንዲጠና ቢጠይቁ ፣ ሉተራውያን ስለ ጌታ ሥጋና ደም ፣ ስለ ማዕርገ ክህነት ወዘተ. የሚያስተምሩት ስሕተት ስለሆነ ፓትርያርኩ ጥያቄውን የማይቀበል መሆኑን ገለጸላቸው ።

እንዲሁም ካልቪኒስቶች በበኩላቸው ከግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድነት ለመፍጠር ባደረጉት ጥረት ከቊስጥንጥንያው ፓትርያርክ ከቄርሎስ ሉካሪስ (1572–1638) ጋር ስምምነት ደርሰው ነበር። ነገር ግን የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ይህንኑ ስምምነት በጥብቅ በመቃወም ሉካሪስን ከመንበረ ፓትርያርኩ አውርደው ስምምነቱን ሠረዙት ። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አባቶች በ1638 ዓ.ም ፣ ቊስጥንጥንያ ውስጥ ፤ በ1640 ዓ.ም ኪየቭ ውስጥ ፤ በ1642 ዓ.ም ጃስየ ውስጥ ፤ በ1672 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ውስጥ በአደረጉአቸው ሲኖዶሶች ሉካሪስ ያዘጋጀው የካልቪንን ትምህርት የሚያንጸባርቀው የመሠረተ ሃይማኖት ጽሑፍ (መጽሐፍ) ይዘት ተወግዟል ።

## መ) አናባፕቲስቶች (ዳግም አጥማቂዎች)

በዐሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የተነሡት አናባፕቲስቶች



www.ethiopianorthodox.org

በሕፃንነት የሚፈጸመውን ጥምቀት በጥብቅ በመቃወም ወደነሱ እምነት የገቡትን ክርስቲያኖች ሁሉ እንደገና ደግመው አጠመቁ ።

በ1522 ዓ.ም ዊተንበርግ ውስጥ እስቶርች ፣ ሙንዘርና ከዝዊኩ የሄዱ ነቢያት ነን ባዮች ይህንኑ እምነታቸውን ማስተማርና በተግባር ላይ ማዋል (እንደገና ማጥመቅ) በመጀመራቸው ምክንያት የተነሣው ሁከት በሉተር ስብከት መብረዱን ቀደም ሲል ተመልክተናል ።

በ1525 ዓ.ም በኮንራድ ግሬቤልና በፌልፕስ ማንዝ መሪነት የተሰበከው የአናባፕቲስቶች ትምህርት ስዊዘርላንድ ውስጥ በዙሪክ አካባቢ እየተስፋፋ ሄደ ። የዙሪክ ከተማ መንግሥት በ1526 ዓ.ም በአናባፕቲስቶች ላይ አሰቃቂና ጠንካራ እርምጃ እንዲወሰድ አደረገ ። ይኸውም እርምጃ እንዲወሰድባቸው ውሳኔውን ካስተላለፉት ባለ ሥልጣኖች መካከል አንዱ አስተምሮ በማሳመን ሊመልሳቸው ያልቻለው ዝዊንግል ነበር ።

ከ1525 እስከ 1528 ዓ.ም ድረስ በጀርመን ፣ በተለይም ትራስበርግና አግስቡርግ ውስጥ ንቅናቄው ተስፋፍቶ ነበር ። የንቅናቄው አባላት የሀገርን ጸጥታ ለማደፍረስና መንግሥት ለማናጋት የተነሡ አመጸኞች ናቸው ተብሎ በብዙዎች ዘንድ ይታመን ስለነበር በየሀገሩ መንግሥታትና አስተዳዳሪዎች ትእዛዝ ከፍ ያለ ሥቃይ ደርሶባቸዋል ። ቀደም ሲል በ1529 ዓ.ም እስፒርስ ውስጥ በተደረገችው ጉባኤ የተገኙት የካቶሊክና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ስለመናፍቃን ቅጣት በነገሥታቱ የተላለፈውን ትእዛዝ በማጽደቃቸው እንደገና ያጠመቁና የተጠመቁ ሁሉ ያለ ሕጋዊ ፍርድ እንዲታሰሩና እንዲገደሉ ተወሰነ ። በዚሁ ውሳኔ መሠረት በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ አናባፕቲስቶች ተፈጅተዋል ።

በመጀመሪያ ጊዜ ሉተር በአናባፕቲስቶች ላይ በሕገ ወጥ መንገድ የሚፈጸመውን ቅጣት ተቃውሞ ነበር ። ነገር ግን ንቅናቄአቸው እየተስፋፋ መሄዱን በመመልከት በ1530 ዓ.ም የየሀገሩ ገዥዎች ይህንኑ ንቅናቄ በሰይፍ እንዲያቆሙት አስተማረ ። አናባፕቲስቶች ግን የተለያዩ ቅጣቶችንና ስደቶች ቢገጥሙአቸውም ቅሉ ፣ ከሥቃዩ ያመለጡት በተሰደዱባቸው ሀገሮች ማለት በጀርመን ፣ በስዊዘርላንድ ፣ በኔዘርላንድ ወዘተ. ተግተው ስላስተማሩ ንቅናቄው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ ሄደ ። ሙንዘር፣ ዋልድሸትና መሰሎቻቸው የጀርመን ገበሬዎችን አመጽ በመደ



www.ethiopianorthodox.org

ገፍ በጦርነቱ ላይ አብረው ስላለቁ ከሞት የተረፉት ገበሬዎች ከልውላኑ ጐን በመሆን አብሮ የተቃወማቸውን የሉተርን ትምህርት ርግፍ አድር ገው ትተው የአናባፕቲስቶችን ትምህርት ተቀበሉ ።

ኒዘርላንድ ውስጥ ሜኖ ሲሞንስ ፣ አውስትርያ ውስጥ ጃኮብ ሑተር ይህንኑ ንቅናቄ አስፋፉ ። ሜኖናይትና (ሜኖናውያንና) ሑተራይት (ሑተራውያን) የተባሉት ንቅናቄዎች በስዊዘርላንድ ፣ በአሜሪካ ፣ በካናዳ፣ በሀንጋሪ ፣ በሞራብያ ፣ በፕሩሲያ ፣ በፖላንድ ፣ በጀርመን ፣ በሩሲያና በሌሎች ሀገሮች ተሰራጭተው እምነታቸውን አስፋፍተዋል ። የዚህ ንቅናቄ ተከታዮች ጦርነትን ፣ መሐላን ፣ መጠጥና ዳንኪራ ቤቶች መገኘትን ወዘተ. የሚቃወሙና ተግባረ ዕድን የሚያስፋፉ ናቸው ። በሚያካሂዱአቸው የተግባረ ዕድ ሥራዎች የተመረቱትን በቀላል ዋጋ ያለ ብዙ ትርፍ ሸጠው ገንዘቡን በኅብረት ይጠቀሙበታል ። ከፊሉንም ለድሆች መርጃ ያውሉታል ። ባቋቋሙአቸው የጐጆ ኢንዱስትሪዎችና ታላላቅ ኢንዱስትሪዎች ለሰው ልጆች ማጥፊያ የሚውሉት ጐራዴዎች ፣ ጦሮች ፣ ጠመንጃዎች ወዘተ. እንዲሠሩ አይፈቅዱም ።

የግል ሀብት ፀረፍቅር ነው በማለት አብዛኛውን ጊዜም የግል ሀብትን አጥፍተው ፣ ባላቸው በጋራ እየተጠቀሙ በኅብረት መኖርን ያዘወትራሉ ። የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በቅርብ ጊዜ ውስጥ ይፈጸማል በማለት ጊዜ ወስነው ቢያስተምሩም ቃሉ ትንቢታቸው ሳይፈጸም ቀረ ።

የቤተ ክርስቲያንንም ብሔራዊነት ይቃወማሉ ። ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጻድቃንን ሥዕሎች ወዘተ. አስወግደዋል ። እምነታቸውን በተግባር ለመግለጽ በሚያደርጉት ሐሴትና ፈንጠዝያ (ኤንሱሲያዝም) በመገፋፋት አንዳንድ ጊዜ ሕገ ወጥ ተግባሮችን ፈጽመዋል ።

ይኸውም በ1534 ዓ·ም በቤርናርድ ሮዝማን ፣ በጆን ማቲያስ ወዘተ· የሚመሩ ራዲካል (ተስፈንጣሪ) አናባፕቲስቶች ሙንስቴር የተባለችውን ከተማ በጦር ኃይል ይዘው የጭቁን ቅዱሳን መጠጊያ ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በማለት ሰይመው ጆን ቤውኬልስን አነገሡ ። በግዛታቸው ውስጥም በብሉይ ኪዳን ትምህርት መሠረትና የዜጐቻቸውንም ቊጥር ለማብዛት በማሰብ ብዙ ማግባትን ፈቀዱ ። በዚሁ መሠረት ቤርናርድ ሮዝማን ዘጠኝ ሚስቶችን አግብቷል ። ሀብትና ንብረትም በዐዋጅ የጋራ እንዲሆን ተደረገ ። ይህንኑ ሕግ የተቃወሙ ሁሉ ተገደሉ ። እንደገና



www.ethiopianorthodox.org

አንጠመቅም ያሉ ምእመናንም ከመኖሪያቸው ተባረሩ ። ሆኖም የከተማ ይቱ ጳጳስና አስተዳዳሪ በካቶሊካውያንና በሉተራውያን ወታደሮች እርዳታ በ1535 ዓ·ም ድል አድርጎ ከተማዋን ያዘ ። ከጦርነቱ የተረፉት የአመጹ መሪዎችም በፍርድ ተገደሉ ። ባጠቃላይ አናባፕቲስቶች በሉተር፣ በዝዊንግል ፣ በካልቪንና በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በየጊዜው ተወግዘዋል ።

አናባፕቲስቶች በብዙ ክፍል የተከፋፈሉ በመሆናቸው ምክንያት የሚያስተምሩትም የተለያየ ስለሆነ ከላይ ባጭሩ የተገለጸው የጥቂቶቹ ታሪክ ብቻ ነው ።

እምነትን በነጻ የመከተልና ሐሳብን የመግለጽ መብትን ለመቀዳ ጀት ከፕሮቴስታንቶች ሁሉ በፊት ትግሉን የጀመሩት አናባፕቲስቶች መሆናቸው ይተረካል ።

ባፕቲስት ፣ ኲአኬርስና ብራዘሬን በሚል ስም የሚጠሩት ፕሮቴስ ታንቶች ከአናባፕቲስቶች የተገኙ ባይሆኑም ቅሉ ፣ እምነታቸው ከአናባፕ ቲስቶች እምነት ጋር ግንኙነት አለው ።

ባጠቃላይ እላይ እንደተገለጸው የአናባፕቲስቶችን ትምህርት በመ ቃወም የካቶሊክና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በየጊዜው አውቃይ ተዋቸዋል ።

## ሠ) በኡልሪች ዝዊንግልና በጆን ካልቪን ስዊስ (ስዊዘርላንድ) ውስጥ የተካሄደው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና የመሠረተ ሃይማኖት ለውጥ

የሉተር ትምህርት ጀርመን ፣ ዴንማርክ ፣ ኖርዌና ስዊድን ውስጥ ተስፋፊቶ የየሀገሮቹ መንግሥታት ሃይማኖት ሲሆን ፤ ስዊዘርላንድ ውስጥ ከሉተር ትንሽ ለየት ያለ የፕሮቴስታንት ትምህርት መስፋፋት ጀመረ ። በስዊዘርላንድ የተጀመረችው የሪፎርምድ (የታደሰች) የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሉተር ካስተማረው ቀለል ያለ ስለነበረ በፈረንሳይ ፣ በእስኮትላንድ ፣ በሀንጋሪ ፣ በሖላንድ ፣ በዛ ባሉ የጀርመን ክፍላተ ሀገር ፣ በእንግሊዝ ፣ በሰሜን አሜሪካ ወዘተ በቀላሉ ተቀባይነትን በማግኘት ሊስፋፋ ቻለ ።

በስዊዘርላንድ የተነሡት ፕሮቴስታንቶች የካቶሊክን ቤተ ክርስቲ



www.ethiopianorthodox.org

ያን ሥርዓትና እምነት በሙላ አስወግደው ለእምነታቸው መሠረት ያደረጉ መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ነው ። ከአምልኮ ቦታዎችም (ከቤተ ክርስቲያናቸውም) የጻድቃንን አጽም ፣ ሥዕል ፣ ሐውልት ወዘተ· አስወገዱ ። ወደ ተቀደሱ ቦታዎች ሄዶ ለመሳለም የሚደረገውን ጉዞ ሰረዙ። በዚህ አኳኋን ጀርመን ውስጥ በሉተር ከተካሄደው ለውጥ ይልቅ ይህኛው የበለጠ ተራማጅ ነበር ።

የስዊስን የሃይማኖት ለውጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የመራው ኡልሪች ዝዊንግል (1484–1531) ስዊዘርላንድ ውስጥ በ1484 ዓ·ም ከገበሬ ቤተሰብ ተወልዶ እድሜው ለትምህርት ሲደርስ በርኔና ባሴል በነበሩት ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በ1506 ዓ·ም ማዕርገ ክህነት ተቀብሎ ቤተ ክርስቲያንን ያገለግል ጀመር ። በ1513 ዓ·ም ከስዊስ በፖፑ ለተቀጠሩ ወታደሮች በአበ ነፍስነት አገልግሏል ። በ1518 ዓ·ም የዙሪክ ካቴድራል ሰባኪ ሆኖ ከተመደበበት ጊዜ ጀምሮ ለጻድቃን የሚደረገውን ስግደት ፣ በደጋግ ሥራዎች መዳንን ፣ የፐርጋቶሪን መኖር ፣ የአጽዋማትን ጊዜ ውሳኔ ፣ ማዕርገ ክህነትን ፣ የካህናትን በድንግልና መኖር ፣ ልብሰ ተክህኖን ፣ ሥርዓተ ቅዳሴን ፣ በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ሥዕሎችን ፣ የፖፑን ሥልጣን ፣ የስዊስ ተወላጆች በፖፖች ፣ በፈረንሳይና በሌሎች ነገሥታት ለወታደርነት እየተቀጠሩ መሄድን በጥብቅ በመቃወም አስተ ማረ ። የእምነት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ መሆኑን በመግለጽ ፣ ባጠቃላይ የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት በመቃወም በሚያስተምርበት ወቅት የዙሪክ ከተማ ምክር ቤት አስተዳዳሪዎችና ምእመናን በትምህርቱ በመርካት በ1522 ዓ·ም ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነጻ የሆነች የሪፎርምድ (የታደሰች) ቤተ ክርስቲያን አቋቋሙ ። ሥርዓተ ጸሎቱም በላቲን መሆኑ ቀርቶ ምእመናን በሚረዱት በጀርመንኛ ቋንቋ ይፈጸም ጀመር ። የካቶሊኮችን ገዳማት ሀብት ወርሰው አዲስ ለተመሠረ ተችው ቤተ ክርስቲያን ማስተዳደሪያ ፣ ለትምህርት ቤቶች ማቋቋሚያና ለሆስፒታሎች ማሠሪያ አደረጉት ።

ከ1528 ዓ·ም ጀምሮ ተራማጅ (ራዲካል) የነበረው የዝዊንግል ትምህርት ቤርን ፣ ባሴል ወዘተ በተባሉት የስዊዘርላንድ ነጻ ከተማ ኑአሪዎች ዘንድ ተቀባይነትን ስላገኘ ተስፋፋ ። እነዚህም የፕሮቴስታን ትን እምነት የተቀበሉ ሪፐብሊክ የነበሩ ከተማ አስተዳዳሪዎች በዝዊን


www.ethiopianorthodox.org

ግል ትምህርት መሠረት የእምነትና የአስተዳደር ለውጥ አደረጉ ፡፡

ቀደም ሲል ባካሄዱት ከባድ ጦርነት ከሮማ ኤምፓየር ንጉሥ አገዛዝ ነጻ ወጥተው ስዊስ ውስጥ በፌዴሬሽን ይተዳደሩ ከነበሩት ከዐሥራ ሦስቱ ነጻ ከተሞች (ኮንቶንስ) የካቶሊክን እምነት የሚከተሉ የአምስት ነጻ (ኦቶኖሞስ) ከተሞች መሪዎች አንድነት መሥርተውና ተባብረው በኦው ስትርያው ንጉሥ በፌርዲናንድ እየተረዱ ዙሪክ በነበሩት ፕሮቴስታንቶች ላይ ተነሡ ፡፡ እነሱም ቅድመ ዝግጅት ካላደረጉት ከዝዊንግል ተከታዮች ጋር ካፔል ከተባለ ቦታ ላይ በ1531 ዓ.ም ጦርነት ገጥመው ሳለ ዝዊንግልም ጦሩን መዞ በጀግንነት ሲዋጋ ከጦርነቱ ሜዳ ላይ ዐረፈ ፡፡ ከጦርነቱ በኋላ እያንዳንዱ ነጻ ከተማ የየራሱን አምልኮ በነጻ እንዲፈጽም የሚያስችል ስምምነት ተደረገ ፡፡ በስዊስ የተካሄደው ለውጥ በዝዊንግል ቢጀመርና "ሪፎርምድ" የተባለው ቅጽል ቢሰጠውም እንኳ ፣ መሠረቱ እየጠበቀና እየተስፋፋ የሄደው ቀጥለን እንደምንመለከተው በካልቪን ትጋት ነው ፡፡ በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ዘመን አጋማሽ አካባቢ ዙሪክ የነበሩ የዝዊንግል ተከታዮች ከካልቪን ተከታዮች ጋር በስምምነት አንድ ሆኑ ፡፡ በዚህ አኳኋን ጀኔቫ ፣ ዙሪክ ፣ ቤርኔ ፣ ባሴል ወዘተ. የነበሩት ካልቪኒስቶች እምነታቸውን በትጋት በየሀገሩ ማዳረስ (ማሰራጨት) ጀመሩ ፡፡

ከዝዊንግል ዕረፍት በኋላ የተነሣው ጆን ካልቪን (1509–1564) ፈረንሳይ ውስጥ ኖዮን እተባለች ከተማ በ1509 ዓ.ም ተወለደ ፡፡ በኦርሌአንስ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ በ1531 ዓ.ም አባቱ ስለዐረፈና የወደፊት ሕይወቱን በራሱ ፍላጎት የመምራት መብት ስላገኘ ፣ ከኦርሊያንስ ወደ ፓሪስ ተመልሶ ላቲን ፣ ግሪክኛ ፣ እብራይስጥና ቴዎሎጂ አጠና ፡፡ ወዲያው እግዚአብሔር እንደጠራው ስለተረዳ የክርስት ናን ትምህርት ማስፋፋት ተቀዳሚ ተግባሩ መሆኑን አምኖ ከፕሮቴስታን ቶች ጋር ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብና በማኅበር መጸለይ ጀመረ ፡፡ እንዲሁም የፖፑ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበላይነት በቅዱሳት መጻሕፍት ያልተደገፈ የአምባገነንነት (የፈላጭ ቆራጭነት) ሥልጣን ነው የሚል እምነቱን መግለጽ ጀመረ ፡፡ ከፕሮቴስታንቶች ጋር ባደረገው ግንኙነትና በፖፑ ሥልጣን ላይ ባንጸባረቀው ተቃውሞ ምክንያት ካቶሊካውያን ባለ ሥልጣኖች ይዘው ለማሰር ስለፈለጉት ከፓሪስ ሸሽቶ


www.ethiopianorthodox.org

በመውጣት ወደ እስትራስበርግ ሄደ ። እዚያም የእስትራስበርግ ዩኒቨር ሲቲ የቴዎሎጂ መምህርና የፕሮቴስታንቶች መሪ ማርቴን ቡሴር ተቀብሎ አስተናገደው ።

ካልቪን የፕሮቴስታንትን እምነት ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ ይህንኑ እምነት በግምባር ቀደምትነት ተግቶ አስተማረ ። በ1535 ዓ·ም በስደተኛ ነት ባሴል ሄዶ ጥናቱን ቀጠለ ። እዚያው ሳለ በ1536 ዓ·ም የፕሮቴስታን ትን ቴዎሎጂ የሚያብራራውን ከፍ ያለ ዝና ያተረፈለትን "የክርስትና ሃይማኖት ተቋም" የተባለውን መጽሐፍ በላቲን አዘጋጅቶ አሳተመ ። ይህም መጽሐፍ የተዘጋጀው የሐዋርያትን የሃይማኖት ውሳኔ መሠረት በማድረግ ነበር ። ጽሑፉም የሚገልጸው ሉተር ፥ ካልቪንና መሰሎቻቸው የሚያስተምሩት አዲስ ቴዎሎጂ ሳይሆን ፥ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በየጊዜው የተጨመሩትን የተንዛዙ መሠረተ ሃይማኖቶች ትተው ጌታ ፥ ሐዋርያትና በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ክፍለ ዘመናት የተነሡት ክርስቲያ ኖች ባስተማሩት ትምህርት ላይ ብቻ እንዲወሰኑ ለማስገንዘብ ነው ይላሉ። ይኸው መጽሐፍ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተሻሽሎና ይዘቱም በዛ ብሎ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ከተጻፈ በኋላ ወደ ጀርመንኛ ፥ እንግሊዝኛ ፥ ኢጣልያንኛ ፥ እስጳንኛ ወዘተ· ቋንቋዎች ተተርጕሞ ለካህናትና ለምእመ ናን ከፍ ያለ ጥቅም አበርክቷል ። ከዚህም ጽሑፍ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስን አብራርቶ ተርጕሟል ።

በ1536 ዓ·ም ካልቪን ከፈረንሳይ የተሰደዱ ፕሮቴስታንቶች በሚኖ ሩበት በጀኔቫ በኩል ወደ እስትራስበርግ ሲያልፍ የከተማዋ ፓስተር (ቄስ) ዊልያም ፋሬል የከተማው ሕዝብ ተሰጥኦ ያለውና ጠንካራ መምህር ስለሚያሻው ካልቪን እዚያው ሆኖ እንዲያስተምር በእግዚአብሔር ስም ተማጸነው ። እሱም ይህ ጥያቄ የአምላክ ጥሪ መሆኑን በማመን ጀኔቫ ተቀምጦ ማስተማር ጀመረ ።

ወዲያው ለቤተ ክርስቲያኑ የአስተዳደርና የእምነት መመሪያ የሚሆን የመሠረተ ሃይማኖት መጽሐፍ አዘጋጀ ። ለልጆችም መማሪያ የሚሆን የውሉደ ክርስቲያን (የሰንበት) ትምህርት ማስተማሪያ መጽሐፍ አዘጋጀ ።

ካልቪን ጀኔቫ ከመሄዱ በፊት በሕዝቡ ዘንድ ሥር ሰደው የነበሩትን እንደ ቁማር ፥ ስካር ፥ ጭፈራ ፥ ዳንኪራ ፥ ዝሙት ወዘተ· የመሳሰሉትን ወደ



www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአት የሚመሩ ተግባሮች በማጥፋት እንደ መጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በሐዲስ ኪዳን ትምህርት መሠረት በመኖር በአካባቢው ሀገሮች ለሚኖሩት ክርስቲያኖች የፍጹም ክርስቲያንነት ሞዴል እንዲሆኑ አስተማረ ። ትምህርቱን በመቃወም እላይ የተጠቀሱትን ሕገ ወጥ ድርጊቶች ሲፈጽሙ የተገኙ ሁሉ በእስራትና በሞት እንዲቀጡ አደርጓል ።

ካልቪን እንደ ሉተር የክርስትና እምነት መገኛ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ መሆኑን ፡ ሰው በሥራው ሳይሆን በእምነት ብቻ የሚድን መሆኑን ፤ ማንኛውም ሰው ግብረ ገብ የሆነ ኑሮን ከኖረና መንፈሳዊ ትምህርት ካለው በካህንነት ሊያገለግል የሚችል መሆኑን ወዘተ አስተማረ ። እንዲሁም የእመቤታችንን ፡ የጻድቃንን ፣ የመላእክትን ክብርና ማማለድ በመቃወም አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የነበሩት የጌታ ፣ የመቤታችን የጻድቃን ፡ የሰማዕታትና የመላእክት ሥዕሎች ፣ ሐውልቶች ፣ የካህናት አልባሳት ወዘተ እንዲወገዱ አደረገ ። እንዲሁም ሉተርና ካልቪን ለጌታ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለውን የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ ይቀበላሉ ።

ካልቪን ትምህርቱን ሰምተው በማይፈጽሙት ላይ ውግዘትና ቅጣት የሚያስከትል ሕግ አወጣ ። ምንም እንኳ በስም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ቢሆኑም ቅሉ ፣ ይህ ትምህርትና ሕግ አልዋጥላቸው ያሉ የጀኔቫ አስተዳዳሪዎች ካልቪንንና ፋሬልን በወታደር ኃይል አባረሩአቸው ። ካልቪን እንደገና ወደ እስትራስበርግ ሄዶ ከፈረንሳይ ተሰደው እዚያ ለሚኖሩ ምእመናን ፓስተር (አገልጋይ ፣ ኖሉት ፣ ቄስ) ሆኖ ለሦስት ዓመታት ያህል አገለገለ ። ከሉተርና ከፊልጶስ ሜላንክቶን ጋር ለመተዋወቅ የቻለውም በዚያን ጊዜ ነበር ። የቅርብ ጐረቤቱም ከጥቂት ጊዜ በኋላ የካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የቴዎሎጂ ፕሮፌሰር የሆነው ማርቲን ቡሴር ነበር።

ካልቪን ከተባረረ በኋላ ጀኔቫ ውስጥ ብዙ ችግር ስለተፈጠረ ከከተማይቱ አስተዳዳሪዎችና መማክርት አብዛኞቹ ችግሩ እየተባባሰ የሄደው የካልቪንን ምክርና ትምህርት ሰምተው በተግባር ላይ ባለማዋላቸው መሆኑን ተገነዘቡ ። ቀስ በቀስም የከተማይቱ ነጻነት በአደጋ ላይ ስለወደቀ መፍትሔው ካልቪንን ወደ ጀኔቫ ጠርቶ በትምህርቱ መመራት መሆኑን ስለተገነዘቡ ወደ ጀኔቫ እንዲመለስላቸው ለመኑት ። እሱም እስትራስበርግ ውስጥ የጀመረውን የማስተማር ተግባር አቋርጦ መሄድን



www.ethiopianorthodox.org

አልፈቀደም ነበር ። ነገር ግን የጥንት ወዳጆቹ አጥብቀው ስለለመኑት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው በማለት ለመመለስ ተስማማ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በክርስቶስ ትምህርት መሠረት ዲሲፕሊን ፣ ግብረገብነት ወዘተ· እንዲሰፍን በማድረግ ከምክር ቤቱ አባላት ጋር በመግባባት በቴዎክራሲ (በመንግሥተ እግዚአብሔር) ሲስተም ከተማዋን አስተዳድሯል (ገዝቷል) ።

እንደ ሁለተኛ ሀገሩ በሚቈጥራት በጀኔቫ ውስጥ ለሃያ አራት ዓመታት በመስበክ ፣ በማስተማር ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በተብራራ ትርጓሜ በማዘጋጀት ወዘተ· በትጋት ሠራ ። ካልቪን ምእመናን እንደ ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ትእዛዝ መሠረት ፓስተሮችን ፣ መምህራንን ፣ ሽማግሌዎችንና ዲያቆናትን ለቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪነት (መሪነት) መርጠው እንዲተዳደሩ ፤ በመንፈሳዊው ተግባርም ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥቱ ተጽእኖ ነጻ እንድትሆን ፤ ሲቪሉ የመንግሥት አስተዳደርም በእግዚአብሔር የተመረጠ ስለሆነ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን አንዱ በሌላው ጉዳይ ጣልቃ ሳይገባ ተባብረው መሥራት እንደሚገባቸው ገልጿል ። በዚህ አኳኋን ሉተር ቤተ ክርስቲያን በልዑላን ሥር እንድትተዳደር ሲያደርግ ፣ ዝዊንግል ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት በአንድነት እጅና ጓንት ሆነው እንዲሠሩ ሞክሮ ነበር ። ካልቪን ግን ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ በመተዳደር ከሀገሩ መንግሥት ጋር ተባብራ እንድትሠራ አስተምሯል ።

እንዲሁም ካልቪን የሰው ልጆች አዳኝ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ሲገልጽ "የማንኛውም ሰው ዘለዓለማዊ ድኅነትም ሆነ ጥፋት (ቅጣት) አስቀድሞ በእግዚአብሔር ተወስኗል" በማለት አስተምሯል ።

ካልቪን ጀኔቫ ውስጥ የማስተማር ተግባሩ ሊከናወንለት የቻለው ተግቶ ከማስተማሩ በተጨማሪ የፕሮቴስታንትን እምነት በመከተላቸው ምክንያት ከደረሰባቸው ሥቃይ ለማምለጥ ከፈረንሳይ ፣ ከእስኮትላንድ ፣ ከኢጣልያ ፣ ከኔዘርላንድና ከኢንግላንድ ተሰደው ወደ ጀኔቫ ከገቡት ፕሮቴስታንቶች በአብዛኞቹ በመደገፉም ጭምር ነው ። ሆኖም የእስጳኝ ተወላጅ የነበረው ሚካኤል ሴርቤቱስ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት (ዶክትሪን) በመካዱ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ባለ ሥልጣኖች ተይዞ በእሳት እንዲቃጠል ተፈርዶበት ሳለ ፣ ከእስር ቤት አምልጦ ጀኔቫ ከገባ



www.ethiopianorthodox.org

በኋላ ከክሕደቱ በተጨማሪ በከተማዋ ያሉ ተቀዋሚዎቹን በመቀስቀስ ረብሻ ያስነሳብኛል ብሎ በመሥጋት በ1553 ዓ.ም ካልቪን ከከተማዋ ሹማምንት ጋር በመስማማት አስይዞ በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት አደረገ። በዚህም ድርጊቱ ከብዙዎች ዘንድ ስሙን ያጐደፉ ትችቶች ተሰንዝረውበታል ።

በካልቪን የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን "የፕሬዝቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን" ትባላለች ።

በከፍተኛ ትምህርት አስፈላጊነት አጥብቆ ያምን ስለነበር በ1559 ዓ.ም የጀኔቫን አካዳሚ ከፈተ ። ይኸውም አካዳሚ ቁየት ብሎ በካልቪን እግር በተተካው በቴዎዶሬ ቤዛ ትጋት ከዓለማዊው ትምህርት ጋር የመንፈሳዊ ትምህርት መስጫ ማዕከል በመሆን በአውሮጳ ውስጥ ተሠማርተው ያስተማሩ ብዙ የካልቪን ተከታይ የነበሩ ካህናትንና ሚስዮናውያንን አፍርቷል ።

## ረ) በሌሎች የአውሮጳ ሀገሮች የፕሮቴስታንት (የሪፎርምድ ፣ የታደሰች ቤተ ክርስቲያን) ትምህርት መስፋፋት

የፕሮቴስታንት ትምህርት እላይ ከተጠቀሱት ሀገሮች በስተቀር በመጠኑም ቢሆን በፈረንሳይ ፣ በኒዘርላንድ ፣ በሀንጋሪ ፣ በእስጳኝ ፣ በኢጣልያ ተሰብኳል ። ይኸውም

1ኛ) ፈረንሳይ ውስጥ የካልቪን ትምህርት ተስፋፍቶ ነበር ። ነገሥታቱ ቀዳማዊ ፍራንሲስ ፣ ዳግማዊ ሔንሪ ወዘተ. በካቶሊካውያን የተደገፈውን ዙፋናቸውን አናውጸው የካልቪንን ትምህርት በሀገሪቱ ውስጥ ለማስፋፋትና ፈረንሳይን እንደ ጀኔቫ በቴዎክራሲ ሲስተም በፈላጭ ቆራጭነት (በዲክታተርነት) ለማስተዳደር የተነሡ ናቸው በሚል ፖለቲካዊ ምክንያት ፈረንሳይ ውስጥ የነበሩትን ፕሮቴስታንቶች ሲያሳድዱና ሲጨፈጭፉ ፣ በሌላው ወገን ደግሞ ጀርመን አንድነቷን በማጣት ተከፋፍላ እንድትኖር በመሻት ጀርመን የነበሩትን ፕሮቴስታንቶች ይረዱ ነበር ። ፈረንሳይ ውስጥ ተጠናክረው የነበሩትን ሁጉኤኖትስ በመባል የታወቁትን የካልቪን ተከታዮች ፣ በካልቪኒስቱ በናቫሬ ንጉሥ በሔንሪ አራተኛና በካቶሊካዊቲቱ በማርጉኤሬት መካከል ጋብቻ መሥርተው የሁለቱ እምነት ተከታዮች በመካከላቸው ሰላምን ለመመሥረት


www.ethiopianorthodox.org

ከካቶሊኮች ጋር በ1572 ዓ·ም ስምምነት አደረጉ ። በዚሁ ስምምነት መሠረት የሁለቱም ወገኖች የቅዱስ በርተሎሜዎስ በዓል ዕለት የጋብቻቸ ውን ሥነ ሥርዓት ለመፈጸምና ለማክበር ፓሪስ ውስጥ ተሰብስበው ሳለ በድንገት ሳያስቡት በንግሥቲቱ እናት በካቶሊካዊቲቱ በእቴጌ ካቴሪኔ ዲ·ሜዲስ በምሥጢር የተዘጋጁ ካቶሊኮች ፕሮቴስታንቶችን በመጨፍ ጨፍ ዐሥር ሺህ የሚሆኑትን ገደሉ ። ይህ ሁሉ ሥቃይ ቢደርስባቸውም ፈረንሳይ የነበሩ ፕሮቴስታንቶች በካቶሊኮች አልተደመሰሱም ። በ1589 ዓ·ም ወንድሙ ሣልሳዊ ሔንሪ ሲሞት ሔንሪ አራተኛ የፈረንሳይን ዙፋን ወረሰ ። ነገር ግን ምንም እንኳ የነገሥታት ዘር ቢሆንም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ በመሆኑ በሮሙ ፖፕና በእስጳኙ ንጉሥ በሚደገፉ በፈረንሳይ ካቶሊኮች ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም ። ሆኖም መንግሥቱ ጸንቶ ሀገሪቱን በሰላም ለመግዛት በማሰብ በ1593 ዓ·ም የካቶሊክን እምነት ተቀበለ ። በንጉሡ ትእዛዝ በ1598 ዓ·ም ናንቴ ውስጥ በተደረገው ጉባኤ ፕሮቴስታንቶች (ሁጉኤኖቶች) የሃይማኖትና የአምልኮ ነጻነት ስለተሰጣቸው ፈረንሳይ ውስጥ ሲካሄድ የቈየው የሃይማኖት ጦርነት ቆመ። ነገር ግን በ1685 ዓ·ም በሉዊስ ዐሥራ አራተኛ የአምልኮ ነጻነታቸውን እንደገና ስለተገፈፉ ጥቂቶቹ ወደ ኢንግላንድ ፣ ሆላንድ ፣ ፕሩሲያና አሜሪካ ሲሰደዱ አብዛኞቹ የፈረንሳይ ሪቮሉሽን እስከተጀመረ በት ጊዜ ድረስ እዚያው ሀገራቸው ውስጥ ሲሠቃዩ ኖሩ ።

2ኛ) <u>ኔዘርላንድ</u> ውስጥ የካልቪን ትምህርት ቀደም ሲል ብዙ ተከታዮችን አፍርቶ ነበር ። ሆኖም የእስጳኙ ንጉሥ ዳግማዊ ፊልፕ (ፊልጶስ) በ1555 ዓ·ም ኢንኩዚሽን የተባለውን መናፍቃን ናቸው በመባል የተጠረጠሩትን የማሠቃያ ፍርድ ቤት (ድርጅት) ስላቋቋመ በሚገዛቸው ሀገሮች ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ሲያነብ ወዘተ· የተገኘ ምእመን በእሳትና በተለያዩ መንገዶች ይቀጣ ነበር ። ይህ ዓይነቱ ቅጣት በኦሬንጁ ልዑል በዊልያም መሪነት የኔዘርላንድ (የሆላንድ) ሕዝብ ከ1568 ዓ·ም ጀምሮ ከእስጳኝ ጋር ባካሄደው ጦርነት በ1581 ዓ·ም ከቅኝ ተገዥነት ነጻ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ቀጥሎ ነበር ። ኔዘርላንድ ከእስጳኝ ነጻ ከወጣች በኋላ ግን የካልቪን ተከታዮች እምነታቸውን በነጻና በሰላም ያካሂዱ ጀመር ። ዊልያምም በ1573 ዓ·ም የካልቪንን ትምህርት በመቀበል የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ሆነ ። ከ1579 ዓ·ም ጀምሮ


www.ethiopianorthodox.org

በሀገሪቱ ደቡባዊ ክፍል ካቶሊኮች በብዛት ሲኖሩ ፡ በሰሜኑ ክፍል ደግሞ ካልቪኒስቶች በብዛት ይኖሩ ነበር ።

3ኛ) በ16ኛው ክፍለ ዘመን የካልቪን ትምህርት ሀንጋሪ ውስጥ ተስፋፋ ።

ፕሮቴስታንቶች በቻርልስ አምስተኛና ተከታዮቹ በሆኑ ካቶሊካውያን ነገሥታት በየጊዜው የተሰነዘሩባቸውን ስደቶችና ሥቃዮች በመቋቋም ከቈዩ በኋላ በ1781 ዓ·ም የሃይማኖት ነጻነት ተሰጣቸው ። እነሱም የፕሬዝቢቴሪያንን ቤተ ክርስቲያን በመመሥረት በተጠናከረ ሁኔታ ተቋቋሙ ።

4ኛ/ በእስጳኝ ንጉሥና በሮሙ ፖፕ የተቋቋመው ኢንኩዚሽኖች የማስተማር ተግባራቸውን ቢያሰናክሉባቸውም እንኳ የሉተር ተከታዮች እስጳኝና ኢጣልያ ውስጥ በማስተማር ጥቂት ተከታዮች አግኝተው ነበር። ሆኖም እስጳኝ ውስጥ የተጀመረው የሉተራውያን ንቅናቄ በ1560 ዓ·ም በርጎራኄ ቢሱ ኢንኩዚሽን መሣሪያነት ሲወድምና ሲያከትም ፡ ኢጣልያ ውስጥ ይካሄድ የነበረው ኢንኩዚሽን ግን ለዘብ ያለ ስለነበረ በሰሜን ኢጣልያ ተራራዎች አካባቢ ዋልዴኔስ የተባሉት ከጥፋት ተርፈው ነበር ። እነሱም የፕሬዝቢቴሪያንን ቤተ ክርስቲያን ሕግ (ፖሊሲ) በመከተል እስከ 1848 ዓ·ም ድረስ አምልኮአቸውን በነጻ ይፈጽሙ ነበር ።

## ሰ) በእንግሊዝ ሀገር ውስጥ የተካሄደው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና የመሠረተ ሃይማኖት ለውጥ

### (1) ኢንግላንድ ውስጥ የተካሄደው ለውጥ

በእንግሊዝ ሀገር ውስጥ የተደረገው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና የመሠረተ ሃይማኖት ለውጥ የሉተርንና የካልቪንን ትምህርት ሳይከተል በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚ ወዘተ· ምክንያት በቀጥታ በንጉሡ በሔንሪ ስምንተኛ (1509–1547) የተጀመረ ስለሆነ በጀርመን ፣ በጀኔቫ ፣ በእስኮትላንድ ወዘተ· ከተካሄዱት ለውጦች ለየት ያለ ነው ።

የለውጡ መንሥኤም ፍጹም ካቶሊካዊ የነበረው ፤ ሉተር ያስተማረውን የተዛባ ትምህርት ተቃውሞ በሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን


www.ethiopianorthodox.org

የእግዚአብሔር ጸጋ የሚሰጥ መሆኑን አብራርቶ በመጻፉ በፖፕ ልዮን ዐሥረኛ “የእምነት ጠባቂ” የሚል ክብር የተሰጠው ንጉሥ ሔንሪ መንግሥቱን የሚወርስ ወንድ ልጅ ልትወልድለት ያልቻለችውን የእስጳኝ ገዥዎች የፌርዲናንድንና የኢዛቤላን ልጅ ካቴሪኒ ዘአራጎንን ፈትቶ አን ቦሌይንን ለማግባት ፈለገ ። ፍላጎቱንም ከግቡ ለማድረስ በኢንግላንድ የፖፑ እንደራሴና የንጉሡም ዋና ባለሟል በነበረው በእንግሊዛዊው በካርዲናል ቶማስ ዌልሴይ አማካይነት ከሮሙ ፖፕ የፍች ፈቃድ ቢጠይቅ ፖፑ ከለከለው ። እሷም ተፋትታ በምንኵስና ተወስና ገዳም ገብታ እንድትኖር ብትጠየቅ ፈቃደኛ ስላልሆነች ፤ ሌላም ሰላማዊ የሆነ አማራጭ መንገድ ስለጠፋ ፤ በንጉሡ ግፊት በተመሩት የፓርላማው አባላት ውሳኔ መሠረት በ1532 ዓ·ም የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን ከቍጥጥሩ ሥር አድርጎ ከሮሙ ፖፕ ከቀሌምንጦስ ሰባተኛ አስተዳደር ነጻ የወጣች መሆኗን ወሰነ ። ካርዲናል ዌልሴይም ፍችውን በተግባር ላይ ለማዋል ፈቃደኛ ስላልሆነ በንጉሡ ትእዛዝ ከሥልጣኑ ተወገደ ። ፖፑ ይህንኑ ድርጊት እንደሰማ ንጉሡንና ተባባሪዎቹን ቢያወግዝም ቅሉ ተቀባይ አላገኘም ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለፖፑ የሚላከው ገጸ በረከትና ዓሥራት ተቋረጠ ።

በ1533 ዓ·ም ቶማስ ክራንሜርን የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን እንዲመራ የካንቴርበሪ ሊቀ ጳጳስ አድርጎ ከሾመው በኋላ ፤ በክራንሜር ትእዛዝ ከካቴሪኒ ጋር የነበረው ጋብቻ ተሰርዞ አን ቦሌይንን አገባ ። ቈየት ብሎም የንግሥት ኤልሳቤጥን እናት አን ቦሌይንን አመነዘረች በሚል ሰበብ ከፈታት በኋላ በ1537 ዓ·ም ኤድዋርድ የተባለውን ወንድ ልጅ የወለደችለትን ጄን ሴይሙርን አግብቶ ነበር ።

ከ1534 ዓ·ም ጀምሮ በሮም ፖፕና በእንግሊዝ (በኤጲስኮፓል) ቤተ ክርስቲያን መካከል የነበረው አንድነት ፈጽሞ ተቋረጠ ። ፓርላሜንቱም የሮሙን ፖፕ ሥልጣን ሰርዞ ንጉሡ የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ መሪ መሆኑን በውሳኔ አጸደቀ ። ምድራዊውን አስተዳደር ለማካሄድ የተሰየመው ፓርላማ ፖፑ በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያለውን መንፈሳዊ ሥልጣን የመሻር (የመግፈፍ) መብት የለውም በማለት በ1535 ዓ·ም የንጉሡን የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ መሪ መሆን የተቃወሙና ለንጉሡ ታማኝነታቸውን በቃለ መሐላ ለመግለጽ አሻፈረን ያሉ እነ አቡነ ጆን



www.ethiopianorthodox.org

ፊሸር ፣ ሰር ቶማስ ሞር ወዘተ· በሰይፍ ተገደሉ ።

አብዛኞቹ ካህናት ግን ከፈሎቹ በፍርሃት ፣ ከፊሎቹ ደግሞ አምነው በት የንጉሡን የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ መሪ መሆን ተቀብለው ታማኝነታቸውን በቃለ መሐላ አረጋገጡ ።

በሔንሪ ትእዛዝ በግፍ ለተገደሉት ለአቡነ ጆን ፊሸርና ለቶማስ ሞር ከሌሎች አምሳ ሰማዕታት ጋር በ1935 ዓ·ም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳንነት ማዕርግ (ክብር) ተሰጥቷቸዋል ።

ምንም እንኳ ከነዊክሊፍ ዘመን ጀምሮ ከእንግሊዝ ምሁራን ጥቂቶች ቅዱሳት መጻሕፍትን በቋንቋቸው ተርጒመው ማንበብና የሮምን ቤተ ክርስቲያን መቃወም ቢሞክሩም ከካቶሊክ እምነትና ሥርዓት እምብዛም የተለየ ጠለቅ ያለ መሠረታዊ ለውጥ ለማካሄድ አልቻሉም ነበር ። በሔንሪ ጊዜም ቢሆን በፖፑ ፈንታ ንጉሡ የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ መሪ ሆነ እንጂ እንደነ ሉተር የጐላና ተጨባጭ የሆነ ለውጥ አልተደረገም ። ሆኖም በአንድ ወቅት በነሉተር ተዘጋጅቶ በቲንዳሌና በኮቨርዳሌ ወደ እንግሊዝኛ የተተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ በየአብያተ ክርስቲያናቱ እንዲቀመጥና ምእመናንም እንዲያነቡ ቅስቀሳ እንዲደረግላቸው በነቶማስ ክሮምዌል ተወስኖ በተግባር ላይ ውሎ ነበር ። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የማይገኙ ገንዘብ ከፍሎ ለጻድቃን ሥዕሎች ሻማ ማብራት ፣ ቅዱሳን ቦታዎችን ለመሳለም መጓዝ ወዘተ· እንዲቋረጥ ተወስኖ ሲሠራበት ከቈየ በኋላ ጳጳሳቱ ይህንን የለውጥ አዝማሚያ የሚቃወም መመሪያ በማውጣት የለውጡን አዝጋሚ ሂደት በአጭሩ ገትተው ሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያንና የመሳሰሉት መሠረተ እምነቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲፈጸሙ አደረጉ ። ታላቁ ሊቅ ዊሊያም ቲንዳሌ ሐዲስ ኪዳንን ከግሪክኛ ሕዝቡ ወደሚረዳው ቋንቋ ወደ እንግሊዝኛ በመተርጐም ላይ ሳለ ፣ የፕሮቴስታንቶችን እምነት የምትከተል መናፍቅ ነህ በመባል በመሪዎች ተወግዞ እንዲሰደድ በመደረጉ የትርጒም ተግባሩን ጀርመን በምትገኝ ወርምስ ከተባለች ከተማ ውስጥ በስደት በነበረበት ወቅት ፈጽሞ በ1525 ዓ·ም አሳተመ ። በተጨማሪም የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖትና የአስተዳደር ጉድለት በመቃወም የተለያዩ ጽሑፎችን አሳትሟል ። ጽሑፎቹም በድብቅ በብዛት ኢንግላንድና እስኮትላንድ በመግባት ለካህናትና ለምእመናን ከፍ



www.ethiopianorthodox.org

ያለ ጥቅምን አበርክተዋል ። እሱም የሉተርን ትምህርት በምእመናን ዘንድ የምታሰራጭ መናፍቅ ነህ በመባል በ1536 ዓ·ም ብራስልስ አጠገብ በምትገኝ ቪልቮርዴ ውስጥ በእሳት ተቃጥሎ ሞተ ። በምእመናን እጅ የተገኙ ጽሑፎቹም እየተሰበሰቡ እንዲቃጠሉ ተወሰነ ።

ሔንሪ በ1536 እና በ1539 ዓ·ም የሃይማኖት ሚኒስትር አድርጎ በሾመው በቶማስ ክሮምዌል አማካይነት ገዳማትን ዘግቶ በቦታው የነበረውን ተንቀሳቃሽ ንብረትና መተዳደሪያቸው የነበሩትን መሬቶች በመሸጥ ብዙ ገንዘብ አገኘ ። ከዚህም ገንዘብ ጥቂቱ እንደ ኦክስፎርድና ካምብሪጅ ለመሳሰሉ ትምህርት ቤቶች መርጃና ከገዳም ለተባረሩት ጡረታ ሲውል ፡ የቀረው ለመንግሥቱ ሥራ ማካሄጃ ሆኖአል ። ንጉሡ በራሱ ግምት በመካሄድ ላይ የነበረው የመሠረተ ሃይማኖትና የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ለውጥ ሂደት ፈጣንና ከሕዝቡም ዘንድ ተቃውሞ የሚያስነሣበት መስሎ ስለታየው የለውጡን ሂደት መግታት ጀመረ ። በዚህም በመጀመሪያው የፀረ ለውጥ ዘመቻ በጸሎተ ቅዳሴ ወቅት የኅብስቱንና የወይኑን ወደ ጌታ ሥጋና ደም መለወጥ የሚክድ ፡ ለካህናት መናዘዝ አይገባም የሚል ፡ ካህናት ማግባት ይገባቸዋል የሚል ወዘተ· በስቅላት ፡ በሰይፍና በመቃጠል እንዲገደል አዘዘ ። ከንጉሡ ዓላማ ለየት ያለ አስተሳሰብ የነበራቸው ፕሮቴስታንቶችም ሆኑ ካቶሊኮች በንጉሡ ትእዛዝ ተገደሉ ። የንጉሡ ባለሟል የነበረው ቶማስ ክሮምዌልም ንጉሡን በማሳሳት ወደ ጥፋት መርቷል ፡ የሉተራንንም እምነት ይደግፋል በሚል ምክንያት በ1540 ዓ·ም ተሰይፎ ሞተ ። ንጉሡ በ1547 ዓ·ም በሞተበት ወቅት ከእንግሊዝ ጳጳሳትና ሕዝብ ከፊሉ የፕሮቴስታንቶችን ትምህርት ሲቀበል ፡ ሌላው ክፍል ደግሞ የካቶሊክን እምነት ጠብቆ መቈየትን በመምረጥ ይታመስ ነበር ።

ከሔንሪ ዕረፍት በኋላ የክራንሜር ወዳጅና ለተጀመረው ለውጥ ደጋፊ በነበረው በእናቱ ወንድም (በአጐቱ) በሴሜርሴቱ ዱክ በሔርትፎርድ ሞግዚትነት በዘጠኝ ዓመቱ የነገሠው ኤድዋርድ ስድስተኛ (1547–1553) የሉተራውያን እምነት ዝንባሌ በነበረው በአንግሊካኑ አቡነ ክራንሜር አስተማሪነት ያደገ የፕሮቴስታንቶችን ትምህርት የሚደግፍ ነበር ። እሱም በአባቱ በሔንሪ የተወሰኑትን ፀረ ፕሮቴስታንት ሕጎች (መመሪያዎች) ሁሉ ስለሰረዛቸው የተለያዩ እምነቶችን የሚከተሉ



www.ethiopianorthodox.org

ፕሮቴስታንቶች በተለይ ካልቪኒስቶች እምነታቸውን በሰላም ማስተማርና አምልኮአቸውን መፈጸም ጀመሩ ። ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሕዝቡ በሚረዳው ቋንቋ በእንግሊዝኛ ይፈጸም ጀመር ። ቅዱስ ቊርባንም እንደ ካቶሊኮች በኅብስቱ ብቻ ሳይሆን በፕሮቴስታንቶች እምነት መሠረት በኅብስትና በወይን ለምእመናን ይሰጥ ጀመር ። የላቲኑን የቅዳሴ መጽሐፍ አስወግደው በ1549 ዓ·ም የሉተርን ትምህርት መንፈስ የተከተለ የጸሎት መጽሐፍ አዘጋጅተው ይገለገሉ ጀመር ። ይህ በ1549 ዓ·ም የተዘጋጀው የጸሎት መጽሐፍ በተራማጅ ፕሮቴስታንቶች ዘንድ የወግ አጥባቂዎችን መንፈስ የተከተለ ነው ተብሎ ስለተገመተ የስዊስ ፕሮቴስታንቶች ስለ ቅዱስ ቊርባን መታሰቢያነት ፡ ስለ ጻድቃንና ቅዱሳን ሥዕሎች ከቤተ ክርስቲያን መወገድ ወዘተ· የሚያስተምሩትን የተከተለ የጸሎት መጽሐፍ በ1552 ዓ·ም ተሻሽሎ ተዘጋጅቶ የፊተኛውን ተካ ። ቀደም ሲል በሔንሪ ዘመነ መንግሥት የተለያዩ የፕሮቴስታንት እምነቶችን በመከተላቸው ምክንያት ተባረው በስደት ይኖሩ የነበሩት እነ ሪድሌይ ፡ ሑፐር ወዘተ· ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ። የፕሮቴስታንትን እምነት ደጋፊ የነበረው ክራንሜር ከስደት የተመለሱትንና በሀገሪቱ ውስጥም ሥቃዩን ታግሠው የቈዩትን ጳጳሳት አድርጎ ሾማቸው ።

በ1547 ዓ·ም ካቶሊካዊው የእስጳኝ ንጉሥ ቻርልስ አምስተኛ ጀርመን የነበሩትን ፕሮቴስታንቶች ድል በአደረገበት ወቅት የፕሮቴስታንቶች ተቋም አደጋ ላይ ስለወደቀ ብዙዎቹ ወደ እንግሊዝ ተሰደዱ ። በስደት እንግሊዝ ከገቡት ሊቃውንት መካከል አንዱ የካልቪን ወዳጅ የነበረው የእስትራስበርጉ ማርቲን ቡሴር ነበር ። እሱም በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የቴዎሎጂ ፕሮፌሰር ሆኖ አገልግሏል ። በስደት ምክንያት ወደ እንግሊዝ የገቡት ፒዩሪታንስ የተባሉት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በእንግሊዝ ሀገር የፕሮቴስታንትን እምነት ሊያስፋፉ ቢሞክሩም ቅሉ ፡ ዓላማቸው ግቡን ሊመታ አልቻለም ። ስለዚህ እስከ ዛሬ ድረስ በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓትና እምነት ከሞላ ጎደል (በከፊል) ይፈጸማል ።

በእናቷ ወገኖች በእስጳኝ ካቶሊኮች ሞግዚትነት አድጋ ኤድዋርድ በዐሥራ ስድስት ዓመቱ በሳምባ በሽታ ታሞ በ1553 ዓ·ም ከዐረፈ በኋላ በነገሠችው በንግሥት ሜሪ ቱዶር (1553–1558) ዘመነ መንግሥት



www.ethiopianorthodox.org

የካቶሊክ እምነት እንደገና በኃይል በእንግሊዝ ሀገር ተስፋፋ ። ንግሥት ሜሪ እንደ እስጳኛዊቲቱ እናቷ እንደ ካቴሪኒ ፋናቲክ ካቶሊካዊት ስለነበረች የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን ወደ ካቶሊክ (ፖፑ) መንበር ሥር ለመመለስ ቈርጣ ተነሣች ። በዕቅዷ መሠረት በ1553 ዓ.ም ማንኛውም ካህን ከመንግሥት ፈቃድ ሳያገኝ እንዳይሰብክና መጻሕፍትም እንዳያሳትም በመወሰን የፕሮቴስታንትን እምነት መስፋፋት ለማገድ ቻለች ። ወዲያው ክራንሜር ፡ ሪድሌ ፡ ኮቤርዳሌ ፡ ሑፐርና ላትሜር የተባሉት ጳጳሳት ወደ እስር ቤት ተልከው በምትካቸው ካቶሊካውያን ጳጳሳት ተሾሙ ።

የእንግሊዝን ሀገር በእስጳኝ ግዛት ሥር ለማዋልና ቤተ ክርስቲያኒቱንም በሮም ፖፕ ሥር ለማድረግ በማሰብ በ1554 ዓ.ም በእድሜ ዐሥራ አንድ ዓመት የሚያንሳትን የንጉሥ ቻርልስ አምስተኛን ልጅ ዳግማዊ ፊልጶን አገባች ። ይህ ዓይነቱ ወግ አጥባቂ የሆኑት ካቶሊኮች በጋብቻ መተሣሠር በሀገሩ ነጻነት ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በመገንዘብ አብዛኛው የእንግሊዝ ሕዝብ አዘነ ።

በ1554 ዓ.ም. አምስት መቶ የሚሆኑ የፓርላማ አባላት ቀደም ሲል የካቶሊክን እምነት በመቃወም ስለፈጸሙት ስሕተት ይቅርታ እንዲደረግላቸው በመጠየቃቸው የሜሪ ያክስት ልጅ የነበረው የሮሙ ፖፕ ተወካይ ካርዲናል ፖሌ ኃጢአታቸውን አስተሠረየላቸው ። በንግሥት ሜሪ ዘመነ መንግሥት በፓርላሜንቱ ውሳኔ የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ አስተዳዳሪነት ሥልጣን ወደ ፖፑ ተላለፈ ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትም በየቤተ ክርስቲያኑ ይፈጸም ጀመር ። የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና እምነት በሚቃወሙ ላይ ከፍ ያለ ስደት ተነሣ ። በዚሁ የስደት ዘመን ጆን ሮጀርስ ፣ አቡነ ሑፐር ፣ አቡነ ሪድሌና አቡነ ላትሜር የተባሉት ፕሮታስታንቶች በእሳት ተቃጠሉ ። አቡነ ክራንሜር ግን በተሰማው ፍርኃት ምክንያት ከሞት የተረፍሁ መስሎት ቀደም ሲል የካቶሊክን እምነት መቃወሙ ስሕተት መሆኑን በአደባባይ ተናዞ ከፈጸመ በኋላ ምሕረተ ቢስ የነበረችው ንግሥት ሜሪ በተለይ የናቷን ፍች ወስኖ ማጽደቁ አበሳጭቷት ስለነበር በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት አዘዘች። እሱም በሚቃጠልበት ቦታ ለተሰበሰበው ሕዝብ በመንፈስ ድክመት ምክንያት መናዘዙና መፈረሙ ታላቅ ስሕተት መሆኑን ገልጾ ቀደም ሲል



www.ethiopianorthodox.org

ያስተማራቸውን የፕሮቴስታንት እምነት እንዲከተሉ ካስረዳቸው በኋላ በመጀመሪያ የፈረመባቸውን ጣቶቹን ወደ እሳቱ ከትቶ ካቃጠለ በኋላ መላ ሰውነቱ ተቃጥሎ ሞተ ።

ባጠቃላይ ከ1555 ዓ·ም ጀምሮ በሦስት ዓመት ከመንፈቅ ውስጥ በሜሪ ፥ ባማካሪዋ በጋርድነርና በካርዲናል ፖሌ በተቋቋመው ፍርድ ቤት ብያኔ መሠረት እላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የፕሮቴስታንትን እምነት የሚከተሉ መናፍቃን ናቸው በመባል ወደ ሦስት መቶ የሚጠጉ ካህናትና ምእመናን በእሳት ተቃጥለዋል ።

ንግሥት ሜሪ ቱዶርም ዙፋኗን የሚወርስ ዘር ሳትተካ (ሳትወልድ) በ1558 ዓ·ም ዐረፈች ።

የአስተዳደርና አርቆ የማሰብ ችሎታ የነበራት ፥ በአቡነ ክራንሜር አስተማሪነት ያደገችው የአን ቦሌይን ልጅ ንግሥት ኤልሳቤጥ አንደኛ እንደነገሠች (1558–1603) በንግሥት ሜሪ ሲካሄድ የቈየው ስደት ቆመ ። ቀደም ሲል በየሀገሩ ተሰደው የነበሩ ፕሮቴስታንቶችም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው አምልኮአቸውን በነጻና በሰላም ያከናውኑ ጀመር ። ምንም እንኳ ንግሥት ኤልሳቤጥ ለፕሮቴስታንቶች የአምልኮ ነጻነት ብትሰጥም ቅሉ ፡ በጀኔቫ የተስፋፋውን (የተሰበከውን) የፕሮቴስታንት ትምህርት ትጠላ ነበር ።

የሮም ፖፖች የሔንሪንና የካቴሪኒን ጋብቻ ፍች ስላልተቀበሉት ከሔንሪና ከአን ቦሌይን የተወለደችው ኤልሳቤጥ ዲቃላ ናት በማለት የእንግሊዝ ዙፋን ሕጋዊ ወራሽ ካቶሊካዊቲቱ የእስኮትላንድ ልዕልት ሜሪ እስቱአርት ናት ብለው ያምኑና ያስተምሩ ነበር ። የፈረንሳይ መንግሥትም ልዕልት ሜሪ እስቱአርት የእንግሊዝን ዙፋን ወርሳ እንድትነግሥ ይጥር ነበር ። ንግሥት ኤልሳቤጥም የሮማ ካቶሊካውያንን ሥርዓተ ጸሎት ብትወድም እንኳ ለዙፋኗ ተቀናቃኞች ስለነበሩ ወደ ፕሮቴስታንቶች ማዘንበልን መረጠች ።

የፈረንሳይና የእስጳኝ ገዥዎች ካቶሊካዊቲቱን የእስኮትላንድ ልዕልት ሜሪን ስለሚደግፉ እነዚህን መንግሥታት መወዳጀት አልፈለገችም ነበር ። በዚህ አኳኋን ኤልሳቤጥ የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን ለመደገፍ ቈርጣ ተነሣች ። ምክር ቤቱ በ1559 ዓ·ም በወሰነው መሠረት እንደ አባቷ የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂነት ሥልጣን ጨበጠች ።



www.ethiopianorthodox.org

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለፖፑ የሚላከው ገንዘብና የሚቀርበው አቤቱታ ተቋረጠ ። እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኒቱ የሚካሄደው የለውጥ ሂደት ደጋፊ የነበረው ዶክተር ማቴዎስ ፓርከር የካንቴርበሪ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን እንዲያስተዳድር ተወሰነ ። በሀገሪቱ የነበሩት ካቶሊካውያን ጳጳሳት የማዕርገ ጵጵስናውን ሥርዓተ ጸሎት እንዲፈጽሙለት ቢጠየቁ የሮሙ ፖፕ ሳይፈቅድ አንችልም ፤ ስላሉ ፤ በሔንሪና በኤድዋርድ ዘመነ መንግሥት ያገለገሉ የለውጡ ደጋፊ የነበሩ አረጋውያን ጳጳሳት በ1559 ዓ·ም ላምቤስ መንበረ ጵጵስና ግቢ በሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጵጵስናውን ፈጸሙለት ። ይህ ያለፖፑ ፈቃድ የተፈጸመው የሊቀ ጵጵስና ማዕርግ ሕጋዊነት የእንግሊዝንና የካቶሊክን አብያተ ክርስቲያናት ለብዙ ጊዜ በተለይ በፖፕ ልዮን ዐሥራ ሦስተኛ ዘመን ሲያወዛግብ ኖሯል ።

በ1552 ዓ·ም የተዘጋጀው የጸሎት መጽሐፍ በመጠኑ በወግ አጥባቂዎች ተሻሽሎ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ መገልገያ ሆነ ። እንዲሁም እነሉተር ከተነሡበት ከ16ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋም የሚገልጸው መጽሐፍ ቀደም ሲል አርባ ሁለት የመሠረተ እምነት መግለጫ አርቲክሎች (አንቀጾች) በሚል ርእስ በአቡነ ክራንሜር ተዘጋጅቶ እስከ ንግሥት ሜሪ ዘመነ መንግሥት ድረስ ለጥቂት ጊዜ ሲሠራበት ከቈየ በኋላ በኤልሳቤጥ ዘመነ መንግሥት እንደገና ተሻሽሎ ሠላሳ ዘጠኝ አርቲክሎች በሚል ርእስ ተዘጋጅቶ እስከ ዛሬ ድረስ ይሠራበታል ።

ንግሥት ኤልሳቤጥም እነ ዊልያም ሴሲልን የመሳሰሉ አስተዋይ አማካሪዎች ስለነበሩአት የምትወስደው እርምጃ ሁሉ ግቡን ይመታ ነበር። የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የነበረው ሴሲልና መሰሎቹ በእስጳኝ መንግሥት ይገዙ የነበሩት የኒዘርላንድ ፕሮቴስታንቶችን ፤ ሁጉኤኖትስ የተባሉ በፈረንሳይ የሚኖሩ ፕሮቴስታንቶችን ፤ የእስኮትላንድ ፕሮቴስታንቶችን መርዳት የፈረንሳይንና የእስጳኝን መንግሥታት አዳክሞ የእንግሊዝን መንግሥት የሚያጸና መሆኑን አብራርተው ስለገለጹላት እላይ ለተጠቀሱት ወገኖች የማቴሪያልና የጦር መሣሪያ እርዳታ አድርጋለች ።

የእስጳኝና የፈረንሳይ ነገሥታት ኤልሳቤጥን ከዙፋኑአ ለማውረድ ብዙ ጊዜ ሞክረው ነበር ። ፖፕ ፒዮስ አምስተኛ ኤልሳቤጥን በማውገዝ


www.ethiopianorthodox.org

የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ እንግሊዛውያን እንዲያምጹባት ጥሮ ነበር ። ይህ ሁሉ ሙከራ ሳይሳካ ስለቀረ የእስጳኝ ንጉሥ ፊልጶስ በ1588 ዓ·ም አይበገሬ የእስጳኝ አርማዳ በመባል የታወቁትን 160 የጦር መርከቦች ከ30,000 የታጠቁ መርከበኞች ጋር በማዝመት እንግሊዝን ለመውረር ሲጓዝ የእንግሊዝ መርከበኞች አስደናቂ በሆኑ ስልቶች በመጠቀም የእስጳኝን መርከቦች ከነወታደሮቹ በባሕር ላይ በተደረገው ውጊያ አወደሙአቸው ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የካቶሊክ እምነት ደጋፊ የነበረው የእስጳኝ መንግሥት ቅስሙ ስለተሰበረ እየተዳከመ በመሄዱ ፕሮቴስታንቶች ከታላቅ ጥፋት ዳኑ ።

በአጠቃላይ እላይ እንደተመለከትነው በኤድዋርድ ዘመነ መንግሥት ፕሮቴስታንቶች ሥር ሰደው ከቈዩ በኋላ በሜሪ ቱዶር ዘመነ መንግሥት ካቶሊኮች እንደገና ስለተደራጁ ኤልሳቤጥ በነገሠችበት ወቅት ሕዝቡ በሁለት ተቃራኒ የሃይማኖት ጐራ ተከፍሎ ነበር ። ምንም እንኳ በፕሮቴስታንታዊቲቱ እናቷና በአሳዳጊዎቿ ግፊት ምክንያት ለፕሮቴስታንት እምነት ብታደላም ከሀገሪቱ ዜጋ ሁለት ሦስተኛ የነበረውን የካቶሊክ እምነት ተከታይ ሕዝብም የአምልኮ መብቱን በማክበር በጥንቃቄ ስላስተዳደረች በዘመነ መንግሥቷ የጐላ የሃይማኖት ብጥብጥ አልተነሣም ነበር ።

## (2) ኢንግላንድና እስኮትላንድ ከተዋሐዱበት (አንድ ከሆኑበት) ጊዜ ጀምሮ በሀገሪቱ ውስጥ የተፈጸሙ ድርጊቶች

የእስኮትላንድ ንግሥት የሜሪ እስቱአርት ልጅ ንጉሥ ጀምስ ስድስተኛ ከ1567 ዓ.ም ጀምሮ እስኮትላንድን ሲገዛ ከቈየ በኋላ በ1603 ዓ.ም ቀዳማዊ ጀምስ በሚል ስያሜ የኢንግላንድም ንጉሥ በመሆን ሁለቱንም ሀገሮች በአንድነት ገዛ ። የግልና የማኅበር ሞራል በምእመናን ዘንድ በጥብቅ በተግባር ላይ እንዲውል የሚያስተምሩ ፣ የማንኛውም ክርስቲያን እምነትና አምልኮ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ የተደገፈ እንዲሆን የሚሹ ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተደገፈ አምልኮ ግን አምልኮ ጣዖት ነው የሚሉና የኤጲስ ቆጶሳትን አስተዳደር በመቃወም የፕሬዝቢቴሪያንን አስተዳደር የሚደግፉ ኢንግላንድ የሚኖሩ ፒዩሪታንስ በሚል ስም የሚጠሩ ፕሮቴስታንቶች ነበሩ ። እነሱም የፕሬዝቢቴሪያን እምነት



www.ethiopianorthodox.org

ከሰፈነበት ከእስኮትላንድ የሄደው ቀዳማዊ ጀምስ የአምልኮ ነጻነት በመለገስ ከንግሥት ኤልሳቤጥ የተሻለ አስተያየት ያደርግልናል የሚል አስተሳሰብ አደረባቸው ። እሱ ግን የሀገሪቱ ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያኒቱም የበላይ ገዥ የመሆን የሥልጣን ሱስ ስላደረበት "ጳጳስ ከሌለ ንጉሥም ሊኖር አይችልም" የሚል መፈክር እያስተጋባ የፕሮቴስ ታንቶችን ነጻነት ገፈፈ ። ፒዩሪታኖችም የአምልኮ ነጻነት እንዲሰጣቸው ቢጠይቁት በ1604 ዓ.ም ሐምፕቶን ውስጥ በተደረገው ጉባኤ ላይ ተገኝቶ የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን በመደገፍ ፒዩሪታኖችን ገሠጻቸው ። የዚህ ጉባኤ መልካም ውጤት በ1611 ዓ.ም በንጉሥ ጀምስ ትእዛዝ በእንግሊ ዝኛ ተዘጋጅቶ የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነበር ። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ እትም ከእብራይስጥና ከግሪክ የተተረጐመ ስለሆነ ፤ ቀደም ሲል ከተተረጐሙትም እየተነጻጸረ ስለተዘጋጀ መጽሐፍ ቅዱስን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለሚያነቡ ሁሉ ለብዙ ዘመናት አገልግሏል ። ምንም እንኳ በየጊዜው ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ቢዘጋጁም በንጉሥ ጀምስ ትእዛዝ የተዘጋጀው አሁንም ቢሆን ይሠራበታል።

ማንኛውም ዜጋ በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሥር አምልኮቱን በነጻ እንዲፈጽምና የንጉሡንም የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይነት አምኖ እንዲቀበል በማለት ያዘዘውን ትእዛዝ አንቀበልም ያሉ ብዙ ካህናት ከሀገር ተባረሩ ። የቀሩትም ታሰሩ ። የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ አቡነ ባንክሮፍት ከቤተ ክርስቲያኒቱ እምነት ውጭ የነበሩትን ፒዩሪታኖች በጥብቅ ይቃወም ነበር ። ለብዙ ዓመታት በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ተወግደው የነበሩት አልባሳትና የተለያዩ ሥርዓተ ቅዳሴዎች እንደገና እንዲሠራባቸው የተደረጉት በዚሁ ጊዜ ነበር ።

ከአቡነ ባንክሮፍት ቀጥሎ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ሆኖ የተሾመው አቡነ አቦት ለዘብ ያለ መሪ ስለነበረ በፒዩሪታኖች ላይ የተነሣው ስደት ጋብ እንዲል አደረገ ። ወደ አኤርላንድ እየሄዱም እንዲኖሩ አደረገ ። እነሱም አኤርላንድ ውስጥ እምነታቸውን አስፋፉ ።

እንግላንድ ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ፕሮቴስታንቶች (ኮንግሪጌሽናሊ ስቶች ወዘተ.) ሀገራቸው ውስጥ የአምልኮ ነጻነት ስለተነፈጋቸው በ1620 ዓ.ም ጥቂቶቹ ሜይፍላወር በተባለችው መርከብ ቤተሰቦቻቸውን አሳፍ



www.ethiopianorthodox.org

ረው በሃይማኖት መሪያቸው በዊልያም ብሬውስቴር መሪነት የእምነት ነጻነት ሊያገኙ ወደሚችሉበት ሰሜን አሜሪካ (አዲሱ ዓለም) ወደምትገኘው ወደኒው ኢንግላንድ ጉዞ ጀመሩ ። በጉዞው ላይ ካጋጠማቸው ብዙ ውጣውረድና ችግር በኋላ ኒው ኢንግላንድ ወደሚገኘው ፕሌሙስ ወደብ ደረሱ ። እዚያም በመጀመሪያው ከባድ የክረምት ወራት የመጠለያ ፣ የምግብ ወዘተ. ችግር ስለደረሰባቸው ግማሾቹ አለቁ ። ቀስ በቀስ ግን ተግተው በመሥራት ሀገሪቱን አለሚት ። እነዚህ መጀመሪያ የተጓዙት "ፒሊግሪም ፋዘርስ" በመባል ይጠራሉ ። ወደ ኒው ኢንግላንድ ተሰደው ከሄዱት አብዛኞቹ የኮንግሪጌሽናል ቤተ ክርስቲያን አባላት ስለነበሩ እዚያው ቤተ ክርስቲያናቸው ተስፋፋች ።

ባጠቃላይ በሃይማኖት ጭቆናና ስደት ምክንያት የትውልድ ሀገራቸውን እንግሊዝን ትተው ወደ ሰሜን አሜሪካ ከተሰደዱት የኮንግሪጌሽናል፣ የፕሬዝቢቴሪያን ፣ የባፕቲስት ፣ የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት አባላት በተጨማሪ ሎንዶን ለሚገኙ ታላላቅ የንግድ ድርጅቶች ወኪል በመሆን ብዙ ነጋዴዎችም ሄደዋል ።

የጀምስ ልጅ ቀዳማዊ ቻርልስ (1625–1649) ኢንግላንድንና እስኮትላንድን በአንድነት ይገዛ በነበረበት ዘመን የቻርልስ ወዳጅና ደጋፊ የነበረው አቡነ ዊልያም ሎውድ ንጉሡ የሀገሪቱና የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ ገዥ ሆኖ እንዲያስተዳድር በእግዚአብሔር የተመረጠ መሆኑን ፣ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት በኅብረት ሕዝቡ በታማኝነት ቀጥተኛ ተግባሮችን እንዲፈጽም ሊመሩት ይገባል በማለት ለምእመናን ያስተምር ነበር ። ይህንኑ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን አባላት ያልሆኑ ምእመናን የአምልኮ ነጻነት የሚገፈውን አስተሳሰብ በመቃወም ምክር ቤቱ ቢነሣ በ1629 ዓ.ም ንጉሡ ምክር ቤቱን ዘግቶ ዐሥራ አንድ ዓመታት በፈላጭ ቆራጭነት ሀገሪቱን ገዛ ። የንጉሡን በእምነት ላይ የነበረውን ሥልጣን ከተቃወሙ ፒዩሪታኖች አንዳንዶቹ ሲገደሉ ሌሎቹ ደግሞ ወደ እስር ቤት ይላኩ ነበር ። በዚህ አኳኋን ፒዩሪታኖች ሥቃይ ስለጸናባቸው የሃይማኖት ነጻነት ወደሚያገኙበት ወደ ሰሜን አሜሪካ በ1629 ዓ.ም ተጉዘው ማሳቹሴትስ ደርሰው ሳሌም ውስጥ የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያናቸውን ሠሩ ። የሃይማኖት ነጻነት የተነፈጉ ብዙ ምእመናን በየጊዜው ወደ አሜሪካ ጐረፉ ።



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም ቀዳማዊ ቻርልስ በ1632 ዓ.ም ካቶሊካዊውን ሎርድ ባልቲሞርን (ጆርጅ ካልቨርትን) ሰሜን አሜሪካ የምትገኘው የሜሪላንድ ገዥ አድርጎ ሾሞት ስለነበር ፣ እንግሊዝ ውስጥ የሃይማኖት ጭቆና ያንገፈገፋቸው ካቶሊኮች የእምነት መሰላቸው ወደሚያስተዳድራት ወደ ሜሪላንድ በብዛት ገቡ ።

በ1640 ዓ.ም በንጉሡ ጥሪ የተሰበሰበው የእንግሊዝ ፓርላሜንት አባላት ከንግሥት ኤልሳቤጥ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ቀኝ ክንፍ (ወግ አጥባቂ ፣ ኮንሰርቫቲብ) የሆኑት ኤጲስኮፔሊያኖችና ግራ ክንፍ (ተራማጅ፣ ራዲካል) የሆኑት ፒዩሪታኖች የየራሳቸውን አምልኮ በሰላም እየፈጸሙ የዜግነት አንድነታቸውን አጽንተው እንደቈዩ ሁሉ በዚያው እንዲቀጥሉ በማድረግ ፈንታ ኤጲስኮፔሊያኖችን ብቻ ደግፎ ፒዩሪታኖችን ተቃወመ። ይህንኑ ንጉሡ የከፊል ዜጎቹን የአምልኮ ነጻነት ገፎ የሚያካሂደውን ሕገ ወጥ አስተዳደር በጥብቅ በመቃወማቸው ወዘተ. በፓርላማው ውስጥ አምስት የሚሆኑ ቀንደኛ አነሳሾችን ይዞ አሰረ ። በዚህም ምክንያት በ1642 ዓ.ም በንጉሡ ደጋፊዎችና በፓርላማው ደጋፊዎች መካከል የእርስ በእርስ ጦርነት ተጀመረ ።

በመላ የንጉሡ ነገሥቱ ግዛት አንድ ዓይነት ሥርዓተ ጸሎት መፈጸም ይገባል በሚል ሐሳብ በእስኮትላንድ የሚገኙት የፕሬዝቢቴሪያን አብያተ ክርስቲያናት ሥርዓተ ጸሎታቸውን የኤጲስኮፓል ቤተ ክርስቲያን ባዘጋጀችው የጸሎት መጽሐፍ እንዲፈጽሙ ከአቡነ ሎውድ ጋር ሆኖ በማስገደዱ ፣ እንዲሁም ለፕሬዝቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን ሐቀኛ አገልጋይ የነበረውን አንድርው ሜልቪንን ከሀገር በማሳደዱ ተቀይሞ የነበረው የእስኮትላንድ ሕዝብ ከጐናቸው ሆኖ ያንን ዲክታተር ንጉሥ ከነጭፍሮቹ ለመደምሰስ እንዲረዳቸው የእንግሊዝ ፓርላሜንት አባላት ተማጸኑ ። በቻርልስ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ሥር የተሠቃየው የእስኮትላንድ ሕዝብም ጥሪውን በደስታ ተቀብሎ በንጉሡ ላይ ተነሣ ። የፒዩሪታን እምነት ተከታይ በነበረው ኦሊቨር ክሮምዌል በተባለው ጀኔራል የተመራው የፓርላሜንቱ ደጋፊ ሠራዊት የንጉሡን ሠራዊት ገጥሞ ሲዋጋ ከቈየ በኋላ በ1645 ዓ.ም ናስቤ ላይ ድል አደረገው ። ንጉሡ ድል ከተመታ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ፓርላሜንቱ በስም ብቻ የሀገሪቱ አስተዳዳሪ ቢሆንም ፣ በተግባር ግን የሠራዊቱ ድጋፍ የነበረው አስተዳዳሪ ኦሊቨር ክሮምዌል


www.ethiopianorthodox.org

ነበር ። በተለይ ሀገሪቱ ሪፐብሊክ (ኮሞንዌልስ) መሆኗ በሀዋጅ ጸድቆ ከ1649 1658 ዓ.ም ኦሊቨር ክሮምዌል በፈላጭ ቆራጭነት (በዲክታተር ነት) ገዝቷል ። ከእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ለነበሩት ፕሮቴስታን ቶች ማለት ለፒዩሪታኖች ፡ ለፕሬዝቢቴሪያኖች ፡ ለኮንግሪጌሽናሊስቶች ፡ ለባፕቲስቶች ወዘተ. የአምልኮ ነጻነት ሰጥቷል ።

በክሮምዌል ዘመነ መንግሥት ለተለያዩ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ተከታዮች ሙሉ የአምልኮ (የሃይማኖት) ነጻነት ለመስጠት የተደረገው ሙከራ ሁሉ በ1660 ዓ.ም የእንግሊዝ ዙፋን ለዳግማዊ ቻርልስ ሲመለስ ተዳከመ ። እንዲሁም የኤጲስኮፓል (የእንግሊዝ) ቤተ ክርስቲያን ከእንግሊዝ ነገሥታት ጋር ተደጋግፋ በመሥራቷ በክሮምዌል ዘመነ መንግሥት የተሰነዘረባት ጭቆና አክትሞ በነገሥታቱ ድጋፍ የቀድሞ ክብሯን ብትጎናጸፍም ቅሉ በቀዳማዊ ቻርልስና በአቡነ ሎውድ በፕሮቴስታንቶች ላይ የተሰነዘረው ዓይነት ጭቆናና ስደት አልተፈጸመባ ቸውም ።

በአጠቃላይ በእንግሊዝ ሀገር የተካሄደውን የእርስ በርስ ጦርነት ካስነሡት ምክንያቶች ዋነኛው ምክር ቤቱ ሕገ መንግሥቱን ለመለወጥ መነሣቱ ነው ።

የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በታላቋ ብሪታንያ (ኢንግላንድና እስኮትላንድ) የሚኖሩ አብያተ ክርስቲያናት አንድ የሚሆኑበትን መሠ ረት ለመጣል በምክር ቤቱ ፈቃድ ከ1643–1649 ዓ.ም በዌስትሚኒስተር ጉባኤ አድርገው ነበር ። ጉባኤውም የፕሬዝቢቴሪያንን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት (ዶክትሪን) ፣ አጠርና ሰፋ ያሉ ሁለት የሰንበት ትምህርት መስጫ (ካቴኪዝም) መጻሕፍት አዘጋጀ ። በ1647 ዓ.ም በተዘጋጀው የዌስትሚኒስተር ኮንፌሽን (የዌስትሚኒስተር የሃይማኖት መግለጫ) እንግሊዝኛ ተናጋሪ ምእመናን ያሏቸው የፕሬዝቢቴሪያን አብያተ ክርስቲያናት እስከ ዛሬ ድረስ ይጠቀሙበታል ።

ቀዳማዊ ቻርልስ በ1649 ዓ.ም በፍርድ ከተገደለ በኋላ በእስኮትላ ንድ መሪዎችና ባላባቶች ድጋፍ ዳግማዊ ቻርልስ ነገሠ ። እሱም የካቶሊክን እምነት ይወድ ስለነበረ የመንገሡ ዕድል እንዳያመልጠው የዜጎቹን የአምልኮ ነጻነት የሚያከብር መሆኑን ለይስሙላ ያህል ገለጸ ። እንግሊዝ ሀገር የነበሩት ፕሬዝቢቴራውያን የአምልኮ ነጻነታችንን


www.ethiopianorthodox.org

ይሰጠናል በሚል ሐሳብ የዳግማዊ ቻርልስን መንገሥ ደግፈው ነበር ። ነገር ግን ንጉሡ ማንኛውም የእንግሊዝ ዜጋ የእንግሊዝን (የኤጲስኮፓልን ፡ የአንግሊካንን) ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት እንዲከተል ስላዘዘ ከሁለት ሺህ በላይ የሚሆኑ የፕሬዝቢቴሪያን ፣ የባፕቲስት ወዘተ. አብያተ ክርስቲያናት ካህናት ትእዛዙን በመቃወማቸው ከሥራቸው ተወገዱ ። ይኸው አልበቃ ብሎ ዳግማዊ ቻርልስ የካቶሊክ እምነት ተከታይ ስለነበረ ከፈረንሳይ ንጉሥ ከሉዊስ ዐሥራ አራተኛ ጋር ጊዜ ሲያጋጥመው የካቶሊክን እምነት በእንግሊዝ ሀገር መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል በምሥጢር ስምምነት አድርጎ ነበር ። ነገር ግን የሀገሪቱ ፓርላማ ፖሊሲ ይህንን የምሥጢር ስምምነት በተግባር ላይ ለማዋል ስላልፈቀደለት የንጉሡ ዕቅድ ግቡን ሊመታ አልቻለም ። በዚያን ጊዜ የአምልኮ ነጻነት እንዲሰጣቸው በመጠየቃቸው ምክንያት እስር ቤት ከገቡት አንዱ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን አባልና ሰባኪ የነበረው ጆን ቡንያን ነበር ። እሱም ከ1660–1672 ዓ.ም ለዐሥራ ሁለት ዓመታት እቤድፎርድ እስር ቤት በቈየበት ጊዜ "የመናኝ ጉዞ" የተባለውን የሃይማኖት መጽሐፍ አዘጋጀ ። የኰአኬርስን ሃይማኖት በመሠረተው በጆርጅ ፎክስ (1624–1691) ላይም ከፍ ያለ ሥቃይ ደርሶበት ነበር ። በዳግማዊ ቻርልስ ዘመነ መንግሥት በተካሄደው ስደት ምክንያት ብዙዎች ወደ ሰሜን አሜሪካ ተሰደው ሄዱ ። ከተሰደዱትም መካከል ፔንሲልቫንያ ውስጥ የኰአኬርስን ሃይማኖት ያስፋፋው ዊልያም ፔን ይገኝበታል ።

ከዳግማዊ ቻርልስ ቀጥሎ የነገሠው ወንድሙ ዳግማዊ ጀምስ የካቶሊክን እምነት እንግሊዝ ውስጥ መልሶ ለማቋቋም በነበረው ዕቅድ መሠረት የተለያዩ እምነት ተከታዮችን የአምልኮ ነጻነት በመንፈጉ ምክንያት በ1688 ዓ.ም የካልቪን እምነት ተከታይ የነበረው የኦሬንጁ ዊልያምና ባለቤቱ የጀምስ ልጅ ልዕልት ሜሪ ከኔዘርላንድ ወደ እንግሊዝ ሀገር ሄደው ዙፋኑን እንዲወርሱ ተጋበዙ ። ዊልያምም በግብዣው መሠረት ሠራዊቱን አስከትሎ እንግሊዝ ሲደርስ ጀምስ ወደ ፈረንሳይ ሸሽቶ ሄደ ። በ1689 ዓ.ም ዊልያምና ሜሪ የእንግሊዝ መንግሥት ገዥ ሆኑ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል መሠረቱ የጸና ዘላቂ ሰላም ተመሠረተ ። እንግሊዝ ውስጥ በ1689 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

ለተለያዩ እምነት ተከታዮች ማለት ለፕሬዝቢቴሪያኖች ፡ ለኮንግሬጌሽና ሊስቶች ፡ ለባፕቲስቶች ወዘተ. የተሰጠው የአምልኮ (የሃይማኖት) ነጻነት ቀደም ሲል የነበረውን ሥቃይ አስታገሠ እንጂ መንግሥቱ በክርስቲያ ኖች መካከል የሚያደርገው ልዩነት ለብዙ ዓመታት ቀጥሎ ነበር ።

ቀስ በቀስ በአንግሊካን (በኤጲስኮፓል) ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሦስት ክፍሎች ተከሰቱ ። እነሱም ከፍተኛ (ወደ ካቶሊክ እምነት ያዘነበለች ኮንሰርቫቲቭ ፡ ወግ አጥባቂ) ቤተ ክርስቲያን ፡ ወንጌላዊት (ወደ ፕሮቴስታንት እምነት ያዘነበለች) ቤተ ክርስቲያንና ሰፊ (ክርስቲያናዊና ማኅበራዊ ንቅናቄዎችን ለማራመድ የምትጥር ሊብራል) ቤተ ክርስቲያን ይባላሉ ።

እስኮትላንድ ውስጥ የፕሬዝቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን እንደገና በጸና መሠረት ላይ ተቋቋመች ። የእንግሊዝ መንግሥትም ይህችን ቤተ ክርስቲያን በኦፊሲየል አወቃት ። የዌስትሚኒስተር ኮንፌሽን የቤተ ክርስቲያኒቱ የእምነት መመሪያ ሆነ ። በዚህ አኳኋን በፕሮቴስታንት ተከታዮች ላይ በየጊዜው የተነሣው ስደት ቆሞ ሰላም ሰፈነ ።

## ሸ) የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከፕሮቴስታንቶችና ከራሷም አባላት የተሰነዘሩባትን ትችቶች (ክሶች) ለማረም ፡ እንዲሁም በፕሮቴስታንቶች ስብከት ምክንያት የኮበለሉባትን ምእመናን ለመመለስ ያደረገችው ፍሬአማ ትግል (ጥረት)

### (1) በትሬንት ጉባኤ ውሳኔ መሠረት በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የተደረጉ አንዳንድ እርማቶች

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምራ በየጊዜው በውስጧ የሚከሰቱትን የእምነት ፡ የሞራልና የአስተዳደር ስሕተቶች በወቅቱ ስታርም ቆይታለች ። ለወደፊትም በማንኛውም ጊዜ የሚከሰቱትን የምታርም መሆኗ ግልጽ ነው ።

በዐሥራ አምስተኛውና በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ዘመን በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለተከሰቱት ስሕተቶችና ድክመቶች እነ ዮሐንስ ሑስን ከመሳሰሉ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባላትና የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ካልሆኑ ሰዎች ብዙ ሮሮ ተሰንዝሮ ነበር ። ይኸውም የተለያየ ወቀሳና እሮሮ በቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ታፍኖ በመያዙ ምክንያት


www.ethiopianorthodox.org

በጊዜው ተገቢው እርማት ስላልተደረገ በነማርቲን ሉተር የተቀሰቀሰውን የሃይማኖትና የሥርዓት ለውጥ አስከተለ ።

በፕሮቴስታንቶች ንቅናቄ የተነሣው ችግር የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሠራችው ስሕተት ምክንያት በእግዚአብሔር ቁጣ የመጣ ስለሆነ ስሕተቶችን ማረም ይገባናል በማለት ኑሬንበርግ በተሰበሰበው ጉባኤ ላይ በወኪሉ አማካይነት ለመጀመሪያ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱን መሳሳት አምኖ የገለጸ አድርያን ስድስተኛ (1522–1523) የተባለው ፖፕ ነበር ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ከአውሮጳና ከአሜሪካ አብዛኛውን ክፍል በበላይነት ያስተዳድር የነበረውና የጀርመን ግዛት አንድነት ተጠብቆ እንዲኖር የሚሻው ካቶሊካዊው ቻርልስ አምስተኛ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ተገናኝተው በመካከላቸው የተፈጠረውን ልዩነት አስወግደው አንድነታቸውን ለማጽናት የሚያስችል አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ (ሲኖዶስ) በአስቸኳይ እንዲደረግ ቢጠይቅ ፖፖች በተለያዩ ምክንያቶች የጉባኤውን ጊዜ አዘገዩት ።

ጉባኤው ከዘገየበት ምክንያቶችም ጥቂቶቹ በጀርመን ክፍለ ሀገራት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የነበሩት ልዑላን አጠቃላዩ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የፖፑ ተጽእኖ በማይኖርበት ከፖፑ ግዛቶች ውጭ ጀርመን ውስጥ እንዲደረግ ሲጠይቁ ፡ ፖፑ ደግሞ በራሱ ግዛት ውስጥ እንዲደረግ መሻቱ ነበር ። ለምሳሌ ይህ ዐይነቱ አጠቃላይ ጉባኤ ከፖፑ ግዛት ውጭ ቢደረግ ቀደም ሲል በባስልና በኮንስታንስ ጉባኤዎች ከፖፑ ሥልጣን የአጠቃላይ ጉባኤው ሥልጣን ይበልጣል በማለት ፖፖችን መሻርና መሾም በመጀመራቸው ምክንያት የተነሣውን ዓይነት ችግር ይቀሰቅሳል ብሎ በመፍራት የጉባኤው መደረጊያ ጊዜ እንዲራዘም ካደረጉት ፖፖች አንዱ ቀሌምንጦስ ሰባተኛ (1523–1534) ነበር ። ቀሌምንጦስ በመንፈሳዊ አባትነቱ አጠቃላዩ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በአስቸኳይ ተደርጎ የክርስቲያኖች አንድነት የሚፈጠርበትን መንገድ በመሻት ፈንታ ወደ ዓለማዊው ፖለቲካ በማዘንበል የጀርመን አንድነት ጸንቶ የንጉሡ ኃይል እንዲጠናከር ከማይፈልገው ከቻርልስ ደመኛ ጠላት ከፈረንሳይ ንጉሥ ከቀዳማዊ ፍራንሲስ ጋር በማበር በእስጳኙ ንጉሥ በቻርልስ አምስተኛ ላይ ተነሣበት ። ቻርልስም በድርጊቱ በመናደድ


www.ethiopianorthodox.org

ሠራዊቱን ልኮ በ1527 ዓ·ም ሮምን አጥፍቶ ፖፑን እስር ቤት ጨመረው ።
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሮም የሬኔሳንስ ንቅናቄ አከተመ ። በቀሌምንጦስ ፈቃደኛ አለመሆን ምክንያት ያጠቃላዩ ጉባኤ ስብሰባ መዘግየት ፕሮቴስታንቶች እምነታቸውን ለማስፋፋት የሚያስችል በቂ ጊዜ ሰጣቸው ።

ጳውሎስ ሦስተኛ (1534–1549) የተባለው ፖፕና ቻርልስ አምስተኛ ባደረጉት ስምምነት መሠረት ከፖፑ ግዛት ውጭ በንጉሡ ግዛት ውስጥ በአልፕስ አካባቢ በምትገኝ ትሬንት በተባለች ከተማ በ1545 ዓ·ም ዐሥራ ዘጠንኛው የትሬንት አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በቅድስት ማርያም ማጀሬ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጀመረ ።

ቻርልስ ጉባኤው በመጀመሪያ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ እርማት ስለሚያስፈልጋቸው ስሕተቶች ፣ በካቶሊኮችና በፕሮቴስታንቶች መካከል አንድነት ስለሚፈጠርበት መንገድና ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ውይይት ይደረግ ሲል ፤ ፖፑ በበኩሉ ጉባኤው መጀመሪያ በመሠረተ ሃይማኖት ላይ ይነጋገር በማለት ሐሳብ ከተለዋወጡ በኋላ ስለ ዶክትሪንና ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጐን ለጐን እያቀናጀ ጉባኤው ይወያይባቸውና ውሳኔዎችን ያስተላልፍ በማለት ተስማሙ ።

የትሬንት አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ (1545–1563) በፖፑ እንደራሴ ሊቀ መንበርነት ሲጀመር የጀርመን ፕሮቴስታንቶች አልተገኙም ነበር ። ሆኖም በ1552 ዓ·ም በቻርልስ ግፊት ከታች እንደምንመለከተው ፕሮቴስታንቶች የጉባኤው ተካፋይ ሆነዋል ።

በጉባኤው ላይ የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን እምነት በማብራራት ከተወሰኑት ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

1) የሃይማኖት መገኛዎች መጽሐፍ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፉአቸው መጻሕፍት መሆናቸው ፤

2) መጽሐፍ ቅዱስን ልትተረጉም የምትችል ቤተ ክርስቲያን (የቤተ ክርስቲያን መሪዎች) ብቻ መሆኗ (መሆናቸው) ፤

3) ሰዎች የሚድኑት በእምነትና በደጋግ ሥራዎች መሆኑ ፤

4) በካህንነት ለማገልገል በቅድሚያ በአንብሮተ ዕድ ከጳጳሳት ማዕርገ ክህነት መቀበል መገባቱ ፤

5) ካህናት በሙሉ በድንግልና በመኖር እንዲያገለግሉ ፤ ጸሎተ ቅዳሴውም በላቲን ቋንቋ እንዲፈጸም ፤ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያናትም



www.ethiopianorthodox.org

ሰባት መሆናቸው ።

6) ካህኑ በሚጸልይበት ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ ወደ ጌታ ሥጋና ደም መለወጡ ፤

7) ቤተ ክርስቲያን ልትገለገልበት የሚገባ ፕሮቴስታንቶች ከሚቀበሉት 66 መጻሕፍት ከያዘው መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት በመላ የአካተተው ቩልጌት የተባለው መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑ፤

8) ኢንዶልጀንስ የተባለው የኃጢአት ማስተሥርያ ጽሑፍ በተግባር ላይ ከመዋል እንዲቋረጥ ፤

9) ጳጳሳት በጣም አስገዳጅ ተግባር ካላጋጠማቸው በስተቀር ከሀገረ ስብከታቸው ሳይወጡ በየአጥቢያቸው እየዞሩ ምእመናንን እንዲያስተምሩና እንዲመክሩ ፤ በአገልግሎት ላይ የተሠማሩ ካህናትንም እንዲያበረታቱ ፤

10) ጳጳሳት በየመንበረ ጵጵስናቸው የካህናት ማሠልጠኛ ሴሚናሪዎችን እንዲከፍቱ ፤ እየሰለጠኑ የሚወጡ ካህናትም ምእመናንን በማስተማር ፤ በመምከር እንዲያገለግሉና ስብከተ ወንጌልን እንዲያስፋፉ ወዘተ· በማለት ወሰኑ ።

በ1547 ዓ·ም ትሬንት ውስጥ ወረርሽኝ (ተስቦ) ገብቷል በሚል ሰበብ ቍጥራቸው ብዙ በነበረው ኢጣልያውያን የጉባኤው ተካፋዮች ግፊት ጉባኤው በፖፑ ግዛት ሥር ወደምትገኘው ወደ ቦሎኚያ ተዛወረ ። ቻርልስ በቀጥታ ከሚያስተዳድራቸው ከእስጳኝ ፤ ከናፕልስ ወዘተ· በጉባኤው ላይ ተካፋይ የነበሩት ዐሥራ ሦስት ጳጳሳት በንጉሡ ትእዛዝ መሠረት ወደ ቦሎኚያ አንሄድም ብለው ትሬንት ቀሩ ። ሕጋዊው ጉባኤ ትሬንት በቀሩት ጳጳሳት የሚካሄደው ስለሆነ ወደ ቦሎኚያ የሄዱት እንዲመለሱና የጉባኤው ተግባር ያለመከፋፈል በኅብረት እንዲከናወን እንዲያደርግ ለፖፑ አመለከቱ ። ፕሮቴስታንቶች በፖፑ ግዛት ውስጥ በሚደረግ ጉባኤ ላይ ተጽእኖ ይደረግብናል በሚል ሰበብ የማይካፈሉ መሆናቸውን ቻርልስ በመገንዘብ ጳውሎስ ሦስተኛ ጉባኤውን ወደ ትሬንት እንዲመልስ ደጋግሞ ቢጠይቅ ሰሚ አጣ ። ንጉሡና ፖፑ በዚህ ጉዳይ ሲወዛገቡ ከቈዩ በኋላ ጁልዮስ ሦስተኛ (1550–1555) የተባለው ፖፕ በንጉሡ ጥያቄ መሠረት ቀደም ሲል የተጀመረውን አጠቃላይ የቤተ

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ጉባኤ በ1551 ዓ.ም እንደገና ትሬንት ውስጥ ተግባሩን እንዲቀጥል አደረገ ። በቻርልስ ግፊት በ1552 ዓ.ም በትሬንት አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ለመካፈል የሄዱት የጀርመን ፕሮቴስታንት (ሉተራን) ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች ቀደም ሲል እነሱ ባልተካፈሉበት (ባልነበሩበት) ወቅት የተወሰኑት የሃይማኖት ነክ ውሳኔዎች ተሰርዘው በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ብቻ ከሥር ጀምረን እንደገና እንወያይ ። የአጠቃላይ ጉባኤው ሥልጣንም ከፖፑ በላይ ሆኖ ያለ ፖፑ ተወካይ ሊቀ መንበርነትና ተጽእኖ በነጻ ይካሄድ ። ያለበለዚያ ግን የጉባኤው ተካፋይ አንሆንም በማለታቸውና ካቶሊኮችም ሐሳቡን ባለመ ቀበላቸው በሁለቱ ወገኖች መካከል ስምምነት ሊፈጠር አልተቻለም ። ሆኖም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች በልዩ ልዩ የእምነትና የአስተዳደር ነክ ርእሶች ላይ በስፋትና በጥልቀት ተነጋግረው ከላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም ውሳኔዎች ከሰጡ በኋላ በ1563 ዓ.ም ጉባኤው ተግባሩን አጠናቆ ተዘጋ ።

ምንም እንኳ የጉባኤው ተካፋዮች በአንድ ላይ ተሰብስበው የተነጋገሩበት (የተወያዩበት) ጊዜ ሦስት ዓመት ያህል ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች አልፎ አልፎ በመቋረጡ ተግባሩን ያጠናቀቀው ዐሥራ ስምንት ዓመት ከፈጀ በኋላ ነው ።

የጉባኤው ውሳኔ በ1564 ዓ.ም በፒዮስ አራተኛ (1559 1565) ጸድቆ ወዲያው ከታተመ በኋላ ለፖርቱጋል ፣ ለቬኒስ ፣ ለኢጣልያ ፣ ለፖላንድ ፣ ለእስጳኝ ወዘተ. መንግሥታት ተላከ ። የካቶሊክን እምነት የሚከተሉ መንግሥታት መሪዎች ሁሉ የጉባኤው ውሳኔዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረጉ ተግባር ትብብራቸውን እንዲለግሡ ተጠየቁ ። በተለይ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ፖፖች ፣ ጳጳሳት ፣ ካህናት ወዘተ. ውሳኔውን በታላቅ ትጋት በተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ ጀመሩ ። እንዲሁም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የፕሮቴስታንቶችን መስፋፋት ለመግታት የሚያስችለው ዋነኛው መፍትሔ በቤተ ክርስቲያናቸው ላይ ከሚሰነዘሩት ክሶችና ነቀፋዎች ሊወገዱ የሚገባቸውን በማስወገድ መሆኑን በመገንዘብ ቀደም ሲል ሲፈጸሙ የነበሩትን ስሕተቶች በትሬንት ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ማረም ጀመሩ ። የዚህ ጉባኤም ግቡን መምታት የቤተ ክርስቲያኒቱን ክብር ከፍ አደረገው ።



www.ethiopianorthodox.org

የጉባኤው ውሳኔዎች በዓለም በሚገኙ የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ዘንድ በተግባር ላይ እንዲውሉ ከፍ ያለ ጥረት ካደረጉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ፒዮስ አምስተኛ (1566–1572) የተባለው ፖፕ ነበር ። እሱም የለውጡ ሂደት በመንበረ ፖፑ ግቢ ከሚገኙት ካርዲናሎችና ከሮም ከተማ ኑአሪዎች እንዲጀመር አደረገ ። የጉባኤው ውሳኔዎች በተግባር እንዲውሉ የሚያደርግና የካቶሊክን እምነት የሚያስፋፉ በለውጥ ሐዋርያነት የሚሠራ የካርዲናሎች ማኅበር በ1568 ዓ.ም መሠረተ ።

ከፍ ያለ ገቢና ሀብት ለማግኘት ከአንድ በላይ በሆኑ መንበረ ጵጵስናዎች ፡ አድባራት ወዘተ. ላይ በመሾማቸው ምክንያት በሀገረ ስብከታቸው የማይኖሩ ጳጳሳትና ካህናት በየሀገረ ስብከታቸው በመኖር ምእመናንን በትጋት እንዲያስተምሩ ፤ በየጊዜው ሲኖዶስ እየጠሩ ስለሚገጥሟቸው ችግሮች መፍትሔ እንዲሹ ፤ ቀደም ሲል ከካህናቱ አብዛኞቹ ምእመናንን ለማስተማር ፡ ለመስበክ ወዘተ. የሚያበቃ መንፈሳዊ ትምህርት ስላልነበራቸው ይህንኑ ድክመት ለማስወገድ የሚያስችሉ የካህናት ማሠልጠኛ ሴሚናሪዎችን እንዲከፍቱ ተደረገ ።

በገዳማት ውስጥ አስፈላጊ ለውጦች እንዲደረጉ ፤ ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፉ ወዘተ. ለአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ትእዛዝ በመስጠትና ትእዛዙ በሥራ ላይ መዋሉንም በመከታተል ሠርተዋል ።

እንዲሁም ዝሙትን የሚያስፋፉ የመጠጥና የዳንኪራ ቤቶች እንዲዘጉ ፤ በቤተ ክርስቲያኒቱ የአስተዳደር ቦታ ላይ ተቀምጠው በቢሮክራትነት የሚባልጉና ጉቦ የሚቀበሉ እንዲቀጡ ፤ ልጆቻቸውን ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት የማይልኩ ምእመናን እንዲገሠጹ ተደረገ ።

በ1566 ዓ.ም ካህናት ምእመናንን እንዲያስተምሩበት የትሬንትን ጉባኤ ውሳኔ የተከተለ የካቴኪዝም (የሰንበት ትምህርት) መጽሐፍ ፡ የቅዳሴና የጸሎት መጻሕፍት ተዘጋጁ ። በዐሥራ ሦስተኛው መቶ ዘመን በቶማስ አኩናስ የተዘጋጀው "ሱማ ቴዎሎጂካ" የተባለው የመሠረተ ሃይማኖት (የዶግማ) መጽሐፍ በትምህርት ቤቶች የመንፈሳዊ ትምህርት ማስተማሪያ እንዲሆን ተደረገ ።

ከፒዮስ አምስተኛ ቀጥሎ የተነሣው ጎርጎርዮስ ዐሥራ ሦስተኛ (1572–1585) የተባለው ፖፕ በቪየና ፡ በፓሪስ ፡ በማድሪድ ፡ በኮሎኝ ወዘተ. በነበሩ ቋሚ መልእክተኞቹ (አምባሳደሮቹ) አማካይነት የለውጡ



www.ethiopianorthodox.org

ሂደት እንዲፋጠን አደረገ ። በተለይ በመንፈሳዊና በዓለማዊ ትምህርት በኩል ከፍ ያለ መሻሻል እንዲደረግ በማሰብ ከግል ገንዘቡ እርዳታ ብማከል በሮም እንደሚገኘው እንደ ግሪጎርያን ዩኒቨርሲቲ የመሳሰሉ ብዙ ትምህርት ቤቶችን በየሀገሩ ከፍቶ ነበር ። የትምህርት አሰጣጥና አመራር ችሎታ የነበራቸው ኢየሱሳውያን በማስተማሩ ተግባር በሰፊው እንዲካ ፈሉ አድርጓል ። እንዲሁም በ1582 ዓ·ም በስሙ የሚጠራውን የግሪጎር ያን ካላንደር (የዘመን አቈጣጠር ስሌት) ቀድሞ የነበረውን አሻሽሎ ያወጣ እሱ ነው ። ይህ ተሻሽሎ የወጣው የዘመን አቈጣጠር የካቶሊክንና የፕሮቴስታንትን እምነት በሚከተሉ ሀገሮች ቀስ በቀስ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነትን አግኝቶ በሥራ ላይ ውሏል ። በአንዳንድ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሀገሮች ዘንድ ግን ገና ተቀባይነትን አላገኘም ። ሆኖም ከኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሀገሮች መካከል በ1914 ዓ·ም በመቀበል መጀመሪያዋ ሀገር ቡልጋርያ ናት ።

ከፖፖቹ በተጨማሪ የየሀገሩ ጳጳሳት ፡ የፍራንሲስካን ፣ የቤኔዲክቲ ያን ፣ የካፑቺን ፡ የዶሚኒካን ፡ የአውግስቲንያን ወዘተ· ገዳማት (ኦርደርስ) መነኰሳትም ለውጡ በየራሳቸው ገዳማትና በየሀገሩ በሚገኙ የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት እንዲካሄድ አድርገዋል ።

## (2) ኢየሱሳውያን ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መጠናከር ያበረከቱት አስተዋጽኦ

የእስጳኝ መንግሥት በ1521 ዓ·ም ከፈረንሳይ ጋር ሲዋጋ በመኰንን ነት ዘምቶ የነበረው ኢግናቴዎስ ሎየላ (1491–1556) በፈረንሳዮች ከፉኛ እግሩን ተመትቶ ቆስሎ ካገገመ በኋላ በቀሪ ዕድሜው እግዚአብሔርን ለማገልገል ወሰነ ። ይህንኑ ውሳኔውን በተግባር ላይ ለማዋል የሚያስች ለው ዕውቀት ለመቅሰም ከእስጳኝ ወደ ፓሪስ ሄዶ ሞንቴጉ ኮሌጅ የመንፈሳዊና የፍልስፍና ትምህርት ይከታተል በነበረበት ወቅት ሞንት ማርትሬ በነበረው በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በ1534 ዓ·ም ከስድስት ጓደኞቹ ጋር ቢቻል ኢየሩሳሌም ሄደው በመስበክ ቱርኮችን ወደ ክርስትና ለመመለስ ፤ እዚያ መሄድ ካልተቻለ ደግሞ የክርስቶስ እንደራሴ ከሆነው ከፖፑ ትእዛዝ ሥር ሆነው ማንኛውንም ፖፑ ከነሱ የሚሻውን ተግባር ሁሉ ለማከናወን በቃለ መሐላ ተስማሙ ።



www.ethiopianorthodox.org

ሆኖም ፍልስጥኤም በእስላሞች እጅ በመያዟ ምክንያት እዚያ ለማገልገል ስላልቻሉ ወደ ሮም ሄደው ራሳቸውን በፖፑ ትእዛዝ ሥር ለማዋልና ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል የቈረጡ መሆናቸውን ገለጹ ።

ኢግናቴዎስ ሎዮላ በ1537 ዓ·ም ማዕርገ ክህነት ከተቀበለ በኋላ ከካቶሊክ የሃይማኖት ድርጅቶች (ገዳማት ፣ ኦርደርስ) መካከል ከፍተኛ ሚና የተጫወተው የኢየሱሳውያን (የጀስዊትስ) ድርጅት (ኦርደር) በ1540 ዓ·ም በጳውሎስ ሦስተኛ ተመሠረተ ። በ1541 ዓ·ም ኢግናቴዎስ የመጀመሪያው መሪ (ጀኔራል) ሆኖ በመመረጥ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ ይህንኑ ድርጅት በሚገባ መራ ። በተጨማሪም ክርስቲያኖች ሥጋዊ ፈቃዳቸውን ድል ነሥተው ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ለማስገዛት የሚያስችላቸውን ስለ ጾም ፣ ጸሎት ፣ ስግደት ፣ ሱባኤ መግባት ፣ መታዘዝ ወዘተ· የሚገልጽ "መንፈሳዊ ልምምዶች" በሚል ርእስ ያዘጋጀውን ጽሑፍ ራሱ በፕሮግራም በተግባር ላይ በማዋል ተጠቅሞበታል ። ተከታዮቹም በተግባር ላይ በማዋል እንዲጠቀሙበት አድርጓል ። የኢየሱሳውያን ድርጅት ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ አባሎቹ ከፍ ያለ ትምህርት ስለነበራቸው ለጀርመን ፣ ለፈረንሳይ ፣ ለኢጣልያ ወዘተ· ነገሥታትና መኳንንት የነፍስ አባቶችና አማካሪዎች በመሆን ፣ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶችን በመመሥረት ፣ ልዑላንንና የባላባት ልጆችን እያስተ ማሩ ወደ እምነታቸው በመሳብ ፣ በተለያዩ ሀገሮች የወንጌልን ትምህርት በማዳረስ ፣ ለምእመናን መጠቀሚያ የሚሆኑ መጻሕፍትን በመድረስ ፣ በፕሮቴስታንቶች ተቃውሞ ምክንያት ተዳክማ የነበረችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንድትጠናከር ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። በተለይ ከስድስቱ የኢግናቴዎስ ጓደኞች አንዱ ፍራንሲስ ሐቪየር (1506–1552) የተባለው ዝነኛ ሚስዮናዊ እስከ ሕንድና ጃፓን ድረስ ተጉዞ ወንጌልን ሰብኳል ።

በአጠቃላይ የኢየሱሳውያን ድርጅት ለሮም ፖፖች ቀኝ እጅ በመሆን አገልግሏል ።

## ቀ) በካቶሊኮችና በፕሮቴስታንቶች መካከል በመካሄድ ሠላሳ ዓመት የፈጀው የሃይማኖት ጦርነት (1618–1648)

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በ1555 ዓ·ም አግስቡርግ ውስጥ



www.ethiopianorthodox.org

በጀርመን ክፍላተ ሀገር የሚገኙ የካቶሊክና የሉተር እምነት ተከታይ የነበሩ ልዑላን በየግዛቶቻቸው ያሉ ምእመናን በነጻ የየራሳቸውን ሃይማኖት ማስፋፋት የሚችሉ መሆናቸውን በስምምነት አጽድቀው ነበር። ከዜጎቻቸውም መካከል የገዥዎቻቸውን እምነት ለመከተል የማይፈልጉ ሰዎች ሲኖሩ ወደየፈለጉበት ክፍለ ሀገር ሄደው የመኖር መብት ተሰጥቷቸው ነበር ። እንዲሁም ከ1552 ዓ.ም በፊት በፕሮቴስታንት መሪዎች ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተወረሰው ሀብትና ንብረት የራሳቸው ሆኖ እንዲቀር ተወስኖ ነበር ። ማንኛውም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የፕሮቴስታንትን እምነት ለመቀበል ሲሻ በቅድሚያ ከሹመቱ መሰናበት የሚገባ መሆኑ በስምምነቱ ውስጥ ተጠቅሷል ። የካልቪን ተከታዮችና አናባፕቲስቶች ግን በዚህ ስምምነት አልተጠቃለሉም ነበር። ይህ ስምምነት ከሞላ ጐደል ጀርመን ውስጥ እስከ ዐሥራ ሰባተኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ሲሠራበት ከቈየ በኋላ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከትሬንት ጉባኤ ጀምራ በፕሮቴስታንቶች ስብከት የኮበለሉባትን ምእመናን ለመመለስ ባደረገቻቸው ተጋድሎዎች ምክንያት የካቶሊክንና የፕሮቴስታንትን እምነት በሚከተሉ ሕዝቦች መካከል በ1618 ዓ.ም ቦሔምያ (ቼኮዝሎቫኪያ) ውስጥ ጦርነት ተጀመረ ። ለጦርነቱ ቦሔምያ ውስጥ መጫር ምክንያት የሆነው የፕሮቴስታንት እምነት ተወካይ የነበሩ የሀገሪቱ ዜጎች ከተቀደሰው ከሮማ ኤምፓየር ንጉሠ ነገሥት ከዳግማዊ ፌርዲናንድ የተላከውን ካቶሊካዊ ገዥ አንቀበልም በማለት ፕራግ ከሚገኘው ምሽግ በመስኮት ገፍትረው በመጣላቸው፣ ኢየሱሳውያንን ከሀገራቸው አባረው በማስወጣታቸውና በአጠቃላይ በተቀደሰው የሮማ መንግሥት ላይ አምጸው በመነሣታቸው ነበር ።

ጦርነቱም ከካቶሊኮች ወገን በእስጳኝና በአውስትርያ መንግሥታት፣ በጀርመናዊው የቫባርያ ልዑል ወዘተ ፤ ከፕሮቴስታንቶች ወገን ደግሞ በዴንማርክ ፤ በስዊድንና በፈረንሳይ መንግሥታት ፤ በጀርመን የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ በነበሩ ልዑላን ወዘተ እየተደገፈ ጀርመን ውስጥ ተካሄደ ። የስዊድን ንጉሥ ጉስታቩስ አዶልፉስ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ቢሆንም ቅሉ ፤ የጦርነቱ ተካፋይ እንዲሆን የገፋፋው ዋንኛው ምክንያት ባልቲክ የተባለውን የባሕር በር የጀርመን መንግሥት እንዳይወስድበት ለመከላከል በማሰብ ሲሆን ፤ የካቶሊክ



www.ethiopianorthodox.org

እምነት ተከታይ የሆነው የፈረንሳይ መንግሥት ደግሞ የመንግሥቱን ሥልጣን ለማጠናከር በሀገሩ የነበሩትን ፕሮቴስታንቶች የማሳደድና በጀርመን የነበሩትን ፕሮቴስታንቶች የመርዳት ፖሊሲ ስለነበረው ነበር። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የፈረንሳይ ነገሥታት የእስጳኝና የጀርመን (የተቀደሰው የሮማ ኢምፓየር) ንጉሥ የነበረውን ቻርልስ አምስተኛን ለማዳከም የእስልምና ሃይማኖት አስፋፊ የነበሩትን ቱርኮችን እስከመርዳት ደርሰው ነበር ። ይህ ሠላሳ ዓመት የፈጀው አሰቃቂ ጦርነት በጀርመን ሰሜናዊ ክፍል በብዛት የሚገኙትን ፕሮቴስታንቶችና በደቡባዊው ክፍል በብዛት የሚገኙትን ካቶሊኮች ሕይወትና ንብረት ከማውደም በስተቀር ለየትኛውም ወገን ድልን ሊያቀዳጅ ስላልቻለ ቀደም ሲል አግስቡርግ ውስጥ በ1555 ዓ.ም የተደረገውን ስምምነት መሠረት በማድረግ በ1648 ዓ.ም የካቶሊክን ፡ የሉተርን ፡ የካልቪንን ወዘተ ተከታዮች ሕጋዊ የአምልኮ (የሃይማኖት) ነጻነት መብት የሚያረጋግጥ ስምምነት ዌስትፋልያ ውስጥ ተደርጎ ጦርነቱ ቆመ ።

በዌስትፋልያው ስምምነት ካልቪኒስቶች ከካቶሊኮችና ከሉተራን ጋር እኩል የእምነት ነጻነት ተጐናጸፉ ። በዚያው ጊዜ ሌሎችም ፖለቲካ ነክ የሆኑ ውሳኔዎች ተደርገዋል ።

በአጠቃላይ በአውሮጳ የነበረው የእምነት አንድነት ስለተናጋ በኢጣልያ ፡ በእስጳኝ ፡ በፈረንሳይ ፡ በቤልጅግ ፡ በአየርላንድ ፡ በደቡብ ጀርመን ፡ በአውስትርያ ፡ በፖላንድና በሀንጋሪ ከሚኖረው ሕዝብ አብዛኛው የካቶሊክ እምነት ተከታይ ሲሆን ፤ በኢንግላንድ ፡ በእስኮትላንድ ፡ በሆላንድ ፡ በሰሜን ጀርመን ፡ በስዊዘርላንድ ፡ በዴንማርክ ፡ በኖርዌና በስዊድን ከሚኖረው ሕዝብ አብዛኛው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ነበር ።

በየጊዜው በእስጳኝ ፡ በአውስትርያ ነገሥታት ይገዛ የነበረው "የተቀደሰው የሮማ ኤምፓየር" ግዛት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስለተንኮታኮተ የጀርመን ክፍለ ሀገሮች የፖለቲካ ነጻነታቸውንም ተጐናጸፉ ።



www.ethiopianorthodox.org

# ክፍል አምስት

## በ20ኛው መቶ ዘመን የተጀመረው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ንቅናቄ (ጉባኤ ፣ ማኅበር)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ቀጥሎም ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ክርስቲያኖች አንድነት ቢያስተምሩም ቅሉ በክርስቲያኖች መካከል በየጊዜው መለያየት ተፈጠረ ። ይኸውም ቀደም ሲል እንደተመለከትነው በክሕደት ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን አባልነታቸው በጉባኤ ተወግዘው ከተወገዱት ከአርዮስ ፣ ከመቅዶንዮስ ፣ ከንስጥሮስ ፣ ከአውጣኪና ከተከታዮቻቸው በስተቀር ከ5ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ በእምነት አለመስማማት ምክንያት አብያተ ክርስቲያናት እርስ በእርሳቸው እየተወጋገዙ ተለያይተዋል ። እነሱም

1ኛ/ በ451 ዓ.ም ኬልቄዶን በተደረገው ጉባኤ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት" የሚለውን የሮሙን ፖፕ የቀዳማዊ ልዮንን ትምህርት ስሕተት ነው ብሎ ስላወገዘው ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእስክንድርያና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት በእምነት ተለያዩ ። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ሁለት ባሕርይ በሚለው በልዮን ትምህርት ተስማ ማች።

2ኛ/ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን "መንፈስ ቅዱስ ከአብ ሠረፀ (ተገኘ)" ብላ ስታምን ፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን "መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሳይሆን ከወልድም ሠረፀ" ብላ በመወሰን አዲስ ትምህርት ስላስተማረችና የሮሙ ፖፕ በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የበላይነትን መንፈስ ስላሳየ በ1054 ዓ.ም ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ተወጋግዘው ተለያዩ ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ ያን ግን "መንፈስ ቅዱስ ከአብ ሠረፀ" ብላ ታምናለች ።

3ኛ/ በ16ኛው መቶ ዘመን የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ሉተር ፣ ካልቪንና እዝቪንግል የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ለማሻሻል ቈርጠው ስለተነሡ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተለዩ ።



www.ethiopianorthodox.org

4ኛ/ በ1870 ዓ.ም በቫቲካን አንድ ጉባኤ የተወሰነውን የፖፑን አለመሳሳት በመቃወም አሮጌ (የጥንት) ካቶሊኮች በሚል ስም የሚጠሩት ጀርመን ፡ አውስትርያ ፡ ስዊዝና በሌሎችም ሀገሮች የሚገኙ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባላት የነበሩት ከዚችው ቤተ ክርስቲያን ተለዩ ።

5ኛ/ ፕሮቴስታንቶች ከተነሡበት ከ16ኛው መቶ ዘመን ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስን እንደታያቸው (እንደመሰላቸው) የመተርጐም መብት ስላገኙ አንደኛው ወገን የኔ ትርጉምና አስተያየት ይሻላል ሲል ፡ ሌላው ወገን ደግሞ ቀጥተኛውና የተሻለው ትርጉም የኔው ነው በመባባል ስምምነት ላይ ስላልደረሱ በየጊዜው እየተለያዩ ከ260 በላይ በሆኑ በእምነት በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት (ዴኖሚኔሽን) ተከፋፍለዋል ።

እስከ 19ኛው መቶ ዘመን ድረስ ፕሮቴስታንቶች እርስ በእርሳቸው በእምነት ተለያይተው ሲኖሩ ፡ ከሀገሮቻቸው ወደ ውጭ ሀገሮች ከተላኩት ሚስዮናውያንም ጥቂቶቹ በተላኩባቸው ሀገሮች ሕዝቡን አስተምረው በእምነት አንድ የሆነች ቤተ ክርስቲያን በመመሥረት ፈንታ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት አቋቋሙ ። አንዱ የሃይማኖት ድርጅት አስተምሮ ያጠመቃቸውን ምእመናን ከንቱ በሆነ የውድድር መንፈስ በመመራት ሌላው ድርጅት ቀደም ሲል የተቀበላችሁት የክርስ ትና እምነት ስሕተት ስለሆነ የኔ ድርጅት የሚያስተምረውን እምነት ተቀብላችሁ ተጠመቁ በማለት ሕዝቡን ይይዘው ይጨብጠውን በማሳ ጣት ግራ ከማጋባታቸውም ሌላ እርስ በእርሳቸውም የጐሪጥ ይተያዩ ነበር። በተጨማሪም አረማውያንን አስተምረው ወደ ክርስቶስ ለመመለስ በማሰብ ከሀገራቸው የወጡለትን ዓላማ ከግቡ በማድረስ ፈንታ የኦርቶዶ ክስ እምነት ተከታዮችን ወደራሳቸው እምነት መለወጥ (ማስገባት) ስለጀመሩ ከክርስትና ትምህርት ውጭ ስለሆነው ስለዚሁ አጉል ተግባራ ቸው ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባላት ተቃውሞና ጥላቻን አትርፈ ዋል ።

ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት ጥቂቶቹ የቆሙለትን (የተሰለፉለ ትን) ዓላማ በመሳት ምእመናንን ግራ ሲያጋቡ አብዛኞቹ ደግሞ በየቦታው እየተዘዋወሩ አረማውያንን በማስተማር ፡ ትምህርት ቤቶች ፡ ክሊኒኮችና የመሳሰሉትን ጠቃሚ ድርጅቶች በማቋቋም ተገቢ እርዳታ ማበርከታ ቸው ግልጽ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

በ19ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረው ዊሊያም ካሬይ የተባለው የወንጌል መልእክተኛ ተለያይ ተው የሚሠሩ ሚስዮናውያን ሁሉ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ለማጥበብና በኅብረት የሚሠሩበትን ዕቅድ ለማዘጋጀት በየዐሥር ዓመቱ እየተሰበሰቡ መወያየት የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በመግለጽ ያስተላለፈ ላቸው መልእክት ምንም እንኳን ለጊዜው ተቀባይ ባያገኝም ከ19ኛው መቶ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በካሬይ ሐሳብ መሠረት ሚስዮናውያን በልዩ ልዩ ቦታዎች እየተሰበሰቡ በኅብረት ስለሚሠሩበት መንገድ ይወያዩ ጀመር ። በዚሁ ዘመን በአሜሪካ ፥ በእንግሊዝና በካናዳ በእምነት ተለያይተው ይኖሩ ከነበሩት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ጥቂቶቹ ልዩነታቸውን በውይይት እያስወገዱ አንድ ሆነዋል ። እንዲሁም ሕንድ ውስጥ ተለያይተው በየፊናቸው ይሠሩ የነበሩት አብያተ ክርስቲያ ናት በ20ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ "በደቡባዊ ሕንድ አንድ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን" በሚል ስያሜ አንድ ሆነው በኅብረት መንፈሳዊ ተልእኮአቸውን ያከናውናሉ ።

በየጊዜው የወንጌል መልእክተኞች ያደረጉአቸው ኦፊሲየል ያል ሆኑ ውይይቶች ኤደንበርግ ውስጥ በ1910 ዓ.ም የዓለም ሚስዮናውያን ኮንፈራንስ እንዲሰበሰብ ረዱ ። በዚሁ ኮንፈራንስ የልዩ ልዩ ሚስዮናው ያን ድርጅቶችንና አብያተ ክርስቲያናትን የሚወክሉ 1200 የሚሆኑ መልእክተኞች ተካፍለዋል ።

የኮንፈራንሱ ዓላማም ሚስዮናውያን የወንጌልን ትምህርት በዓለም በሚያዳርሱበት ወቅት ስለሚገጥሙአቸው ችግሮች ለመወያየትና እርስ በእርስ መወዳደርን ርግፍ አድርገው ትተው በወንድማማችነት መንፈስ በመመራት እየተረዳዱ በኅብረት የሚሠሩበትን መንገድ ለመሻት ነበር ። በጉባኤው የተገኙት መልእክተኞች አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በኅብረት በመሥራት ወንጌልን በዓለም እንዲያዳርሱ ተስማሙ ።

ስብሰባው ከመዘጋቱ በፊት ዓላማውን ከግቡ የሚያደርስ ቋሚ ኮሚቴ በመምረጥ ኮንፈራንሱ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የሚቋቋምበትን መሠረት ጣለ ።

ኤደንበርግ ውስጥ የተደረገው ኮንፈራንስ ጠቃሚ ውጤት እንዲያስ ገኝ ያለመሰልቸት የደከሙ የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረው



www.ethiopianorthodox.org

ጆን አር ሞትና የኢንተርናሽናል ሚስዮን ካውንስል ጸሐፊ የነበረው ጆ ሴች አልድሐም የተባሉት ምእመናን ነበሩ ።

በኤደንበርግ ኮንፈራንስ ሥራውን እንዲቀጥል የተቋቋመው ቋሚ ኮሚቴ በ1921 ዓ.ም ኢንተርናሽናል ሚሽኔሪ ካውንስል በሚል ስም ይጠራ ጀመር ።

እንዲሁም ኤደንበርግ በተደረገው ኮንፈራንስ ተካፋይ የነበረው የኤጲስኮፓል ቤተ ክርስቲያን አባል አቡነ ቻርለስ ብሬንትና ጠበቃ የነበረው ሮበርት ጋርድነር በአንዳንድ ነጥቦች ላይ በእምነት የሚለያዩ አብያተ ክርስቲያናት በብዙ ነጥቦች ፡ በተለይም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካችንና መድኃኒታችን መሆኑን በማመን ስለሚመሳሰሉ በየጊዜው በወንድማማችነት መንፈስ እየተወያዩ የሚቀራረቡበትን መንገድ የሚቀይሰውን "እምነትና ሥርዓት" የተባለውን ንቅናቄ በ1927 ዓ.ም አቋቋሙ ። ይኸው ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በስተቀር ከ127 አብያተ ክርስቲያናት የተወከሉ 400 መልእክተኞች የተካፈሉበት በብሬንት ሊቀ መንበርነት በ1927 ዓ.ም ሎዛን ውስጥ የተደረገው የእምነትና ሥርዓት ኮንፈራንስ በክርስቲያኖች መካከል አንድነት እንዲፈጠር ጥሪ አደረገ ።

አቡነ ብሬንት በ1929 ዓ.ም ስላረፈ የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዊሊያም ቴምፕል የሊቀ መንበርነቱን ሥራ ተረክቦ እስከ ዐረፈበት እስከ 1944 ዓ.ም ድረስ ንቅናቄውን ከግቡ ለማድረስ በትጋት ሠርቷል ።

የክርስትናን ትምህርት በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም በመግለጽ ለዓለም ሕዝብ የሶሻል ፡ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ኑሮ መሻሻል አብያተ ክርስቲያናት በኅብረት በመሥራት ማበርከት ያለባቸውን የተቀደሰ ተግባር የሚገልጸው "ሕይወትና ሥራ" የተባለው ዓለማቀፋዊ የክርስቲያኖች ንቅናቄ በሉተራዊው በአቡነ ናታን ሶደሬ ብሎም ሊቀ መንበርነት በ1925 ዓ.ም እስቶክሆልም ውስጥ ተደረገ ። በዚሁ ጉባኤ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በስተቀር ከ93 አብያተ ክርስቲያናት የተወከሉ 500 መልእክተኞች ተገኝተው ነበር ። የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ በ1920 ዓ.ም ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በላከው ደብዳቤ አብያተ ክርስቲያናት ተቀራርበው በኅብረት እንዲሠሩ በገለጸው መሠረት የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዚሁ ስብሰባ ተካፋይ የሚሆኑ መልእክተኞቿን



www.ethiopianorthodox.org

ልካለች። አቡነ ጀርመኖስ የተባለው የትያጥሮን ሊቀ ጳጳስ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እላይ ለተጠቀሱት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ንቅናቄዎች ተካፋይ እንድትሆን ረድቷል ።

በ1937 ዓ.ም አክስፎርድ ውስጥ በአቡነ ዊሊያም ቴምፕል ሊቀ መንበርነት ሁለተኛው "የሕይወትና ሥራ" ዓለማቀፋዊ ስብሰባ ሲደረግ በተከታታይ ከዋቂት ቀኖች በኋላ ደግሞ ኤደንበርግ ውስጥ "የእምነትና ሥርዓት" ዓለማቀፋዊ ስብሰባ ተደረገ ። የናዚ ሂትለር መንግሥት ፈቃድ ስለከለከላቸው ጀርመን የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞቻቸ ውን ልከው የስብሰባው ተካፋይ ለመሆን አልቻሉም ። ምንም እንኳ እነዚሁ ሁለቱ ዓለማቀፋዊ ንቅናቄዎች የተቋቋሙባቸው ዓላማዎችና የሚያዘጋጁአቸው ዕቅዶች የተለያዩ ቢሆኑም ቅሉ አብዛኛውን ጊዜ የሚያስተሣሥር የጠበቀ ግንኙነት ስላላቸው ተደባልቀው በአንድ ድርጅት ሥር ሆነው እንዲሠሩ ተወሰነ ። ከሁለቱ ንቅናቄዎች ኅብረት "የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ" ተገኘ ። ይኸው አዲሱ ድርጅት "የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ" ተብሎ እንዲጠራ የመጀመሪያ ውን ሐሳብ ያቀረበ ዶክተር ካቤርት ነው ።

ሁለቱ ንቅናቄዎች አንድ ድርጅት ከሆኑ በኋላ በአቡነ ዊሊያም ቴምፕል ሊቀ መንበርነት በ1938 ዓ.ም ኡትሬች ውስጥ የተሰበሰበው ኮሚቴ ለወደፊት በ1941 ዓ.ም ሊደረግ ለታቀደው ለመጀመሪያው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ አባል ለመሆን የሚችሉ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላካችን አዳኛችን መሆኑን የሚያምኑ አብያተ ክርስቲያናት" ብቻ መሆናቸውን የሚገልጸውንና የድርጅቱን ጠቅላላ ደንብ አወጣ ። በ1941 ዓ.ም ይደረጋል ተብሎ የታሰበው መጀመሪያው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በ1939 ዓ.ም በመጀመሩና ጀርመን ውስጥ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ዓለማቀፋ በሆኑ ኮንፈራንሶች ተገኝተው ለመካፈል ባለመቻላቸው ምክንያት ጉባኤው በታሰበው ጊዜ ሳይሰበሰብ ቀረ ።

በማኅበር አንድ ለመሆን በመደራጀት ላይ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በጦርነቱ ወቅት ሥቃይ ለደረሰባቸው ሰዎችና ለጦር እሥረኞች ከፍ ያለ ርዳታ አበርክተዋል ።

በክርስቲያኖች ዘንድ በናፍቆት ሲጠበቅ የቈየው መጀመሪያው



www.ethiopianorthodox.org

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በነሐሴ ወር 1948 ዓ.ም አምስተር ዳም ውስጥ ተደረገ ። ዶክተር ቪሴር ትሑፍት የጉባኤው ዋና ጸሐፊ ሆኖ ተሾመ ። በጉባኤው ከ147 አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ 351 መልእክተ ኞች ተካፋይ ሆነዋል ። በዚህ ጉባኤ ላይ የተካፈሉ አብያተ ክርስቲያናት የፕሮቴስታንት ፡ የግሪክ ኦርቶዶክስ ፡ የአሮጌ ካቶሊክ ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ፡ የእስክንድርያ ኮፕት ፡ የሕንድ ኦርቶዶክስ ወዘተ. ናቸው።

ጉባኤው የተነጋገረባቸው ነገሮች ሁሉ መመንጫ የሆነው የጉባ ኤው መሪ ሐሳብ "የሰው ልጅ ሕገወጥነትና የእግዚአብሔር ዕቅድ" የሚል ነበር ።

መልእክተኞቹ በጉባኤው ወቅት በአንድ ላይ ተሰብስበው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በመነጋገር ብቻ ሳይወሰኑ "በአንድ ላይ ተባብረን ለመኖር እንሻለን" የሚል ውሳኔ አስተላልፈዋል ።

ምንም እንኳ አንዳንድ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑ ሊቃውንት የጉባኤውን ዓላማ በመደገፍ ተካፋይ ለመሆን ፈቃደኞች መሆናቸውን ቢገልጹም ቅሉ በፖፕ ፒዮስ 12ኛ ትእዛዝ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባላት በጉባኤው ላይ እንዳይገኙ ተከለከሉ ። እንዲሁም የሩሲያ ፡ የሩማንያ ፡ የቡልጋርያና የፖላንድ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞቻቸውን ለመላክ ስላልፈቀዱ የጉባኤው ተካ ፋይ አልሆኑም ።

በጉባኤው ላይ የተገኙት መልእክተኞች የዓለም አብያተ ክርስቲያ ናት በኅብረት ስብከተ ወንጌልን ማስፋፋትና ለዓለም ሕዝብ ማዳረስ እንደሚገባቸው ፡ ሥልጣነ ክህነት የሌላቸው ምእመናን የቤተ ክርስቲያን አባላትና ደጋፊዎች ስለሆኑ ተገቢው መብት እንዲሰጣቸው ፡ ጦርነት ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ተቃራኒና ለሰው ልጆች መቅሠፍት ስለሆነ እንዲወገዝ ፡ የሰው ልጆች ሕጋዊ መብት የሆነው ሰብአዊ መብትና የሃይማኖት ነጻነት እንዲከበር በሚሉና በመሳሰሉ አርእስት ላይ ተወያይ ተዋል ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ንቅናቄ ዓላማ አንድ ኃያልና ከሁሉ በላይ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ሳይሆን ፤ የዓለም ክርስቲያኖች ሁሉ በወንድማማችነትና በእኩልነት መንፈስ እየተሰበሰቡ በመካከላ ቸው የተፈጠሩትንና ለወደፊትም የሚፈጠሩትን ችግሮች ለማስወገድ ፤



www.ethiopianorthodox.org

የክርስትናን ትምህርት በኅብረት ለማስተማር ፣ ስለ ዓለም ሰላም ለመሟገት ፣ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ለመርዳት ወዘተ· ነው ።

አጠቃላይ ጉባኤም በየ7 ዓመት እንዲደረግ ተስማምተዋል ። የድርጅቱ ዋና ጽሕፈት ቤት ጀኔቭ ነው ።

ሁለተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በነሐሴ ወር 1954 ዓ·ም ኤቫንስተን ውስጥ ተደረገ ። ከ161 አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ 502 መልእክተኞች በጉባኤው ተካፋይ ሆነዋል ። የጉባኤው መሪ ሐሳብ "ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ተስፋ ነው" የሚል ነበር ።

ጉባኤው ምእመናን በወንጌል መልእክተኛነት ሥራ ላይ በሰፊው ስለሚካፈሉበት መንገድ ፣ ስለዓለም ሰላምና ፍትሕ ፣ ስለ ሃይማኖት ነጻነት ፣ ከዓለም ውስጥ ዘረኛነት ተወግዶ እኩልነት ስለሚመሠረትበት መንገድ ወዘተ· ተወያይቶአል ። በተጨማሪም "ሁላችንም እራሳችንን ለእግዚአብሔር አስገዝተን በአንድ ላይ ለማደግ እንዲያስችለን እንመኛ ለን" የሚል ውሳኔ አሳልፎአል ። የሮሙ ፖፕ ፒዮስ 12ኛ ዐርፎ ዮሐንስ 23ኛ እስከ ተሾመበት እስከ 1958 ዓ·ም ድረስ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባላት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት በሚያዘጋጃቸው ኮንፈራንሶችና ጉባኤዎች እንዳይካፈሉ በጥብቅ ተከልክለው ነበር ። ዮሐንስ 23ኛ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፖፕ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ግን የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ሊያቀራርብ የቻለውን ቫቲካን ሁለት የተባለውን 21ኛውን ጠቅላላ ጉባኤ የሚከፍት መሆኑን በ1959 ዓ·ም አስታወቀ ። በዚሁ ጉባኤ ወቅት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለማንኛውም ችግር መፍትሔ የምትሻለት ፍቅርን በተከተለ መንፈስ በመወያየት እንጂ በክርክርና በውግዘት አለመሆኑን ገለጸ ። ወዲያው በካርዲናል አውግስቲን ቤአ የሚመራ የክርስቲያኖችን አንድነት የሚያራ ምድ ጽሕፈት ቤት ተቋቋመ ።

በ1960 ዓ·ም ሴንት አንድርውስ ውስጥ በተደረገው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ንኡስ ክፍል በሆነው "የእምነትና የሥርዓት ኮሚ ሽን" ስብሰባ ላይ የሚገኙ ተመልካቾችን እንድትልክ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጥሪ አደረገ ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ጥሪውን ተቀብላ መልእክተኞቿን ላከች ። በዚህ ስብሰባ ላይ ሁለቱም ወገኖች የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ኒው ዴልሂ



www.ethiopianorthodox.org

በሚደረገው በሦስተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ተመልካ ቾች ስለምትልክበት መንገድ ፤ እንዲሁም ካቶሊክ ያልሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ የቫቲካን ሁለት ጉባኤ በሚደረግበት ጊዜ መልእክተ ኞቻቸውን ስለሚልኩበት አኳኋንና በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይተ ዋል። ሁለቱም ወገኖች ባደረጉት ውይይትና ስምምነት መሠረት የካቶ ሊክ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ አምስት መልእክተኞችን በተመል ካችነት ደረጃ ወደ ኒው ዴልሂ በመላክ ስላሳየችው ትብብር የጉባኤው ተካፋዮች የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል ።

እንዲሁም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጥሪ መሠረት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ አባላት የሆኑ ዐሥራ ሰባት የኦርቶዶክስና የፕሮቴስታ ንት አብያተ ክርስቲያናት ተመልካቾቻቸውን በጥቅምት ወር 1962 ዓ.ም በፖፕ ዮሐንስ 23ኛ በተከፈተው በቫቲካን ሁለት ጉባኤ እንዲገኙ ልከዋል ።

በሰኔ ወር 1963 ዓ.ም ዮሐንስ 23ኛ እንዳረፈ የተሾመው ፖፕ ጳውሎስ 6ኛ "የሮሙ ፖፕ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበላይ ነው" የሚለው ሕግ እንደተጠበቀ ሆኖ የቫቲካን ሁለት ጉባኤ ዮሐንስ 23ኛ በተለመው ፈር በመቀጠል የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር የሚያቀራርቡ ውሳኔዎችን እንዲያስገኝ የሚ ጥር መሆኑን ገለጸ ።

በፖፑና በቊስጥንጥንያው የዓለም ፓትርያርክ መካከል በተደረ ገው ስምምነት መሠረት በ1054 ዓ.ም ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት እርስ በእርሳቸው የተለዋወጡትን ውግዘት በ1965 ዓ.ም አነሡት ። እንዲሁም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከሉተራን ፤ ከሜቶዲስትና ከመሳሰሉት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ስለ ኅብረትና ስለ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ በመወያየት ላይ ናት ። ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፖፕ ሆኖ በተሾመ በ34ኛው ቀን ባረፈው በቀዳማዊ ዮሐንስ ጳውሎስ ምትክ በጥቅምት ወር 1979 ዓ.ም ተመርጦ የተሾመው ፖላንዳዊው ዳግማዊ ዮሐንስ ጳውሎስ እላይ ስማቸው የተጠቀሱት ፖፖች የወሰኑትን የቫቲካን ሁለት ጉባኤን የለውጥ ፕሮግራም (መርሐ ግብር) በሥራ ላይ አውሎ በተግባር የሚገልጽ መሆኑን አስታውቋል ።

እንዲሁም በኅዳር ወር 1980 ዓ.ም ፖፕ ዮሐንስ ጳውሎስ 2ኛና



www.ethiopianorthodox.org

የግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ ዲሚትሪዎስ እስታንቡል (ቍስጥንጥንያ) ውስጥ ተገናኝተው ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት በመካከላቸው ያለውን ልዩነት አስወግደው በኅብረት መንፈሳዊ ተልእኮአቸውን ስለሚያከናው ኑበት መንገድ ተወያይተዋል ።

ባጠቃላይ ከቫቲካን ሁለት ጉባኤ ወዲህ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባላት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባላት ጋር በየጊዜው እየተገናኙ ውይይት ያደርጋሉ ። በየዓመቱ በጥር ወር ውስጥ አንድ ሳምንት ስለ ክርስቲያኖች አንድነት በኅብረት ይጸልያሉ ። እንዲሁም ርዳታ ለሚያስፈ ልጋቸው አብያተ ክርስቲያናት ፣ ለስደተኞችና ለመሳሰሉት በኅብረት ይለግሳሉ ። በተጨማሪም ምእመናን ሊረዱአቸው በሚችሉአቸው ቋንቋዎች መጽሐፍ ቅዱስ እየተተረጐመ በብዛት ታትሞ ለሕዝብ እንዲዳረስ በማሰብ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ጋር ተስማምታ ትሠራለች ።

ሦስተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በኅዳር ወር 1961 ዓ.ም ኒው ዴልሂ ውስጥ ተደረገ ። ጉባኤው አዲስ ከተቀበላቸው አባላት ጋር ከ197 አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ 577 መልእክተኞች በጉባኤው ተካፋይ ሆነዋል ። ይኸው ጉባኤ በአዲስ አባልነት ከተቀበላቸው 23 አብያተ ክርስቲያናት መካከል የሩሲያ ፣ የሩማንያ ፣ የቡልጋርያና የፖላንድ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ይገኙባቸዋል ። የአርመን ቤተ ክርስቲያንም አባል የሆነችው በዚሁ ጊዜ ነበር ።

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳ አባል ለመሆን ፈቃደኛ ባትሆንም በጉባኤው ላይ በተመልካችነት እንዲገኙ አምስት መልእክተ ኞቿን ለመጀመሪያ ጊዜ ልካለች ።

ኢንተርናሽናል ሚሽኔሪ ካውንስል የተባለው ድርጅት በዚሁ ወቅት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ድርጅት (ንቅናቄ) ጋር ተዋሐደ ።

የጉባኤው መሪ ሐሳብ "ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ነው" የሚል ነበር ።

ጉባኤው የእግዚአብሔርን ቃል ስለመመስከር ፣ አገልግሎትን በሰፊው ዘርግቶ ስለማዳረስና አንድ ስለመሆን በሚሉ አርእስት በሰፊው ተወያይቶአል ።



www.ethiopianorthodox.org

ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አባል ለመሆን የሚችሉ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አዳኛችን መሆኑን" የሚቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ እንደነበሩ ቀደም ብሎ ተገልጧል ።

በኒው ዴልሂ ጉባኤ የተሰበሰቡት መልእክተኞች የፊተኛውን ለአባልነት የሚያበቃውን የእምነት መግለጫ እንደሚከተለው አሻሻሉት "የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ አባላት በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አዳኛችን መሆኑን የሚያምኑ ፤ እንዲሁም ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን የወል ጥሪ አንድ ለሆነው አምላክ ለእግዚአብሔር አብ ፤ ለእግዚአብሔር ወልድና ለእግዚ አብሔር መንፈስ ቅዱስ ክብር መስጫ ለማዋል ፈቃደኞች የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው" ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ተባባሪ አባል የሆነው የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ሚያዝያ 20 ቀን 1963 ዓ.ም ካምፓላ ውስጥ ተደረገ ።

አራተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በሰኔ ወር 1968 ዓ.ም ኡፕሳላ ውስጥ ተደረገ ። በጉባኤው ከ235 አብያተ ክርስቲያናት የተወከሉ 704 መልእክተኞች ተገኝተዋል ። እንዲሁም አባላት ካልሆኑ 29 አብያተ ክርስቲያናት በተመልካችነት የተላኩ መልእክተኞች በጉባ ኤው ተገኝተዋል ። እነሱም 14 ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፤ 4 ከሚዙሪ ሲኖድ የሉተራውያን ቤተ ክርስቲያን ፤ 3 ከአድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያ ንና ከመሳሰሉት አብያተ ክርስቲያናት በተመልካችነት የተላኩ ነበሩ ።

ፖፑና ካርዲናል ቤአ ለኡፕሳላ ጉባኤ የመልካም ምኞት መግለጫ መልእክት አስተላልፈዋል ። እንዲሁም አባ ሮቤርቶ ቱሲ የተባሉት ካቶሊካዊ ካህን ለጉባኤው ንግግር አድርገዋል ።

ጉባኤው ከመከፈቱ ጥቂት ቀደም ብላ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ዘጠኝ አባላት በመላክ "የእምነትና ሥርዓት ኮሚሽን" ለተባለው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ንኡስ ክፍል ሙሉ አባል ሆናለች ። ሆኖም ምንም እንኳ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ አባላት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የድርጅቱ ሙሉ አባል ሁና ንቅናቄው መላ ክርስቲያኖችን ወክሎ ተግባሩን በቀለጠፈ መንገድ ለማከናወን እንዲችል ለማድረግ ቢጥርም ቅሉ በአንዳንድ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሕጎች ምክንያት እስከ አሁን ድረስ ሙሉ አባል አልሆነችም ።



www.ethiopianorthodox.org

የጉባኤው መሪ ሐሳብ "እነሆ ሁሉንም ነገር አዲስ አደርጋለሁ" የሚል ነበር ።

በአሜሪካ የሚኖሩትን ጥቁሮች በዘረኞች ከሚፈጸምባቸው አሰቃቂና ኢሰብአዊ ከሆነው ጭቆና በሰላማዊ መንገድ ነጻ ለማውጣት ይታገል የነበረውና የኖቬልን ሽልማት የተቀዳጀው ማርቲን ሉተር ኪንግ የተባለው ካህን በጉባኤው መክፈቻ ላይ ንግግር እንዲያደርግ ተጋብዞ ነበር ። ነገር ግን በዘረኞች ስለተገደለ ንግግሩ ሳይደረግ ቀረ ።

በዚሁ ጉባኤ መክፈቻ ላይ የዛምቢያው መሪ ኬኔት ካውንዳ "የበለጸጉትና የደኸዩት ሀገሮች" በሚል ርእስ ለጉባኤው ጠቃሚ ንግግር አድርጓል ።

ጉባኤው በዘር ፣ በሀብትና በዕውቀት ምክንያት የሚደረገው አድልዎ ስለሚቆምበት ፤ በችግር ላይ ለሚገኙት ምግብ ስለሚታደልበት፤ ስለ ወሊድ ቁጥጥር ፤ በዓለማችን ሰላምና ፍትሕ ስለሚሰፍንበት ፤ ማንኛውም ቀዝቃዛ ጦርነትና የኑክሌር ጦርነት ስለሚታገድበት ፤ ስለ ሰብአዊ ክብርና ስለሃይማኖት ነጻነት ፤ ዘረኛነት ሰይጣናዊ ሥራና የዓለምን ሰላም የሚያደፈርስ ስለመሆኑ ፤ ስደተኞችን ስለመርዳት ፤ እስከአሁን ድረስ ሲሠራበት የቈየው የአምልኮ ሥርዓት ለአዲሱ ትውልድ እንደሚስማማ ሆኖ ስለሚዘጋጅበት ፤ ስለ ሴቶች ሙሉ ነጻነት ማግኘትና በመሳሰሉት አርእስት ላይ ተነጋግሮአል ።

አምስተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በኅዳር ወር 1976 ዓ.ም ናይሮቢ ውስጥ ተደረገ ። በጉባኤውም ከ271 አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ 700 የሚሆኑ መልእክተኞች ተካፋይ ሆነዋል ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም በተመልካችነት ደረጃ 16 መልእክተኞች ልካለች ። እንዲሁም የአይሁድን ፣ የእስልምናን ፣ የቡዲሂዝምንና የሂንዱይዝምን እምነት የሚከተሉ ጥቂት እንግዶች በጉባኤው ተገኝተው ነበር ።

የናይሮቢ ጉባኤ 15 አብያተ ክርስቲያናትን በአባልነት ተቀብሏል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአፍሪካ አህጉር በጥንታዊትነቷ ስለተመረጠች በጉባኤው ላይ ጸሎተ ቅዳሴና ሥርዓተ ማኅሌት አድርሳለች ።

የሮሙ ፖፕ ፣ የቍስጥንጥንያ ፓትርያርክ ፣ የመስኮብ ፓትርያርክና የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ጉባኤው የተቃና ውጤት እንዲያስገኝ የሚጸልዩ


www.ethiopianorthodox.org

መሆናቸውን የሚገልጹ መልእክቶች ልከዋል ።

የጉባኤው መሪ ሐሳብ "ኢየሱስ ክርስቶስ ነጻ ያወጣናል ፤ አንድም ያደርገናል" የሚል ነበር ።

የጃማይካው ጠቅላይ ሚንስትር ኤን ማንሌ ለጉባኤው ባደረገው ንግግር የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ አባላት በኅብረት ጭቆናን ፤ የቅኝ ገዥነትን ፤ ዘረኝነትን ፤ በካፒታሊስቶች ግብዝነት ምክንያት በዓለም ውስጥ ተቃውሶ የሚታየውን የኢኮኖሚ ሥርዓትና የመሳሰሉትን ችግሮች ከሰው ልጆች ጫንቃ ላይ ለማውረድና ከዓለማችን ለማጥፋት መታገል ተቀዳሚና የተቀደሰ ተግባራቸው መሆኑን አብራርቶ በመግለጽ አስረድቷል ። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ አባላት እላይ በተጠቀሱትና በመሳሰሉት ችግሮች ምክንያት የሰው ልጆች ሲሠቃዩ እየተመለከቱ በግድየለሽነት ቸል በማለት ስለ ሰዎች የነፍስ ድኅነት ብቻ ማስተማራቸውን መቀጠሉ በእግዚአብሔር እንደመቀለድ የሚያስቈጥር መሆኑንም በንግግሩ ገልጿል ።

ስለ ሴቶች ጭቆናና ብሶት ስድስት ሴቶች ለጉባኤው ባደረጉአቸው ንግግሮች አብራርተው ገልጸዋል ።

ጉባኤው ዘረኛነትን ስለመቋቋም ፣ ሰብአዊ መብትና የሃይማኖት ነጻነት እንዲከበር ስለማድረግ ፣ በሀብታሞችና በድኾች መካከል ያለው ልዩነት እየጠበበ የሚሄድበትን መንገድ ስለመፈለግ ፣ እምነት ከሥራ መለየት ስለማይገባው ፣ በመካከለኛው ምሥራቅና በአንጎላ የተፈጠሩት ችግሮች ስለሚቃለሉበት መንገድ ወዘተ· በሰፊው ተነጋግሮ ውሳኔ አሳልፎአል ።

ከናይሮቢ ጉባኤ በኋላ ቍጥራቸው 286 የደረሰው አባል የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ጥምቀትን ፣ ቅዱስ ቍርባንንና መንፈሳዊ አገልግሎትን በአንድ ዓይነት መንገድ ለመፈጸም እንዲስማሙ የሚያሳስብ መልእክት ለመላክ ተወስኖአል ።

ስድስተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በነሐሴ ወር 1983 ዓ·ም ቫንኮቨር ውስጥ ተደረገ ።

የጉባኤው አባላት ከሆኑ 301 አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ 847 የሚሆኑ መልእክተኞች ተካፋይ ሆነዋል ። የማኅበሩ አባል ካልሆኑት ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና ከተለያዩ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያ


www.ethiopianorthodox.org

ናት በተመልካችነት ደረጃ የተላኩ መልእክተኞች በጉባኤው ላይ ተገኝተዋል ። እንዲሁም መጀመሪያው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዋና ጸሐፊ የነበረው ዶክተር ቪሴር ትሑፍት ፣ የሮሙ ፖፕ ዳግማዊ ዮሐንስ ጳውሎስ ወዘተ· ያስተላለፉአቸው የመልካም ምኞት መግለጫ መልእክ ቶች ለጉባኤው ተነበዋል ።

በሰላማዊ መንገድ የነጻነት ታጋይ የሆነው አቡነ ዴዝሞን ቱቱ በጉባኤው ተገኝቶ "እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ያሸንፈናል ..." (ሮሜ 8፡31) የሚለውን ጥቅስ መነሻ በማድረግ ሀገሩ ደቡብ አፍሪካ አንድ ቀን ከዘረኛ ገዥዎች መዳፍ (ቀንበር) ሥር ነጻ እንደምትወጣና ዜጎቿ ሁሉ የእኩልነትን ጸጋ እንደሚጐናጸፉ ያለውን እምነት ገልጿል ።

ጉባኤው የኒካራጓ ባፕቲስት ኮንቬንሽንንና የደቡብ አፍሪካ ወንጌላ ዊት ፕሬዝቢቴሪያንን አብያተ ክርስቲያናት በአባልነት ተቀብሏል ። የጉባኤው መሪ ሐሳብ "ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ሕይወት ነው" የሚል ነበር ።

ጉባኤው ይጠቀምባቸው ከነበሩት ካምስቱ እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳ ይኛ ፣ ጀርመንኛ ፣ እስጳንኛ ፣ ራሽኛ ፣ ቋንቋዎች በተጨማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ በግሪክኛም ተጠቅሟል ።

እንዲሁም ለመካከለኛው ምሥራቅ ፍጅት (እልቂት) ሰላማዊ መፍትሔ እንዲፈለግለት ፤ በሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚካሄዱ ጦርነቶ ችም በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ መፍትሔ እንዲፈለግላቸው ለሚመለከ ታቸው ክፍሎች መልእክት አስተላልፏል ። ኢሰብአዊና አሳፋሪ የሆነ ውን የደቡብ አፍሪካ የዘረኝነት አገዛዝ አውግዞ ፣ የሀገሪቱ ኑአሪዎች ሁሉ ዲሞክራሲን በተከተለ መንገድ በሰላም ፣ በእኩልነትና በነጻነት የሚኖሩ ባት ሀገር እንድትሆን አሳስቧል ።

ቀደም ሲል በአምስተኛው በናይሮቢ ጉባኤ በተጀመረው መሠረት አባል የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ጥምቀትን፣ ቅዱስ ቊርባንንና መንፈ ሳዊ አገልግሎትን በተቀራረበ (በአንድ ዓይነት) መንገድ በመፈጸም አንድነታቸውን ለማጽናት ስለሚችሉበት ሁኔታ ተወያይተዋል።

በተጨማሪም በሕዝቦች ዘንድ ካሉት የተለያዩ ባህሎች ገምቢ የሆኑት ስለሚጠበቁበት፤ ወደፊት የአብያተ ክርስቲያናትን አመራር የሚረከቡ ሕፃናትና ወጣቶች በመንፈሳዊ ትምህርት ታንጸው በቤተ


www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን አገልግሎቶች ተካፋይ ስለሚሆኑበት፤ በዕድሜ የገፉ አዛውንት የቤተ ክርስቲያን አገልገሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተካፋይ በመሆን ለብዙ ዓመታት ያካበቱትን ልምድ ለምእመናን ስለሚያካፍሉበት፤ አካለ ስንኩላን በምእመናን (በቤተ ክርስቲያን) ስለሚረዱበትና እነሱም አብያተ ክርስቲያናት በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ስለሚካፈሉባቸው ወዘተ· መንገዶች ተወያይተዋል ።

ሰባተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በየካቲት ወር 1991 ዓ·ም ካምቤራ ውስጥ ተደረገ። የጉባኤው አባላት ከ310 አብያተ ክርስቲያናት የተወከሉ 852 መልእክተኞች በጉባኤው ተገኝተው ተካፍለዋል። ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በተመልካችነት የተላኩ 23 መልእክተኞች በጉባኤው ላይ ተገኝተዋል። እንዲሁም ሌሎች የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ አባል ያልሆኑ ቍጥራቸው በዛ ያለ እንግዶች፤ ተርጓሚዎች፥ ጋዜጠኞች፤ ሃይማኖታቸው ከክርስትና እምነት ውጭ የሆነ ዐሥር ሰዎች፤ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጽ/ቤት ሠራተኞች ወዘተ· በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት በተመልካችነት ተገኝተዋል። ስድስት አብያተ ክርስቲያናትን ጉባኤው በአባልነት ተቀብሏል። በሕዝባዊት ሪፑብሊክ ቻይና የምትገኘዋን የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያንም በአባልነት ተቀብሏል። ከዚችም ቤተ ክርስቲያን ጋር የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባላት ቍጥር 317 ደርሷል።

ከቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ከቀዳማዊ ዲሜጥሮስ፤ ከሩሲያ ፓትርያርክ ከዳግማዊ አሌክሲ፤ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፖፕ ከዳግማዊ ዮሐንስ ጳውሎስ የተላኩ የመልካም ምኞት መግለጫ መልእክቶች ለጉባኤው ተነበዋል።

የአውስትራልያ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦብ ሐውክ ለጉባኤው የመክፈቻ ንግግር አድርጓል።

በቫንኰቨር ከተደረገው ከስድስተኛው ጉባኤ ወዲህ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መጀመሪያ ጸሐፊ የነበረው ዶክተር ቪሴር ትሑፍት፤ ሁለተኛ ጸሐፊ የነበረው ዶክተር ኤውጂኔ ካርሶን ብሌክና ሌሎችም ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ንቅናቄ መሳካትና ርምጃ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደረጉ አባላት በሞት ከዚህ ዓለም ስለተለዩ ጉባኤው ጥልቅ የሆነ ኃዘኑን ገልጿል።



www.ethiopianorthodox.org

በጸሎት መልክ የቀረበው የጉባኤው መሪ ሐሳብ "መንፈስ ቅዱስ፣ ና፤ ፍጥረታትን ሁሉ አድስ" የሚል ነበር። እንደሚታወቀው በዘመናችን ፍጥረታት በድህነት፣ በጦርነት፣ በጭቆና፣ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ መዘዝ በተከሰተ የአየር መበከል ወዘተ. ላይ ወድቀውና (ወድቀንና) ተበክለው በመሠቃየት ላይ ይገኛሉ። በተለይም ጉባኤው የተደረገበት ሀገር ቀደምትና የሀገሪቱ ተወላጅ የሆኑትን አቦርጅናል የተባሉትን ነገዶች ከአውሮጳና ከተለያዩ ሀገሮች ሄደው ቅኝ ገዥ የሆኑት በግፍ እየጨፈጨፉ ሀብታቸውንና ርስታቸውን በመቀማታቸው እጅግ አስከፊ በሆነ ድህነት ላይ ወድቀው ይገኛሉ። እነሱም የተነጠቁት መሬታቸውና መብታቸው እንዲመለስላቸው ለጉባኤው ስላመለከቱ ጉባኤው ተወያይቶ በታል። የአቦርጅናሎችን አቤቱታ የሚደግፈው ውሳኔ ምንም እንኳ የተፈጻሚነት ኃይል ባይኖረውም በሀገሪቱ መንግሥት፣ በአስተዳዳሪዎ ችና በሕዝቡ ላይ የሞራል ተጽእኖ የሚያደርግ መሆኑ ግልጽ ነው።

እንዲሁም ኢራቅ ኩዌትን በግፍ በመውረሯ ምክንያት የፋርስ ባሕረ ሰላጤ ጦርነት በጉባኤው ወቅት ተጀምሮ ስለነበር ተወያይቶበታል። በወንጌልና በባህል መካከል ሊኖሩ በሚገቡ ግንኙነቶች ላይም ተወያይ ቷል። እነዚህንና የመሳሰሉትን ችግሮች ሁሉ ፍጡራን ተቋቁመው ሊያቃልሏቸውና ሊያስወግዷቸው አለመቻላቸው እሙን ነው። አማራጭ የሌለውና ዋናው መፍትሔ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የፈጠረውን ዓለም እንዲያድስ (እንዲፈውስ)፤ እንዲሁም ለጰራቅሊጦስ ዕለት በሐዋርያት ላይ ወርዶ፣ የምእመናንን ልብ ከፍቶ በክርስቶስ እንዲያምኑ በማድረግ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተና በመም ራት ላይ ያለ መንፈስ ቅዱስ አሁንም የአብያተ ክርስቲያናትን የአንድነት ዓላማ ውጥን አሳክቶ በኅብረት በመሥራት ክርስትናን በዓለም እንዲያዳ ርሱ እንዲረዳ ወዘተ. ፍጥረታት ሁሉ ከልብ በጸሎት መለመን ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ ጉባኤው በዚሁ መሪ ሐሳብ ላይ ጸሎት፣ የተለያዩ ንግግሮችና ውይይቶች አድርጓል። በዚሁ መሪ ሐሳብ ላይ ንግግር ካደረጉት መካከል በእስክንድርያ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሣልሳዊ ፓርቴንዮስና በደቡብ ኮርያ ዋና ከተማ በሴውል ኤዋሐ የሴቶች ዩኒቨርስቲ የቴዎሎጂ ፕሮፌሰር ወይዘሮ ቹንግ ሒዩን ኪዩንግ ይገኙበታል።



www.ethiopianorthodox.org

## የክርስትናን እምነት የሚከተሉ ምእመናን ቊጥር ግምት

1ኛ/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባላት ...................... 580,000,000
2ኛ/ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አባላት ......... 230,000,000
3ኛ/ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት አባላት ..... 280,000.000
ድምር ........................................................... 1,090,000,000

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org